# ባህልና ልማት በኢትዮጵያ

## በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች

አርታኢ
ሺፈራው በቀለ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

# ባህልና ልማት በኢትዮጵያ

## በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች


አርታኢ
**ሺፈራው በቀለ**



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

© 2004 ዓ.ም. ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው።

አዲስ አበባ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፦ ቆንጅት በለጠ

ISBN: 978-99944-50-41-1

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ. ቁጥር 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ www.fssethiopia.org

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት፣ ከዴንማርክ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ።

# መቅድም

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ካሉት ዋና ዋና አላማዎች አንዱ በልማት መስክ ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ባለሙያዎችን፣ የልማት ሊቃውንትንና ተመራማሪዎችን የሚያገናኙ ምሁራዊ ውይይቶችን በማድረግ የህብረተሰቡን ቁልፍ ችግሮች መዳሰስና መፍትሄ ማፈላለግ ነው፡፡ ለዚህም ነው የተለያዩ የህብረተሰብ ባለድርሻዎች በአገሪቱ የልማት ጉዳዮች ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑና ሂደቱን ለማቀላጠፍ የሚረዱ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ ህዝባዊ ውይይቶችን ማካሄድ አንዱ አላማው አድርጐ የተንቀሳቀሰው፡፡ በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ከተደረጉ አያሌ የውይይት ጭብጦች ውስጥ «ባህልና ልማት» በሚል ርዕስ የተደረጉት ተከታታይ ውይይቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ በየሁለት ወሩ የተደረጉ ውይይቶች አሥራ ሁለት ሲሆኑ ከመጋቢት 2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥር 2003 ዓ.ም. ድረስ ዘልቀዋል፡፡ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎቹ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ወይም ለረጅም ዘመን በተግባር ከችግሩ ጋር ሲታገሉ የቆዩና በዚህም የተነሳ ጥልቅ ልምድና ሰፊ እውቀት ያካበቱ ኤክስፐርቶች ናቸው፡፡

አድማጮቹም በተለምዶ አነጋገር «የልማት አስፈጻሚዎች» (Development Practitioners) የሚባሉት ሲሆኑ እነሱም ከሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የተጋበዙ የባህልና የልማት ባለሙያዎች፣ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ መያዶች (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ውስጥ የሚሠሩ የልማት ኤክስፐርቶች ናቸው፡፡ የቀረቡት 12ቱም ወረቀቶች ሰፊና የሞቁ ውይይቶች ተካሂደውባቸው ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ላቀረቡት እንዲሁም የረጅም ጊዜ የበለጸገ የሙያ ልምዳቸውን ለታዳሚዎች ላካፈሉት ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አንዳንድ ተካፋዮች በጋዜጣ ላይ አስተያየት ይሰጡ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ በወቅቱ በስፋት ይነበብ የነበረው *አዲስ ነገር* የተባለው የግል ጋዜጣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን በአመቱ ተጽእኖ ፈጣሪ ከነበሩ ድርጅቶች አንዱ አድርጐ እንዲመርጥ ካስቻሉት መስፈርቶች አንዱ ይኼው ውይይት እንደነበር ጠቅሷል፡፡

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በምርምርና በንባብ ላይ የተመሰረቱ ወይም ከጥልቅ ልምድ የመነጩ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ እንዲሁም በስፋት ቢነበቡና በየቤተ መጻህፍቱም ውስጥ ቢቀመጡ ሊኖራቸው የሚችለውን ፋይዳ በማጤን እንዲታተሙ ወስኗል፡፡ በዚህም ውሳኔ

# ማውጫ

| | |
|---|---|
| *መቅድም* | iv |
| *ምህረት አየነው* | |
| *መግቢያ* | vi |
| *ሺፈራው በቀለ* | |
| ባሕልና ልማት፡- ምንነታቸውና ትስስራቸው | 1 |
| *የራስወርቅ አድማሴ* | |
| የብሄራዊ ቅርስ ልማትና ቱሪዝም | 27 |
| *ቴዎድሮስ አጥላባቸው* | |
| የሙስና ባሕላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ | 47 |
| *ክቡር ገና* | |
| ባሕል ከልማትና ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለው ግንኙነት | 67 |
| *ዘውዴ አበጋዝ* | |
| ሀገራዊ እውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ | 77 |
| *አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ* | |
| ቁዘማ፡- ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ | 97 |
| *ፈቃደ አዘዘ* | |
| እምነት-ነክ ክብረ በዓላት፣ ባሕላዊ ክንውኖችና የልማት አንድምታቸው | 139 |
| *ፈለቀ ታደለ* | |
| የአደባባይ ልመና-ምፅዋት | 159 |
| *የራስወርቅ አድማሴ* | |
| ሥነ ጥበብና ልማት | 181 |
| *አስፋው ዳምጤ* | |
| የሥዕል ጥበብ ለባህልና ልማት ዕድገት | 191 |
| *እሸቱ ጥሩነህ* | |
| የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ | 203 |
| *ውዱ ጣፈጠ* | |
| "የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናት" አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ | 219 |
| *አበባው በቀለ* | |
| ዋቢ መጻሕፍት | 241 |
| ደራሲዎቹ | 251 |

መሰረት ሰፊ አርትኦት ከተደረገባቸው በኂላ እነሆ እዚህ መጽሀፍ ውስጥ ተካትተው ሊወጡ በቅተዋል።

ውይይቶቹ እንዲደረጉ እርዳታ የለገሱንን ድርጅቶች ማመስገን እወዳለሁ፤ እነርሱም የኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት፣ የዴንማርክ ኤምባሲ፣ የአየርላንድ ኤምባሲና የእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት ናቸው። በተጨማሪም ግዮን ሆቴል አስተዳደር ላደረገልን ትብብርና ለሰጠን አገልግሎት ምስጋና አቀርባለሁ። በመጨረሻም፣ ውይይቶቹ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄዱና መጽሀፉም ጥሩ ሆኖ እንዲወጣ ላደረጉት ጥረት የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሰራተኞችን ከልብ ማመስገን እወዳለሁ።

ምህረት አየነው (ዶ/ር)
የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈጻሚ ዳሬክተር

# መግቢያ

ባሁኑ ጊዜ ልማት ከባህል ተለይቶ መታየት የለበትም የሚለው አስተሳሰብ ሰፊ ተቀባይነት ያለው ቢመስልም የልማትን ታሪክ በምናጠናበት ጊዜ የምንገነዘበው በቀደሙት ጊዜያት ለባህል ትኩረትም ሆነ ሥፍራ ያልተሰጠው መሆኑን ነው። እንዲያውም የልማትን የትምህርት መስኮች (Development Studies) ጉዞ ቀረብ ብለን ያየን እንደሆነ ብዙዎቹ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ የተነሱ ቢሆኑም ባብዛኛው የሚያተኩሩት በእድገት ላይ ብቻ እንጅ ልማት ያለ ባህል ሊሳካ እንደማይችል የተገነዘቡ አይመስልም ነበር።

እርግጥ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት እጅግ ቀድሞ ያስተምር የነበረው ማክስ ቬበር የተባለው የጀርመን የሶሽሎጂ ሊቅ የባህልንና የልማትን ጥብቅ ቁርኝት በመገንዘቡ የምእራብ አውሮፓ አገሮች በቴክኖሎጂና በካፒታሊዝም ፈጥነው ሊጓዙ የቻሉት የፕሮቴስታንትን መርህ (ኤቲክ) በመከተላቸው ነው እስከማለት ደርሶ ነበር። ይህም አስተሳሰቡ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶለት ነበር። ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ ደግሞ የምስራቅ ኤስያ አገሮች (መጀመሪያ ጃፓን፣ ቀጥሎ ደቡብ ኮርያ፣ ታይዋን፣ ሆንግ ኮንግና ሲንጋፖር) ሊመነደጉ የቻሉት የኮንፍዬሽስ እምነትና አስተሳሰብ ተከታይ ስለነበሩ ይህ እምነትና አስተሳሰብም የጠበቀ የስራ ዲስፒሊን፣ ጠንካራ የቁጠባ ልማድና ስር የሰደደ የመደራጀት ክሂሎት ህዝቡንም ሆነ የፖለቲካውንና የቢዝነስ ልሂቃንን ስለሰጣቸው ነበር የሚል አመለካከት ነበር።

የልማት ሳይንሶች ላይ የነገሰው አስተሳሰብ ግን ለባህል ስፍራ የማይሰጥ፤ ልማት እንዲኖር ከተፈለገ ወሳኞቹ ሁነቶች (Variables) የማእድን መኖር፣ ወይም በሌላ መልክ ካፒታል ማግኘት፣ በነዚህም ላይ ተመስርቶ ትምህርትን ማስፋፋት፣ ኢንቬስትመንትን ማሳደግ...ወዘተ የመሳሰሉት ስለነበሩ ሊቃውንቱ ይህንኑ ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ከልማት የትምህርት መስኮች ውስጥ አንዱ የሆነው ኢኮኖሚክስን ብንወስድ ልማታዊ ኢኮኖሚክስ መልክ ይዞ ከተፈጠረበት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ እስከ 1980ዎቹ (እ.ኤ.አ) ማብቂያ ድረስ ባሉት አራቱ አስርት ዘመናት ውስጥ ባህል በኤኮኖሚ እድገት ውስጥ ለሚኖረው ድርሻ ይህ ነው የሚባል ግምት አልተሰጠውም ነበር። ሁኔታዎች መቀየር የጀመሩት በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነው።

የተባበሩት መንግስታት ባህል ለልማት የሚኖረውን ወሳኝ አስተዋጽኦ በመገንዘብ በ1988 (እ.ኤ.አ) United Nation's Decade for Cultural Development from 1988 to 1997 የሚል አወጀ። ይህም ልማትና ባህል ያላቸውን ቁርኝት በአካዳሚ መስክና

በፖሊሲ ትግበራ እንዲሁም በልማት አመራርና አስተዳደር ጐላ ብሎ እንዲወጣና የውይይቶች እምብርት እንዲሆን ረድቷል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ባህል በልማት ነክ ውይይቶችና ክርክሮች ውስጥ ማእከላዊ ስፍራ ሊይዝ በቃ። በሌላ አነጋገር፣ የልማት ሊቃውንት፣ የአለም ባንክ ኤክስፐርቶች እና የልማት ፈጻሚዎች ልማት እንዲመጣ ከተፈለገ ባህልም መካተት እንዳለበት ከፍ ባለ ድምጽ መከራከር ጀመሩ። የአንዳንዶቹ ጥናታዊ ጽሁፎች አርእስት ብቻ የክርክሩን አቅጣጫ ሊጠቁሙ ይችላሉ። አንድ ዴቪስ (S. Davis) የተባለ ተመራማሪ ያሳተመው "Bringing Culture into the Development Paradigm: The View from the World Bank" (1999) የሚለው ጽሁፍ ጥሩ ምሣሌ ሊሆን ይችላል። (በተጨማሪም UNESCO 1995ን እና UNESCO 2000 ን ይመለከቷል።) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በበኩሉ በ1998 ዓ.ም. UN Report on the Stockholm Intergovernmental Conference on Culture and Development የተሰኘ መጽሀፍ አሳተመ። ከላይ የተጠቀሱት ተደራራቢና ተደጋጋፊ ጥረቶች ይህንን አስተሳሰብ ዩኒቨርሲቲዎችም መቀበል እንዲጀምሩ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ጥልቀትና ስፋት ያለው ክርክር በልማት ላይ በ1980ዎቹም ሆነ ከዚያ በፊት ተካሂዷል ብሉ አፍ ሞልቶ መናገር ይከብዳል። የሆነ ሆኖ አንዳንድ ሊቃውንት ባህል ለልማት ያለውን ፋይዳ ማንሳታቸው አልቀረም። ከበደ ሚካኤል በጻፉዋቸው አንዳንድ መጻህፍት ውስጥ (ለምሳሌ *ጃፓን እንደምን ሰለጠነች*፣ 1946) ጉዳዩን ጠቁመውት ነበር። ምናልባት ግምባር ቀደም ሊሆኑ የሚችሉት ግን በልማት ጉዳይ ላይ የተመራመሩትና የተከራከሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ናቸው። ገና አብዮቱ ከመፈንዳቱ በፊት በአደባባይ የባህልን ፋይዳ አንስተው ተከራክረው ነበር። (Mesfin, 1966a) በደርግ ዘመን የባህልንና የልማትን ቁርኝት በተደጋጋሚ ያነሱት ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ናቸው። ዶ/ር ፈቃደ የስነጽሁፍና የፎክሎር ተመራማሪ ናቸው፤ የፎክሎር የትምህርት ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲከፈት ሲከራከሩ አንዱ ማጠየቂያቸው ፎክሎር ለልማት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው የሚለው መከራከያ ነጥባቸው ነበር። (የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ 6 ይመለከቷል) ይሁንና እነዚህና (ምናልባት እኔ ያላወቅኳቸው) ሌሎች ድምጾች ተሰሚነት ነበራቸው ማለት አይቻልም።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ አመራር የባህልንና የልማትን ከፍተኛ ቁርኝት በመገንዘብ ጥናታዊ ጽሁፎች እየቀረቡበት በሚደረግ ሕዝባዊ ውይይት ጭብጡ እንዲዳሰስ ይወስናል። ተናጋሪዎቹን የመምረጥና ውይይቱን የማዘጋጀት ኃላፊነት ለኔ ይሰጠኛል። እኔም በጊዜው የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈጻሚ ከነበሩት ከፕ/ር ባህሩ ዘውዴ ጋር በመመካከር 12 ርእሶችንና

ወረቀት አቅራቢዎችን መረጥኩ፡፡ ውይይቱም ከመጋቢት 2001 ዓ.ም. እስከ ጥር 2003 ዓ.ም. ድረስ በየሁለት ወሩ ተካሄደ፡፡ እያንዳንዱ ወረቀት ከቀረበ በኋላ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ እውቀት ያለው (ያላት) ምሁር እንዲተችበት (እንድትተችበት) ተደርጓል፡፡ ከዚያ በኋላ አድማጮች ሃሳባቸውን እንዲያሰሙ፣ ጥያቄ እንዲያቀርቡ፣ ወይም ሂስ እንዲሰነዝሩ እድል ይሰጥ ነበር፡፡ በዚህ አይነት ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እያንዳንዱ ደራሲ የተሰነዘሩትን ጥያቄዎችና የቀረቡበትን ትችቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ጽሁፉን እንዲከልስ ተደርጓል፡፡ ውጤቱ ይህ መጽሀፍ ነው፡፡

መጽሀፉ ብዙ ባህልና ልማት የሚገናኙባቸውን ገጽታዎችን ይዳስሳል፡፡ በዚህም የተነሳ አያሌ ወጥ የሆኑ ሀሳቦች በየምእራፎቹ ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ፡፡ መጽሀፉ ሲጀምር በዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ ጽሁፍ ሲሆን ይህ ምዕራፍ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑትን የባህል ትርጉሞች ከዳሰሰ በኋላ ለዚህ አላማ ሊሆን የሚችለውን ትርጉም ያቀርባል፡፡ ምእራፉ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ የሶሽዮሎጂ ቲኦሪዎችን በመቃኘቱ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ለቋንቋው አበርክቷል ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ ከመጀመሪያው ምእራፍ በኋላ የሚመጡት ጽሁፎች ልዩ ልዩ የባህልና የልማት ገጽታዎችንና ግንኙነቶቻቸውን የሚዳስሱ ሲሆን እያንዳንዳቸው እስካሁን ያልነተሱ ጉዳዮችን በማቅረባቸው ፣ ወይም እስካሁን ያልታተሙ መረጃዎችን (data) በማምጣታቸው ወጥነት አግኝተዋል፡፡ በዚህ ጭብጥ ላይ ይህ ህትመት የመጀመሪያውና ፈር ቀዳጅ ስለሆነ መጽሀፉ አዳዲስ ምርምሮች ወደፊት እንዲደረጉ መንገድ ይከፍታል የሚል ተስፋ አለን፡፡

ይህንን መጽሀፍ ለህትመት ስናዘጋጅ አንዳንድ የአርትኦት ውሳኔዎች አድርገናል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የሞክሼ ሆሄያት ጉዳይ አሁንም ያልተፈታ ችግር እንደሆነ በመገንዘብ፣ የደራሲዎቹን የሆሄ አመራረጥ እንዳለ ትተነዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የሞክሼ ሆሄያት አጠቃቀም ዝብርቅርቅ ያለ ይመስላል፤ ይሁን እንጅ በኛ አመለካከት ሊሆን ይገባል በምንለው አካሄድ (ማለትም ሞክሼዎቹን ሆሄያት - ሃ፣ሐ፣ሠ፣ኀ - በሙሉ አጥፍቶ የመጀመሪያዎቹን ሆሄያት - ሀ፣ሰ፣አን - ብቻ መጠቀም) ጽሁፎቹን ለመቀየር ጥያቄ ስናቀርብ አንዳንዶቹ ደራሲዎች ጠንካራ ተቃውሞ ስላነሱ እንዳለ መተውን መርጠናል፡፡

ሌላው ከዚህ ጋራ የተያያዘው ችግር ስርአተ ነጥብን የሚመለከት ይሆናል፤ በተለይም ድርብ ሰረዝን ይመለከታል፡፡ የቋንቋውን ህግጋት ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚባሉት ሊቃውንት እንኳ ድርብ ሰረዝን በሚመለከት አንድ አይነት ስርአት

አይከተሉም። አንዱ በነጠላ ሰረዝ የሚለያያቸውን ሀረጐች ሌላው በድርብ ሰረዝ ይለያያቸዋል።ሌላ ልናነሳው የምንፈልገው የአመተ ምህረት አጻጻፍን ነው። አንዳንዱ ደራሲ ቁጥሮችን በግእዝ ሲጽፍ ሌላው የአረብኛውን ይከተላል። በነዚህ ሁሉ ላይ የደራሲዎችን ምርጫ ለማክበር ሞክረናል።

በመጨረሻም መልካም ንባብ እንላለን።

ሺፈራው በቀለ
አርታኢ

# ባሕልና ልማት፡- ምንነታቸውና ትስስራቸው

*የራስወርቅ አድማሴ*

ይኽ ፅሑፍ በባሕልና ልማት ጉዳይ ላይ የሚደረገው የውይይት መርሃ-ግብር መክፈቻ ነው፡፡ በመሆኑም፤ በባሕል፣ በልማትና በሌሎች ተያያዥ ፅንሰ-ሃሳቦች ፍችና አጠቃላይ ትስስር ላይ ያተኩራል፡፡ ባሕልና ልማት ስንል ምን ማለታችን ነው? የባሕልና የልማት ትስስርስ ምን መሳይ ነው? የባህል ለውጥ ኅብረተሰባዊ ልማት ያመጣል ወይ? በተቃራኒውስ የባህል ኋላቀርነት ኅብረተሰባዊ ልማትን ይገታል ወይ? ለሚሉትና ለተያያዥ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

የተለያዩ የዕውቀትና የምርምር ዘርፎች እንደ "ባሕል" እና "ልማት" ላሉ ፅንሰ-ሃሳቦች ያሏቸው ግንዛቤና የሚሰጧቸው ትርጉሞች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይለያያሉ፡፡ በየአንድአንዱ የዕውቀት ዘርፍም ውስጥ ቢሆን የተለያዩ የአመለካከት አዝማሚያዎች ባለመጥፋታቸው የተነሳ፤ እንደ "ባሕል" እና "ልማት" ያሉ ፅንሰ-ሃሳቦችን በተለያየ መንገድ የመገንዘብና የመገልገል ልዩነቶች መከሰታቸው አይቀርም፡፡ በነዚህ የተነሳ ማንኛቸውም ኅብረተሰብን የሚመለከቱ ፅንሰ-ሃሳቦች በርካታ ፍችዎች ይኖሯቸዋልና፤ ከሁሉ አስቀድመን በዋነኛዎቹ ፅንሰ-ሃሳቦች ፍች ላይ በማተኮር መነሻችንን ማጥራት ይኖርብናል፡፡

## 1. የ"ባሕል" ፅንሰ-ሃሳብ ፍቺ

በሃገራችን "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ባሕል" በሚለው የአማርኛ ቃል ተተርጉሞ ሲሰራበት የቆዬና የተለመደ በመሆኑ ሁለቱን ቃላት በተመለከተ ምንም የሰፋ የትርጉም ክፍተትና የጎላ ያለመገጣጠም ችግር የለም፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 (እ.ኤ.አ) ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ-ቃላት "ባሕል" የሚለውን ቃል "የኅብረተሰብ[1] የአነዋንዋር ዘዴ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት" ብሎ ይፈታዋል፡፡ ይኽም ፍች "ካልቸር" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከሚሰጡት የተለያዩ ፍችዎች ቢያንስ የጥቂቶቹን ይዘት ደህና አድርጎ የሚጋራ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ያለምንም ተጨማሪ ማስረጃ፣ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ "ካልቸር" ስንል "ባሕል"፤ "ባሕል" ስንልም "ካልቸር" ማለታችን መሆኑን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሳታውቀን ወደ ዋናዎቹ የፅንሰ-ሃሳቦች ፍች ጉዳይ እናልፋለን፡፡

"ባሕል" ለሚለው ቃል ትርጉም የመስጠቱና ከበስተጀርባው ያለውን ፅንሰ-ሃሳብ ግልፅ የማድረጉ ተግባር ቀላል አይደለም፡፡ የዚህ የአማርኛ ቃል አቻ የሆነውን የእንግሊዝኛ ቃል አስመልክቶ ሬመንድ ዊሊያም "ካልቸር በእንግሊዘኛ ቋንቋ

---

[1] በዚህ ፅሑፍ ውስጥ "ኅብረተሰብ" የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት እንግሊዝኛ "ሶሳይቲ" ለሚለው፤ "ማኅበረሰብ" የሚለውን ደግሞ እንግሊዝኛ "ኮሚዩኒቲ" ለሚለው አቻ በማድረግ ነው፡፡

ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ወይም ሶስት እጅግ የተወሳሰቡ ቃላት መካከል አንዱ ነው" ያለው (ጀንክስ 2007: 928)፤ ለአማርኛውም ቃል በሚገባ ይሰራል:: ይኸ "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃልና ከበስተጀርባው ያለው ፅንሰ-ሃሳብ የፈለቀውና በሥራ ላይ መዋል የጀመረው በምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ ኅብረተሰባዊ ለውጦች በተካሄዱባቸው በአስራ-ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት ማብቂያና በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት ውስጥ መሆኑ ከነዚያ ገና በመጠናት ላይ ካሉ ዝብርቅርቅ የለውጥ ክስተቶችና መጠሪያዎቻቸው ጋር በመያያዝ "ባሕል" የሚለውም ቃል ትርጉም እንደዚሁ የተወሳሰበና ላይ-ላዩን ሲያዩት የሚያምር፣ ሲመረምሩት ደግሞ የሚያደናግር እንዲሆን አድርጎታል:: በዚህም የተነሳ በዚህ ጉዳይ ላይ አበክረን እንድናትት ሁኔታው ያስገድደናል::

ቀደም ሲል መሬት ከማረስ (the cultivation of land) ጋር ተያይዞ የመነጨው "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ሁለት ዋነኛ ዘመናዊ ትርጉሞች ይዞአል:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:- በአስራ-ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት የፈለቀውና ኪነ-ጥበብን፣ ሙዚቃን፣ እና ሥነ-ፅሁፍን የሚመለከተው ሂዩማኒስቲክ ትርጉም እና፤ በአስራ-ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት ጠቅላላ የሰው-ልጅን ተግባራት ድምር ለማመልከት የተተከለው የአንትሮፓሎጅ ትርጉም ናቸው:: እነዚህ ሁለት ተርጉሞች ዛሬም የሚሰራባቸው በመሆናቸው፣ ሁለቱም መዘንጋት የለባቸውም::

ይሁንና፣ የመጀመሪያው ትርጉም እኔ እስከማወቀው ድረስ አወዛጋቢ ባለመሆኑና ከራሴ መደበኛ የሙያ መስመርም ውጭ በመሆኑ የተነሳ፤ ይህንን ሂዩማኒስቲክ ትርጉሙን የመተንተኑን ተግባር ወደፊት በዚሁ ዛሬ ሀ-ብለን በጀመርነው መርሀ-ግብር ውስጥ ከጉዳዩ ጋር በተያያዙ አርእስት ላይ የጥናቶቻቸውን ወጤቶች ለሚያቀረቡልንና ለጉዳዩ ቅርበት ላላቸው ምሁራን እተውና በቀጥታ ወደ አንትሮፓሎጅ-ሶሲዮሎጅ ትርጉሙ አልፋለሁ::

ባለፈው ምዕተ-ዓመት አንትሮፖሎጅስቶች "ባሕል" ለሚለው ፅንሰ-ሃሳብ በርከታ ትርጉሞች ሰጥተዋል:: በዚህ የተነሳና ከዚህ ተከትሎ የመጣውን የፍች ትርምስምስ ለማሳየትም፤ክሮበር እና ክሉክኾኽን የተባሉ ሁለት አንትሮፖሎጅስቶች የዛሬ ሃምሳ ስምንት ዓመት (እ.ኤ.አ. በ 1952) ባደረጉት ጥናት፤ በዚያን ጊዜ አንድ መቶ ስልሳ የተለያዩ የ"ባሕል" ፍችዎች እንደነበሩ አሳይተዋል (ፌራሮ 2001: 22):: ከዚያን ጊዜ ወዲህ በተቆጠሩት ዓመታት ደግሞ በርካታ ተጨማሪ ፍችዎች እንደተሰጡት መገመት ይቻላል::

"ባሕል" ለሚለው ፅንሰ-ሃሳብ የተሰጡት ትርጉሞች፤ እጅግ ከመበራከታቸው በተጨማሪ አንድ ዓይነተኛ የጋራ ጠባይ አላቸው:: የሚገለፁባቸው ፊደላት ቁጥር ይብዛም ይነስ፤ ከሞላ-ጎደል ሁሉም ማለት ይቻላል፤ ሲበዛ ሁሉ-አቀፍ ናቸው:: እግረ-መንገዳችንን ይህን አያጤን፤ የተለያዩ የባሕል ፍችዎችን በናሙናነት እንቃኝ::

አንድ የቆየ ግን እስከዛሬ ዘመን ድረስ በሰፊው የሚጠቀስ የ"ባሕል" ፍቺ፤ ኤድዋርድ ቴለር እ.ኤ.አ. በ 1871 የሰጠው ሲሆን፤ እንደሚከተለው ይነበባል፤

> *ባሕል ወይም ስልጣኔ፤ ያ ዕውቀትን፣ እምነትን፣ ኪነ-ጥበብን፣ ሞራልን፣ ሕግን፣ ወግን፣ እና ሌሎች ሰው የኅብረተሰብ አባል በመሆኑ የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ልምዶች ጭምር የሚያጠቃልለው ውስብስብ የሆነ ዉሁድ ነው* (ካልሁን 2002: 105)::

ቀረብ ባለ ጊዜ ደግሞ፤ "ባሕል" በዶንስ (1971) እንደሚከተለው ተፈቶ ይነበባል፤

> ባሕል ከአካባቢያችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያሉንን ግንኙነቶች በተመለከተ የሚመራን የዐዕምሮ/የሕሊና ካርታ (mental map) ነው (ፌራሮ 2001: 22)::

በፊደላት ብዛት ረገድ ካለፈው ባጠረ መንገድም እነደሚከተለው ሃች በተባለ ተመራማሪ (1985) ተፈትቶአል፤

> ባሕል የአንድ ሕዝብ የአኗኗር ዘዴ ነው (ፌራሮ 2001: 22)::

ከላይ የተጠቀሱት አልበቁ ይመስል፤ የፍችው ፍሰት እንደቀጠለ ነው:: በ2001 ለሕትመት በበቃ መፅሐፉ ውስጥ ጌሪ ፌራሮ የሚከተለውን ይላል::

> *አስቀድመው በተሰጡት በርካታ ፍቺዎች ላይ በመጨመር፤ ለኛ ጉዳይ ስንል፤ የባሕልን ፅንሰ-ሃሳብ ሰዎች እንደ ህብረተሰብ አባላት ያላቸው፣ የሚያስቡት፣ እና የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር ሁሉ ነው፤ ብለን እንተረጉመዋለን* (ፌራሮ 2001: 22)::

በመቀጠልም፣ ፌራሮ ይህንን ከላይ የሰጠውን ፍች እንደሚከተለው ያብራራል:: ማብራሪያውም፣ በዙሀኑ አንትሮፖሎጅስቶች የሚጋሩዋቸውንና እኛም በተራችን ለተነሳንበት ጉዳይ ጠቃሚ የሆኑ ቁም-ነገሮችን ያቀፈ በመሆኑ ቀጥለን እንዳለ አስፍረነዋል::

> *ይኸ ፍቺ ጠቋሚነት አለው:: ምክንያቱም፤ በውስጡ የያዛቸው ሦስቱ ግሦች ከሦስቱ ዋነኛ የባሕል ይዘቶች ጋር ይገጥማሉና ነው:: ይኸውም፤ ማንኛውም ሰዎች ያላቸው ነገር ሁሉ የሚለው ቁስ-አካላዊ ንብረትን ያመለክታል፤ ማንኛ ውም ሰዎች የሚያስቡት ነገር ሁሉ የሚለው በጭንቅላታቸው ይዘው የሚዞሩትን እንደ ሃሳቦች፣ ህብረተሰባዊ ደንቦችና፣አመለካከቶች ያሉትን፤ እናም ማንኛውም ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ሁሉ የሚለው ደግሞ መልክ የያዘ ባሕርያቸውን ያመለክታል:: ስለዚህም፤ ባሕሎች ሁሉ ቁስ-አካላዊ ነገሮችን/ንብረትን፤ እናም ሃሳቦችን፣ ኅብረተሰባዊ ደንቦችንና፣ አመለካከቶችን፤ እንዲሁም መልክ-የያዘ ባሕርይን ያቅፋሉ ማለት ነው* (ፌራሮ 2000: 23)::

ከላይ ያቀረብናቸው የ"ባሕል" ፍችዎች በሚገባ እንደሚያሳዩት፤ የሶሺያል-አንትሮፖሎጂ የዕውቀት ዘርፍ የ"ባሕል"ን ፅንሰ-ሃሳብ የሚገነዘበው እጅግ ሰፊና መላ ኅብረተሰባዊ ይዘቶችን (ክስተቶችን) በሚያካትት መልኩ ነው:: በዚህ ግንዛቤ "ባሕል" ማለት የአንድ ኅብረተሰብ አባላት የሚረከቡአቸውን የተጠራቀሙ ዕውቀቶች፣ ዕምነቶች፣ ኪነ-ጥበባት፣ መመሪያዎች፣ አርማዎች፣ አመለካከቶች፣ ሥነ-ምግባራት፣ ህግጋት፣ ወጎች፣ ተለምዶዎችና፣ ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁስ-አካላዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውሁድ ነው:: ይህንን የ"ባሕል" ግንዛቤ ይዘን ዋነኛ ጉዳያችን ወደ ሆነው የባሕልንና የልማትን ትስስር የመመርመር ሥራ የዞርን እንደሆነ፤ አስቸጋሪ የ"ጥምጥም ትንታኔ" ማጥ ውስጥ እንገባና፤ "ሁሉንም ነገር የሚያቅፈው ባሕል ሁሉንም ነገር

የሚመለከተውን ልማት ይወስናል" ወደሚል ፋይዳ-ቢስ ድምዳሜ እንደርሳለን::

ስለዚህ፣ በጠባብ ትርጉሙ በመውሰድ፤ "ባሕል" አንድን *ኅብረተሰባዊ የወጎች ሥርዓትን* (a system of social norms) *ያመለክታል*:: ይኸም *ኅብረተሰባዊ የወጎች ሥርዓት* ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ወጎቸን፣ ልምዶችንና፣ እርሞችን፣ ልማዳዊ-ሕጎችን፣ ድንጋጌዎችንና፣ ከነዚህ ጋር የተዛመዱ እምነቶችን፤ አመለካከቶችንና፣ ጠባዮችን ያቅፋል ብለን ብንነሳ፤ ለያዝነው "የባሕልና የልማት ትስስር" ጉዳይ ጠቃሚ የሚሆነን ይመስለኛል::

## 2. ለባሕል ተቀራራቢና አሳሳች የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦችና መጠሪያ ቃላቶቻቸው

ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው "ባሕል" የሚለው ቃልና የቆመለት ጽንሰ-ሃሳብ አጅግ ሰፊና ሁሉ-አቀፍ ከመሆን አልፎ የሀሳብ መንሰራፋት አስከትሏል:: ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ፣ በኛ አገር ደግሞ፤ ለባሕል ተቀራራቢ የሆኑ ሌሎች ፅንሰ-ሀሳቦችን ለይተን በማውጣት መጠሪያ ስሞች በመስጠት ፋንታ ከባሕል ጋር አብረን ወቅጠን ቀብረናቸዋል:: በእንደዚህም ስለ ባሕል ያለንን ግንዛቤ ከማድበስበስ አልፈን ከሆነው የበለጠ አግዝፈነዋል፤ ያልሆነውን አድርገነዋል፤ ላልዋለበትም ሁሉ ተጠያቂ እያደርግነውማል:: ለዚህም እንደ "ጎጂ-ባሕል"፣ "ባሕላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች"፣ "የባሕል-ልብስ"፣ "የባሕል-ምግብ"፣ የሚሉትንና የመሳሰሉትን አባባሎችንና አጠቃቀሞችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል:: በመቀጠል፤ እነዚህን የባሕል ተቀራራቢና አሳሳች የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦችና ፍቺዎቻቸውን እንመልከት::

*ትራዲሽን* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚፈታ በመዝገበ ቃላትም ሆነ በአጠቃቀም መሰረት የያዘ የአማርኛ ቃል ላገኝ አልቻልኩም፤ በጥቅም ላይ ያልዋለ ነገር ደግሞ ከሌለ የሚቆጠር ይመስለኛል:: ምናልባት "ነባር-ልምድ" የሚለው ይቀርበው ይሆናል:: *ትራዲሽን (ነባር-ልምድ)* ባጠቃላይ ከቀድሞው ተያያዥነት እንዳላቸው የሚያመለክቱና የሚያስደምጡ ነባር ባሕላዊ ገጽታዎችን ሁሉ ያመለክታል:: እነዚህም፤ በመሰረቱ፤ ማንኛውም ዓይነት እምነቶች፣ልምዶች፣ ልማዶች፣ እውቀቶች፣ ወይም የኅብረተሰብ ዋነኛ ደንቦች ሊሆኑ ይችላሉ (ካልሁን 2002: 488):: ባጭሩ፤ "ሲወርድ-ሲዋረድ" የመጣ ነባር የሆነ ኅበረተሰባዊ ክስተት፣ አድራጎት፣ ወይም አሰራር፣ ሁሉ ትራዲሽን ይባላል ማለት ነው:: – ፍልሚያ ሆነ ጉማ፣ አንደርቢ ሆነ መፈትሄ-ስራይ፣ ምግብ ሆነ አመጋገብ፣ ልብስ ሆነ አለባበስ፣ ነባር መሆኑን እስካመለከተንና እስካስደመጥን ድረስ ትራዲሽን ይባላል ማለት ነው::

እዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ የግድ መነሳቱ አይቀርም:: አንድ ህብረተሰባዊ ክስተት፣ አድራጎት፣ ወይም አሰራር፣ ምን ያህል ጊዜ ካስቆጠረ ወይም ስንት ትውልድ ከዘለለ በሁዋላ ነው ነባር-ልምድ ወይም ትራዲሽናል ሊባል የሚችለው? ይህ ጉዳይ ስናድበሰብሳቸው ከቆየነው ዋነኛ የጽንሰ-ሃሳብ ክፍተቶች አንዱ ነው::

*ልምድ* (custom) ማንኛውም የአንድ ማኅበረሰባዊ ስብስብ አይነተኛ የሆነ አድራጎት ወይም ወግ ነው:: ይሁንና፤ ይህ ጽንሰ-ሃሳብ ባብዛኛው ባሕል በሚለው ስር እየተጠቃለለ መጥቷል (ካልሁን 2002: 107)::

*ልማዳዊ-ሕግ* (customary law) በተፃፈ ድንጋጌ መልክ ሳይሆን በነባር-ልማድ አማካይነት ተላልፎ የመጣ ሕግ ነው (ካልሁን 2002: 107))::

*"ወግ"ን* (norm) ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 (እ.ኤ.አ) ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ-ቃላት፤ *"ስርዓት፤ ደንብ (ከጥንት ሲያያዝ የመጣ)"* ይለዋል::

## 3. አንዳንድ የባሕል ገፀ-ባሕርያት

*ባሕል፣ ማንኛውም ኅብረተሰባዊ ሥርዓት ከሚያቅፋቸው አራት ይዘቶቹ ውስጥ አንደኛው ሲሆን፤* ሌሎቹ ሦስቱ የኅብረተሰባዊ ስርዓት ይዘቶች ኅብረተሰባዊ ሥርዓት (social structure) ፣ ሕዝብ (population)፣ እና የአካባቢ፣ የተፈጥሮና የፍጥረታት ትስስር (ecology) ናቸው::

*የባሕል ባለቤት ኅብረተሰብ፤ ዝቅ ሲል ማኅበረሰብ ነው::* ባሕል በኅብረተሰብ ወይም በማኅበረሰብ ውስጥ የታቀፉ ሰዎች የሚጋሩት እንጅ፤ የግል ጉዳይ አይደለም፤ ሊሆንም አይችል::

*ሰዎች ባሕልን ይማሩታል እንጅ በደም አይወርሱትም::* ከአንድ ትውልድ ወደሚቀጥለው በመማማር እየተሸጋገረ ይቀጥላል:: በውልደት ይሁን በማደጎ ወደ አንድ ኅብረተሰብ የገባ አዲስ አባል፤ የኅብረተሰቡን ባሕል በኅብረተሰባዊ የአስተዳደግ ሂደት ውስጥ እንደ ቤተሰብ፤ የአቻዎች ቡድን፤ ትምህርት ቤትና፤ የዕምነት ቤቶች በመሳሰሉት አማካይነት ይላበሰዋል::

*ባሕል ያስችላል፤ ይረዳል እንጅ አይወስንም::* ባሕል የሰዎችን አስተሳሰብ በማረቅ ሳያሰላስሉ አንድን ነገር ከሌላው አባል እንዲጠብቁ ወይም እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል እንጅ፤ የግድ ይህንን ወይም ያንን እንዲያደርጉ ወይም እንዲሆኑ አይወስንባቸውም፤ አያስገድዳቸውም:: ሰዎች የሚገነዘቡትን፤ የሚያደርጉትንና ከማድረግ የሚታቀቡትን በተመለከተ አንፃራዊ ነፃነት አላቸው ማለት ነው::

*አንድ ኅብረተሰብ አባላቱ በሙሉ የሚጋሩት አንድ ነጠላ ባሕልን ብቻ ወይም ብዙ ባሕሎችን ሊያስተናግድ የቻላል::* አንዳንድ የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆኑ ኅብረተሰቦችና ማህበረሰቦች በመላ አባላታቸው የተደመጠ ነጠላ ባሕል ሊኖራቸው ይችላል፤ ኖሯቸውም ታይቷል:: የዘመናችን ሰፋፊ ኅብረተሰቦች ግን፤ ከኅብረተሰቡ *ዋነኛ-ባሕል* ጎን-ለጎን በርካታ *ንዑሳን ባሕሎችን* ያስተናግዳሉ:: አልፎ-አልፎም በዋነኛ ባሕሉ በተወከለው አገር-አቀፍ ጥቅም-ፍላጎትና በአካባቢው *ንዑስ/ክፍል-ባሕል* በተወከለው ጥቅም-ፍላጎት መካከል ግጭት ይፈጠራል:: ከነዚህ ንዑሳን/ክፍለ-ባሕሎች መካከል አንዳንዶቹ ከዋነኛው-ባሕል መለየት ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተቃራኒው ሆነው በሚገኙበት ጊዜ *ተፃራሪ-ባሕሎች* ይባላሉ:: በአንዳንዶቹ ህብረተሰቦች ውስጥማ የቱ ዋነኛ የቱ-የቱ ንዑሳን-ባሕሎች መሆናቸውን መለየት እስከሚያዳግት ድረስ የተመጣጠኑና

የተነባበሩ ከመሆናቸው የተነሳ *ባሕለ-ብዙ ኅብረተሰብ* በመባል ይታወቃሉ። የኛ ም፤ የዘመናችን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ እንደዚህ ዓይነት ይመስለኛል።

*ባሕል በሂደት ይለወጣል፤ እንጅ ፍፁም እንደነበረ ሆኖ አይቀጥልም አይኖርም።* ባሕል በሂደት ይለወጣል። ተፈላጊ ሆነው የተገኙ የባሕል ኤለመንቶች ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ በአዲስ ይከሰታሉ፤ ተፈላጊ ያልሆኑት ደግሞ ቀስ-በቀስ መልካቸውን ይቀይራሉ ወይንም ከናካቴው ይከስማሉ። የለውጡም ሂደት ሁለት መንገዶችን የተከተለ ነው፤ *ፈጠራ-ግኝት እና ውርስ።* አንድ ኅብረተሰብ ወይ አዳዲስ የባሕል ኤለመንቶችን በራሱ ፈጥሮ-አመንጭቶ ይገለገልባቸዋል አልያም ከሌላ ወርሶ ያዋህዳቸዋል፤ ንብረቱ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪ፤ የለውጡ አመጣጥ፤ ዘገምተኛ ወይም ድንገተኛ ሲሆን፤ በሰላም ወይም በግጭት ታጅቦ ሊወለድ ይችላል።

ይኸ በመጨረሻ ያስቀመጥነው የባሕል ጠባይ፣ ከ "ኅብረተሰባዊ ለውጥ" (ሶሽያል-ቼንጅ) ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ፣ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ያሸጋግረናል።

## 4. የ"ልማት" ፅንሰ-ሃሳብ ፍቺ

ሁለተኛው ዋነኛ የውይይታችን ዋልታ "ልማት" ብለን የምንጠራው ፅንሰ-ሃሳብ እንደመሆኑ፤ ከዚህ ላይ ደግሞ እይታችንን ወደዚህ ጉዳይ እናዞር። ብዙዎቻችን "ልማት" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዳለን አጠያያቂ አይደለም። ወደ ዝርዝሩ ስንገባ ግን፣ ሁኔታው የሚመስለውን ያህል ቀላል አይደለም።

"ልማት" አንድ ዓይነት ኅበረተሰባዊ ለውጥ ሲሆን፤ ማንኛውም "ኅብረተሰባዊ ለውጥ" ልማት ነው ማለት አይደለም። "ልማት" አዎንታዊ፣ በጎ፣ ወይም ጠቃሚ፣ ኅብረተሰባዊ ለውጥ ማለት ነው። ኅብረተሰባዊ ለውጥ ከምንላቸው ክስተቶች ውስጥ አንዳንዳቹ በአንድ ወይም በሌላ ጎናቸው ይበልጡን አሉታዊ፤ ማለትም ከአጠቃላይ ኅብረተሰባዊ ደኅንነት አንፃር ይበልጡን ጎጅና እኩይ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ አዎንታዊ፤ ማለትም በአንድ ወይም በሌላ ጎናቸው ይበልጡን ጠቃሚዎች ሆነው ይገኛሉ። "ልማት" በምንለው አጠቃላይ አርዕስት ስር የሚካተቱት ኅብረተሰባዊ ለውጦችም፤ የኋለኛዎቹን ዓይነት ማለትም ባብዛኛ ው ጠቃሚ የሆኑትን መሻሻሎች ነው። "ባብዛኛው" የሚለውን ቃል ደጋግመን የተጠቀምንበትም ሆን ብለን ነው። ማንኛውም ለውጥ በተወሰነ መጠን አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖች ስለማያጣና፣ እንከን የማይገኝለት ፍፁም ጠቃሚ ወይም ፍፁም ጎጅ ብቻ የሆነ ለውጥ ኖሮ ስለማያውቅና ስለሌለ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር መጨመር ያስፈልጋል። እንደማንኛውም ኅብረተሰባዊ ለውጥ ሁሉ፤ "ልማት" ታስቦበትና ሆን ተብሎ የተወሰደ እርምጃ ውጤት ሊሆን፤ አለያም ያልታሰበና ወይም በራሱ ታስቦበት ከተወሰደ እርምጃ በመከተል የመጣ ላይሆን መቻሉ ዋና ጉዳይ ነው።

"ልማት" ብለን የምንጠራው ህብረተሰባዊ ክስተትና ሂደት በርካታ ንዑስ ይዘቶችን ያቀፈ በመሆኑና፣ ይህን በተመለከተም በተመራማሪዎች ዘንድም

በተወሰነ ደረጃ የተለያዩ  አስተያየቶች ስለሚስተናገዱ፣ መጠነኛ ዝርዝር ውስጥ እንድንገባ ያስፈልጋል::

ቀደም ባለው ጊዜ፣ ማለትም በ1950ዎቹና 60ዎቹ አካባቢ፣ የአንድ ኅብረተሰብ ልማት ከኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር አንድ እንደሆነ፣ ወይንም የፊተኛው ከኋለኛው ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑ የተነሳ አብሮት እንደሚጓዝ ማየቱ የተለመደና የተንሰራፋ አመለካከት ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ አመለካከት በመሰረቱ ተለውጦ፣ "ልማት" ሲባል በሰፊው ትርጉሙ በመወሰድ  የኢኮኖሚ ልማትንና የሕዝብን የፓለቲካና የሶሺያል ደህንነትን እንዲያቅፍ ተደርጓል (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2009):: የኢኮኖሚ ልማት ያልነውም ቢሆን በጠባብ ትርጉሙ በአንድ ሃገር ከፓለቲካና ከሶሺያል ደህንነት ጋር ተያይዞ በመምጣት ከቀላልና ከዝቅተኛ-ገቢ ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊና ከፍተኛ-ገቢ ኢኮኖሚ የሚደረግ የኅብረተሰብን ለውጥና የሕዝብን ኑሮ መሻሻል የሚያመለክት ሆኖ እየተወሰደ ነው:: እውነተኛ የኑሮ መሻሻል መለኪያ የሆነው የሕዝብ አማካይ ደስተኛነትም ቢሆን የአንድን አገር አማካይ የገቢ-መጠን እድገት ተከትሎ የሚከሰት አለመሆኑ ተረጋግጧል::

ከላይ በተመለከትነው መንገድ "ልማት" በሰፊው ትርጉሙ እየተወሰደ በመሄዱ የተነሳ፤ ተጓዳኝ የሆኑና የተለያዩ የ"ልማት ዓይነቶች"ን  የሚገልፁ ቃላቶች ፈልቀዋል:: እነዚህም  "የኢኮኖሚ ዕድገት"፤ "የኢኮኖማ ልማት"፤ "ኅብረተሰባዊ ልማት"  "ሰብዓዊ ዕድገት"፤ "ቀጣይ ልማት" እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤"ልማት" የምንለው እነዚህን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2009)::

## 5. የባሕልና የኅብረተሰባዊ ለውጥ ትስስር

አለም-አቀፋዊና መንግሥታዊ ፖሊሲ አውጭዎች፤ ህብረተሰባዊ ወጎች (social norms) በሰዎች አመለካከትና ምርጫ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ በመገንዘብ፤ ለባሕላዊ ጉዳዮች ዕውቅና እየሰጡ ሄደዋል:: በመሆኑም፤ ቀስ በቀስ የባህል  ጉዳይ በልማት ዙሪያ በሚካሄደው ውይይት ውስጥ ቦታ እያገኘ መጥቷል:: ይሁንና፤ ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን ጫና፤ መጠንና፤ ለፓሊስም ያለውን ተፈላጊነት በተመለከ ተ  አሁንም ልዩነቶች አሉ:: የተለያዩ አስተያየቶችም እየተሰጡ ናቸው::

ግለሰቦችን እንደ ነፃ-ወሳኝ (autonomous) ተዋንያን የሚቆጥረው መደበኛው የራሺናል ቾይስ (rational choice) አመለካከት በአንድ በኩል፤ ግለሰቦችን በመሰረቱ የህብረተሰብ ፍጡራንና ተዋንያን አድርጎ በመውሰድ ታሪክ የህብረተሰብ አደረጃጀትና የሃይል ግፊት ውጤት ነው የሚለው አክራሪ መዋቅራዊ (structural) አመለካከት በሌላ በኩል፤ ሁለት ፅንፋዊ አቋሞች በመሆን በመካከላቸው የተለያዩ ወዲህና ወዲያ ያዘመሙ አመለካከቶችን ያቅፋሉ:: በተለያዩ ደረጃም አንዳንዶቹ ተመራማሪዎች የኅብረተሰብ አደረጃጀትን (መዋቅርን) የበላይ ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ ዋናነትን ለተዋናዩ ግለሰብ ወይም ስብስብ ይቸራሉ::

የባህልን ሂደት በተመለከተ ሁለት ርዕዮቶች እንዳሉ መገንዘብ ጠቃሚ ነው:: በአንድ በኩል ባህልን አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደተፈጠረ ግግር የሚቆጥረው ስታቲክ (static ) ርዕዮት ሲገኝ፣በሌላ በኩል የዚህ ተቃራኒ  የሆነው ርዕዮት ደግሞ ባህልን

እንደ ተለዋዋጭ ወይም ታዳጊ (dynamic) ፍሰት ይገነዘበዋል:: ከዚህ በመያያዝም፣ ባህልን እንደ ቋሚ ግግር የሚያመለክቱት ባህልን እንደ አፍራሽና የዕድገት እንቅፋት ሲወስዱትና ሲኮንኑት፣ እንደ ታዳጊ ፍሰት የሚገነዘቡት ደግሞ ከልማት ጋር ተያያዥ ሆኖ ራሱም እያደገና እየለማ የሚሄድ የልማት አጋዥ አድርገው ያዩታል:: ታዲያ ከዚህ ወጣ ያሉም አስተያየቶች አሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ ፅንፈኛ የባህል ተንከባካቢዎች፣የአንድን ባህል በሂደት መለወጥ እንደዚያ ባህል መክሰም በመቁጠር ፈፅሞ እንዳይቀየርና እንዳያድግድ በመፈለግ ማንኛውንም ተያያዥ ልማት አበክረው ይቃወማሉ:: ለምሳሌ፣ የዛሬ ሃያ ዓመት አካባቢ የሀመርን አገር ከአካባቢው የሚያገናኝ የመኪና መንገድ መሰራቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩ አንድ የዚህ አመለካከት ተጋሪና የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ መምህር ለብዙ ደቂቃዎች በሃዘን በመዋጥ ጭንቅላቱን በሁለት እጁ ይዞ፣ ፈዞና ተኮራምቶ እንደ ቀረ አብረውት የነበሩ የዚያን ጊዜ ተማሪዎቹ ዛሬም ድረስ የአስተማሪያቸውን መሪር ሃዘን በመገረም ያስታውሱታል::

ሳተላይት ቴሌቪዥን ብድር ይግባውና፣ ብዙዎቻችን እንድንጋራው ያደረገንን ሌላ ተመሳሳይ ትዝብት እናንሳ:: በ2001 ዓ.ም የዚህ ፅሁፍ ጭብጥ ለታዳሚዎች በቀረበበት ሳምንት ውስጥ በቢ.ቢ.ሲ. ቴሌቪዥን የግልገል ግቤ-ሦስት ግድብን በማስመልከት በቀረበ ኘሮግራም፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቡ መገንባት የአካባቢውን ሕዝብ የሚያጠፋ እርምጃ ነው ተብሎ በአውሮፓውያን አንትሮፓሎጅስቶች ሲፈረጅና ለዕገዱ-ዘመቻ ኢላማነት ሲመቻች ማየታችንን እናስታውሳለን (BBC, The Dam that divides Ethiopians, 26 March 2009):: አስቀድሞ በራሳቸው በፕሮግራሙ አጋፋሪዎች ግድቡ ስለሚያስከትለው ጣጣ "በቂ ገለፃ" የተደረገላቸውን የአካባቢ ሽማግሌዎች አስተያዬት መነሻ በማድረግ፣ ማርኮ ባሲ የተባለው ኢጣሊያዊ የቡድኑ አባል፣ "ግድቡ ከተሰራ የአካባቢው ነዋሪዎች ምን ይበጃቸዋል?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ፣ ፍርጥም ብሎ የሰጠው ፍርድ አይሉት ትንቢት "ሁሉም ይሞታሉ" የሚል ነበር:: በዚህ ሰው አመለካከት፤ የግልገል ግቤ ወንዝ ውሃ ፍሰት በግድቡ አማካይነት ከተገራና፣ በክረምት እጅግ እየሞላና በበጋ ደግሞ እጅግ እየቀነሰ የታች አገሩን ሕዝብ በመጥለቅለቅና በድርቅ ዋልታዎች መካከል ማዋተቱ ከቀረ፣ ይህንን አስቸጋሪ የተፈጥሮ ክስተት ለመቋቋም የአካቢው ሕዝብ በዘመናት ያሳደገውና ያቆየው ነባር-ልምድ አብሮት ሊለወጥ ነው:: ስለዚህም፣ ግድቡ ሊያመጣለት የሚችለው ዋስትና ያለው የውሃ አቅርቦትና የኑሮ መሻሻል ቀርቶበት ነባር-ልምዱን እንዳለ አንቆ ቢኖር ይሻለዋል:: በእንደዚህ ከኖረ ደግሞ፤ ለነዚሁ የውጭ-ሃገር "አጥኚዎች" እና በመሰናዶ ላይ ለሚገኙት ደቀመዝሙሮቻቸው እንዳለ ተቀምጦ ይጠብቃቸዋል፤ የጥቅም ምንጫቸው እንደሆነም ይቀጥላል ማለት ነው::

ባሕል የልማት አካል ነው:: አማርቲያ ሴን (2004፡ 39) ደህንነት የሚመሥርተው በነፍስ-ወከፍ አጠቃላይ አገራዊ ምርት ላይ ብቻ እንዳልሆነ ሲያመለክት፤ በተጨማሪም በባህላዊ ክንዋኔዎች የመሳተፍ ነፃነትና ዕድል፣ እንዲሁም የልማት አካል የሆነው የባሕሉ መበልፀግ ከመሰረታዊ መብቶች አንዱ እንደሆነ ያስረዳል:: የ **2004 ሂዩማን ዴቬሎኘመንት ሪፖርት (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2004)** በበኩሉ ሁለት ዋነኛ

ጭብጦችን አስፍሯል፡፡ የመጀመሪያው ባሕላዊ መብቶች፡ ለሰው ልጅ መብቶች መሠረታዊ መሆናቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የባሕላዊ መብቶች መረጋገጥ ደግሞ ለባሕል ጉዳይ ተገቢውን ቁብ ለሚሰጡ የልማት አካሄዶች የመጀመሪያ ወሳኝ እርምጃ መሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ አሳሳቢ ጉዳይን እንድናነሳ የግድ ይላል፡፡ የተለያዩ ባሕሎች ባንድ ቦታና ጊዜ በሚገኙበት ሁኔታ "የባሕላዊ መብት መረጋገጥ" የሚለው ሃረግ ምን ፍች ይኖረዋል? በተለይም፣ አንዱ ንዑስ የኅብረተሰብ ክፍል በዋንኛው ኅብረተሰብ ባህል መከበር የተነሳ በቀጥታ ተጠቂ ሆኖ በሚገኝበት ሁኔታ የመብቶች ግጭት አይከሰትም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ፡፡ የዚህን ችግር ምንነት ቀጥለን በምሳሌ እናብራራ፡፡ የብሄር-ብሄረሰቦች መብት መረጋገጥ በሚነገርላት በዛሬዋ ኢትዮጵያ ብዙዎቹ -- እንዲያውም ከሞላ ጎደል ሁሉም -- የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች በውስጣቸው በሸክላ ሥራ፣ በቆዳ ማልፋት፣ ብረት ቅጥቀጣ፣ ወዘተ… የተሰማሩ የሙያተኛ ማኅበረሰቦችን እንደሚያቅፉ ይታወቃል፡፡ እነዚህም የሙያተኛ ማህበረሰቦች ይብዛም ይነስ በሁሉም ዘንድ የተናቁ የተገፉና የተጨቆኑ ናቸው፡፡ ታዲያ፡- የብሄር ብሄረሰቦቹ ባሕላዊ መብት መረጋገጥ በቀጥታ ትርጉሙ ከተወሰደ የነዚህ የሙያ ማኅበረሰቦች በቀጣይነት መናቅና መገፋትን በማስከተል አባሎቻቸው እንደ ሰው ያላቸውን መብት በመግፈፍ ሌላው ቀርቶ ለትምህርትና ለጤና አገልግሎት ያላቸውን የዕድል በር ይዘጋል፡፡

የባሕልና የልማትን ቁርኝት ስናስብ ሁለት የተለያዩ እይታዎች ሊኖሩን ይችላል፡፡ አንደኛው በጣም አጠቃላይ በሆነ መንገድ ባህልን ለማንኛውም የልማት ችግር ምክንያት እያደረግን በሰበብ ጨዋታ የምንዘፍቅበት እይታ ነው፡፡ ለምሳሌ "በሃገራችን ድህነት የነገሰው የሥራ ባሕል ስለሌለን ነው" የሚለው አይነት ልቅ አባባል ይህን እይታ ይወክላል[2]፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ዝርዝርና ተጨባጭ ከሆኑ የልማት ወይም የዕድገት ተግባራት ጋር ተያያዥ ለሆኑ የባሕል ገፅታዎች ተገቢውን ቁብ ሰጥተንና በበቂ አበክረን በመገንዘብ ተግባሮቻችን እንዲሰምሩ ለማድረግ የምንጣጣርበት አስተያየትና አካሄድ ነው፡፡ ለዚህኛው የኤች.አይ.ቪ. ኤድስን መስፋፋት ለመግታት አንዳንድ ባሕላዊ የፍትወት ግንኙነቶችን ለመገንዘብ የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ "ማኅበረሰባዊ ውይይቶች" ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ማኅበረሰባዊ ውይይቶች ካስገኟቸው ግኝቶች አንዱ ሰዎችን ወዳልተገደበ የፍትወት ግንኙነት ይጋብዙና ያበረታቱ የነበሩ የባህል ይዘቶችን (ኤለመትስ) ለይቶ በማውጣት፣ ግንዛቤ ማስጨበጥና፣ ከባሕል መሪዎች ጋር በመተባበር የባሕል ለውጥ ማምጣትን ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው፣የአንዳንድ የባህል ይዘቶች (ኤለመትስ) መለወጥ ወይም እንዳሉ መቀጠል የኅብረተሰቡ "የሞት-የሽረት" ጥያቄ ሆኖ

---

[2] ይህን ዓይነቱን አስተያዬት በተመለከተ ሜሪ ዳግላስ (2004) የሰጠችውን ትችት መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

ሲገኝ በፍጥነት መለወጣቸው የግድ መሆኑንና መለወጣቸውንም ነው:: እዚህ ላይ፤ ታሪክ የብዙ ራሳቸውን ለተፈላጊ ወሳኝ ለውጥ ሳያዘጋጁ በመቅረት ባሕላቸውን መለወጥ ያልፈለጉ ወይም የተሳናቸው ኅብረተሰቦች መቃብር መሆኑን ልናስምርበት ይገባል:: የባሕል እንዳለ መቀጠል አንፃራዊ መሆኑንና፤ የባሕል መለወጥ ፍፁማዊ መሆኑንም እንዲሁ::

በሕልና ልማት (ማለትም አዎንታዊ ኅብረተሰባዊ ለውጥ) ቁርኝት አላቸው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከመነሳታችን በፊት፤ ጥያቄውን ራሱን ለመረዳት እንሞክር:: ምን-ምንን ሊሸፍን እንደሚችልም እንመልከት:: በመጀመሪያ በሁለቱ፤ በባሕልና በልማት፤ መካከል ልዩነት አለ ወይ ብለን ስንጠይቅ፤ እነዚህ ሁለቱ በሰፋፊ ትርጉሞቻቸው እጅግ ተነባባሪ ፅንሰ-ሃሳቦች ከመሆናቸው የተነሳ ጥያቄውን እንዳለ ለመመለስ መሞከሩ የዙሪያ-ጥምጥም አመክንዮ ወስጥ የሚከተን ይመስለኛል:: እርግጥ ሁለቱንም አጥብበን በመመልከት ባሕልን እንደ ነባር-ልምድ (ትራዲሽን) ልማትን ደግሞ እንደ ማዘመን (ሞደርናይዜሽን) ከወሰድናቸው የተለያዩ ከመሆን አልፈው ተቃራኒም ሊሆኑ ይችላሉ::

በእኔ አስተያዬት፤ ባሕልና ልማት (አዎንታዊ ህብረተሰባዊ ለውጥ) ምክንያታዊ ቁርኝት አላቸው ወይ? የሚለው አጠቃላይ ጥያቄ በበቂ ይመለስ ዘንድ የሚያቅፋቸው ንዑስ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ተተንትነው መቅረብ ይኖርባቸዋል::

*የመጀመሪያው ዝርዝር ጥያቄ፤* ልማት ይመጣ ወይም ይገኝ ዘንድ የግድ አስፈላጊው የባሕል ለውጥ አስቀድሞ መምጣት አለበት ወይ? *ሁለተኛው፤* አስፈላጊው የባሕል ለውጥ ቀድሞ ከመጣስ፤ የግድ ልማት ይከተላል ወይ? የሚለው ሲሆን፤ *ሦስተኛው ጥያቄ፤* አንድ አዲስ የባሕል ኤለመንት ይመጣ ወይም ይገኝስ ዘንድ አስቀድሞ አስፈላጊ የሆነ ልማት መምጣት አለበት ወይ? *አራተኛው፤* አስፈላጊው ልማት ቀድሞ ከመጣስ፤ የግድ አዲስ የባሕል ኤለመንት ይከተላል ወይ? *የመጨረሻውና ዋነኛው ጥያቄ* የሚከተለው ነው:: አስቀድመን እንዳየነው እጅግ ሁላቀፉ የሆነውን ባሕል ለሁዋላ-ቀርነትም ሆነ ለልማት ምክንያት ነው ማለት ምን ትርጉም ይኖረዋል? ባይሆን ይህ እና ያ ነባር ልማድ ለዚህ ወይም ለዚያ ኋላቀርነት ምክንያት ሆኖ ይቀርብ እንደሆነ እንጅ እንዴት ሁሉን የሚያቅፍ ባሕል ልማትን ያመጣል ወይም ያግዳል ሊባል ይችላል? ልማትን በማገድ በኩል ባሕልን ተጠያቂ ማድረጉስ ሰበብ ከማላከክ፤ ተጠያቂነትንና ሃላፊነትን ከዘመኑ ትውልድ ትከሻ ወዳለፈው ከማሻገር፤ እናም ለምሁራዊ ስንፍና ሽፋን ከመስጠት ያለፈ ምን የሚፈይደው ይኖረዋል?

በሕልና ልማት ቁርኝት አላቸው ወይ? ብለን ስንጠይቅ፤ ምክንያታዊ ቁርኝት እንዳላቸው፤ ማለትም በአንዱ ላይ የመጣ ለውጥ በሌላው ላይ ትይዩ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መጠየቃችን መሆን አለበት:: ይኸ ሳይሆን ቀርቶ፤ እንዲያው "በአንደኛው ዘንድ በጎ ለውጥ ይመጣ ዘንድ ሌላኛውም ቢታሰብበት ተገቢ ይሆናል" ዓይነት አስተያዬት የማቅረብ ነገር ከሆነ ግን፤ ይህ ተጨባጭ እውነታን የመግለፅ ጉዳይ ሳይሆን ምክር-አዘል አባባል (normatve statement) የመሰንዘር ነገር ብቻ በመሆኑ አከራካሪ አይሆንም:: በዛሬው ዘመን፤ ልማት በሚወጠንበት ጊዜ የአካባቢው ባሕላዊ ነገሮች ወይም ነባር-ልምዶች ታሳቢ


መሆን የለባቸውም የሚል ክርክር የሚነሳ አይመስለኝም፡፡

ወደ ዋናው የባሕልና ኅብረተሰባዊ-ለውጥ ትስስር ጥያቄ ስንመለስ፤ ኅብረተሰባዊ-ለውጥን አንቀሳቃሽ ኃይል አስመልክቶ የተነሳው ክርክር ለዋነኛዎቹ የህብረተሰብ ሳይንስ የቲዮሪ ጎራዎች መከሰት ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ እድሜ-ልካቸውን ምርምር ያካሄዱ ስመ-ጥር ምሁራን ያቀረቧቸውን ትንተናዎችና የሰጡዋቸውን ምላሾች ላንድአፍታ እንቃኝ፡፡

አንትሮፖሎጅስቶች ለጥናት የሚሰማሩባቸው ኅብረተሰቦች አነስተኛነት ባሕልን እንዳለ በውሕድነቱ ወስደው ያጠኑት ዘንድ ሲፈቅድላቸው፤ ባሁኑ ዘመን ተንሰራፍተው በሚገኙት ሰፋፊና ውስብስብ ኅብረተሰቦች ላይ የሚያተኩሩት ሶሲዮሎጅስቶች ደግሞ ለየት ያለ መንገድ ይከተሉ ዘንድ ሁኔታው የግድ ይላቸዋል፡፡ ለነገሩ፤ ይህ ለየት ያለ መንገድ ከራሱ ከአንትሮፖሎጅ ጭምር የመነጨ ነበር፡፡ በዩናይትድ-ስቴትስ ስር ከሰደደውና ባሕልን በራሱ በብቸኝነቱ ማጥናት ይቻላል ከሚሉት ካልቸራል-አንትሮፖሎጅስቶች ተለይተው የወጡት የፈረንሳይና የብሪታንያ ፋንክሽናሊስትና ስትራክቸራል-ፋንክሽናሊስት ርዕዮት የሚያራምዱ ሶሽያል-አንትሮፖሎጅስቶች ኅብረተሰባዊ መዋቅርና አደረጃጀት ላይ አተኮሩ፡፡ በሶሲዮሎጅም የዚህ መስመር መሥራች ታዋቂው ኤሚል ደርካይም ነበር፡፡

የሶሲዮሎጅ የዕውቀት ዘርፍ ሲፈጠር ጀምሮ ኢኮኖሚው ባንድ በኩል፤ እንደ ሃሳብ፤ ባሕልና፤ ነባር ልምድ ያሉ ሰብአዊ ክስተቶች በሌላ በኩል ሆነው በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ዘመናት ያስቆጠረ ክርክር በተለያዩ መልክና ስም እንደቀጠለ አለ፡፡ ሁሉም የክርክሩ ተሳታፊዎች አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መቀበላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንዱ ጎራ ለኢኮኖሚው ሌላው ጎራ ለሰብአዊ ክስተቶቹ የመጨረሻ ወሳኝነት ሚና ስለሚሰጡ ልዩነታቸው እንዳለ ዘልቋል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ጎራዎች በተጨማሪ የኅብረተሰብ አባላትን ባሕርይ መልክ ለሚያሲዙ ህብረተሰባዊ ሥርዓታት ሚና ከፍተኛ እውቅና የሚቸረው ሦስተኛ ጎራ ሆኖ በክርክሩ ውስጥ ትልቅ ቦታ ይዟል፡፡

ሦስቱ የባሕል ክፍሎችና የቲዮሪ ጎራዎች



እነዚህ ሦስት ጎራዎች ቀደም ብለን ካየናቸው ሦስት የባሕል ክፍልፋይ አካላት ላንዱ ወይም ለሌላው፤ *ማለትም ለቁስ-አካላዊ ነገሮች/ንብረት፤ ወይም ለሃሳቦች፤ ሀብረተሰባዊ ልማዶችና፤ አመለካከቶች፤* ወይም *መልክ-ለያዘ ባሕርይ* የወሳኝነት ሚና ይሰጣሉ ማለት ነው:: በተጨማሪ፤ ባጋጣሚ ሳይሆን፤ ያነሱዋቸው ጥያቄዎች መሰረታዊነትና የትንታኔአቸው ጥልቀት ባፈራላቸው ዘላቂ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታቸው የተነሳ የሶሲዮሎጅ የዕውቀት-ዘርፍ መስራች አባቶች ተብለው የሚወሰዱት *ካርል ማርክስ* (1818 - 1883)፤ *ማክስ ቬበር* (1864 - 1920)፤ እና *ኤሚል ደርካይም* (1858 - 1917) የእነዚህ ሦስት የቲዮሪ ጎራዎች መስራቾች ናቸው::

በወግ፤ ልምድ፤ ዕምነት፤ አመለካከት፤ ወዘተ... በአንድ በኩልና በኅብረተሰባዊ-ለውጥ መካከል መተሳሰር እንዳለ ማለትም አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር በጉዳዩ ላይ ንድፈ ሃሳብ ካቀረቡ ፀሐፊዎች እጅግ ብዙዎች የሚስማሙበት መደምደሚያ ነው:: ይሁንና ጠለቅ ብለው በመግባት ከሁለቱ የትኛው የኅብረተሰብን ዕድገት በማንቀሳቀስ በኩል የበላይነት እንዳለው በሚያወሱበት ጊዜ ተንታኞቹ በሁለት ይከፈላሉ:: አንዳንድቹ ወደ ኢኮኖሚው ሲያጋድሉ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ባሕል የበላይነት ያዘማሉ::

ከፊተኞቹ አይነት የኅብረተሰብ ተመራማሪዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ካርል ማርክስ ሲሆን፤ ከኋለኞቹ አዘውትሮ የሚጠቀሰው ደግሞ ማክስ ቬበር ነው:: ማርክስ፣ በኢኮኖሚና በላዕላይ-መዋቅር መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣ አንዱ በሌላው ላይ፣ በየተራቸው ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ ካስቀመጠ በኋላ "ዞሮ ዞሮ" ኢኮኖሚው በመሪነት ብቅ ይላል በማለት ለኢኮኖሚው ቅድሚያ ይሰጣል (ማርክስና ኤንግልስ 1962: 304)::

ቬበር በበኩሉ፤ ምንም እንኳን ቀደም ሲል የማርክስ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ያሳደረበት ቢሆንም[3]፤ የማርክስን ወደ ኢኮኖሚው ያዘመመ አስተያየት አቃናለሁ ብሎ በመነሳት ወደ ላዕላይ-መዋቅሩ እያደላ ሄደ:: በዚህ ጥረቱ ነው እንግዲህ የካፒታሊዝምን በአውሮፓ ምድር መነሳት ከኘሮቴስታንት ሃይማኖት መመሥረትና ካስከተለው ህሊናዊና ሥነ-ምግባራዊ ለውጥ ጋር የሚያያይዘው:: ያም ሆኖ ታዲያ፤ የቬበር ሃተታ የሚመለከተው ባጠቃላይ የኘሮቴስታንትን ዕምነት ሳይሆን የዚህ ዕምነት አንድ አነስተኛ ክፋይ የሆነውን ካልቪኒዝምን፤ የኘሮቴስታንት ዕምነት የተሰበከበትን ምድር ሁላ ሳይሆን አውሮፓን ብቻ ነበር (ቬበር [1930] 1971)::

በተጨማሪ፤ ለቬበር የታየው የካልቪኒዝምና የብልፅግና ግንኙነት ቀጥተኛ ሳይሆን ዘወርዋራ ሆኖ ነበር:: ማለትም፤ ቬበር የካልቪኒዝም ዕምነት ወይም

[3] ይህንን ተፅዕኖ ለማሳዬት፤ ራሱ ቬበር በፅሁፍ ያስቀመጠውን በእንግሊዝኛ ትርጉሙ እንዳለ ቀጥለን አስፍረነዋል:: "Not ideas, but material and ideal interests, directly govern men's conduct. Yet very frequently the 'world images' that have been created by 'ideas' have, like switchmen, determined the tracks along which action has been pushed by the dynamic of interests." (Weber 1946: 280)

የዚህ ዕምነት ተከታይነት በራሱ ታታሪ ያደርጋልና ያበለፅጋል የሚል ነገር አላሰፈረም:: ይህንን በተመለከተ የእሱ ስሌትና አባባል ባጭሩ እንደሚከተለው ነው:: የካልቪኒዝም ዋነኛ ቀኖና "የማንኛውም ሰው መፅደቅ ወይም መኮነን በራሱ በሰውየው ዕምነትና ምግባር የሚወሰን ሳይሆን አስቀድሞ በፈጣሪ የተወሰነ ነው" የሚለው የ"ቅድመ-ፍርጃ" (predestination) ሲሆን፤ የዚህ ተጨማሪ የሆነው ቀኖና ደግሞ "ማንም ሰው ለፅድቅ ከተመረጡት ጥቂቶች አንዱ መሆን አለመሆኑን ሊያውቅ አይቻለውም" ይላል:: በዚህም የተነሳ በካልቪን ተከታዮች ዘንድ ይህ ነው የማይባል ጭንቀት እንደነገሰና አማኞች ሁሉ በ"በምሕረት ጉዳይ በጭንቀትና መርበትበት" (salvation panic) እንደተዋጡ ቬበር ይጠቁምና፤ ሕዝቡን በከፊልም ቢሆን ለማረጋጋት ሲባል ደግሞ "አንድም መልካም ዛፍ መርዘኛ ፍሬ እንደማያፈራ ሁሉ፤ ሰዎችም ያለ እግዚአብሄር ቡራኬ በዚህ ዓለም ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ አይቻላቸውም" እና በዚህ ዓለም ስኬታማ ሆኖ መገኘት ለፅድቅ የመመረጥ ምልክት ሆኖ ሊወሰድ ይችላል የሚል ሃሳብ የእምነቱ ማለዘቢያ ሆኖ ቀረበና ተወሰደ:: በዚህ ዓይነትም የቅድመ-ፍርጃው አለመታወቅ ቀኖና የፈጠረው ጭንቀት ረገብ እንዲል ሆነ:: ጭንቀቱ ይበልጥ ይረግብ ዘንድ ደግሞ፤ "አማኞች ሥራን ጨምሮ በሚያደርጉት ሁሉ እግዚአብሄርን ማክበር እንደሚኖርባቸውና ከዚህ ዝንፍ ብሎ ወደ ስንፍና፤ ደካማነት፤ መንደላቀቅና፤ ኪሳራ መውደቅ የኩነኔ ፈጣን ምልክት ነው" የሚል ዕምነት ተጨመረበት:: ከዚያ ወዲያ እንግዲህ፤ እነዚህ በዚያን ዘመን በምዕራብ-አውሮፓ ይኖሩ በነበሩ የፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖታዊ ልባስ ያገኙት ያቆጣቢነት፤ ሥነ-ሥርዓት አክባሪነት፤ በልኩ መኖርና፤ ለስኬታማነት መጣጣር ፍላጎቶችና ባሕርዮች ተዳምረው ከካፒታሊስት መንፈስ ጋር አብሮ የሚሄድ የሥራ ሥነ-ምግባር ለማነፅ ረዱ (ዌብስተር 1984: 47-8)::

ከላይ ያቀረብነው ሀተታ እንደሚያሳየው፤ ቬበር ከፕሮቴስታንት ዕምነት የካፒታሊስት መንፈስ ካልመነጨ በስተቀር የኢኮኖሚ እምርታ አይደረግም፤ ወይም የካፒታሊስት ዕድገት ይመዘገብ ዘንድ የግድ የፕሮቴስታንት ዕምነት ያስፈልጋል ወደሚል መደምደሚያ አልደረሰም ነበር:: ነገር ግን፤ በአንዳንድ ተከታዮቹ አማካይነት፤ ቬበር በአውሮፓ የተካሄደውን የሥርዓት ሽግግር አስመልክቶ ያቀረበውን ትንታኔ በመላ ዓለም እንደሚሰራ ቲዮሪ ከፍ ለማድረግ የተያዘው ሙከራ፤ ሳይውል-ሳያድር ጃፓን ባስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሳቢያ ከጥያቄ ውስጥ ገባ። ቬበራውያን ተከራካሪዎችም የመውጫ ቀዳዳ ፍለጋ፤ የጃፓንን አንዳንድ ለየት-ያሉ የባሕል ይዘቶችን -- በተለይም ሽንቶይዝምን -- እየጠቃቀሱ ቬበር አውሮፓን አስመልክቶ ያቀረበውን ንድፈ-ሃሳብ ዓለምአቀፋዊ ገፅታ በመስጠቱ ሂደት ገፉበት:: በዚያን ጊዜ ጃፓን እንዴት እንደነ ቻይናና ሕንድ ካሉት የእስያ ሃገሮች በባሕሏና በህዝቧ ሥነልቦና የተለየች እንደሆነች አስረግጠው መከራከራቸውን ቀጥለውበት ነበር:: ይኸው ዛሬ ደግሞ የቻይናንና የሌሎች ብዙ የእስያ ሀገሮችን በኢኮኖሚ ዕድገት መመንጠቅ በ"ሃሳባዊ-አመለካከት" ላይ የተመሰረተውን ንድፈ-ሃሳባቸውን በእጅጉ ስለተፈታተነባቸው ከዚህ ማጥ ለመውጣት በሚያደርጉት ሙከራ ሳቢያ "ልዩ

ስለሆነው የእስያውያን ካፒታሊስታዊ ባህል" በሰፊው እያወሩልን ነው:: በዚህ ሂደት ከቀጠልን እንግዲህ፤ ለጊዜው የቀረውና ተራውን በመጠባበቅ ላይ የሚገኘው በዋነኛነት የአፍሪካ አህጉር ብቻ ስለሆነ፤ እሱንም የልማት አድባር የታረቀችው ቀን ያንን ልማት ያስከተለው የአፍሪካ ባሕል ነው የሚል አዋጅ ሳይነገር የሚቀር አይመስለኝም::

ኤሚል ደርካይም የተባለው፣ በቬበር የዕድሜ-ዘመን የኖረ፣ ታላቅ የኅብረተሰብ ተመራማሪ ወግ፤ ልምድ፤ ዕምነት፤ አመለካከትና፤ ወዘተ... በልማት ላይ ለሚያሳድሩት ተፅዕኖ እውቅና እየሰጠ እያለ፤ አመጣጣቸውን በተመለከተ ግን ከቬበር የተለየ ትንታኔ ያቀርባል:: ደርካይም ኅብረተሰቦችን በሁለት ዓቢይ ክፍሎች ለይቶ ይመለከታል:: በሱ አስተያየት፤ የሙያ ወይም የሥራ ክፍፍል ያልዳበረባቸው ቀደም ያሉት፤ አነስተኛ (simple)፤ እና ቅድመ-ኢንዱስትሪ ኅብረተሰቦች አባሎቻቸው በሚጋሯቸው ወይም በጋራ በተደመጡ ደንቦቻቸውና ወጎቻቸው ላይ የተመሠረተ አንድነት ሲኖራቸው፤ የሙያ የሥራ ክፍፍል ወደፊት የገፋባቸው፡ ሰፋፊና ውስብስብ የሆኑቱ የኢንዱስትሪ-ዘመን ህብረተሰቦች አንድነት ግን የተመሠረተው አንዱ የኅብረተሰብ አካል ለሌላው አካል በሚያበረክተው የአገልግሎት መደጋገፍና ከዚህ በሚመነጨው ጥብቅ ትስስር ላይ ነው፤ በመሆኑም ከበፊተኞቹ ሲወዳደር በኋለኛዎቹ ዓይነት ህብረተሰቦች ውስጥ የሰዎች የወል ደንቦችና የጋራ ህሊና (collective conscience) ጠንካራ ስላልሆኑ፤ የሰዎችን አመለካከትና ተግባር ይቆጣጠሩ ዘንድ የሕግ ሥርዓቶች ዋነኛ እየሆኑ ይመጣሉ (ደርካይም [1893] 1984)::

አገራችን ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ዕድገት ወደፊት ከገፋት ከአውሮፓ አገሮች ጋር ግንኙነት ከፈጠረችበት ጊዜ አንስቶ፤ የኋላቀርነቷን ምክንያቶች ለይቶ ለማወቅና ለማሳወቅ የውጭና እያደርም ሃገሬው ምሁራን የየበኩላቸውን ሞክረዋል:: በተለይም የምዕራቡ ሥልጣኔ የኢንዱስትሪ አብዮቱን በማካሄድ የተፋጠነ የኢኮኖሚና የሶሺያል እርምጃዎችን ማስመዝገብ ከጀመረበትና በምዕራቡ ዓለምና በሃገራችን መካከል ያለው የዕድገት ልዩነት እጅግ እየሰፋ መሄድ ከጀመረበት ከ18ኛው ምዕተ-ዓመት ወዲህ ወደ ሃገራችን በብዛት ብቅ ማለት የጀመሩት አውሮፓውያን ሚሲዮናውያንና አገር ጎብኝዎች ይኸን ጉዳይ በተመለከተ የየበኩላቸውን ብለዋል:: ይሁንና የአብዛኛዎቹ አመለካከት በአንድ አቅጣጫ ያነጣጠረ ነበር:: ይህም የአገሪቱን ኋላቀርነት በአገሬው ዕምነት፣ ወግና ልምድ ላይ የሚላክክ ነበር::

በ19ኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ አካባቢ እንደ ፕሮቴስታንት ያለ የክርስትና ዕምነት "ተሃድሶ" እንዲያመጡ በእንግሊዙ ቼርች ሚሺነሪ ሶሳይቲ (Church Missionary Society) ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ጎባት፣ አይዘንበርግና፣ ክራፕፍ፤ ፈጣሪ ትክክለኛ ሃይማኖት ወይም ዕምነት የያዘን ህዝብ በሃብትና ብልፅግና እንደሚሸልም፣ የእንግሊዝን የኢንዱስትሪና የግዛት የበላይነትን በማስረጃነት በማቅረብ ይከራከሩ ነበር:: የኢትዮጵያንም ኋላቀርነት ከተዋህዶ ክርስትና ዕምነቷ የመነጨ እንደሆነና፣ የዕምነት መሻሻል ብታደርግ ግን ወደ ብልፅግና

ኅዳና እንደምታመራ ደጋግመው ያሰምሩበት ነበር። የክርክራቸውንም አቅጣጫ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ይልቅ ወደ ባሕላዊ ጉዳዮች ማዞርን ዋና ስልት አድርገውት ነበር (ቻፐል 1986: 26-37)።

በዚህ ስልት በመጠቀም፣ ክራኘፍ የተባለው ሦስተኛው ሚሲዮናዊ "ምዕንተ ማርያም" ብለው ማደሪያ ለሚሹ መንገደኞች መጠጊያ የመስጠት ባሕልን፣ የሆቴል ኢንዱስትሪ እንዳይስፋፋ ያደረገ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕክል ነው በማለት እስከመተቸት ደርሶ ይህን ትችቱን በማስታወሻው ላይ ያሰፍራል። ታዲያ ሰው የእጁን አያጣም እንደሚባለው፣ ሰውዬው የኢትዮጵያ ቆይታውን ጨርሶ ወደ ምፅዋ ወደብ በሚጓዝበት ወቅት አደጋ ይደርስበታል። አደራ ቢሌ በሚባል ባላባት ወሎ ላይ ይዘረፍና ያን የጠላውን "ምዕንት ማርያም፣ አሳድሩኝ" እያነበነበና ለኢትዮጵያ ባሕል ያለውን ንቀትና የማስታወሻ ደብተሩን እንደጨበጠ ምፅዋ ገባ (ቻፐል 1986: 32-4)።

ከላይ የተወሳው አስተያየት በተለያየ መልኩ እስከ ዛሬው ጊዜ ቢዘልቅም፤ ከዚህ የተለየ አስተያየታቸውን የቸሩ ኢትዮጵያዊ ምሁራን አልጠፉም -- በተለይ ቆየት ባለው ጊዜ። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን በጽሑፍ ያቆዩን፡ በሃያኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ የአውሮፓንና የጃፓንን ሥልጣኔ በቦታው ተገኝተው የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከሚሲዮናውያኑ የተለየ አቋም ነበራቸው። በእነሱ አስተያየት የኋላቀርነታችን ዋነኛ ውስጣዊ ምክንያቶች መዋቅራዊ (structural) ናቸው። ከነዚህ ምሁራን መካከል በጉዳዩ ላይ ዝርዝር ሃተታ በሰጡት በነጋድረስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አስተያየት ላይ ለአፍታ እናተኩር።

በነጋድረስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አስተያየት የኢትዮጵያን ዕደገት ቀፍድደው የያዙት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። አምራችነት የማይጋብዘው ያልተረጋገጠ የመሬት ባለቤትነት መብት፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የብዙሃኑ ባለህብት አለመሆን፣ የህግ የበላይነት አለመረጋገጥ፣ የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ እንዳይሄድ የሚያደርጉት የሕዝብ ቁጥር ማነስ፣ የመገናኛ መስመሮች አለመኖር፣ የመገበያያ ገንዘብና በተለይም የአነስተኛ ምንዛሪ (ሽርፍራፊ) እጦት፣ ወዘተ ናቸው። ነጋድራስ ያተኮሩባቸው የኋላቀርነት ውስጣዊ ምክንያቶች እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ እንጅ ባዕላትን ማክበር ወይም እጀ-ጠቢባንን ዝቅ አድርጎ ማየትን የመሳሰሉትን ወጎችና ልማዶች አይደሉም። እዚህ ላይ ውስጣዊ ምክንያቶችን አልን እንጂ የውጭ ምክንያቶችን በተመለከተ ነጋድረስ ገብረ ሕይወት የሚያሰምሩባቸው ሌሎችም ጉዳዮች ነበሩ። ከነዚህም አንዱ አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ዕቃዎች በሙሉ እንደ ቆዳና ቡና የመሳሰሉ ጥሬ ሸቀጦች መሆናቸውና እሳቸው እንደሚሉት በዚህም የህዝቧን የሥራ ወይም የላብ ፍሬ ሳይሆን የመሬቷን ፍግ ሌላ ህዝብ ጉልበቱን ላፈሰሰበት ምርት የምትለውጥ ሃገር ሆና መቀጠሏ ነው (ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ [1924] 2002 ዓም)።

በአጠቃላይ ከኢጣሊያ ወረራ ማግስት የተፈጠረው የኢትዮጵያ ምሁር፣ የዕድገት ማነቆዎችን በተመለከተ ከነጋድረስ ገብረሕይወትና ከመሰሎቻቸው የተለየና በመሠረቱ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ የነበሩ ሚሲዮናውያን ይሰብኩት ከነበረው ጋር የሚቀራረብ አቋም ያንፀባርቀ ይመስለኛል።

በ19 መቶ ሃምሳዎቹና ስልሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የጊዜው ተራማጅ ግጥሞች፣ ልብ-ወለዶች፣ ቲያትሮችና፣ መጣጥፎች ያስተጋቧቸው ከነበሩት አስተያቶች አንዱ፣ ለአገራችን የኢኮኖሚ ኋላቀርነትና ላለመልማቷ ዋነኛ ህብረተሰባዊ ምክንያት ሆኖ የኖረው እጅ-ጠቢባንን የሚያጣጥለው፣ የውትድርናና የጦረኛ ሙያን ከፍ-ከፍ የሚያደርገው፣ የሰዎችን የወደፊት ዕድል ፍፁም ከነሱ ቁጥጥር ውጭ አድርጎ የሚያቀርበውና፣ ሌሎችንም መሰል ነባር-አመለካከቶች የሚያቅፈው ኋላቀር ባህላችን ነው፣ የሚለው ነበር። በርካታ የዘመኑ ግጥሞች፣ አጫጫር ልብወለዶች፣ ቲያትሮችና፣ ምሁራዊ መጣጥፎች ይኽንኑ ያንፀባርቁ ነበር (ለምሳሌ ያህል፣ መስፍን ወልደማርያም፣ 1966 ይመልከቱ)። ይህ ዘመን ሚሲዮናውያንና ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ ዝቅተኛና ከፍተኛ ትምህርት ላይ የበላይነት ያገኙበትን ድሕረ-የኢጣልያ ወረራ ወቅት ተከትሎ የመጣ እንደመሆኑ፣ ሁኔታው እጅግም አያስገርምም ይሆናል። በዚህም ሂደት ውስጥ የውጭ ሃገር ተመራማሪዎች የሥራ ውጤቶች፣ በተለይም የዶናልድ ሌቪን «ዋክስ ኤንድ ጎልድ» ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።[4]

እ.ኤ.አ. ከስልሳዎቹ አጋማሽ ጀምሮ አብዛኛው ወጣትና ምሁር በአጠቃላይ በአብዮታዊ ርዕዮተ-ዓለም፣ በተለይም በማርክሲስት ፍልስፍና ስር እየዋለ መጣ። በመሆኑም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኋላቀርነታችንን ለማስረዳት በተፈለገ ቁጥር የተለያዩ ሥርዓታዊ ምክንያቶችን መደርደር የተለመደ ሆነ።

እነሆ ደግሞ፣ ባለፉት ሦስት ዓስርተ-ዓመታት የተከሰተው የካፒታሊስት ኢኮኖሚና የምዕራቡ ሊበራል ዴሞክራቲክ ርዕዮተ-ዓለም የበላይነት መያዝ፣ እንደ ፍራንሲስ ፉኩያማ ያሉ ምሁራንን አፍ ሞልተው "ከንግዲህ ታሪክ አብቅቶለታል" ብለው እስከማወጅ ያደረሰ የተጋነነ የአመለካከት ዝንባሌ አስከትሏል (ፉኩያማ 1992)። በሌሎች ጥያቄዎች ላይ እንደደረሰው የአመለካከት ለውጥ ሁሉ፣ የዕድገትን ዋነኛ ማነቆዎች በሚመለከትም መሰል የተጋነነ የዕይታ መቀልበስ በመምጣት ላይ ያለ ይመስላል። የአመለካከት ለውጡ የውቀት መሰረት ያለውና የተሻሻለ ግንዛቤን የሚያስጨብጥ ከሆነ ማለፊያ ነው። ወደ ቀድሞው የተጋነነ "ባህላዊ ትንታኔ" (cultural explanation/paradigm) ከተመለሰ ግን ከ "ሰበብ-ጨዋታ" ባለፈ ምን እንደሚፈይድ አላውቅም።

በርካታ ምሁራንና ተከታዮቻቸው ለሃገራችን ኋላቀርነት ሲወርድ-ሲዋረድ የመጣውን የጦረኛና ያለመተማመን ጠባይ እንዲሁም ሥራን የመናቅ ባሕላችን

---

[4] ይኽ *ዋክስ ኤንድ ጎልድ* የተባለው የዶናልድ ሌቪን መፅሃፍ ያሳደረውን ጫና በተመለከተ ለተሰጠ ሃተታ የራስወርቅ አድማሴ 2006ን ይመልከቱ።

ነው የሚሉትን ዋነኛ ምክንያት በማድረግ ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን፤ ባሕል ወይም ነባር-ልምድ፣ ኅብረተሰባዊ ደንቦች፣ ወጎች፣ ልምዶችና፣ ልማዳዊ ሕጎች ለኢትዮጵያ ኋላቀርነት አበርክተዋል የሚባለውን አሉታዊ አስተዋፅዖ በሚመለከት በርግጠኝነት አንድ ነገር ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ባሕል ከብዙዎች የኋላቀርነት ምክንያቶች መካከል ግፋ-ቢል አንዱ ብቻ ይሆን እንደሆነ እንጅ ከዚያ አይዘልም፡፡ ሌሎች እንደ መልክዓ-ምድራዊ/አካባቢዊ፤ ሥርአታዊ፤ ኢኮኖሚያዊና፤ ፖለቲካዊ ምክንያቶች ከባሕል ያልተናነሰ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ለሰው ህይወትና ለንብረት ይዞታ አስተማማኝነት በማስገኘት ለልማትና ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሆነው የተረጋጋ ሥርዓት ለረዥም ጊዜ ያልነበረ መሆኑ ትልቁ ማነቆ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ይህን ኅብረተሰባዊ ትርምስ ያመጡት ደግሞ ሦስት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ክስተቶች ነበሩ፡፡ እነሱም የዘውድ ውርስን በሰላማዊ መንገድ ማካሄድ የተሳነው የፖለቲካው ሥርዓት፤ ቋሚ የንብረት ይዞታን የሚፃረረው የጉልት ሹመት-ንብረት ሥርዓት፤ እና የአራሹን መሬት ይዞታ በዘር-ሃረግ ከሚወረስ የወል የገባርነት ዕዳና አርሶ የመገልገል መብት ጋር አቆራኝቶ የኖረው የርስት ሥርዓት ነበሩ፡፡

በአውሮፓና በእስያ ዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገት ይገኝ ዘንድ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው ጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በተቀራኒው፤ በኢትየጵያችን የዚህ ሥርዓት በቀጣይነት አለመገኘት ደግሞ፤ ዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገትን ሊያመጣ ይችል በነበረው ቋሚ አቅድ ባለውና ሰላማዊ በሆነ የሥልጣንና የንብረት ሽግግር ሥርዓት ፋንታ ኅብረተሰባችን የሥልጣንና የንብረትን ውርስ ከሞላ-ጎደል ከሻሞ ባልተናነሰ ኅብረተሰባዊ ትርምስና ሁከት አማካይነት በማስተናገድ ኪሳራ ሲያስተናግድና ሲማቅቅ ኖሯል፡፡ ይኽ በጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት መታጣት በዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ጫና ምን ያህል ወሳኝ መሆኑን የሚያሳየን አንድ ተያያዥ ጭብጥ አለ፡፡ ከሳሃራ-በታች ባሉት ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ሁሉ ይኽ በጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት አለመኖሩንና ይህም ሁኔታ የየአገሮቹን እድገት ገትተው ካኖሩት ዋነኛ ማዕቀቦች መካከል አንዱ መሆኑን በአፅንዖት የሚያመልክቱ ምሁራን አሉ (ሪደር 1998)፡፡

ሁለተኛው፡ ባሕል ወይም ልምዶች ራሳቸው ከሌሎች የሥርዓቱ ይዘቶች እንደመነጩ መታወቅ አለበት፡፡ በዚህ ዓይነት በሰሜን ኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን (ማለትም ዘመናዊ አስተዳደር መዘርጋት እስከተጀመረበት እስከ ምኒልክ የግዛት ዘመን ድረስ) ተንሰራፍቶ ይገኝ የነበረውን "የዝርፊያ ባህል" ምንጭ ከስርዓቱ መዋቅር ውስጥ መሻት ይቻላል፡፡ "የዝርፊያ ባህል" የምንለው ህብረተሰባዊ ደንብ ሆኖ በአንድ አጋጣሚ በጉልበቱ አሸናፊ ሆኖ የወጣው ወገን የተሸናፊውን ሕይወት፣ ነፃነትና ንብረት ("ሰዎቹን" ጨምሮ) እንዲነጥቅና ጊዜ በተራው እስኪጥለው ድረስ የሁሉ ባለቤት እንዲሆን የሚፈቅድ ባሕል ከላይ ካነሳናቸው መረጋጋትን ከሚያፋልሱ ሦስት ክስተቶች የመነጨ ነበር፡፡

ባሕል በኢትዮጵያ ኋላቀርነት ውስጥ የተጫወተውንና አሁንም በመጫወት ላይ ያለውን ሚና በተመለከተ ውይይቱ ይቀጥል ይሆናል። መቀጠልም አለበት። ይሁንና በቀድሞው ሁኔታ ላይ ከማተኮር ይልቅ አሁን ያለውን ሁኔታ በመገንዘብና ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለብልጽግናና፣ ለኅብረተሰባዊ ልማት ጠቃሚ የሆነ የባሕል ለውጥ ለማስገኘት ማድረግ በሚቻለውና መወሰድም ባለባቸው እርምጃዎች ላይ ማተኮሩ ይበልጥ ጠቃሚ ይመስለኛል።

ቀድም ሲል ያነሳናቸው የኅብረተሰብ ተመራማሪዎች ሁሉም፡ በአጠቃላይ በባህልና በልማት መካከል መደጋገፍ መኖሩን እንደሚቀበሉ አንስተን ነበር። እኛም ከዚህ በመነሳት፣ የግድ አቻ የሆነ የባሕል ለውጥ በራሱ እስኪመጣ ከመጠበቅ ይልቅ ሰዎች አወንታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ለውጡ ከባህል በኩል ጭምር እንዲመጣና የልማቱን ሂደት እንዲያፋጥነው ማድረግ እንደሚገባ ልናሰምርበት እንወዳለን።

በዚህ ሂደት ውስጥ እንደ ትምህርት ቤቶችና የመገናኛ ብዙሃን ባሉ መድረኮች አማካኝነት ከሚከሰተው አዝጋሚ የባህል ለውጥ በተጨማሪ፣ ፈጣን የሆነ የባሕል ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል ኅብረተሰባዊ መሣሪያ በኅብረተሰቡ፣ በተለይም በመንግሥታዊ አውታሮች እጅ ይገኛል። ፋላጎቱና ቆራጥነቱ ካለ፣ ያለንበት ሁኔታና ጊዜ የሚጠይቋቸውን ሕጎችንና ደንቦችን በስፋት በመደንገግ፣ በማሻሻል፣ በማሳወቅ፣ ሥራ ላይ በማዋልና፣ በማስከበር፣ በአጭሩ የሕግ መዋቅሮችን በማዳበር ለልማትድጋፍ ሰጭ የሆኑ ባሕሎችን መፍጠርና መንከባከብ፣ ጎጅ ወይም ጎታች የሆኑትን ደግሞ መግታትና በሂደት ማጥፋት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ካሉት እጅግ ኂላቀር ከሆኑ ሃገሮች አንዷ ብትሆንም፣ ከጠቅላላው አለማቀፋዊ ለውጥና ዕድገት ጋር በተያያዘ፣ ህብረተሰቧ ሰፊ፣ ዘመናዊና፣ ትስስሩ ወደ በዛ (large-scale modern and complex) ኅብረተሰብነት ተሸጋግሯል። በአሁኑ ጊዜ በአንድ ገበያ፣ በአንድ የሶሽያል መድረክ፣ ወይም የፓለቲካ ሥርዓት ጎን ለጎን የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ የመልክዓ-ምድርና የባሕል አካባቢዎችና ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመጡ ናቸው። ቀደም ብለን የጠቀስነው ሶሽዮሎጂስቱ ኤሚል ደርካይም እንደሚያስገነዝበን ደግሞ፣ በዚህ አይነቱ ሁኔታ የሰዎችን አመለካከት፣ ባሕርይና፣ ተግባር በዋነኛ ነት የሚቀርፁና የሚመሩ፣ በጋራ የተደመጡ ደንቦችና ወጎች (shared values and norms) ወይም የጋራ ህሊና (collective consciousness) ሳይሆኑ፣ የሕግ ሥርዓቶችና መዋቅሮች ናቸው። በእንደዚህ፣ የሕግ ሥርዓቶቻችንና መዋቅሮቻችን ባሕላችንን ጊዜው በሚጠይቀውና በሚፈቅደው አቅጣጫና ፍጥነት በመለወጡና በመገንባቱ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ በእጃችን ያሉ መሳሪያዎች ሆነዋል። በነዚህ በተገቢው መገልገሉና ክፍት የሆነ ዕድልን አለማሳለፉ የኛ ፋንታ ነው።

ከዚህ ጋር ወደ ተያያዘ ቁም ነገር የሚያመራንን አንድ ገጠመኜን ላንሳ። የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ በሃገራችን አድጎ የአማርኛ ቋንቋን አቀላጥፎ የሚናገረው

የኖርዌዩ ዜጋ ዶ/ር ዩሃን ሄላንድ ስለ ኢትዮጵያ የዕድገት ማነቆዎች በምንወያይበት ወቅት አንድ ትዝብቱን አነሳብኝ፡፡ "በአማርኛ ቋንቋ ሜንቴናንስ (maintenance) ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ እንደሌለውና፣ ጥገና ወይም እድሳት የሚሉት ቃላት አንድ እንደ ሕንፃ፣ አውራ-ጎዳና፣ ወይም ተሽከርካሪ ያለ ቁሳዊ ነገር ወይም ንብረት እስኪበላሽ ድረስ ቆይቶ ከዚያ በኋላ የሚደረግ ማስተካከልን ማለትም ጥገና ማድረግን እንጅ እየተገለገሉ በዚያውም እንደ ነበር ጠብቆ ማቆዬትን እንደማያመለክቱ ታውቃለህ ወይ? ደግሞም የቃሉ አለመኖር እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ሁሌ የሚደረገው አንድ ነገር ተበላሽቶ ወይም አልቆ እስከሚያበቃለት ቆይቶ ከዚያ ወደ እድሳት መግባት እንደሆነ ልብ ብለሃል ወይ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ይህ ውይይታችን በነገሩ ላይ እንዳስብበትና ከሥራ ባልደረቦቼም ጋር እንድወያይበት አደረገኝ፡፡ ጉዳዩ ሜንቴን ማድረግ፣ ወይም "በጥቅም ላይ እያዋሉ እንደ ነበር ጠብቆ ማቆዬት"፣ ወይም ባጭሩ "ማንበር"፤ የሚል ገላጭ ቃል አለመኖርን ብቻ ሳይሆን፤ የተገላጨን ደንብ ወይም ስርዓትን አለመኖር የሚያመለክት ነው፡፡ በሃገራችን "ነገሮችን እየተጠቀሙ የማንበር" አሰራር ወይም አካሄድ አለመኖርን በተመለከተ በየአመቱ ለከፍተኛ ኪሳራ የሚዳርገንና፤ ካወቅንበት ደግሞ በቀላሉ ልንሸፍነው የምንችል፤ የአሰራርና የሥርአት ክፍተት አለ ማለት ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ሌሎችም ልንጨነቅባቸው የሚገቡና ልንደፍናቸው የምንችል ለልማታችን ማነቆ የሆኑብን የሥርዓት ክፍተቶች ሞልተዋል፡፡

እዚህ ላይ ደግሞ፤ እንዴት እነዚህ ዓይነቶችን የልማት እንቅፋቶች ለማስወግድ እንደሚቻል ሁለት የቅርብ ጊዜ ተሞክሮዎች ለምሳሌ ያህል ብቻ ልጥቀስ፡፡ ሁለቱም ምሳሌዎች ትራፊክን የሚመለከቱ በመሆናቸው የተነሳ፤ በሁለቱም በኩል የነበረው የትራፊክ ሥርዓት ጉድለትና ከሱም የሚመነጨው የባሕል ክፍተት በነኛ በፈረደባቸው አባቶቻችን ሊሳበብ አይችልምና፤ ምሳሌዎቹ ጠቃሚ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ከባሕር-ዳር እስከ ደብረ-ማርቆስ አዲስ በተሰራው አስፋልት አውራ ጎዳና ዙሪያ የሚኖረውን ሕዝብ ይመለከታል፡፡ ከመንገዱ ሥራ ጋር ተያይዞ እግረኞች ግራቸውን ይዘው እንዲጓዙ፤ ተማሪዎችም ከጎዳናው ውስጥ ገብተው እንዳይቆሙ፤ ኳስም እንዳይጫወቱ የሚደነግግ ደንብ ወጥቶና በሰሌዳ ላይ ተፅፎ በየአምስት ኪሎሜትር ያህል ርቀት ተሰቀለ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ ይህን ደንብ ተከትሎ አዲሱን የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓትና ባሕል በሚገባ ከመላበሱ የተነሳ የግል ጠባዩ አካል አድርጎት ሲያበቃ፤ የጎዳናውን ቀኝ ይዘን ስንደናበር ለተገኘን ከተሜዎች ምክር ለጋሽ ሆኗል፡፡

ቀጥሎ ደግሞ ወደ ዝርዝር ሳልገባ አንባቢ ጠንቅቆ የሚያውቀውንና አስቀድሞ የተረዳውን ሁለተኛ የትራፊክ ጉድለትና አቀራረፉን ላንሳ፡፡ የመኪና ቀበቶ ባለመጠቀም፤ በተንቀሳቃሽ ስልክ እየተነጋገሩ መኪና በማሽከርከርና፤ በትራፊክ መብራቶች አካባቢ በሚካሄድ ልመናና-ምፅዋት ሳቢያ ምን ያህል አላስፈላጊ አደጋዎች እንደደረሱና ከፍተኛ የሕይወት፤ የአካልና፤ የንብረት ኪሳራ እንደደረሰብን ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ ይኸው ታዲያ፤ በአንድ-አፍታ ተደንግጎና ታውቆ በሥራ ላይ በዋለ ደንብ/ሥርዓት አማካይነት ያንመሳይ ማነቆ

ሊወገድ ቻለ። አሸከርካሪዎችም በአጭር ጊዜ አዲሱን ሥርዓት ተላብሰው ከውጭ እንደተጣለባቸው ሸክም ሳይሆን እንደ ጠቃሚ ባሕላቸውና የራሳቸው እንደሆነ ግላዊ ባሕርይ ያከብሩት ዘንድ እንደሚመራቸው ተግባር ያዩት ይዘዋል።

*ኤሚል ደርካይም* ሰፋፊና ውስብስብ በሆኑት የዘመኑ ኅብረተሰቦች ውስጥ ሕግና የሕግ ሥርአቶች የሰዎችን ባሕርይ መልክ በማስያዝ በኩል ልማድን እና ልማዳዊ ሕግን እንደተኩ በማሳየት ለህብረተሰባዊ ለውጥ/ልማት የሚያደርጉትን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አመልክቷል (ደርካይም [1893] 1984)። እኔም የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ከዚህ ቀደም በተለያዩ መድረኮችና መጣጥፎች እንደገለፅኩት ሁሉ አሁንም ሕግና የሕግ ሥርአትን እድገት መሠረት የደረገ የህብረሰባዊ ሥርአታት መገንባትና መጠናከር የሚያስከትለው የባሕሪይ መልክ ማስያዝ ለሃገራችን ልማት ብቻ ሳይሆን ለባሕላችንም እድገት ወሳኝ ነው በማለት *የኤሚል ደርካይምን* መሠረታዊ አስተሳሰብ እጋራለሁ። በዛሬው ዘመን፤ የአካባቢ ንዑስ-ባሕሎችም ቢሆኑ በዝመና ስም ከተለያዩ ኃይሎች የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ በተሳካ መንገድ ሊከላከሉ የሚችሉት የሕግ ከለላ ሲያገኙ ብቻ ይመስለኛል።

ይኽ ፅሁፍ እስከዚህ ነጥብ ድረስ በዋነኛነት ያተኮረው ባሕላችን በአገራችን ኋላቀርነት ውስጥ የተጫወተውንና አሁንም በመጫወት ላይ ያለውን አሉታዊ ሚና በመዳሰሱ ላይ ነበር። እስኪ አሁን ደግሞ የቁስአካላዊና የረቂቅ (ታንጀብልና ኢንታንጀብል) ባሕላችን ውጤቶችና አካላት የሆኑት ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ለኢኮኖሚና ህብረተሰባዊ ልማት የሚያደርጉትን ቀጥተኛ አሉታዊ አስተዋፅዖዎች እንመልከት። አንደኛ፣ የባሕል አካል የሆኑት እንደ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ሥነ-ፅሁፍ፣ ሥነ-ቃል፣ ወዘተ... የመሳሰሉት ቅርሶች የሕዝቦች የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ የዕውቀት ማፍለቂያ፣ ማከማቻና፣ ማስተላለፊያ በመሆን ለልማት ቀጥተኛ አገልግሎት ይቸራሉ። የነሱም የመፍለቂያ መንበሮችና ጠባቂዎች ሆነው ያቆዩዋቸው ኅብረተሰብአዊ ሥርዓቶችና ተቋሞችም ለፈፀሟቸው ታሪካዊ ተግባሮች እውቅና ሊሰጣቸውና በአሁኑም ጊዜ ቀጣይነት ያለው ልማት በማስገኘት በኩል የሚጫወቱትን አሉታዊ ሚና መገንዘብ፣ ቁብ መስጠትና፣ ማዳበር ያስፈልጋል።

ሁለተኛ፣ የባሕል ክፋይ የሆኑት ቁስአካላዊ ባሕልና ነባር-ልምዶች የአገራችን ኢኮኖሚ በዋነኛነት የቆመባቸውን እርሻ፣ ከብት እርባታ፣ ባልትና፣ ሽመናንና የቆዳ መፋቅን ጨምሮ ሌሎች ዕደ-ጥበባት፣ የተለያዩ የቤት አሰራርንና ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይመለከታሉ። እነዚህ የኋለኞቹ ደግሞ የሃገራችን መለያ የሆኑትን እንደ ጤፍ፣ ዳጉሳና፣ የሃገር አልባሳትንና ነባር የምግብ ማዘጋጃና መመገቢያ ቁሳቁሶችን ወዘተ... ስለሚያቅፉ ባሕል በቀን-ተቀን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴአችን ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና ልንስተው አንችልም።

ሦስተኛ፣ ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ዋነኛዎቹ የቱሪስት መስህቦቻችን በመሆን እያደገ ለሚሄደው የአገራችን የቱሪስት ኢንዱስትሪና ለሚያስገኘው ገቢ፣ ለሚፈጥራቸው የሥራ ዕድሎችና፣ ሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞች መሠረት

ናቸው:: ውቅርና በተለያዬ መንገድ ድንቅ የሆኑ አብያተክርስቲያኖች፣ ጥንታዊ ከተሞች፣ ነባር የእምነት ሥርዓትና በዓላት፣ እንዲሁም ነባር-አልባሳት፣ ምግቦች፣ ጌጣ-ጌጦች፣ ዜማዎች፣ ጭፈራዎች፣ ወጎችና፣ የመሳሰሉት ባይኖሩ ኖሮ ምን ያህሉ ቱሪስት በአገራችን የተፈጥሮ ውበት ብቻ ተስቦ ይመጣ እንደነበር መገመት ይቻላል::

አራተኛ፣ እነዚህ ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ዋጋ በማውጣትና ቀጥተኛ የኢኮኖሚ ጥቅማ-ጥቅም በማስገኘት የአገር ልማትን የሚደግፉት በዚሁ በአገራችን መልክዓ-ምድር ተወስነው ብቻ ሳይሆን ድንበርና ወሰን በመሻገርም ጭምር ነው:: ታታሪነቱ በሰፊው የሚነገርለት በመላው ዓለም ተንሰራፍቶ የሚኖረው የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አንድም ያልሰለጠነበት ሙያና ያልገባበት የሥራ መስክ መኖሩ አጠራጣሪ ቢሆንም፣ የንግድ እንቅስቀሴውን የተመለከትን እንደሆነ አንድ አይነተኛ ጠባይ እንዳለው እንረዳለን:: አብዛኛው የዲያስፖራው ነጋዴ ለሥራው መነሻ የሚያደርገውና ስኬታማ ሆኖ የሚቀጥለው በ“ባሕል ምግብ”፣ “ባሕላዊ ሙዚቃና ጨዋታ”፣ “ያገር ልብስ” እና ሹሩባ ስራ ሳይቀር ሌሎች ሌሎችን ቁስአካላዊ የባሕል ፍሬዎችንና እንደ እቁብና የቤተሰብ መረዳጃ ማሕበር ያሉ ከነባር-ልምዶቻችን የተገኙ ባሕላዊ ካፒታሎችን በመጠቀም ነው:: ከጎረቤት አገሮች በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በኬንያና በደቡብ አፍሪካ፤ ከባሕር-ማዶ አገሮች ደግሞ በተለይ በዩናይትድ ስቴትስ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓና፣ በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ የዲያስፖራው አባላት የሚያካሄዱት የንግድ-ሥራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ የባሕል ትሩፋቶች ጋር እጅግ የተሳሰረ ከመሆኑ የተነሳ በንግድ-ስራቸው ኦፊሲያል አገልግሎትና በተጨማሪ በሚያከናውኑት ኦፊሲያል-ያልሆነ የባሕል አምባሳደርነት ተግባር መካከል ያለው ድንበር ደብዛዛ ነው:: በሁለቱ ተግባራት መካከል ግጭት ሳይሆን መደጋገፍ ነው የሚታዬው::

በአምስተኛነትና በመጨረሻ ልናነሳው የምንፈልገው ባሕል በልማት ላይ የሚያሳድረው ቀጥተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ፣ ረቂቁን ከነባር-ሥርዓታትና ከነባር-ልምድ የሚገኘውን ህብረተሰባዊ-ካፒታልን (ሶሻል-ካፒታል) ሚናን ይመለከታል:: ከዚህ ቀደም እንደፃፍኩት፡-

> በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰዎች በአንድነት ተቀናጅተው (ቦንድ አድርገው) በመተጋገዝ ውስን የሆኑ ቁሳዊና ሌሎች እንደመተማመን፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ ዓይነት ንብረቶችን ለማንቀሳቀስና በጥቅም ላይ ለማዋል ያላቸው ችሎታ ሶሻል-ካፒታል ይባላል:: ሶሻል-ካፒታል ንብረቶቹ ራሳቸው ሳይሆኑ፣ ንብረቶቹን በተፈለገ ጊዜ አንቀሳቅሶ ለመጠቀም የሰዎቹ ስብስብ ወይም ቡድን ያለው ህብረተሰባዊ አቅም ነው:: ስለዚህም ሶሻል-ካፒታል እንደንብረቶቹ በጥቅም ላይ በዋለ መጠን አይፈጅም-አያረጅም፣ አያልቅም:: እንዲያውም እያደገ፣ እየጨመረና እየበረታ ይሄዳል እንጂ (Long, 2001: 132-4):: በእንደዚህ፣ በተለይ ኋላ ቀር በሆኑ ሃገራት ልማት ውስጥ እንደ ኢኮኖሚ-ካፒታል እና የሰው- [ሂዩማን] ካፒታል ሁሉ ወሳኝ ሚና ሊጫወት የሚችለውን ይህን ሶሻል-ካፒታል በማስገኘት በኩል ሥርዓታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: የውስጥ ልማዳዊ ሥርዓታቱን ጠብቆ ያቆየው የጉራጌ ሕዝብ በዚህ የተነሳ የማይናቅ ሶሺያል-ካፒታል ባለቤት በመሆን ለአባላቱና ለሃገር ልማት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኘበት ሂደት የዚህን ክስተት ምንነትና

ከሥርዓታት መኖር የሚመነጭ መሆኑን በተጨባጭ ያስረዳል (የራስወርቅ አድማሴ 2006: 9)::

በእንደዚህ ከባሕላችን ጋር በጥብቅ የተያያዙት ነባር-ሥርዓቶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ይኸንን ሶሻል ካፒታል በመለገስ ለአገራችን ልማት የሚያደርጉት አስተዋፅዖ ሊሰመርበት ይገባል::

## 6. ዘመናዊነት – የጊዜያችን የልማትና የባሕል ለውጥ ዓይነተኛ ገፅታ

*ዘመናዊነት፤ መዘመን፤ ማዘመን ወይም ዘመናዊ መሆን፣ ዘመናዊ ማድረግ* (ሞደርናይዜሽን) ማለት ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን፣ አሰራሮችን፣ ወይም አካሄዶችን በአኳሁዋናቸውና በጠባያቸው ማዘመን ማለት ነው:: ጊዜው ያመጣውን፣ የሚፈቅደውንና፣ የሚጠይቀውን አሰራር፣ ዘዴ፣ አኳኋን፣ ወይም ገፅታ መቀበልና ማዋሃድ ማለት ነው:: ዘመናዊነት አንድ አይነት የባሕል ለውጥ ሂደት ነው:: በመሆኑም፤ ይኸ ፅንሰ-ሃሳብ የግድ በጊዜ ስር የሚሰድ ኅብረተሰባዊ ሂደትን (ሶሻል ፕሮሴስን) ያመለክታል እንጅ አንድን ድንገት ዱብ የሚል ክስተትን አያመለክትም:: ዱብ የሚል ከሆነም ዘላቂ የባሕል ለውጥን የሚያስከትል ሳይሆን እንደ አባባሉ "ዱብ-ዕዳ" ብቻ በመሆኑ፤ ብቅ ከማለቱ በዚያው ከስሞ የሚቀር ይሆናል:: ይሁንና፤ የዘመናዊነት ሂደት፡ አንድም ዘገምተኛ አንድም ፈጣን ሊሆን ይችላል:: እጅግ ዘገምተኛ ወይም እጅግ ፈጣን ሲሆን ደግሞ ከራሱ ከሂደቱ የመነጨ ችግር ያስከትላል::

ዘመናዊነት አንድ አይነት የባሕል ለውጥ ሂደት እንደመሆኑ በዘመናዊነትና በባህል መካከል አስገዳጅ ተቃርኖ የለም:: ዘመናዊነት ሊቃረን የሚችለው ከባሕል ይዘቶች አንዱ ከሆነው ከነባር ልማድ ጋር ነው ::

እንደማንኛውም የባህል ለውጥ ሁሉ የዘመናዊነት ይዘቶችም ከአንድ ሥርዓተ-ባሕል ከራሱ ሊመነጩ ወይም ከውጭ በትውስት ተገልብጠው ሊገቡ፤ ሊዋሀዱና፤ሥር ሰድደው ሊያብቡ ይችላሉ:: የዘመናዊ ባህል ይዘቶች ከውጭ በተውሶ መወሰድ በራሱ ምንም ችግር የለውም:: በመላው አለም በየስርዓተ-ባሕሉ ለምተውና ሰፍነው የሚገኙ እጅግ አብዛኛዎቹ የባሕል ይዘቶች ከውጭ የተወሰዱ ሆነው ሳለ፤ በየገቡበት ስርዓተ-ባሕል ውስጥ ፍፁም ከመዋሀዳቸው የተነሳ፤ የባዕድነት ደብዛቸው ጭራሹን ጠፍቶ የየስርዓተ-ባሕሉ አካልና አምሳል ሆነው ይኖራሉ::

ይኸን በቀላሉ ለማስረገጥ ጥቂት የሀገራችንን ስርዓተ-ባሕል ይዘቶች እንደ ምሳሌ ወስደን እንመልከት:: የወንዶች ሀበሻ-ልብሳችን መሰረቱ የቅርብ-ምስራቅ ቅጅ ነው:: ወደ ቅርብ-ምስራቅ የገባው ደግሞ ከሕንድ ክፍለ-አሕጉር በነአፍጋኒስታን በኩል እያቆራረጠ ነበር:: በስፔን ላይ ሰልጥነውባት የነበሩት አረቦች፤ እነሱም እንደኛ «ቀሚስ» የሚሉትን የላይ ተላባሹን ወደ ስፔን ከነስሙ ይዘውት ገቡ:: በዚያ ሀገር የመታወቂያ ስሙ ግን እንደማንኛውም ተወራሽ የባሕል ይዘት ያገሬውን ቋንቋ ቅላፄ ወስዶ "ካሚሳ" (camisa) ሆነ:: «ካሚሳ»ም የፒሬኔስን የተራራ ሰንሰለት ተሻግሮ ፈረንሳይ ሲደርስ በቅርፅም በስምም የአገሩን ዘዬ

ተከትሎ የፊትለፊት ተከፋቹንና በአዝራር ተቆላፊውን "ሸሚዝ" ሆነ። በዚህ ዓይነት ሂዙሮ መጣና፤ የኛነቱን ደብቆ በመግባት አለባበሳችንን አዘመነ፤ ከዘመናዊነት ምልክቶቻችንም አንዱ ሆነ። ባሁኑ ጊዜ እንደ ነባር-አልባሳት የምናያቸው እነ ካባና በርኖስም ቢሆኑ፤ ከውጭ በገቡበት ቀደም ባለው ጊዜ፤ የዘመናዊነት መገለጫ እንደነበሩ ትክክለኛ ግምት መስጠት ይቻላል።

ሌሎችም ብዙ የሥርዓተ-ባሕላችንን ይዘቶች ጀርባ ብንፈትሽ፤ የተመሳሳይ የመውረስና የመወራረስ ሂደቶች ውጤት ሆነው እናገኛቸዋለን። ለነገሩ ከበርበሬ የበለጠ ከስር ከመሰረቱ ፍፁም ኢትዮጵያዊ መሳይ የምግብ ግብአትና የምግብ ባሕላችን ዓይነተኛ መለያ ባልነበረ። ግን እሱም ቢሆን፤ ቆየ እንጅ፤ በ15ኛውና በ16ኛው ምዕተ-ዓመታት አፍሪቃን አካለው ብቅ ባሉት ፖርቱጊዝ ነጋዴዎች አማካይነት ከተገኘበት ከ"አዲሱ-ዓለም" መጥቶ የለመደ መሆኑን፤ ሩቅ ሳያስኬደን፤ ራሱ "ፔሪፔሪ" የተሰኘው የስሙ ስረ-ቃል በበቂ ያስረዳናል። በእንደዚህ፤ ከባሕር-ማሽላና ከባሕር-ዛፍ በተጨማሪ ሌሎች እጅግ ብዙ የባሕር-ማዶ ነገሮች በሥርዓተ-ባሕላችን (ባሕሎቻችን) ተወርሰውና የምንጫቸው ደብዛ እስከሚጠፋ ድረስ ተዋሕደው እንደሚኖሩ እንገነዘባለን። ከሌሎች የባሕል ይዘቶችን መውረስ፤ ጨርሶ ማዋሃድ፤ የራስ አድርጎም ማበልፀግና ሕያው አድርጎ ማኖር ደግሞ ከፍተኛ የባሕል ችሎታን የሚጠይቅ መሆኑን መረሳት የለበትም።

ከዚህ የባሕል ይዘቶች መወራረስ ጋር የተያያዘ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ አለ። ይኸም ከፍ ብለን የጠቀስነውን በ"ዘመናዊነት ወይም ማዘመን" (ሞደርናይዜሽን) እና ከባሕል ይዘቶች አንዱ በሆነው "ነባር-ልማድ" (ትራዲሽን) መካከል ሊኖር የሚችለውን ተቃርኖና ግጭት ይመለከታል። ማንኛውም ባሕል በቴክኖሎጂ እድገት እየታገዘ የሚመጣን ዘመናዊ የባሕል ይዘቶችን ተቀብሎ እንደሚያዋሕድ ከላይ ያሰመርንበት ጉዳይ ቢሆንም፤ ይኸ አባባላችን በሃገራችን የሚታየውን መረን-በለቀቀ ደረጃ በመካሄድ ላይ ያለውን የ"ነባር-ልማድ" ናሙናዎች መወረርና መደፈር አሳዛኝ ሂደትን መሸፈንና ማለሳለስ የለበትም። እርግጥ፤ አንዳንድ ነባር የሆኑ የሥነ-ፅሁፍ፣ የስዕል፣ የሙዚቃ፣ የጭፈራ፣ የምግብ/የአመጋገብ፣ የልብስ/የአለባበስ፣ ወዘተ... ዘመናዊ መልክ እያገኙና አዳዲስ ጥቅም ላይ እየዋሉ ሄደዋል። የፊትልና የጥበብ ልብስን ዘመናዊ ዕድገት እንደምሳሌ ብንወስድ፤ ከሁለተኛው የዓለም-ጦርነት ወዲህ በዚህ ዘርፍ የተደረገውን እርምጃ ማሳነስ ወይም ማንቋሸሽ አይቻልም። ከመክሰም መትረፍ ብቻ ሳይሆን፤ እያበበ የሄደና አለ ሊባል የሚችለው ብቸኛ "የፋሽን-ኢንዱስትሪያችን" ምሰሶ የሆነው፤ ሳይዘምንና የጥቅም አድማሱን ሳያስፋ ቀርቶ ባለሁበት ልርገጥ ባለማለቱ ነው። ግን፣ ከዚህ በጎ የማዘመን ሂደት ጎን-ለጎን ነባሩን ለይቶ መስቀመጥና ሳያዳቅሉ ጠብቆ ማቆየት ያስፈልግ ነበር። ለምሳሌ፤ አንዳንድ "ባሕላዊ የኪነት ቡድኖች" የአማራ ሕዝብ የ"ባሕል ልብስ" ብለው በኢቲቪ ሳይቀር የሚያቀርቡት እዚሁ-በዚሁ (እለቱን ማለት ይቻላል) አራዳ ክፍለ-ከተማ የተፈለሰፈ፣ ከቻይና ስሞኑን በገባ ሲንተቲክ ቲ-ሸርት የደመቀና፣ ምንነቱ ያልታወቀ ምስቅልቅል አልባስ ነው። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ፤ ከኛ ከተራ ተመልካቾቹ ባሻገር የባሕል መሪ ባላደራና ባለድርሻ የሆኑት የኪነት ጠበብት ጭምር ይህን ዓይነት ጠንቀኛ ሂደት በዝምታ ማለፋቸው ነው።

የ"ኪነት ነፃነት" ጉዳይ ቢሆንም እኮ ልክና መልክ አለው::

## 7. መደምደሚያ – የወደፊቱን የውይይት አቅጣጫ በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦች

እኛ፤ የዚህ የ "ባሕል እና ልማት በኢትዮጵያ" ውይይት መድረክ ተሳታፊዎች የሆንነው የጉዳዩ ባለድርሻዎች፤ በዚህ ርዕስ ስር የምናካሂዳቸውን ጥናቶችና ውይይቶች እንዲሁም የምናሰራጫቸውን ሃሳቦች በተመለከተ አንድ-አንድ መርሆች ልንከተል ይገባል:: ከዚህ በመቀጠል ከተዘረዘሩት ወስጥ አንድ አንዶቹን ማጤን ጠቃሚ ይመስለኛል::

- በባሕል ፅንስ-ሀሳብ አመጣጥ፣ የተለያዩ ትርጉሞችና፣ አጠቃቀሞች ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጥ፤
- በባሕልና በሌሎች ተቀራራቢው በሆኑ ፅንስ-ሀሳቦች መካከል ባሉት ልዩነቶችና አንድነቶች ላይ ግልፅ መሆን፤
- በኅብረተሰባዊ ለውጥ፣ በልማትና፣ በመዘመን ፅንስ-ሀሳቦች ላይ ግልፅ መሆን፤
- ጥቅል አባባሎችና ጥቅል አንድምታ የትም እንደማያደርሰን በመገንዘብ፤ በዝርዝር ጉዳዮችና ትስስሮች ላይ ማተኮር:: ለምሳሌ፣ የትኛውና የመቼው ጊዜ የባሕል ኤለመንት ወይም ነባር-ልምድ ለየትኛውና ለመቼው ጊዜ የልማት ሂደት ነው ማነቆ ወይም መፍትሄ የሆነው? ለምን ሲባልና በምን አካባቢ የፈለቀ የባሕል ኤለመንት (ለምሳሌ የገጠር) በሌላ አካባቢ (ለምሳሌ የከተማ) ተገኝቶ ልማትን አደናቀፈ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ማንሳትና መመርመር፤
- በጥናትና በምርምር ያልተደገፉና ስለተደጋገሙ ብቻ ሰፊ ተቀባይነት ያገኙ ሃሳቦችና አባባሎችን ትክክለኛነት መጠየቅ፣ መመርመርና ድክመታቸውን ማሳዬት አለብን:: ለምሳሌ፣ እንደ "አበሻ አብሮ መስራት አይችልም" የሚል ያልተፈተሸ መፈክር ይዞ ከመፍሰስ ይልቅ የሰው-ስብስቦች አብሮ የመስራት ችግር (problem of collective action) የበርካታ ምሁራንን ልፋትና እልህ ያስጨረሰ አለም-አቀፋዊ ችግር እንደሆነ ተገንዝቦ ከነዚያ ትጉሃን ጎራ መደባለቅ ይጠቅመናል:: "ሰዓት የማናከብረው ለጊዜ ዋጋ በማይሰጠው የቆየ ባሕላችን የተነሳ ነው" ማለት፤ እንደ የቀጠሮና የሥራ ሰዓት ላሉ የአሁን ዘመን መለያ ክስተቶች የቆየውን ባሕል ተጠያቂ ማድረግ፤ ለሞባይል ስልክና ለኢንተርኔት አጠቃቀማችን የሚመች ባሕል ተደላድሎ አልጠበቀንም ብሎ አስቂኝ እሮሮ ማሰማት፤ እና ይኸና ያ የፖለቲካ ችግር የገጠመን "የዲሞክራሲ ባሕል ወይንም የመቻቻል ባሕል ስለሌለን ነው" ብሎ ማወጅ "በባሕል ቀሚስ" ተከልሎ ከጥያቄው ለማምለጥ ከመሞከር ሌላ ምንም ትርጉም እንደሌለው ተቀብሎ ትርጉም ያለው ትንተና ለማቅረብ መጣጣር ተመራጭ ነው::

- በባሕል ላይ ሰበብ የማላከክ ጨዋታን ትተን፤ ለጊዜያችንና ለሁኔታችን የሚመጥን የባሕል ኤለመንቶች የምንፈጥርበትንና የምናዳብርበትን መንገድ መሻትና የባሕል ዕድገትን ያቀፈ ኅብረተሰባዊ ልማት ለማምጣት ለሚረዱ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት፤
- ባሕል በልማት ላይ ሊያሳድር በሚችለው ተፅዕኖ ላይ ብቻ ሳይሆን በልማት ስም በተለይ በአካባቢያዊ ንዑስ ባሕላት ላይ ሊደርሱ በሚችሉ አሉታዊ ተፅእኖዎች ላይ ጭምር፤ በፍትሃዊ ሆኖም ባልተጋነነ ተነሳሽነት ማተኮር፤

በመጨረሻም፤ እንደ ኢትዮጵያችን ያሉትን በኢኮኖሚ ዕድገት ኋላቀር የሆኑ ሀገራትን በተመለከተ ለልማት ጠንቅ በሆኑ የባሕል ይዘቶች ላይ ብቻ ማተኮር ጊዜው ያለፈበት አመለካከት እየሆነ መምጣቱንና፤ በዛሬው የዕውቀትና የምርምር ዓለም፣ ለልማት ጠቃሚ የሆኑትን የነዚህን ህብረተሰቦች የባሕል ይዘቶችን ጭምር የሚያካትት፣ ሚዛናዊና፣ ብሎም ጠቃሚ የሆነ የምርምርና የትንታኔ አካሄድ የበላይነትን እያገኘ መምጣቱን ማብሰር እንወዳለን (እንደ ምሳሌ፤ ደግላስን 2004 እና ሞንክሪፈን 2004 ይመልከቱ)::

# የብሔራዊ ቅርስ ልማትና ቱሪዝም

*ቴዎድሮስ አጥላባቸው*

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ የተለያዩ ልምዶች፣ እምነቶች፣ አባባሎች፣ ወጎች፣ ሥርዓቶች እና የአኗኗር ዘዴዎች አሉን፡፡ እነዚህ ዕሴቶች ከሰዎች የአኗኗር ዘይቤዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፡፡ በስፋት ተቀባይነትን በሚያገኙበት ጊዜ ባሕል በመሆን የአንድን ጎሣ፣ ብሔረሰብ . . . ወዘተ፣ የአኗኗር ሁኔታን ያንፀባርቃሉ፡፡ በስፋት ተቀባይነትን ያገኘ ባሕል ለአንድ ጎሣ፣ ብሔረሰብ . . . ወዘተ ከተደነገጉ ህጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ባላነሰ ሁኔታ ተቀባይነትን አግኝቶ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን አንዴ እና ለዘልዓለም የተሰጠ ወይም የተፈለሰፈ ሕግ ወይም ደንብ አይደለም፡፡ ጊዜ ሲያልፍ እና ትውልድ ሲተካ አዳዲስ ልምዶች፣ እምነቶች፣ አባባሎች፣ ወጎች፣ ሥርዓቶችና የአኗኗር ዘዴዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ቀደምት ባሕሎች በአዳዲስ ባሕሎች ይተካሉ፡፡

ተፈጥሮ የለገሰን በርካታ ሀብቶች፣ እንደዚሁም ከአያቶቻችንና ከቅድመ አያቶቻችን (our ancestors) የወረስናቸው ባሕላዊና ተፈጥሮአዊ ዕሴቶች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ ከእነዚህ ውስጥ፣ በተለያዩ መመዘኛዎች የላቀ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸው፣ እንደየቅደም ተከተላቸው ብሔራዊ ቅርስ እና የዓለም ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ቅርስ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት፣ አብዛኛውን ጊዜ መተኪያ የማይገኝለት፣ በይዘቱና በዓይነቱ ስፋትና ጥልቀት ያለው እንደዚሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቅርስ ከፍተኛ ዕሴት ያለው የተፈጥሮ ስጦታና የሰዎች የፈጠራ ውጤት እንደመሆኑ በርካታ ባሕላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንደዚሁም ከግንዛቤና ከአያያዝ ጉድለቶች ስፍር ቁጥር የሌለው የዓለማችን ቅርስ ወድሟል፣ በመውደም ላይም ይገኛል፡፡ ከወደመው ቅርስ ሊገኙ ይችሉ የነበሩ በርካታ ጠቀሜታዎችም ባክነው ቀርተዋል፡፡ ባለንበት ዘመን ስለቅርስ ያለው የግንዛቤ አድማስ እየሰፋ በመምጣቱ፣ ቅርስን በአግባቡ ጠብቆ፣ ተንከባክቦ እና ተጠቅሞ ለመጪው ትውልድ የማስተላለፉ ጉዳይ በበርካታ አገሮችና ህዝቦች ልዩ ትኩረትን አግኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የቅርስ አጠባበቅን፣ አጠቃቀምን እና አያያዝን በተመለከተ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ በርካታ የምርምር ሥራዎች ተከናውነዋል፣ የቅርስን ጉዳይ በቅርበት ለመከታተል እንዲቻልም ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣

አገራዊ… ወዘተ ተቋማት ተመሥርተው ሥራዎቻቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ቅርስ እና ልማት በመሆኑ *"ቅርስን መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማት፣ በሥርዓት መጠቀምና ለመጪው ትውልድ በአግባቡ ማስተላለፍ"* የሚለው ዐረፍተ ነገር መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡ ይህንንም ዕውን ለማድረግ የቱሪዝም ሚና ከፍተኛ እንደሆነና ቀጣይነት ያለው የልማት እቅድና ስትራቴጂ አስፈላጊነትም ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው በቅርስ ሁለንተናዊ ትንተና ላይ ሲሆን ፣ ከልማት ጋር በተገናኘ መልኩ፣ በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡ በተለይም ብሔራዊ ቅርሶቻችንን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመጠበቅ፣ ለማልማት፣ ለመጠቀምና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል፤ በቅርስና በቱሪዝም መካከል ስላለውና ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ለውይይት የሚረዱ ሀሳቦችን ማቅረብ የፅሁፉ አቢይ አላማ ይሆናል፡፡

## 2. ቅርስና የቅርስ ዓይነቶች

ቅርስ በተለያዩ አገሮችና ግለሰቦች የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የቅርስን ትርጉም ለማቅረብ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ለውይይታችን መግባቢያ ሆኖ ያገለግል ዘንድ ጽንሰ ሀሳቡን በቀላል አገላለጽ ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ቅርስ በውስጡ ካካተተው ከፍተኛ ዕሴት አኳያ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ መስፈርቶች፤ ማለትም ከእድሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅየነቱ … ወዘተ፣ አኳያ በተለያዩ መመዘኛዎች የተመረጠ የተፈጥሮ ስጦታና ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት ወይም ሁለቱንም በጣምራ (የተፈጥሮና ባሕላዊ ቅርስን) ያካተተ ነው ቢባል ለቅርስ ከተሰጡት በርካታ ትርጉሞችና ከቅርስ ጽንሰ ሀሳቦች ጋር ይስማማል እንጂ አይቃረንም፡፡

ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንንና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን የፈጠራ ውጤቶች ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩና ዓይነቱ እጅግ ብዙ ነው፡፡ በመሆኑም ለግንዛቤ እንዲረዳ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት አራት የቅርስ ዓይነቶች ከፋፍሎ ማየቱ ለጽሑፉ ዓላማና ለውይይታችን አስፈላጊ ይመስለናል፡፡

### 2.1 ባሕላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ

ቅርስ ሲባል አብዛኞቻችን የምናስበው ከባሕል ጋር በተገናዘበ መልኩ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅርስ የተመረጡ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና የሰው ልጅን የፈጠራ ውጤቶች ወይም የሁለቱንም ጥምረት የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ባሕላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

*የባሕል ቅርስ፤* የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶችን ማለትም ሐውልቶችን፣ ህንፃዎችን፣ ዋሻዎችን፣ በድንጋይና በብራና ..ወዘተ፣ በመሳሰሉት ላይ የተጻፉ ወይም የተቀረፁ ፅሁፎችን፣ ቅርፃቅርጾችን፣ አልባሳቶችን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ሥርዓቶችን... ወዘተ፣ ሁሉ ያካትታል፡፡

*የተፈጥሮ ቅርስ፤* በላቀ ጠቀሜታቸው የተመረጡ ማራኪና ውብ የሆኑ ደኖችን፣ ሐይቆችን፣ ዋሻዎችን፣ ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የእንስሳት መጠለያዎችን፣ በአጠቃላይ ህይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ፍጡሮች እና እነርሱም የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያካትታል፡፡

## 2.2 የዓለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ

ቅርስ ካለው ጠቀሜታ አንፃር የዓለምና የብሔራዊ ቅርስ በሚል በሁለት ይከፈላል፡፡ አንድ ቅርስ (የባሕል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት ባወጣው መመዘኛ መሠረት በውስጡ የላቀ ዓለም አቀፍ ዕሴት ካለው፤ የዓለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቦ የዓለም ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ብሔራዊ ቅርስን በተመለከተ ደግሞ፣ እያንዳንዱ መንግሥት ባወጣው መመዘኛ መሠረት ማንኛውም ብሔራዊ ዕሴት ያለው ቅርስ (የባሕል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቦ ብሔራዊ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡

እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 16 ቀን 1972 ዓ.ም. የዓለምን የባሕልንና የተፈጥሮን ቅርስ ለመጠበቅና ለመንከባከብ በፓሪስ ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባው ላይ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት (UNESCO) የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ በውሳኔ ሰነዱ አንቀጽ አንድ እና ሁለት ላይ የዓለም የባሕልና የተፈጥሮ ቅርስ ትርጉሞችን አጽድቋል፡፡

የጸደቁትን ትርጉሞች ይዘት፤ ቀለል ባለ መልኩ ወደ አማርኛ በመተርጎም፤ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### *የዓለም የባሕል ቅርስ*

- **ሐውልቶች (Monuments)፡-** ከታሪክ፣ ከሥነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ሐውልቶች፣ ማለትም በዚህ ውስጥ የሚካተቱ የምህንድስና ሥራዎች፣ ቅርፃ ቅርፆችና ሥዕሎች፣ በቁፋሮ የተገኙ የሐውልት ባሕሪይ ያላቸው አቋሞች፣ የተቀረፁ ጽሑፎች፣ ዋሻዎችና ተመሳሳይ ባሕሪይ ያላቸው፤
- **ሕንፃዎች (Buildings)፡-** ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ሕንፃዎች፤ ማለትም ካላቸው የላቀ

የምህንድስና ጥበብ፣ ካቀማመጣቸው ውበት፣ ከአሰራራቸው ወጥነት አንፃር የተመረጡት፤ እና

- **ቦታዎች** (Sites)፡- ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ቦታዎች፤ ማለትም በሰው የተሰሩ ወይም የተፈጥሮና የሰው ሥራዎችን በአንድ ላይ ያጣመሩ የቁፋሮ ቦታዎችንም (Archaeological Sites) ጭምር ያካተቱ ሁሉ የባሕል ቅርስ ተብለው እንዲወሰዱ ወስኗል፡፡

***የዓለም የተፈጥሮ ቅርስ***

የተፈጥሮ ቅርስ፤ ማራኪ ገጽታ፣ ውበት እና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እንደዚሁም በብርቅነታቸው እንክብካቤን የሚሹ እና የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው *ተፈጥሯዊ ክስተቶችን* (ተፈጥሯዊና ስነህይወታዊ ፍጥረቶችን ወይም ሁለቱንም በጣምራ ያካተቱ)፤ *ስነ ምድራዊ አቀማመጦችን* (ዘራቸው ለመጥፋት የተቃረበ የዕፅዋትና የእንስሳት *መኖሪያ ቦታዎችንም* ያካተቱ) እና *ማራኪ የተፈጥሮ ቦታዎችን* (ልዩ ጥበቃና እንክብካቤን የሚሹ ወይም ድንቅ የተፈጥሮ አካባቢዎችን) ሁሉ ያካትታል፡፡

## 2.3 ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ

ከዓይነቱ፤ ከተፈጥሮውና ከመጠኑ አንፃር ቅርስ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

ተንቀሳቃሽ የሚባለው በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የሚችል የቅርስ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በቅርስነት የተመዘገቡ በብራና ላይ የተፃፉ ጽሑፎች፣ አልባሳት፣ በተለያዩ ቁሳቁሶች (ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከሸክላ፣ ከድንጋይ፣ ከወርቅ... ወዘተ) የተሰሩ ዕቃዎችና ቅርፃ ቅርፆች፣ መጠናቸው አነስተኛ የሆነ በቁፋሮ የተገኙ ጥንታዊ የመገልገያ ዕቃዎች... ወዘተ፣ የመሳሰሉት በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ ስለሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

የማይንቀሳቀስ የሚባለው በቀላሉ ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ታሪካዊው የሐረር ከተማ ጀጎል፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ... ወዘተ፣ ይጠቀሳሉ፡፡ በዓለም ቅርስነትም የተመዘገቡ ናቸው፡፡ ከአፈጣጠራቸው፤ ከግዝፈታቸው እና ከሚገኙባቸው ቦታዎች አኳያ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ አንዳንዶቹን ደግሞ ፈጽሞ ለማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ አንዳንዶቹ ቢንቀሳቀሱ እንኳን (የአክሱም ሐውልት ወደ ኢጣሊያ በተወሰደው ዓይነት) እሴቶቻቸውን ያጣሉ፡፡ የላቀ ትርጉም የሚኖራቸው ከተፈጠሩበት ወይም ከተሰሩበት ቦታ ላይ ሲገኙ ብቻ ነውና፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ

ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ የሚችሉ ስላልሆኑ የማይንቀሳቀስ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## 2.4 ተጨባጭ (Tangible) እና ተጨባጭ ያልሆነ (Intangible) ቅርስ

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ፣ በአጠቃላይ በሁሉም ስሜተ ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ሐውልቶች፣ ህንፃዎች፣ ዋሻዎች፣ መጻሕፍት፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርጾች፣ አልባሳት… ወዘተ፣ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ፣ የማንችለው፣ ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ፣ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ በመባል ይታወቃል፡፡ ወጎች፣ ተረቶች፣ ሥርዓቶች፣ ማራኪ እይታዎች… ወዘተ፣ ቁሶች አይደሉም በተፈጥሯቸውም ተጨባጭ አይደሉም፡፡ በውስጣቸው ግን መንፈሳችንን የሚያነሳሱ፣ የአእምሮ እርካታንም የሚሰጡን በርካታ እሴቶች አሏቸው፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማወቅን፣ መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መደሰትን… ወዘተ፣ ሁሉ ይፈልጋል፡፡ ፍላጎቶቹ ሁሉ ግን በቁሳዊ ፍላጎቶቹ ብቻ ሊረኩ ከቶውንም አይቻላቸውም፡፡ ተጨባጭ ከሆኑት ወይም ከቁሳዊ ፍላጎቶቹ በተጨማሪ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ያልሆኑ ፍላጎቶችም አሉት፡፡ በመሆኑም፤ ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች፤ በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

# 3. የቅርስ አያያዝና አጠቃቀም

ቅርስ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት የተፈጥሮ ስጦታና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት እንደመሆኑ ልዩ ትኩረትን የሚሻ መተኪያ የሌለው ሀብት ነው፡፡ በዓለማችን ውስጥ በቅርስነት ሊመዘገቡ የሚችሉና በቅርስነት የተመዘገቡ በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በተለያዩ ዘመናት፤ ስለቅርስ የነበሩት ግንዛቤዎች የተለያዩ ቢሆኑም፤ ህዝቦች በተለያዩ የአኗኗር ዘዴዎቻቸውና ባህሎቻቸው፤ እምነትን፤ ክብርን፤ ዝናን… ወዘተ መሠረት በማድረግ፤ ቅርስን ጠብቀውና ተንከባክበው ለአሁኑ ትውልድ አስተላልፈዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች (ጦርነቶች፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ… ወዘተ)፤ በግንዛቤ እጥረት፣ ኑሮን ለማሸነፍ በሚደረግ ጥረት… ወዘተ፣ በርካታ የዓለማችን ቅርስ ወድሟል፣ በመውደምም ላይ ይገኛል፡፡

ባለንበት ዘመን፤ ስለ ቅርስ ያለው ግንዛቤ ከመቸውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ጎልብቶ ይገኛል፡፡ በብሔራዊ መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቅርስን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለመጠቀም እና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ

መዋቅሮች ተዘርግተዋል። በአገራችን ውስጥ በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥር "የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን" በሚል መጠሪያ ሙሉ ሥልጣን ያለው መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። በተለያዩ የክልል መስተዳድሮችም ባሕልና ቅርስን በተመለከተ መዋቅሮች ተዘርግተው ቅርስን በመንከባከብ ረገድ አበረታች እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1946 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር "የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት" (United Nations Educational Scientific and Cultural Organization) በሚል መጠሪያ አንድ የሥራ ክፍል ተቋቁሞ እስካሁን ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። ይህ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ውስጥ አባል አገሮች ባፀደቁት የምርጫ መስፈርት መሠረት፣ የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያለውን ቅርስ በመምረጥ በዓለም ቅርስነት መመዝገብ እና ቅርስን በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለመጠቀምና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፎችን ለአባል አገሮች መስጠት ይገኙበታል።

እ.ኤ.አ. እስከ ኦክቶበር 2007 ዓ.ም. ባለው ጊዜ 193 አገሮች የድርጅቱ ቋሚ አባል እንደዚሁም 6 አገሮች ደግሞ ተባባሪ አባል በመሆን ተመዝግበዋል። ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ. ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ የድርጅቱ አባል አገር ሆና ተመዝግባለች።

ድርጅቱ እ.ኤ.አ. በኤፕሪል ወር 2009 ዓ.ም. ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በጥቅሉ 878 ንብረቶች በዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል። ከነዚህም ውስጥ 679 የባሕል ቅርስ፣ 174 የተፈጥሮ ቅርስ እና 25 የባሕልና የተፈጥሮ ቅርስ ድብልቅ (ጣምራ) ይገኙባቸዋል።

አገራችን የበርካታ ቅርስ ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፤ ከነዚህም ውስጥ ስምንቱን የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት በዓለም ቅርስነት መዝግቧቸዋል። (ዝርዝራቸው በሠንጠረዥ 1 ቀርቧል።)*

በአህጉራችን ደረጃ ሲታይ ኢትዮጵያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካና ቱኒዝያ እያንዳንዳቸው ስምንት የዓለም ቅርስ በማስመዝገባቸው የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ። ሌሎች የአፍሪካ አገሮች እያንዳንዳቸው ከስምንት ያነሰ፤ አንዳንዶቹም ምንም ያላስመዘገቡ ይገኙበታል። ለመጥቀስ ያህል ግብፅ 7፣ ኬንያ 4፣ ሱዳን 1 የዓለም ቅርስ አስመዝግበዋል። (ዝርዝሩ በአባሪ 02 ቀርቧል)

በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት ስምንት ንብረቶች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የባሕልና የሰው ሰራሽ ቅርስ ክምችት እንዳለ ይታወቃል። ከቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የተገኘው መረጃ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ ቤተ መንግሥቶችና ሙዚየሞች

---

* ይህ ጽሁፍ ከተዘጋጀ በኋላ አንድ የባህልና የተፈጥሮ ቅርስ በዩኔስኮ ተመዝግቧል፤ ይህም የኮንሶ የእርከን ስራ ነው። ከአዘጋጁ

ውስጥ ከ40,000 በላይ የሚንቀሳቀሱ ቅርሶች ተመዝግበው የመለያ ኮድ የተሰጣቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ መረጃ በግለሰቦች እጅ የሚገኘውን ቅርስ እንደማያካትትም ተጠቅሷል፡፡ በየጊዜው የተመዘገበውን የቅርስ ዓይነትና መጠን የሚያመለክት ስታቲስቲካዊ መረጃ ማግኘት ባይቻልም፤ የተመዘገበው ቅርስ ከተጠቀሰው በላይ እንደሆነ አንዳንድ ምንጮች ይገልፃሉ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ ንብረቶች

| ተ/ቁ | በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ ንብረት | የተመዘገበበት ጊዜ (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|
| 1. | የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት | 1978 |
| 2. | ሰሜን ተራራ ብሔራዊ ፓርክ | 1978 |
| 3. | የፋሲል ግቢ እና የጎንደር አካባቢ | 1979 |
| 4. | አክሱም | 1980 |
| 5. | የታችኛው አዋሽ ሸለቆ | 1980 |
| 6. | የታችኛው ኦሞ ሸለቆ | 1980 |
| 7. | ጢያ | 1980 |
| 8. | ጥንታዊው የሐረር ከተማ (ጁጎል) | 2006 |

የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡ ራሱን የቻለና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ የአሠራር ዘዴም አለው፡፡ በአገራችንም ውስጥ ይህንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘውን የአሠራር ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፤ በመደረግም ላይ ይገኛሉ፡፡ ቅርስን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከሚያስፈልጉት ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## 3.1 የቅርስ ምዝገባና ሰነዳ (Inventory and Documentation)

ቅርስን በአግባቡ ለመንከባከብና ለመጠቀም በቅድሚያ የት ቦታ እንደሚገኝ፤ ዓይነቱ፣ ብዛቱ፣ የተሰራበት ዘመን፣ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም በጽሑፍ፣ በፎቶግራፍ እና በፊልም በተደገፈ መልኩ መመዝገብና የምዝገባ መለያ (code) መስጠት ይገባል፡፡ ይህ ከተከናወነ በኋላ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ አሰባስቦ፤ ደህንነቱ በሚያስተማምን ሁኔታ በተጠበቀ ማዕከል (ሙዚየም) ውስጥ ማከማቸት ወይም ማንቀሳቀስ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ባለበት ቦታ ተገቢው እንክብካቤ ተደርጎለት፤ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አገራችን የበርካታ ቅርስ ባለቤት መሆንዋ ቢታመንም አብዛኛው ቅርስ ግን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት

እንዳልተመዘገበ ይታወቃል። ካለው ባሕልና የአሰራር ልምድ፣ አብዛኛው ቅርስ የሚገኘው በገዳማት፣ በመስጊዶች እና በግለሰቦች እጅ ነው። ገና በቁፋሮ ያልተገኘ በመሬት ውስጥ የተቀበረ በርካታ የቅርስ ክምችት እንዳለና ተመራማሪዎች ያልደረሱበት ሌላ የተፈጥሮ ቅርስም በመሬት ላይ ሊኖር እንደሚችል ይገመታል። ይህ ግን ቅርስን የመመዝገብና የማከማቸት ሥራ እየተሠራ አይደለም ለማለት አይደለም። ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች አቅማቸው በፈቀደ መሠረት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳሉ ይታወቃል። አበረታች ውጤቶችም ተገኝተዋል። ቅርስ ካልተመዘገበ፣ የት እና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ካልታወቀ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣ ተገቢውን እንክብካቤም አያገኝም። ስለዚህ የቅርስ ምዝገባና ክምችት እጅግ አስፈላጊ ተግባር መሆኑ አያጠያይቅም።

## 3.2 የቅርስ እንክብካቤ እና አስተዳደር

አንዳንዱ ቅርስ በእርጅና ወይም በአያያዝ ጉድለት የተጎዳና የተበላሸ ነው። በመሆኑም ልዩ እንክብካቤን፣ ማለትም በነበረበት ሁኔታ መጠገንን (Restoration) ይፈልጋል። የቅርስ ጥገና ሥራ እጅግ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው። አገራችንም የዚህ ዓይነቱን የጥገና ሥራ በቂ በጀት መድባ በራሷ ለማከናወን የሚያስችል አቅም የላትም። ታዳጊ አገር እንደመሆኗ ልዩ ቅድሚያን የሚሹ ሌሎች በርካታ የልማት፣ የጤና፣ የትምህርት ... ወዘተ፣ ሥራዎች ማከናወን ስለአለባት ለቅርስ የምታውለው የሰው ሆነ የቁሳቁስ ሀብት እጅግ የተመጠነ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ከዓመታት በፊት፣ ሞስኮ ውስጥ የሚገኘው ቦልሾይ ቲአትር በመባል የሚታወቀው ታሪካዊው ቴአትር ቤት ህንፃው የመሰንጠቅ ጉዳት ስለደረሰበት በነበረበት ሁኔታ ለመጠገን ከ300 እስከ 350 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገምቶ ነበር። በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ወጪው በዚያን ጊዜ ከተገመተው በላይ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ለመጠገን የሚያስፈልገው ወጪ ከዚህ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። አገሪቱ ካላት የኢኮኖሚ አቅም አኳያ እነዚህን ውቅር ቤተ ክርስቲያናት በነበሩበት ሁኔታ ለመጠገን ባለመቻሉ የበለጠ ውድመት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የእንክብካቤ ሥራ ብቻ በመከናወን ላይ ይገኛል። ይህም እራሱ ከፍተኛ ወጪንና ሙያን የሚጠይቅ በመሆኑ እየተከናወነ ያለው ከአውሮፓ ሕብረት በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ እርዳታ መሆኑ ይታወቃል። መጠኑ አነስተኛ የሆነ ቅርስን (ቅርፃ ቅርፆች፣ ጽሑፎች .. ወዘተ) በአገር ውስጥ ባለሙያዎች ለመጠገን ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ላያስፈልግ ይችላል፣ ነገር ግን ልዩ የሙያ ክሂሎትን ይጠይቃል።

ለማጠቃለል ያህል ቅርስን ከመመዝገብና ከማከማቸት በተጨማሪ፣ በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኘውን በልዩ እንክብካቤ መያዝ፣ እንደዚሁም የተበላሸና የተጎዳን ቅርስ በአግባቡ ጠግኖ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረጉ ተግባር ልዩ ትኩረትን ይፈልጋል።



# ባህልና ልማት በኢትዮጵያ

## በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች


አርታኢ

ሺፈራው በቀለ



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

Forum for Social Studies

# ባህልና ልማት በኢትዮጵያ

## በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች

አርታኢ
ሺፈራው በቀለ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

© 2004 ዓ.ም. ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው።

አዲስ አበባ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፡- ቆንጅት በለጠ

ISBN: 978-99944-50-41-1

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ. ቁጥር 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ www.fssethiopia.org

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት፣ ከዴንማርክ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ።

# መቅድም

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ካሉት ዋና ዋና አላማዎች አንዱ በልማት መስክ ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ባለሙያዎችን፣ የልማት ሊቃውንትንና ተመራማሪዎችን የሚያገናኙ ምሁራዊ ውይይቶችን በማድረግ የህብረተሰቡን ቁልፍ ችግሮች መዳሰስና መፍትሄ ማፈላለግ ነው፡፡ ለዚህም ነው የተለያዩ የህብረተሰብ ባለድርሻዎች በአገሪቱ የልማት ጉዳዮች ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑና ሂደቱን ለማቀላጠፍ የሚረዱ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ ህዝባዊ ውይይቶችን ማካሄድ አንዱ አላማው አድርጎ የተንቀሳቀሰው፡፡ በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ከተደረጉ አያሌ የውይይት ጭብጦች ውስጥ «ባህልና ልማት» በሚል ርዕስ የተደረጉት ተከታታይ ውይይቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ በየሁለት ወሩ የተደረጉ ውይይቶች አሥራ ሁለት ሲሆኑ ከመጋቢት 2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥር 2003 ዓ.ም. ድረስ ዘልቀዋል፡፡ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎቹ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ወይም ለረጅም ዘመን በተግባር ከችግሩ ጋር ሲታገሉ የቆዩና በዚህም የተነሳ ጥልቅ ልምድና ሰፊ እውቀት ያካበቱ ኤክስፐርቶች ናቸው፡፡

አድማጮቹም በተለምዶ አነጋገር «የልማት አስፈጻሚዎች» (Development Practitioners) የሚባሉት ሲሆኑ እነሱም ከሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የተጋበዙ የባህልና የልማት ባለሙያዎች፣ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ መያዶች (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ውስጥ የሚሠሩ የልማት ኤክስፐርቶች ናቸው፡፡ የቀረቡት 12ቱም ወረቀቶች ሰፊና የሞቁ ውይይቶች ተካሂደውባቸው ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ላቀረቡት እንዲሁም የረጅም ጊዜ የበለጸገ የሙያ ልምዳቸውን ለታዳሚዎች ላካፈሉት ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አንዳንድ ተካፋዮች በጋዜጣ ላይ አስተያየት ይሰጡ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ በወቅቱ በስፋት ይነበብ የነበረው *አዲስ ነገር* የተባለው የግል ጋዜጣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን በአመቱ ተጽእኖ ፈጣሪ ከነበሩ ድርጅቶች አንዱ አድርጎ እንዲመርጥ ካስቻሉት መስፈርቶች አንዱ ይኼው ውይይት እንደነበር ጠቅሷል፡፡

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በምርምርና በንባብ ላይ የተመሰረቱ ወይም ከጥልቅ ልምድ የመነጩ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ እንዲሁም በስፋት ቢነበቡና በየቤተ መጻህፍቱም ውስጥ ቢቀመጡ ሊኖራቸው የሚችለውን ፋይዳ በማጤን እንዲታተሙ ወስኗል፡፡ በዚህም ውሳኔ

# ማውጫ

| | |
|---|---|
| *መቅድም* | iv |
| *ምህረት አየነው* | |
| *መግቢያ* | vi |
| *ሺፈራው በቀለ* | |
| ባሕልና ልማት፡- ምንነታቸውና ትስስራቸው | 1 |
| *የራስወርቅ አድማሴ* | |
| የብሄራዊ ቅርስ ልማትና ቱሪዝም | 27 |
| *ቴዎድሮስ አጥላባቸው* | |
| የሙስና ባሕላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ | 47 |
| *ክቡር ገና* | |
| ባሕል ከልማትና ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለው ግንኙነት | 67 |
| *ዘውዴ አበጋዝ* | |
| ሀገራዊ እውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ | 77 |
| *አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ* | |
| ቁዘማ፡- ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ | 97 |
| *ፈቃደ አዘዘ* | |
| እምነት-ነክ ክብረ በዓላት፣ ባሕላዊ ክንውኖችና የልማት አንድምታቸው | 139 |
| *ፈለቀ ታደለ* | |
| የአደባባይ ልመና-ምፅዋት | 159 |
| *የራስወርቅ አድማሴ* | |
| ሥነ ጥበብና ልማት | 181 |
| *አስፋው ዳምጤ* | |
| የሥዕል ጥበብ ለባህልና ልማት ዕድገት | 191 |
| *እሸቱ ጥሩነህ* | |
| የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ | 203 |
| *ውዱ ጣፈጠ* | |
| "የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናት" አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ | 219 |
| *አበባው በቀለ* | |
| ዋቢ መጻሕፍት | 241 |
| ደራሲዎቹ | 251 |

መሰረት ሰፊ አርትኦት ከተደረገባቸው በኋላ እነሆ እዚህ መጽሀፍ ውስጥ ተካትተው ሊወጡ በቅተዋል፡፡

ውይይቶቹ እንዲደረጉ እርዳታ የለገሱንን ድርጅቶች ማመስገን እወዳለሁ፤ እነርሱም የኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት፣ የዴንማርክ ኤምባሲ፣ የአየርላንድ ኤምባሲና የእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ግዮን ሆቴል አስተዳደር ላደረገልን ትብብርና ለሰጠን አገልግሎት ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም፣ ውይይቶቹ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄዱና መጽሀፉም ጥሩ ሆኖ እንዲወጣ ላደረጉት ጥረት የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሰራተኞችን ከልብ ማመስገን እወዳለሁ፡፡

ምህረት አየነው (ዶ/ር)
የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈጻሚ ዳሬክተር

# መግቢያ

ባሁኑ ጊዜ ልማት ከባህል ተለይቶ መታየት የለበትም የሚለው አስተሳሰብ ሰፊ ተቀባይነት ያለው ቢመስልም የልማትን ታሪክ በምናጠናበት ጊዜ የምንገነዘበው በቀደሙት ጊዜያት ለባህል ትኩረትም ሆነ ሥፍራ ያልተሰጠው መሆኑን ነው። እንዲያውም የልማትን የትምህርት መስኮች (Development Studies) ጉዞ ቀረብ ብለን ያየን እንደሆነ ብዙዎቹ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ የተነሱ ቢሆኑም ባብዛኛው የሚያተኩሩት በእድገት ላይ ብቻ እንጅ ልማት ያለ ባህል ሊሳካ እንደማይችል የተገነዘቡ አይመስልም ነበር።

እርግጥ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት እጅግ ቀድሞ ያስተምር የነበረው ማክስ ቬበር የተባለው የጀርመን የሶሽሎጂ ሊቅ የባህልንና የልማትን ጥብቅ ቁርኝት በመገንዘቡ የምእራብ አውሮፓ አገሮች በቴክኖሎጂና በካፒታሊዝም ፈጥነው ሊጓዙ የቻሉት የፕሮቴስታንትን መርህ (ኤቲክ) በመከተላቸው ነው እስከማለት ደርሶ ነበር። ይህም አስተሳሰቡ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶለት ነበር። ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ ደግሞ የምስራቅ ኤስያ አገሮች (መጀመሪያ ጃፓን፣ ቀጥሎ ደቡብ ኮርያ፣ ታይዋን፣ ሆንግ ኮንግና ሲንጋፖር) ሊመነደጉ የቻሉት የኮንፍዬሽስ እምነትና አስተሳሰብ ተከታይ ስለነበሩ ይህ እምነትና አስተሳሰብም የጠበቀ የስራ ዲስፒሊን፣ ጠንካራ የቁጠባ ልማድና ስር የሰደደ የመደራጀት ክሂሎት ህዝቡንም ሆነ የፖለቲካውንና የቢዝነስ ልሂቃንን ስለሰጣቸው ነበር የሚል አመለካከት ነበር።

የልማት ሳይንሶች ላይ የነገሰው አስተሳሰብ ግን ለባህል ስፍራ የማይሰጥ፤ ልማት እንዲኖር ከተፈለገ ወሳኞቹ ሁነቶች (Variables) የማእድን መኖር፣ ወይም በሌላ መልክ ካፒታል ማግኘት፣ በነዚህም ላይ ተመስርቶ ትምህርትን ማስፋፋት፣ ኢንቬስትመንትን ማሳደግ...ወዘተ የመሳሰሉት ስለነበሩ ሊቃውንቱ ይህንኑ ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ከልማት የትምህርት መስኮች ውስጥ አንዱ የሆነው ኢኮኖሚክስን ብንወስድ ልማታዊ ኢኮኖሚክስ መልክ ይዞ ከተፈጠረበት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ እስከ 1980ዎቹ (እ.ኤ.አ) ማብቂያ ድረስ ባሉት አራቱ አስርት ዘመናት ውስጥ ባህል በኤኮኖሚ እድገት ውስጥ ለሚኖረው ድርሻ ይህ ነው የሚባል ግምት አልተሰጠውም ነበር። ሁኔታዎች መቀየር የጀመሩት በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነው።

የተባበሩት መንግስታት ባህል ለልማት የሚኖረውን ወሳኝ አስተዋጽኦ በመገንዘብ በ1988 (እ.ኤ.አ) United Nation's Decade for Cultural Development from 1988 to 1997 የሚል አወጀ። ይህም ልማትና ባህል ያላቸውን ቁርኝት በአካዳሚ መስክና

በፖሊሲ ትግበራ እንዲሁም በልማት አመራርና አስተዳደር ጉላ ብሎ እንዲወጣና የውይይቶች እምብርት እንዲሆን ረድቷል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ባህል በልማት ነክ ውይይቶችና ክርክሮች ውስጥ ማእከላዊ ስፍራ ሊይዝ በቃ። በሌላ አነጋገር፣ የልማት ሊቃውንት፣ የአለም ባንክ ኤክስፐርቶች እና የልማት ፈጻሚዎች ልማት እንዲመጣ ከተፈለገ ባህልም መካተት እንዳለበት ከፍ ባለ ድምጽ መከራከር ጀመሩ። የአንዳንዶቹ ጥናታዊ ጽሁፎች አርእስት ብቻ የክርክሩን አቅጣጫ ሊጠቁሙ ይችላሉ። አንድ ዴቪስ (S. Davis) የተባለ ተመራማሪ ያሳተመው "Bringing Culture into the Development Paradigm: The View from the World Bank" (1999) የሚለው ጽሁፍ ጥሩ ምሣሌ ሊሆን ይችላል። (በተጨማሪም UNESCO 1995ን እና UNESCO 2000 ን ይመለከቷል።) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በበኩሉ በ1998 ዓ.ም. UN Report on the Stockholm Intergovernmental Conference on Culture and Development የተሰኘ መጽሀፍ አሳተመ። ከላይ የተጠቀሱት ተደራራቢና ተደጋጋፊ ጥረቶች ይህንን አስተሳሰብ ዩኒቨርሲቲዎችም መቀበል እንዲጀምሩ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ጥልቀትና ስፋት ያለው ክርክር በልማት ላይ በ1980ዎቹም ሆነ ከዚያ በፊት ተካሂዷል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይከብዳል። የሆነ ሆኖ አንዳንድ ሊቃውንት ባህል ለልማት ያለውን ፋይዳ ማንሳታቸው አልቀረም። ከበደ ሚካኤል በጻፉዋቸው አንዳንድ መጻህፍት ውስጥ (ለምሳሌ *ጃፓን እንደምን ሰለጠነች*፣ 1946) ጉዳዩን ጠቁመውት ነበር። ምናልባት ግምባር ቀደም ሊሆኑ የሚችሉት ግን በልማት ጉዳይ ላይ የተመራመሩትና የተከራከሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ናቸው። ገና አብዮቱ ከመፈንዳቱ በፊት በአደባባይ የባህልን ፋይዳ አንስተው ተከራክረው ነበር። (Mesfin, 1966a) በደርግ ዘመን የባህልንና የልማትን ቁርኝት በተደጋጋሚ ያነሱት ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ናቸው። ዶ/ር ፈቃደ የስነጽሁፍና የፎክሎር ተመራማሪ ናቸው፤ የፎክሎር የትምህርት ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲከፈት ሲከራከሩ አንዱ ማጠየቂያቸው ፎክሎር ለልማት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው የሚለው መከራከያ ነጥባቸው ነበር። (የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ 6 ይመለከቷል) ይሁንና እነዚህና (ምናልባት እኔ ያላወቅኳቸው) ሌሎች ድምጾች ተሰሚነት ነበራቸው ማለት አይቻልም።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ አመራር የባህልንና የልማትን ከፍተኛ ቁርኝት በመገንዘብ ጥናታዊ ጽሁፎች እየቀረቡበት በሚደረግ ሕዝባዊ ውይይት ጭብጡ እንዲዳሰስ ይወስናል። ተናጋሪዎቹን የመምረጥና ውይይቱን የማዘጋጀት ኃላፊነት ለኔ ይሰጠኛል። እኔም በጊዜው የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ሥራ አስፈጻሚ ከነበሩት ከፕ/ር ባህሩ ዘውዴ ጋር በመመካከር 12 ርእሶችንና

ወረቀት አቅራቢዎችን መረጥኩ። ውይይቱም ከመጋቢት 2001 ዓ.ም. እስከ ጥር 2003 ዓ.ም. ድረስ በየሁለት ወሩ ተካሄደ። እያንዳንዱ ወረቀት ከቀረበ በኋላ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ እውቀት ያለው (ያላት) ምሁር እንዲተችበት (እንድትተችበት) ተደርጓል። ከዚያ በኋላ አድማጮች ሃሳባቸውን እንዲያሰሙ፣ ጥያቄ እንዲያቀርቡ፣ ወይም ሂስ እንዲሰነዝሩ እድል ይሰጥ ነበር። በዚህ አይነት ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እያንዳንዱ ደራሲ የተሰነዘሩትን ጥያቄዎችና የቀረቡበትን ትችቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ጽሁፉን እንዲከልስ ተደርጓል። ውጤቱ ይህ መጽሀፍ ነው።

መጽሀፉ ብዙ ባህልና ልማት የሚገናኙባቸውን ገጽታዎችን ይዳስሳል። በዚህም የተነሳ አያሌ ወጥ የሆኑ ሀሳቦች በየምእራፎቹ ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ። መጽሀፉ ሲጀምር በዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ ጽሁፍ ሲሆን ይህ ምዕራፍ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑትን የባህል ትርጉሞች ከዳሰሰ በኋላ ለዚህ አላማ ሊሆን የሚችለውን ትርጉም ያቀርባል። ምእራፉ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ የሶሽዮሎጂ ቲኦሪዎችን በመቃኘቱ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ለቋንቋው አበርክቷል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ከመጀመሪያው ምእራፍ በኋላ የሚመጡት ጽሁፎች ልዩ ልዩ የባህልና የልማት ገጽታዎችንና ግንኙነቶቻቸውን የሚዳስሱ ሲሆን እያንዳንዳቸው እስካሁን ያልነተሱ ጉዳዮችን በማቅረባቸው ፣ ወይም እስካሁን ያልታተሙ መረጃዎችን (data) በማምጣታቸው ወጥነት አግኝተዋል። በዚህ ጭብጥ ላይ ይህ ህትመት የመጀመሪያውና ፈር ቀዳጅ ስለሆነ መጽሀፉ አዳዲስ ምርምሮች ወደፊት እንዲደረጉ መንገድ ይከፍታል የሚል ተስፋ አለን።

ይህንን መጽሀፍ ለህትመት ስናዘጋጅ አንዳንድ የአርትኦት ውሳኔዎች አድርገናል። የአማርኛ ቋንቋ የሞክሼ ሆሄያት ጉዳይ አሁንም ያልተፈታ ችግር እንደሆነ በመገንዘብ፣ የደራሲዎቹን የሆሄ አመራረጥ እንዳለ ትተነዋል። በዚህ የተነሳ የሞክሼ ሆሄያት አጠቃቀም ዝብርቅርቅ ያለ ይመስላል፤ ይሁን እንጅ በኛ አመለካከት ሊሆን ይገባል በምንለው አካሄድ (ማለትም ሞክሼዎቹን ሆሄያት - ሃ፣ሐ፣ሠ፣ኀ - በሙሉ አጥፍቶ የመጀመሪያዎቹን ሆሄያት - ሀ፣ሰ፣አን - ብቻ መጠቀም) ጽሁፎቹን ለመቀየር ጥያቄ ስናቀርብ አንዳንዶቹ ደራሲዎች ጠንካራ ተቃውሞ ስላነሱ እንዳለ መተውን መርጠናል።

ሌላው ከዚህ ጋራ የተያያዘው ችግር ስርአተ ነጥብን የሚመለከት ይሆናል፤ በተለይም ድርብ ሰረዝን ይመለከታል። የቋንቋውን ህግጋት ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚባሉት ሊቃውንት እንኳ ድርብ ሰረዝን በሚመለከት አንድ አይነት ስርአት

አይከተሉም፡፡ አንዱ በነጠላ ሰረዝ የሚለያያቸውን ሀረጐች ሌላው በድርብ ሰረዝ ይለያያቸዋል፡፡ሌላ ልናነሳው የምንፈልገው የአመተ ምህረት አጻጻፍን ነው፡፡ አንዳንዱ ደራሲ ቁጥሮችን በግእዝ ሲጽፍ ሌላው የአረብኛውን ይከተላል፡፡ በነዚህ ሁሉ ላይ የደራሲዎችን ምርጫ ለማክበር ሞክረናል፡፡

በመጨረሻም መልካም ንባብ እንላለን፡፡

ሺፈራው በቀለ
አርታኢ

# ባሕልና ልማት:- ምንነታቸውና ትስስራቸው

## *የራስወርቅ አድማሴ*

ይኽ ፅሑፍ በባሕልና ልማት ጉዳይ ላይ የሚደረገው የውይይት መርሃ-ግብር መክፈቻ ነው:: በመሆኑም፤ በባሕል፣ በልማትና በሌሎች ተያያዥ ፅንሰ-ሃሳቦች ፍችና አጠቃላይ ትስስር ላይ ያተኩራል:: ባሕልና ልማት ስንል ምን ማለታችን ነው? የባሕልና የልማት ትስስርስ ምን መሳይ ነው? የባህል ለውጥ ኅብረተሰባዊ ልማት ያመጣል ወይ? በተቃራኒውስ የባህል ኋላቀርነት ኅብረተሰባዊ ልማትን ይገታል ወይ? ለሚሉትና ለተያያዥ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል::

የተለያዩ የዕውቀትና የምርምር ዘርፎች እንደ "ባሕል" እና "ልማት" ላሉ ፅንሰ-ሃሳቦች ያሏቸው ግንዛቤና የሚሰጧቸው ትርጉሞች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይለያያሉ:: በየአንድአንዱ የዕውቀት ዘርፍም ውስጥ ቢሆን የተለያዩ የአመለካከት አዝማሚያዎች ባለመጥፋታቸው የተነሳ፤ እንደ "ባሕል" እና "ልማት" ያሉ ፅንሰ-ሃሳቦችን በተለያየ መንገድ የመገንዘብና የመገልገል ልዩነቶች መከሰታቸው አይቀርም:: በነዚህ የተነሳ ማንኛቸውም ኅብረተሰብን የሚመለከቱ ፅንሰ-ሃሳቦች በርካታ ፍችዎች ይኖሯቸዋልና፤ ከሁሉ አስቀድመን በዋነኞቹ ፅንሰ-ሃሳቦች ፍች ላይ በማተኮር መነሻችንን ማጥራት ይኖርብናል::

## 1. የ"ባሕል" ፅንሰ-ሃሳብ ፍቺ

በሃገራችን "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ባሕል" በሚለው የአማርኛ ቃል ተተርጉሞ ሲሰራበት የቆዬና የተለመደ በመሆኑ ሁለቱን ቃላት በተመለከተ ምንም የሰፋ የትርጉም ክፍተትና የጎላ ያለመገጣጠም ችግር የለም:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 (እ.ኤ.አ) ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ-ቃላት "ባሕል" የሚለውን ቃል "የኅብረተሰብ[1] የአነዋንዋር ዘዴ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት" ብሎ ይፈታዋል:: ይኽም ፍች "ካልቸር" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከሚሰጡት የተለያዩ ፍችዎች ቢያንስ የጥቂቶቹን ይዘት ደህና አድርጎ የሚጋራ ነው:: በመሆኑም፣ ያለምንም ተጨማሪ ማስረጃ፣ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ "ካልቸር" ስንል "ባሕል"፤ "ባሕል" ስንልም "ካልቸር" ማለታችን መሆኑን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሳታውቀን ወደ ዋናዎቹ የፅንሰ-ሃሳቦች ፍች ጉዳይ እናልፋለን::

"ባሕል" ለሚለው ቃል ትርጉም የመስጠቱና ከበስተጀርባው ያለውን ፅንሰ-ሃሳብ ግልፅ የማድረጉ ተግባር ቀላል አይደለም:: የዚህ የአማርኛ ቃል አቻ የሆነውን የእንግሊዝኛ ቃል አስመልክቶ ሬመንድ ዊሊያም "ካልቸር በእንግሊዘኛ ቋንቋ

---

[1] በዚህ ፅሑፍ ውስጥ "ኅብረተሰብ" የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት እንግሊዝኛ "ሶሳይቲ" ለሚለው፤ "ማኅብረሰብ" የሚለውን ደግሞ እንግሊዝኛ "ኮሚዩኒቲ" ለሚለው አቻ በማድረግ ነው::

ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ወይም ሶስት እጅግ የተወሳሰቡ ቃላት መካከል አንዱ ነው" ያለው (ጀንክስ 2007: 928)፤ ለአማርኛውም ቃል በሚገባ ይሰራል:: ይኸ "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃልና ከበስተጀርባው ያለው ፅንሰ-ሃሳብ የፈለቀውና በሥራ ላይ መዋል የጀመረው በምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ ኅብረተሰባዊ ለውጦች በተካሄዱባቸው በአስራ-ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት ማብቂያና በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት ውስጥ መሆኑ ከነዚያ ገና በመጠናት ላይ ካሉ ዝብርቅርቅ የለውጥ ክስተቶችና መጠሪያዎቻቸው ጋር በመያያዝ "ባሕል" የሚለውም ቃል ትርጉም እንደዚሁ የተወሳሰበና ላይ-ላዩን ሲያዩት የሚያምር፣ ሲመረምሩት ደግሞ የሚያደናግር እንዲሆን አድርጎታል:: በዚህም የተነሳ በዚህ ጉዳይ ላይ አበክረን እንድናትት ሁኔታው ያስገድደናል::

ቀደም ሲል መሬት ከማረስ (the cultivation of land) ጋር ተያይዞ የመነጨው "ካልቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ሁለት ዋነኛ ዘመናዊ ትርጉሞች ይዞአል:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:- በአስራ-ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት የፈለቀውና ኪነ-ጥበብን፣ ሙዚቃን፣ እና ሥነ-ፅሁፍን የሚመለከተው ሂዩማኒስቲክ ትርጉም እና፤ በአስራ-ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት ጠቅላላ የሰው-ልጅን ተግባራት ድምር ለማመልከት የተተከለው የአንትሮፓሎጅ ትርጉም ናቸው:: እነዚህ ሁለት ተርጉሞች ዛሬም የሚሰራባቸው በመሆናቸው፣ ሁለቱም መዘንጋት የለባቸውም::

ይሁንና፣ የመጀመሪያው ትርጉም እኔ እስከማወቀው ድረስ አወዛጋቢ ባለመሆኑና ከራሴ መደበኛ የሙያ መስመርም ውጭ በመሆኑ የተነሳ፤ ይህንን ሂዩማኒስቲክ ትርጉሙን የመተንተኑን ተግባር ወደፊት በዚሁ ዛሬ ሀ-ብለን በጀመርነው መ'ርሀ-ግብር ውስጥ ከጉዳዩ ጋር በተያያዙ አርእስት ላይ የጥናቶቻቸውን ወጤቶች ለሚያቀረቡልንና ለጉዳዩ ቅርበት ላላቸው ምሁራን እተውና በቀጥታ ወደ አንትሮፓሎጅ-ሶሲዮሎጅ ትርጉሙ አልፋለሁ::

ባለፈው ምዕተ-ዓመት አንትሮፖሎጅስቶች "ባሕል" ለሚለው ፅንሰ-ሃሳብ በርከታ ትርጉሞች ሰጥተዋል:: በዚህ የተነሳና ከዚህ ተከትሎ የመጣውን የፍች ትርምስምስ ለማሳየትም፤ክሮበር እና ክሉክኾኽን የተባሉ ሁለት አንትሮፖሎጅስቶች የዛሬ ሃምሳ ስምንት ዓመት (እ.ኤ.አ. በ 1952) ባደረጉት ጥናት፤ በዚያን ጊዜ አንድ መቶ ስልሳ የተለያዩ የ"ባሕል" ፍችዎች እንደነበሩ አሳይተዋል (ፌራሮ 2001: 22):: ከዚያን ጊዜ ወዲህ በተቆጠሩት ዓመታት ደግሞ በርካታ ተጨማሪ ፍችዎች እንደተሰጡት መገመት ይቻላል::

"ባሕል" ለሚለው ፅንሰ-ሃሳብ የተሰጡት ትርጉሞች፤ እጅግ ከመበራከታቸው በተጨማሪ አንድ ዓይነተኛ የጋራ ጠባይ አላቸው:: የሚገለፁባቸው ፊደላት ቁጥር ይብዛም ይነስ፤ ከሞላ-ጎደል ሁሉም ማለት ይቻላል፤ ሲበዛ ሁሉ-አቀፍ ናቸው:: እግረ-መንገዳችንን ይህን አያጤን፤ የተለያዩ የባሕል ፍችዎችን በናሙናነት እንቃኝ::

አንድ የቆየ ግን እስከዛሬ ዘመን ድረስ በሰፊው የሚጠቀስ የ"ባሕል" ፍቺ፤ ኤድዋርድ ቴለር እ.ኤ.አ. በ 1871 የሰጠው ሲሆን፤ እንደሚከተለው ይነበባል፤

> *ባሕል ወይም ስልጣኔ፤ ያ ዕውቀትን፣ እምነትን፣ ኪነ-ጥበብን፣ ሞራልን፣ ሕግን፣ ወግን፣ እና ሌሎች ሰው የኅብረተሰብ አባል በመሆኑ የቀሰማቸውን ክህሎቶችና ልምዶች ጭምር የሚያጠቃልለው ውስብስብ የሆነ ዉሁድ ነው* (ካልሁን 2002: 105)::

ቀረብ ባለ ጊዜ ደግሞ፤ "ባሕል" በዶንስ (1971) እንደሚከተለው ተፈቶ ይነበባል፤

> ባሕል ከአካባቢያችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያሉንን ግንኙነቶች በተመለከተ የሚመራን የዐዕምሮ/የሕሊና ካርታ (mental map) ነው (ፌራሮ 2001: 22)::

በፊደላት ብዛት ረገድ ካለፈው ባጠረ መንገድም እነደሚከተለው ሃች በተባለ ተመራማሪ (1985) ተፈትቶአል፤

> ባሕል የአንድ ሕዝብ የአኗኗር ዘዴ ነው (ፌራሮ 2001: 22)::

ከላይ የተጠቀሱት አልበቁ ይመስል፤ የፍችው ፍሰት እንደቀጠለ ነው:: በ2001 ለሕትመት በበቃ መፅሐፉ ውስጥ ጌሪ ፌራሮ የሚከተለውን ይላል::

> *አስቀድመው በተሰጡት በርካታ ፍቺዎች ላይ በመጨመር፤ ለኛ ጉዳይ ስንል፤ የባሕልን ፅንሰ-ሃሳብ ሰዎች እንደ ህብረተሰብ አባላት ያላቸው፣ የሚያስቡት፣ እና የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር ሁሉ ነው፤ ብለን* እንተረጉመዋለን (ፌራሮ 2001: 22)::

በመቀጠልም፣ ፌራሮ ይህንን ከላይ የሰጠውን ፍች እንደሚከተለው ያብራራል:: ማብራሪያውም፣ በዙሀኑ አንትሮፖሎጅስቶች የሚጋሩዋቸውንና እኛም በተራችን ለተነሳንበት ጉዳይ ጠቃሚ የሆኑ ቁም-ነገሮችን ያቀፈ በመሆኑ ቀጥለን እንዳለ አስፍረነዋል::

> *ይኽ ፍቺ ጠቋሚነት አለው:: ምክንያቱም፤ በውስጡ የያዛቸው ሦስቱ ግሦች ከሦስቱ ዋነኛ የባሕል ይዘቶች ጋር ይገጥማሉና ነው:: ይኸውም፤ ማንኛውም ሰዎች ያላቸው ነገር ሁሉ የሚለው ቁስ-አካላዊ ንብረትን ያመለክታል፤ ማንኛ ውም ሰዎች የሚያስቡት ነገር ሁሉ የሚለው በጭንቅላታቸው ይዘው የሚዞሩትን እንደ ሃሳቦች፣ ህብረተሰባዊ ደንቦችና፣ አመለካከቶች ያሉትን፤ እናም ማንኛውም ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ሁሉ የሚለው ደግሞ መልክ የያዘ ባሕርያቸውን ያመለክታል:: ስለዚህም፤ ባሕሎች ሁሉ ቁስ-አካላዊ ነገሮችን/ንብረትን፤ እናም ሃሳቦችን፣ ኅብረተሰባዊ ደንቦችንና፣ አመለካከቶችን፤ እንዲሁም መልክ-የያዘ ባሕርይን ያቅፋሉ ማለት ነው* (ፌራሮ 2000: 23)::

ከላይ ያቀረብናቸው የ"ባሕል" ፍችዎች በሚገባ እንደሚያሳዩት፤ የሶሺያል-አንትሮፓሎጂ የዕውቀት ዘርፍ የ"ባሕል"ን ፅንሰ-ሃሳብ የሚገነዘበው እጅግ ሰፊና መላ ኅብረተሰባዊ ይዘቶችን (ክስተቶችን) በሚያካትት መልኩ ነው:: በዚህ ግንዛቤ "ባሕል" ማለት የአንድ ኅብረተሰብ አባላት የሚረከቡአቸውን የተጠራቀሙ ዕውቀቶች፣ ዕምነቶች፣ ኪነ-ጥበባት፣ መመሪያዎች፣ አርማዎች፣ አመለካከቶች፣ ሥነ-ምግባራት፣ ህግጋት፣ ወጎች፣ ተለምዶዎችና፣ ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁስ-አካላዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውሁድ ነው:: ይህንን የ"ባሕል" ግንዛቤ ይዘን ዋነኛ ጉዳያችን ወደ ሆነው የባሕልንና የልማትን ትስስር የመመርመር ሥራ የዞርን እንደሆነ፤ አስቸጋሪ የ"ጥምጥም ትንታኔ" ማጥ ውስጥ እንገባና፤ "ሁሉንም ነገር የሚያቅፈው ባሕል ሁሉንም ነገር

የሚመለከተውን ልማት ይወስናል" ወደሚል ፋይዳ-ቢስ ድምዳሜ እንደርሳለን::

ስለዚህ፣ በጠባብ ትርጉሙ በመውሰድ፤ "ባሕል" አንድን *ኅብረተሰባዊ የወጎች ሥርዓትን* (a system of social norms) *ያመለክታል::* ይኸም *ኅብረተሰባዊ የወጎች ሥርዓት* ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ወጎቹን፣ ልምዶችንና፣ እርሞችን፣ ልማዳዊ-ሕጎችን፣ ድንጋጌዎችንና፣ ከነዚህ ጋር የተዛመዱ እምነቶችን፤ አመለካከቶችንና፣ ጠባዮችን ያቅፋል ብለን ብንነሳ፤ ለያዝነው "የባሕልና የልማት ትስስር" ጉዳይ ጠቃሚ የሚሆነን ይመስለኛል::

## 2. ለባሕል ተቀራራቢና አሳሳች የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦችና መጠሪያ ቃላቶቻቸው

ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው "ባሕል" የሚለው ቃልና የቆመለት ጽንሰ-ሃሳብ አጅግ ሰፊና ሁሉ-አቀፍ ከመሆን አልፎ የሀሳብ መንስራፋት አስከትሏል:: ከድጡ ወደ ማጡ እነዲሉ፣ በኛ አገር ደግሞ፤ ለባሕል ተቀራራቢ የሆኑ ሌሎች ፅንሰ-ሀሳቦችን ለይተን በማውጣት መጠሪያ ስሞች በመስጠት ፋንታ ከባሕል ጋር አብረን ወቅጠን ቀብረናቸዋል:: በእንደዚህም ስለ ባሕል ያለንን ግንዛቤ ከማድበስበስ አልፈን ከሆነው የበለጠ አግዝፈነዋል፤ ያልሆነውን አድርገነዋል፤ ላልዋለበትም ሁሉ ተጠያቂ እያደርግነውማል:: ለዚህም እንደ "ጎጂ-ባሕል"፣ "ባሕላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች"፣ "የባሕል-ልብስ"፣ "የባሕል-ምግብ"፣ የሚሉትንና የመሳሰሉት:ን አባባሎችንና አጠቃቀሞችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል:: በመቀጠል፤ እነዚህን የባሕል ተቀራራቢና አሳሳች የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦችና ፍቺዎቻቸውን እንመልከት::

*ትራዲሽን* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚፈታ በመዝገበ ቃላትም ሆነ በአጠቃቀም መሰረት የያዘ የአማርኛ ቃል ላገኝ አልቻልኩም፤ በጥቅም ላይ ያልዋለ ነገር ደግሞ ከሌለ የሚቆጠር ይመስለኛል:: ምናልባት "ነባር-ልምድ" የሚለው ይቀርበው ይሆናል:: *ትራዲሽን (ነባር-ልምድ)* ባጠቃላይ ከቀድሞው ተያያዥነት እንዳላቸው የሚያመለክቱና የሚያስደምጡ ነባር ባሕላዊ ገጽታዎቸን ሁሉ ያመለክታል:: እነዚህም፤ በመሰረቱ፤ ማንኛውም ዓይነት እምነቶች፣ልምዶች፣ ልማዶች፣ እውቀቶች፣ ወይም የኅብረተሰብ ዋነኛ ደንቦች ሊሆኑ ይችላሉ (ካልሁን 2002: 488):: ባጭሩ፤ "ሲወርድ-ሲዋረድ" የመጣ ነባር የሆነ ኅበረተሰባዊ ክስተት፣ አድራጎት፣ ወይም አሰራር፣ ሁሉ ትራዲሽን ይባላል ማለት ነው:: -- ፍልሚያ ሆነ ጉማ፣ አንደርቢ ሆነ መፈትሄ-ስራይ፣ ምግብ ሆነ አመጋገብ፣ ልብስ ሆነ አለባበስ፣ ነባር መሆኑን እስካመለከተንና እስካስደመጥን ድረስ ትራዲሽን ይባላል ማለት ነው::

እዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ የግድ መነሳቱ አይቀርም:: አንድ ህብረተሰባዊ ክስተት፣ አድራጎት፣ ወይም አሰራር፣ ምን ያህል ጊዜ ካስቆጠረ ወይም ስንት ትውልድ ከዘለለ በሁዋላ ነው ነባር-ልምድ ወይም ትራዲሽናል ሊባል የሚችለው? ይህ ጉዳይ ስናድበሰብሳቸው ከቆየነው ዋነኛ የጽንሰ-ሃሳብ ክፍተቶች አንዱ ነው::

*ልምድ* (custom) ማንኛውም የአንድ ማኅበረሰባዊ ስብስብ አይነተኛ የሆነ አድራጎት ወይም ወግ ነው:: ይሁንና፤ ይህ ጽንሰ-ሃሳብ ባብዛኛው ባሕል በሚለው ስር እየተጠቃለለ መጥቷል (ካልሁን 2002: 107)::

*ልማዳዊ-ሕግ* (customary law) በተፃፈ ድንጋጌ መልክ ሳይሆን በነባር-ልማድ አማካይነት ተላልፎ የመጣ ሕግ ነው (ካልሁን 2002: 107))::

*"ወግ"ን* (norm) ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 (እ.ኤ.አ) ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ-ቃላት፤ *"ስርዓት፣ ደንብ (ከጥንት ሲያያዝ የመጣ)"* ይለዋል::

## 3. አንዳንድ የባሕል ገፀ-ባሕርያት

*ባሕል፣ ማንኛውም ኅብረተሰባዊ ሥርዓት ከሚያቅፋቸው አራት ይዘቶቹ ውስጥ አንደኛው ሲሆን፤* ሌሎቹ ሦስቱ የኅብረተሰባዊ ስርዓት ይዘቶች ኅብረተሰባዊ ሥርዓት (social structure) ፣ ሕዝብ (population)፣ እና የአካባቢ፣ የተፈጥሮና የፍጥረታት ትስስር (ecology) ናቸው::

*የባሕል ባለቤት ኅብረተሰብ፣ ዝቅ ሲል ማኅበረሰብ ነው::* ባሕል በኅብረተሰብ ወይም በማኅበረሰብ ውስጥ የታቀፉ ሰዎች የሚጋሩት እንጅ፤ የግል ጉዳይ አይደለም፤ ሊሆንም አይችል::

*ሰዎች ባሕልን ይማሩታል እንጅ በደም አይወርሱትም::* ከአንድ ትውልድ ወደሚቀጥለው በመማማር እየተሸጋገረ ይቀጥላል:: በውልደት ይሁን በማደጎ ወደ አንድ ኅብረተሰብ የገባ አዲስ አባል፤ የኅብረተሰቡን ባሕል በኅብረተሰባዊ የአስተዳደግ ሂደት ውስጥ እንደ ቤተሰብ፤ የአቻዎች ቡድን፤ ትምህርት ቤትና፤ የዕምነት ቤቶች በመሳሰሉት አማካይነት ይላበሰዋል::

*ባሕል ያስችላል፣ ይረዳል እንጅ አይወስንም::* ባሕል የሰዎችን አስተሳሰብ በማረቅ ሳያሰላስሉ አንድን ነገር ከሌላው አባል እንዲጠብቁ ወይም እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል እንጅ፤ የግድ ይህንን ወይም ያንን እንዲያደርጉ ወይም እንዲሆኑ አይወስንባቸውም፤ አያስገድዳቸውም:: ሰዎች የሚገነዘቡትን፤ የሚያደርጉትንና ከማድረግ የሚታቀቡትን በተመለከተ አንፃራዊ ነፃነት አላቸው ማለት ነው::

*አንድ ኅብረተሰብ አባላቱ በሙሉ የሚጋሩት አንድ ነጠላ ባሕልን ብቻ ወይም ብዙ ባሕሎችን ሊያስተናግድ የቻላል::* አንዳንድ የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆኑ ኅብረተሰቦችና ማህበረሰቦች በመላ አባላታቸው የተደመጠ ነጠላ ባሕል ሊኖራቸው ይችላል፤ ኖሯቸውም ታይቷል:: የዘመናችን ሰፋፊ ኅብረተሰቦች ግን፤ ከኅብረተሰቡ *ዋነኛ-ባሕል* ጎን-ለጎን በርካታ *ንዑሳን ባሕሎችን* ያስተናግዳሉ:: አልፎ-አልፎም በዋነኛ ባሕሉ በተወከለው አገር-አቀፍ ጥቅም-ፍላጎትና በአካባቢው *ንዑስ/ክፍል-ባሕል* በተወከለው ጥቅም-ፍላጎት መካከል ግጭት ይፈጠራል:: ከነዚህ ንዑሳን/ክፍለ-ባሕሎች መካከል አንዳንዶቹ ከዋነኛው-ባሕል መለየት ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተቃራኒው ሆነው በሚገኙበት ጊዜ *ተፃራሪ-ባሕሎች* ይባላሉ:: በአንዳንዶቹ ህብረተሰቦች ውስጥማ የቱ ዋነኛ የቱ-የቱ ንዑሳን-ባሕሎች መሆናቸውን መለየት እስከሚያዳግት ድረስ የተመጣጠኑና

የተነባበሩ ከመሆናቸው የተነሳ *ባሕለ-ብዙ ኅብረተሰብ* በመባል ይታወቃሉ:: የኛ ም፣ የዘመናችን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ እንደዚህ ዓይነት ይመስለኛል::

*ባሕል በሂደት ይለወጣል፣ እንጅ ፍፁም እንደነበረ ሆኖ አይቀጥልም አይኖርም::* ባሕል በሂደት ይለወጣል:: ተፈላጊ ሆነው የተገኙ የባሕል ኤለመንቶች ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ በአዲስ ይከሰታሉ፣ ተፈላጊ ያልሆኑት ደግሞ ቀስ-በቀስ መልካቸውን ይቀይራሉ ወይንም ከናካቴው ይከስማሉ:: የለውጡም ሂደት ሁለት መንገዶችን የተከተለ ነው፣ *ፈጠራ-ግኝት እና ውርስ::* አንድ ኅብረተሰብ ወይ አዳዲስ የባሕል ኤለመንቶችን በራሱ ፈጥሮ-አመንጭቶ ይገለገልባቸዋል አልያም ከሌላ ወርሶ ያዋህዳቸዋል፣ ንብረቱ ያደርጋቸዋል:: በተጨማሪ፣ የለውጡ አመጣጥ፣ ዘገምተኛ ወይም ድንገተኛ ሲሆን፣ በሰላም ወይም በግጭት ታጅቦ ሊወለድ ይችላል::

ይኸ በመጨረሻ ያስቀመጥነው የባሕል ጠባይ፣ ከ "ኅብረተሰባዊ ለውጥ" (ሶሽያል-ቼንጅ) ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ፣ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ያሸጋግረናል::

## 4. የ"ልማት" ፅንሰ-ሃሳብ ፍቺ

ሁለተኛው ዋነኛ የውይይታችን ዋልታ "ልማት" ብለን የምንጠራው ፅንሰ-ሃሳብ እንደመሆኑ፣ ከዚህ ላይ ደግሞ እይታችንን ወደዚህ ጉዳይ እናዙር:: ብዙዎቻችን "ልማት" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዳለን አጠያያቂ አይደለም:: ወደ ዝርዝሩ ስንገባ ግን፣ ሁኔታው የሚመስለውን ያህል ቀላል አይደለም::

"ልማት" አንድ ዓይነት ኅብረተሰባዊ ለውጥ ሲሆን፣ ማንኛውም "ኅብረተሰባዊ ለውጥ" ልማት ነው ማለት አይደለም:: "ልማት" አዎንታዊ፣ በጎ፣ ወይም ጠቃሚ፣ ኅብረተሰባዊ ለውጥ ማለት ነው:: ኅብረተሰባዊ ለውጥ ከምንላቸው ክስተቶች ውስጥ አንዳንዳቹ በአንድ ወይም በሌላ ጎናቸው ይበልጡን አሉታዊ፣ ማለትም ከአጠቃላይ ኅብረተሰባዊ ደኅንነት አንፃር ይበልጡን ጎጅና እኩይ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ አዎንታዊ፣ ማለትም በአንድ ወይም በሌላ ጎናቸው ይበልጡን ጠቃሚዎች ሆነው ይገኛሉ:: "ልማት" በምንለው አጠቃላይ አርዕስት ስር የሚካተቱት ኅብረተሰባዊ ለውጦችም፣ የኋለኛዎቹን ዓይነት ማለትም ባብዛኛ ው ጠቃሚ የሆኑትን መሻሻሎች ነው:: "ባብዛኛው" የሚለውን ቃል ደጋግመን የተጠቀምንበትም ሆን ብለን ነው:: ማንኛውም ለውጥ በተወሰነ መጠን አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖች ስለማያጣና፣ እንከን የማይገኝለት ፍፁም ጠቃሚ ወይም ፍፁም ጎጅ ብቻ የሆነ ለውጥ ኖሮ ስለማያውቅና ስለሌለ ነው::

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር መጨመር ያስፈልጋል:: እንደማንኛውም ኅብረተሰባዊ ለውጥ ሁሉ፣ "ልማት" ታስቦበትና ሆን ተብሎ የተወሰደ እርምጃ ውጤት ሊሆን፣ አለያም ያልታሰበና ወይም በራሱ ታስቦበት ከተወሰደ እርምጃ በመከተል የመጣ ላይሆን መቻሉ ዋና ጉዳይ ነው::

"ልማት" ብለን የምንጠራው ህብረተሰባዊ ክስተትና ሂደት በርካታ ንዑስ ይዘቶችን ያቀፈ በመሆኑና፣ ይህን በተመለከተም በተመራማሪዎች ዘንድም

በተወሰነ ደረጃ የተለያዩ አስተያየቶች ስለሚስተናገዱ፣ መጠነኛ ዝርዝር ውስጥ እንድንገባ ያስፈልጋል::

ቀደም ባለው ጊዜ፣ ማለትም በ1950ዎቹና 60ዎቹ አካባቢ፣ የአንድ ኅብረተሰብ ልማት ከኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር አንድ እንደሆነ፣ ወይንም የፊተኛው ከኋለኛው ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑ የተነሳ አብሮት እንደሚጓዝ ማየቱ የተለመደና የተንሰራፋ አመለካከት ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ አመለካከት በመሰረቱ ተለውጦ፣ "ልማት" ሲባል በሰፊው ትርጉሙ በመወሰድ የኢኮኖሚ ልማትንና የሕዝብን የፓለቲካና የሶሺያል ደህንነትን እንዲያቅፍ ተደርጓል (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2009):: የኢኮኖሚ ልማት ያልነውም ቢሆን በጠባብ ትርጉሙ በአንድ ሃገር ከፓለቲካና ከሶሺያል ደህንነት ጋር ተያይዞ በመምጣት ከቀላልና ከዝቅተኛ-ገቢ ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊና ከፍተኛ-ገቢ ኢኮኖሚ የሚደረግ የኅብረተሰብን ለውጥና የሕዝብን ኑሮ መሻሻል የሚያመለክት ሆኖ እየተወሰደ ነው:: እውነተኛ የኑሮ መሻሻል መለኪያ የሆነው የሕዝብ አማካይ ደስተኛነትም ቢሆን የአንድን አገር አማካይ የገቢ-መጠን እድገት ተከትሎ የሚከሰት አለመሆኑ ተረጋግጧል::

ከላይ በተመለከትነው መንገድ "ልማት" በሰፊው ትርጉሙ እየተወሰደ በመሄዱ የተነሳ፣ ተጓዳኝ የሆኑና የተለያዩ የ"ልማት ዓይነቶች"ን የሚገልፁ ቃላቶች ፈልቀዋል:: እነዚህም "የኢኮኖሚ ዕድገት"፣ "የኢኮኖማ ልማት"፣ "ኅብረተሰባዊ ልማት" "ሰብዓዊ ዕድገት"፣ "ቀጣይ ልማት" እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣"ልማት" የምንለው እነዚህን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2009)::

## 5. የባሕልና የኅብረተሰባዊ ለውጥ ትስስር

አለም-አቀፋዊና መንግሥታዊ ፖሊሲ አውጭዎች፣ ህብረተሰባዊ ወጎች (social norms) በሰዎች አመለካከትና ምርጫ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ በመገንዘብ፣ ለባሕላዊ ጉዳዮች ዕውቅና እየሰጡ ሄደዋል:: በመሆኑም፣ ቀስ በቀስ የባህል ጉዳይ በልማት ዙሪያ በሚካሄደው ውይይት ውስጥ ቦታ እያገኘ መጥቷል:: ይሁንና፣ ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን ጫና፣ መጠንና፣ ለፖሊስም ያለውን ተፈላጊነት በተመለከ ተ አሁንም ልዩነቶች አሉ:: የተለያዩ አስተያየቶችም እየተሰጡ ናቸው::

ግለሰቦችን እንደ ነፃ-ወሳኝ (autonomous) ተዋንያን የሚቆጥረው መደበኛው የራሺናል ቾይስ (rational choice) አመለካከት በአንድ በኩል፣ ግለሰቦችን በመሰረቱ የህብረተሰብ ፍጡራንና ተዋንያን አድርጎ በመውሰድ ታሪክ የህብረተሰብ አደረጃጀትና የሃይል ግፊት ውጤት ነው የሚለው አክራሪ መዋቅራዊ (structural) አመለካከት በሌላ በኩል፣ ሁለት ፅንፋዊ አቋሞች በመሆን በመካከላቸው የተለያዩ ወዲህና ወዲያ ያዘመሙ አመለካከቶችን ያቅፋሉ:: በተለያዩ ደረጃም አንዳንዶቹ ተመራማሪዎች የኅብረተሰብ አደረጃጀትን (መዋቅርን) የበላይ ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ ዋናነትን ለተዋናዩ ግለሰብ ወይም ስብስብ ይቸራሉ::

የባህልን ሂደት በተመለከተ ሁለት ርዕዮቶች እንዳሉ መገንዘብ ጠቃሚ ነው:: በአንድ በኩል ባህልን አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደተፈጠረ ግግር የሚቆጥረው ስታቲክ (static ) ርዕዮት ሲገኝ፣በሌላ በኩል የዚህ ተቃራኒ የሆነው ርዕዮት ደግሞ ባህልን

እንደ ተለዋዋጭ ወይም ታዳጊ (dynamic) ፍሰት ይገነዘበዋል፡፡ ከዚህ በመያያዝም፣ ባህልን እንደ ቋሚ ግግር የሚያመለክቱት ባህልን እንደ አፍራሽና የዕድገት እንቅፋት ሲወስዱትና ሲኮንኑት፣ እንደ ታዳጊ ፍሰት የሚገነዘቡት ደግሞ ከልማት ጋር ተያያዥ ሆኖ ራሱም እያደገና እየለማ የሚሄድ የልማት አጋዥ አድርገው ያዩታል፡፡ ታዲያ ከዚህ ወጣ ያሉም አስተያየቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ፅንፈኛ የባህል ተንከባካቢዎች፣የአንድን ባህል በሂደት መለወጥ እንደዚያ ባህል መክሰም በመቁጠር ፈፅሞ እንዳይቀየርና እንዳያድግድ በመፈለግ ማንኛውንም ተያያዥ ልማት አበክረው ይቃወማሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የዛሬ ሃያ ዓመት አካባቢ የሀመርን አገር ከአካባቢው የሚያገናኝ የመኪና መንገድ መሰራቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩ አንድ የዚህ አመለካከት ተጋሪና የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ መምህር ለብዙ ደቂቃዎች በሃዘን በመዋጥ ጭንቅላቱን በሁለት እጁ ይዞ፣ ፈዞና ተኮራምቶ እንደ ቀረ አብረውት የነበሩ የዚያን ጊዜ ተማሪዎቹ ዛሬም ድረስ የአስተማሪያቸውን መሪር ሃዘን በመገረም ያስታውሱታል፡፡

ሳተላይት ቴሌቪዥን ብድር ይግባውና፣ ብዙዎቻችን እንድንጋራው ያደረገንን ሌላ ተመሳሳይ ትዝብት እናንሳ፡፡ በ2001 ዓ.ም የዚህ ፅሁፍ ጭብጥ ለታዳሚዎች በቀረበበት ሳምንት ውስጥ በቢ.ቢ.ሲ. ቴሌቪዥን የግልገል ግቤ-ሦስት ግድብን በማስመልከት በቀረበ ኘሮግራም፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቡ መገንባት የአካባቢውን ሕዝብ የሚያጠፋ እርምጃ ነው ተብሎ በአውሮፓውያን አንትሮፖሎጅስቶች ሲፈረጅና ለዕገዳ-ዘመቻ ኢላማነት ሲመቻች ማየታችንን እናስታውሳለን (BBC, The Dam that divides Ethiopians, 26 March 2009)፡፡ አስቀድሞ በራሳቸው በፕሮግራሙ አጋፋሪዎች ግድቡ ስለሚያስከትለው ጣጣ "በቂ ገለፃ" የተደረገላቸውን የአካባቢ ሽማግሌዎች አስተያዬት መነሻ በማድረግ፣ ማርኮ ባሲ የተባለው ኢጣሊያዊ የቡድኑ አባል፣ "ግድቡ ከተሰራ የአካባቢው ነዋሪዎች ምን ይበጃቸዋል?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ፣ ፍርጥም ብሎ የሰጠው ፍርድ አይሉት ትንቢት "ሁሉም ይሞታሉ" የሚል ነበር፡፡ በዚህ ሰው አመለካከት፤ የግልገል ግቤ ወንዝ ውሃ ፍሰት በግድቡ አማካይነት ከተገራና፣ በክረምት እጅግ እየሞላና በበጋ ደግሞ እጅግ እየቀነሰ የታች አገሩን ሕዝብ በመጥለቅለቅና በድርቅ ዋልታዎች መካከል ማዋተቱ ከቀረ፣ ይህንን አስቸጋሪ የተፈጥሮ ክስተት ለመቋቋም የአካቢው ሕዝብ በዘመናት ያሳደገውና ያቀየው ነባር-ልምድ አብሮት ሊለወጥ ነው፡፡ ስለዚህም፣ ግድቡ ሊያመጣለት የሚችለው ዋስትና ያለው የውሃ አቅርቦትና የኑሮ መሻሻል ቀርቶበት ነባር-ልምዱን እንዳለ አንቆ ቢኖር ይሻለዋል፡፡ በእንደዚህ ከኖረ ደግሞ፤ ለነዚሁ የውጭ-ሃገር "አጥኝዎች" እና በመሰናዶ ላይ ለሚገኙት ደቀመዝሙሮቻቸው እንዳለ ተቀምጦ ይጠብቃቸዋል፤ የጥቅም ምንጫቸው እንደሆነም ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ባሕል የልማት አካል ነው፡፡ አማርቲያ ሴን (2004፡ 39) ደህንነት የሚመሥርተው በነፍስ-ወከፍ አጠቃላይ አገራዊ ምርት ላይ ብቻ እንዳልሆነ ሲያመለክት፤ በተጨማሪም በባህላዊ ክንዋኔዎች የመሳተፍ ነፃነትና ዕድል፣ እንዲሁም የልማት አካል የሆነው የባሕሉ መበልፀግ ከመሰረታዊ መብቶች አንዱ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ የ 2004 ሂዩማን ዴቬሎኘመንት ሪፖርት (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. 2004) በበኩሉ ሁለት ዋነኛ

ጭብጦችን አስፍሯል፡፡ የመጀመሪያው ባሕላዊ መብቶች፡ ለሰው ልጅ መብቶች መሠረታዊ መሆናቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የባሕላዊ መብቶች መረጋገጥ ደግሞ ለባሕል ጉዳይ ተገቢውን ቁብ ለሚሰጡ የልማት አካሄዶች የመጀመሪያ ወሳኝ እርምጃ መሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ አሳሳቢ ጉዳይን እንድናነሳ የግድ ይላል፡፡ የተለያዩ ባሕሎች ባንድ ቦታና ጊዜ በሚገኙበት ሁኔታ "የባሕላዊ መብት መረጋገጥ" የሚለው ሃረግ ምን ፍች ይኖረዋል? በተለይም፣ አንዱ ንዑስ የኅብረተሰብ ክፍል በዋንኛው ኅብረተሰብ ባህል መከበር የተነሳ በቀጥታ ተጠቂ ሆኖ በሚገኝበት ሁኔታ የመብቶች ግጭት አይከሰትም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ፡፡ የዚህን ችግር ምንነት ቀጥለን በምሳሌ እናብራራ፡፡ የብሄር-ብሄረሰቦች መብት መረጋገጥ በሚነገርላት በዛሬዋ ኢትዮጵያ ብዙዎቹ -- እንዲያውም ከሞላ ጎደል ሁሉም -- የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች በውስጣቸው በሸክላ ሥራ፣ በቆዳ ማልፋት፣ ብረት ቅጥቀጣ፣ ወዘተ… የተሰማሩ የሙያተኛ ማኅበረሰቦችን እንደሚያቅፉ ይታወቃል፡፡ እነዚህም የሙያተኛ ማህበረሰቦች ይብዛም ይነስ በሁሉም ዘንድ የተናቁ የተገፉና የተጨቆኑ ናቸው፡፡ ታዲያ፡- የብሄር ብሄረሰቦቹ ባሕላዊ መብት መረጋገጥ በቀጥታ ትርጉሙ ከተወሰደ የነዚህ የሙያ ማኅበረሰቦች በቀጣይነት መናቅና መገፋትን በማስከተል አባሎቻቸው እንደ ሰው ያላቸውን መብት በመግፈፍ ሌላው ቀርቶ ለትምህርትና ለጤና አገልግሎት ያላቸውን የዕድል በር ይዘጋል፡፡

የባሕልና የልማትን ቁርኝት ስናስብ ሁለት የተለያዩ እይታዎች ሊኖሩን ይችላል፡፡ አንደኛው በጣም አጠቃላይ በሆነ መንገድ ባህልን ለማንኛውም የልማት ችግር ምክንያት እያደረግን በሰበብ ጨዋታ የምንዘፍቅበት እይታ ነው፡፡ ለምሳሌ "በሃገራችን ድህነት የነገሰው የሥራ ባሕል ስለሌለን ነው" የሚለው አይነት ልቅ አባባል ይህን እይታ ይወክላል[2]፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ዝርዝርና ተጨባጭ ከሆኑ የልማት ወይም የዕድገት ተግባራት ጋር ተያያዥ ለሆኑ የባሕል ገፅታዎች ተገቢውን ቁብ ሰጥተንና በበቂ አበክረን በመገንዘብ ተግባሮቻችን እንዲሰምሩ ለማድረግ የምንጣጣርበት አስተያየትና አካሄድ ነው፡፡ ለዚህኛው የኤች.አይ.ቪ. ኤድስን መስፋፋት ለመግታት አንዳንድ ባሕላዊ የፍትወት ግንኙነቶችን ለመገንዘብ የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ "ማኅበረሰባዊ ውይይቶች" ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ማኅበረሰባዊ ውይይቶች ካስገኟቸው ግኝቶች አንዱ ሰዎችን ወዳልተገደበ የፍትወት ግንኙነት ይጋብዙና ያበረታቱ የነበሩ የባህል ይዘቶችን (ኤለመትስ) ለይቶ በማውጣት፣ ግንዛቤ ማስጨበጥና፣ ከባሕል መሪዎች ጋር በመተባበር የባሕል ለውጥ ማምጣትን ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው፣የአንዳንድ የባህል ይዘቶች (ኤለመትስ) መለወጥ ወይም እንዳሉ መቀጠል የኅብረተሰቡ "የሞት-የሽረት" ጥያቄ ሆኖ

---

[2] ይህን ዓይነቱን አስተያዬት በተመለከተ ሜሪ ዳግላስ (2004) የሰጠችውን ትችት መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

ሲገኝ በፍጥነት መለወጣቸው የግድ መሆኑንና መለወጣቸውንም ነው:: እዚህ ላይ፤ ታሪክ የብዙ ራሳቸውን ለተፈላጊ ወሳኝ ለውጥ ሳያዘጋጁ በመቅረት ባሕላቸውን መለወጥ ያልፈለጉ ወይም የተሳናቸው ኅብረተሰቦች መቃብር መሆኑን ልናስምርበት ይገባል:: የባሕል እንዳለ መቀጠል አንፃራዊ መሆኑንና፤ የባሕል መለወጥ ፍፁማዊ መሆኑንም እንዲሁ::

በሕልና ልማት (ማለትም አዎንታዊ ኅብረተሰባዊ ለውጥ) ቁርኝት አላቸው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከመነሳታችን በፊት፤ ጥያቄውን ራሱን ለመረዳት እንሞክር:: ምን-ምንን ሊሸፍን እንደሚችልም እንመልከት:: በመጀመሪያ በሁለቱ፤ በባሕልና በልማት፤ መካከል ልዩነት አለ ወይ ብለን ስንጠይቅ፤ እነዚህ ሁለቱ በሰፋፊ ትርጉሞቻቸው እጅግ ተነባባሪ ፅንሰ-ሃሳቦች ከመሆናቸው የተነሳ ጥያቄውን እንዳለ ለመመለስ መሞከሩ የዙሪያ-ጥምጥም አመክንዮ ወስጥ የሚከተን ይመስለኛል:: እርግጥ ሁለቱንም አጥብበን በመመልከት ባሕልን እንደ ነባር-ልምድ (ትራዲሽን) ልማትን ደግሞ እንደ ማዘመን (ሞደርናይዜሽን) ከወሰድናቸው የተለያዩ ከመሆን አልፈው ተቃራኒም ሊሆኑ ይችላሉ::

በእኔ አስተያዬት፤ ባሕልና ልማት (አዎንታዊ ህብረተሰባዊ ለውጥ) ምክንያታዊ ቁርኝት አላቸው ወይ? የሚለው አጠቃላይ ጥያቄ በበቂ ይመለስ ዘንድ የሚያቅፋቸው ንዑስ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ተተንትነው መቅረብ ይኖርባቸዋል::

*የመጀመሪያው ዝርዝር ጥያቄ፤* ልማት ይመጣ ወይም ይገኝ ዘንድ የግድ አስፈላጊው የባሕል ለውጥ አስቀድሞ መምጣት አለበት ወይ? *ሁለተኛው፤* አስፈላጊው የባሕል ለውጥ ቀድሞ ከመጣስ፤ የግድ ልማት ይከተላል ወይ? የሚለው ሲሆን፤ *ሦስተኛው ጥያቄ፤* አንድ አዲስ የባሕል ኤለመንት ይመጣ ወይም ይገኝስ ዘንድ አስቀድሞ አስፈላጊ የሆነ ልማት መምጣት አለበት ወይ? *አራተኛው፤* አስፈላጊው ልማት ቀድሞ ከመጣስ፤ የግድ አዲስ የባሕል ኤለመንት ይከተላል ወይ? *የመጨረሻውና ዋነኛው ጥያቄ* የሚከተለው ነው:: አስቀድመን እንዳየነው እጅግ ሁላቀፉ የሆነውን ባሕል ለሁዋላ-ቀርነትም ሆነ ለልማት ምክንያት ነው ማለት ምን ትርጉም ይኖረዋል? ባይሆን ይህ እና ያ ነባር ልማድ ለዚህ ወይም ለዚያ ኋላቀርነት ምክንያት ሆኖ ይቀርብ እንደሆነ እንጅ እንዴት ሁሉን የሚያቅፍ ባሕል ልማትን ያመጣል ወይም ያግዳል ሊባል ይችላል? ልማትን በማገድ በኩል ባሕልን ተጠያቂ ማድረጉስ ሰበብ ከማላከክ፤ ተጠያቂነትንና ሃላፊነትን ከዘመኑ ትውልድ ትከሻ ወዳለፈው ከማሻገር፤ እናም ለምሁራዊ ስንፍና ሽፋን ከመስጠት ያለፈ ምን የሚፈይደው ይኖረዋል?

በሕልና ልማት ቁርኝት አላቸው ወይ? ብለን ስንጠይቅ፤ ምክንያታዊ ቁርኝት እንዳላቸው፤ ማለትም በአንዱ ላይ የመጣ ለውጥ በሌላው ላይ ትይዩ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ መጠየቃችን መሆን አለበት:: ይኽ ሳይሆን ቀርቶ፤ እንዲያው "በአንደኛው ዘንድ በጎ ለውጥ ይመጣ ዘንድ ሌላኛውም ቢታሰብበት ተገቢ ይሆናል" ዓይነት አስተያዬት የማቅረብ ነገር ከሆነ ግን፤ ይህ ተጨባጭ እውነታን የመግለፅ ጉዳይ ሳይሆን ምክር-አዘል አባባል (normatve statement) የመሰንዘር ነገር ብቻ በመሆኑ አከራካሪ አይሆንም:: በዛሬው ዘመን፤ ልማት በሚወጠንበት ጊዜ የአካባቢው ባሕላዊ ነገሮች ወይም ነባር-ልምዶች ታሳቢ


መሆን የለባቸውም የሚል ክርክር የሚነሳ አይመስለኝም፡፡

ወደ ዋናው የባሕልና ኅብረተሰባዊ-ለውጥ ትስስር ጥያቄ ስንመለስ፤ ኅብረተሰባዊ-ለውጥን አንቀሳቃሽ ኃይል አስመልክቶ የተነሳው ክርክር ለዋነኛዎቹ የህብረተሰብ ሳይንስ የቲዮሪ ጎራዎች መከሰት ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ እድሜ-ልካቸውን ምርምር ያካሄዱ ስመ-ጥር ምሁራን ያቀረቧቸውን ትንተናዎችና የሰጡዋቸውን ምላሾች ላንድአፍታ እንቃኝ፡፡

አንትሮፖሎጅስቶች ለጥናት የሚሰማሩባቸው ኅብረተሰቦች አነስተኛነት ባሕልን እንዳለ በውሕድነቱ ወስደው ያጠኑት ዘንድ ሲፈቅድላቸው፤ ባሁኑ ዘመን ተንሰራፍተው በሚገኙት ሰፋፊና ውስብስብ ኅብረተሰቦች ላይ የሚያተኩሩት ሶሲዮሎጅስቶች ደግሞ ለየት ያለ መንገድ ይከተሉ ዘንድ ሁኔታው የግድ ይላቸዋል፡፡ ለነገሩ፤ ይህ ለየት ያለ መንገድ ከራሱ ከአንትሮፖሎጅ ጭምር የመነጨ ነበር፡፡ በዩናይትድ-ስቴትስ ስር ከሰደደውና ባሕልን በራሱ በብቸኝነቱ ማጥናት ይቻላል ከሚሉት ካልቸራል-አንትሮፖሎጅስቶች ተለይተው የወጡት የፈረንሳይና የብሪታንያ ፋንክሽናሊስትና ስትራክቸራል-ፋንክሽናሊስት ርዕዮት የሚያራምዱ ሶሽያል-አንትሮፖሎጅስቶች ኅብረተሰባዊ መዋቅርና አደረጃጀት ላይ አተኮሩ፡፡ በሶሲዮሎጅም የዚህ መስመር መሥራች ታዋቂው ኤሚል ደርካይም ነበር፡፡

የሶሲዮሎጅ የዕውቀት ዘርፍ ሲፈጠር ጀምሮ ኢኮኖሚው ባንድ በኩል፤ እንደ ሃሳብ፤ ባሕልና፤ ነባር ልምድ ያሉ ሰብአዊ ክስተቶች በሌላ በኩል ሆነው በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ዘመናት ያስቆጠረ ክርክር በተለያዩ መልክና ስም እንደቀጠለ አለ፡፡ ሁሉም የክርክሩ ተሳታፊዎች አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መቀበላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንዱ ጎራ ለኢኮኖሚው ሌላው ጎራ ለሰብአዊ ክስተቶቹ የመጨረሻ ወሳኝነት ሚና ስለሚሰጡ ልዩነታቸው እንዳለ ዘልቋል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ጎራዎች በተጨማሪ የኅብረተሰብ አባላትን ባሕርይ መልክ ለሚያሲዙ ህብረተሰባዊ ሥርዓታት ሚና ከፍተኛ እውቅና የሚቸረው ሦስተኛ ጎራ ሆኖ በክርክሩ ውስጥ ትልቅ ቦታ ይዟል፡፡

*ሦስቱ የባሕል ክፍሎችና የቲዮሪ ጎራዎች*



እነዚህ ሦስት ጎራዎች ቀደም ብለን ካየናቸው ሦስት የባሕል ክፍልፋይ አካላት ላንዱ ወይም ለሌላው፤ ማለትም *ለቁስ-አካላዊ ነገሮች/ንብረት፤* ወይም *ለሃሳቦች፤ ህብረተሰባዊ ልማዶችና፤ አመለካከቶች፤* ወይም *መልክ-ለያዘ ባሕርይ* የወሳኝነት ሚና ይሰጣሉ ማለት ነው:: በተጨማሪ፤ ባጋጣሚ ሳይሆን፤ ያነሱዋቸው ጥያቄዎች መሰረታዊነትና የትንታኔአቸው ጥልቀት ባፈራላቸው ዘላቂ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታቸው የተነሳ የሶሲዮሎጅ የዕውቀት-ዘርፍ መስራች አባቶች ተብለው የሚወሰዱት *ካርል ማርክስ* (1818 - 1883)፤ *ማክስ ቬበር* (1864 - 1920)፤ እና *ኤሚል ደርካይም* (1858 - 1917) የእነዚህ ሦስት የቲዮሪ ጎራዎች መስራቾች ናቸው::

በወግ፤ ልምድ፤ ዕምነት፤ አመለካከት፤ ወዘተ... በአንድ በኩልና በኅብረተሰባዊ-ለውጥ መካከል መተሳሰር እንዳለ ማለትም አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር በጉዳዩ ላይ ንድፈ ሃሳብ ካቀረቡ ፀሐፊዎች እጅግ ብዙዎች የሚስማሙበት መደምደሚያ ነው:: ይሁንና ጠለቅ ብለው በመግባት ከሁለቱ የትኛው የኅብረተሰብን ዕድገት በማንቀሳቀስ በኩል የበላይነት እንዳለው በሚያወሱበት ጊዜ ተንታኞቹ በሁለት ይከፈላሉ:: አንዳንድቹ ወደ ኢኮኖሚው ሲያጋድሉ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ባሕል የበላይነት ያዘማሉ::

ከፊተኞቹ አይነት የኅብረተሰብ ተመራማሪዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ካርል ማርክስ ሲሆን፤ ከኋለኞቹ አዘውትሮ የሚጠቀሰው ደግሞ ማክስ ቬበር ነው:: ማርክስ፣ በኢኮኖሚና በላዕላይ-መዋቅር መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣ አንዱ በሌላው ላይ፣ በየተራቸው ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ ካስቀመጠ በኋላ "ዞሮ ዞሮ" ኢኮኖሚው በመሪነት ብቅ ይላል በማለት ለኢኮኖሚው ቅድሚያ ይሰጣል (ማርክስና ኤንግልስ 1962: 304)::

ቬበር በበኩሉ፤ ምንም እንኳን ቀደም ሲል የማርክስ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ያሳደረበት ቢሆንም[3]፤ የማርክስን ወደ ኢኮኖሚው ያዘመመ አስተያየት አቃናለሁ ብሎ በመነሳት ወደ ላዕላይ-መዋቅሩ እያደላ ሄደ:: በዚህ ጥረቱ ነው እንግዲህ የካፒታሊዝምን በአውሮፓ ምድር መነሳት ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት መመሥረትና ካስከተለው ህሊናዊና ሥነ-ምግባራዊ ለውጥ ጋር የሚያያይዘው:: ያም ሆኖ ታዲያ፤ የቬበር ሃተታ የሚመለከተው ባጠቃላይ የፕሮቴስታንትን ዕምነት ሳይሆን የዚህ ዕምነት አንድ አነስተኛ ክፋይ የሆነውን ካልቪኒዝምን፤ የፕሮቴስታንት ዕምነት የተሰበከበትን ምድር ሁላ ሳይሆን አውሮፓን ብቻ ነበር (ቬበር [1930] 1971)::

በተጨማሪ፤ ለቬበር የታየው የካልቪኒዝምና የብልፅግና ግንኙነት ቀጥተኛ ሳይሆን ዘወርዋራ ሆኖ ነበር:: ማለትም፤ ቬበር የካልቪኒዝም ዕምነት ወይም

---

3 ይህንን ተፅዕኖ ለማሳዬት፤ ራሱ ቬበር በፅሁፍ ያስቀመጠውን በእንግሊዝኛ ትርጉሙ እንዳለ ቀጥለን አስፍረነዋል:: "Not ideas, but material and ideal interests, directly govern men's conduct. Yet very frequently the 'world images' that have been created by 'ideas' have, like switchmen, determined the tracks along which action has been pushed by the dynamic of interests." (Weber 1946: 280)

የዚህ ዕምነት ተከታይነት በራሱ ታታሪ ያደርጋልና ያበለፅጋል የሚል ነገር አላሰፈረም:: ይህንን በተመለከተ የእሱ ስሌትና አባባል ባጭሩ እንደሚከተለው ነው:: የካልቪኒዝም ዋነኛ ቀኖና "የማንኛውም ሰው መፅደቅ ወይም መኮነን በራሱ በሰውየው ዕምነትና ምግባር የሚወሰን ሳይሆን አስቀድሞ በፈጣሪ የተወሰነ ነው" የሚለው የ"ቅድመ-ፍርጃ" (predestination) ሲሆን፤ የዚህ ተጨማሪ የሆነው ቀኖና ደግሞ "ማንም ሰው ለፅድቅ ከተመረጡት ጥቂቶች አንዱ መሆን አለመሆኑን ሊያውቅ አይቻለውም" ይላል:: በዚህም የተነሳ በካልቪን ተከታዮች ዘንድ ይህ ነው የማይባል ጭንቀት እንደነገሰና አማኞች ሁሉ በ"በምሕረት ጉዳይ በጭንቀትና መርበትበት" (salvation panic) እንደተዋጡ ቬበር ይጠቁምና፤ ሕዝቡን በከፊልም ቢሆን ለማረጋጋት ሲባል ደግሞ "አንድም መልካም ዛፍ መርዘኛ ፍሬ እንደማያፈራ ሁሉ፤ ሰዎችም ያለ እግዚአብሄር ቡራኬ በዚህ ዓለም ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ አይቻላቸውም" እና በዚህ ዓለም ስኬታማ ሆኖ መገኘት ለፅድቅ የመመረጥ ምልክት ሆኖ ሊወሰድ ይችላል የሚል ሃሳብ የእምነቱ ማለዘቢያ ሆኖ ቀረበና ተወሰደ:: በዚህ ዓይነትም የቅድመ-ፍርጃው አለመታወቅ ቀኖና የፈጠረው ጭንቀት ረገብ እንዲል ሆነ:: ጭንቀቱ ይበልጥ ይረግብ ዘንድ ደግሞ፤ "አማኞች ሥራን ጨምሮ በሚያደርጉት ሁሉ እግዚአብሄርን ማክበር እንደሚኖርባቸውና ከዚህ ዝንፍ ብሎ ወደ ስንፍና፤ ደካማነት፤ መንደላቀቅና፤ ኪሳራ መውደቅ የኩነኔ ፈጣን ምልክት ነው" የሚል ዕምነት ተጨመረበት:: ከዚያ ወዲያ እንግዲህ፤ እነዚህ በዚያን ዘመን በምዕራብ-አውሮፓ ይኖሩ በነበሩ የፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖታዊ ልባስ ያገኙት ያቆጣቢነት፤ ሥነ-ሥርዓት አክባሪነት፤ በልኩ መኖርና፤ ለስኬታማነት መጣጣር ፍላጎቶችና ባሕርዮች ተዳምረው ከካፒታሊስት መንፈስ ጋር አብሮ የሚሄድ የሥራ ሥነ-ምግባር ለማነፅ ረዱ (ዌብስተር 1984: 47-8)::

ከላይ ያቀረብነው ሀተታ እንደሚያሳየው፤ ቬበር ከፕሮቴስታንት ዕምነት የካፒታሊስት መንፈስ ካልመነጨ በስተቀር የኢኮኖሚ እምርታ አይደረግም፤ ወይም የካፒታሊስት ዕድገት ይመዘገብ ዘንድ የግድ የፕሮቴስታንት ዕምነት ያስፈልጋል ወደሚል መደምደሚያ አልደረሰም ነበር:: ነገር ግን፤ በአንዳንድ ተከታዮቹ አማካይነት፤ ቬበር በአውሮፓ የተካሄደውን የሥርዓት ሽግግር አስመልክቶ ያቀረበውን ትንታኔ በመላ ዓለም እንደሚሰራ ቲዮሪ ከፍ ለማድረግ የተያዘው ሙከራ፤ ሳይውል-ሳያድር ጃፓን ባስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሳቢያ ከጥያቄ ውስጥ ገባ:: ቬበራውያን ተከራካሪዎችም የመውጫ ቀዳዳ ፍለጋ፤ የጃፓንን አንዳንድ ለየት-ያሉ የባሕል ይዘቶችን -- በተለይም ሽንቶይዝምን -- እየጠቃቀሱ ቬበር አውሮፓን አስመልክቶ ያቀረበውን ንድፈ-ሃሳብ ዓለምአቀፋዊ ገፅታ በመስጠቱ ሂደት ገፉበት:: በዚያን ጊዜ ጃፓን እንዴት እንደነ ቻይናና ሕንድ ካሉት የእስያ ሃገሮች በባሕሏና በህዝቧ ሥነልቦና የተለየች እንደሆነች አስረግጠው መከራከራቸውን ቀጥለውበት ነበር:: ይኸው ዛሬ ደግሞ የቻይናንና የሌሎች ብዙ የእስያ ሀገሮችን በኢኮኖሚ ዕድገት መመንጠቅ በ"ሃሳባዊ-አመለካከት" ላይ የተመሰረተውን ንድፈ-ሃሳባቸውን በእጅጉ ስለተፈታተነባቸው ከዚህ ማጥ ለመውጣት በሚያደርጉት ሙከራ ሳቢያ "ልዩ

ስለሆነው የእስያውያን ካፒታሊስታዊ ባህል" በሰፊው እያወሩልን ነው። በዚህ ሂደት ከቀጠልን እንግዲህ፤ ለጊዜው የቀረውና ተራውን በመጠባበቅ ላይ የሚገኘው በዋነኛነት የአፍሪካ አህጉር ብቻ ስለሆነ፤ እሱንም የልማት አድባር የታረቀችው ቀን ያንን ልማት ያስከተለው የአፍሪካ ባሕል ነው የሚል አዋጅ ሳይነገር የሚቀር አይመስለኝም።

ኤሚል ደርካይም የተባለው፣ በቬበር የዕድሜ-ዘመን የኖረ፣ ታላቅ የኅብረተሰብ ተመራማሪ ወግ፤ ልምድ፤ ዕምነት፤ አመለካከትና፤ ወዘተ... በልማት ላይ ለሚያሳድሩት ተፅዕኖ እውቅና እየሰጠ እያለ፤ አመጣጣቸውን በተመለከተ ግን ከቬበር የተለየ ትንታኔ ያቀርባል። ደርካይም ኅብረተሰቦችን በሁለት ዓቢይ ክፍሎች ለይቶ ይመለከታል። በሱ አስተያየት፤ የሙያ ወይም የሥራ ክፍፍል ያልዳበረባቸው ቀደም ያሉት፤ አነስተኛ (simple)፤ እና ቅድመ-ኢንዱስትሪ ኅብረተሰቦች አባሎቻቸው በሚጋሯቸው ወይም በጋራ በተደመጡ ደንቦቻቸውና ወጎቻቸው ላይ የተመሠረተ አንድነት ሲኖራቸው፤ የሙያ የሥራ ክፍፍል ወደፊት የገፋባቸው፡ ሰፋፊና ውስብስብ የሆኑቱ የኢንዱስትሪ-ዘመን ህብረተሰቦች አንድነት ግን የተመሠረተው አንዱ የኅብረተሰብ አካል ለሌላው አካል በሚያበረክተው የአገልግሎት መደጋገፍና ከዚህ በሚመነጨው ጥብቅ ትስስር ላይ ነው፤ በመሆኑም ከበፊተኞቹ ሲወዳደር በኋለኛዎቹ ዓይነት ህብረተሰቦች ውስጥ የሰዎች የወል ደንቦችና የጋራ ህሊና (collective conscience) ጠንካራ ስላልሆኑ፤ የሰዎችን አመለካከትና ተግባር ይቆጣጠሩ ዘንድ የሕግ ሥርዓቶች ዋነኛ እየሆኑ ይመጣሉ (ደርካይም [1893] 1984)።

አገራችን ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ዕድገት ወደፊት ከገፉት ከአውሮፓ አገሮች ጋር ግንኙነት ከፈጠረችበት ጊዜ አንስቶ፤ የኋላቀርነቷን ምክንያቶች ለይቶ ለማወቅና ለማሳወቅ የውጭና እያደርም ሃገሬው ምሁራን የየበኩላቸውን ሞክረዋል። በተለይም የምዕራቡ ሥልጣኔ የኢንዱስትሪ አብዮቱን በማካሄድ የተፋጠነ የኢኮኖሚና የሶሺያል እርምጃዎችን ማስመዝገብ ከጀመረበትና በምዕራቡ ዓለምና በሃገራችን መካከል ያለው የዕድገት ልዩነት እጅግ እየሰፋ መሄድ ከጀመረበት ከ18ኛው ምዕተ-ዓመት ወዲህ ወደ ሃገራችን በብዛት ብቅ ማለት የጀመሩት አውሮፓውያን ሚሲዮናውያንና አገር ጎብኝዎች ይኸን ጉዳይ በተመለከተ የየበኩላቸውን ብለዋል። ይሁንና የአብዛኛዎቹ አመለካከት በአንድ አቅጣጫ ያነጣጠረ ነበር። ይህም የአገሪቱን ኋላቀርነት በአገሬው ዕምነት፣ ወግና ልምድ ላይ የሚላክክ ነበር።

በ19ኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ አካባቢ እንደ ፕሮቴስታንት ያለ የክርስትና ዕምነት "ተሃድሶ" እንዲያመጡ በእንግሊዙ ቼርች ሚሺነሪ ሶሳይቲ (Church Missionary Society) ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ጎባት፣ አይዘንበርግና፣ ክራፕፍ፤ ፈጣሪ ትክክለኛ ሃይማኖት ወይም ዕምነት የያዘን ህዝብ በሃብትና ብልፅግና እንደሚሸልም፣ የእንግሊዝን የኢንዱስትሪና የግዛት የበላይነትን በማስረጃነት በማቅረብ ይከራከሩ ነበር። የኢትዮጵያንም ኋላቀርነት ከተዋህዶ ክርስትና ዕምነቷ የመነጨ እንደሆነና፣ የዕምነት መሻሻል ብታደርግ ግን ወደ ብልፅግና

ጎዳና እንደምታመራ ደጋግመው ያሰምሩበት ነበር። የክርክራቸውንም አቅጣጫ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ይልቅ ወደ ባሕላዊ ጉዳዮች ማዞርን ዋና ስልት አድርገውት ነበር (ቻፕል 1986: 26-37)።

በዚህ ስልት በመጠቀም፣ ክራኘፍ የተባለው ሦስተኛው ሚሲዮናዊ "ምዕንተ ማርያም" ብለው ማደሪያ ለሚሹ መንገደኞች መጠጊያ የመስጠት ባሕልን፣ የሆቴል ኢንዱስትሪ እንዳይስፋፋ ያደረገ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕክል ነው በማለት እስከመተቸት ደርሶ ይህን ትችቱን በማስታወሻው ላይ ያሰፍራል። ታዲያ ሰው የእጁን አያጣም እንደሚባለው፣ ሰውዬው የኢትዮጵያ ቆይታውን ጨርሶ ወደ ምፅዋ ወደብ በሚጓዝበት ወቅት አደጋ ይደርስበታል። አደራ ቢሌ በሚባል ባላባት ወሎ ላይ ይዘረፍና ያን የጠላውን "ምዕንት ማርያም፣ አሳድሩኝ" እያነበነበና ለኢትዮጵያ ባሕል ያለውን ንቀትና የማስታወሻ ደብተሩን እንደጨበጠ ምፅዋ ገባ (ቻፕል 1986: 32-4)።

ከላይ የተወሳው አስተያየት በተለያየ መልኩ እስከ ዛሬው ጊዜ ቢዘልቅም፤ ከዚህ የተለየ አስተያየታቸውን የቸሩ ኢትዮጵያዊ ምሁራን አልጠፉም -- በተለይ ቆየት ባለው ጊዜ። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን በጽሑፍ ያቆዩን፡ በሃያኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ የአውሮፓንና የጃፓንን ሥልጣኔ በቦታው ተገኝተው የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከሚሲዮናውያኑ የተለየ አቋም ነበራቸው። በእነሱ አስተያየት የኋላቀርነታችን ዋነኛ ውስጣዊ ምክንያቶች መዋቅራዊ (structural) ናቸው። ከነዚህ ምሁራን መካከል በጉዳዩ ላይ ዝርዝር ሃተታ በሰጡት በነጋድረስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አስተያየት ላይ ለአፍታ እናተኩር።

በነጋድረስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አስተያየት የኢትዮጵያን ዕደገት ቀፍድደው የያዙት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። አምራችነት የማይጋብዘው ያልተረጋገጠ የመሬት ባለቤትነት መብት፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የብዙሃኑ ባለህብት አለመሆን፣ የህግ የበላይነት አለመረጋገጥ፣ የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ እንዳይሄድ የሚያደርጉት የሕዝብ ቁጥር ማነስ፣ የመገናኛ መስመሮች አለመኖር፣ የመገበያያ ገንዘብና በተለይም የአነስተኛ ምንዛሪ (ሽርፍራፊ) እጦት፣ ወዘተ ናቸው። ነጋድራስ ያተኮሩባቸው የኋላቀርነት ውስጣዊ ምክንያቶች እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ እንጅ ባዕላትን ማክበር ወይም እጀ-ጠቢባንን ዝቅ አድርጎ ማየትን የመሳሰሉትን ወጎችና ልማዶች አይደሉም። እዚህ ላይ ውስጣዊ ምክንያቶችን አልን እንጂ የውጭ ምክንያቶችን በተመለከተ ነጋድረስ ገብረ ሕይወት የሚያሰምሩባቸው ሌሎችም ጉዳዮች ነበሩ። ከነዚህም አንዱ አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ዕቃዎች በሙሉ እንደ ቆዳና ቡና የመሳሰሉ ጥሬ ሸቀጦች መሆናቸውና እሳቸው እንደሚሉት በዚህም የህዝቧን የሥራ ወይም የላብ ፍሬ ሳይሆን የመሬቷን ፍግ ሌላ ህዝብ ጉልበቱን ላፈሰሰበት ምርት የምትለውጥ ሃገር ሆና መቀጠሏ ነው (ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ [1924] 2002 ዓም)።

በአጠቃላይ ከኢጣሊያ ወረራ ማግስት የተፈጠረው የኢትዮጵያ ምሁር፣ የዕድገት ማነቆዎችን በተመለከተ ከነጋድረስ ገብረሕይወትና ከመሰሎቻቸው የተለየና በመሠረቱ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ የነበሩ ሚሲዮናውያን ይሰብኩት ከነበረው ጋር የሚቀራረብ አቋም ያንፀባርቀ ይመስለኛል።

በ19 መቶ ሃምሳዎቹና ስልሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የጊዜው ተራማጅ ግጥሞች፣ ልብ-ወለዶች፣ ቲያትሮችና፣ መጣጥፎች ያስተጋቧቸው ከነበሩት አስተያቶች አንዱ፣ ለአገራችን የኢኮኖሚ ኋላቀርነትና ላለመልማቷ ዋነኛ ህብረተሰባዊ ምክንያት ሆኖ የኖረው እጅ-ጠቢባንን የሚያጣጥለው፣ የውትድርናና የጦረኛ ሙያን ከፍ-ከፍ የሚያደርገው፣ የሰዎችን የወደፊት ዕድል ፍፁም ከነሱ ቁጥጥር ውጭ አድርጎ የሚያቀርበውና፣ ሌሎችንም መሰል ነባር-አመለካከቶች የሚያቅፈው ኋላቀር ባህላችን ነው፣ የሚለው ነበር። በርካታ የዘመኑ ግጥሞች፣ አጫጫር ልብወለዶች፣ ቲያትሮችና፣ ምሁራዊ መጣጥፎች ይኽንኑ ያንፀባርቁ ነበር (ለምሳሌ ያህል፣ መስፍን ወልደማርያም፣ 1966 ይመልከቱ)። ይህ ዘመን ሚሲዮናውያንና ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ ዝቅተኛና ከፍተኛ ትምህርት ላይ የበላይነት ያገኙበትን ድሕረ-የኢጣልያ ወረራ ወቅት ተከትሎ የመጣ እንደመሆኑ፣ ሁኔታው እጅግም አያስገርምም ይሆናል። በዚህም ሂደት ውስጥ የውጭ ሃገር ተመራማሪዎች የሥራ ውጤቶች፣ በተለይም የዶናልድ ሌቪን «ዋክስ ኤንድ ጎልድ» ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።[4]

እ.ኤ.አ. ከስልሳዎቹ አጋማሽ ጀምሮ አብዛኛው ወጣትና ምሁር በአጠቃላይ በአብዮታዊ ርዕዮተ-ዓለም፣ በተለይም በማርክሲስት ፍልስፍና ስር እየዋለ መጣ። በመሆኑም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኋላቀርነታችንን ለማስረዳት በተፈለገ ቁጥር የተለያዩ ሥርዓታዊ ምክንያቶችን መደርደር የተለመደ ሆነ።

እነሆ ደግሞ፣ ባለፉት ሦስት ዓሰርተ-ዓመታት የተከሰተው የካፒታሊስት ኢኮኖሚና የምዕራቡ ሊበራል ዴሞክራቲክ ርዕዮተ-ዓለም የበላይነት መያዝ፣ እንደ ፍራንሲስ ፉኩያማ ያሉ ምሁራንን አፍ ሞልተው "ከንግዲህ ታሪክ አብቅቶለታል" ብለው እስከማወጅ ያደረሰ የተጋነነ የአመለካከት ዝንባሌ አስከትሏል (ፉኩያማ 1992)። በሌሎች ጥያቄዎች ላይ እንደደረሰው የአመለካከት ለውጥ ሁሉ፣ የዕድገትን ዋነኛ ማነቆዎች በሚመለከትም መሰል የተጋነነ የዕይታ መቀልበስ በመምጣት ላይ ያለ ይመስላል። የአመለካከት ለውጡ የውቀት መሰረት ያለውና የተሻሻለ ግንዛቤን የሚያስጨብጥ ከሆነ ማለፊያ ነው። ወደ ቀድሞው የተጋነነ "ባህላዊ ትንታኔ" (cultural explanation/paradigm) ከተመለሰ ግን ከ "ሰበብ-ጨዋታ" ባለፈ ምን እንደሚፈይድ አላውቅም።

በርካታ ምሁራንና ተከታዮቻቸው ለሃገራችን ኋላቀርነት ሲወርድ-ሲዋረድ የመጣውን የጦረኛና ያለመተማመን ጠባይ እንዲሁም ሥራን የመናቅ ባሕላችን

[4] ይኽ *ዋክስ ኤንድ ጎልድ* የተባለው የዶናልድ ሌቪን መፅሃፍ ያሳደረውን ጫና በተመለከተ ለተሰጠ ሃተታ የራስወርቅ አድማሴ 2006ን ይመልከቱ።

ነው የሚሉትን ዋነኛ ምክንያት በማድረግ ያቀርባሉ። ነገር ግን፤ ባሕል ወይም ነባር-ልምድ፣ ኅብረተሰባዊ ደንቦች፣ ወጎች፣ ልምዶችና፣ ልማዳዊ ሕጎች ለኢትዮጵያ ኋላቀርነት አበርክተዋል የሚባለውን አሉታዊ አስተዋፅዖ በሚመለከት በርግጠኝነት አንድ ነገር ማለት የሚቻል ይመስለኛል። ባሕል ከብዙዎች የኋላቀርነት ምክንያቶች መካከል ግፋ-ቢል አንዱ ብቻ ይሆን እንደሆነ እንጅ ከዚያ አይዘልም። ሌሎች እንደ መልክዓ-ምድራዊ/አካባቢዊ፤ ሥርአታዊ፤ ኢኮኖሚያዊና፤ ፖለቲካዊ ምክንያቶች ከባሕል ያልተናነሰ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ለምሳሌ ያህል፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ለሰው ህይወትና ለንብረት ይዞታ አስተማማኝነት በማስገኘት ለልማትና ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሆነው የተረጋጋ ሥርዓት ለረዥም ጊዜ ያልነበረ መሆኑ ትልቁ ማነቆ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። ይህን ኅብረተሰባዊ ትርምስ ያመጡት ደግሞ ሦስት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ክስተቶች ነበሩ። እነሱም የዘውድ ውርስን በሰላማዊ መንገድ ማካሄድ የተሳነው የፖለቲካው ሥርዓት፤ ቋሚ የንብረት ይዞታን የሚፃረረው የጉልት ሹመት-ንብረት ሥርዓት፤ እና የአራሹን መሬት ይዞታ በዘር-ሃረግ ከሚወረስ የወል የገባርነት ዕዳና አርሶ የመገልገል መብት ጋር አቆራኝቶ የኖረው የርስት ሥርዓት ነበሩ።

በአውሮፓና በእስያ ዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገት ይገኝ ዘንድ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው ጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት እንደነበረ ይታወቃል። በተቀራኒው፤ በኢትየጵያችን የዚህ ሥርዓት በቀጣይነት አለመገኘት ደግሞ፤ ዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገትን ሊያመጣ ይችል በነበረው ቋሚ አቅድ ባለው፣ና ሰላማዊ በሆነ የሥልጣንና የንብረት ሽግግር ሥርዓት ፋንታ ኅብረተሰባችን የሥልጣንና የንብረትን ውርስ ከሞላ-ጎደል ከሻሞ ባልተናነሰ ኅብረተሰባዊ ትርምስና ሁከት አማካይነት በማስተናገድ ኪሳራ ሲያስተናግድና ሲማቅቅ ኖሯል። ይኸ በጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት መታጣት በዘላቂ ኅብረተሰባዊ እድገት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ጫና ምን ያህል ወሳኝ መሆኑን የሚያሳየን አንድ ተያያዥ ጭብጥ አለ። ከሳሃራ-በታች ባሉት ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ሁሉ ይኸ በጥብቅ የብኩርና ፕሪንስፕል ላይ የተመሰረተ የውርስ ሥርዓት አለመኖሩንና ይህም ሁኔታ የየአገሮቹን እድገት ገትተው ካኖሩት ዋነኛ ማዕቀቦች መካከል አንዱ መሆኑን በአፅንዖት የሚያመልክቱ ምሁራን አሉ (ሪደር 1998)።

ሁለተኛው፣ ባሕል ወይም ልምዶች ራሳቸው ከሌሎች የሥርዓቱ ይዘቶች እንደመነጩ መታወቅ አለበት። በዚህ ዓይነት በሰሜን ኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን (ማለትም ዘመናዊ አስተዳደር መዘርጋት እስከተጀመረበት እስከ ምኒልክ የግዛት ዘመን ድረስ) ተንሰራፍቶ ይገኝ የነበረውን "የዝርፊያ ባህል" ምንጭ ከስርዓቱ መዋቅር ውስጥ መሻት ይቻላል። "የዝርፊያ ባህል" የምንለው ህብረተሰባዊ ደንብ ሆኖ በአንድ አጋጣሚ በጉልበቱ አሸናፊ ሆኖ የወጣው ወገን የተሸናፊውን ሕይወት፣ ነፃነትና ንብረት ("ሰዎቹን" ጨምሮ) እንዲነጥቅና ጊዜ በተራው እስኪጥለው ድረስ የሁሉ ባለቤት እንዲሆን የሚፈቅድ ባሕል ከላይ ካነሳናቸው መረጋጋትን ከሚያፋልሱ ሦስት ክስተቶች የመነጨ ነበር።

ባሕል በኢትዮጵያ ኋላቀርነት ውስጥ የተጫወተውንና አሁንም በመጫወት ላይ ያለውን ሚና በተመለከተ ውይይቱ ይቀጥል ይሆናል፡፡ መቀጠልም አለበት፡፡ ይሁንና በቀድሞው ሁኔታ ላይ ከማተኮር ይልቅ አሁን ያለውን ሁኔታ በመገንዘብና ለኢኮኖሚ እድገት፤ ለብልጽግናና፤ ለኅብረተሰባዊ ልማት ጠቃሚ የሆነ የባሕል ለውጥ ለማስገኘት ማድረግ በሚቻለውና መወሰድም ባለባቸው እርምጃዎች ላይ ማተኮሩ ይበልጥ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ቀድም ሲል ያነሳናቸው የኅብረተሰብ ተመራማሪዎች ሁሉም፡ በአጠቃላይ በባህልና በልማት መካከል መደጋገፍ መኖሩን እንደሚቀበሉ አንስተን ነበር፡፡ እኛም ከዚህ በመነሳት፤ የግድ አቻ የሆነ የባሕል ለውጥ በራሱ እስኪመጣ ከመጠበቅ ይልቅ ሰዎች አወንታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ለውጡ ከባህል በኩል ጭምር እንዲመጣና የልማቱን ሂደት እንዲያፋጥነው ማድረግ እንደሚገባ ልናሰምርበት እንወዳለን፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ እንደ ትምህርት ቤቶችና የመገናኛ ብዙሃን ባሉ መድረኮች አማካኝነት ከሚከሰተው አዝጋሚ የባህል ለውጥ በተጨማሪ፣ ፈጣን የሆነ የባሕል ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል ኅብረተሰባዊ መሣሪያ በኅብረተሰቡ፤ በተለይም በመንግሥታዊ አውታሮች እጅ ይገኛል፡፡ ፋላጎቱና ቆራጥነቱ ካለ፣ ያለንበት ሁኔታና ጊዜ የሚጠይቋቸውን ሕጎችንና ደንቦችን በስፋት በመደንገግ፣ በማሻሻል፣ በማሳወቅ፣ ሥራ ላይ በማዋልና፤ በማስከበር፤ በአጭሩ የሕግ መዋቅሮችን በማዳበር ለልማትድጋፍ ሰጭ የሆኑ ባሕሎችን መፍጠርና መንከባከብ፤ ጎጅ ወይም ጎታች የሆኑትን ደግሞ መግታትና በሂደት ማጥፋት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ካሉት እጅግ ኋላቀር ከሆኑ ሃገሮች አንዷ ብትሆንም፤ ከጠቅላላው አለማቀፋዊ ለውጥና ዕድገት ጋር በተያያዘ፤ ህብረተሰቧ ሰፊ፤ ዘመናዊና፤ ትስስሩ ወደ በዛ (large-scale modern and complex) ኅብረተሰብነት ተሸጋግሯል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአንድ ገበያ፤ በአንድ የሶሽያል መድረክ፤ ወይም የፓለቲካ ሥርዓት ጎን ለጎን የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ የመልክዓ-ምድርና የባሕል አካባቢዎችና ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመጡ ናቸው፡፡ ቀደም ብለን የጠቀስነው ሶሽዮሎጂስቱ ኤሚል ደርካይም እንደሚያስገነዝበን ደግሞ፤ በዚህ አይነቱ ሁኔታ የሰዎችን አመለካከት፣ ባሕርይና፣ ተግባር በዋነኛ ነት የሚቀርፁና የሚመሩ፣ በጋራ የተደመጡ ደንቦችና ወጎች (shared values and norms) ወይም የጋራ ህሊና (collective consciousness) ሳይሆኑ፤ የሕግ ሥርዓቶችና መዋቅሮች ናቸው፡፡ በእንደዚህ፤ የሕግ ሥርዓቶቻችንና መዋቅሮቻችን ባሕላችንን ጊዜው በሚጠይቀውና በሚፈቅደው አቅጣጫና ፍጥነት በመለወጡና በመገንባቱ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ በእጃችን ያሉ መሳሪያዎች ሆነዋል፡፡ በነዚህ በተገቢው መገልገሉና ክፍት የሆነ ዕድልን አለማሳለፉ የኛ ፋንታ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ወደ ተያያዘ ቁም ነገር የሚያመራንን አንድ ገጠመኜን ላንሳ፡፡ የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ በሃገራችን አድጎ የአማርኛ ቋንቋን አቀላጥፎ የሚናገረው

የኖርዌዩ ዜጋ ዶ/ር ዩሃን ሄላንድ ስለ ኢትዮጵያ የዕድገት ማነቆዎች በምንወያይበት ወቅት አንድ ትዝብቱን አነሳብኝ፡፡ "በአማርኛ ቋንቋ ሜንቴናንስ (maintenance) ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ እንደሌለውና፣ ጥገና ወይም እድሳት የሚሉት ቃላት አንድ እንደ ሕንፃ፣ አውራ-ጎዳና፣ ወይም ተሽከርካሪ ያለ ቁሳዊ ነገር ወይም ንብረት እስኪበላሽ ድረስ ቆይቶ ከዚያ በኋላ የሚደረግ ማስተካከልን ማለትም ጥገና ማድረግን እንጅ እየተገለገሉ በዚያውም እንደ ነበር ጠብቆ ማቆዩትን እንደማያመለክቱ ታውቃለህ ወይ? ደግሞም የቃሉ አለመኖር እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ሁሌ የሚደረገው አንድ ነገር ተበላሽቶ ወይም አልቆ እስከሚያበቃለት ቆይቶ ከዚያ ወደ እድሳት መግባት እንደሆነ ልብ ብለሃል ወይ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ይህ ውይይታችን በነገሩ ላይ እንዳስብበትና ከሥራ ባልደረቦቼም ጋር እንድወያይበት አደረገኝ፡፡ ጉዳዩ ሜንቴን ማድረግ፣ ወይም "በጥቅም ላይ እያዋሉ እንደ ነበር ጠብቆ ማቆዩት"፣ ወይም ባጭሩ "ማንበር"፤ የሚል ገላጭ ቃል አለመኖርን ብቻ ሳይሆን፤ የተገላጨን ደንብ ወይም ስርዓትን አለመኖር የሚያመለክት ነው፡፡ በሃገራችን "ነገሮችን እየተጠቀሙ የማንበር" አሰራር ወይም አካሄድ አለመኖርን በተመለከተ በየአመቱ ለከፍተኛ ኪሳራ የሚዳርገንና፤ ካወቅንበት ደግሞ በቀላሉ ልንሸፍነው የምንችል፤ የአሰራርና የሥርአት ክፍተት አለ ማለት ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ሌሎችም ልንጨነቅባቸው የሚገቡና ልንደፍናቸው የምንችል ለልማታችን ማነቆ የሆኑብን የሥርዓት ክፍተቶች ሞልተዋል፡፡

እዚህ ላይ ደግሞ፤ እንዴት እነዚህ ዓይነቶችን የልማት እንቅፋቶች ለማስወግድ እንደሚቻል ሁለት የቅርብ ጊዜ ተሞክሮዎች ለምሳሌ ያህል ብቻ ልጥቀስ፡፡ ሁለቱም ምሳሌዎች ትራፊክን የሚመለከቱ በመሆናቸው የተነሳ፤ በሁለቱም በኩል የነበረው የትራፊክ ሥርዓት ጉድለትና ከሱም የሚመነጨው የባሕል ክፍተት በነኛ በፈረደባቸው አባቶቻችን ሊሳበብ አይችልምና፤ ምሳሌዎቹ ጠቃሚ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ከባሕር-ዳር እስከ ደብረ-ማርቆስ አዲስ በተሰራው አስፋልት አውራ ጎዳና ዙሪያ የሚኖረውን ሕዝብ ይመለከታል፡፡ ከመንገዱ ሥራ ጋር ተያይዞ እግረኞች ግራቸውን ይዘው እንዲጓዙ፤ ተማሪዎችም ከጎዳናው ውስጥ ገብተው እንዳይቆሙ፤ ኳስም እንዳይጫወቱ የሚደነግግ ደንብ ወጥቶና በሰሌዳ ላይ ተፅፎ በየአምስት ኪሎሜትር ያህል ርቀት ተሰቀለ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ ይህን ደንብ ተከትሎ አዲሱን የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓትና ባሕል በሚገባ ከመላበሱ የተነሳ የግል ጠባዩ አካል አድርጎት ሲያበቃ፤ የጎዳናውን ቀኝ ይዘን ስንደናበር ለተገኘን ከተሜዎች ምክር ለጋሽ ሆኗል፡፡

ቀጥሎ ደግሞ ወደ ዝርዝር ሳልገባ አንባቢ ጠንቅቆ የሚያውቀውንና አስቀድሞ የተረዳውን ሁለተኛ የትራፊክ ጉድለትና አቀራረፉን ላንሳ፡፡ የመኪና ቀበቶ ባለመጠቀም፤ በተንቀሳቃሽ ስልክ እየተነጋገሩ መኪና በማሽከርከርና፤ በትራፊክ መብራቶች አካባቢ በሚካሄድ ልመናና-ምፅዋት ሳቢያ ምን ያህል አላስፈላጊ አደጋዎች እንደደረሱና ከፍተኛ የሕይወት፤ የአካልና፤ የንብረት ኪሳራ እንደደረሰብን ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ ይኸው ታዲያ፤ በአንድ-አፍታ ተደንግጎና ታውቆ በሥራ ላይ በዋለ ደንብ/ሥርዓት አማካይነት ያንመሳይ ማነቆ

ሊወገድ ቻለ። አሽከርካሪዎችም በአጭር ጊዜ አዲሱን ሥርዓት ተላብሰው ከውጭ እንደተጣለባቸው ሸክም ሳይሆን እንደ ጠቃሚ ባሕላቸውና የራሳቸው እንደሆነ ግላዊ ባሕርይ ያከብሩት ዘንድ እንደሚመራቸው ተግባር ያዩት ይዘዋል።

*ኤሚል ደርካይም* ሰፋፊና ውስብስብ በሆኑት የዘመኑ ኅብረተሰቦች ውስጥ ሕግና የሕግ ሥርአቶች የሰዎችን ባሕርይ መልክ በማስያዝ በኩል ልማድን እና ልማዳዊ ሕግን እንደተኩ በማሳየት ለህብረተሰባዊ ለውጥ/ልማት የሚያደርጉትን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አመልክቷል (ደርካይም [1893] 1984)። እኔም የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ከዚህ ቀደም በተለያዩ መድረኮችና መጣጥፎች እንደገለፅኩት ሁሉ አሁንም ሕግና የሕግ ሥርአትን እድገት መሠረት የደረገ የህብረሰባዊ ሥርአታት መገንባትና መጠናከር የሚያስከትለው የባሕሪይ መልክ ማስያዝ ለሃገራችን ልማት ብቻ ሳይሆን ለባሕላችንም እድገት ወሳኝ ነው በማለት የኤሚል ደርካይምን መሠረታዊ አስተሳሰብ እጋራለሁ። በዛሬው ዘመን፤ የአካባቢ ንዑስ-ባሕሎችም ቢሆኑ በዝመና ስም ከተለያዩ ኃይሎች የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ በተሳካ መንገድ ሊከላከሉ የሚችሉት የሕግ ከለላ ሲያገኙ ብቻ ይመስለኛል።

ይኽ ፅሁፍ እስከዚህ ነጥብ ድረስ በዋነኛነት ያተኮረው ባሕላችን በአገራችን ኋላቀርነት ውስጥ የተጫወተውንና አሁንም በመጫወት ላይ ያለውን አሉታዊ ሚና በመዳሰሱ ላይ ነበር። እስኪ አሁን ደግሞ የቁስአካላዊና የረቂቅ (ታንጀብልና ኢንታንጀብል) ባሕላችን ውጤቶችና አካላት የሆኑት ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ለኢኮኖሚና ህብረተሰባዊ ልማት የሚያደርጉትን ቀጥተኛ አሉታዊ አስተዋፅዖዎች እንመልከት። አንደኛ፣ የባሕል አካል የሆኑት እንደ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ሥነ-ፅሁፍ፣ ሥነ-ቃል፣ ወዘተ... የመሳሰሉት ቅርሶች የሕዝቦች የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ የዕውቀት ማፍለቂያ፣ ማከማቻና፣ ማስተላለፊያ በመሆን ለልማት ቀጥተኛ አገልግሎት ይቸራሉ። የነሱም የመፍለቂያ መንበሮችና ጠባቂዎች ሆነው ያቆዩዋቸው ኅብረተሰብአዊ ሥርዓቶችና ተቋሞችም ለፈፀሟቸው ታሪካዊ ተግባሮች እውቅና ሊሰጣቸውና በአሁኑም ጊዜ ቀጣይነት ያለው ልማት በማስገኘት በኩል የሚጫወቱትን አሉታዊ ሚና መገንዘብ፣ ቁብ መስጠትና፣ ማዳበር ያስፈልጋል።

ሁለተኛ፣ የባሕል ክፋይ የሆኑት ቁስአካላዊ ባሕልና ነባር-ልምዶች የአገራችን ኢኮኖሚ በዋነኛነት የቆመባቸውን እርሻ፣ ከብት እርባታ፣ ባልትና፤ ሽመናንና የቆዳ መፋቅን ጨምሮ ሌሎች ዕደ-ጥበባት፣ የተለያዩ የቤት አሰራርንና ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይመለከታሉ። እነዚህ የኋለኞቹ ደግሞ የሃገራችን መለያ የሆኑትን እንደ ጤፍ፣ ዳጉሳና፣ የሃገር አልባሳትንና ነባር የምግብ ማዘጋጃና መመገቢያ ቁሳቁሶችን ወዘተ... ስለሚያቅፉ ባሕል በቀን-ተቀን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴአችን ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና ልንስተው አንችልም።

ሦስተኛ፣ ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ዋነኛዎቹ የቱሪስት መስህቦቻችን በመሆን እያደገ ለሚሄደው የአገራችን የቱሪስት ኢንዱስትሪና ለሚያስገኘው ገቢ፣ ለሚፈጥራቸው የሥራ ዕድሎችና፣ ሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞች መሠረት

ናቸው። ውቅርና በተለያዬ መንገድ ድንቅ የሆኑ አብያተክርስቲያኖች፣ ጥንታዊ ከተሞች፣ ነባር የእምነት ሥርዓትና በዓላት፣ እንዲሁም ነባር-አልባሳት፣ ምግቦች፣ ጌጣ-ጌጦች፣ ዜማዎች፣ ጭፈራዎች፣ ወጎችና፣ የመሳሰሉት ባይኖሩ ኖሮ ምን ያህሉ ቱሪስት በአገራችን የተፈጥሮ ውበት ብቻ ተስቦ ይመጣ እንደነበር መገመት ይቻላል።

አራተኛ፣ እነዚህ ቅርሶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን ዋጋ በማውጣትና ቀጥተኛ የኢኮኖሚ ጥቅማ-ጥቅም በማስገኘት የአገር ልማትን የሚደግፉት በዚሁ በአገራችን መልክዓ-ምድር ተወስነው ብቻ ሳይሆን ድንበርና ወሰን በመሻገርም ጭምር ነው። ታታሪነቱ በሰፊው የሚነገርለት በመላው ዓለም ተንሰራፍቶ የሚኖረው የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አንድም ያልሰለጠነበት ሙያና ያልገባበት የሥራ መስክ መኖሩ አጠራጣሪ ቢሆንም፣ የንግድ እንቅስቀሴውን የተመለከትን እንደሆነ አንድ አይነተኛ ጠባይ እንዳለው እንረዳለን። አብዛኛው የዲያስፖራው ነጋዴ ለሥራው መነሻ የሚያደርገውና ስኬታማ ሆኖ የሚቀጥለው በ"ባሕል ምግብ"፣ "ባሕላዊ ሙዚቃና ጨዋታ"፣ "ያገር ልብስ" እና ሹሩባ ስራ ሳይቀር ሌሎች ሌሎችን ቁስአካላዊ የባሕል ፍሬዎችንና እንደ እቁብና የቤተሰብ መረዳጃ ማሕበር ያሉ ከነባር-ልምዶቻችን የተገኙ ባሕላዊ ካፒታሎችን በመጠቀም ነው። ከጎረቤት አገሮች በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በኬንያና በደቡብ አፍሪካ፤ ከባሕር-ማዶ አገሮች ደግሞ በተለይ በዩናይትድ ስቴትስ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓና፣ በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ የዲያስፖራው አባላት የሚያካሄዱት የንግድ-ሥራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ የባሕል ትሩፋቶች ጋር እጅግ የተሳሰረ ከመሆኑ የተነሳ በንግድ-ስራቸው ኦፊሲያል አገልግሎትና በተጨማሪ በሚያከናውኑት ኦፊሲያል-ያልሆነ የባሕል አምባሳደርነት ተግባር መካከል ያለው ድንበር ደብዛዛ ነው። በሁለቱ ተግባራት መካከል ግጭት ሳይሆን መደጋገፍ ነው የሚታዬው።

በአምስተኛነትና በመጨረሻ ልናነሳው የምንፈልገው ባሕል በልማት ላይ የሚያሳድረው ቀጥተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ፣ ረቂቁን ከነባር-ሥርዓታትና ከነባር-ልምድ የሚገኘውን ህብረተሰባዊ-ካፒታልን (ሶሻል-ካፒታል) ሚናን ይመለከታል። ከዚህ ቀደም እንደፃፍኩት፡-

> በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰዎች በአንድነት ተቀናጅተው (ቦንድ አድርገው) በመተጋገዝ ውስን የሆኑ ቁሳዊና ሌሎች እንደመተማመን፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ ዓይነት ንብረቶችን ለማንቀሳቀስና በጥቅም ላይ ለማዋል ያላቸው ችሎታ ሶሻል-ካፒታል ይባላል። ሶሻል-ካፒታል ንብረቶቹ ራሳቸው ሳይሆኑ፣ ንብረቶቹን በተፈለገ ጊዜ አንቀሳቅሶ ለመጠቀም የሰዎቹ ስብስብ ወይም ቡድን ያለው ህብረተሰባዊ አቅም ነው። ስለዚህም ሶሻል-ካፒታል እንደንብረቶቹ በጥቅም ላይ በዋለ መጠን አይፈጅም-አያረጅም፣ አያልቅም። እንዲያውም እያደገ፣ እየጨመረና እየበረታ ይሄዳል እንጂ (Long, 2001: 132-4)። በእንደዚህ፣ በተለይ ኋላ ቀር በሆኑ ሃገራት ልማት ውስጥ እንደ ኢኮኖሚ-ካፒታል እና የሰው- [ሂዩማን] ካፒታል ሁሉ ወሳኝ ሚና ሊጫወት የሚችለውን ይህን ሶሻል-ካፒታል በማስገኘት በኩል ሥርዓታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የውስጥ ልማዳዊ ሥርዓታቱን ጠብቆ ያቆየው የጉራጌ ሕዝብ በዚህ የተነሳ የማይናቅ ሶሺያል-ካፒታል ባለቤት በመሆን ለአባላቱና ለሃገር ልማት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኘበት ሂደት የዚህን ክስተት ምንነትና

ከሥርዓታት መኖር የሚመነጭ መሆኑን በተጨባጭ ያስረዳል (የራስወርቅ አድማሴ 2006: 9)::

በእንደዚህ ከባሕላችን ጋር በጥብቅ የተያያዙት ነባር-ሥርዓቶቻችንና ነባር-ልምዶቻችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ይኸንን ሶሻል ካፒታል በመለገስ ለአገራችን ልማት የሚያደርጉት አስተዋፅዖ ሊሰመርበት ይገባል::

## 6. ዘመናዊነት – የጊዜያችን የልማትና የባሕል ለውጥ ዓይነተኛ ገፅታ

*ዘመናዊነት፤ መዘመን፤ ማዘመን ወይም ዘመናዊ መሆን፣ ዘመናዊ ማድረግ* (ሞደርናይዜሽን) ማለት ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን፣ አሰራሮችን፣ ወይም አካሄዶችን በአኗሁዋናቸውና በጠባያቸው ማዘመን ማለት ነው:: ጊዜው ያመጣውን፣ የሚፈቅደውንና፣ የሚጠይቀውን አሰራር፣ ዘዴ፣ አኳኋን፣ ወይም ገፅታ መቀበልና ማዋሃድ ማለት ነው:: ዘመናዊነት አንድ አይነት የባሕል ለውጥ ሂደት ነው:: በመሆኑም፤ ይኽ ፅንሰ-ሃሳብ የግድ በጊዜ ስር የሚሰድ ኅብረተሰባዊ ሂደትን (ሶሻል ፕሮሴስን) ያመለክታል እንጅ አንድን ድንገት ዱብ የሚል ክስተትን አያመለክትም:: ዱብ የሚል ከሆነም ዘላቂ የባሕል ለውጥን የሚያስከትል ሳይሆን እንደ አባባሉ "ዱብ-ዕዳ" ብቻ በመሆኑ፤ ብቅ ከማለቱ በዚያው ከስሞ የሚቀር ይሆናል:: ይሁንና፤ የዘመናዊነት ሂደት፡ አንድም ዘገምተኛ አንድም ፈጣን ሊሆን ይችላል:: እጅግ ዘገምተኛ ወይም እጅግ ፈጣን ሲሆን ደግሞ ከራሱ ከሂደቱ የመነጨ ችግር ያስከትላል::

ዘመናዊነት አንድ አይነት የባሕል ለውጥ ሂደት እንደመሆኑ በዘመናዊነትና በባህል መካከል አስገዳጅ ተቃርኖ የለም:: ዘመናዊነት ሊቃረን የሚችለው ከባሕል ይዘቶች አንዱ ከሆነው ከነባር ልማድ ጋር ነው ::

እንደማንኛውም የባህል ለውጥ ሁሉ የዘመናዊነት ይዘቶችም ከአንድ ሥርዓተ-ባሕል ከራሱ ሊመነጩ ወይም ከውጭ በትውስት ተገልብጠው ሊገቡ፤ ሊዋሀዱና፤ሥር ሰድደው ሊያብቡ ይችላሉ:: የዘመናዊ ባህል ይዘቶች ከውጭ በተውሶ መወሰድ በራሱ ምንም ችግር የለውም:: በመላው አለም በየስርዓተ-ባሕሉ ለምተውና ሰፍነው የሚገኙ እጅግ አብዛኛዎቹ የባሕል ይዘቶች ከውጭ የተወሰዱ ሆነው ሳለ፤ በየገቡበት ስርዓተ-ባሕል ውስጥ ፍፁም ከመዋሀዳቸው የተነሳ፤ የባዕድነት ደብዛቸው ጭራሹን ጠፍቶ የየስርዓተ-ባሕሉ አካልና አምሳል ሆነው ይኖራሉ::

ይኸን በቀላሉ ለማስረገጥ ጥቂት የሀገራችንን ስርዓተ-ባሕል ይዘቶች እንደ ምሳሌ ወስደን እንመልከት:: የወንዶች ሀበሻ-ልብሳችን መሰረቱ የቅርብ-ምስራቅ ቅጅ ነው:: ወደ ቅርብ-ምስራቅ የገባው ደግሞ ከሕንድ ክፍለ-አሕጉር በነአፍጋኒስታን በኩል እያቆራረጠ ነበር:: በስፔን ላይ ሰልጥነውባት የነበሩት አረቦች፤ እነሱም እንደኛ «ቀሚስ» የሚሉትን የላይ ተላባሹን ወደ ስፔን ከነስሙ ይዘውት ገቡ:: በዚያ ሀገር የመታወቂያ ስሙ ግን እንደማንኛውም ተወራሽ የባሕል ይዘት ያገሬውን ቋንቋ ቅላፄ ወስዶ "ካሚሳ" (camisa) ሆነ:: «ካሚሳ»ም የፒሬኔስን የተራራ ሰንሰለት ተሻግሮ ፈረንሳይ ሲደርስ በቅርፅም በስምም የአገሩን ዘዬ

ተከትሎ የፌትለፊት ተከፋቹንና በአዝራር ተቆላፊውን "ሸሚዝ" ሆነ። በዚህ ዓይነት ሂዙሮ መጣና፤ የኛነቱን ደብቆ በመግባት አለባበሳችንን አዘመነ፤ ከዘመናዊነት ምልክቶቻችንም አንዱ ሆነ። ባሁኑ ጊዜ እንደ ነባር-አልባሳት የምናያቸው እነ ካባና በርኖስም ቢሆኑ፤ ከውጭ በገቡበት ቀደም ባለው ጊዜ፤ የዘመናዊነት መገለጫ እንደነበሩ ትክክለኛ ግምት መስጠት ይቻላል።

ሌሎችም ብዙ የሥርዓተ-ባሕላችንን ይዘቶች ጀርባ ብንፈትሽ፤ የተመሳሳይ የመውረስና የመወራረስ ሂደቶች ውጤት ሆነው እናገኛቸዋለን። ለነገሩ ከበርበሬ የበለጠ ከስር ከመሰረቱ ፍፁም ኢትዮጵያዊ መሳይ የምግብ ግብአትና የምግብ ባሕላችን ዓይነተኛ መለያ ባልነበረ። ግን እሱም ቢሆን፤ ቆየ እንጅ፤ በ15ኛውና በ16ኛው ምዕተ-ዓመታት አፍሪቃን አካለው ብቅ ባሉት ፖርቱጊዝ ነጋዴዎች አማካይነት ከተገኘበት ከ"አዲሱ-ዓለም" መጥቶ የለመደ መሆኑን፤ ሩቅ ሳያስኬደን፤ ራሱ "ፔሪፔሪ" የተሰኘው የስሙ ስረ-ቃል በበቂ ያስረዳናል። በእንደዚህ፤ ከባሕር-ማሽላና ከባሕር-ዛፍ በተጨማሪ ሌሎች እጅግ ብዙ የባሕር-ማዶ ነገሮች በሥርዓተ-ባሕላችን (ባሕሎቻችን) ተወርሰውና የምንጫቸው ደብዛ እስከሚጠፋ ድረስ ተዋሕደው እንደሚኖሩ እንገነዘባለን። ከሌሎች የባሕል ይዘቶችን መውረስ፤ ጨርሶ ማዋሃድ፤ የራስ አድርጎም ማበልፀግና ሕያው አድርጎ ማኖር ደግሞ ከፍተኛ የባሕል ችሎታን የሚጠይቅ መሆኑን መረሳት የለበትም።

ከዚህ የባሕል ይዘቶች መወራረስ ጋር የተያያዘ አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ አለ። ይኸም ከፍ ብለን የጠቀስነውን በ"ዘመናዊነት ወይም ማዘመን" (ሞደርናይዜሽን) እና ከባሕል ይዘቶች አንዱ በሆነው "ነባር-ልማድ" (ትራዲሽን) መካከል ሊኖር የሚችለውን ተቃርኖና ግጭት ይመለከታል። ማንኛውም ባሕል በቴክኖሎጂ እድገት እየታገዘ የሚመጣን ዘመናዊ የባሕል ይዘቶችን ተቀብሎ እንደሚያዋሕድ ከላይ ያሰመርንበት ጉዳይ ቢሆንም፤ ይኸ አባባላችን በሃገራችን የሚታየውን መረን-በለቀቀ ደረጃ በመካሄድ ላይ ያለውን የ"ነባር-ልማድ" ናሙናዎች መወረርና መደፈር አሳዛኝ ሂደትን መሸፈንና ማለሳለስ የለበትም። እርግጥ፤ አንዳንድ ነባር የሆኑ የሥነ-ፅሁፍ፣ የስዕል፣ የሙዚቃ፣ የጭፈራ፣ የምግብ/የአመጋገብ፣ የልብስ/የአለባበስ፣ ወዘተ... ዘመናዊ መልክ እያገኙና አዳዲስ ጥቅም ላይ እየዋሉ ሄደዋል። የፈትልና የጥበብ ልብስን ዘመናዊ ዕድገት እንደምሳሌ ብንወስድ፤ ከሁለተኛው የዓለም-ጦርነት ወዲህ በዚህ ዘርፍ የተደረገውን እርምጃ ማሳነስ ወይም ማንቋሸሽ አይቻልም። ከመክሰም መትረፍ ብቻ ሳይሆን፤ እያበበ የሄደና አለ ሊባል የሚችለው ብቸኛ "የፋሽን-ኢንዱስትሪያችን" ምሰሶ የሆነው፤ ሳይዘምንና የጥቅም አድማሱን ሳያሰፋ ቀርቶ ባለሁበት ልርገጥ ባለማለቱ ነው። ግን፣ ከዚህ በጎ የማዘመን ሂደት ጎን-ለጎን ነባሩን ለይቶ መስቀመጥና ሳያዳቅሉ ጠብቆ ማቆየት ያስፈልግ ነበር። ለምሳሌ፤ አንዳንድ "ባሕላዊ የኪነት ቡድኖች" የአማራ ሕዝብ የ"ባሕል ልብስ" ብለው በኢቲቪ ሳይቀር የሚያቀርቡት እዚሁ-በዚሁ (እለቱን ማለት ይቻላል) አራዳ ክፍለ-ከተማ የተፈለሰፈ፣ ከቻይና ሰሞኑን በገባ ሲንተቲክ ቲ-ሸርት የደመቀና፣ ምንነቱ ያልታወቀ ምስቅልቅል አልባስ ነው። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ፤ ከኛ ከተራ ተመልካቾቹ ባሻገር የባሕል መሪ ባላደራና ባለድርሻ የሆኑት የኪነት ጠበብት ጭምር ይህን ዓይነት ጠንቀኛ ሂደት በዝምታ ማለፋቸው ነው።

የ"ኪነት ነፃነት" ጉዳይ ቢሆንም እኮ ልክና መልክ አለው::

## 7. መደምደሚያ – የወደፊቱን የውይይት አቅጣጫ በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦች

እኛ፤ የዚህ የ "ባሕል እና ልማት በኢትዮጵያ" ውይይት መድረክ ተሳታፊዎች የሆንነው የጉዳዩ ባለድርሻዎች፤ በዚህ ርዕስ ስር የምናካሂዳቸውን ጥናቶችና ውይይቶች እንዲሁም የምናስራጫቸውን ሃሳቦች በተመለከተ አንድ-አንድ መርሆች ልንከተል ይገባል:: ከዚህ በመቀጠል ከተዘረዘሩት ወስጥ አንድ አንዶቹን ማጤን ጠቃሚ ይመስለኛል::

- በባሕል ፅንሰ-ሀሳብ አመጣጥ፣ የተለያዩ ትርጉሞችና፣ አጠቃቀሞች ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጥ፤
- በባሕልና በሌሎች ተቀራራቢው በሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦች መካከል ባሉት ልዩነቶችና አንድነቶች ላይ ግልፅ መሆን፤
- በኅብረተሰባዊ ለውጥ፣ በልማትና፣ በመዘመን ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ ግልፅ መሆን፤
- ጥቅል አባባሎችና ጥቅል አንድምታ የትም እንደማያደርሰን በመገንዘብ፤ በዝርዝር ጉዳዮችና ትስስሮች ላይ ማተኮር:: ለምሳሌ፣ የትኛውና የመቼው ጊዜ የባሕል ኤለመንት ወይም ነባር-ልምድ ለየትኛውና ለመቼው ጊዜ የልማት ሂደት ነው ማነቀ ወይም መፍትሄ የሆነው? ለምን ሲባልና በምን አካባቢ የፈለቀ የባሕል ኤለመንት (ለምሳሌ የገጠር) በሌላ አካባቢ (ለምሳሌ የከተማ) ተገኝቶ ልማትን አደናቀፈ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ማንሳትና መመርመር፤
- በጥናትና በምርምር ያልተደገፉና ስለተደጋገሙ ብቻ ሰፊ ተቀባይነት ያገኙ ሃሳቦችና አባባሎችን ትክክለኛነት መጠየቅ፣ መመርመርና ድክመታቸውን ማሳዬት አለብን:: ለምሳሌ፣ እንደ "አበሻ አብሮ መስራት አይችልም" የሚል ያልተፈተሸ መፈክር ይዞ ከመፍሰስ ይልቅ የሰው-ስብስቦች አብሮ የመስራት ችግር (problem of collective action) የበርካታ ምሁራንን ልፋትና እልህ ያስጨረሰ አለም-አቀፋዊ ችግር እንደሆነ ተገንዝቦ ከነዚያ ትጉሃን ጎራ መደባለቅ ይጠቅመናል:: "ሰዓት የማናከብረው ለጊዜ ዋጋ በማይሰጠው የቆየ ባሕላችን የተነሳ ነው" ማለት፤ እንደ የቀጠሮና የሥራ ሰዓት ላሉ የአሁን ዘመን መለያ ክስተቶች የቆየውን ባሕል ተጠያቂ ማድረግ፤ ለሞባይል ስልክና ለኢንተርኔት አጠቃቀማችን የሚመች ባሕል ተደላድሎ አልጠበቀንም ብሎ አስቂኝ እሮሮ ማሰማት፤ እና ይኸና ያ የፖለቲካ ችግር የገጠመን "የዲሞክራሲ ባሕል ወይንም የመቻቻል ባሕል ስለሌለን ነው" ብሎ ማወጅ "በባሕል ቀሚስ" ተክልሎ ከጥያቄው ለማምለጥ ከመሞከር ሌላ ምንም ትርጉም እንደሌለው ተቀብሎ ትርጉም ያለው ትንተና ለማቅረብ መጣጣር ተመራጭ ነው::

- በባሕል ላይ ሰበብ የማላከክ ጨዋታን ትተን፤ ለጊዜያችንና ለሁኔታችን የሚመጥን የባሕል ኤለመንቶች የምንፈጥርበትንና የምናዳብርበትን መንገድ መሻትና የባሕል ዕድገትን ያቀፈ ኅብረተሰባዊ ልማት ለማምጣት ለሚረዱ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት፤
- ባሕል በልማት ላይ ሊያሳድር በሚችለው ተፅዕኖ ላይ ብቻ ሳይሆን በልማት ስም በተለይ በአካባቢያዊ ንዑስ ባሕላት ላይ ሊደርሱ በሚችሉ አሉታዊ ተፅእኖዎች ላይ ጭምር፤ በፍትሃዊ ሆኖም ባልተጋነነ ተነሳሽነት ማተኮር፤

በመጨረሻም፤ እንደ ኢትዮጵያችን ያሉትን በኢኮኖሚ ዕድገት ኋላቀር የሆኑ ሀገራትን በተመለከተ ለልማት ጠንቅ በሆኑ የባሕል ይዘቶች ላይ ብቻ ማተኮር ጊዜው ያለፈበት አመለካከት እየሆነ መምጣቱንና፤ በዛሬው የዕውቀትና የምርምር ዓለም፣ ለልማት ጠቃሚ የሆኑትን የነዚህን ህብረተሰቦች የባሕል ይዘቶችን ጭምር የሚያካትት፣ ሚዛናዊና፣ ብሎም ጠቃሚ የሆነ የምርምርና የትንታኔ አካሄድ የበላይነትን እያገኘ መምጣቱን ማብሰር እንወዳለን (እንደ ምሳሌ፤ ደግላስን 2004 እና ሞንክሪፈን 2004 ይመልከቱ)::

# የብሔራዊ ቅርስ ልማትና ቱሪዝም

## *ቴዎድሮስ አጥላባቸው*

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ የተለያዩ ልምዶች፤ እምነቶች፤ አባባሎች፤ ወጎች፤ ሥርዓቶች እና የአኗኗር ዘዴዎች አሉን፡፡ እነዚህ ዕሴቶች ከሰዎች የአኗኗር ዘይቤዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፡፡ በስፋት ተቀባይነትን በሚያገኙበት ጊዜ ባሕል በመሆን የአንድን ጎሣ፤ ብሔረሰብ . . . ወዘተ፣ የአኗኗር ሁኔታን ያንፀባርቃሉ፡፡ በስፋት ተቀባይነትን ያገኘ ባሕል ለአንድ ጎሣ፣ ብሔረሰብ . . . ወዘተ ከተደነገጉ ህጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ባላነሰ ሁኔታ ተቀባይነትን አግኝቶ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን አንዴ እና ለዘልዓለም የተሰጠ ወይም የተፈለሰፈ ሕግ ወይም ደንብ አይደለም፡፡ ጊዜ ሲያልፍ እና ትውልድ ሲተካ አዳዲስ ልምዶች፣ እምነቶች፣ አባባሎች፣ ወጎች፣ ሥርዓቶችና የአኗኗር ዘዴዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ቀደምት ባሕሎች በአዳዲስ ባሕሎች ይተካሉ፡፡

ተፈጥሮ የለገሰን በርካታ ሀብቶች፣ እንደዚሁም ከአያቶቻችንና ከቅድመ አያቶቻችን (our ancestors) የወረስናቸው ባሕላዊና ተፈጥሮአዊ ዕሴቶች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ ከእነዚህ ውስጥ፣ በተለያዩ መመዘኛዎች የላቀ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸው፤ እንደየቅደም ተከተላቸው ብሔራዊ ቅርስ እና የዓለም ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ቅርስ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት፤ አብዛኛውን ጊዜ መተኪያ የማይገኝለት፤ በይዘቱና በዓይነቱ ስፋትና ጥልቀት ያለው እንደዚሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቅርስ ከፍተኛ ዕሴት ያለው የተፈጥሮ ስጦታና የሰዎች የፈጠራ ውጤት እንደመሆኑ በርካታ ባሕላዊ፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንደዚሁም ከግንዛቤና ከአያያዝ ጉድለቶች ስፍር ቁጥር የሌለው የዓለማችን ቅርስ ወድሟል፤ በመውደም ላይም ይገኛል፡፡ ከወደመው ቅርስ ሊገኙ ይችሉ የነበሩ በርካታ ጠቀሜታዎችም ባክነው ቀርተዋል፡፡ ባለንበት ዘመን ስለቅርስ ያለው የግንዛቤ አድማስ እየሰፋ በመምጣቱ፤ ቅርስን በአግባቡ ጠብቆ፤ ተንከባክቦ እና ተጠቅሞ ለመጪው ትውልድ የማስተላለፉ ጉዳይ በበርካታ አገሮችና ህዝቦች ልዩ ትኩረትን አግኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የቅርስ አጠባበቅን፣ አጠቃቀምን እና አያያዝን በተመለከተ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ በርካታ የምርምር ሥራዎች ተከናውነዋል፤ የቅርስን ጉዳይ በቅርበት ለመከታተል እንዲቻልም ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣

አገራዊ… ወዘተ ተቋማት ተመሥርተው ሥራዎቻቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ቅርስ እና ልማት በመሆኑ *“ቅርስን መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማት፣ በሥርዓት መጠቀምና ለመጪው ትውልድ በአግባቡ ማስተላለፍ”* የሚለው ዐረፍተ ነገር መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡ ይህንንም ዕውን ለማድረግ የቱሪዝም ሚና ከፍተኛ እንደሆነና ቀጣይነት ያለው የልማት እቅድና ስትራቴጂ አስፈላጊነትም ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው በቅርስ ሁለንተናዊ ትንተና ላይ ሲሆን ፣ ከልማት ጋር በተገናኘ መልኩ፣ በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡ በተለይም ብሔራዊ ቅርሶቻችንን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመጠበቅ፣ ለማልማት፣ ለመጠቀምና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል፤ በቅርስና በቱሪዝም መካከል ስላለውና ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ለውይይት የሚረዱ ሀሳቦችን ማቅረብ የፅሁፉ አቢይ አላማ ይሆናል፡፡

## 2. ቅርስና የቅርስ ዓይነቶች

ቅርስ በተለያዩ አገሮችና ግለሰቦች የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የቅርስን ትርጉም ለማቅረብ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ለውይይታችን መግባቢያ ሆኖ ያገለግል ዘንድ ጽንሰ ሀሳቡን በቀላል አገላለጽ ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ቅርስ በውስጡ ካካተተው ከፍተኛ ዕሴት አኳያ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ መስፈርቶች፤ ማለትም ከእድሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅየነቱ … ወዘተ፣ አኳያ በተለያዩ መመዘኛዎች የተመረጠ የተፈጥሮ ስጦታና ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት ወይም ሁለቱንም በጣምራ (የተፈጥሮና ባሕላዊ ቅርስን) ያካተተ ነው ቢባል ለቅርስ ከተሰጡት በርካታ ትርጉሞችና ከቅርስ ጽንሰ ሀሳቦች ጋር ይስማማል እንጂ አይቃረንም፡፡

ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንንና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን የፈጠራ ውጤቶች ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩና ዓይነቱ እጅግ ብዙ ነው፡፡ በመሆኑም ለግንዛቤ እንዲረዳ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት አራት የቅርስ ዓይነቶች ከፋፍሎ ማየቱ ለጽሑፉ ዓላማና ለውይይታችን አስፈላጊ ይመስለናል፡፡

### 2.1 ባሕላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ

ቅርስ ሲባል አብዛኞቻችን የምናስበው ከባሕል ጋር በተገናዘበ መልኩ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅርስ የተመረጡ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና የሰው ልጅን የፈጠራ ውጤቶች ወይም የሁለቱንም ጥምረት የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ባሕላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

*የባሕል ቅርስ፣* የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶችን ማለትም ሐውልቶችን፣ ህንፃዎችን፣ ዋሻዎችን፣ በድንጋይና በብራና ..ወዘተ፣ በመሳሰሉት ላይ የተጻፉ ወይም የተቀረፁ ፅሁፎችን፣ ቅርፃቅርጾችን፣ አልባሳቶችን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ሥርዓቶችን... ወዘተ፣ ሁሉ ያካትታል፡፡

*የተፈጥሮ ቅርስ፣* በላቀ ጠቀሜታቸው የተመረጡ ማራኪና ውብ የሆኑ ደኖችን፣ ሐይቆችን፣ ዋሻዎችን፣ ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የእንስሳት መጠለያዎችን፣ በአጠቃላይ ህይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ፍጡሮች እና እነርሱም የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያካትታል፡፡

## 2.2 የዓለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ

ቅርስ ካለው ጠቀሜታ አንፃር የዓለምና የብሔራዊ ቅርስ በሚል በሁለት ይከፈላል፡፡ አንድ ቅርስ (የባሕል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት ባወጣው መመዘኛ መሠረት በውስጡ የላቀ ዓለም አቀፍ ዕሴት ካለው፣ የዓለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቦ የዓለም ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ብሔራዊ ቅርስን በተመለከተ ደግሞ፣ እያንዳንዱ መንግሥት ባወጣው መመዘኛ መሠረት ማንኛውም ብሔራዊ ዕሴት ያለው ቅርስ (የባሕል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቦ ብሔራዊ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡

እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 16 ቀን 1972 ዓ.ም. የዓለምን የባሕልንና የተፈጥሮን ቅርስ ለመጠበቅና ለመንከባከብ በፓሪስ ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባው ላይ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት (UNESCO) የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ በውሳኔ ሰነዱ አንቀጽ አንድ እና ሁለት ላይ የዓለም የባሕልና የተፈጥሮ ቅርስ ትርጉሞችን አጽድቋል፡፡

የጸደቁትን ትርጉሞች ይዘት፣ ቀለል ባለ መልኩ ወደ አማርኛ በመተርጎም፣ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### *የዓለም የባሕል ቅርስ*

- **ሐውልቶች (Monuments)፡-** ከታሪክ፣ ከሥነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ሐውልቶች፣ ማለትም በዚህ ውስጥ የሚካተቱ የምህንድስና ሥራዎች፣ ቅርፃ ቅርፆችና ሥዕሎች፣ በቁፋሮ የተገኙ የሐውልት ባሕሪይ ያላቸው አቋሞች፣ የተቀረፁ ጽሑፎች፣ ዋሻዎችና ተመሳሳይ ባሕሪይ ያላቸው፣
- **ሕንፃዎች (Buildings)፡-** ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ሕንፃዎች፣ ማለትም ካላቸው የላቀ

የምህንድስና ጥበብ፣ ካቀማመጣቸው ውበት፣ ከአሰራራቸው ወጥነት አንፃር የተመረጡት፤ እና

- **ቦታዎች** (Sites)፡- ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንፃር የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው ቦታዎች፤ ማለትም በሰው የተሰሩ ወይም የተፈጥሮና የሰው ሥራዎችን በአንድ ላይ ያጣመሩ የቁፋሮ ቦታዎችንም (Archaeological Sites) ጭምር ያካተቱ ሁሉ የባሕል ቅርስ ተብለው እንዲወሰዱ ወስኗል፡፡

### *የዓለም የተፈጥሮ ቅርስ*

የተፈጥሮ ቅርስ፤ ማራኪ ገጽታ፣ ውበት እና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እንደዚሁም በብርቅነታቸው እንክብካቤን የሚሹ እና የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው *ተፈጥሯዊ ክስተቶችን* (ተፈጥሯዊና ስነህይወታዊ ፍጥረቶችን ወይም ሁለቱንም በጣምራ ያካተቱ)፤ *ስነ ምድራዊ አቀማመጦችን* (ዘራቸው ለመጥፋት የተቃረበ የዕፅዋትና የእንስሳት *መኖሪያ ቦታዎችንም* ያካተቱ) እና *ማራኪ የተፈጥሮ ቦታዎችን* (ልዩ ጥበቃና እንክብካቤን የሚሹ ወይም ድንቅ የተፈጥሮ አካባቢዎችን) ሁሉ ያካትታል፡፡

## 2.3 ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ቅርስ

ከዓይነቱ፤ ከተፈጥሮውና ከመጠኑ አንፃር ቅርስ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

ተንቀሳቃሽ የሚባለው በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የሚችል የቅርስ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በቅርስነት የተመዘገቡ በብራና ላይ የተፃፉ ጽሑፎች፣ አልባሳት፣ በተለያዩ ቁሳቁሶች (ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከሸክላ፣ ከድንጋይ፣ ከወርቅ... ወዘተ) የተሰሩ ዕቃዎችና ቅርፃ ቅርፆች፣ መጠናቸው አነስተኛ የሆነ በቁፋሮ የተገኙ ጥንታዊ የመገልገያ ዕቃዎች... ወዘተ፣ የመሳሰሉት በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ ስለሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

የማይንቀሳቀስ የሚባለው በቀላሉ ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ታሪካዊው የሐረር ከተማ ጀጎል፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ... ወዘተ፣ ይጠቀሳሉ፡፡ በዓለም ቅርስነትም የተመዘገቡ ናቸው፡፡ ከአፈጣጠራቸው፤ ከግዝፈታቸው እና ከሚገኙባቸው ቦታዎች አኳያ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ አንዳንዶቹን ደግሞ ፈጽሞ ለማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ አንዳንዶቹ ቢንቀሳቀሱ እንኳን (የአክሱም ሐውልት ወደ ኢጣሊያ በተወሰደው ዓይነት) እሴቶቻቸውን ያጣሉ፡፡ የላቀ ትርጉም የሚኖራቸው ከተፈጠሩበት ወይም ከተሰሩበት ቦታ ላይ ሲገኙ ብቻ ነውና፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ

ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ የሚችሉ ስላልሆኑ የማይንቀሳቀስ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## 2.4 ተጨባጭ (Tangible) እና ተጨባጭ ያልሆነ (Intangible) ቅርስ

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ፣ በአጠቃላይ በሁሉም ስሜተ ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ሐውልቶች፣ ህንፃዎች፣ ዋሻዎች፣ መጻሕፍት፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርጾች፣ አልባሳት… ወዘተ፣ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው… ወዘተ፣ የማንችለው፣ ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ፣ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ በመባል ይታወቃል፡፡ ወጎች፣ ተረቶች፣ ሥርዓቶች፣ ማራኪ እይታዎች… ወዘተ፣ ቁሶች አይደሉም በተፈጥሯቸውም ተጨባጭ አይደሉም፡፡ በውስጣቸው ግን መንፈሳችንን የሚያነሳሱ፣ የአእምሮ እርካታንም የሚሰጡን በርካታ እሴቶች አሏቸው፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማወቅን፣ መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መደሰትን… ወዘተ፣ ሁሉ ይፈልጋል፡፡ ፍላጎቶቹ ሁሉ ግን በቁሳዊ ፍላጎቶቹ ብቻ ሊረኩ ከቶውንም አይቻላቸውም፡፡ ተጨባጭ ከሆኑት ወይም ከቁሳዊ ፍላጎቶቹ በተጨማሪ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ያልሆኑ ፍላጎቶችም አሉት፡፡ በመሆኑም፤ ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች፤ በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

# 3. የቅርስ አያያዝና አጠቃቀም

ቅርስ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት የተፈጥሮ ስጦታና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት እንደመሆኑ ልዩ ትኩረትን የሚሻ መተኪያ የሌለው ሀብት ነው፡፡ በዓለማችን ውስጥ በቅርስነት ሊመዘገቡ የሚችሉና በቅርስነት የተመዘገቡ በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በተለያዩ ዘመኖች፤ ስለቅርስ የነበሩት ግንዛቤዎች የተለያዩ ቢሆኑም፤ ህዝቦች በተለያዩ የአኗኗር ዘዴዎቻቸውና ባህሎቻቸው፤ እምነትን፤ ክብርን፤ ዝናን… ወዘተ መሠረት በማድረግ፤ ቅርስን ጠብቀውና ተንከባክበው ለአሁኑ ትውልድ አስተላልፈዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች (ጦርነቶች፣ የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ… ወዘተ)፤ በግንዛቤ እጥረት፣ ኑሮን ለማሸነፍ በሚደረግ ጥረት… ወዘተ፣ በርካታ የዓለማችን ቅርስ ወድሟል፣ በመውደምም ላይ ይገኛል፡፡

ባለንበት ዘመን፤ ስለ ቅርስ ያለው ግንዛቤ ከመቸውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ጎልብቶ ይገኛል፡፡ በብሔራዊ መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቅርስን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለመጠቀም እና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ

መዋቅሮች ተዘርግተዋል፡፡ በአገራችን ውስጥ በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥር "የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን" በሚል መጠሪያ ሙሉ ሥልጣን ያለው መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተለያዩ የክልል መስተዳድሮችም ባሕልና ቅርስን በተመለከተ መዋቅሮች ተዘርግተው ቅርስን በመንከባከብ ረገድ አበረታች እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1946 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር "የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት" (United Nations Educational Scientific and Cultural Organization) በሚል መጠሪያ አንድ የሥራ ክፍል ተቋቁሞ እስካሁን ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ውስጥ አባል አገሮች ባፀደቁት የምርጫ መስፈርት መሠረት፣ የላቀ ዓለም አቀፍ እሴት ያለውን ቅርስ በመምረጥ በዓለም ቅርስነት መመዝገብ እና ቅርስን በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለመጠቀምና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፎችን ለአባል አገሮች መስጠት ይገኙበታል፡፡

እ.ኤ.አ. እስከ ኦክቶበር 2007 ዓ.ም. ባለው ጊዜ 193 አገሮች የድርጅቱ ቋሚ አባል እንደዚሁም 6 አገሮች ደግሞ ተባባሪ አባል በመሆን ተመዝግበዋል፡፡ ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ. ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ የድርጅቱ አባል አገር ሆና ተመዝግባለች፡፡

ድርጅቱ እ.ኤ.አ. በኤፕሪል ወር 2009 ዓ.ም. ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በጥቅሉ 878 ንብረቶች በዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 679 የባሕል ቅርስ፣ 174 የተፈጥሮ ቅርስ እና 25 የባሕልና የተፈጥሮ ቅርስ ድብልቅ (ጣምራ) ይገኙባቸዋል፡፡

አገራችን የበርካታ ቅርስ ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፤ ከነዚህም ውስጥ ስምንቱን የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት በዓለም ቅርስነት መዝግቧቸዋል፡፡ (ዝርዝራቸው በሠንጠረዥ 1 ቀርቧል፡፡)*

በአህጉራችን ደረጃ ሲታይ ኢትዮጵያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካና ቱኒዝያ እያንዳንዳቸው ስምንት የዓለም ቅርስ በማስመዝገባቸው የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ፡፡ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች እያንዳንዳቸው ከስምንት ያነሰ፤ አንዳንዶቹም ምንም ያላስመዘገቡ ይገኙበታል፡፡ ለመጥቀስ ያህል ግብፅ 7፣ ኬንያ 4፣ ሱዳን 1 የዓለም ቅርስ አስመዝግበዋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 02 ቀርቧል)

በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት ስምንት ንብረቶች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የባሕልና የሰው ሰራሽ ቅርስ ክምችት እንዳለ ይታወቃል፡፡ ከቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የተገኘው መረጃ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ ቤተ መንግሥቶችና ሙዚየሞች

---

* ይህ ጽሁፍ ከተዘጋጀ በኋላ አንድ የባህልና የተፈጥሮ ቅርስ በዩኔስኮ ተመዝግቧል፤ ይህም የኮንሶ የእርከን ስራ ነው፡፡ ከአዘጋጁ

ውስጥ ከ40,000 በላይ የሚንቀሳቀሱ ቅርሶች ተመዝግበው የመለያ ኮድ የተሰጣቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ መረጃ በግለሰቦች እጅ የሚገኘውን ቅርስ እንደማያካትትም ተጠቅሷል። በየጊዜው የተመዘገበውን የቅርስ ዓይነትና መጠን የሚያመለክት ስታቲስቲካዊ መረጃ ማግኘት ባይቻልም፤ የተመዘገበው ቅርስ ከተጠቀሰው በላይ እንደሆነ አንዳንድ ምንጮች ይገልፃሉ።

ሠንጠረዥ 1፡- በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ ንብረቶች

| ተ/ቁ | በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ ንብረት | የተመዘገበበት ጊዜ (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|
| 1. | የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት | 1978 |
| 2. | ሰሜን ተራራ ብሔራዊ ፓርክ | 1978 |
| 3. | የፋሲል ግቢ እና የጎንደር አካባቢ | 1979 |
| 4. | አክሱም | 1980 |
| 5. | የታችኛው አዋሽ ሸለቆ | 1980 |
| 6. | የታችኛው ኦሞ ሸለቆ | 1980 |
| 7. | ጢያ | 1980 |
| 8. | ጥንታዊው የሐረር ከተማ (ጀጎል) | 2006 |

የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። ራሱን የቻለና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ የአሠራር ዘዴም አለው። በአገራችንም ውስጥ ይህንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘውን የአሠራር ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፤ በመደረግም ላይ ይገኛሉ። ቅርስን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከሚያስፈልጉት ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

## 3.1 የቅርስ ምዝገባና ስነዳ (Inventory and Documentation)

ቅርስን በአግባቡ ለመንከባከብና ለመጠቀም በቅድሚያ የት ቦታ እንደሚገኝ፤ ዓይነቱ፣ ብዛቱ፣ የተሰራበት ዘመን፣ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መታወቅ ይኖርበታል። ለዚህም በጽሑፍ፣ በፎቶግራፍ እና በፊልም በተደገፈ መልኩ መመዝገብና የምዝገባ መለያ (code) መስጠት ይገባል። ይህ ከተከናወነ በኋላ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ አሰባስቦ፤ ደህንነቱ በሚያስተማምን ሁኔታ በተጠበቀ ማዕከል (ሙዚየም) ውስጥ ማከማቸት ወይም ማንቀሳቀስ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ባለበት ቦታ ተገቢው እንክብካቤ ተደርጎለት፤ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ያስፈልጋል። አገራችን የበርካታ ቅርስ ባለቤት መሆንዋ ቢታመንም አብዛኛው ቅርስ ግን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት

እንዳልተመዘገበ ይታወቃል። ካለው ባሕልና የአሰራር ልምድ፣ አብዛኛው ቅርስ የሚገኘው በገዳማት፣ በመስጊዶች እና በግለሰቦች እጅ ነው። ገና በቁፋሮ ያልተገኘ በመሬት ውስጥ የተቀበረ በርካታ የቅርስ ክምችት እንዳለና ተመራማሪዎች ያልደረሱበት ሌላ የተፈጥሮ ቅርስም በመሬት ላይ ሊኖር እንደሚችል ይገመታል። ይህ ግን ቅርስን የመመዝገብና የማከማቸት ሥራ እየተሠራ አይደለም ለማለት አይደለም። ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች አቅማቸው በፈቀደ መሠረት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳሉ ይታወቃል። አበረታች ውጤቶችም ተገኝተዋል። ቅርስ ካልተመዘገበ፣ የት እና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ካልታወቀ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣ ተገቢውን እንክብካቤም አያገኝም። ስለዚህ የቅርስ ምዝገባና ክምችት እጅግ አስፈላጊ ተግባር መሆኑ አያጠያይቅም።

## 3.2 የቅርስ እንክብካቤ እና አስተዳደር

አንዳንዱ ቅርስ በእርጅና ወይም በአያያዝ ጉድለት የተጎዳና የተበላሸ ነው። በመሆኑም ልዩ እንክብካቤን፣ ማለትም በነበረበት ሁኔታ መጠገንን (Restoration) ይፈልጋል። የቅርስ ጥገና ሥራ እጅግ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው። አገራችንም የዚህ ዓይነቱን የጥገና ሥራ በቂ በጀት መድባ በራሷ ለማከናወን የሚያስችል አቅም የላትም። ታዳጊ አገር እንደመሆኗ ልዩ ቅድሚያን የሚሹ ሌሎች በርካታ የልማት፣ የጤና፣ የትምህርት ... ወዘተ፣ ሥራዎች ማከናወን ስለአለባት ለቅርስ የምታውለው የሰው ሆነ የቁሳቁስ ሀብት እጅግ የተመጠነ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ከዓመታት በፊት፣ ሞስኮ ውስጥ የሚገኘው ቦልሾይ ቲአትር በመባል የሚታወቀው ታሪካዊው ቴአትር ቤት ህንፃው የመሰንጠቅ ጉዳት ስለደረሰበት በነበረበት ሁኔታ ለመጠገን ከ300 እስከ 350 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግ ተገምቶ ነበር። በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ወጪው በዚያን ጊዜ ከተገመተው በላይ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ለመጠገን የሚያስፈልገው ወጪ ከዚህ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። አገሪቱ ካላት የኢኮኖሚ አቅም አኳያ እነዚህን ውቅር ቤተ ክርስቲያናት በነበሩበት ሁኔታ ለመጠገን ባለመቻሉ የበለጠ ውድመት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የእንክብካቤ ሥራ ብቻ በመከናወን ላይ ይገኛል። ይህም እራሱ ከፍተኛ ወጪንና ሙያን የሚጠይቅ በመሆኑ እየተከናወነ ያለው ከአውሮፓ ሕብረት በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ እርዳታ መሆኑ ይታወቃል። መጠኑ አነስተኛ የሆነ ቅርስን (ቅርፃ ቅርፆች፣ ጽሑፎች .. ወዘተ) በአገር ውስጥ ባለሙያዎች ለመጠገን ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ላያስፈልግ ይችላል፣ ነገር ግን ልዩ የሙያ ክሂሎትን ይጠይቃል።

ለማጠቃለል ያህል ቅርስን ከመመዝገብና ከማከማቸት በተጨማሪ፣ በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኘውን በልዩ እንክብካቤ መያዝ፣ እንደዚሁም የተበላሸና የተጎዳን ቅርስ በአግባቡ ጠግኖ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረጉ ተግባር ልዩ ትኩረትን ይፈልጋል።

***ወገንተኝነት /መወገን/ (Patronage)፤*** ወገንተኝነት አንድን ወገን አለአግባብ መጥቀምን ወይም መደገፍን ይመለከታል:: አንድ በምርጫ ያሸነፈ ፓርቲ ፖሊሲዬን ያስፈፅሙልኛል የሚላቸውን ሰዎች በቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች ሊያስቀምጥ ይችላል:: ሆኖም ለቦታው የተሻለ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሰዎች እያሉ ሥርዓቱን ስለሚደግፉ ብቻ በወገንተኝነት የአመራር ቦታ እንዲይዙ ማድረግ ሙስና ነው:: በአብዛኞቹ ዲሞክራሲያዊ ባልሆኑ እና ወደ ዲሞክራሲ ለመሸጋገር በሚታትሩ ሀገሮች የመንግስት ባለሥልጣናት ቦታ የሚሰጣቸው በችሎታቸው ሳይሆን ለሥርዓቱ ባላቸው ታማኝነት ነው:: ይህ በእኛም ሀገር ሥር የሰደደ ችግር ሆኖአል:: የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝቅተኛ የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ሳይቀሩ ለፖለቲካው ታማኝ በሆኑ ግለሰቦች የሚያዙበት ሁኔታ ይታያል::

***በሥልጣን መባለግ (Abuse of power)፤*** ዘመድ አዝማድን መጥቀም (Nepotism and cronyism)፤ ለምሳሌ የተደነገገውን ሕግ በማዛባት ዘመድ አዝማድን፣ ጓደኛንና የቅርብ ሰዎችን ደንቡ ከሚፈቅደው ውጪ ሥራ እንዲቀጠሩና ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ የሙስና ዓይነት ነው:: ይህ በጉቦ ከመሥራት ጋር የተቆራኘ የሚመስልበት ሁኔታም አለ:: አንድ ባለሥልጣን በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ዘመዱ እንዲቀጠር አድርጎ የድርጅቱን እንቅስቃሴ በተዘዋዋሪ መንገድ ከተቆጣጠረ የለየለት ሙስና ነው:: በዘመድ አዝማድ መሥራት፣ ቤተሰብን መጥቀም በአገር ደረጃ ተግባራዊ ሲደረግ ደግሞ ጉዳቱ የከፋ ይሆናል:: ሰሜን ኮርያንና ሶርያን በምሳሌነት ብንወስድ የመንግስት ሥልጣን ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍበት ሁኔታ እንዳለ እንገነዘባለን::

ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢ ተወላጅነት፣ የአንድ የትምህርት ተቋም ምሩቃን በመሆንና በጓደኝነት በመሰባሰብ እርስ በርስ ለመጠቃቀም የሚደረገው ጥረት ሁሉ ሙስና ነው:: በዘመድ አዝማድና በጓደኝነት የተሰባሰቡ ወገኖች ጠላቶቻችን ናቸው በሚሏቸው ወገኖችና ግለሰቦች ላይ ያላቸውን ሥልጣን ተጠቅመው እርምጃ ከመውሰድ አይመለሱም:: በተለይ እኩይ ድርጊታቸውን በሚያጋልጡ ጋዜጠኞች ላይ ርህራሄ የላቸውም::

በዘመድ አዝማድ የመሥራት ጉዳይ እንደ ሌሎች ታዳጊ ሀገሮች ሁሉ በእኛም ሀገር ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን በርካታ ሰዎች በቅሬታ ሲገልፁ ይደመጣሉ::

***ስርቆትና ዘረፋ (Embezzlement)፤*** ሥርቆትና ዘረፋ ከፍተኛ የሙስና መገለጫ ደረጃዎች ናቸው:: ሙሰኞች የህዝብን ሀብት በመስረቅና በመዝረፍ የግል ሀብታቸውን ያዳብራሉ:: በህዝብ ሀብት ላይ ስርቆት የሚፈፅም ባለሥልጣን የሚመራው ድርጅት የኮንስትራክሽን ተቋም ከሆነ ተቋሙ ለግሉ ህንፃ እንዲሰራለት ያደርጋል::

***የጥቅም ተካፋይነት (Kickbacks)፤*** ይህ ተግባር ከሌሎች በሙስና ከተዘፈቁ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ጋር በመመሳጠር የሚካሄድ፣ የተዘረፈን ገንዘብ ወይም ንብረት የመካፈል ሂደት ነው:: ለህዝብ አገልግሎት የሚውልን አንድ ፕሮጀክት የሚመራ ባለሥልጣን ለጥቅሙ ሲል ዝቅተኛ አቅም ያለውን

ኮንትራክተር ሊመርጥ ይችላል:: ወይም ደግሞ ፕሮጀክቱን ለሚያከናውነው አካል ከዋጋው በላይ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ የጥቅም ተካፋይ ይሆናል::

## 1.2 ለሙስና መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎች:-

*የመረጃ ዕጦት*

- የመንግስት ግልፅ ያለመሆን
- የመረጃ ነፃነት ህግ ያለመውጣት
- የአገር ውስጥ የምርመራ ጋዜጠኝነት ያለመኖር
- የመናገር ነፃነትና የፕሬስ ነፃነት ተግባራዊ እንዳይሆኑ ችል ማለት ወይም ለነዚህ ነፃነቶች ጥላቻ ማሳየት
- በወቅታዊ የፋይናንስ አስተዳደር የማይመራ ደካማ የሂሳብ አያያዝ
- የሙስናን ደረጃ ለመለካት የሚያስችል መሥፈርት አለመኖር
- የታክስ ገቢን መሰወር

*ደካማ የመንግስት አስተዳደር*

- የዴሞክራሲ ያለመኖር
- የመንግስትን እንቅስቃሴ ሊከታተሉ የሚችሉ የሲቪል ማህበራትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አለመኖር
- ዜጎች በምርጫ ወሳኝ ድምፅ ያላቸው መሆኑን አለማወቃቸው (የፖለቲካ ተሳትፎ ደካማነት)
- ደካማ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት
- የህግ የበላይነት አለመከበር
- የህግ ሙያ ደካማነት
- የዳኝነት ነፃነት አለመኖር
- ጠቃሚ መረጃ ለሚሰጡ ዜጎች በመንግስት የሚሰጠው ከለላ ደካማ መሆን
- የተሻለ አፈፃፀም ካላቸው አገሮች መልካም ተሞክሮዎችን የመቅሰም ልምድ አለመኖር

*አመቺ ያልሆኑ አሰራሮች*

- ኃላፊዎች በገንዘብ ላይ እንዳሻቸው የሚያዙ መሆናቸው
- ቁጥጥር የማይደረግባቸው ግዙፍ ኢንቬስትመንቶች መኖራቸው
- በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ሲሸጡና ወደ ግል ባለሀብትነት ሲዛወሩ ተገቢው ጥንቃቄ አለመደረግ

- ለመንግስት ሠራተኞች የሚከፈለው ደሞዝ ዝቅተኛ መሆኑ
- በመንግሥት ፈቃድ የሚካሄዱ የንግድ ሥራዎች ግለሰቦችን ለጉቦና ለጥቅማ ጥቅም መገፋፋታቸው
- አንድ የመንግስት ሠራተኛ ለረጅም ዓመታት በአንድ ቦታ መሥራቱ ከደንበኞች ጋር ለመቀራረብና ወደ ሙስና እንዲያመራ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርለት መሆኑ
- ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡ የፖለቲካ ቅስቀሳዎች
- በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማይታገዝ የሲቪል ሰርቪስ
- የተፈጥሮ ጥሬ ሀብትን ወደ ውጭ በመላክ ሂደት የሚገኘው ጉርሻ ሠራተኞችን ለሙስና መገፋፋቱ
- ጦርነትና ግጭት የህዝብ ደህንነቱን አደጋ ላይ መጣላቸው

***መልካም ያልሆኑ ማህበራዊ ግንኙነቶች***

- ለራሱ ጥቅም ብቻ የሚሠራ የጥቂት ስብስቦች ቡድን መኖር
- በቤተሰብና ቤተዘመድ የተሰባሰበ የማህበራዊ መዋቅር መኖር
- በስጦታና በጥቅማ ጥቅም መተሳሰር
- ለግለሰባዊ ብቃትና ችሎታ ከበሬታ የማይሰጥ ማህበራዊ አወቃቀር
- የመሀይምነት መንሠራፋት
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠር አንዱ ሌላውን ማግለልና አምባገሮ
- አንዱን ብሔረሰብ ብቻ ለይቶ መጥቀምና ጎጠኝነት
- በሥልጣን ተዋረድ ውስጥ የሴቶች ውክልና (በቁጥር) ማነስ

## 2. የሙስና ባሕል ምንድን ነው?

የሙስና ባሕል በገንዘብ ማጭበርበር ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ገንዘብ ከአንድ እጅ ወደ ሌላ ሳይዛወር ራስን በሙስና ማሰር እንደሚቻል ማስመር ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም እንደገና የሙስናን ትርጉም እንመልከት፡፡ ቀደም ብዬ ሙስና - “ያለአግባብ በሥልጣን ተመክቶ የህዝብን ገንዘብ ወደ ራስ ማዛወር” የሚለውን አስቀምጬ ነበር፡፡ ባብዛኛው ሙስና ላይ ትኩረት የሚሰጡ ጥናቶችም ይህንን ትርጉም መሠረት አድርገው ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡

ሆኖም ሌላ ለየት ያለ ከLectric የሕግ ቤተመጻሕፍት ያገኘሁትን ትርጉም ላስቀምጥ፡፡ «An act done with an intent to give some advantage inconsistent with official duty and the rights of the others» ትርጉሙ “ከሥልጣን ውጭ የሌሎችንም መብት በመጣስ ጥቅም ለማስገኘት የሚወሰድ እርምጃ” ሙስና ተብሎ ሊገለፅ እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡ ይህ አገላለፅ ገንዘብን ጨምሮ

ሌሎችንም የህዝብን መብት የሚቃረኑ ከሥልጣን ውጪ የሚወሰዱ እርምጃዎችንም ያጠቃልላል፡፡

በሌላ አነጋገር የሙስና ባሕል የሚያስደነግጠው ከሕግ ውጭ በሚወሰዱ ርምጃዎች ብቻ አለመገደቡና በተለይም በሕግ ከለላ ሥር ተቀምጠው ነገር ግን ከሥልጣን ውጭ፣ ከመብት ጥሰት አኳያ የሚገኘውንም ጥቅማጥቅም ያካትታል፡፡ ያላግባብ መሬት ከመንግሥት በሊዝ ወስዶ ትርፍ በላዩ ላይ ቆልሎ መልሶ መሸጥ ሕጋዊነት ያለው ቢመስልም ከጅምሩ ይህ እንዲሆንና ዕድሉንም ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይ ቡድን መስጠቱ ሥርዓቱን ከሙስና ውጭ አያደርገውም፡፡ ፍርድ ቤት ስላልተቀመ ወይ ክስ ስላልተመሰረተ ይህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሙስና ተብለው ሊጠሩ አይችሉም ለማለት ያስቸግራል፡፡

ይህን የመሳሰሉ ችግሮች በሀገራችን የሉም ለማለት አይቻልም፡፡ የአደባባይ ምሥጢር ሆነው ሕዝብ የሚነጋገርባቸው ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተወሰኑ ሰዎች ከፍተኛ ሀብት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የተወሰኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በዚህ ዓይነት አሰራር ውስጥ እንደሚሳተፉ ይሰማል፡፡ በተለይ ዛሬ በእድሜያቸው ገና ብዙ ልምድ የሚያንሳቸውን ወጣቶች ብንመለከት የሚቆጣጠሩትን የገንዘብና የሀብት ብዛት ስንሰማ ብዙዎቻችንን ማስገረሙ አይቀርም፡፡ የሙስና ባህል ስንል እንግዲህ የአስተዳደሩንም አወቃቀርና አሠራር ያካትታል፡፡ በአብዛኛው በዚህ የሙስና ባህል የሚፈረጁ 3 ዓይነት ገጽታዎች አሉ፡፡

ሀ/ የመንግሥት ድርጅቶች ሙስናን ለማካሄድ የተመቻቹ ሲሆኑ፤

ለ/ የመንግሥት ፖሊሲ አወጣጥና አፈፃጸም ሙስናን ለማራመድ እንዲችሉ ሆነው ሲደነገጉ «ለምሳሌ ለህዝብ የሚጠቅሙ መረጃዎች እንዳይለቀቁ ሲደረግ»፤

ሐ/ የመንግሥት ዋና ዋና አወቃቀርና አሰራር ለሙስና ሲያመች፣ ለምሳሌ የሕግ አወጣጥ ፈጽሞ በወገንተኝነት ሲደነገግ ወይ ያለ ተሳትፎ በአንድ ቀን ተረቆ በአንድ ቀን ሲጸድቅ፣ የፓርላማ ውሳኔዎች እንዲጣሱ ሲደረግ ወዘተ... በአጠቃላይ ሊደረግ የተፈለገውና ሊደረግ የታቀደው በፍጹም ሳይገናኙ ሲቀር ለሙስና ባሕል መስፈን በር ይከፍታል፡፡ የድርጅት መሪዎች በችሎታቸውና በእውቀታቸው ሳይሆን በዓይናቸው ቀለም ሲመረጡ፣ የሚያመጡት ለውጥ ለሀገር ሳይሆን የተወሰነ ግለሰብ ወይ ቡድን ለመጥቀም መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ባጭሩ የሙስና ባሕል በመጠኑም ቢሆን የሚያመጣው ብልሹ ሥርዓት አደገኛነቱ ሀገር ከመበታተንና ከማፈራረስ ወደ ኋላ አይልም፡፡ ሥርዓት ፈርሶ አስተዳደር በጥቅሻ ወይ በፍጥጫ ወይ ራስ በማወዛወዝ የሚገፋ ከሆነ መዘዙ እንዲህ ቀላል አይሆንም፡፡

## 3. ሙስና ምን ያህል ተንሰራፍቷል?

የሙስናን ትርጉም ጥርትና ግልፅ ባለመልኩ ማስቀመጥ አስቸጋሪ እንደሆነ አይተናል:: ሙስና በባህሪው ውስብስብና ዘርፈ ብዙ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል::

"ሙስና ምንድን ነው?" የሚለው አወዛጋቢ እንደሆነ ሁሉ የሙስና ደረጃዎችም በተመራማሪዎች ዘንድ ጥናት እየተደረገባቸው ናቸው:: ለምሣሌ እ.ኤ.አ. በ2003 ዓ.ም በኡጋንዳ የተካሄደውን የሙስና ደረጃ ጥናት መጥቀስ ይቻላል::

በጥናቱ መሠረት በአገሪቱ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት የግል ድርጅቶች ወይም ኩባንያዎች ሥራቸውን ለማከናወን ለባለሥልጣናት ጉቦ እንደሚሰጡ ተደርሶበታል::

በ2004 ዓ.ም በኡጋንዳ የትምህርት ፕሮግራም ላይ በተካሄደው የሙስና ደረጃ ጥናትም አስገራሚ ውጤት ተገኝቷል:: እ.ኤ.አ. ከ1991-1995 በአገሪቱ በሚገኙ 250 ትምህርት ቤቶች ላይ በተደረገው ጥናት ከማዕከላዊው መንግስት ለትምህርት ቤቶች የትምህርት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከተላከው ገንዘብ ውስጥ ትምህርት ቤቶች ያገኙት 13 በመቶ የሚሆነውን ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል:: እንዲያውም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከተላከው ገንዘብ ውስጥ ምንም እንዳልደረሳቸው ታውቋል:: 87 በመቶ የሚሆነውን የአካባቢው ባለሥልጣናትና ፖለቲከኞች እንደተቀራመቱት በጥናቱ ተደርሶበታል::

ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ለመንገዶች ግንባታ ከሚመደበው ገንዘብ ውስጥ 29 በመቶ የሚሆነው በሙሰኛ ባለሥልጣናት እንደሚዘረፍም በጥናት ተረጋግጧል:: በኢንዶኔዥያ በፀረ-ድህነት ፕሮግራም ላይ በተደረገ ጥናት ለድሆች ከሚሰጠው የሩዝ ድጎማ ውስጥ 18 በመቶው ሙሰኞች ኪስ እንደሚገባ ታውቋል::

የሙስናን ደረጃ ለማወቅ ተመሳሳይ ጥናት በኢራቅ ተካሂዶ ነዳጅ ለምግብ ከሚባለው ፕሮግራም 4 ቢሊዮን ዶላር እንደተመዘበረ ታውቋል:: በአርጀንቲና ዋና ከተማ በቦነስ አይረስ ከተማ ለመንግስት ሆስፒታሎች ግብአት የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ለማሟላት በተደረገው የግዢ ሂደት ከፍተኛ ምዝበራ መካሄዱ ተደርሶበታል::

የሙስና ደረጃዎችን በመጠንና በዓይነት የመለየቱ ጥናት አሁንም ገና የዳበረ አይደለም:: እየተካሄዱ ያሉት ጥናቶች የተበታተኑና በአንድ የተለየ ርዕስ ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ናቸው:: በአብዛኛው ከንግድ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ነዋ ትኩረቱ:: በሌላ አነጋገር ንግድንም ሆነ የመንግስት ሥልጣንን ለመቆጣጠር ሙስና ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ተገኝቷል:: የዓለም ግዙፍ ድርጅቶች (MNCs) ንጥቂያቸውን ለማካሄድ ከሙስና ውጭ አማራጭ እንደሌለ አድርገው ሲንቀሳቀሱ የመንግሥትን ማዕከላዊ ሥርዓት የሚቆጣጠረውም በተዋረድ ሥልጣኑን ለማጠናከር በሙስና ላይ የተመሰረተና ሕግን ከለላ ባደረገ መልኩ ሁኔታዎችን ሲያመቻች ይታያል:: የሙስና ባሕል የሚፈጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው::

## 4. ከፍተኛ የደሞዝ ክፍያ ሙስናን ይቀንሳል?

የተለያዩ እርዳታ ሰጪና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለመንግስት ሠራተኛው ደሞዝ በመጨመር ሙስናን መከላከል ይቻላል የሚል እምነት አላቸው:: ለዚህ ደግሞ እንደምሳሌ የሚጠቅሷት ስዊዲንን ነው:: ስዊዲን በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በከፍተኛ ሁኔታ በሙስና ከተዘፈቁ አገራት መካከል አንደኛዋ ነበረች:: በስዊዲን የሠራተኛውን ደሞዝ በመጨመር፣ ማነቆ የሆኑ መመሪያዎችን በማስወገድ፣ የመንግስት ሠራተኛውን ተወዳዳሪነት በመጨመር፣ ሠራተኛው ለራሱ ያለው ክብር ከፍ እንዲል በማድረግ ሙስና እየቀነሰ ሄዶ አገሪቱን አሁን ላለችበት የላቀ ደረጃ ማድረስ መቻሉ ይገለፃል::

ሌሎች ወገኖች ደግሞ ተገቢው ተቆጣጣሪ አካል በሌለበት ሁኔታ ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ ማድረግ የሙሰኛውን ለሙስና የመደራደር አቅም ያሳድግለታል ባይ ናቸው:: ከፍተኛ ደሞዝ የሚከፈለው ጉቦ ተቀባይ ከጉቦ ሰጪው ጋር ሲደራደር ደሞዙን እንደ መነሻ ሊጠቀምበት ይችላል:: «እኔ እኮ ይህንን ያህል የሚከፈለኝ ሰው ነኝ» ሊል ይችላል:: ስለዚህ ጉቦ ሰጪው ጉዳዩን ለማስፈፀም ሙሰኛው አሁን እያገኘ ካለው ደሞዝ በላይ ለመስጠት ይገደዳል::

እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ም ሶስት ምሑራን በርካታ አገራትን ባካተተው ጥናታቸው ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ በሙስና መቀነስ ላይ የሚኖረው ለውጥ አመርቂ እንዳልሆነ አመልክተዋል::

ሌሎች ምሑራን ደግሞ የደሞዝ ጭማሪ ስልታዊ የሆነ ቁጥጥር ከታከለበት ሙስናን በመቀነስ ረገድ ውጤት እንደሚያመጣ ያስረዳሉ:: ሠራተኛው ወይም ባለሥልጣኑ ደሞዝ ከተጨመረለት በኋላ ከደንበኞች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ስልታዊ በሆነና ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል ባይ ናቸው::እንዲህ ከተደረገ ያለጥርጥር ሙስናን በመቀነስ ረገድ ለውጥ ሊመጣ ይችላል ይላሉ::

በቅርቡ በአገራችን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ መደረጉ ይታወሳል:: ይህ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀው ጭማሪ በኢትዮጵያ የመንግሥት ሠራተኞች የደሞዝ ስኬል ታሪክ ሪከርድ የሰበረ ነው:: ለሙስና በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ለሆነው ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች የተፈቀደው ይህ ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ ባለሥልጣኑ ይታማበት የነበረውን ሙስና ይቀንሰው እንደሆን ወደፊት የምናየው ይሆናል::

## 5. ውድድር ሙስናን ሊቀንስ ይችላል?

በመሠረቱ ውድድር ግልጽነትን፣ መረጃ የማግኘት ዕድልን በመክፈት ሙስናን ለመቀነስ ከሚመረጡ መሣሪያዎች አንዱ ነው:: ለምሳሌ በአዲስ አበባ የውል ምዝገባና የሰነድ ማረጋገጫ መሥሪያ ቤት ቅርንጫፍ መክፈቱን በውድድር መልክ ብንመለከተው ተገልጋዩ የሚፈልገውን አገልግሎት ከተሻለው ቅርንጫፍ ሊያገኝ በመቻሉ ሙስና እንዳይስፋፋ ይረዳል ተብሎ ይገመታል::

በሌላ በኩል በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ውድድር መኖሩ ደግሞ ሙስናን በመቀነስ ረገድ አነስተኛ ሊሆን ይችላል:: በኡጋንዳ የትምህርት

ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ላይ የተፈፀመውን ሙስና እንደምሳሌ እንውሰድ:: በየምክንያቱ ትምህርት ቤቱ ዋጋ ቢጨምር በዚህ ረገድ ወላጆች ሁለት አማራጭ ነው ያላቸው:: አንድም ቅሬታቸውን ለበላይ አካል መግለፅ (ሊያውም የሚሰማቸው ከተገኘ) አለበለዚያ ደግሞ ልጆቻቸውን የትምህርት ፕሮግራም ማስፈፀሚያው በጀት ከተበላበት የመንግስት ትምህርት ቤት አስወጥተው በግል ትምህርት ቤት ማስገባት ነው::

ወላጆች ልጆቻቸውን ከመንግስት ት/ቤት አስወጥተው ተወዳዳሪ በሆኑ የግል ትምህርት ቤት አስገብተው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ካደረጉ ሙሰኞቹ ባለሥልጣናትና ፖለቲከኞች ለለቀቁት ተማሪዎች ወጪ ይደረግ የነበረውን በጀት ጨምረው ይበሉታል::

## 6. የፀረ-ሙስና ትግል ለምንድነው በጥቂቱ ብቻ ውጤታማ የሆነው?

አብዛኞቹ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች በፍትህና ዳኝነት ሥርዓቱ፣ በፋይናንስ የኦዲት ተቋማት፣ በፖሊስና በመሳሰሉት ተቋማት ድጋፍና እገዛ ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: አሳዛኙ ነገር ግን በአብዛኞቹ ድሀ አገራት እነዚህ ተቋማት ወይ ደካማ ወይ ራሳቸው በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸው ነው::

ሌላው ሙስናን የሚዋጉ ማዕከሎች ጥረታቸው ትምህርት ወይ ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት በማያስችሉ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ነው:: ለቴሌቪዥንና ለሬድዮ ማስታወቂያዎች እንዲሁም ለስብሰባዎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ርብርብ ያደርጋሉ:: አልፎ አልፎ የተወሰኑ ሰዎችና ድርጅቶች በሙስና ሊጠየቁ መሆኑን የሚገልጹ ዜናዎች ይቀርባሉ:: የነዚህ ተጠርጣሪዎች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምን ደረሰ ለሚለው ጥያቄ መልስ የለም:: በሌላ አነጋገር የሙስና መንስኤው ቀርቶ እንዲሁ ዙሪያ ዙሪያውን ብቻ በመሽከርከር በተወሰኑ ግለሰቦች ላይ ባተኮረ ዘመቻ ጊዜው ይባክናል:: ይህ የብዙ ሰዎች አስተያየት ነው::

ሥልጣን ላይ የተቀመጡ የመንግሥትም ሆኑ የፖርቲ ሰዎች ሙስና ምን ያህል እንደተንሰራፋ ሳያውቁ ቀርተው አይደለም፣ ነገር ግን ለጊዜው ዝም ማለቱን የተሻለ ሆኖ ያገኙት ይመስላል::

ባጭሩ ሙስናን በሁለት መልኩ መዋጋት ይቻላል፡-

1ኛ. ሙስናን ራሱን መዋጋት

2ኛ. በሙስና የተዘፈቁትን መዋጋት ናቸው

በሌላ አነጋገር ሙስናን መዋጋት ማለት ጠቅላላ ሥርአቱንና (ሲስተሙን) መነሻውን (Cause) የሚያካትት ሲሆን ሙሰኞችን መዋጋት ደግሞ ውጤቱን (Consequence) ወይም ግለሰቡን በመታገል ላይ ያተኩራል:: ለህዝቡ "አበበ" "ታፈሰ" "ግርማ" የተባሉት ሰዎች እስራት ወይ ሞት ተፈረደባቸው ብሎ

መግለጽ ሙስናን አያጠፋውም፣ ይገታው ይሆናል። መሠረቱ ወይም መንስኤው ካልተስተካከለ ሌሎች ሙሰኞች በተራቸው መቅረባቸው አይቀርም።

ስለዚህ ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ካሁኑ ሀገር ከመፈራረሱ በፊት ሙስናን የሚያከስሙ ለውጦችን ማካሄድ የግድ ይላል። እስቲ ልብ በሉ። በትምህርት አካባቢ የሰፈነው (Intellectual) የዕውቀት ሙስና፣ በኃይማኖት ድርጅቶች ዙሪያ የሚታየው ሙስና፣ በግልጽ በመንግሥት መ/ቤቶች እየተስፋፋ ያለው ሙስና ቢገታ፣ በብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካ ላይ የተንሠራፋው ሙስና ቢመከት ምን ዓይነት የተከበረች ሀገር ልትኖረን እንደምትችል መገመት አይሳንም።

## 7. ሙስና በእድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል?

ሙስና በዕድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች ለንግድም ሆነ ለምርት እንቅስቃሴ ማነቆ የሆነ ቢሮክራሲ ባለበት የመንግስት አስተዳደር ውስጥ ውጤታማ የሆኑ የግል ድርጅቶች ጉቦ በመስጠት ሥራቸውን ማቀላጠፍ ይችላሉ ባይ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ወገኖች ከአንድ የግል ድርጅት ወይም ተቋም እውነተኛ ትርፍ በሙስና በሚወሰድበት ወቅት ድርጅቱ መደበኛ ወዳልሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገባ ይችላል ይላሉ። ሙስናው የከፋ ሲሆን ደግሞ የግል ሥራ ያንቀሳቅሱ የነበሩ ግለሰቦች ድርጅታቸውን ዘግተው ራሳቸውን ለሙስና በሚረዳ መልኩ የሚያንቀሳቅሱበት አጋጣሚ ይኖራል።

አንድ ምሑር እ.ኤ.አ. በ1981 ዓ.ም ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት ላይ ባደረገው ጥናት ገበሬዎች መላ ባጣ ሙስና ምክንያት የተትረፈረፈ ምርት ከማምረት ታቅበው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ምርት ወደ ማምረት ደረጃ እንደደረሱ ያመለክታል። በዚህም ምክንያት የምግብ እህል ምርት መቀነስና የኑሮ ደረጃ የማሽቆልቆል ሁኔታ ታይቷል። የላቲን አሜሪካ አገር በሆነችው በፔሩ በከፍተኛ ሙስና ምክንያት የማምረቻ ተቋማት ወደ ስውርና ጥቃቅን ተቋምነት ተለውጠው ከሙሰኞች ለማምለጥ ጥረት ማድረጋቸው ይጠቀሳል።

እ.ኤ.አ. በ2001 ዓ.ም በተደረገ አንድ ጥናት ደግሞ በኢንዶኔዥያ አንዳንድ ተቋማት በፖለቲካ ንቅዘትና በሙስና ከመማረራቸው የተነሳ ራሳቸው ሙሰኝነት ተጠናውቷቸው የኪራይ ሰብሳቢነትንና ሌሎች የሙስና መገለጫ ባህርያትን መላበሳቸውን አመልክቷል።

ሙስና በዕድገት ላይ ከሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ይልቅ ጉዳቱ በግልፅ እየታየ ያለው በማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ላይ መዳከምን የሚፈጥር መሆኑ ነው። ስለዚህም ሙስና በተንሰራፋባቸው አገሮች በተለይም በድሆቹ ላይ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት የተመናመነ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው።

ሙስናና የግል ድርጅቶች ቁርኝትን በተመለከተ ግን በግል ድርጅቶች ላይ የሚከሰት የአንድ በመቶ የጉቦ ጭማሪ የተቋሙን ዕድገት በሶስት በመቶ እንደሚቀንሰው ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም በመንግስት ታክስ ጫና ከሚፈጥረው በሶስት ዕጥፍ የሚበልጥ መሆኑን ነው የሚያሳየው።

እንዲህም ሆኖ ግን ሁሉም ዓይነት ሙስናዎች ለዕድገት ጎጂዎች ናቸው ማለት አይቻልም የሚሉ ወገኖች አሉ። የትኞቹ ዓይነት ሙስናዎች በዕድገት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ለይቶ ማወቅ ይገባል ባይ ናቸው። ለዚህ አባባል እንደምሳሌ የምትጠቀሰው ቻይና ነች። በቻይና ሙስና አለ። ነገር ግን ቻይና በየዓመቱ በከፍተኛ ሁኔታ ዕድገት እንዳታስመዘግብ አላገዳትም።

በእኛም ሀገር ሙስና ተንሰራፍቶም ባለፉት ተከታታይ አምስት ዓመታት ባለሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት እንደተመዘገበ ተደምጧል።

## 8. በከፍተኛ ሙስና የተዘፈቁ አገራት ባህርያት ምንድን ናቸው?

ሁሉም በከፍተኛ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው የሚገኙ አገራት ታዳጊ አገሮችና በሽግግር ኢኮኖሚ ላይ የሚገኙ አገሮች መሆናቸው ተደርሶበታል። የሚያስደንቀው ደግሞ አብዛኞቹ በከፍተኛ ሙስና ውስጥ ያሉ አገራት በሶሻሊስት መንግስታት የሚመሩና ሲመሩ የነበሩ መሆናቸው ነው። ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኞቹ የሙስና ስለባ የሆኑ አገሮች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ናቸው።

እ.ኤ.አ. በ1995 በተደረገ ጥናት መሠረት ከኢንዶኔዥያ በስተቀር አብዛኞቹ ሙስና የተንሰራፋባቸው አገሮች ዝግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚጠቀሙ ናቸው። በጥናቱ መሠረት ዝግ ኢኮኖሚ ተግባራዊ ከሚሆንባቸው ነጥቦች መካከል፣ አገራቱ ከ40 በመቶ በላይ የትርፍ መጠን ያላቸው መሆኑ፣ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸው፣ የወጪ ንግዱ በመንግሥት ሞኖፖሊ የተያዘ መሆኑና የጥቁር ገበያ መደበኛ ምንዛሪውን እስከ 20 በመቶ የሚበልጥ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም የነፍስ ወከፍ ገቢና የትምህርት ሥርጭትም አንዲት አገር በሙስና ረገድ ያለችበትን ሁኔታ ሊጠቁም እንደሚችልም ተመልክቷል። ለምሳሌ ትምህርትና የሰው ሀብት እንደ ፍርድ ቤትና የመሳሰሉትን ተቋማት በተገቢው ሁኔታ ለማንቀሳቀስ አስፈላጊ ናቸው። የአንድ አገር ህዝብ በአመዛኙ መሐይም ከሆነ የዚያ አገር መንግስት ብሔራዊ ምርጫዎችን በቀላሉ ለማጭበርበር ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል። የተማረ ሰው በሌለበት ሁኔታ ሙሰኛ መንግሥታትን የሚፈታተን ማህበረሰብ አይኖርም።

የጐረቤት ሀገር ኬንያን ብንወስድ ሙስና በመንግስት ደረጃ የተንሠራፋ ሆኖ እናገኘዋለን። ኬንያ የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሔር ሳይሆን በIdeology (የፓርቲዎች ሥም እንደሚያመለክተው) ተቋቁመው የሚወዳደሩባት ሀገር ናት። በመጠኑም ቢሆን በኢኮኖሚዋ ጠንካራ ከሚባሉት የአፍሪካ ሀገሮች ትመደባለች። የሥልጣን ሥርዓቱን ስንመለከት ግን እያንዳንዱ ብሔር “በተራ በተራ እንብላ” የሚል መርሆን ተከትሎ የሚንቀሳቀስ ይመስላል። በጆሞ ኬንያታ ዘመን ኩኩዩ፣ በሞይ ዘመን ካሌንጂን ባለፈው በኪባኪ ዘመን ኩኩዩ ተመልሰው ሥልጣን ሲይዙ አሁን በቅርቡ ደግሞ የኦዲንጋ ፓርቲ በተደረገው ምርጫ ተራዬን ተቀምቻለሁ በሚል የተነሳው ግጭት እና ያስከተለው ጭፍጨፋ የሙስና መገለጫ ሆኖ ይታያል።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በሃይማኖት እና በብሔር የተለያዩ ህብረተሰቦች በሚኖሩበት፣ የባሕል ልዩነቱና የህዝብ አስተሳሰብ በብሔር በሚለያይበት ሀገር ሙስናን ለመቆጣጠር እንደሚያስቸግር ግልጽ ይመስለኛል። ማን በማን ክልል ሊያዝ? ቅድሚያስ የሚሰጠው ለየትኛው ወገን ይሆናል?

## 9. የትኞቹ አገራት በከፋ ሙስና ውስጥ ይገኛሉ?

ሙስና በተፈጥሮው በስውር ወይም በድብቅ የሚካሄድና ዘርፈ ብዙ ገፅታ ያለው በመሆኑ በያንዳንዱ አገር ያለውን የሙስና ደረጃ ተንትኖ በማወቅ ደረጃ መስጠት ቀላል ተግባር አይደለም። ሆኖም ኢንተርናሽናል ካንትሪ ሪስክ ጋይድ፣ ትራንስፖረንሲ ኢንተርናሽናል፣ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ፖስዋ እና ፖለቲካል ሪስክ ሰርቪስ የተባሉ ተቋማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ባደረጉት ጥናት በከፋ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው የሚገኙ አገራት ተለይተዋል።

በመጨረሻዎቹ የሙስና አረንቋ ውስጥ የሚዳክሩ አገራት ከ1ኛ እስከ 10ኛ ደረጃ የተሰጣቸው ሲሆን ለምሳሌ 1ኛ ደረጃ ውስጥ ሁለት አገራት ይገኛሉ። በዚህም መሠረት 1ኛ ሶማሌና ማይንማር (በርማ)፣ 2ኛ ኢራቅ፣ 3ኛ ሃይቲ፣ 4ኛ ቶንጋና ኡዝቤክስታን፣ 5ኛ አፍጋኒስታን፣ ቻድ፣ ሱዳን፣ 6ኛ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ኢኳቶሪያል ጊኒ፣ ጊኒ፣ ላኦስ፣ 7ኛ ባንግላዴሽ፣ ካምቦዲያ፣ ማዕከላዊ አፍሪካ፣ ፓፑዋ፣ኒው ጊኒ፣ ቬንዚዌላ የተጠቀሱ ሲሆን አገራችን ኢትዮጵያም ከካሜሩን፣ ከፓኪስታን፣ ከፓራጓይና ከሶርያ ጋር በመሆን በደረጃ ትገኛለች።

ከ190 የዓለም ሀገራት ውስጥ 180ዎቹ በዚህ ጥናት የተካተቱ ሲሆን በጥናቱ በ9.4 ነጥብ እጅግ ዝቅተኛ ወይም ምንም ሙስና የለባቸውም ተብለው በአንደኝነት የተቀመጡት ኒውዚላንድ፣ ዴንማርክና ፊላንድ ሲሆኑ ማይናማር እና ሱማሌ ከ180 አገሮች 2 ነጥብ በማምጣት 179ኛ ወጥተዋል። በዚህ የሙስና ደረጃ ልኬት ኢትዮጵያ ከ180 አገሮች 2.4 ነጥብ በማግኘት 138ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይህ ማለት በሙስና ደረጃቸው (ሙስናን በመቆጣጠር) የተሻሉ የሚባሉ 137 ሀገሮች ከፊቷ ይገኛሉ ማለት ነው። በዚህ የሙስና ደረጃ ስሌት መሠረት ከ5 ነጥብ በታች ያገኙ አገሮች በከፋ የሙስና ቀለበት ውስጥ የሚገኙ ተብለው የተፈረጁ ናቸው። ኢትዮጵያም ከዓለም በሙስና እግር ከወርች ከተተበተቡ 10 ቀንደኛ ሀገራት ቀጥላ ነው የምትገኘው።

የአገራችንን የሙስና ደረጃ ያወጡት ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት ዓለም አቀፍ ተቋማት ደረጃዎቹን ለማውጣት ሶስት መሥፈርቶችን የተጠቀሙ ሲሆን መሥፈርቶቹም የሙስና አመለካከቶችና የሙስና ቁጥጥር መለኪያዎች ናቸው። ተቋማቱ እነዚህን መለኪያዎች በመጠቀም አገራቱን ሙስና ከተንሰራፋባቸው ምንም ወይም ጥቂት ሙስና ካለባቸው አገሮች ድረስ በደረጃ አስቀምጠዋል።

በመሥፈርቱ መሠረት አገራችን ያለችበት ደረጃ አሳሳቢ በመሆኑ እኛስ እንደ ህዝብና እንደ ሀገር ምን እናስባለን? በቀጣዮቹ ገጾች በኢትዮጵያ ያለውን የሙስና ገፅታና መወሰድ ስላለበት እርምጃ እንቃኛለን።

# 10. በሙስናና በባሕል መካከል ግንኙነት አለ?

መንግስታት የሙስና ባሕል (ልማድ) ዜጎችን ከድህነትና ኋላቀርነት አዙሪት ውስጥ እንደሚከት በአፅንኦት ያመለክታሉ። ስለሙስና ባህል ከመናገራችን በፊት ግን የሙስና ባሕልን ትርጉም ማስቀመጥ ተገቢ ነው። የሙስና ባሕል በአንድ አገር አለ የሚባለው የመንግስት ሠራተኛውና ህብረተሰቡ ሙስናን ለመሸከም ፈቃደኛ ሲሆን ነው።

በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ታዳጊ አገሮች የሙስና ባሕል አለ ወይም የለም ብሎ እቅጩን ለመናገር አከራካሪ ነው። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሙስና ለአገሪቱ አስፈላጊና ጥሩ ነገር ነው ብሎ አያምንም። ሆኖም ግን የአገሪቱም ሆነ የሌሎች የታዳጊ አገር ዜጎች ጉዳያቸውን ለማስፈፀም ወይም ለመፈፀም ጉቦ አይሰጡም ወይም አይቀበሉም ማለት አይደለም። ይህም ሆኖ ግን ሙስናን ተቀብለውታል ወይም አብሯቸው እንዲኖር ፈቅደዋል ማለት አይደለም። እንዲያውም ሲያወግዙት ይደመጣል።

አገራችንን ጨምሮ ሙስና በእጅጉ በተንሰራፋባቸው የአፍሪካ አገራትና በሌሎች ድሆችና ታዳጊ አገራት በሰፊው ህዝብ ዘንድ የሙስና ባህል አለ ብሎ በግልፅና በትክክል ለመደምደም አይቻልም። ህዝባችን ጫንቃው ሙስናን ለመሸከም ይችላል ወይም ፈቃደኛ ነው ልንል አንችልም። ምክንያቱም ሙስና የህዝብን በራስ የመተማመን መንፈስ ያጠፋልና። ነገር ግን ህዝቡም ሆነ የፖለቲካ መሪዎች በዚህ ጉዳይ የሚገልጹት፣ የሚጽፉትና የሚከራከሩበት ባለመሆኑ ሙስናን ተቀብለን የምንኖር ያስመስልብናል። በተለይም በብሔር ዙሪያ የሚታየውን የሙስና ባሕል ማውገዝ አለመቻላችን አልፎም ለማጥፋት አለመሞከራችን አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ይታየናል።

## 10.1 የሙስና ባሕል በመንግስት ቢሮክራሲ ውስጥ

በአገራችንም ሆነ በሌሎቹ የሙስና ሰለባ በሆኑ አገሮች በዝቅተኛው የመንግስት አስተዳደር ዘንድ ጉቦ መቀበልና ሌሎችም የሙስና ዓይነቶች የዕለት ተዕለት ሥራን እንደሚያቀላጥፉ ተደርገው መታሰባቸው አይቀርም። ህብረተሰቡ በነዚህ የሙስና መገለጫዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ ፍላጎት እንዳለው ሁሉ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘው የመንግስት ሠራተኛም ሙስና ቢወገድ የሚጠላ አይደለም።

በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ዘንድ ግን የሙስና ጉዳይ በተራቀቀ ስልት የሚካሄድ ነው። በባለሥልጣናቱ ዘንድ በላቀ ደረጃና ምቾት ባልተለያቸው ቅንጡ ሥፍራዎች ሙስና ይፈፀማል። እነዚህ ወገኖች ሙስናን የሚያካሂዱት ተፅዕኖ በማሳደር፣ በማግባባትና የኪራይ ሰብሳቢነት በተጠናወተው መንፈስ ነው። በዚህ ደረጃ የሚፈፀመው ሙስና ግን የሥራ አስኪያጆች ትዕዛዝ፣ የአስተዳደር ውሳኔ፣ ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሉ ታፔላዎች ተለጥፎባቸውና የህጋዊነት ካባ ተላብሰው ነው። ሙስናው በሙሉ በህጋዊ ሽፋን የተፈፀመ በመሆኑ በህግ ፊት ክስ ሊመሠረትበት ከቶ አይችልም።

በታዳጊ አገሮች በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ለሚፈፀሙት ሙስናዎች አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው የሹመት አሰጣጥ ጉዳይ ነው:: በቢሮክራሲው ውስጥ ሙስና ሥሩን በሰደደባቸው የአፍሪካ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ አገራት ባለሥልጣናት የፈለጉትን ለመሾም የሚያዳግታቸው ነገር የለም:: በህግ በተሰጣቸው ሥልጣን በመጠቀም በችሎታም ሆነ በትምህርት ደረጃው ለቦታው ብቁ ያልሆነ ሰው በወገንተኝነት፣ በጥቅማ ጥቅምና በዘመድ አዝማድ በመሳሳብ ይሾማሉ:: ለዚህም ነው በነዚህ አገራት ምንም የአመራር ብቃትና መልካም ሥነ-ምግባር ሳይኖራቸው ለሥርዓቱ ታማኝ በመሆናቸው ብቻ በርካታ ሰዎች በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚቀመጡት:: እነዚህ ሰዎች በተመሳሳይ መልኩ በሥራቸው ለእነሱ የሚያጎበድዱና ተላላኪ የሚሆኑ ምስለኔዎቻቸውን ይሰገስጋሉ::

በዚህ መልክ የየአገራቸውን ፖለቲካና ኢኮኖሚ የሚመሩና የሚቆጣጠሩ ብልሹና በሥልጣን የባለጉ ሰዎች የሙስና ባሕል ሥር እንዲሰድና እንዲስፋፋ ያደርጋሉ:: የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቅማቸውን እንዲሁም ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ እንጂ ህዝባቸውን በልማትና በዴሞክራሲ ጎዳና ለመምራት አይጠቀሙበትም:: ይህ ባህሪያቸው ሁሉንም ያመሳስላቸዋል:: ተመሳሳይ ባህሪም ስላላቸው የቱንም ያህል እርስ በእርስ ባይዋደዱ ለራሱ ህልውና ሲል አንዱ ለአንዱ ከለላ ይሰጣል:: አንዱ ሌላውን በምንም አይነት አሳልፎ አይሰጥም::

ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥት ትላልቅ ፕሮጀክቶችን አከናውኖ ጥሩ ውጤቶችን ያስመዘገበባቸው ሥራዎች እንዳሉ እናያለን :: ነገር ግን ሙስናን በሚመለከት የተደረገው ጥረት ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር የህዝብን ቀልብ ስቦ ውጤት ለማምጣት የቻለ አይደለም:: ገና ብዙ ይቀረናል::

## 10.2 የባሕል ንቅዘት

ባሕል (ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው) በአንድ ወቅት የሚከሰት ሁኔታ ሳይሆን በህዝብ ድጋፍ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፍ የራሱ የሆነ ባህርይና ይዘት ያለው ውጤት ነው:: ባሕል ይቀየራል፣ ነገር ግን በአንድ ጊዜ አይደለም:: ከኢኮኖሚውና ከንግዱ ጋር የተያያዙ የአኗኗር ዘይቤዎቻችን በሙስና ሊቀየሩ እንደሚችሉ ዛሬ እንገነዘባለን:: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከልክ በላይ ትርፍ ለመሰብሰብ መሻት፣ ሳይሰሩና ሳይደክሙ ሀብት ማካበት፣ ጎረቤት፣ ሠፈርተኛ፣ ወይ ሀገር ሲጎዳ አይመለከተኝም ብሎ መቀመጥ ከሙስና የፈለቁ ሙስናን የሚያስፋፉ ባህሪዎች ይሆናሉ::

በርካታ ሰዎች እንደሚሉት ቀድሞ በሀገራችን የነበረው ከዘመድ፣ ከጐረቤትና ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ተሳስቦና ተፋቅሮ የመኖር ልማድ በተለይ በከተሞች አካባቢ እየተዳከመ ነው:: ከዚህ ቀደም ሀብታሙና ደሀው በአንድ ሰፈር ውስጥ በእድር፣ በእቁብና በማህበር ተሰባስቦ ይኖር ነበር:: ዛሬ ያ መልካም ባሕል ደብዝዞአል:: ሀብታሙና ደሀው ማህበራዊ ሕይወታቸውና የመኖሪያ ሰፈራቸው እየተለያየ ነው:: በማህበረሰብ ውስጥ ከዚህ ቀደም የነበሩት ይሉኝታ፣ ሀቀኝነት፣ ሞራልና ግብረ ገብነት እየተዳከሙ የባሕል መዝቀጥ ተምሳሌት በሆኑት ራስ ወዳድነት፣ አስመሳይነት፣ ከራስ በላይ ንፋስ አመለካከቶችና እኩይ ባህርያት በመተካት ላይ ናቸው::

የሙስና ባሕል (የባሕል መዝቀጥ) እንደ ሌላው የሙስና ዓይነት ጉቦ ከመስጠትና ከመቀበል ወይም ከሌሎች የሙስና መገለጫዎች ጋር ተነፃጽሮ የሚታይ አይደለም። አንድ ባለሥልጣን ወጥ በሆነ አሰራር አገልግሎት የማይሰጥና የሌሎችን መብት የሚጥስ ከሆነ ይህ ሙስና ነው። ግን እንደ ጉቦ ከመሳሰሉ የገንዘብ ልውውጥ ከሚታይባቸው ክንውኖች የተለየ ነው። ባለሥልጣኑ በዚህ ሙስና ስላልተከሰሰ ብቻ ሙስና አልሰራም ለማለት አይቻልም።

በርካታ ሰዎች ከሚሰጡት አስተያየት ብንነሳ በሀገራችን በመንግስት አካላት ዘንድ የሙስና ባሕል ተንሰራፍቶ እንደሚገኝ እንገነዘባለን። (ስለ ሙስና የሚያጠኑ የዓለም አቀፍ ተቋማትም የህዝቡን አስተያየት እንደ አንድ መለኪያ ስለሚጠቀሙበት እኛም ህዝቡ ስለሙስና የሚያስበውንና ከምልከታ (Observation) የተገኘውን ማካተታችን ተገቢ ነው።) የመንግስት ሠራተኛው የመንግሥትን ቢሮ የግል ጉዳዩን ማስፈጸሚያና ርእዮተ ዓለማዊ አመለካከቱን ማራመጃ አድርጐ ሲሰራበት ይታያል። መሬት እንዴት ለእገሌ ሰጥቶ፤ኮንትራቱን ደግሞ ለእገሌ አስጨርሶ ለራሱ ዘመናዊ መኪና ገዝቶ ኑሮውን እንደሚገፋ እንጂ ሀገር እንዴት እንደሚለማ፣ ህዝብ እንዴት እንደሚማር ወይ የሥራ ዕድል እንዴት እንደሚስፋፋ ማሰብ አቁሟል።

የመንግስት ተሿሚዎች በመንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ የፖለቲካ ሥራ ያከናውናሉ። በተለያየ ደረጃ በሚገኙ ምክር ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አባላት የግል ጥቅማቸውን ያሳድዳሉ። አብዛኞቹ የቆሙት የቡድናቸውን ፍላጐት ለሟሟላት ነው። በርካቶች እንደሚስማሙበት ይህ ሙስና ነው።

የሙስና ፅንሰ ሀሳብ አንድ መንግሥት የሚመራበትን የአስተዳደር ስልት የሚያንቀሳቅስበት ሁኔታን ሁሉ ያካትታል። አብዛኞቹ ታዳጊ አገሮች፣ የኛንም ጨምሮ ፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በፖሊሲ ቀረጻና በፖሊሲ ማፅደቅ ሂደት ውስጥ እንዲሁም በአጠቃላዩ በመንግሥት መዋቅርና የሥራ ሂደት ውስጥ ሙስና በተለያየ ዓይነትና መጠን ይንፀባረቃል።

በተለይ ሕግን ለፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መጠቀም እንደኛ ባሉ ታዳጊ አገሮች የተዘወተረ ተግባር ነው። በነዚህ ሀገሮች መንግስታት ሀገር የሚመሩት በሕግ ሳይሆን እንደ አሻጥረኞች የነሱ ጉዳይ አስፈፃሚ ከሆኑ አካላት ጋር በመጠቃቀስ ነው። በሀገራችንም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተገኙ አስተያየት ሰጪዎች ሥርዓቱ የራሱ የሆነ የሙስና ባሕል መገለጫ እንደሚስተዋልበት ያመለክታሉ።

## 10.3 የሙስና ገጽታ በኢትዮጵያ ምን ይመስላል?

በሀገራችን ሙስናን ለማጥፋት የተደረገ ዘመቻ ኖሮ አያውቅም። በርግጥ የተወሰኑ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ለማሰር ወይ ከፖለቲካ መድረኩ እንዲሸሹ ለማድረግ በተወሰነ መልኩ ሙስናን ለመዋጋት በሚል የተወሰዱ እርምጃዎች አሉ። ይህ አሰራር በፖለቲካው መድረክ ተለምዷል። ዛሬ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መሪን ወይም አንድ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኝ ኃላፊን ለማጥመድ እንዲቻል ተስተካክሎ የተቀመጠ አሰራር በመኖሩ ሁሉም በፍርሃት

ተጠምዶ የሚኖርበት ሁኔታ አለ:: የትኛው ባለሥልጣን ምን እንደሰራ፣ ምን ያህል ሀብት እንዳለው፣ ከዬት እንዳገኘው፣ በማን ባለቤትነት ሥር እንደሆነ፣ የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ እያለ ሁሉም ተቻችሎና ተፈራርቶ ይኖራል:: ተናካሽ እስከሌለ ይህ ዘመኑ ያፈራው የሙስና ባሕል ነው::

## 10.4 ሙስና በአገራችን ምን ያህል አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል?

በአገሪቱ ሙሰኞችን የማጋለጥና ለፍርድ የማቅረብ ሥራ የተጓተተና በወጪም ደረጃ ሲታይ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ ነው:: ከሚፈፀመው ሙስና ስፋት አንፃር ለፍርድ የሚቀርበውና በጥፋተኝነት የሚፈረድበት ኢምንት ነው:: ይህም ሁኔታ ህዝቡ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴውን በጥርጣሬ እንዲያይና አመኔታ እንዲያጣ በር ከፍቷል:: በሙሰኞች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ዳተኛ መሆን የህዝቡን በራስ የመተማመን መንፈስ እየሸረሸረ ከመሆኑም በላይ የሙስና ባሕል ሥር እንዲሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል::

## 10.5 የግሉ የንግድ ዘርፍና ሙስና

በሌሎች ታዳጊ አገሮች እንደሚፈፀመው ሁሉ በኢትዮጵያም በሕግ ከለላ አማካኝነት በግል የንግድ ዘርፍ አካባቢ ሙስና ሲፈፀም ይታያል:: በተለይም ባለፉት ዓመታት በፋይናንስ ዘርፍ የሚከናወኑ ተግባራት ለሙስና የሚያጋልጡ ናቸው:: ለምሳሌ የቦርድ አባላት በልዩ ሁኔታ ደንቡን ለራሳቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ሁኔታዎችን ሲያመቻቹ ይታያሉ:: ብድር ወይ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የሚከፈል "ኮሚሽን" አለ:: የሂሳብ አያያዝ ለግብር ሰብሳቢ፣ ለባንክ ብድር፣ ለራስ ሂሳብ መቆጣጠሪያ ተስተካክለውና ተለያይተው ይሠራሉ::

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በንግድ አካባቢ የሚታየው ሂደት በፍጥነት ሳይደክሙና ሳይለፉ ከልክ በላይ ትርፍ መፈለግ፣ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሳይቀር ስግብግብ ባለ መልክ ለመክበር መሯሯጥ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ተገን በማድረግ ንብረት መዝረፍና ማካበት የንግዱ ሕብረተሰብ ባህርይና መለያ ሆኗል:: በልክ (Reasonable Rate of Return) ማትረፍ ሞኝነት መስሎ ይታያል:: ለፍቶ ጥሮና ግሮ ዓመታት ደክሞ ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚፍጨረጨረው ወገን ቦታ እየተነፈገው ይገኛል::

## 10.6 ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ የሚለው ተረትና ምሳሌ ስረ መሠረቱ ኢትዮጵያዊ ቢሆንም ለሁሉም ታዳጊ አገሮች መሪዎችና ፖለቲከኞች የሚሰራ ነው:: እነዚህ ወገኖች ፍፁም ድሃ የሆነች አገራቸው ከምትጋግረው ዳቦ ላይ ለራሳቸው የሚቆርሱት የሰማይ ስባሪ የሚያክለውን ነው:: ለህዝቡ የሚተውት ፍርፋሪውን ብቻ ነው:: ሲያውም ከትልቁ ባለሥልጣን እስከ ግልገሉ ባለሥልጣን ተቀራምተውት የሚተርፍ ፍርፋሪ ከተገኘ ነው::

ባለሥልጣናቱ የአንበሳውን ድርሻ ቆርሰው የሚወስዱት ግን በሕግ ማእቀፍ ውስጥ ሆነው ነው:: ባለሥልጣናቱ በሥልጣን ላይ ሳሉና ከወረዱ በኋላ ስለሚያገኙት ጥቅማ ጥቅም በፖርላማ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት

ያስወስናሉ:: የአንበሳውን ድርሻ የወሰዱት ሕግን ተገን አድርገው በመሆኑ በሕግ ፊት በሙስና ሊያስጠይቃቸው አይችልም::

ግን የሚላስ የሚቀመስ የሌለው በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ ሥራ አጥ ከሆነበት፣ የንግድ እንቅስቃሴዎች በኪሣራ ላይ ከሚገኙባት፣ ኢኮኖሚው ከተዳከመባትና ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ በድህነት አረንቋ ከሚኖርባት አገራቸው እድሜ ልካቸውን ከነቤተሰባቸው ሊያኖራቸው የሚችል ጥቅማ ጥቅም በሕግ ስም መውሰድ ሙስና መሆኑን እነሱ እራሳቸው ሳይረዱት ቀርተው ነው?

## 10.7 ምን መደረግ አለበት?

በሀገራችን ሙስናን ለመከላከል መንግስት በ1993 ዓ.ም. የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ማቋቋሙ ይታወሳል:: ኮሚሽኑ በተቋም ደረጃ መቋቋሙ መልካም ነው:: ግን ውጤታማ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው::

ኮሚሽኑ እ.ኤ.አ. በ2001 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር አስጠናሁት ባለው ጥናት በሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ጉቦ፣ ስርቆት፣ ማታለል፣ በሥልጣን ያለ አግባብ መጠቀም፣ እምነት ማጉደልና በመንግስት ሥራ ላይ ዘመድን መመደብ ዋና ዋና የሙስና መገለጫ እንደሆኑ ያመለክታል:: ከዚያ ወዲህ የተሠራ ጥናት አላገኘሁም::

የሙስና ምክንያቶች፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የተጠያቂነትና የግልፅነት አሰራር አለመኖር፣ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍተው የቆዩ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዞች፣ በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች የዜጎች ተሳትፎ አናሳነት፣ የመመሪያዎችና የሥልጣን ገደብ በግልፅ ያለመቀመጥ፣ ድህነትና ኢ-ፍትሐዊነት፣ በቤተሰባዊና በብሔረሰብ ቁርኝት ምክንያት የሚኖር አድልኦ፣ የግል ፍላጐትን ከመንግስት ፍላጐት ጋር ማደበላለቅ፣ ደካማ የፋይናንስ ማኔጅመንት፣ ብቃት የጐደለው የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሥርዓት፣ ያልተጠናከረ የሕግና የፍትህ ሥርዓት፣ የተንዛዛ ቢሮክራሲ፣ የህብረተሰቡ የሞራልና የስነምግባር እሴቶች መሸርሸር፣ ስግብግብነትና ብቃት የሌለው ሲቪል ሰርቪስ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ያትታል::

ኮሚሽኑ በአምስት ዓመታት ውስጥ በሙስና በተጠረጠሩ ከአምስት መቶ በላይ ግለሰቦች ላይ ክስ መስርቶ በ65ቱ ላይ ከአንድ ዓመት እስከ አስራ ዘጠኝ ዓመት በሚደርስ እስራትና የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ማድረጉን በድረ-ገጹ ላይ ካወጣው መረጃ መረዳት ይቻላል:: የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ ዐባይን በጭልፋ ይመስላል:: በሀገሪቱ ከተንሰራፋው የሙስና ወንጀል ስፋት አንፃር የተወሰደው እርምጃ ከችግሩ ግዙፍነት ጋር ይመጣጠናል ለማለት አያስደፍርም::

ኮሚሽኑ ያጋጣመኝ ችግር ብሎ እንደገለፀው የሙስና ወንጀል ውስብስብ ባህርይ ያለው መሆኑን ሁሉም የአገራችን የፍርድ ቤት ዳኞች ተገንዝበው ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት ለመስጠት ያለመሞከራቸው ኮሚሽኑ የሙስናን ወንጀል በመዋጋት ዙሪያ የተፈለገውን ውጤት እንዳያስመዘግብ አድርጐታል:: ከዚህ በተጨማሪም ሙስናን በመዋጋት ረገድ ሕብረተሰቡ የሚጠበቅበትን ያህል

ያለመሳተፉና ሚዲያው ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ ሌላው የሚጠቀስ ችግር ነው ብሎአል፡፡

ይህ መግለጫ ለኮሚሽኑ አመርቂ ውጤት አለማስመዝገብ የኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ በተገቢው አቅጣጫ ላይ ነው ወይ? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡ ለማንኛውም ኮሚሽኑ በቴክኒክ ሥራ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የሚሰጠውም ቴክኒካል ምላሽ ነው፡፡ ስንት ሰው ከሰስኩ፤ አሳሰርኩ እንጂ ሥርአቱ መለወጥ፣ መስተካከል አለበት፣ የፖለቲካው ሥርዓት መቀየር አለበት ብሎ አይነሳም ፡፡

ኮሚሽኑ በተቋቋመበት የመጀመሪያ ዓመታት በጣት የሚቆጠሩ ከፍተኛ ባለሥልጠናትን (አንዳንዱን በሚያጠያይቅ ሁኔታ) ከሶ ከማስቀጣቱ ሌላ ሁኔታዎችን ሊለውጥ የሚችል ውጤት አምጥቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ መልሱ ቀላል አይሆንም፡፡ እንዲያውም ሙስና አስፈላጊ የአስተዳደር መሣሪያ ሊሆን አይችልም ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት የግድ ይላል፡፡ የመንግሥት መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማጠናከር በሙስና መደገፍ ይኖርባቸዋላ! ሰላም ለመፍጠር፤ ወይ ጠላቶቻቸውን ለማዳከም መሪዎች ከሙስና ውጭ የተሻለ መሳሪያ ካላገኙ ምን ይመከራል? በብዙ አቅጣጫ ሲታይ ይህ ሁኔታ ከእውነታው አይርቅም፡፡ በኛም አገር ሲከሰት ይስተዋላል፡፡ ጥያቄው ይህ ክስተት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተንሰራፍቶ ካለ እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሙስና ተብሎ ሊገለጽ ይገባል ወይ? ለማንኛውም የሙስና ጥፋት ግልጽ እስከሆነ ድረስ በሚቀጥሉት ዓመታት እንደኔ በሀገሪቷ የሥልጣን ግልጽነት፣ ማን ምን ፈረመ? ለማን ኮንትራት ተሰጠ? በምን ያህል ገንዘብ ተጠናቀቀ? ወዘተ… የመሳሰሉት ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ ይፋ ሲደረጉ፣ የሚዲያ ነፃነት ሲረጋገጥ፣ የባለሥልጣናት ሀብት ምዝገባ ሲጠናቀቅ፣ የጠቋሚዎች ህይወትና የወደፊት ዕጣ ፈንታ ዋስትና ሲያገኝ፣ የኑሮ ደረጃ እንዳይዘቅጥ የሚደግፉ በተለይም የሀገሪቷ ሀብት ለብዙሀኑ እንዲዳረስ የሚረዱ ፖሊሲዎች ሲወጡ፣ ከብሔር አልፈን ለእድገታችን በሀገራችን ልማትና በፍትህ ላይ ስናተኩር፣ ሙስና መቀነስ ይጀምራል ብዬ እገምታለሁ፡፡

# ባሕል ከልማትና ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለው ግንኙነት

*ዘውዴ አበጋዝ*

## 1. መግቢያ

በዚህ ጽሁፍ ባሕልና ከባሕል ጋር የተያያዙ እሴቶች በልማትና በሥርዓተ ፆታ እኩልነት ላይ ያላቸውን በጎና ጎጂ ተፅእኖ ለማየት እንሞክራለን፡፡ ባሕል ሁሉን አቀፍና ባለብዙ ፈርጅ የሆነ ቁሳዊና ቁስአዊ ያልሆኑ እሴቶችን የሚያካትት ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ቃል የአንድን ሕዝብ ማህበራዊ ተቋማትና እሴቶች ፣ያ ህዝብ ተገቢና ተገቢ ያልሆነ ብሎ የሚቀበላቸውን ባሕርያት፣ የአኗኗር ዘይቤንና ሲወራረሱ የመጡ አስተሳሰቦችን ያካትታል፡፡ በዘመናት እየተወራረሰ የመጣ ትምህርትና ቴክኖሎጂንም ይጨምራል፡፡ በመጨረሻም የልማዳዊ እውቀትና ድርጊቶች መዋቅር በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ግንኙነትና ትስስር መልክ ያስይዛል፡፡ ልማት ደግሞ ተለምዶአዊ አስተሳሰቦችና ተቋማት ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡ መንግስት የህብረተሰብን ባህል ለማሻሻል ወይም ለመቀየር የሚጠቀምበት ስልት የልማትን ውጤታማ መሆንና አለመሆንን ይወስናል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ ግንዛቤያችን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የምናየው የሴቶች ልማታዊ ለውጥ ከልማዳዊ እውቀት፣አስተሳሰብና ተቀባይነት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ መሆኑን ነው፡፡ በሴቶች ላይ የሚደረግ ተፅእኖ በባዶ ቦታ ወይም በአየር ላይ የሚደረግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሴቶችን ልማታዊ ፍላጐቶች ማዕከል አድርጎ ለመነሳት መወሰድ ካለባቸው እምርጃዎች አንዱ ባህላዊ ለውጥ ማምጣት ነው፤ ስለዚህም ህብረተሰቡ፣ ሴቶችን ለማበረታታት ወይም እንቅፋት ለመሆን ወይም ተነሳሽነትን ለመገደብና ተስፋ ለማስቆረጥ፣ ወይም ብቃታቸውን በሁሉም አቅጣጫ ከማጎልበት ይልቅ የተለያዩ እክሎችን በመፍጠር ለማቀጨጭ የሚጠቀምባቸውን ስልቶች አካሄዶችና አስተሳሰቦች በጥልቅ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ባጭሩ፣ ሚዛኑን የጠበቀና ሁለቱንም ፆታዎች በእኩልነት የሚጠቅም ዘላቂ ልማት ለማምጣት ምርምራችን ባህልንም ሊፈትሽ ይገባል፡፡

ባሕላዊ ሥርዓቶችና እሴቶች ብንወድም ብንጠላም በልማትም ሆነ በፆታዎች እኩልነት ላይ ተጽእኖ ስላላቸው ስለ ልማቱ ስናስብ በምንወስዳቸው እርምጃዎችና በምንጠቀምባቸው ስልቶች ውስጥ ባሕሉ ከጎናችን እንዲቆም እኩልነትንና ልማትን እንዳይቦረቡርብን አስፈላጊውን መከላከያና ለውጥ አብረን መቀየስ አለብን፡፡

የልማት ውጤቱ ለሰው ልጆች፣ ማለትም ለወንዶችም ለሴቶችም፣ እኩል እንዲሆንና ዘላቂነትም እንዲኖረው በወንዶችና በሴቶች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ በተጨባጭ ለውጥ አምጥቶ እንዲታይ ከተፈለገ ባሕሉ በአጋርነት ከጎናችን

መቆም ስላለበት ምን ማድረግ አለብን የሚለው የሁላችንም አንገብጋቢ ጥያቄ መሆን ይገባዋል፡፡ ለምሳሌ የበዓላትን ቀናትን የሚያበዛ ሃይማኖታዊ እሴትን ፀረ ሃይማኖት ሳያሰኝን እንዴት መለወጥ የሚቻለው? ይህም ለውጥ እንዴት ነው በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኝልን? ገበሬው ዓመት ሙሉ የለፋበትን ምርት ያለ አግባብ በተለያዩ ድግሶች ሳያባክን ያለውን ጥሪት ለዘላቂ ልማት ማዋል እንዲችል የድግስ እሴቱን እንዴት እንለውጠው? በሴት ልጅ ትምህርት የማያምንና ለሴት ልጅ ትምህርት ዋጋ የማይሰጥን ኅብረተሰብ አስተሳሰብ ለውጠን ወንዶችና ሴቶች ልጆች እኩል የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ምን ዓይነት ግንዛቤ እንፍጠር? ባጭሩ፣ እንዴት አይነት የአመለካከት ለውጥ እናምጣ? ብሎ መጨነቅና መፍትሔ መፈለግ የግድ ነው፡፡ ስለዚህ የሴቶችን ጭቆና በተፈጥሮ እንደመጣና ተገቢ እንደሆነም በሚያምን ኅብረተሰብ ላይ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት የልማቱ ግማሽ ኃይልና ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን ሴቶችን የዘላቂው ልማት አምጪና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ያለዚያ ልማቱም አይመጣም፤ ግማሹ ሕዝብ ተጠቃሚ ባልሆነበት ሁኔታ ውስጥም ድህነት አይቀሬ ይሆናል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ በባህሉ ውስጥ በወንዶችና በሴቶች እኩልነት የሚያምኑ አዝማሚያዎችና ፍንጮች ካሉ ደግሞ እነሱን አጉልቶ ማውጣት ልማቱን ሊያፋጥነው ይችላል፡፡ የሴት ልጆች ግርዛት፣ሴት ልጅ ከመውለድ ወንድ ልጅ መውለድ ይሻላል የሚል ጎጂ አመለካከት፣ የልጅነት ጋብቻ፣ የጠለፋ ጋብቻና ሌሎችም ተመሳሳይ ጎጂ ልምዶች፣ የውርስ ጋብቻ፣ ንብረትን ባሏ የሞተባት ሴት እንዳትወርስ የሚከለክል ልምድ፤ በፍቺ ጊዜ የመካፈል መብት ማሳጣት፣ ወዘተ እነዚህ እሴቶችና አመለካከቶች ሴቶችን በእጅጉ ይጐዳሉ፤ የኢኮኖሚ ጥገኛ ሁለተኛና አናሳ ዜጋ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ አመለካከቶች ጨርሶ የሚወገዱበትና በጠቃሚ ልምዶች የሚተኩበት ሥራ ካልተሠራ በሁለቱም ፆታዎች ትብብር የሚገነባና ኅብረተሰቡን አስማምቶ እንደ ሰንሰለት አያይዞ የሚጓዝ ሥርዓት ማቆም አይቻልም፡፡ ባሕል ሰውን ማለትም ወንድንም ሴትንም እኩል መብት የሚያላብስ፣ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው የሚለውን አምላካዊ ቃል ጠብቆ የሚፈጥር፣ የሚያድግ፣ የሚበለፅግም መሆን አለበት እንጂ ፍርደ ገምድል የሆነ በሃይማኖቱ፣ በመመሪያው፣ በዘፈኑ፣ በፎክሎሩ፣ በግጥሙ፣ በታሪክና ምሳሌው ወዘተ አማካይነት የሴቶችን ሰብአዊ መብት የሚጥስ መሆን የለበትም፡፡

ልማት ባሕልና የፆታዎች እኩልነት በጣም የተወሳሰበ ግንኙነት አላቸው፡፡ እርስ በእርሳቸው ይደጋገፋሉ፤ ይጋጫሉ፤ የዚህም ውጤት በሦስቱም ገጽታ ላይ ይንፀባረቃል፡፡ የሴቶችንና የወንዶችን እኩልነት ለማረጋገጥ በሚኬድበት እንቅስቃሴ ላይ ምናልባት በተለምዶ ልክ ነው ብለን ስንፈፅመው የነበረው ስህተት ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ «ሴትንና አህያን በዱላ» የሚለው አነጋገር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ስለሆነ ልክ ሊመስለን ይችላል፤ ግን እጅግ የተሳሳተና የተዛባ አመለካከትን የሚያንጸባርቅ ዘይቤ ነው፡፡

በመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ጊዜ የገጠመኝን የግል ተሞክሮ ሃሳቤን ይበልጥ ሊያብራራ ስለሚችል ባቀርበው እወዳለሁ። አንድ በሀገራችን ጠረፍ አካባቢ የሚገኝ የትምህርት ዕድል ፈጽሞ የተነፈገ ብሔረሰብ ውስጥ የመሠረተ ትምህርትና መሠረተ ልማት እንቅስቃሴዎች ለመጀመር በወቅቱ የምሰራበት መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅት ተገቢውን መሰናዶ ካደረገ በኂላ ወደ ተግባር ስንገባ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች አንድ ቅድመ ሁኔታ ያቀርቡልናል፤ ይህም ሴቶች መሠረተ ትምህርት ይከታተሉ እንዳንል ነው።

ከእነርሱም ጋር መሥራት ከፈለግን በቀረበው ቅድመ ሁኔታ መስማማት አለብን፤ ያለዚያ ግን ሥራችንን መጀመር እንደማንችል ተነገረን። ይህንን ካወቅን በኂላ ይህ በከፊል መንግሥታዊ የሆነ ድርጅት ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ገባ። ለዕርዳታ ለጋሾቻችንም ይህን ያህል ሴት ይማራል ማለት ስለአለብን ምን እናድርግ ብለን በስብሰባ ስንመካከር ከፊሉ ወገን እዚህ ብሔረሰብ ውስጥ ሥራ መጀመር የለብንም ሲል ከፊሉ ደግሞ የሚገደዱበት መንገድ ይፈለግ ይል ነበር፡ ፡ በቁጥር አነስተኛ የሆነው ሦስተኛ አካል ግን ትተን መሔድም ማስገደድም የለብንም፤ ስልታዊ ሆነን፣ ማለትም ለአንድ ዓመት ያህል ብሔረሰቡ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ተቀብለን እንሥራ፤ የማስተማሪያ ቁሳቁሶቻችንን ግን እንለውጣቸው፣ በአብዛኛው ሁሉም የመማሪያ ጽሁፎች በምግብ ሳይንስ ላይ እንዲያተኩሩ እናደርግ፤ በኮርሱ መጨረሻም የምረቃ በዓል አዘጋጅተን በቲያትር መልክ ስለ ምግብ ሳይንስ ከፍተኛ ሽፋን እንስጥ። ይህንን ሁሉ የምናደርገው ይህ ትምህርት እኮ ይበልጥ ሴቶች ቢማሩት በቤታችን ውስጥ ጥሩ ምግብ እንመገባለን፤ ጥሩ እንክብካቤም እናገኛለን በሚል ግንዛቤ በሁለተኛው ዙር ሴቶች ገብተው ይማሩ ሊሉ ይችላሉ ብሎ ተከራከረ። ሀሳቡ አሳማኝ ሆኖ ስለተገኘ ተቀባይነት አግኝቶ ሥራው ተጀመረ። የመጀመሪያው ዙር እንዳለቀም ትልቅ በዓል ተደርጎ በምግብ ሳይንስ ላይ ያተኮረ መዝሙርና ቲያትር ቀርቦ ዝግጅቱ አበቃ። ስለሁለተኛው ዙር ለመነጋገር ከብሔረሰቡ መሪዎች ጋር ለመወያየት በተቀመጥንበት ጊዜ መሠረተ ትምህርቱም ሆነ መሠረተ ልማቱ እንዲቀጥል ሲስማሙ በተጨማሪም የትምህርቱ ይዘት ይበልጥ ሴቶች ቢማሩት ለኅብረተሰቡ የተሻለ ጥቅም ሊሰጥ ስለሚችል ሁሉም ሴቶች መሠረተ ትምህርት ይማሩ የሚለውን ሀሳብ ተቀበሉት።

ከዚህ ገጠመኝ እንደምናየው ባህላዊ እሴቱ ለልማቱ (ለመሠረተ ትምህርቱ) እንቅፋት ነበር። በስልት ግን ብሔረሰቡንም ሳናስቀይም እሴቱን ለመለወጥ ችለን ነበር። ስለሆነም በዛ ማህበረሰብ ውስጥ የተማሩ ወንዶችና የተማሩ ሴቶች ግንኙነት ከድሮ ይልቅ በመመካከር ላይ የተመሠረተ ሆነ።

ለልማት አምጪው ፈታኙ ነገር ሚዛኑን የጠበቀ ልማትና እኩልነትን ባሕሉ ያደረገ ኅብረተሰብ መፍጠር ነው። ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ የሥርዓተ ፆታን ችግር እየፈታ በጎ ጎኑን እያጠናከረ የሚሄድ መሆን አለበት። ምንም እንኳ ጎጂ ልምድ ይቀጥል ባንልም እኩልነትን እሴቱ ያደረገ ኅብረተሰብ መፍጠር ግን ስልት እየቀያየሩ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ቀንና ሌሊት ሊሠራበት

የሚገባ ነው፡፡ በጎ ባሕሎች እንዲጎለብቱና በልማታዊ ባሕሎች እንዲተኩ ማድረግ የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

የብዙ የልማት ሠራተኞችና አጋሮች ሥጋት የወንዶችና የሴቶች እኩልነትን እውን ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የአካባቢውን ባሕል ያናጋል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ለባሕል እንክብካቤ ሲባል የወንዶችንና የሴቶችን እኩልነት እንደ ልማት ጥያቄ አድርገን በማንሳት ከልማት ጋር ልናስተሳስረው አይገባም ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የአካባቢው ባሕል ለልማትና ለእኩልነት እንቅፋት ከሆነ ባሕሉን ለመለወጥ ጥረት ማድረግ አለብን ይላሉ፡፡

እንደምናየው በሁለቱ አመለካከቶች መሃከል የከረረ ልዩነት አለ፤ ለመለወጥም የምናደርገው ጥረት ቀላል አይሆንም፡፡

## 2. እውነት ሥርዓተ ፆታ ከባሕል ጋር ቁርኝት አለው?

ኅብረተሰቡ ከእያንዳንዳችን የሚጠብቀው ነገር ምንድን ነው? ለወንዶች ተገቢ ነው/አይደለም ለሴቶች ተገቢ ነው/ አይደለም የሚለው አለባበስ፣ አካሔድ፣ አነጋገር፣ የሥራ ድርሻ፣እውቅና፣ ዋጋ መስጠት በጠቅላላው አመለካከትና ክንውኖች በሙሉ በባሕል የተቀረጹ ናቸው፡፡ የፆታዎች መታወቂያዎችና ግንኙነቶች በሙሉ የባሕል ገጽታ አላቸው፡፡ ይህም የእያንዳንዱን ሰው ዕለታዊ ሁኔታ፣ የቤተሰብ አኗኗር፣ የኅብረተሰቡንና የሥራ ቦታን ገጽታ ያመለክታል፡፡

ሥርዓተ ፆታ የራሱ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅርና የአሠራር ሥልት አለው፡፡ ሴትነትና ወንድነት ትርጉማቸው ምን እንዲሆን ሥርዓተ ፆታው ይነግረናል፡፡ ይህም በተለይ የወንድ ሥራና የሴት ሥራ በሚለው በቤትም በኅብረተሰብም አልፎም በመንግስታዊ ተቋማት ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡

ለዚህም ክስተት የመግለጫ አሰጣጡና አካሄዱ በየብሔረሰቡ የተለያየ ሊሆን ቢችልም በጠቅላላው ግን የሴቶችን የበታችነት፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት፣ የሀብትና የጥረት ባለቤት አለመሆንን እንደ ትክክለኛ አካሄድ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ በውሳኔ ሰጭነት ላይም ማዳመጥ እና ከበስተጀርባ ጥቃቅን አስተያየት መስጠት እንጂ የውሳኔው ባለቤት መሆን አለመቻላቸውን እንደ ትክክለኛ ነገር ያስቀምጣል፡፡ ተረቱም ‹‹ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ›› ስለሚል ኅብረተሰቡ የሰጣትን ቦታ አውቃ እንድትታዘዝ ያስገድዳታል፡፡

## 3. ባሕልና ልምድ የማይለወጡ ናቸውን?

እንደምናውቀው ኅብረተሰብና ባሕል ባሉበት የሚቀመጡ የማይለወጡ አይደሉም፡፡ ሕይወት ያላቸውና ያለማቋረጥ የሚታደሱና እራሳቸውን እንደ ተጨባጩ ሁኔታ የሚለዋወጡ ናቸው፡፡ ሥርዓተ ፆታም እንዲሁ የሚለዋወጥ ነው፡፡ ሥርዓተ ፆታ በጥቅሉ ሲታይ ኅብረተሰቡ ያስተማረን ከእያንዳንዳችን የሚጠብቀው ባሕሪ ነው፡፡ ይህም ከባሕል ትልልቁ አካሎች አንዱ ነው፡፡

ሰው ሠራሽ በመሆኑም እንደተጨባጩ ሁኔታ ይለዋወጣል፡፡ ለውጥ ከብዙ አቅጣጫም ይመጣል፡፡ የኢኮኖሚ ለውጥ በመጣ ቁጥር ራሱን ለማስማማት ሥርዓተ ፆታም ይለወጣል፡፡ ለምሳሌ ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚን ሲለወጥ ወንዶችና ሴቶች ሚናቸው ይለወጣል፡፡ ሚና ሲለወጥ ደግሞ ሰንሰለቱና ግንኙነቱም እንዲሁ ይለወጣል፡፡ የራስ መተማመን በሚያመጡ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሲገባ የእኩልነት ግንኙነት እየተፈጠረ ይመጣል፡፡ ለምሳሌ ሴቶች ተካፋይ ሠራተኞች ሲሆኑ የኢኮኖሚ ጥገኝነት ስለማይኖርባቸው ተገዥነታቸው እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በኢንዱስትሪ ከተሞች አካባቢ ብዙ ሴቶች በሥራ ላይ የተሠማሩ ከሆነ ታዋቂነታቸውና ተሳትፎአቸው እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ከዚያም አልፎ ተቋማት ፖሊሲ በሚያወጡበት ጊዜ ለሴቶች ፍላጎትና ችግርም መልስ መስጠት እንዳለባቸው ይበልጥ እየተገነዘቡ ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ የፖሊሲ፣ የሕግና የአስተዳደር መመሪያዎችና የሴቶች እኩልነትን ባገናዘበ መልኩ መውጣታቸው ይኀለብታል፡፡

ባሕል እየተለወጠና እሴቶች እየተለወጡ በሄዱ ቁጥር ደግሞ የሰዎች አስተያየት ይለወጣል፡፡ እስከአሁን የተደረገውን ጥረት በምናይበት ጊዜ ለውጥ ለማምጣት የተሞከረው በሴቶች እኩልነት ላይ የሰውን አስተሳሰብ መቀየር፣ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሴት ተማሪዎችን ቁጥር መጨመር፣ የሴቶችን የሥራ ዕድል ማስፋት፣ በሴቶች ላይ የሚፈፀም የሀይል ጥቃትን መቀነስ፣ ጨርሶም ማጥፋት ላይ ነበር፡፡ አዲሱ አካሄድ ግን ለባሕል ልማታዊ ትርጉም በመስጠት ኅብረተሰቡ ራሱ ፋና ወጊ የሆኑ ግለሰቦችን አጉልቶ በማውጣት በሰፊው የባሕርይ ለውጥ የሚያመጡ ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ብዙ ህዝብ የሚደግፈውና ወደ ኋላ የማይመለስ ለውጥ ይመጣል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ባህላዊ እሴቶች እየተለወጡ ይሄዳሉ፡፡

## 4. ባሕል ሆነ ማለት የማይለወጥ የማይጠየቅ ሆነ ማለት ነውን?

ከላይ እንደተገለጸው ባሕላዊ እሴቶች ካለው ተጨባጭ ሁኔታና ካለው ጊዜያዊ ፍላጎት ጋር በማጣጣም አዳዲስ ትርጓሜ እየተሰጣቸው ኑረዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡ አንዳንድ እሴቶች እየተጠናከሩ ሲሔዱ አንዳንዶቹ ግን ጊዜው ያለፈባቸው እየሆኑ እንዲለወጡ ይገደዳሉ፡፡ ዓላማው የአንድን ብሔራዊ ባሕል ለመቀየር ሳይሆን ለምሳሌ ‹‹ድንጋይ አትርገጥ ማን ተከለው ብለህ፤ የሴት ልጅ አታግባ ማን ቀጣት ብለህ›› የሚለው አባባል ከእውነት የራቀና ዋነኛዋ የልጆች አሳዳጊ ሴት መሆኗንና ጥሩ አድርጋ ሥነ ሥርዓት አስይዛ የምታሳድግ እናት መኖሯን የሚክድ አባባል ነው፡፡ ይህ ዘይቤ፣ ሴቶች ልጆችን በማሳደግ ያላቸውን ገንቢ ሚና በሚያሳይ አባባል ሊለወጥ ይገባል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ወንድን የሠራው እጁን ታጥቦ ነው›› የሚለው አባባል የወንድን ክቡርነት የሴትን ዝቅተኝነት የሚያሳይ ስለሆነ ሊለወጥ ይገባል፡፡ ‹‹የቄስ ሚስት አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሀፍ አጠበች›› ይህም ሴት መደነቅና

መወደስን መቀበል እንደማትችል አድርጎ የሚያቀርብ ነው። እንደነዚህ አይነት አባባሎችና ቀልዶች አስተሳሰቦች እንደልብ በሚነገሩበት ባሕል አንዱን ሰው (ሴትን) ከሌላው ሰው (ወንድ) አሳንሶ የሚያሳይ ስለሆነ እንዲለወጥ ጥረት የማይደረግበት ምክንያት የለም።

## 5. ከግንዛቤአችን ውስጥ ልናስገባቸው የሚገባ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች አሉን?

ከላይ እንደተገነዘብነው የሥርዓተ ፆታ መለያና ግንኙነት ወሳኝ የሆነ የባሕል ገጽታ አላቸው። ይህንንም የምንልበት ምክንያት የሰውን የዕለት ተዕለት ገጽታ ስለሚስሉ ነው። በሥርዓተ ፆታ ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ተቃውሞ ይገጥማቸዋል።ምክንያቱም ለውጡ ወዲያው በወንዶችና በሴቶች ሚና ላይ ስለሚታይ ነው። በተለይ የሴቶች የሚስትነትና የእናትነት ሚና የባሕል መሠረት ወይም የባሕል ቀጣይት ምልክት በመሆናቸው ነው። እምቅ የፖለቲካ ኃይል ምልክትም ናቸው። ስለሆነም ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በሴቶች ሚና ላይ በአብዛኛው ያተኩራሉ። ይህም ትኩረት በሃይማኖትና በባህል እሴቶች ላይ እንድናተኩር አድርጎናል። በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ የተያዘ አእምሮ ደግሞ ለውጥን ማምጣት ያስቸግራል። እንዲያውም በሥርዓተ አበው ሕግና ሥርዓት የተወጠረ ማኅበረሰብ የባሕል ለውጥ ለሃይማኖት መመሪያዎች አለመገዛትና የምዕራባዊያን ባሕል ተገዢ መሆን ነው በሚል የለውጥ ሃሳቦችን የሚቃወሙ ይኖራሉ። እውነቱ ግን ይህ ሳይሆን ለሃይማኖትና ለእምነት እንዲሁም ለብሔራዊ መለያዎች ሴቶች ትልቅ ዋጋ የሚሰጡ መሆናቸው ነው።

በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴቶች ለሃይማኖት ሕግጋት ተገዢ እና የልምዶችእና የብሔራዊ እሴቶች ተንከባካቢ ናቸው። ባሕላዊ እሴቶች የማይለወጡ ሳይሆን ቀስ በቀስ መልካቸውን እየለዋወጡ በመሄድ ላይ ያሉና በሂደትም ለተለያዩ ቡድኖች ብሶት መፍትሄ እየሰጡ የሚሄዱ መሆን አለባቸው። ስለሆነም ስለ ሴቶች ሚና አንዱ ቡድን የሚያንጸባርቀውን አመለካከት ሌላው ቡድን ላያንጸባርቀው ይችላል። ስለሆነም ሚዛኑን የጠበቀ እኩልነትን ለማምጣት እምቅ ኃይል ያለውን እንቅስቃሴ ለመጀመር የሚመለከታቸው ሁሉ ተዋንያን የሚሆኑበት መንገድ መቀየስ አለበት። ለምሳሌ ከሶቪየት ህብረት መከፋፈል በኋላ የኮምኒስቱ ሥርዓት ሲንኮታኮት የታየው ነገር ያለሴቶች ተሳትፎ አብዮቱ ግቡን አይመታም እንዳልተባለ ሁሉ፤ ሴቶች ሴት በመሆናቸው ብቻ ለማንኛውም ተፅእኖ ተጋላጭነታቸውና ያለሥራ መኖራቸው ፈፅሞ በሶሻሊስቱ ሥርዓት የቀረ ቢመስልም፤ እውነተኛ ሁኔታው ግን ሴቶቹ በወንድ ዓለም ውስጥ ገብተው ያለችውን ጥቂት የሥራ ዕድል ተካፍለውና ሰብአዊ መብታቸውን አስከብረው ለመኖር እልህ አስጨራሽ ትግል እያደረጉ እንደነበረ ነው።

## 6. ልማታዊ እንቅስቃሴዎች ከባሕል ተጽዕኖ ውጭ ናቸው ወይ?

ልማት ለውጥ ማለት ነው፡፡ በመንግስት፣መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በልማት ድርጅቶች የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች ውስጥ ውጤት ለማምጣት የሚደረጉ ኢንቬስትሜንቶች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ እንቅስቃሴዎች ደግሞ ጠቃሚ ያልሆኑ እሴቶችንና ልምዶችን በመለወጥና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በተሻለ ሁኔታ በመቅረጽ ላይ ያነጣጥራሉ፡፡ ለምሳሌ በቤተሰብ ዕቅድ ላይ ያነጣጠረ እንቅስቃሴ የቤተሰብን መዋቅር ይነካል፡፡ ከዚሁም ጋር የተያያዙት ባሕላዊ እሴቶች በልማቱ ላይ በጎም ሆነ ጎጂ ተጽእኖ ማምጣታቸው አያጠራጥርም፡፡ ስለዚህ የልማት ሞዴሎች ባሕላዊ እሴቶችን ከግንዛቤ እያስገቡ ማቀድ ግድ ይላቸዋል፡፡ ለምሳሌ የመንገድ ሥራ ግንባታ ገጠሩንና ከተማውን ሲያገናኝ ሰዎችና ምርቶቻቸው እንደልብ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ አርሶአደሮችም ምርታቸውን ወደተለያዩ ገበያዎች በመወሰድ በተሻለ ዋጋ ይሸጣሉ፡፡ በቀላሉ ወደ ጤና ተቋማት በመምጣት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ የገጠር ተማሪዎች እንደልብ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ በአንጻሩ ግን የሸክላ ሠሪዎች ምርቶች ከተማ በሚመረቱ ርካሽና ያነሰ ጥንካሬ ባላቸው የፕላስቲክ እቃዎች ይተካሉ፡፡ በመንገዱ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሕዝብ ፍልሰት ይባባሳል፡፡ይህም የገጠሩ ቤተሰብ አባዋራው እየለቀቀ ወደ ከተማ ሲገባ የገጠር እማወራዎች የተጠናከረ የኢኮኖሚ ተሳትፎ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህም የሁለቱንም ሚና ይለውጣል፡፡ ባጠቃላይ እንደነዚህ ዓይነት ልማታዊ እንቅስቃሴዎች በወንዶችና በሴቶች መካከል ሚናዊና አስተዳደራዊ ለውጥ ያመጣሉ፡፡ የኃይል አሰላለፉም የዛኑ ያህል ይለወጣል፡፡ ባሕሉም እነዚህን ለውጦች ለመቀበል እሴቶች ለውጥ ያደርጋል፡፡

## 7. የልማት እንቅስቃሴዎች ከሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ነፃ ናቸውን?

በልማቱ እቅድ ላይ እኩልነት ነጥሮ የወጣ ጉዳይ ባይሆንም እንኳ በእድገት ሂደት ውስጥ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ሁሉ በሥርዓተ ፆታ ላይ በጎም ሆነ ጎጂ ተጽእኖ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ የአካባቢ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት ሲነደፍ ሴቶች በጥናቱ ወቅት አጫጭር እርቀትን በመጠቀም የውኃውን ዓይነትና ጥራት በመለየት እንዲሳተፉ ጥረት ማድረጉ ተገቢ ነው በሚል አስተሳሰብ ሔደን ሴቶችን ካላሳተፍን ውሳኔው የወንድን ፍላጎት ብቻ የሚያካትት በመሆኑ የፕሮጀክቱ ጠቃሚነትና ዘላቂነት፣ የወጣበት ወጪም አጠያያቂ ይሆናል፡፡

የሲቪልን ኮድ ለማሻሻል የሚሞክር መንግስት የሕዝብ ምክክርና ጥናት በሚደርግበት ወቅት በጋብቻ፣በፍቺ፣በሀብት ክፍፍል፣ በውርስ ወዘተ ጥያቄዎች ላይ ወንዶችን ብቻ የሚያሳትፍ ከሆነ የሲቪል ሕጉ እንደቀድሞው ሁሉ በሴቶች ላይ የሚያዳላ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ህጉን

ለማሻሻል በተደረጉ ውይይቶች ሴቶች በጠንካራ ሁኔታ ስለተካፈሉ ከሲቪል ሕጉ ውስጥ 23 አንቀፆች በሴት ዜጎች ላይ ተጽእኖ ያላቸው በመሆኑ እንዲቀየሩ ተደርጎአል፡፡ የጡረታ ሕጉም እንዲሁ፡፡ የተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫም ዱሮ ያልነበሩ ጠቃሚ ህጎች እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ደካማ የነበሩ ሕጎችም በእጅጉ ተሻሽለዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ሴቶች ሃሳባቸውን ለመግለጽ የተለያየ መድረክ ስለተከፈተላቸውና ገደብ የሌለው ተሳትፎ ስላደረጉ ነው፡፡

## 8. እኩልነትን እውን ለማድረግ ዋነኛ ዓለማ አድርጎ ለልማት መንቀሳቀስ የምዕራባውያንን እሴቶች ማንፀባረቅ ይሆንን?

የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን በልማታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እውን ማድረግ የምዕራባውያንን ባሕል መቀበል ወይም ማንፀባረቅ ነው ማለት አገሮች እስከአሁን ለሴቶች ጥያቄ መልስ ለመስጠት ያደረጉትን ጥረት መካድ ነው፡፡ ይነስም ይብዛም አብዛኞቹ ሀገራት ለሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተገቢ መልስ ለመስጠት ጥረት አድርገዋል፤ በጎ ውጤቶችንም አግኝተዋል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያንም ጨምሮ ሕገ መንግሥት፣ ሕጎች፣ደንቦችና ፖሊሲዎች ሲሻሻሉ እኩልነት መንፀባረቁና አለመንፀባረቁ እንዳንድ መስፈርት ተወስዷል፡፡ እየተወሰደም ነው፡፡ አብዛኞቹ ሀገሮች የተባበሩት መንግስታትን Convention on the Elimination of Discrimination Against Women (CEDAW) አጽድቀዋል፡፡ የቤጅንግም ውሳኔዎች ተቀብለው አቅምና ግንዛቤ በፈቀደ መጠን ተግባራዊ እያደረጉ ነው፡፡ በባሕላዊ እሴቶች ላይ ለውጥ እንዲመጣ መንግሥታት ብዙ ሙከራ እያደረጉ ነው፡፡ የሴቶች ማህበራትም የፆታዎች እኩልነትን ለማምጣት ብዙ ተጋድሎ አድርገዋል፤ እያደረጉም ናቸው፡፡ (CEDAW AND PFA) ተግባራዊ እንዲሆኑ ብዙ የቅስቀሳ ሥራ ሠርተዋል፡፡ እንዲያውም መንግሥታት የገቡትን ቃል ተግባራዊ እንዲያደርጉ ብዙ ግፊት አድርገዋል፡፡

## 9. የባሕል ሴንሲቲቪቲ አስፈላጊ ነው ወይ?

ባሕልን ማክበርና ተገቢውን እንክብካቤ ለባሕል እድገት ማድረግ ተገቢ ነው፤ ነገር ግን የሰውን መብት የሚጋፉ፣ በጤናና በዕድገት እንዲሁም በልማታዊ አስተሳሰብ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ፣ ባሕሎች እንዲፈተሹ ሲባል አፈንጋጭነት አለመሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡

በCEDAW ድንጋጌ መሠረት አድልዎን ማጥፋት የትምህርት፣የሥራ፣የጤና አገልግሎት ወዘተ በእኩልነት መጠቀም አፈንጋጭነት አይደለም፡፡

## 10. የወንዶች ሚና እኩልነትን በማምጣቱ ላይ

ይህ ቁም ነገር ብዙ ጊዜ ትኩረት የሚሰጥበት አይደለም፡፡ ሥርዓተ ፆታ ማለት ግን በወንዶች ላይ ጣት መቀሰር ወይም የሴቶችን ተጎጂነት ለመቀየር በሴቶች ጥረት ብቻ መፍትሔ ለማምጣት መሞከር ማለት አይደለም፡፡ በሴቶች ሚና

ዙሪያ ኅብረተሰቡ የሚጠብቀው እንዳለ ሁሉ እንደ መሪ፣እንደ ባል፣እንደ አባት፣ እንደ ወንድም፣ እንደ ወንድ ልጅ ከወንዶች የሚጠበቁ ጉዳዮችም አሉ። እኩልነትን ለማምጣት በሁለቱም ፆታዎች ጥረት መደረግ አለበት። አንዳንድ አገሮች ውስጥ ይህን የተገነዘቡ ወንዶች ኔትወርክ በመፍጠር ለሴቶች እኩልነት እየታገሉ ነው። ለምሳሌ የሴቶችን የሀይል ጥቃት ለማስቀም ወንዶች በወንዶች ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት አንዳንድ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ናቸው። ውጤታቸውም ቀላል የማይባል ነው። ብዙ የልማት ድርጅቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለእኩልነት መምጣት የወንዶች ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን እየተገነዘቡ ናቸው። የሴቶች እንቅስቃሴ ለኅብረተሰቡ በጠቅላላ ምን በጎ ጎን እንዳለው ያልተገነዘቡ ወንዶች እንቅፋት ሲሆኑ የተገነዘቡት ደግሞ ብዙ ጥቅም ያስገኛሉ። የቤተሰብ ደህንነትና የሴቶች ከተፅዕኖ ነፃ መውጣት ምን ያህል ትስስር እንዳላቸው ብዙ ወንዶች እየተገነዘቡ ድጋፍም እየሰጡ ናቸው።

## 11. ድምዳሜ ምን ማድረግ አለብን?

ጥያቄው ባሕልን አንንካው ወይስ እንንካው የሚል ሳይሆን ለውጡ ለሁለቱም ፆታዎች ጠቃሚ ውጤት እንዲያመጣ እንዴት እንሂድበት፣ ከድህነት ለመውጣትና የፆታዎችን እኩልነት ለማረጋገጥ ምን ስልት እንጠቀም የሚል ይሆናል።

ለልማት እንቅስቃሴ ጥያቄው ምን አይነት አዎንታዊ አካሄድ እንሂድ፤ የግለሰቦችን ብሎም የኅብረተሰቡን አመለካከትና ባሕል ልማታዊና የፆታ እኩልነት እሴቱ ያደረገ ኅብረተሰብ እንዴት እንፍጠር ይሆናል። በወንዶችና በሴቶች ላይ ልማት የሚያመጣው በጎ ውጤት እንዴት ይስፋፋ? እንዴትስ ዘለቄታ ያለው ይሁን? የሚለው የወቅቱ ጥያቄ መሆን አለበት።

ስለዚህ በመጀመሪያ ስለጉዳዮቹ ትስስርና ዝምድና ጥርት ባለ መልኩ ግንዛቤ እንውሰድ። ለምሳሌ ሥርዓተ አበው ምንድነው? ከልማት፣ ከፆታ እኩልነትና ከባሕል ጋር ያለው ግንኙነት ብዥታ በሌለበት ሁኔታ ሊገባን ይገባል። ማንኛውም ሕብረተሰብ እምቅ ሀብት አለው። ሀብቶቹም የአየር ንብረቱ፣ መሬቱ፣ ሰዉ፣ የሰዉ እውቀትና ቴክኖሎጂ አጸዋትም ጭምር ናቸው። እነዚህን እምቅ ሀብቶች ለመጠቀም ኅብረተሰቡ የራሱን ድርጅት፣ ለድርጅቱ መዋቅር ማስፈጸሚያ ሕጎች፣ ደምቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የሰዎችን የዕለት ከዕለት ግንኙነት የሚመሩ ስልቶች አሉት። ከነዚህም አንዱ ባሕል ነው። በዚህ ሁኔታ ሥርዓተ አበው ማለት ወንዶች በበላይነትና በብቸኝነት የኅብረተሰቡ እምቅ ሀብት ባለቤት የሆኑበት እውነታ ሲሆን ይህንኑ ለማስተዳደር፣ ለማስተላለፍና ለመጠቀም የኅብረተሰቡን መተዳደሪያ ሕግ ማውጣት ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ ባሕሎችን መለየት፣ በሃይማኖት ተግባራዊነቱን መቆጣጠር፣ በሕግና ደንብ አፈንጋጩን መቅጣት ስለሚያስፈልግ ነው። ለዚሁ የሚስማማ ደንብና ሕግ፣ ፖሊሲ አውጥቶ ገዢና፣ ተገዢን ተጠቃሚና ተጎጂን አስማምቶ መሔድ ቻለ።

ይህንንም ልክ እንደሆነ አድርጐ ተቀባይነት እንዲያገኝ የአስተሳሰብ ለውጥ የማምጫውን ትምህርት ሰጠ፡፡ ስለሆነም የኀብረተሰቡ እምቅ ሀብት ባለቤት የሚያስተዳድርበት ዘይቤ በኀብረተሰቡ መተዳደሪያዎች በኢኮኖሚው በፖለቲካው፣ በባሕል ሂደቱ ሁሉ እየተተረጎመ መጣ፡፡ እነዚህ አካሄዶች ደግሞ በንብረት ክፍፍሉ፣ በማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት በመናናቅና በመከባበር በመጠቀምና ባለመጠቀም በታላቅነትና በበታችነት እየተገለጡ መጡ፡፡ እነዚህ ክስተቶች ደግሞ የግለሰቦች፣የቤተሰብ፣የኀብረተሰብና የብሔሮች ጥሪትና ሀብት ተጠቃሚነትም እንዲሁ ልዩነት እየተፈጠረበት መጣ፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ የፆታዎች እኩል አለመሆንን ፈጠረ፡፡ ይህን ጥርት ባለ መልኩ ከተረዳን ቀጣዩ ሥራ ችግሩን እንዴት እንደምንፈታው ውይይት ማድረግ፣የሥርዓተ ፆታ ትንታኔ (Gender Analysis) መሥራት፣ ማን ተጠቃሚና ማን ተጎጂ እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ነው፡፡ በመጨረሻም አዳዲስና ውጤታማ የሆኑና የሰውን ቀልብ የሚስቡ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

ለውጥ ለማምጣት በቂ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ የሰዎችን ችሎታ መገንባት፣ የባሕርይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ብዙ የለውጥ ሐዋርያት መፍጠር፣ሕግና ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎች በማውጣት ከባህል ውስጥ ለልማትና ለፆታ እኩልነት እንቅፋት የሚሆኑትን ብዙ ቅራኔ ውስጥ ሳይገባ መፍትሔ ሊመጣ የሚችልበትን ስልት መቀየስ ካልሆነ ግን ልማትና እኩልነት መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶች ስለሆኑ ተግባራዊነታቸውን በብልሀትና በቆራጥነት መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ልንገነዘብ የሚገባን የፆታዎች እኩልነት ለልማት አንዱና ዋናው አስፈላጊ ነገር መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ልማት መሠረታዊ የሴቶችና የወንዶች መብት ስለሆነ ነው፡፡ ልማታዊው አስተሳሰብ በቆራጥነትና በተነሳሽነት ሲጀመር የፆታ እኩልነት አንዱና ዋና ዓላማው አድርጎ ይነሳል፡፡ ያም መፍትሔ የሚያመጣና እስካሁን ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ጠቃሚነቱም ለሁሉም ይደርሳል፡፡

# ሀገራዊ ዕውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ

*አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ*

## 1. መግቢያ

የሰው ልጅ ለመኖር ቁሣዊ፣ መንፈሳዊና ሌሎች ፍላጐቶቹ ሊሟሉለት ይገባል። እነዚህን ፍላጐቶች ለማሟላት ሰዎች ከተፈጥሮ ጋርና እርስ በርስ የማያቋርጥ ግንኙነት ያደርጋሉ። በዚህ የግንኙነት ሂደት ወቅት ዕውቀት ይፈጠራል/ይዳብራል፣ ልምድ ይካበታል፣ ክህሎት ይገኛል፣ ግንዛቤ ይሰፋል፣ ወዘተ... እነዚህ የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልገውን ከአካባቢው ያገኝ ዘንድ የሚረዱ ዕሴቶች በሀገራዊ/ባህላዊ ዕውቀት ስር ይመደባሉ። በተለያየ ምክንያት በሰዎችና በተፈጥሮ መሀል እንዲሁም በሰዎች መሀከል የሚደረገው ግንኙት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለያይ ይችላል። ይህንን ተከትሎ አገናኝ መሣሪያ ሆኖ የሚያለግለው ሀገራዊ ዕውቀትም ይቀየራል፣ ይሻሻላል።

የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልገውን ነገር በሳይንሳዊ ዕውቀት እገዛም ሊያገኝ እንደሚችል ተረጋግጧል። የምዕራቡን ዓለም ህይወት ለዚህ አባባል እንደምሣሌ መጥቀስ ይቻላል። ሳይንሳዊ ዕውቀት ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ስላለው በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ልማት ለማምጣት ያስችላል በሚል እምነት የምዕራቡ ቴክኖሎጂ ወደ ታዳጊ አገሮች ይላካል። የቴክኖሎጂ ዝውውሩ ሂደት ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም የተጠበቀውን ውጤት አላመጣም። በዚህም የተነሣ የቴክኖሎጂ ዝውውርን የልማት መሠረት አድርጐ ይወስድ የነበረው የሞደርናይዜሽን ንድፈ-ሀሣብ ክፉኛ ተተችቶ አማራጭ የልማት አቅጣጫ ማፈላለግ ተጀመረ (Gebre 2005)።

በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ ልማት የሚመጣው ከላይ ወደታች በሚወርድ የጫና አግባብ ሣይሆን ከታች ወደላይ በሚገለፅ የሰዎች ፍላጐት/ምርጫ ነው የሚለው አስተሳሰብ በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ተቀባይነት አገኘ። ይህ አማራጭ አስተሳሰብ የተለያዩ ዘርፎች አሉት። ከእነዚህ አንዱ ሀገራዊ ዕውቀትን በማጐልበት ከልማት ጋር ማጣጣም ይቻላል የሚለው አመለካከት ነው። ሀገራዊ ዕውቀት ዘርፈ-ብዙ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መጠቆም አስፈላጊ ይመስለናል። ከነዚህ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም፣ የግብርና ዕውቀት፣ ባህላዊ የሰውና የከብት ጤና አጠባበቅ ዕውቀት፣ የልጆች አስተዳደግ፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣ ባህላዊ የግጭት ማስወገድ ዕውቀት፣ ዕደ-ጥበባትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

የዚህም ጽሑፍ ዓላማ ሀገራዊ ዕውቀት ምንድነው፣ ከሳይንሳዊ ዕውቀት ጋር ያለው ተዛምዶና ልዩነት ምን ይመስላል የሚለውን ማየትና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አገራዊ ዕውቀቶች በተለይም ዕደ-ጥበባት እንዴት ከሳንይሳዊ ዕውቀት ጋር ሊጣጣሙና ለልማት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችሉ ማመላከት ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የበርካታ እደ ጥበባት ባለሀብት ናት። ሆኖም የተለያዩ እደ ጥበባት ያላቸው ታሪካዊ ጥልቀት፣ ከባሕል ጋር ያላቸው ትስስር፣ አሠራራቸው የተለወጠበት መጠን፣ የውጭ አገርና የሀገር ውስጥ የፋብሪካ ምርቶች ውድድር ለመቋቋም ያላቸው አቅምና አሰራራቸውን ለማሻሻልና ከዘመናዊ አሰራር ጋር ለማዛመድ ያላቸው እድል በጣም የሚለያይ ነው። ስለሆነም ጥቅል አስተያየት ከመስጠት በፊት የተለያዩ እደ ጥበባትን በተናጠል በየንዑስ አርዕስቱ መዳሰስ ይጠቅማል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስድስት የእደ ጥበባት ዓይነትን እንደ ምሳሌ እናቀርባለን። እነዚህም የቆዳ፣ የብረት፣ የሸክላ፣ የእንጨት፣ የሽመናና የግንባታ ሥራዎች ናቸው።

# 2. የሀገራዊ ዕውቀት ግንዛቤና ጭብጥ

## 2.1 የሀገራዊ ዕውቀት ፍቺ፣ ስያሜና ገጽታዎች

የተለያዩ ፀሐፊዎች ለሀገራዊ ዕውቀት የተለያየ ፍቺ ሰጥተውታል። ብዙዎቹ የሚያነሱት አገራዊ ዕውቀት በአብዛኛው በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠር፣ ከትውልድ ትውልድ የሚወራረስ፣ በጊዜ የተፈተነና የህብረተሰቡ ተሳታፊ አባላት ለተለያየ ጉዳይ የሚጠቀሙበት ሀብት መሆኑን ነው። በመስኩ ታዋቂ የሆነውና በርካታ ጽሁፍ ያሣተመው ዋረን (1991) ሲገልፅ፡- "ሀገራዊ እውቀት በአንድ ባህል ወይም ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ልዩ አካባቢያዊ እውቀት ነው።... ሀገራዊ ዕውቀት በግብርና፣ በጤና አጠባበቅ፣ በምግብ ዝግጅት፣ በትምህርት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን መሠረት ነው።"

ሀገራዊ ዕውቀት ፍቺው ብቻ ሣይሆን ስያሜውም እጅግ በርካታ ነው። ወደ አማርኛ በትክክል መተርጐሙ አስቸጋሪ ስለሆነ የእንግሊዘኛ ሥያሜዎችን እንዳሉ ለመፃፍ ተገደናል።

- Indigenous knowledge
- Indigenous technical knowledge
- Rural people's knowledge
- Ethnoscience
- Folk science
- Indigenous/people's science
- Traditional knowledge
- Local knowledge
- Farmer's knowledge
- Ethnoecology
- Folk knowledge

የሀገራዊ እውቀት ገጽታዎች፡-

- ከህብረተሰቡ ባህልና እምነት ጋር ተዛማጅነት ሊኖረው ይችላል፡፡
- አብዛኛው ሰው ወይም የተወሰነ ክፍል ብቻ ሊሳተፍበት ይችላል፡፡
- በይዘት፣ ቅርጽ፣ ዓይነትና ብዛት በቦታና ጊዜ ሊለያይ ይችላል፡፡
- ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፊያው በቃልና እይታ ነው፡፡
- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ይቀጥላል፡፡
- ከሌላ ሕብረተሰብ የመዋስ ሁኔታ ቢኖርም ልዩነት ጠብቆ ይሄዳል፡፡

## 2.2 የሀገራዊ ዕውቀትና ሣይንሳዊ ዕውቀት ንፅፅር

ሀገራዊ ዕውቀትና ሣይንሣዊ ዕውቀት ሁለት የተለያዩ ዘርፎች እንደሆኑ በአብዛኛው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች መሀል ልዩነቶች አሉ፡፡ ዋነኛው ልዩነት ሳይንሳዊ ዕውቀት በመደበኛ ቋንቋ፣ በሂሣብ ቀመርና በጽሕፍ የሚገለፅ ዓለማዊ ዕውቀት ሲሆን ሀገራዊ ዕውቀት ግን በጽሑፍና በቀመር የማይተነተንና በአብዛኛው ዓላማዊና መንፈሳዊ አስተሳሰቦችን አጣምሮ የያዘ ዕውቀት መሆኑ ነው፡፡ በአብዛኛው የሚጠቀሱ ልዩነቶቹ እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡፡

ሰንጠረዥ 1. የሀገራዊና ሳይንሣዊ ዕውቀቶች ልዩነት

| ሀገራዊ ዕውቀት | ሣይንሳዊ ዕውቀት |
|---|---|
| ዓላማዊና መንፈሣዊ | ዓለማዊ |
| በመስማትና በማየት ይታወቃል | በማንበብ ይታወቃል |
| ግምታዊ (intuitive) ተጨባጭ ያልሆነ | ምክንያታዊ (አናልቲካል) ተጨባጭ |
| አካባቢያዊ ይዘት ያለው | ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው |
| ለመማር ጊዜ ይፈጃል | በአጭር ጊዜ መማር ይቻላል |
| ዝቅተኛ ቦታ ይሰጠዋል | ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል |

ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች ተመሣሣይነትም እንዳላቸው ማጤን ያስፈልጋል። ዕውቀት ለማፍራት/ለማዳበር የሚጠቀሙበት ዘዴ ተቀራራቢነት (ለምሣሌ ምልከታ፣ ሙከራ፣ ድግግሞሽ) እና ለሰው ልጅ ችግር መፍትሄ መሆናቸው በአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ የተነሣ ልዩነት ላይ ማተኮሩ አግባብ አይደለም የሚሉ አሉ። ለዚህም አንዱ ምክንያት የሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች ተመሣሣይነት እንዳይታይ ይጋርዳል የሚል ሲሆን ሌላው እያንዳንዱ የእውቀት ዘርፍ የውስጥ ልዩነት የሌለው ያስመስላል የሚል ነው። ሶስተኛው ሥጋት ልዩነት ላይ ማተኮሩ ሣይንሳዊ ዕውቀትን የተሻለና ተመራጭ አድርጐ ሀገራዊ ዕውቀት ዝቅተኛ ደረጃ እንዲሰጠው ያደረጋል የሚል ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ሥጋቶች አግባብነት ያላቸው ቢሆንም ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ማነፃፀሩ የማናመልጠው ሀቅ ብቻ ሣይሆን ምናልባትም ጠቃሚ አካሄድ አድርጐ መውሰድ ይረዳል። ዛሬ በምንገኝነበት የዓለም ሁኔታ ሁለቱን ክስተቶች አማራጭ የዕውቀት ምንጭ ወይም አማራጭ የልማት መሠረት አድርጐ መውሰድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ይልቁንም መሆን ያለበት የሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ልዩነትና የእያንዳንዱን ድክመት ተገንዝቦ ተዛማጅና ተደጋጊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለይቶ መጠቀም ነው። ሀገራዊ ዕውቀትንና ሳይንሳዊ ዕውቀትን በሁለት የተለያየ ጐራ እንደሚገኙ ተቃራኒ ነገሮች ሣይሆን በአንድ መሥመር ጫፍና ጫፍ የሚገኙና በመሀል የሚገናኙ ሁለት ክስተቶች አድርጐ መውሰዱ ዘርፎቹ እንዲደጋገፉ መንገድ ይከፍታል።

| ሀገራዊ ዕውቀት ያለው ተራ ገበሬ | ⟷ | ሳይንሳዊ ዕውቀት ያለው የግብርና ሣይንስ ሊቅ |
|---|---|---|

ከላይ በቀስት በተገለፀው ሁኔታ ጫፍና ጫፍ የሚገኙት ገበሬና የግብርና ሣይንስ ሊቅ ስለግብርና የተለያየ ደረጃ ዕውቀት አላቸው፡፡ በሁለቱ መሐል ደግሞ ስለሀገራዊውና ሳይንሳዊው ዕውቀት የተለያየ ግንዛቤ ያላቸው በርካቶች አሉ፡፡ ለምሣሌ ያህል ከገበሬው ጫፍ አካባቢ ተነስተን የሀሣብ መስመሩን ተከትለን ወደ ሊቁ ጫፍ አቅጣጫ ብንጓዝ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚያገኙ ገበሬዎች፣ የገጠር ተማሪዎች፣ የገጠር መምህራን፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች፣ የብዙሃን መገናኛ ሠራተኞች፣ የግብርና ሣይንስ ተማሪዎች፣ የግብርና ሣይንስ መምህራን፣ ወዘተ ልናገኝ እንችላለን፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ሰዎችና ሙያተኞች አማካኝነት ዕውቀት ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ ስለሚጓጓዝ ሀገራዊና ሳይንሳዊ ዕውቀትን ማገናኘት ይቻላል፡፡ ሌላውም የዕውቀት ዘርፍ እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊገናኝና ሊደጋገፍ እንደሚችል መገንዘብ ያሻል፡፡

## 2.3 ሀገራዊ ዕውቀትና ልማት

በባህልና ልማት መሀል ቁርኝነት እንዳለ ከተገለፀ በርካታ አመታት አልፈዋል፡፡ ለአውሮፖዊያን ዕድገት ተራማጅ ባሕላዊና እምነታዊ አመለካከቶች አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን የዘገበው ማክስ ዌበር በስፋት በዋቢነት ይጠቀሣል (Weber 1930) ፡፡ በኤሲያ በተለይም በሩቅ ምሥራቅ አካባቢ ለታየው ዕድገት ባህላዊ ምክንያት ሲሰጠው እናስተውላለን (Sen 2001)፡፡ ነገር ግን በቴክኖሎጂ ወሳኝነትና በላይነት የሚያምኑት የዘመናዊነት ንድፈ-ሀሳብ አራማጆች ሀገራዊ እውቀት የልማት እንቅፋት ነው ያሉበት ወቅት እንደነበር ይታወሣል (Huntington & Weiner 1987; Black 1991; Crewe & Harrison 1998)፡፡ የነበረው ዘመናዊነት አስተሣሰብ ተተችቶ ሀገራዊ እውቀት ከልማት ጋር ገንቢ ቁርኝት አለው ወደሚለው አቋም መመለስ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክቷል (Gebre 2005)፡፡

ለተገለፀው የአስተሳሰብ መቀየር ዋናው ተጠቃሽ ምክንያት ከላይ ወደታች በሚወርድ ውሣኔ ልማትን ማምጣት አስቸጋሪ መሆኑን መታመኑ ነው፡፡ በሌላ አባባል ልማት እንዲመጣ ከተፈለገ ህዝቡን በውሣኔ አሰጣጥ ማሳተፍ፣ የህብረተሰቡን ፍላጐትና ባህል ግምት ውስጥ ማስገባት፣ እንዲሁም በአካባቢው የሚገኘውን ሀብትና ዕውቀት መጠቀም የግድ እንደሚሆን በስፋት ታመነበት፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ነው አገራዊ ዕውቀትም ትኩረት እያገኘ የመጣው፡፡

ግሪጐሪ ናይት (1974) የተባለው ተመራማሪ ምናልባትም የመጀመሪያው የሀገራዊ/ባህላዊ ዕውቀትን ጠቃሚነትና ወሣኝነት መስካሪ ሣይሆን አይቀርም፡፡ በታንዛንያ ንይሃ አካባቢ ግብርና ላይ ጥናት ያደረገው ናይት (1974) እንደዘገበው ከሆነ "አንድ ህብረተሰብ መልክ የያዘ አስተሳሰብ፣ በጊዜ የተፈተነና ባህል ሆኖ ለተከታታይ ትውልድ የቆየ እውቀት ይኖረዋል፡፡...ንይሃ ወይም ሌሎች ስለተፈጥሮ የሚያስተምሩን አንዳንድ ነገሮች አሏቸው፡፡" የናይት ሥራ ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ እነ ዋረን (1990፣ 1989)፣ ቻምበርስ (1992፣ 1980)፣ ብሮከንሻ (1980)፣ ሰራገልዲንና ታቦሮፍ (1994)፣ ዩኔስኮ (2000፣ 1995)፣ ገብሬ (2005)፣ እንዲሁም ሌሎች ስለሀገራዊ ዕውቀት ብዙ ዘግበዋል፡፡ ብዙዎች የሚጋሩት ሀሣብ የልማት ታዳሚ ህዝብ ባህላዊ ዕውቀት ስላለው ይህንን የዕውቀት ሀብት ልክ እንደተፈጥሮ ሀብትና ገንዘብ መጠቀም ለስኬት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚለውን ነው፡፡

ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ ይህ የሚገለጸው እንደአካባቢው ሁኔታ የሀገራዊ ዕውቀትን አስፈላጊነት ተገንዝቦና አስገንዝቦ በስፋት መጠቀም፣ የሀገራዊ ዕውቀት ውጤቶችን ጥራት አሻሽሎ ለሀገርና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ ሙያውን/ክህሎቱን እንደዚሁ አሻሽሎ ብክነትን መቀነስና ሌሎችንም ያጠቃልላል፡፡

## 2.4 ስጋቶችና አስቸጋሪ ሁኔታዎች

- አገራዊ ዕውቀት ዘመናዊ ገጽታ ሲሰጠው ጥበቃና እንክብካቤ ካልተደረገለት ባህላዊ ቅርስነቱንና የማንነት መገለጫነቱን ሊያጣ ይችላል፡፡
- አንዳንድ አካባቢ የእጅ ሙያ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጠው ማህበራዊ ቦታ ዝቅተኛ ስለሆነ የሙያውን ዕድገት ክፉኛ ይፈታተናል፡፡
- ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ በተለይ ወጣቱ ክፍል የከተማ ኑሮንና የውጭ አገር ዕውቀት ውጤቶችን ስለሚመርጥና ስለሚያደንቅ ባህላዊ ዕውቀት ተቀባይነት እያጣ ይሄዳል፡፡
- ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የሀገራዊ ዕውቀት ዘርፎች በሀገር ልማት ዕቅድ ውስጥ አይካተቱም፤ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና አይሰጥም፤ የገበያ ሁኔታም አይመቻችላቸውም፡፡
- ሀገራዊ ዕውቀት በጽሑፍ አይቀመጥም፤ ለመደበኛ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ አይመችም፤ አንዳንዶቹ እንዲያውም በምስጢር ይያዛሉ፡፡
- ተመራማሪዎች የመጀመሪያው ሥራ መሆን ያለበት ሀገራዊ ዕውቀትን መለየት፣ ማጥናት፣ መዝግቦ መኖርና አሻሽሎ መጠቀም ነው ይላሉ፡፡ ሀገራዊ

ዕውቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ እየተሻሻለ የሚሄድ ስለሆነ በጥናት ወቅት ባሣየው ባሕርይ ብቻ ዘወትር ሊገለፅ አይችልም።

- በጭፍኑ ሀገራዊ ዕውቀትን የልማት አማራጭ መንገድ አድርጐ መውሰድ የሰውን ልጅ ጥንት ወደነበረበት ለመመለስ የማሰብ ያህል ነው የሚሉ አሉ።
- ስለሀገራዊ እውቀት በስፋት የተዘገበው ባደጉት አገር ተመራማሪዎች በመሆኑ በርግጥም በመፍትሔነቱ ታምኖበት ነው ወይስ ታዳጊ አገሮች እዚያው ራሳችሁን ቻሉ ለማለት ታስቦ ነው የሚሉ ተጠራጣሪዎችም አሉ።

## 3. እደ ጥበባት እንደ ሀገራዊ እውቀት ምሳሌዎችና ከልማት ጋራ ያላቸው ትስስር

በዚህ ንዑስ ክፍል በመጀመሪም ስለ እደ ጥበባት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ቀጥሎም በኢትዮጵያ እደ ጥበባት ከሥርዓተ ፆታና ሥርዓተ መደብ ጋር ያላቸውን ትስስር እንዳስሳለን። ከዚያም በመቀጠል በታሪክ ሂደት የመጡ ለውጦች እደ ጥበባትን እንዴት እንደቀየሩ በማየት በተለይም የውድድር፣ የአደረጃጀት ሥርዓቶች የአስተሳሰብ ተጽእኖና የጥሬ ዕቃ መቀነስ የተለያዩ እደ ጥበባት ዘላቂነት የሌላቸውና አጠራጣሪ እንዲሆኑ ቢያደርጉ እንኳ፤ ለምን የተለያዩ እደ ጥበባት ቀጣይነት እንደሚኖራቸው ለማስረዳት እንሞክራለን። በመቀጠልም እደ ጥበባትን ለማዘመን ከተደረጉ ጥረቶች መሀል በመንግሥትም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችም እርዳታ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማቅረብ ሀገራዊ እውቀትን ከተዛማጅ ቴክኖሎጂ ጋር ለማቀናጀት የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች ናቸው የሚባሉት ምክንያቶች ይፈተሻሉ። ብዙውን ጊዜ ችግሩ ከባህል የመነጨ ሳይሆን የገበያ ሁኔታና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ተመጣጣኝ አለመሆንና የአደረጃጀት ሥርዓቶችና የእደ ጥበባት የሥራ ባህርይ አለመመጣጠን ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ብሎ መከራከር ይቻላል። በመጨረሻም እደ ጥበባት ለሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዲችሉ ዕድገታቸው ከገበያ፣ ከከተማ ፍላጎትና ከቱሪዝም ጋር መያያዝ ሲኖርባቸው ስለ እደ ጥበባት ያለንን አስተሳሰብ ግን መለወጥ መቻል አለብን። ባህላዊ ወይንም ሀገራዊ እውቀት ለማዘመንና ከሳይንሳዊ እውቀት ጋር ለማዛመድና ለማጣጣም ከተፈለገ ሀገራዊ እውቀት ሳይናቅ ተከብሮ ጠቃሚ ጎኑ እንዲታመንበት ያስፈልጋል።

### 3.1 እደ ጥበባት ከታሪክ አንፃር

ለተሻለ ግንዛቤ እንዲያመች የተወሰኑትን እደ ጥበባት እንደ ምሳሌ ከተጠቀሱት ጉዳዮች አንፃር ባጭሩ ማነፃፀር አስፈላጊ ይሆናል። ከታሪክ አንፃር የቆዳ መፋቅ ሥራ እጅግ በጣም ጥንታዊ እንደሆነ ይታመናል። በዓለም ላይ እስከአሁን ድረስ

በድንጋይ በተለይም በባልጩት ቆዳ የመፋቅ አሠራር የሚገኘው በደቡብ ኢትዮጵያ ብቻ ነው፡፡ የተጠረቡ ወይንም በሌላ ድንጋይ በማጋጨት የተቀረጹ የድንጋይ መሣሪያዎች ከ 200,000 ዓመታት በላይ - ምናልባትም ከአንድ ሚልዮን አመታት በላይ - እድሜ ያላቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ተገኝተዋል፡፡ ይህንንም በማየት አንዳንድ ምሁራን የዛሬ ፋቂዎችን በማጥናት ስለ ጥንታዊ ሰዎች ዕውቀትና አጠቃላይ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል ብለው ነበር፡፡ ሆኖም ይህ አመለካከት ሶስት ዐቢይ ምክንያቶች፡፡

1. ፋቂዎች (ቆዳን ለማለስለስ ፣ ፀጉር ለማስለቀቅ ፣ ቀለም ለመቀባትና ለማስዋብ) የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎችና የአሠራር ዘዴዎች እድሜ ከተወሰኑ ሺህ አመታት በላይ መሆኑም አጠራጣሪ ነው፡፡

2. ፋቂዎች ከገበሬዎችና ከነገስታት ሥርዓቶች የተሳሰረ ታሪክ ኖሯቸው በነበሩት ሥርዓቶች ውስጥ የራሳቸው የሥራ ድርሻ ተሰጥቷቸው አኗኗራቸው ከሌላው ህብረተሰብ ጋር የተያያዘና በበታችነት የታሰሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ስለዚህም ይህ ሁኔታ የሚጠቀሙበትን መሣርያ አይነትንና አሠራርን ሳይለውጠው አይቀርም፡፡

3. የራሳቸው ለየት ያለ ዘር፣ ቋንቋና ባህል ሊኖራቸው ይችላል የሚለው አስተሳሰብ አሳማኝ መረጃ አልተገኘለትም፡፡ አብዛኞቹ የእደ ጥበባት ሠራተኞች የሚናገሩት ቋንቋ አብረው ከሚኖሩት ህብረተሰብ ጋር አንድ ሲሆን ቢበዛ የዘይቤ ልዩነት ሊኖር ይችላል፤ ወይንም ከሙያቸው ጋር የተያያዙ ቃላቶችንና አንዳንድ የሚስጥር ቃላቶችን ይጨምራሉ፡፡

የሸክላ ሥራን ስንመለከት በሰሜን ኢትዮጵያ የጥንት ታሪክ ጥናት እንደሚያመለክተውና እንደነአክሱም አካባቢ የጥናት ቁፋሮዎችም እንደሚያሳዩት የሸክላ አሰራር ዘዴዎችን ለብዙ ዘመናት ያልተቀየሩ መሆኑንና የምርት ውጤቶች በተለይ የቤት ቁሳቁሶች እንደነበሩ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የብረት ሥራን ስንመለከት ረጅም ታሪክ አለው፡፡ የብረት ማቅለጥ እውቀት በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የቆየ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የማረሻ አሰራር ከክርስቶስ በፊት በነበረው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በአክሱም ዘመን ወርቅ በማቅለጥ የተሰሩ የፍራንክ አይነቶች ዝነኛ ናቸው፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ የዲሜ ብሔረሰብ አባላት የብረት አቅላጮች ታዋቂ ሆነው እስከ አብዮቱ ጊዜ ያመርቱ ነበር፡፡

የእንጨት ሥራን ስንመለከት የጥንት ባህል መሆኑ ይታወቃል። በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙት ከእንጨት የተሰሩ የአንገት ማስደገፊያዎች (ቦርኮቶ የሚባሉት) በተመሳሳይ አሠራር በጥንት የግብጽ የመቃብር ፒራሚዶችም ውስጥ ተገኝተዋል። የእንጨት ሥራ መሳሪያዎች ከብረት የተሰሩ በመሆናቸው ከብረት ሥራ ታሪክ ጋር ትስስር ሳይኖረው አይቀርም።

ወደ ሽመና ሥራ ስንዞር የጥጥ ዘርና የእንጨት ሥራ የሽመና አሠራር ጥበብ ከዓረብ ሀገሮች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መጥቶ እንደነበር የታሪክ መረጃዎች ያመለክታሉ። በደቡብ ኢትዮጵያም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የሽመና አሠራር እንደተስፋፋ ተረጋግጧል።

በመጨረሻም የግንባታ ሥራን ስንመለከት አሰራራቸው የሚያስደንቅ የአክሱም ሀውልታት እንደዚሁም በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የድንጋይ የመቃብር ምልክቶች፣ የላሊበላና የትግራይ የዋሻ አብያተ ክርስትያናት፣ የጎንደር ግንቦችና ቤተ መንግሥቶች ቀጣይነት ያለው ከዘመን ወደ ዘመን የተሸጋገረ የግንባታ ሥርዓት መኖሩን ያመለክታሉ። ምንም እንኳን አንዳንድ የውጭ ምሁራን እነዚህ የግንባታ ባህሎች ከውጭ የመጡ ናቸው ብለው ለመከራከር ቢሞክሩም የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ የድንጋይና የእንጨት የግንባታ ጥበብ ጥንታዊና ለዚህም የደብረ ዳሞ ገዳም አሠራር በቂ መረጃ ሊሆን ይችላል።

## 3.2 እደ ጥበባትና የፆታና መደብ ሥርዓቶች

የብረትና የእንጨት ሥራ የወንዶች የሥራ ክፍል ሲሆን የቆዳ ሥራም (ከኮንሶና ሲዳማ ብሔረሰቦች በስተቀር) እንደዚሁ የወንዶች የሥራ ድርሻ ነው። የሸክላ ሥራ ብቻ በሴቶች ሲመራ የሽመና ሥራ የወንዶች ሲሆን የሴቶች በጥጥ ፈተላ አጋርነት ያስፈልገዋል።

የእደ ጥበብ ሥራ ለህብረተሰብና ለዕለት አኗኗር ወሳኝ ሚና ቢኖረውም ሰራተኞቹ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል አንፃር የሚሰጣቸው ማህበራዊ ቦ  በጣም ዝቅተኛ ነው። በቀደምት ሥርዓቶች ወቅት መሬት መያዝ አይችሉም ነበር። በአንዳንድ አካባቢዎች እንስሳት ማርባትና ሰብል መዝራት አይፈቀድላቸውም ነበር። ከሌላው ህብረተሰብ ጋር መቀላቀል አይችሉም ነበር። በጋብቻና በሞት ሥነሥርዓቶች ላይ ሲገኙ ለብቻ ነው የሚቀመጡት። የሚሰጣቸው ምግብ የተለየ ወይንም ያልተፈለገ ትርፍራፊ የሆነ የሚጠጡበት ኩባያና የሚበሉበት ሳህን የሚጣል፣ የሚሰበር ወይንም ለብቻ የሚቀመጥ፣ በቀብር ሥነሥርዓት የሚሳተፉት በመቃብር ቆፋሪነት ወይንም ሙዚቃ መሳሪያዎችን በመንፋት ነበር።

ከዚህም ሌላ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን ክፉ ዓይን እንዳላቸውና ሰውን እንደሚጎዱ ይታመን ነበር። ከነሱ ጋር ጋብቻ መፈጸም ፈጽሞ የተከለከለ ነበር። በተቃራኒው በእጅ ሙያቸው በአንዳንድ አካባቢ በህክምና በተለይ በወጌሻነት የእደ ጥበብ ሠራተኞች የታወቁ ነበሩ። በእኩል ዓይን የማይታዩበት ምክንያቶች ባሕላዊና ውስብስብ ስለሆኑ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በዝርዝር አንገባበትም። ሆኖም በዘር ልዩነት ወይንም በሥርዓተ መደብ በቀላሉ ሊብራራ እንደማይችልም ሳናስገነዝብ አናልፍም። ሁሉም ዓይነት የእደ ጥበብ ሙያተኞች ባንድ ዓይን አይታዩም። በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ወደ እንጨት ሥራ የገቡ የቀድሞ አዳኞች በአብዛኛው አካባቢ ከሁሉም በላይ የተናቁና የተገለሉ ነበሩ። የቆዳ ሠራተኞች ከብረት ሰራተኞች ዝቅ እንደሚሉና የብረት ሠራተኞች ደግሞ በአንፃሩ ከሸክላ ሠራተኞች ዝቅ ያሉ እንደሆኑ ተደርጎ የመውሰድ አዝማሚያ በብዙ አካባቢ ይስተዋላል። ሸማኔዎችና አዳኝ ያልነበሩ የእንጨት ሰራተኞች በአብዛኛው የገጠር አካባቢዎች አይናቁም። ሆኖም ወደ ከተሞች ሲመጡ የከተማ ነዋሪዎች ዝቅ አድርገው ይመለከትዋቸው ነበር ነበር። እንደምሳሌ ዶርዜዎችን መጥቀስ ይቻላል።

## 3.3 ለውጦችና የእደ ጥበባት ቀጣይነትና ዘላቂነት

ምንም እንኳ እደ ጥበባት ለብዙ ዘመናት ሳይቀየሩ ቆይተዋል የሚል አስተሳሰብ በብዙ ሰዎች አእምሮ የተቀረፀ ቢሆንም የእደ ጥበባት አሠራር ዘዴዎች ብዙ ለውጦች አሳይተዋል። ለምሳሌ ያህል ጥሬ ዕቃን ብንመለከት ሸማኔዎችና የብረት ሠራተኞች በገበያ የሚያገኙዋቸው ጥሬ እቃዎች ላይ የነበራቸው መተማመን እየጨመረ መጣ። የእንጨት ሠራተኞች ደኖች በመጨፍጨፋቸውና በመመንመናቸው ሥራቸው ተጎድቷል። እንደዚሁም የብረትና የሸክላ ሠራተኞች ከሰልና እንጨት ስለሚያስፈልጋቸው በእንጨት መጥፋትና የዋጋ መናር ተጎድተው ነበር።

የእደ ጥበባት አሠራር ዘዴዎች ለብዙ ዘመናት በዝግመት እንጂ በፍጥነት ሲቀየሩ አይስተዋልም ነበር። ሆኖም የብረት ማቅለጥ እውቀት በመጥፋት ላይ ይገኛል። ለመጨረሻ ጊዜ የታየው በደቡብ ኢትዮጵያ በዲሜ አካባቢ በ1980 ዓ.ም. ነበር። የጉራጌ ብረት ሠራተኞች ወደ ከተሞች ፈልሰው የተሻለ መሳሪያ በማግኘት ምርታቸውን ማሻሻልና ተጨማሪ የሠው ሀይል በመቅጠር ውጤታማነታቸውን መጨመር ችለዋል። አንዳንዶቹ የፋብሪካ ውጤቶች በማየት ተመሳሳይ መሳሪያዎች ለምሳሌ ወጥመድ፡ ሚዛን፣ ጋሪና የመስኖ ቱቦዎች ሰርተዋል። ጥቂቶቹ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ መቁረጫዎችና መበየጃዎች ገዝተው ይጠቀማሉ። በሽመና ስራ ዋና ለውጦች የፋብሪካ ክሮች መጠቀምና የጥበብ አሠራር ፈጠራዎች

ናቸው። ለዚህም የሴቶች ልብስ የአለባበስና አሠራር ፉክክር ራሱን የቻለ ድርሻ ነበረው።

በአጠቃላይ ስንመለከተው የባህላዊ እደ ጥበባት አሠራር ከብዙ አንጻር ቀንሰዋል ማለት ይቻላል። የቀነሰበት ምክንያቶች የተለያዩ ሲሆኑ ሁሉም የእደ ጥበባት ዓይነቶች እኩል እንዳልተጠቁ ለመገንዘብ ይቻላል። ምክንያቶቹን በሶስት ልንከፍላቸው እንችላለን:: እነሱም የገበያ ውድድር ሥርዓትና አስተሳሰብ እንዲሁም የጥሬ ዕቃ መጠን መቀነስና ዋጋ መናር ናቸው።

ውድድርን ስንተነትነው ከውጭ የመጡ እቃዎች ተጽእኖ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ መገመት ይቻላል። ሀረር አካባቢ እ.እ.አ. በ1888 ፓውሊትችከ የሚባለው ፀሐፊ ከውጭ መጡ ጨርቆችና የብረት እቃዎች የእደ ጥበብ ሥራ እንዲአቆሉቁል አድርጎታል ብሎ ጽፎ ነበር። እንዲሁም ሜራብ የሚባለው ሀኪም አዲስ አበባ አካባቢ የብረትና የሸማ ሥራ ከጀርመን ሀገር የሚሰሩ የብረት እቃዎችና ከማንቸስተር የሚሰሩ የፋብሪካ ጨርቆች ጋራ መወዳደር እንደማይችሉ እ.እ.አ. በ1909 ሲተነብይ ነበር። በዚያን ጊዜ ይሄንኑ ፀሐፊ የአውሮፓ ልብስ የሚለብሱ ኢትዮጵያውያን ከ100 እንደማይበልጡ ገምቶ ነበር። ሆኖም የስፌት መሳሪያዎችን ነጋዴዎች በማስመጣታቸው ሁኔታው በፍጥነት ተለወጠ።

በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩት መንግሥታት በአፄ ሚኒሊክ ጦር ሲሸነፉ የእደ ጥበባት ሠራተኞች ከነገሥታቱና ከባላባቶቹ ጋር የነበራቸው ትስስር በመቋረጡ ለሚሠሩት ዕቃዎች የነበረው ፍላጎት በመቀነስ የአንዳንድ እደ ጥበብ ሙያ፣ በተለይም የወርቅ ስራ እንዲቀንስ አድርጎ ነበር ይባላል። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ሀገረ ገዢዎች የቆዳ ልብስ መልበስ ኋላ ቀር ነው በማለት ማስከልከላቸው ይታወሳል። በአሁኑ ወቅት በደቡብ ኦሞ ከሚኖሩ እንደ ሀመር ብሔረሰብ ሴቶች በስተቀር ቆዳ መልበስ ቀርቷል። በአሁኑ ጊዜ ለጋብቻ በጥሎሽ መልክ በዳውሮ እንደሚሰጡት በቀለም የሚጌጡ ቆዳዎች በስተቀር ባህላዊ የቆዳ ስራ እየጠፋ ነው ማለት ይቻላል። የቆዳ ውጤቶች በዓለም ደረጃ ዋጋቸው እየጨመረ መምጣቱ በባህላዊው የቆዳ ሥራ ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ አሳርፏል።

እንደዚሁም የሽመናን ሥራ በተመለከተ ከውጭ ሀገር የሚመጡ ጨርቆች ባገር ውስጥም በስፌት መኪናዎች ልብሶች እየተሰፉ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች እየተመሠረቱ በቅርቡ ደግሞ የአሮጌ ልብስ (ሳልቫጅ) እና ከቻይና የሚመጣ ልብስ ወረራ እየተስፋፋ ሲመጣ የሽመና ሥራ ውጤቶች ፍላጎት እንዲቀንስ አደረገ። ሆኖም የሽመና ሥራ እንዲቀጥልና በአንዳንድ ረገድ እንዲስፋፋ ያደረገው ባህላዊ ተፈላጊነቱ ነው ማለት ይቻላል። ሴቶች ከቤት ሲወጡ ነጠላ ወይንም የአንገት

ልብስ የመልበሰ ልምድ ሥርዓት ደግሞ የማዘቅዘቅ ባህል ሴቶች ነጠላ እንዲኖራቸው አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ ከዚያም በላይ የሀበሻ ልብስ ተብሎ የተሰየመው ለዓመት በአል በተለይ በከተሞች ለሰርግም ለዝነጣም የጥበቡ ርዝመት በመጨመሩ እየተኮራበት ሸማኔዎችና የልብስ ስፌት ቤቶች እየተፎካከሩበት ራሱን የቻለ ህይወትና ህልውና አግኝቷል፡፡

የሸክላ ሥራን ከተመለከትን ከውጭ የሚመጡ የብረት፣ የብርጭቆና የፕላስቲክ ዕቃዎች ከዚያም በተጨማሪ የአገር ውስጥ የፋብሪካ ምርቶች እንደነ ጀሪካን፣ ፌስታል ወዘተ እየተስፋፉ በሄዱ ቁጥር የሸክላ ስራ ተፈላጊነት እንዲቀንስና እንዲያቆለቁል አድርጎታል፡፡ በ1977 ዓ.ም. የነበረው ድርቅና ረሀብ የእርዳታ ዘይት የመጡበት ቆርቆሮና የፕላስቲክ መያዣዎች ይህንን ለውጥ ማፋጠን ጀምሮ ነበር፡፡ እነዚህ የፕላስቲክና የብረት እቃዎች ክብደታቸው ከሸክላ የቀነሰ በመሆኑና በቀላሉ ስለማይሰበሩ ዘላቂ በመሆናቸው የገጠር ነዋሪዎች ይመርጧቸው ጀመር፡፡ ሆኖም የሸክላ ውጤቶች ርካሽ በመሆናቸው ቢሰበሩም ተጥለው እንደገና በርካሹ መገዛት ስለሚችሉ ከገበያ በራቁ አካባቢዎች በፍጥነት አልተተኩም፡፡ በከተማ አካባቢም የተሻሉ ምርቶች እየተስፋፉ ናቸው፡፡ ለምሳል ያህል የቀጨኔ ሸክላ ስሪዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የብረት ሥራን ስንመለከት የፋብሪካ መሳሪያዎች ከውጪም በሀገር ውስጥም በፋብሪካ በመሰራታቸው የባህላዊ ብረት ሥራን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ ሊተካው አይችልም፡፡ የብረት ሠራተኞች በየገጠሩ ዋና ሚና ማረሻና ሌሎች የእርሻ መሳሪያዎች ሲበላሹ መጠገንና ስለታቸው ሲደነዝዝ ማሾል ነው፡፡ ይህ ሥራ ምን ጊዜም አስፈላጊ መሆኑ አይቀርም፡፡

የእንጨት ሥራን ስንመለከት የደኖች መመናመን በተለይ ትላልቅ ጠንካራ እንጨት ያላቸው ሀገር በቀል እንደነ ዝግባ ያሉ ዛፎች ብዛት መቀነስና የደን ጥበቃ ህጎች፣ ሥርዓቶችና ቁጥጥሮች የባህላዊ እንጨት ሥራ እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡ ሆኖም አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ባህላዊ እቃዎችና ቁሳቁሶች ለምሳሌ የቡና ረከቦት፣ በርጩማና የእርሻ መሳሪያዎች በባለሙያዎች መሥራታቸው የትላልቅ ሀገር በቀል የደን መመናመንና የእንጨት ሥራ ምርቶች ሽያጭ መከልከል ባህላዊ እንጨት ሥራ ጥበብን አዳክሞታል፡፡ በሌላ በኩል የነበሩት ጥናታዊ ምርቶችና ባህላዊ ዕቃዎች በብዛት ለአገር ጎብኚዎች እየተሸጠ በመሆኑ የእንጨት ዕደጥበብ ውጤቶች ከሀገር እየጠፉ ነው፡፡

በመጨረሻም የግንባታ ሥራን ስንመለከት በየአካባቢው የቤት ሥራ የተለመደ ሲሆን የአናጢ፣ የግንበኛ፣ የለሳኝ ሙያዎች እየተስፋፉ ነው፡፡ የባህላዊ የቤት

አሰራር ዘዴዎችም ለምሳሌ፣ የጉራጌ የሲዳማና የኮንሶ ቤት አሠራር ራሳቸውን የቻሉ ሙያተኞች ከመኖራቸውም በላይ ባህሉ ቀጣይነት አለው፡፡ ሆኖም በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ጥንታዊ የድንጋይና የእንጨት አገነባብ ዘዴዎችና በአዲስ አበባ የጭቃና እንጨት ቤቶች አሰራር ዕውቀት ምን ያህል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደተላለፈና እንደዘለቀ ያጠራጥራል፡፡

ለማጠቃለል የእደ ጥበባት ምርቶች በተጠቀሱት ምክንያቶች የመቀነስ አዝማሚያ አሳይተዋል፡፡ ሆኖም የተለያዩ እደ ጥበባት ዘላቂነት እድል የተለያየ ከመሆኑ በላይ፡ ባህላዊ እደ ጥበባት በአጠቃላይ የሚለው የተባለው ትንቢት እውን አልሆነም፡፡

## 3.4 እደ ጥበባትን ለማዘመን ከተደረጉ ጥረቶች ምሳሌዎች

የባህላዊ እደ ጥበባት መቀነስ ወይንም መጥፋት ላገራችን ጉዳት አያጠራጥርም፡፡ በህዝብ ቁጥር መብዛት የእርሻን መሬት መጠን በመቀነሱ በገጠር አካባቢዎች ከእርሻ በስተቀር ሌላ መተዳደርያና የሥራ ዕድል መኖር አለበት፡፡ እደ ጥበባት ለገጠር ህዝብ የሥራ እድል ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ለገጠሬውም ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ ከውጭ አንዳንድ ቁሳቁሶች ከማስመጣት ይልቅ በሀገር ውስጥ ቢመረቱ የውጪ ምንዛሬ ለማዳን ይቻላል፡፡ በተለይ ባህላዊ ጥበባት ከቱሪዝም ፍላጎት ጋር በማገናዘብ ለሀገሪቷ ሆነ ለየአካባቢው ህብረተሰብ ጠቃሚ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሆኖም በመንግሥት በኩል ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በባለሀብቶችና በለጋሽ ድርጅቶች ለዚህ ጉዳይ በቂ ትኩረት የተሰጠ አይመስልም፡፡ ምናልባትም ይህ ሁኔታ ከባህላዊ አስተሳሰብና የዕደ ጥበባት ሥራ መናቅ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ የቀድሞ ነገሥታት የሚያስፈልጓቸውን የእደ ጥበብ ሠራተኞች ያቀርቧቸው እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእደ ጥበብ ሙያ እንዲስፋፋ የተደረጉ ጥረቶች ውስን ናቸው፡፡ በ1948 ዓ.ም. በኮልፌ አካባቢ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ሥም የዕደ ጥበብ ት/ቤት ተከፍቶ ነበር፡፡ በ1957 ዓ.ም. የእቴጌ መነን የእደ ጥበብ ትምህርት ቤት ተቋቁሞ ከአብዮት በኋላ የኢትዮጵያ እደ ጥበባት ማዕከል ተብሎ ተሰየመ፡፡ ሆኖም የመንግስት ፖሊሲ ትኩረት እስካሁን ግብርናና በኢንዱስትሪ ላይ ሲሆን ለባህላዊ እደ ጥበባት ትኩረት የተሰጠው አይመስልም፡፡ በደርግ ዘመን አብዛኛው ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ትኩረት ማህበራትን ለማስፋፋት ነበር፡፡ በ1969 ዓ.ም. የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና እደ ጥበባት ማስፋፊያ ድርጅት ይሄንን ዓላማ ለማሳካት ተቋቋመ፡፡ የድርጅቱ ትኩረት አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ላይ ሲሆን የእደ ጥበብ ሰራተኞችን በማህበራት ለማደራጀት የተደረገው ጥረት የተፈለገውን ውጤት ያላስገኘበት አንዱ ዋና ምክንያት የእደ ጥበብ ሰራተኞች በማህበራት የመደራጀት ልምድና ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

በቀጣይነት በ1986 የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና እደ ጥበባት ልማት ማስፋፊያ ድርጅት ተቋቋመ። ይሄም ድርጅት ትኩረቱ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ላይ ነው። በተለያዩ ዘርፎች የቆዳ ሥራን በሚመለከት ትልልቅ ፋብሪካዎች ለማቋቋም እንጂ ነባር ባህላዊ እውቀትን ለማሻሻልና ከገበያና ከቱሪዝም ጋራ ለማገናኘት የተደረጉ ጥረቶች ውሱን ናቸው። ሆኖም የእደ ጥበብ ሰራተኞች በታችነትና መናቅ እንዲቀር፤ መሬትም የማግኘት መብት እንዲኖራቸው በተለይ በደርግ ዘመን ተሞክሮ ነበር። የተወሰነ ለውጥ ቢታይ እንኳ የመናቅ ስሜት ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ማለት አይቻልም። ለቅርብ ጊዜያት አንዳንድ አካባቢዎች እንዲያውም እያንሰራሩ ነው።

የተወሰኑ ዓለም አቀፍና የውጭ እርዳታ ድርጅቶች እደ ጥበባት እንዲሻሻሉ ጥረቶች አድርገዋል። ባለፉት ሃያ አመታት ከተደረጉት ሙከራዎች አንዳንዱን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። የዓለም የምግብና የግብርና ድርጅት (FAO) የብረትና ሸክላ ሥራን ለማሻሻል ፕሮግራሞች ነበሩት። ለምሣሌ ለሸክላ ሠራተኞችን በማሽከርከር ውጤቶችን ማምረት የሚረዳ መሳሪያ ተሰጥቷቸው ሊለምዱት አልቻሉም በማለት መሳሪያዎቹ ተመለሱ። ይኼ የሚያሳየው የተሻለ አሠራርና መሣሪያዎችን ለማቅረብ የተደረጉ ጥረቶች ውሱንና ውጤታማ ያለመሆናቸው ነው። ከዚህም ሌላ ከገበያ ፍላጎት ጋር የሚሄዱ ምርቶችን የዕደጥበብ ሠራተኞች እንዲያመርቱ በማድረግ በቂ ጥረት አልተደረገም ነበር።

ኤስ ኦ ኤስ ሳሄል (SOS- Sahel) የተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከብረት ሠራተኞች ጋር በመነጋገር ያላቸውን ልምድ ለማዳበር ሙከራ አድርጎ ነበር። በወላይታ አካባቢ የሚገኙትን የብረት ሠራተኞች ከውጭ የሚመጡትን አካፋና ዶማዎች ወደ ተለመደውና በገበሬ ተፈላጊነት ያለው መኮትኮቻ እያቀለጡ እንዲለውጡ እገዛ ተደርጐላቸዋል። በመቄት አካባቢ የብረት ሠራተኞችን በማህበር እንዲደራጁ በማገዝ በኢትዮጵያ ላሉት የአውሮፓ ህብረት የጭነት መኪኖች የባሌስትራ ማስሪያዎች እንዲሠሩ ህብረቱ ኮንትራት ሰጥቷቸው ነበር። እንዲሁም አኮርድ (ACORD) የሚባለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሻሸመኔ የሚገኙ የሸክላ ሠራተኞችን የአነሥተኛ ብድር ድርጅት በየእድራቸው እንዲያቋቁሙ፣ ብድርና ስልጠናን እንዲያገኙና የተሻለ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ጥረት አድርጎ ነበር። ሆኖም አኮርድ ሲለቅና የአነስተኛ ብድር ድርጅቱ ሲስፋፋ የሸክላ ሠራተኞች አቅም አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛው ብድርና ተሳትፎ በሌሎች ዕድሮችና ግለሰቦች ተያዘ። እንደዚሁም ኤስ ኦ ኤስ ሳሄል በወላይታ የሸክላ ሠራተኞች የተሻለ ዘመናዊ ምድጃ እንዲሠሩ አሰልጥነዋቸው ነበር። ሆኖም ተፈላጊነቱ አነስተኛ ሆኖ ልምዱ ሳይስፋፋ ቀረ። አክሽን ኤይድ (Action Aid) የሚባለው ድርጅት በበኩሉ ዳውሮ

የሚገኙት ማንጃ የሚባሉትን የቀድሞ አዳኞችና የእደ ጥበብ ሠራተኞችማህበራዊ አቋም እንዲሻሻል ብዙ ጥረት አድርጓል።

## 3.5 ባህላዊ አሠራርን ለማሻሻል ጥረቶች የግብርና ዘርፍ ምሳሌዎች

በአጠቃላይ ባህላዊ አሠራርን ለመለወጥና ለማሻሻል ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል። ለምሳሌ ያህል ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (International Livestock Research Institute) የማረሻ አሠራርን ለማሻሻል ሞክሮ ነበር። ማረሻውን በሰንሰለት በማበጀት በጥልቀት በማረስ ፋንታ ሰፋ ያለ መደብርና ቦዮች መስራት እንዲቻል ተደርጓል። ይኼም የጥቁር ዋልካ አፈር በክረምት ወራት ውኃ የመቋጠር ጠባይን ለመቋቋም የሚያመች ዘዴ እንደሆነ በሙከራ ጣቢያ ተረጋግጧል። ለዚህ ቴክኖሎጂ ተስማሚ ለመብቀል ረጅም ጊዜ የሚፈጅ የተሻለ ምርጥ የስንዴ ዘርና ማዳበርያ በተቀናጀ የአቅርቦት ሥርዓት ወይንም ፓኬጅ እንዲሰራጭ ተሞክሮ ነበር። ሆኖም በሙከራ ጣቢያ የሚጠቅም አሠራርና ቴክኖሎጂ መሆኑ ቢረጋገጥም በገበሬው ዘንድ እምብዛም ተቀባይነት አላገኘም። የዚህም ምክንያት ሲጠና አጠቃላይ የአቅርቦት ሥርዓቱን አብዛኛው አርሦአደር አስተማማኝ ሆኖ አላገኘውም። ማረስ የሚአመቸው ጥቂት ዘንቦ መሬቱ ርሶ በአካባቢው አባባል "ነሸ" ሆኖ ግን ሳይጨቀይ ነው። ነገር ግን የተሻሻለው ቴክኖሎጂ አርሦ አደሩን ማዳበሪያ ስለሚያስገዛው ይኼም በመንግሥት ላይ እንዲተማመን ስለሚያደርገው ብዙም ትኩረት አልሳበም ነበር።

## 3.6 ሀገራዊ እውቀትን ከተዛማጅ ቴክኖሎጂ ጋር ለማቀናጀት የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች

በአጠቃላይ ስንመለከት ሀገራዊ እውቀትን ከተዛማጅ ቴክኖሎጂ ጋር ለማቀናጀት የሚደረጉ ሙከራዎች ብዙ ጊዜ የሚከሽፉበት ምክንያቶች መጠናት አለባቸው። እነዚህን እንቅፋቶች እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል መረዳት አለብን። የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን በአራት ዓይነት ከፍለን በአጭሩ በተከታታይ ልናነሳቸውና ምን ያህል አሳማኝ እንደሆኑ ለመገምገም ይቻላል።

### 3.6.1 ቴክኖሎጂው ራሱ ከባለሙያ እውቀትና ችሎታ ጋር አለመመጣጠን

ለምሳሌ ያህል የሸክላ ሥራን ለመሥራት የሚያገለግሉ የሚሽከረከሩ መሣሪያዎች ሸክላ ሠሪዎቹ ሊለምዱት አልቻሉም ይባላል። ሆኖም ሲጠና ብዙ ጊዜ ከነዚህ ምክንያቶች ጀርባ ሌሎች ጉዳዮች ይገኛሉ። ከነዚህም መሀል የገበያ ሁኔታና አዲስ የምርት ዓይነቶች ተቀባይነት ወይም ተፈላጊነት ስለሌላቸው ወይንም ዋጋቸው ከገዢ አቅም ከፍ ማለት ሊሆን ይችላል።

እንደዚሁም የስፊ መደብ ማረሻው ገበሬዎች ከለመዱት ውጪ በመሆኑ አልወደዱትም ተብሎ ነበር። ሆኖም ምንም እንኳ የተቀየረው ማረሻ ለገበሬዎች ለመሸከምና ለበሬዎች ለመጎተት ያስቸግራቸዋል ቢባልም የብዙ ገበሬዎች ዋና ስጋት የነበረው የአስተራረስ ዘዴው አስተማማኝ ካልሆነው የመንግሥት የዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት መተሳሰርና የብድር ማነቆ ውስጥ መግባት ነበር።

### 3.6.2 ቴክኖሎጂ ከአካባቢው ባህል ጋር ሊዛመድ አለመቻሉ

ይህ ምክንያት ማለትም ለማንኛውም ልማት አለመሳካት ባህልን መወንጀል ወይም ሰበብ ማድረግ በተለይ አዲስ ቴክኖሎጂ በሚአመጡ ድርጅቶች በጣም የተለመደ ነው። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ኢልሪ (ILRI) በምርጥ ዘር ዲቃላ ላሞች ማረስ እንደሚቻል በሙከራ ጣቢያቸው ማረጋገጥ ቻሉ። ላሞቹን ለሶስት ጥቅም ማዋል ቻሉ፤ ማለትም ለርቢ ለወተትና ለእርሻ። ገበሬው በአንድ ከብት ሶስት ጥቅም አግኝቶ ወጪውንም ቀንሶ ምርታማነቱን ጨምሮ የከብቱም ብዛት በመቀነስ አካባቢውንና ተፈጥሮን መጠበቅ ይችላል በሚል እምነት ላሞች ለገበሬዎቹ በብድር ታደሉ። ነገር ግን ላሞቹን ወስደው ለእርሻ መጠቀሙን ሲተው ድርጅቱ ሙከራውን ያከሸፈው በባህል በሴት እንስሳ ማረስ የተከለከለ ስለሆነ ነው ብለው ደመደሙ። ሆኖም ጉዳዩ ሲጠና ከዚህ ምክንያት ይልቅ አሳማኝ የሆኑ ከገበሬው ኑሮና ህልውና ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ነበሩ። የቀረበው አዲስ አሠራርን አብዛኛዎቹ ገበሬዎች ሀብታምም ሆኑ ደሀ አመቺ ወይንም ጠቃሚ ሆኖ አላገኙትም። ሀብታም ገበሬ ምርጥ ላም የሚፈልገው ብዙ ወተት አምርቶ ሸጦ ለመጠቀም ስለሆነ በውድ ላም ከሚያርስ ባሉት በሬዎች ቢጠቀም ይመርጣል። በሌላ ደግሞ ደሀ የሆነ ገበሬ ውድ የሆነች ላም ብትታመምበት ወይንም ብትሞትበት ከባድ እዳ ውስጥ ስለሚገባ ስጋት አደረበት። ለዚች ላም የመኖ መሬት አዘጋጅቶ፣ ፍሩሽካ ገዝቶ፣ እረኛ መድቦ፣ ወተት ሸጦ ጥቅም አግኝቶ፡ ብድሩን መመለስ ያጠራጥረው ነበር። ስለዚህም ደሀ ገበሬ ይህችን አንድ ውድ የምርጥ ዘር ላም ከሚኖረው፣ ሁለት ወይንም አቅሙ ሲፈቅድ ከዛ በላይ ከብት ወይንም በግ ፍየልና ዶሮ እያረባ ቀስ በቀስ ህይወቱን ማሻሻል ይመርጣል። አንድ እንስሳ ቢሞትበት ሌላው እንደምንም ያድነዋል። ይሄንን ስንገነዘብ ደሀ ሆነ ሀብታም ገበሬ በላም ማረስ አለመፈለግ ዝም ብሎ የባህል ተጽኖ ነው ማለት ያዳግታል። በላም ማረስ የተከለከለ ነው ቢባል እንኳ ዋነኛው የገበሬዎቹ ተቃውሞ ለኑሮዋቸው አላዋጣ ስላላቸው ነው።

### 3.6.3 የገበያ ሁኔታና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ተመጣጣኝ አለመሆን

አንዳንድ ጊዜ በተሻለ ቴክኖሎጂ ለማምረት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ወጪዎች ስላሉ ምርቱ የሚሸጥበት ዋጋ ከፍ ማለት አለበት። በምርጥ ዘር ላሞች ምሳሌ

አይተነዋል። ይሄንን ችግር ለመፍታት የገጠርና የከተማ ግኝኙነትና የመንገድና የምርት ማጓጓዣ ሁኔታ በማሻሻል ሊፈታ ይችላል እንጂ በአብዛኛው ጊዜ የእውቀት ወይንም የባህል ችግር አይደለም። ከዚያም በላይ የከተማ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የውጪ ጎብኚዎችም የእደ ጥበባት ውጤቶችን ለመግዛት ፍላጎትና አቅም ስላላቸው የእደ ጥበባት እድገትና መስፋፋት ከንግድና ቱሪዝም ጋር አብሮ መታየት ይገባዋል።

ሆኖም የገበያ መስፋፋት ራሱን የቻለ አደጋ ሊያመጣ ይችላል። ምክንያቱም ቅርስ የሆኑ የእደ ጥበባት ውጤቶች ተሸጠው ካገር ሊጠፉ ይችላሉ። ይሄም አጠቃላይ ሁኔታ ሲታሰብ የቅርስ ጥበቃ ለየት ያለ ጥንቃቄ ኖሮት የእደ ጥበባት ሥራ መስፋፋት ታሪካዊ ቅርሶች እንደነ ብራና፡ መስቀል ደግሞም ባህላዊ ቅርሶች እንደነ የጅማ ወንበሮች ወይንም የኮንሶ "ዋ.ጋ" የሚባሉ የመቃብር ሀውልቶች ወደ ውጭ ሀገር ተሸጠው እንዳይጠፉ ራሱን የቻለ ድርሻ ሊኖረው ይገባል።

### 3.6.4 የአደረጃጀት ሥርዓትና የእደ ጥበባት የሥራ ባህርይ

የእደ ጥበባት ሥራ ይስፋፋና ይሻሻል ሲባል ብዙ ጊዜ በማህበራት ሠራተኞችን ለማደራጀት የተደረጉ ሙከራዎች ይከሽፋሉ። የእደ ጥበብ ሰራተኞች እንደ ወዛደር ተቀጥረው ጥብቅ በሆነ የሥራ ሰዓትና ቦታ፣ ተሰማርተው በደሞዝ መቀጠር ከጥበብ ሠራተኞች ጠባይና የሥራ ባህሪ ጋር ላይስማማ ይችላል። ለምሳሌ ያህል ሸማኔዎች ለገበያ ለማድረስ በፍጥነት በመሠራት ለፍተው ከጨረሱ በኋላ ከገበያው ቀን በኋላ ማረፍ ይፈልጋሉ። ለየግላቸው ወይንም ሁለት ሆነው ወይም ከሚተማመኑባቸው ሰዎች ጋር በቡድን መስራት እንጂ ጥቅሙ በደንብ ያዋጣኛል ብለው ካላመኑበት እንደተቀጣሪ ደሞዝተኛ መሥራት ብዙ ጊዜ አይመርጡም። ስለዚህም ደረጃውን ጠብቆ፣ ጥራቱን አሻሽሎ፣ ከገበያ ፍላጎት ጋር አገናዝቦ፣ የእደ ጥበባት ሠራተኞች ከገዢዎች በማገናኘት ወይንም በኮንትራት የሚሠሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት የሚስማማቸው ሁኔታዎችና የምርታቸው ጥራትና ብዛት ማሳደግ ይቻላል።

## 4. ማጠቃለያ ሀሳቦች

ሀገራዊ ዕውቀትና ሳይንሳዊ ዕውቀት ሁለት በተቃራኒ ጎራ እንደሚገኙ ዘርፎች ወይም አንዱ ከሌላው እንደሚበልጥ አድርጐ መውሰድ ተመሳሳይነታቸውንና ተደጋጋፊነታቸውን ያለመረዳት ነው። ከላይ በጽሁፍ ውስጥ በዝርዝር እንደተገለፀው ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች በተቃራኒ ጎራ የተሰለፉ ወይም በደረጃ የሚበላለጡ ሳይሆኑ ይልቁንም ከላይ (ገጽ 83) የሚገኘው ቀስት እንደሚያመለክተው በአንድ መስመር ጫፍና ጫፍ ሆነው በመሀል የሚገናኙ

ተደጋጋፊ ዕሴቶች ናቸው:: ይህ አስተሳሰብ በይዘቱ አዲስ አይደለም:: በምዕራቡና በምሥራቁ የዓለማችን ክፍሎች ለታየው ልማትና ዕድገት ባህል የበኩሉን ገንቢ አስተዋጽኦ ስለማድረጉ ታሪክ ይመሰክራል:: ይሁን እንጂ በአንድ ወቅት በቴክኖሎጂ ወሳኝነት የሚያምኑት የዘመናዊነት ንድፈ-ሀሳብ ሰባኪዎች ባህልን በደፈናው የልማት እንቅፋት ነው ማለታቸው የሚታወስ ነው:: ነገር ግን ዛሬ ይህ አመለካከት ጨርሶ የተሳሳተ መሆኑ ስለታመነበት ለዘመናት የካበተ ባህላዊ ዕሴት ወይም ሀገራዊ ዕውቀት ለልማት አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል የሚለው አስተሳሰብ እንደገና ተቀባይነት ያገኘ መጥቷል:: የባህልና ልማት ቁርኝት በተለያየ መንገድ ሊገለፅ ይችላል:: ልማት የታዳሚዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተና አሳታፊ መሆን እንደሚኖርበት ይታመናል:: የሰዎች ፍላጎት ደግሞ በአብዛኛው ከባህላዊ ህይወታቸው ጋር የተሳሰረ በመሆኑ አሳታፊ የልማት አካሄድ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል፤ ለስኬትም ይበቃል:: ቀጥተኛው አግባብ ሀገራዊ ዕውቀት ከሳይንሳዊ ዕውቀት ጋር ተደጋግፎ ለልማት ግብአት እንዲውል ማድረግ ነው:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ዘርፈ-ብዙ የሆነውን ሀገራዊ ዕውቀት ለይቶ እንዴት ለልማት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚቻል ማጤን የግድ ይላል::

ከዚህ አንፃር ይህ ጽሑፍ ትኩረቱን በኢትዮጵያ ዕደ-ጥበባት ላይ አድርጓል:: ኢትዮጵያ በታሪክ የእደ ጥበባት ባለፀጋ ብትሆንም እንኳን ሙያተኞቹ ለብዙ ዘመናት የተናቁና ምርታቸውም በጣም በአነስተኛ ዋጋ ሲሸጥ ቆይቷል::: የእደ ጥበባት ውጤቶች በብዙ አካባቢዎች እየቀነሱ፣ ሙያውም እየተረሳ፣ ባለሙያዎቹም እየጠፉ የመጡበት ሁኔታ ተከስቷል:: እንደ ሙያው ዓይነት ቢለያይም እንኳን በውጭና በሀገር ውስጥ የፋብሪካ ምርቶች ውድድር፣ በሥርዓት ለውጥና ስለ እደ ጥበባት የንቀት አስተሳሰብ፣ በጥሬ እቃዎች አለመገኘት ወይንም መመናመን፣ ምክንያቶች በአጠቃላይ የመቀነስ አዝማሚያ ታይቶባቸዋል:: ሆኖም እደተተነበየው የእደ ጥበባት ሙያ ያልጠፋበትና የሚቀጥልበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ:: ከነዚህም ውስጥ የሸክላ ሥራ ርካሽነት፣ የብረት ሥራ ለግብርና መሣሪያዎች መጠገን ወሳኝ ሚናና፣ የሽማ ሥራ ባህላዊ ተፈላጊነት ዋነኞቹ ናቸው::

የእደ ጥበባት ሙያን ለማስፋፋትና ለማሻሻል የተደረጉት ሙከራዎች ውሱን ናቸው:: ብዙዎቹም የተጠበቀባቸውን ውጤቶች አላስመዘገቡም:: ለዚህም በቂ ትኩረት ያልተሰጠበት አንዱና ወሳኝ ምክንያት ከባህል አንፃር እደ ጥበባት ተንቀው ጠቃሚነታቸው ስላልታመነበት ሊሆን ይችላል ብለን ማሰብ እንችላለን::

የባህላዊ እደ ጥበባትን ለማሻሻልና ወደ ዘመናዊ አሰራር ለመለወጥ የተደረጉት ጥረቶች ብዙ ጊዜ ያልተሳኩ የሆነባቸው ምክንያቶችን ስንፈትሽ አሠራሩ ከባድ ሆኖ ከአካባቢው ልምድና ባህል ጋር ስለማይገናኝ ነው የሚለው አስተሳሰብ አንዳንድ ጊዜ እንደ ቀላል ሰበብ ሆኖ ይታያል:: ከተጠቀሱት ምሳሌዎች በመነሳት የገበያ ሁኔታ

አለመጠናትና አለመጣጣም፣ የአሠራር ሥርዓቶች ለሙያተኛው አመቺ ሳይሆኑ የሥራ ነፃነታቸውን የሚያግዱ መሆኑ እንደ አብይ ምክንያቶች ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። ስለዚህም የሙያ ማሻሻል የቴክኒክ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከኢኮኖሚው ሁኔታና ከአመቺ አሠራር ሥርዓቶች ጋር የተቀናጀ መሆን አለበት እንጂ ባህልን ያለ አሳማኝ መረጃ መወንጀል አያሻም።

እደ ጥበባት ለሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ። የህዝብ ብዛት በጨመረ ቁጥር፣ መሬት በቀነሰ ቁጥር፣ የከተሞች እድገትና አቅም እየተሟላ ሲሄድ፣ በገጠር ከግብርና ውጭ የመተዳደሪያ እድሎች ማስፋፋት ለዕድገት ወሳኝ እየሆነ ይመጣል። የእደ ጥበባት ዕድገት ከገበያና ከከተማ ፍላጎት ጋር ተያይዞ፣ ከዚያም በላይ ከቱሪዝም ገበያዎች ጋር ከተገናኘ ለሙያተኞች የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ከውስጥና ከውጪ ገበያና ከቱሪዝም ፍላጎት ሁኔታ ጋር ከተቀናጀ የእደ ጥበባት ጥራት ሊሻሻልና ብዛቱ ጨምሮ ሙያተኞቹ በሥራቸው ኩራት ተሰምቷቸው በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ንቀት እቀነሰ ሊመጣ ይችላል። አንዳንድ አካባቢዎችና በተለይ በከተሞች የእደ ጥበባት ለውጦች እየታዩ፣ የእደ ጥበብ ሠራተኞች እየበለጸጉ ሌላው ህብረተሰብ እያከበራቸው ለጋብቻም ጭምር ሲፈልጓቸው የተወሰኑ የለውጥ ምሳሌ አርአያዎች ታይተዋል።

በኢትዮጵያ ሊመረቱ የሚችሉት ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ከውጭ ከማስመጣት ይልቅ የውጭ ምንዛሬ በማዳን እደ ጥበባት ላገሪቷ ኢኮኖሚና ለባህልና ቅርሳ ቅርስ ጥበቃና ዕድገት ራሱን የቻለ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ እንዲሟላና እንዲሳካ ከተፈለገ ስለ እደ ጥበባት ያለንን አስተሳሰብ መለወጥ መቻል አለብን።

# ቁዘማ:- ፎክሎር[1] (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ

*ፈቃደ አዘዘ*

> የቆዬ ልማድ የቆዬ በመሆኑ ሁሉ አይወድቅም፣ ወይም ሁሉ አይያዝም። መልካሙና ጠቃሚው ይያዛል የሚሻሻለው ይሻሻላል ሊሻሻል የማይችለው ይወድቃል። ነገር ግን የሚወድቀውም ክፉ ልማድ ከስራ ይወገዳል እንጂ ከታሪክ ጸሀፊዎች መጽሀፍና ከደራሲዎች ድርሰት ሊወገድ አይገባውም። ያለዚያ በዬጊዜው የሚደረገው የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚክ ወይም ያስተዳደርና የማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል ከምን ተነስቶ እምን እንደ ደረሰ ሊታወቅ አይችልም።
>
> ሀዲስ ዓለማየሁ፥ ፍቅር እስከ መቃብር - ልብ ወለድ ታሪክ፥ አዲስ አበባ፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፥ 1963፥ ገፅ 10። ልብ ወለዱ መጀመሪያ የታተመው በ1958 ነው። እዚህ የጠቀስኩት ግን በ1963 የትምህርት ሚኒስቴር ካሳተመው ነው።

ከሁሉ አስቀድሜ «ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ» ባህልና ልማት በሚል ርእስ ተከታታይ ፕሮግራሞች ስላዘጋጀ እና እኔም ሃሳቤን ከክቡራትና ክቡራን ጋር እንድጋራ ስለጋበዘኝ አመሰግናለሁ።

ሰኔ 18 ቀን 1996 በተቀራራቢ ርእስ፥ «የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር» ባዘጋጀው የ «ርዕይ 2020» መድረክ ላይ ንግግር አድርጌ ነበር። ስድስት ዓመት ሊሆነው ሶስት ወር ገደማ ነው የቀረው። ከጊዜው ርዝመት ጋር የሚመጣጠን አዲስ ጽሑፍ ገና አልጻፍኩም። ታዲያ ዛሬ ለምን እፊታችሁ ተገኘሁ? ምክንያቶቼን ሳላቀርብ የቋጠርኳትን ማቅረቤ ትክክል ስለማይመስለኝ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን «ባህልና ልማት» በሚል ርእስ ኤፍ. ኤስ. ኤስ. ባዘጋጀው ተከታታይ ውይይት ላይ እንድሳተፍ ስጋበዝ «አዲስ ዝግጅት የለኝም» ብሎ፥ ይቅርታ መጠየቅ በጣም እያማረኝ አምሮቴን ቀስ በቀስ ፊት ነሳሁት። አለመሳተፍ በጣም ከበደኝ። በዚህ ላይ ግብዣውን እቢሮዬ ይዞ የመጣው ሰው የዋዛ ሰው አልነበረም። እራሴን የሥነጽሑፍና የፎክሎር ተማሪ ብቻ ሳይሆን የአደባባይ አስተዋዋቂያቸውም (በሌላ አነጋገር መልካም ወትዋች) አድርጌ ስለምመለከት፥ በሀገርኛ ቋንቋ በተገኘው መድረክ ሁሉ፥ የፎክሎርን እና የልማትን ትስስር፥

---

[1] ለብዙ አድማጮቼ «ፎክሎር» የሚለው ቃል እንግዳ ሆኖ መልእክቴን እንዳያድበሰብስብኝ አልፎ-አልፎ «ፎክሎር/ባህል» እያልኩ እጓዛለሁ። ወደፊት፥ በጽሞና አንድ ዘዴ ላበጅለት እስባለሁ። ለዛሬ ግን ከስያሜው ይልቅ በውስጡ ምን-ምን እንደሚያካትት እመግለጽ ላይ አተኩራለሁ።

ማስተዋወቅ ይጠቅማል እል ስለነበር አጋጣሚው አጓጓኝ። ሶስተኛ፥ «ርዕይ 2020» ላይ በተቀራራቢ ርእስ ሰኔ 18 ቀን 1996 አቅርቤው የነበረው ጽሑፍ እኔ የምመኘውን ያህል አለመሰራጨቱን ከተረዳሁ ስለቆየሁ በዚህ መድረክ እርሱን ማስተዋወቅም አማረኝ። አራተኛ፥ ስለ ፎክሎር በሰዎች ዘንድ ዛሬ ያለው አስተያየት የዛሬ 30 እና 40 ዓመት ከነበረው የተሻለ ቢሆንም ቁምነገሩ በወጉ የሰረጸ አለመሆኑን ተገንዝቤ ነበርና ደጋግሞ የመጻፍና የመወያየት አስፈላጊነት ገፍቶ መጣ። አምስተኛ፥ በፊተኛው ቁዘማ ውስጥ ስለ ፎክሎር ዘርፎች፥ ስለ ዐበይት ተግባሮቻቸው፥ በሀገራችን ስላለው የፎክሎር ትምህርትና ምርምር፥ እና ስለ ፎክሎር እና ልማት ወይም ስለ ተግባራዊ ፎክሎር (applied folklore) አንዳንድ የውጭ ሀገር የፎክሎር ምሁራንን ሃሳብና ልምዶችን ስላላስተዋወቅሁ፥ ስለነርሱም በሩጫም ቢሆን ጥቂት ብናገር ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።

ስለዚህ የዛሬው ንግግሬ እንደ ዱለት ብጤ ነው። ጿሚዎችን ይቅርታ እየጠየቅሁ፥ እስከዛሬ ከታተሙና ካልታተሙ ጽሁፎቼ አልፎ-አልፎ እንደልቤ እየወሰድሁ እንደማቀርብ ከወዲሁ እገልጻለሁ። የምጀምረው ስለፎክሎር በጥቅሉና ስለዛሬው የእኔና የእናንተ ውሎ በሚያወሳ ወጋዊ መንደርደሪያ ነው። ከዚያ የፎክሎርን ድፍየና (definition) እና ውገና (categorization) በሚመለከት አንዳንድ አጠቃላይ ነጥቦችን ስንዝሬ ስለፎክሎር እና ልማት መሰረታዊ የምለውን ነጥብ ብቻ አነሳለሁ። ቀጥዬ ስለ ተግባራዊ ፎክሎር (applied folklore) የአንድ ታዋቂ ምሁርን ሀሳብ እና የአንድ ታዋቂ ፎክሎረኛ የምርምር ስራ መሰረት አድርጌ አወጋችኋለሁ። በኢትዮጵያ ያለውን የፎክሎር ምርምር እና ትምህርት በቢጋር መልክ ከነደፍኩ በኋላ ምን ብናደርግ እንደሚሻል ጠቁሜ አበቃለሁ። የጋባዦቼን ጥቆማ መነሻ በማድረግ ዋና ዋና የምላቸውን ከፎክሎር ጋር የተያያዙ ጽሑፎቼን ዝርዝር፥ በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ ያቀረብኩ መሆኔንም አስታውቃለሁ።

## 1. ወጋዊ መንደርደሪያ - በጥቅሉ፡ ቅድመ ልደት እስከ ድኅረ ሞት

እያንዳንዳችን፥ በያደግንበት ባህል መሰረት ከመወለዳችን በፊት፥ ልንወለድ ስንል በምጥ ላይ፥ ከተወለድን በኋላ፥ በጉልምስናና በአረጋዊነት እድሜያችን እና ከዚህ ዓለም እስክናልፍ ድረስ በስማችን ወይም በእኛ ምክንያት ብዙ ባህላዊ ስነስርዓቶች፥ ስለቶች፥ ዘፈኖች፥ ጸሎቶች፥ ጨዋታዎች፥ ለቅሶዎች፥ ምርቃቶች፥ ርግማኖች ወዘተ ተኪያሂደዋል። አሁንም እየተኪያሄዱ ናቸው። በአንዳንድ የሀገራችን ባህሎች፥ ስርዓቶቹ ከልደት እስከ ሞት ብቻ የሚኪያሄዱ አይደሉም። ሰው ከመጸነሱ በፊት፥ ተወልዶ እስኪሞት፥ እና ከሞተ በኋላ የሚያኪያሄዷቸው ስርዓቶች አሏቸው። በየባህሉ ይለያያል። ፎክሎር እነዚህን የሕይወት ክስተቶች በየዘመናቱ ሲገልጽ

የነበረና ዛሬም እየገለጸ ያለ ነው ማለት ይቻላል። ሰው ከመጸነሱ በፊት፥ በሕይወት ዘመኑ፥ በሞቱ ጊዜና ከሞቱም በኋላ የተከናወኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህላዊ ስርዓቶችና ድርጊቶች የሚጠሩበት የጥቅል ስም ነው ማለት የሚቻል ከመሰለኝ ቆይቷል።

እኔ ካደግሁበት ሁኔታ አንዳንድ ተጨባጭ ምሳሌዎች እየጠቀስሁ እስካሁን የተናገርኩትን እንዳብራራ ፍቀዱልኝ። እናንተም ያደጋችሁበትን እያሰላሰላችሁ ብትከተሉኝ ልብ ለልብ እየተደማመጥን አብረን እንጓዛለን፥ ስለዚህም ብዙው ነገር ግልፅ ይሆናል። ብዙው ነገር ግልፅ ከሆነ ደግሞ የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች ፎክሎር በእውቀት፥ በስርዓትና በጥንቃቄ እንሰብስብ፥ እንቅረስ፥ እንመርምር፥ እንተንትን ስንባባል ሌላው ቢቀር ስለምን ጉዳይ፥ ለምን እንደምንነጋገር በውል እናውቃለን ማለት ነው።

እኔ ባደግሁበት አካባቢ፥ አንድ የጋብቻ ስነስርዓት ከመከናወኑና የቤተሰብ መሰረት ከመጣሉ በፊት ብዙ ነገሮች ይከናወናሉ። ብዙ ጊዜ ሽማግሌ ወደሴቷ ወላጆች ዘንድ ይላካል። የወንድም የሴትም ወገን በየበኩላቸው ዘር ቆጥረው (በዘመዶች፥ በቅርብ የጎሳ አባላት መሀከል ትዳር እንዳይመሰረት፥ የመደብ የበላይነትን ለመጠበቅ ወዘተ)፥ የጤናን ሁኔታ[2] (ለምሳሌ ቂጥኝ-ውርዴነት፥ የአእምሮ ህመም ወዘተ. በቤተሰቡ መኖር አለመኖሩን ማጣራት፣ መሆንነት በቤተሰቡ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ወዘተ.) እና ቤተሰብ መስርቶ ለማስተዳደር[3] ያለ ብቃትን ያጣራሉ። እነዚህን የሚያደርጉት፥ የተለያዩ የማኅበረሰብ ወገኖች የተለያየ ዓላማ ሊኖራቸው ቢችልም፥ አንዱ መሰረታዊ ምክንያት፥ እራሱን ማስተዳደር የማይችል ሰው፥ የማያስተዳድረው ቤተሰብ መስርቶ የራሱ እና የማኅበረሰብ ጠንቅ እንዳይሆን ቀድሞ ለመከላከል ይመስለኛል። ጋብቻው ከተመሰረተም በኋላ፥ አንድ ልጅ/ልጅት ከመፀነሱ/ሷ በፊት የሚከናወን ስርዓት አለ። ቢያንስ ቢያንስ ስለት አለ። እንደየሁኔታውም ወደጠበል፥ ወደ አዋቂ መሄድ አለ። ከተረገዘ በኋላም ፅንሱ እንዲይዝ የሚከናወን የእርግዝና ወቅት ስርዓት አለ። ሲወለድ ጸሎት አለ፥ በኦርቶዶክስ «ማርያም ማርያም!» አለ፥ ቢላ ማፏጨት፥ ቢላ ከግርጌም ይሁን ከራስጌ ማድረግ አለ። ስትገላገልም እልልታና ተኩስ አለ። ሌላም ሌላም። የግዝረት፥ የክርስትና ማስነሳትን የመሳሰሉትና ከዚያም የልጅነት ጨዋታዎቹ፡-

[2] ዛሬ የጤና ሁኔታ ስለተለወጠ የተጫጩ ሰዎች ለኤች. አይ. ቪ.፥ ለመውለድ ብቃት እና ለሌላም የጤና ምርመራ ከጋብቻ በፊት ወደ ሀኪም ቤት መሄድ ይችላሉ። ጥንት ግን እንዲህ ዓይነት አማራጭ አልነበረም። ስለዚህ መንገዳቸው ከዘመናቸው ሁኔታ ጋር የሚመዘን ነው።

[3] ይሄም ቢሆን በተለያየ መንገድ ዛሬም ይጠየቃል። «ስራ አለው? ቤት አለው? መኪና አለው?» ይባላል። አንዳንዴም፥ በተለይ የቢሮ፣ እንደገና በተለይ የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ደግሞ ፥ ሌላ መተዳደሪያ፥ ሌላ የገቢ መደጎሚያ ይኑረው አይኑረው ይጠየቃል።

ድብብቆሹ፥ ኩኩሉው፥ አጸለሌው፥ ጨረቃ ድምቡልቦቃው፥ ሽክክሞሹ፥ እንቆቅልሹ አሉ። ሌሎች ገና በወጉ ያልሰበሰብናቸው ብዙ ፎክሎሮች አሉ። ዝርዝሩ ብዙ ነው። ይሄ፥ እኔ ካደግሁበት ሁኔታ የተቀነጨበ ነው። የናንተስ? ቁጥራቸውን ገና በእቅጩ ያላወቅናቸው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችስ? ይሄ ነው፥ ልብ ልንለውና ልንመክርበት የሚገባ አንዱ መሰረታዊ ነጥብ።

## 2. ወጋዊ መንደርደሪያ - በእቅጩ ፡ የዛሬው የመጋቢት 17 ቀን 2002 የእስካሁኗ ሰዓት ውሏችን፤

እስካሁን በጥቅሉ ነው ያወጋሁት። በጥቅሉ መነጋገር በየፊናችን ሩቅ መንገድ እንደመጓዝ ነው። አፍርንጅ «አብስትራክት» የሚሉትን ይመስላል። እሱ ደግሞ እንደ ወዳጄ ዘበርጋ ብዙዎቻችንን፥ ፊደል ቆጠርንም አልቆጠርን ያስቸግራል። የወንድሜ ዘበርጋ ነገር እንዲህ ነው። መሰረተ ትምህርት በሚኪያሄድበት ክፍል ፥ ሂሳብ አስተማሪው፥ ስለማባዛት ያስተምርና ተማሪዎቹ ገብቷቸው እንደሆነ ለማወቅ ፤ «አንድ በግ 5 ብር ቢያወጣ 4 በግ ስንት ያወጣል?» ይላል። ዘበርጋ እጁን እያወጣ፥ ከወንበሩም እንደመነሳት እያለ፥ «እኔ! እኔ! ቲቸር» ስላለ መምህሩ ለመመለስ ለተጣደፈው ዘበርጋ እድሉን ይሰጠዋል። የዘበርጋ መልስ «የት ነው?»ነበር። ለካስ የተጣደፈው ቦታውን አውቆ በግ ግዢ ሊሄድ ነው። ይህንን፥ የሂሳብን ጉዳይ በረቂቁ ማስላትን ትቶ ወደ ተጨባጩ ጉዳይ መብረር እንደማለት አድርገን እንውሰደው።

አሁን ደግሞ እስቲ ስለእኔና ስለእናንተ በቀጥታ፥ በተለይም ደግሞ ስለዛሬዋ ቀን ዘበርጋን ተከትለን ተጨባጭ-ተጨባጩን እናውጋ! ዛሬ ከየቤታችን ወጥተን፥ ወደዚህ ከመምጣታችን በፊት፥ ወደዚህ ውይይት ስንመጣ፥ እዚህም ከደረስን በኋላ የሆነውን፥ ያደረግነውን እናሰላስል። በእውነት ልብ አእምሯችንን እንበርብር። ይሄኔ'ኮ ስንት ፎክሎር-ነክ ነገሮች ተናግረናል፥ አስበናል፥ ከውነናል፥ ሰርተናል።

አንዳንድ መቀስቀሻ ጥያቄዎችን ላንሳ? ....እሺ !!!!!

- ዛሬ፥ ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ «በደኅና ያሳደርከኝ በደኅና አውለኝ! ምቀኛን ያዝልኝ!» ብላችሁ ይሆናል። ፊታችሁን ያስታጠባችሁ ሰው ከነበረ ደግሞ፥ አዛውንት ከሆናችሁ፥ «እደግ ተመንደግ! ሽንትህ ይባረክ! የሚጦር ልጅ ይስጥህ! እንጀራህን ከፍ ያድርገው!» ብላችሁ መርቃችሁ፥ እንቱፍቱፍ ብላችሁ ይሆናል። ጎልማሳ ከሆናችሁ ደግሞ፥ «ይቅናህ! ዲቪ ይድረስህ» ብላችሁ መርቃችሁ ይሆናል። የጨነቃችሁ ወጣት ከሆናችሁ ደግሞ፥ «ኤንጂኦ ያስቀጥርህ! የሚቦጨቅ ያለበት ስራ ይስጥህ! ሀብታም፥

ፍንዳታ ባልቴት ይጣልልህ! የሌሊት ቱሪስት፥ የቼችኒያ መሪ ያርግህ! ወዘተ» ብላችሁ ይሆናል - እንደቀልድም፥ በቁምነገርም።

- ቁርስ ልትበሉ ቀርባችሁ፥ መጀመሪያ ከምግቡ ቆንጥራችሁ ፈንጠቅ አድርጋችሁ ይሆናል።
- ወደዚህ ስብሰባ ለመምጣት ከቤታችሁ ወጥታችሁ መንገድ ላይ ግራ እግራችሁን እንቅፋት መትቷችሁ ተጨንቃችሁ ይሆናል። ቀናችሁ መጥፎ እንዳይሆን ሰግታችሁም ተመልሳችሁ ወደ ቤታችሁ ገብታችሁ፥ አረፍ ብላችሁ፥ እንደገና ወጥታችሁ ይሆናል እዚህ የመጣችሁት። እንደገና እንዳይመታችሁም ተሸቀዳድማችሁ ቀኝ እግራችሁን እንቅፋት አስመትታችሁ ይሆናል። ወይም፤
- ውስጥ እጃችሁን አሳክኳችሁ «አሜሪካ፥ አዲስ አበባ፥ አዋሳ ወይም እሌላ ሀገር ያለ ዘመድ ዶላር ወይም ብር ሊልክ ይሆን?» ብላችሁ አስባችሁ ይሆናል።
- አሁን እዚህ ካለነው፥ በግራ ወይም በቀኝ ክንዳችን ላይ ትምህርት እንዲገባን፥ ወይም ደግሞ ሰው መድኃኒት ቢያደርግብን እንዲያረክስልን በማለት ድግምት፥ ክታብ ወይም ሌላ ባህላዊ መከላከያ ያሰርን እንኖር ይሆናል።
- በተለያየ ምክንያት፥ ከቤት ስንወጣ ጤናዳም አኝከን፥ ነጭ ሽንኩርት በልተን፥ በባዶ ሆዳችን ሎሚ አሽትተን ወይም መጥጠን፥ ወይም በሆነ ቅጠል ወይም ተክል (አሪቲ፥ ዳማከሴ ወዘተ) ሰውነታችንን አባብሰን የመጣን እንኖራለን።
- ቡና አስፈልተንም ይሁን አፍልተን፤ ከርቤ፥ እጣን ወይም ወገርት አጢሰን ወይም ታጥነን፤ ተለማምነን፤ ቡናውን ከመጠጣታችን በፊት አንዱ ስኒ ላይ ጠብ አድርገን፥ ከስኒ ስኒ ገልብጠን፥ በመጨረሻ እቤት ውስጥ እንደዘበት ረጭተን ከዚያ የስኒውን ሆድ ያነበብን ወይ ያስነበብን እንኖር ይሆናል።
- ጎረቤት የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ በጧት ተነስተን የሽምግልና ስራ ያከናወንንም እንኖር ይሆናል።

መቼም ይህንን ሁሉ ዛሬ ሁላችንም ፈጽመናል ማለት አይደለም። ከመሀከላችን አንዳንዱን ያደረግን ግን እንኖር ይሆናል። ለምሳሌ ፥ እኔ ከቁርሴ በፊት፥ በባዶ ሆዴ ሎሚ መጥጫለሁ። አልፎ አልፎ ሰውነቴ የሚነግረኝን እየሰማሁ

ከማደርጋቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ እናቶች «ውቃቢዬ ነግሮኝ» የሚሉትን «ሰውነቴ ነግሮኝ» ማለቴን ልብ በሉልኝ!

እነዚህን የደረደርኩት፥ አንድም፥ ስለፎክሎር/ስለባህል ሳላወሳ ስለምን ዓይነት ጉዳዮች እንደማወጋ እንድትገነዘቡልኝ፤ በእለት ተእለት ሕይወታችን ከምንፈፅማቸውና ከዘመን ዘመን እየተላለፉ እኛ ዘንድ ከደረሱ ድርጊቶችና እምነቶች ጥቂት ምሳሌዎችን በማቅረብ ረቂቁ ግዘፍ እንዲነሳ፤ በጊዜና በቦታ ቅርብ በመሆን በኩል ለስሜትና ለአእምሮም ቅርብ ቢሆንልኝ ብዬ ነው፡፡ አንድም ደግሞ በእነዚህ እምነቶች፥ ሃሳቦችና ተግባራት የተዋቀርን ሰዎች በዘመናዊ (ሞደርን) ቴክኖሎጂ፥ በኢኮኖሚ፥ በፖለቲካ እና በማኀበራዊ መስኮች ሀገራችንን እናለማለን ስንል ምን-ምን ጉዳዮች ሀሳባችንን እና እቅዳችንን፥ ብዙ ጊዜ እኛ ሳናውቅ እንዴት እንደሚመሩዋቸው (influence እንደሚያደርጓቸው) አብረን እንድናሰላስል፥ እንድንመረምር ለመጋበዝም ነው፡፡

ታድያ፥ አንድ ማሳሰቢያ ማቅረብ አለብኝ፡፡ ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸው የፎክሎርም ይባሉ የባህል ጉዳዮች በቴክኖሎጂ ከመሰልጠን ወይም ካለመሰልጠን ጋር የተያያዙ አይደሉም፡፡ የደኃ ሕዝብ፥ የአፍሪካ፥ የገጠር ነዋሪዎች ጉዳይ ብቻም አይደሉም፡፡ የሀብታም ፥ የአውሮፓና የአሜሪካ እና የከተሜም ጉዳይ ናቸው፡፡ እርግጥ እኛ ጋ፥ በየትምህርቱ ውስጥ፥ በየቢሮው፥ በየፖለቲካ ክርክሩ፤ በየሬድዮው፥ በየቴሌቪዥኑ፥ በየማስታወቂያው፥ በየቤተስብከቱ ወዘተ. ውስጥ ፎክሎሩ በጣም ገንኖ፥ ኮርቶ፥ እጅ እግሩን ዘርግቶ ተኝቷል፡፡ ነገር ግን በቁሳዊ ስልጣኔያቸው እጅግ ተራምደዋል ተብለው የሚመኩት አውሮፓና አሜሪካም የራሳቸው ዓይነት ክታብ፥ የራሳቸው ዓይነት ስለት፥ የራሳቸው ዓይነት እርግማንና ምርቃት አላቸው፡፡ ከ13 ቁጥር ጋር እንኳ የተያያዘ ስንት ነገር አላቸው አይደል?

ስለዚህ ነገሩ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ብዙ ነገሮችን ያካትታል፡፡ እዚህ ጋ ከደረስን፥ ከዚህ ቀጥዬ ስለፎክሎር ዘርፎች አንዳንድ ነጥቦችን እናገራለሁ፡፡ ይህንን የማደርገው፥ እስካሁን፥ ከእለት ተእለት ሕይወት እየጠቀስሁ ያቀርብኳቸው ቁምነገሮች በቀሪው ጉዟችን ይበልጥ እየተግባባን ለመጓዝ የሚያስችለንን መሰረት በትንሹም ቢሆን ጥለዋል ብዬ ስለምገምት ነው፡፡

# 3. የፎክሎር ዘርፎች[4]

በዚህ ንግግር ውስጥ «ፎክሎር» የሚለውን ቃል ቀጥዬ የምዘረዝራቸውን አራት የጥናት ዘርፎች የሚያጠቃልል አድርጌ እወስዳለሁ።

## 3.1. ስነቃል (oral literature)፡-

በቃላት አማካይነት ከሚፈጠሩት፥ ከሚሰራጩትና ከሚከወኑት እንደ ተረት፥ ሌጀንድ፥ ሚት፥ ቃልግጥም፥ ምሳሌያዊ ንግግር፥ እንቆቅልሽ፥ እንካሰላንቲያ ያሉት፣ እና እነርሱን የመሳሰሉት የሚጠሩበት የጥቅል ስም ነው። የጠቀስኳቸው ምሳሌዎች፥ ባብዛኛው ከገበሬና ከገጠር ነዋሪዎች የሚገኙ የጥንት ነገሮች ሊመስሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ከማንኛውም ሰው ሊገኙ የሚችሉ፥ ጥንትም የነበሩ ዛሬም ያሉ፥ በተለያየ መልክና ቅርፅ ከዘመን ዘመን የሚሸጋገሩ ናቸው። በተጨማሪ፥ ዱሮ ከስነቃል ተቆጥረው እምብዛም የማይሰበሰቡት፥ የማይቀረሱት እና የማይጠኑት ቀልዶች ዛሬ በስነቃል ምርምር ውስጥ ተካትተዋል። መቃብርጡፎች፥ የጥልፍ ጥቅሶች፥ የግድግዳ ፅሁፎች፥ ሽኖኞች (latrinalia) ፥ ልዩ ልዩ ስሞች ሁሉ በስነቃል ስር ይጠናሉ።

## 3.2. ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk arts)

በዚህ የጥቅል ስም የሚጠሩት የሀገረሰብ ሙዚቃ፣ የሀገረሰብ እስክስታ፥ ረገዳ (ዳንስ)፣ እና የሀገረሰብ ድራማ ናቸው።

## 3.3. ሀገረሰባዊ ልማድ (social folk customs)

ሁላችንም፥ እንደየአቅማችን፥ በአደባባይና በየልባችን፥ ከሕይወት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መጠየቃችን አይቀርም። ለምሳሌ፥ አጥብቀን በያዝናቸው እምነቶች ለምን እንደምናምን፥ እምነቶቹ ከምን እንደመነጩ፥ ፍቻቸው ምን እንደሆነ፥ መጠየቃችን አይቀርም። «በእነዚህ ነገሮች ባናምን መኖር እንችላለን? ወይስ አንችልም? ከቻልን የማኅበረሰባችን አወቃቀር ምን ዓይነት ይሆን ነበር?  ስላመንንስ ምን ዓይነት ሆኗል እያልን የምንመራመርም እንኖራለን። እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ብዙ ጊዜ

---

[4] ስለ ፎክሎር ድፍየና መናገር ጊዜ ይወስዳል። ሁሉም ባለሙያ የሚስማማበት አንድ ድፍየናም ስለሌለ በዚህ መድረክ ስለፕሮብሌሙ ማንሳት አስፈላጊ አይመስለኝም። አንቱ የተባሉት ፎክሎረኞች እንደሚያደርጉት ዘርፎቹን ማስተዋወቅ ለያዝነው ጉዳይ ይበቃል። ዘርፎቹም ብዙ ስለሆኑ፥ እስከዛሬ ባማርኛ ስጽፍ እንደማደርገው፥ እዚህ አሳጥሬ ያቀረብኩት የሪቻርድ ዶርሰንን ነው። እርሱንና በተራ ቁጥር 4 ያቀረብሁትን አሳጥሬ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያስገባሁት ሃሳቤን ከእናንተ ጋር ለመጋራት የማደርገውን ጥረት ያቃናል ብዬ ነው። እዚህ ካቀረብኩት የላቀ ዝርዝር ለማግኘት የምትሹ ***የስነቃል መምሪያን*** እንድትመለከቱ እጋብዛለሁ።

ፈላስፎች፥ ደራስያን፥ ስነሰበኞች (Anthropologists) እና ፎክሎረኞች ጊዜ ወስደው የሚመራመሩባቸውና የሚጽፉባቸው ቢሆንም ፥ ሃሳባችንን እንደነሱ አንጻፍ እንጂ፥ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሁላችንም እንደየአቅማችን የምናሰላስላቸው ናቸው፡፡ በተለያዩ ፎክሎሮች ውስጥም እነዚህ እምነቶች ሲገለጹና ሲከወኑ ነበር፤ አሁንም ይነገራሉ፤ ይከናወናሉ፡፡ በፎክሎረኛው በሪቻርድ ዶርሰን መፅሀፍ ውስጥ በዚህ ርእሰ-ነገር ስር ይጠናሉ ስለተባሉ ጉዳዮች ከተወሳው ከእፍታው ጨልፈን ነው፡፡

አንጋፋው ፎክሎረኛ ዶርሰን በ «ሀገረሰባዊ ልማድ» ውስጥ «ፌስቲቫልና ክብረ በዓል (ከበራ)» (festival and celebration) ፥«መዝናኛዎችና ጨዋታዎች» (recreations and games) ፥ «ሀገረሰባዊ መድኃኒት» (folk medicine) እና «ሀገረሰባዊ ሃይማኖት» (folk religion) እንደሚካተቱ በዚህ ክፍል ባስገባቸው መጣጥፎች አመልክቶልናል፡፡

### 3.4. ቁሳዊ ባህል (material culture)

የሀገረሰብ እጅስራ (folk crafts) ፥ የሀገረሰብ ስእል (folk art) ፥ የሀገረሰብ ምህንድስና (folk architecture) ፥ የሀገረሰብ ልብስ (folk costume) ፥ እና የሀገረሰብ ምግብና የምግብ አሰራር (folk food and folk cookery) ፥ በቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ የቁሳዊ ባህል ጥናት በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን፥ በተለይ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፥ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሠሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፤ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር፥ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፤ የልብስ፥ የቤት፥ የአጥር ወዘተ አሠራርን፤ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችን፥ ከእነዚህ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የመደብ፥ የጾታ፥ እና ሌሎች ማኅበራዊ ግንኙነቶችን እና ልዩ ልዩ ትእምርታዊ ፍች ያላቸውን ቁምነገሮችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ያጠናል፡፡ ምክንያቱም የፎክሎረኛው ተግባር የአንድን ቁስ ቁሳዊ ገጽታዎች፥ ማለትም ቁሱ ምን እንደሆነ፤ ከምን፥ መቼ፥ እንዴት፥ በማን እንደተሰራ በዝርዝር መመዝገብና መቅረስ ብቻ አይደለም፡፡ ይህንን ማድረግ አለበት፡፡ ነገር ግን የሰበሰባቸውን መሰረታዊ መረጃዎች ይዞ በእነርሱ ውስጥ የተነገሩትን ማኅበራዊ፥ ባህላዊ ፥ ስነልቡናዊ እና ታሪካዊ ምስጢሮች ፈልፍሎ አውጥቶ በትንተና ማሳየትም ሙያዊ ግዴታው ነው፡፡

## 4. የፎክሎር (የስነቃል) አጠቃላይ ተግባር

የፎክሎርን/የስነቃልን ተግባራት በስድስት ዐበይት ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነርሱም (1ኛ) የመግለጥ ተግባር፥ (2ኛ) የማጠናከር፥ የመትከል ተግባር፥ (3ኛ)

የማምለጭ ተግባር፥ (4ኛ) የማስተማር ተግባር፥ (5ኛ) የመግታት-የመቆጣጠር ተግባር፥ (6ኛ) የፖለቲካ ተግባር ናቸው።

## 4.1 የመግለጥ ተግባር

ፎክሎሮች የሰው ልጅ ባካባቢው ያሉትን ነገራት እና ዓለማት ኬትመጣ (origin) ይገልጻሉ። የራሱን የሰውልጅንም ኬትመጣ ይተርካሉ። የሰው ልጅ፥ በዙሪያው ላለው የተዘበራረቀ ዓለም በፎክሎሩ አማካይነት ስርዓትና ቅርጽ በማበጀት ለሕይወቱ ፍች፥ ለኑሮው መልክ፥ ለኅሊናውም አንጻራዊ መረጋጋትን ይሰጣል። ይህ ሚና ነው የፎክሎር <u>የመግለጥ ተግባር</u> የተባለው።

## 4.2 የማጠናከርና የመትከል ተግባር

ሰዎች ራሳቸውንና ቁሳዊውን ዓለም ለመግለፅና ለመረዳት እንደሚሞክሩት ሁሉ፥ ራሳቸው በፈጠሯቸው ማኅበራዊ ድርጅቶች እና ባህሎች፥ የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ፤ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፥ ቀጣይነት እንዲኖራቸው በፎክሎር ያጠናክራሉ። ለምሳሌ፥ ከልደት፥ ከግርዘት፥ ከጋብቻ፥ ከጀግንነት፥ ከሞት ወዘተ ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ቀጣይነት ያረጋግጣሉ። መሠረታቸው እንዳይናጋ አጥብቀው ይተክላሉ። <u>የማጠናከር-የመትከል ተግባር</u> የተባለው ይኼ ነው።

## 4.3 የማምለጭ ተግባር

የእለት ተእለት ኑሯችን በተደጋጋሚ ክስተቶች በእጅጉ የተሞላ ነው። አሰልች የሚሆንበትም ጊዜ ጥቂት አይደለም። የሰው ልጅ ከዚህ ከወትሮአዊው የዕለት ተዕለት የህይወት ውጣ ውረድ ማምለጭ[5] እና በምናቡ አዲስ ዓለም ውስጥ መግባት ይፈልጋል። በገሃዳዊውና በምድራዊ ኑሮው ያጣውን እፎይታ በምናባዊ ዓለም ለማግኘት ይታገላል እንደማለት አድርገን ልንቆጥረው እንችላለን። ፎክሎሩ ከገሃዱ ዓለም ተመንጥቆ የሚያርግበት የሚያመልጭበት አንዱ መንገድ ነው። ስለዚህም ፤

- በሳቅ ፥ በጨዋታና በቀልድ ከሰለቹት እለታዊ ክስተቶች ያመልጫል።
- በልማድና በባህል ስም የተጫኑበት የመሰሉትን አይነኬ ደንቦች (taboos) በምናቡ በመድፈርና በእነርሱ በማላገጥ ያመልጫል። ለምሳሌ ፥ ደሀ

---

[5] «ማምለጭ» የሚለውን ቃል የፈለግሁት ማንኛውንም ከቁሳዊ አካባቢ በመንፈስ የመሸፈት ፥ የመመነን እና የማምለጥ ተግባርን እንዲገልፅልኝ ነው። ይህንን ያደረግሁት ፥ በአካል ሮጦ ከማንኛውም ነገር ከማምለጥ የተለየ ስለሆነ፥ ይህንን ልዩ ፍች ይዞ እንዲለመድ ስለፈለግሁ ነው።

ሀብታምን በማግባት ወይም በምናባዊ ዓለም በወሲባዊ ትዕይንቶች በመፈንጨት ያመልጫል፡፡

- ከመንደሩ፥ ከወረዳው፥ ከክልሉ፥ ባጭሩ ከተከበበበት ጂኦግራፊያዊ አጥርና ድንበር በምናቡ ያመልጫል፡፡ ባዮሎጂያዊ ባህርዩ እንደማይፈቅድለት እያወቀ እንደ ወፍ ይበራል፥ እንደ አንበሳ ይሰብራል፥ እንደ ዝሆን ይደፈጥጣል፡፡

## 4.4 የማስተማር ተግባር

ፎክሎር ስለአበላል፥ ስለአጠጣጥ፥ ስለአለባበስ፥ ስለአቀማመጥ፥ ስለአነጋገር፥ ስለአኪያሄድ ሥርዓት ያሳውቃል፡፡ ትጋት፥ ለጋስነት፥ ሕብረት ወዘተ... በኑሮ ውስጥ የሚሰጡትን ጥቅም አጥብቆ ይሰብካል፡፡ በተለይ የልጆችና የወጣቶች ባህርይ ገና ከለጋነታቸው ጀምሮ የሚቀረጸው ብዙ ጊዜ በፎክሎር ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.5 የመግታት-የመቆጣጠር ተግባር

በጎ ምግባርን የሚያስተምረው ፎክሎር፥ አስነዋሪ የተባሉ ባህርያትን (ለምሳሌ፥ የስርቆትን፥ የመዋሸትን፥ የስስትን፥ የክፋትን፥ የፈሪነትን) መስፋፋትም በልግጫና በማጥላላት ይቆጣጠራል፡፡ ዓላማው ከመልካም እሴቶች ያፈነገጡትን በግሣፄ ወደ ጀማው (ወደ ብዙኃኑ) አስተሳሰብ መመለስ ነው፡፡ የ"አድብ ! እረፍ" ማስጠንቀቂያዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል፥ የማኅበረሰቡን ዐበይት እሴቶች የሚያከብሩትን ሰዎች ደግሞ በትረካዎችና ቀልዶች፥ በግጥሞችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ያሞግሳቸዋል፡፡ ባጭሩ፥ ፎክሎር እነዚህን መንታ ስዕሎች እንደየሁኔታው እየሳለ የማኅበረሰቡ እሴቶች እንዳይናጉ ገና በህፃንነት፥ በእሹሩሩ ዜማዎችና አጫጭር ትረካዎች ጭምር ይቆጣጠራል ቢባልም፤ የ"ጅብ ይበላሃል" ና የጭራቅ ተረቶች ማስፈራርቾዎች ሆነው ለጊዜው ቢያገለግሉም፤ በህፃኑ ሰብእና (personality) ውስጥ የሚጠነስሱት ሥነልቡናዊ ፕሮብሌም ግን መኖሩ የማይቀር ይመስላል፡፡ ይህም ወደፊት በጥናት ከሚመረመሩት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡

## 4.6 የፖለቲካ ተግባር

- የፖለቲካ መሪዎች ሕዝባቸውን ለመምራትና ለመግዛትም በፎክሎር ተጠቅመዋል፡፡
- አንድ ሀገር ወይም ሕዝብ የራሱን ባህልና ማንነት እንዲያውቅና እንዲያከብር ፤ በራሱ እንዲተማመንና እንዲኮራ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የፊንላንድና የአየርላንድ ስም በፎክሎር ምርምር ውስጥ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ የአርያንን ዘር (The Aryan Race) ታላቅነትና የበላይነት ሂትለርና የፕሮፓጋንዳ ካድሬዎቹ በፎክሎርም እንዳስፋፉ ይታወቃል።
- የኢትዮጵያ፥ የኬንያ (የማኡማኡ)፥ የዚምባብዌ፥ የደቡብ አፍሪካ ("የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግሬስ")፥ የናሚብያ ወዘተ. አርበኞችም የወረራቸውን ጠላት ለመዋጋት በስነቃል እንደተጠቀሙ ይታወቃል።
- ባለፉት 40 ግድም ዓመታትም በአገራችን የፖለቲካ መድረክ፥ በፎክሎር አማካይነት ሕዝቡን ለተለያዩ ተግባራት መቀስቀስ እየተስፋፋ የመጣ ይመስላል። ዋናው ቁምነገር ፎክሎር፥ በፖለቲካም መስክ፥ ለአዎንታዊና ለአሉታዊ ግልጋሎት በቀላሉ ሊውል የሚችል የባህል ሀብት መሆኑን መገንዘብ ነው።

በ ***የስነቃል መምሪያ*** ውስጥ ስለ እነዚህ ተግባራት ያስተዋልኩትን አንድ ቁምነገር ከእናንተ ጋር ተጋርቼ ወደሚቀጥለው ክፍል እንዳቀና ፍቀዱልኝ። እጠቅሳለሁ፤

> ልብ ልንለው የሚገባ አንድ ነጥብ አለ። ባንድ በኩል፥ በግለሰቡ ላይ ደንብ የሚጭንበት፥ አይነኬዎችንና አይደረጌዎችን የሚያኙጎደጉድበት ስነቃል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከጫናው የሚያመልጭበትን መንገድ የሚከፍትለትም ስነቃል ነው። አንድ እሴት ሲጭንም፥ ብዙ ጊዜ፥ በፍርድ እና በእስር ቤት ወይም እነርሱን በመሳሰሉት እያስፈራራ አይደለም። በዚያው በትረካው ውስጥ በሚሳሉ ሁነቶች ነው የአድማጩን አስተያየት ለመቅረፅ የሚሞክረው። ማኅበረሰቡንና ግለሰቡን ለማረጋጋት የሚተክሉት እሴቶች ጫና ሲበዛበትም፥ በትረካው ውስጥ በሚሳሉ ሌሎች ሁነቶች ከጫናዎቹ እንዲያመልጭ ያደርጋል። ይህንን ሚዛናዊ ስርዓት በጥልቀት ማጥናት፤ በፅሁፍ ሲደነገጉ ከቆዩት የሀገራችን ደንቦችና ሕጎች ጋርም ማነፃፀር ይገባል። ከስነቃላዊዎቹና ከተፃፉቱ የትኞቹ ዘላቂ ተፈፃሚነት (ተግባራዊነት) እንደነበራቸውም በምርምር ሊታወቅ የሚገባ ይመስለኛል። ይሁን እንጂ፥ በወጉ ሊጠና የሚችለው በሙያው የሰለጠነ ብርቱ ተመራማሪ ሲኖር እና የእርሱም ትኩረት ወደዚህ ሲያዘነብል ነው (ገጽ 19-20)።

## 5. የፎክሎር ፋይዳ ለልማት

በዚህ ክፍል ስለባህልና ልማት ያልኩትን ለማጠቃለል እሞክራለሁ። የፎክሎርንና የልማትን ትስስር በአንድ አጠቃላይ መርሕ (Principle) እገልጥና ፥ ፎክሎር ለልማት ያለው ፋይዳ የሚታወቀው በምርምር ስለሆነ መነሻ የሚሆን አንድ ቅጽ አቅርቤ በቅጹ በመገልገል ደረጃ በደረጃ ይከናወኑ የምላቸውን ተግባራት እነድፋለሁ።

ከዚህ በላይ በተመለከትነው መሰረት እንኳ፥ ፎክሎር ሰፊ ነገር መሆኑን የተገነዘብን፣ ስለሁሉም ዘርፎቹና ምንጮቹም፥ ባጭር ባጭሩ እንኳን እዚህ መናገር እንደማይቻል የተረዳን ይመስለኛል። በጥቅል ትርጉሙ የማይነካው አስተሳሰብና የአኗኗር ስርዓት ስለሌለ በአንድ መጽሐፍም እንኳ ቢሆን ሙሉ በሙሉ የሚያረካ ሃሳብ ማካተት ያስቸግራል።

- ባህላዊውን አኗኗር መነሻ ወይም መሰረት አድርገን፥ በዛሬው ኑሯችን ውስጥ የምንመለከታቸው የረሃብና ጥጋብ፥ የተአምራዊ ቪላዎችና የጥሻ ኑሮዎች፥ ትዳር የመመስረትና የመፈናቀል ሁኔታዎች ወዘተ. ያስቀዝሙ ነበር። በቀብር ቦታ፥ በለቅሶ፥ በድግስ፥ በመጠጥ፥ በምግብ፥ በጫት፥ በሙስና፥ በገላ ንግድ፥ በወሲብ እና በሌሎች የኑሮ ክስተቶች እና፣ በሥርዓታዊ አኗኗርና በእሴቶች ላይ ስላስከተሏቸው የተለያዩ ለውጦች፣ መቆዘም ብቻ ብዙ ጊዜና ስፍራ ይፈጃል።
- በብዙዎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ፎክሎር ውስጥ ያሉ መልካም እሴቶች (ማኅበራዊ የሽምግልና ጥበቦች፥ የትብብር ስልቶች፥ ድርጅቶች ወዘተ.) እንደምን አድርገው እንድንኗኗር እንዳደረጉን አንዳንድ ጥናቶችን እየጠቀስን እናውጋ፥ መላ እየመታንም እንጫወት ብንል ስንት ጉዳይ በተነሳ!
- የኢትዮጵያን የሬድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፥ ጋዜጦቻችንን እና መፅሔቶቻችንን ይዘን፣ ስለ ብርቱ እና ደካማ ገፅታዎቻቸው መቆዘም፤ በስእል፥ በስነፅሁፍ፥ በትያትር፥ በስነቅርፅ፥ በሙዚቃ፥ በፊልም፥ በቪድዮ እንቅስቃሴዎች የሚቀርቡትን ይዞ መመራመርም እንዲህ በሩጫ የሚሞከር አይደለም።
- በዚህ ላይ ብዙ ጓዝ ያለው፥ ዘርፈ-ብዙው ቁሳዊ ባህል አለ።

ስለዚህ፥ ከፍ ብዬ በዘረዘርኳቸው ርእሶች ከእናንተ ጋር ሆኜ ሳልቆዝም የሚከተለውን ልበል። «ፎክሎር» / «ባህል» የምለው የአኗኗር ዘዴን፥ የአኗኗር ስልትን፥ የአኗኗር ስርዓትን ፥ ያኗኗር ደንብን፤ ኑሮን እራሱን፤ ከመገለጫ ጥበቡ ጋር ጨምሬ ነው።

- በቃል የሚነገር ፥ በስራ ፥ በክዋኔና በቁስ የሚገለፅ ነው፣
- ከትውልድ ትውልድ ፥ ከዘመን ዘመንም ያለማቋረጥ በንግግር ፥ በተግባርና በቁስ የሚተላለፍ ነው፤
- ፊት የነበረ ፥ አሁንም በመኖርና በመተላለፍ ላይ ያለም ነው፤

- ማኅበረሰብም በየጊዜውና እንደየሁኔታው ካለው እየቀነሰ ፥ ያለውን እያዳበረ ፥ አዳዲስ እየጨመረ የሚያጎለብተው ነው፤
- ባብዛኛውና በተለምዶ በቦታ ወይም በሀገር የመከለልና በውስጡ ተወልደው ያደጉ ሰዎች መለያ ሆኖ ሊነገር የሚችል ባህርይም ያለው ነው፤
- ክዋኔው (its performance) ግላዊና ማኅበራዊ ገፅታዎችም ሊኖሩት የሚችሉ፡- ኑሮ ፥ የአኗኗር ስርዓት[6] እና መግለጫውም ነው ማለት ይቻላል።

የፎክሎርን / የባህልን ጽንሰ ሃሳብ ለማስገንዘብ ሲባል በሌላ መንገድም ማቅረብ ይቻላል። እንደዚህ !

ሁላችንም እንደምናውቀው ስንኖር እናስባለን ፥ እንዘፍናለን ፥ እናለቅሳለን ፥ በምሳሌ እንነጋገራለን ፥ በትእምርቶች (symbols) መልእክቶች እንደ ዋዛ እንለዋወጣለን ወዘተ። እነዚህ የመንፈሳዊ ህይወት ገፅታ ስለሆኑ ለመግባባት ያህል «መንፈሳዊ ባህል» (spiritual culture) እንበላቸው። ምጣድ ፥ ገንቦ ፥ ጦር ፥ ከበሮ ፥ አልጋ ፥ ቤት ፥ እንስራ ወዘተ. እንሰራለን። እነዚህ ደግሞ የቁሳዊ ህይወት አካሎች ስለሆኑ ለመግባባት ስንል «ቁሳዊ ባህል» (material culture) እንበላቸው። ታድያ ፥ ቁሳዊውና መንፈሳዊው ሁልጊዜም ፥ ብቻ-ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም። በመሀከላቸው እንደየሁኔታው የሚያይልና የሚለዝብ መስተጋብር (interaction) አለ። ለምሳሌ መድኃኒት ከተለያዩ እፅዋት ስለሚዘጋጅ ከቁሳዊ ባህል ብቻ የሚመደብ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን እፁ የሚቆረጥበትን ወቅት ፥ ሲቆረጥ የሚባሉትን ነገሮች ፥ በኋላ መድኃኒቱ ለተጠቃሚው ሲሰጥ የሚነገረውን እና የሚደገመውን ፥ መድኃኒት አዘጋጁና መድኃኒት ወሳጁ ስለመድኃኒቱ የሚያስቡና የሚያምኑትን ወዘተ. የሚመለከቱ ከመንፈሳዊ ባህል የሚመደቡ እምነቶች እና ብሂሎች አሉ። ለዚህ ነው፥ «ለመግባባት ያህል» እያልኩ ውገናዬን የገለፅኩት።

ወደ «ልማት» ልሻገር። ልማት፥ የሰው ልጆችን ሕይወት አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴና ውጤቱ ይመስለኛል። ሁልጊዜ ፥ ካለው የአኗኗር ሁኔታ ወደተሻለው ለመጓዝ የሚደረግ የሃሳብና የድርጊት እንቅስቃሴ ይመስለኛል። ለምሳሌ ፥ ወደ ተሻለ ሰብእና፥ ወደ ተሻለ አመጋገብ፥ ወደ ተሻለ ስነ ምግባር፥ ወደ ተሻለ ጤና፥ ወደ ተሻለ ትምህርት፥ ወደ ተሻለ ትራንስፖርት፥ ወደ ተሻለ አስተዳደር፥ ወደ ተሻለ ሰላም ወዘተ. ለማምራት የሚደረግ እንቅስቃሴና ትግል ይመስለኛል።

---

[6] ከጥቁር ክብ 'ቡሌቶች' አንጻር የጻፍኳቸው ከ *ርእይ 2020* ጽሑፌ እያደትኩ የወሰድኳቸው ናቸው።

ልማትም መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ጉዳይ ነው። ስንማር ስንፈላሰፍ ፥ እውቀትን ስናመነጭ ፥ ልዩ ልዩ ጥበባዊ ድርሰትን ስንፈጥርና ስንከውን ፥ ተረት ስንተርት እና ስንከውን ለመንፈሳዊ ልማት አስተዋፅኦ እያደረግን ነው። ሞፈር፥ ቀንበር፥ ቢላ፥ ሸማ፥ ስንሰራ፣ እርሻ ስናለማ፥ መንገድ ስንሰራ፥ ህንፃ ስንገነባ ደግሞ ለቁሳዊ ልማት አስተዋፅኦ እያደረግን ነው። አርኪቴክቱና መሐንዲሱ ባይናችን የምናየውን፥ ለምሳሌ የሼራተንን ሕንፃ፥ እኛም እያየን ከመሰረቱ ጀምሮ ይገነባሉ። ይህ ግንባታ ቁሳዊ ስለሆነ ዓይን ያለው ሁሉ በግዱ ያየዋል። አዝማሪው፥ ተራኪው፥ ደራሲውና ፈላስፋው ደግሞ ልዩ ልዩ እሴቶችን፥ የሕይወት ክስተቶችን፥ ልዩ ልዩ ቃላትን፣ ትእምርቶችን ጡባቸው ፥ ብሎኬታቸውና ሸክላቸው አድርገው፥ በረቀቀ መንገድ እሰው አእምሮና ስሜት ውስጥ መንፈሳዊ ሕንፃ ይገነባሉ። ይህ ግንባታ ረቂቅ ስለሆነ በዓይን ብቻ አይታይም። ከፍ ሲል ዓይነ-ኅሊና ያስፈልገዋል። ቢያንስ ቢያንስ ግን ሕይወትን የማስተዋል፥ የማድመጥ፥ የማጣጣም ክሂል ያስፈልገዋል። እዚህም በቁሳዊውና በመንፈሳዊው ልማት መሀከል መስተጋብር (interaction) መኖሩን ጠቅሼ ብቻ ፎክሎር ለልማት ስላለው ፋይዳ አንድ ዓቢይ ነጥብ ወደመሰንዘር ላምራ[7]።

## 5.1. ፎክሎርና ልማት - መንደርደሪያ መርህ

በጥያቄ ልጀምር። «ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህልን መሰብሰብ ፥ ማጥናት እና መተንተን ለልማት አስተዋጽኦ አለው?»[8] የእኔ አጭር መልስ «አዎ አለው !»ነው። ማስረዳቱ ግን እንዲህ አጭር አይደለም። ብዙ ችግሮች አሉ። ሁላችንም ለብዙ ጊዜ የሰማነውን አንድ መሰረታዊ ችግር ብቻ ከዚህ በታች አነሳና «መንደርደሪያ መርህ» የምለውን አስከትላለሁ።

ዛሬ-ዛሬ ፣ በዓለማችን ፥ በተለይ ደግሞ በእንደኛ ዓይነቶቹ ሀገሮች ፥ ስለልማት ሲወሳ ስለሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ስለኢኮኖሚ ልማት እና እድገት ብቻ ማውራት በጣም ተለምዷል። ስለልማት የሚነገረው በምልአት ወይም ደግሞ ውስብስብ ገጽታዎቹን ተምር አጢኖ ሳይሆን፣ ብዙ ጊዜ ፥ እቁሳዊው ላይ ብቻ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እና ተጋንኖ ነው። ይህንን ቁሳዊ ልማት የሚያመጣው ግን ሰው ነው። ሰው ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ፥

---

[7] እስካሁን ያተኮርኩት በተለያዩ ስልቶች እና ከተለያዩ ማእዘኖች (angles) ስለፎክሎር/ስለባህል መሰረታዊ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ ያልኳቸውን ሃሳቦች እማስረጽ ላይ ነው። ይህ እንግዲህ በንግግሬ መግቢያ ላይ የጠቀስኩትን አራተኛ ምክንያት ለመተግበር የተደረገ ሙከራ መሆኑ ነው።

[8] ይህንን ከባድ ጥያቄ አብረን እንመርምር። እኔ አንድ መሰረታዊ የሚመስለኝን ነጥብ አነሳለሁ። እናንተም የየራሳችሁን ሃሳብ እያሰላሰላችሁ ተከተሉኝና በኋላ የሁላችንንም አስተያየቶች በተመደበልን ጊዜ በውይይት አብረን እንመረምራለን። ወደፊት በርእስ ነገሩ ላይ በየፊናችን መቆዘም ፥ መመራመር ፥ መወያየት እና መከራከር ብንቀጥል ደግሞ ድንቅ ይሆናል።

ከመንፈሳዊም ከቁሳዊም 'ንጥረ ነገሮች' የተሰራ ነው፡፡ ከስጋ፥ ከአጥንትና ከደም እንደተሰራው ሁሉ በተለያዩ ውስብስብ የሃሳብና የስሜት መረቦች የተሸመነ ነው፡፡ በመንፈሳዊው፥ በቁሳዊው እና በእነዚህ በሁለቱ መሀከል ባለው መስተጋብርም እየተጎነጎነ፥ በተለያዩ ዘመናትና ስልጣኔዎች ውስጥ የተጓዘ ነው፡፡ ይህንን ሰው፥ ቁሳዊ ፍላጎቱን ብቻ በማልማት ከሙሉ ክብሩ ጋር በልቶ-ጠጥቶ ፥ ለብሶ ፥ መጠለያ አግኝቶ ፥ጤናማና ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖረው ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ሀገር ያለማል የተባለው ሰው እራሱ ፥ በተሟላ ሁኔታ ካልለማ ፥ ማለትም መንፈሳዊውን ፥ ቁሳዊውን እና ከእነርሱ መስተጋብር የመነጨውን ተገንዝቦ በታቀደ መንገድ ካልለማ ፤ የተወጠነው ቁሳዊ ልማትም ጠቃሚ መሆኑን አውቆ ፥ ተረድቶ-አምኖ ፥ አስፈላጊውን ዝግጅት አሟልቶ ፥ በሙሉ ልቡ ወደተግባር ካልተሰማራ፤ የታሰበው ቁሳዊ ልማት በሚታሰበው መጠን ምን ጊዜም ግቡን አይመታም የሚል እምነት አለኝ፡፡

ስለዚህ ፥ አንድ የልማት ስራ ሲታሰብ ፥ ስራውን ይሰራል ተብሎ የሚታሰበው ሰው ፍላጎት፥ እምነት፥ የሕይወት ፍልስፍና፥ የመኖሪያ አበይት እሴቶች፥ ክሂሎቶች ወዘተ. መታወቅ አለባቸው፡፡ እነዚህን ለማወቅ ደግሞ የተለያዩ ባህሎቹን ወይም ፎክሎሮቹን (ማለትም፥ ተረቶቹን፥ አፈ.ዶዎቹን፥ ገድሎቹን፥ ተአምራቶቹን፥ እንቆቅልሾቹን፥ የሕይወት ፍልስፍናዎቹን የሽክላና የአንጥረኛ ስራዎቹን፥ ልዩ ልዩ እምነቶቹን፥ እሴቶቹን እና አምልኮዎቹን ወዘተ.) ማጥናት ይገባል፡፡ በዚህ መልክ፥ ባህሉን አውቆ፥ ሊሰራ የታቀደውን ስራ በዚያ ባህል ውስጥ አቀልጥፎ እንዴት ማከናወን እንደሚቻል አስቦ፥ ልማቱን የሚያከናውነውን ሰው የውጥኑና የስራው ንቁ ተሳታፊና ፈቃደኛ አካል ፥ ዋና ተዋናይ እና ጠንካራ ኃይል አድርጎ መራመድ ካልተቻለ የልማቱ ስራ ችግር ይገጥመዋል፡፡ በጥቅሉ ሲነገር፥ ባህል ለልማት አስተዋፅኦ ያደርጋል ማለት ይህ ይመስለኛል፡፡

ለነገሩ፥ ዞሮ ዞሮ የምናለማው ሰውን ነው፡፡ ማልማት ማለት፥ አካባቢን (environment ን)፥ ዓለምን፥ ወይም 'ተፈጥሮን' (nature ን) ባጉል ስግብግብነት ሳናናጋ፣ ወይም በቸልተኛነት እማንወጣው ቀውስ ውስጥ ሳናስገባ፥ ለሰው ልጅ በሚጠቅም መንገድ መለወጥና ማደራጀት ነው፡፡ ስለዚህ፥ ዋናው ተጠቃሚ ሰው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ የማያቋርጥ ሂደት ይመስላል፡፡ ባህልም ያለማቋረጥ የሚለዋወጥ ስለሆነ ትናንት የነበረውን ለመለወጥና ለማሻሻል የእውቀትና የመንፈስ እድገት ሊኖረን ይገባል፡፡ ውጤቱ፥ ልማትም ባህልም ይባላል[9]፡፡

[9] ብዙ ጊዜ፥ "የት ጋ ቆመህ፥ የምን ባለሙያ ሆነህ?" ነው የምትናገረው ነው ነጥቡ፡፡ አንዳንዴ፥ በተመስጦ ሳስብ ፥ የባህልና የልማት እሳቤ፥ ሙልጭልጭ ይሆንብኛል፡፡

እስካሁን ያልኩት የሚያመራኝ፥ ባህል ለልማት ከእስከዛሬው የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ የባህል ምርምርና ትምህርት በእውቀትና በእቅድ መኪያሄድ መጀመር አለበት፤ ሲጀመርም መንፈሳዊውን እና ቁሳዊውን እያጠናና እየመዘነ ሊሆን ይገባል ወደሚል ይሁንታ (recommendation) ነው፡፡ ለዚህም፥ ከሁሉም በፊት በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች የባህልንና የልማትን ትምህርቶች እያጣጣሙ በሀገርኛ ቋንቋዎች[10] ጭምር ማስተማር በሰፊው መካሄድ ይኖርበታል፡፡ የባህል ፕሮፌሽናሎች በዲግሪ ፕሮግራም በጥራት (በኳሊት[11]) ማፍራት እንዲስፋፋ እስካሁን ከተደረገው የበለጠ ጥረት ማድረግና አስፈላጊውን በጀት መመደብም ይጠበቅብናል፡፡ በተጨማሪም፥ ባጫጭርና በረዥም ጊዜ ስልጠናም የባህልና የልማት ሰራተኞችን አቅም ነገ-ዛሬ ሳይባል በስርዓትና እቅድ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ስልጠና እውን እንዲሆን ደግሞ ስለባህልና ቅርስ፥ ስለባህልና አንድነት፥ ስለባህልና ልማት፥ ስለባህልና ትምህርት፥ ስለ ባህልና ቱሪዝም፥ ስለ ባህልና ሙዝየም፥ ስለባህልና ኪነጥበብ፥ ስለባህልና የብዙኃን መገናኛ ወዘተ. ከከፍተኛ ፖሊሲ አውጭዎችና ባለስልጣናት ጋር ውይይት የሚኪያሄድበት መድረክ አስቀድሞ ቢፈጠር ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ስንደርስበት በዝርዝር የምንነጋገርበት ቢሆንም፥ ከአንደኛ ደረጃ፥ ከሁለተኛ ደረጃና ከከፍተኛ ትምህርት ሁኔታና፤ ከብዙኃን መገናኛ አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ጋር አጣምረን ሳናስብ ስለባህልና ልማት ማሰብ እንደማንችል ከወዲሁ ጠበቅ አድርጎ ማሳሰብ ያስፈልጋል፡፡

## 5.2. የፎክሎር መቃኛ - መምሪያ

ፎክሎርን ሰፊና ጥልቅ ምርምር በማድረግ አጥንተን ፥ ተንትነንና አብራርተን እንወቅ ብያለሁ፡፡ ይህ ጥናት እንዴት ነው የሚያኪያሄደው ? የዚህ ዝርዝር ብዙ ስለሆነ ራሱን በቻለ ሌላ ጽሑፍ/መጽሐፍ የሚቀርብ ነው፡፡ እስከዚያው ግን መነሻ እንዲሆን ቢጋሩን ብቻ እነድፋለሁ፡፡

- በብዙ የምርምር ስራ ላይ በመዋላቸው በፎክሎር መስክ የታወቁትን እና እኛም ፥ ለእኛ ጉዳይ ያስፈልጉናል የምንላቸውን ነጥቦች ጨምረን በምናዘጋጀው ፥ ለጊዜው «የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ፎክሎር መቃኛ ሰነድ» ልንለው በምንችለው የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ በሀገራችን ውስጥ

---

[10] በራስ ቋንቋ የማስተማር፥ የመመራመር እና የምርምር ውጤቱንም የማሰራጨት ጉዳይ በዝርዝር የሚያነጋግርም፣ ራሱን የቻለ፣ አጣዳፊ ብሔራዊ አጀንዳ ይመስለኛል፡፡ ዝምታችንን ቀጥለን፣ ሁኔታውም አሁን በሚጓዝበት መንገድ ከቀጠለ፥ ንግሩ ወይም ስለ ወደፊቱ ሕይወታችን የሚጠቁመን በናፍቆት የምንጠብቀው አይደለም፡፡

[11] Quality ለማለት ነው፡፡

የሚገኙትን ብሔረሰቦች ጥበቦችና እውቀቶች እንሰበስባለን። ይህ ርእያችን (vision) ነው። ወደስራ ስንገባ ግን ዝርዝር እቅድ ማውጣት ይኖርብናል።

- ስራውን በእውቀትና በገለልተኝነት ሊያከናውን የሚችል (1) የሰለጠነ የሰው ኃይል ጉዳይ እና ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ (2) በጀት እና (3) የሕንጻዎችና የልዩ ልዩ መሳሪያዎች ጉዳይም በወጉ የሚታሰብበት ነው።
- የሶስቱን ልክ ወይም አቅማችንን ካወቅን በኋላ በመጀመሪያ የስንት ብሔረሰቦችን ፎክሎር (እውቀትና ጥበብ) እንደምንቃኝ እና ከዚያም እንደምናጠና በምናወጣቸው መስፈርቶች ላይ ተመስርተን እንወስናለን።
- በመጀመሪያው ዙር የሚጠኑትን ስናውቅ በሰነዱ መሰረት የእያንዳንዳቸውን ባህል ሰብስበን ፥ ስብስቦቹን አጥንተን ከውስጣቸው ገናን እውቀቶቻቸውንና ጥበቦቻቸውን እናወጣለን።
- የእያንዳንዳቸውን ገናን ጥበቦች ፥ እውቀቶችና ሌሎች ባህሎች ካወጣን በኋላ ፥ እነርሱን መሰረት አድርገን ሁሉም ብሔረሰቦች ሙሉ በሙሉ የሚጋሯቸውን ለማወቅ እንሞክራለን።
- ያወጣናቸውን የጋራ እሴቶችና (values) ሀብቶች በተለያዩ መሳሪያዎች እንፈትናለን ፥ እንተነትናለን።
- ከዚያ በኋላ የጋራና ጠቃሚ የሆኑት ከሙዋዕለ ህጻናት ጀምሮ በትምህርት ቤቶች ፤ በዩኒቨርስቲዎች ፥ በብዙኃን መገናኛዎች ሊሰራጩ የሚችሉበትን መንገድ አቅደን ፥ በእቅዱ መሰረት እናሰራጫቸዋለን። በተግባር የሚፈተሹትንም ከየሚመለከተው ማኅበረሰብ አውራ አባላት ጋር እየተመካከርን እንፈትሻለን።

በዚህ ዓይነት ፥ በእውቀትና በእቅድ በሚኪያሄድ ተግባር የሀገር ልማትን ከሀገራዊ እውቀትና ጥበብ ጋር ማጣጣም ይቻላል የሚል የቆየ አስተያየት አለኝ። በኢትዮጵያውያን መሀከልም የበለጠ መቀራረብን መገንባት ያስችል ይመስለኛል። ሳናጠናውና ሳናውቀው ፥ እስካሁን አብሮ ያቆየንን ጋሩማ (የጋራ አመለካከት)[12]፥ አፍንጫውን አባብሶ፥ ሾሁን ነቅሎ፥ በከፍተኛ ደረጃ ማዳበር የሚቻል ይመስለኛል። የብሔረሰቦች ባህሎች በሳይንሳዊ ስርዓት (scientific method) ተሰብስበውና ተጠንተው፤ ብዙዎቹ የሚጋሯቸው እሴቶች ተለይተውና ታውቀው፣ የታወቁትም በሀገሪቱ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ***በትምህርት መልክ***፤ በብዙኃን መገናኛዎች ደግሞ ***በመረጃ መልክ*** የሚሰራጩበትን መንገድ ከባለሙያዎች ጋር

[12] የዚህን ዝርዝር ለማወቅ የ *ርእይ 2020* ጽሑፌን ይመልከቱ።

ሆነው መንግስት እና ኢትዮጵያውያን የግል ባለሀብቶች እንዲያመቻቹ እመክራለሁ፡፡ ጀማው የልማት ናፋቂ እና የመልካም ባህል ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊም፥ የፎክሎር ማኅበሮች በያሉበት ቦታ እየመሰረቱ ለብሔራዊው ጋሩማ እና ፎክሎርን ለመቅረስና ለማደስ[13] (revitalize ለማድረግ) የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ ይህ ብሔራዊ ጥሪ በተለያዩ መድረኮች፥ በተለያየ አነጋገር፥ በተለያየ መጠንና ጥልቀት ከ1970 ዓ.ም. ጀምሮ ሲተላለፍ የቆየ መሆኑን ለአድማጮቼ በትኅትና እገልጻለሁ[14]፡፡

እዚህ ጋ ንግግሬን ማቆም እወድ ነበር፡፡ ነገር ግን ላልኳቸው ነገሮች የሩቅ ምስክር መጥቀስ ይጠቅም ይሆናል በሚል የሚከተለውን አክያለሁ፡፡

## 6. ተግባራዊ ፎክሎር (applied folklore)

በዚህ ክፍል፥ ፎክሎርን ለተለያዩ የልማት ተግባራት ስለማዋል አንቶንዮ ግራምሺና (Antonio Gramsci) ማይክል ኦውን ጆንስ (Michael Owen Jones) የተባሉ ምሁራን የጻፉትን አቀነባብሬ[15] አቀርባለሁ፡፡ ይህንን የማደርገው ከዚህ በላይ የፎክሎር ምርምር ለልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ብዬ ጥብቅና የቆምኩለትን ሃሳብ የሌሎች ሀገሮችን ልምዶችና የላቁ ምሁራንን አስተያየት በአማርኛ አቀናብሬ በማስከተል ምስክር ለማቅረብና ፥ ምናልባትም የሃሳብ ተከታይ ለማብዛት ነው[16] ፡፡

[13] የዚህ ዝርዝርና በዚህ ጽሑፍ ያነሳኳቸው ሌሎች ነጥቦች A Folklore Guidebook for Ethiopia: An Introduction to Definitions and Categories, Field Methods, and Resources for Revitalizing Folklore በሚል ርእስ ለ OSSREA, January 2010 የቀረበ ረቂቅ ጽሑፍ በሆነ መልክ ይፋ ሲሆን በዝርዝር ይብራራሉ የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

[14] የዚህ ሃሳብ ጥንስስ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በ1970 ባዘጋጀው ኮንፈረንስ ላይ ባቀረብኩት ጽሑፍ ውስጥ ተጀምሮ በሌሎች ጽሑፎችም በተለያየ መልክ ሲቀርብ የነበረ ነው፡፡

[15] UNESCO እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ታዋቂ ፎክለረኞች፥ ስነሰበኞች እና ድረገጾች በዚህ ርእስ ላይ ብዙ እንደጻፉ የታወቀ ነው፡፡ ሁለቱን ብቻ የጠቀስሁት ርእሰነገሩን ለማስተዋወቅ ያህል ነው፡፡

[16] በአማርኛ ሳቀነባብር ሃሳባቸውን አዛብቼ ብገኝ ኃላፊነቱ የእኔ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የምሁራኑ ምስክርነትም የቄሱና የምእመኑ ዓይነት ተደርጎ እንዳይወሰድብኝ ከወዲሁ አደራ እላለሁ፡፡ ወጉ እንዲህ ነው፡፡ ቄሱ ሲሰብኩ

« ‹ድር ቢያብር አንበሳ ያስር› እንዳለው ሌኒን…›› ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ ፥ አንዱ «መቼ እንደዚህ አለ?» ሲላቸው ፤ «ምን ያላለው ነገር አለ?» አሉት ተብሎ ባለፈው መንግስት ጊዜ በቀልድ መልክ ተነግሯል፡፡

## 6.1. የአንቶኒዮ ግራምሺ ሃሳብ፣

በቅርቡ ከዚህ ዓለም በድንገት በሞት የተለየው ታላቁ አሜሪካዊ ፎክሎረኛ ፥ አለን ዳንደስ ፥ ኢጣልያዊው ምሁር አንቶንዮ ግራምሺ (እ.ኤ.አ. ከ 1891-1937 የኖረ)፥ ከስነፎክሎር (folkloristics) መስራቾች አንዱ ነው ይላል። ስለ ፎክሎር በጻፈው አጭር መጣጥፍ[17] ግራምሺ ካደረጋቸው አስተዋጽኦዎች አንዱ፥ የፎክሎር ጥናት በዘመናዊ አስተሳሰብና ትምህርት ያልተጠኑትን ማኅበራዊ ቡድኖች ርእዮተዓለም ለማጥናት ይጠቅማል ያለው ነው። እርሱ መጣጥፉን በጻፈበት ዘመን (እ.አ.አ. በ1929) እና ከዚያም በፊት ፥ ፎክሎር ይሰበሰብ የነበረው ስለሚያምር፥ ስለሚያስደስት፥ ቋንቋው ስለሚማርክ ነበር። ስለዚህ፥ ይላል ግራምሺ፥ ፎክሎር መጠናት ያለበት ዘመናዊ አስተሳሰብና ትምህርት ያልደረሰባቸው ማኅበራዊ መደቦች፥ ወገኖች ፥ ቡድኖች ዓለምን የቀረፁበት፥ የገለፁበት፥ የሳሉበት፥ የተመለከቱበትና ዛሬም የሚያዩበት መንገድ (ርእዮተዓለማቸው) ተደርጎ ነው። የተጠቀሱት የማኅበረሰብ ክፍሎች ዓለምን የተመለከቱበት መንገድ በወጉ ያልተብራራ ከመሆኑም ባላይ በስርዓት ተደራጅቶ (መልክ-መልክ ይዞ) የሚገኝ አይደለም። ምክንያቱም እላይ የተጠቀሱት ማኅበራዊ ቡድኖች አባላት፥ በመሰረቱ ርእዮተዓለማቸውን አብራርተው ስርዓት ባለው መንገድ የማቅረብ ልምድ የሌላቸው መሆኑ ነው። ይህም ብቻ አይደለም። ርእዮተዓለሙ ራሱ በቁጥርና በዓይነት ብዙ የሆኑ የተለያዩ አመለካከቶች ሜካኒካል በሆነ መንገድ ጎን ለጎን የተቀመጡበት ነው። እንዲያውም በታሪክ ሲከታተሉ-ሲቀጣጠሉ የነበሩ ቁርጥራጭ የዓለም እና የሕይወት አመለካከቶች ሙዝየም ባይሆን ነው? ባጭሩ፥ በእኔ ግምት ፥ ግራምሺ የሚለው በተጠቀሱት ወገኖች ፎክሎር ውስጥ የሚገኙት ርእዮተዓለሞች የተቀነጣጠቡ ፥ በታሪክ ረዥም ሂደት ስለዓለምና ስለሕይወት የተሰነዘሩ የልዩ ልዩ አመለካከቶች ቁርጥራጮች ናቸው። ስለዚህ ርእዮተዓለማቸውን በሚዩዚየም ውስጥ እንደተቀመጡ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ቅርፆች አድርጎ ማየት ይቻላል። እነዚህ ቁሳቁሶች ብቻቸውን የአንድን ማኅበራዊ ቡድን ርእዮተዓለም ሙሉ በሙሉ መግለፅ ያዳግታቸዋል። ነገር ግን ሁላቸውም ሲጠኑ የሚያመለክቱት፥ የሚፈነትዉት ርእዮተዓለም ሊኖር ይችላል።

ሁለተኛው አስተዋጽኦ፥ የፎክሎር ትምህርት በመምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ይሰጥ ያለው ነው። የሚሰጠውም ፥ ሰልጣኙ ከማሰልጠኛ ከወጣ በኋላ የሚያስተምረውን ማንኛውንም ትምህርት የሚያስተምርበትን ዘዴ በተማሪው ባህል

[17] Antonio Gramisci, "Observations on Folklore," in Alan Dundes, ed., *International Folkloristics : classic contributions by the founders of folklore*, 1999. Lanham, Boulder, New York, Oxford: Rowman & Littlefield.

ላይ ተመስርቶ ለማዘጋጀት ብቃት እንዲኖረው ነው። በተባለው መንገድ መዘጋጀቱ ተማሪው ትምህርቱን በትክክል እንዲማር ያደርጋል ብሎም አስቧል።

ይህንኑ ነጥብ ለማብራራት ግራምሺ እንዲህ ብሏል። እንደሚታወቀው ማንኛውም መንግስት የራሱ ርእዮተዓለም፥ እርሱ ዓለምንና ሕይወትን የሚመለከትበት መንገድ አለው። ይህንን ርእዮተዓለም በትምህርት ቤት ውስጥ ማሰራጨት ይፈልጋል። የራሱን አመለካከት የሚያሰራጨው ደግሞ ልዩ ልዩ ባህል፥ ልዩ ልዩ አመለካከት ወዳላቸው ተማሪዎች ነው። አመለካከቱን የሚያሰፍረው ብዙ ጊዜ በስህተት እንደሚገመተው በህፃኑ ንፁህ የአእምሮ ሰሌዳ ወይም በባዶው ጭንቅላቱ (tabula rasa) ላይ አይደለም። ምክንያቱም፥ በተማሪው አእምሮ ውስጥ ልዩ ልዩ ፎክሎሮች ቀድመው ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። ቀድመው ቦታ የያዙት ፎክሎሮች ደግሞ መንግስት በመምህሩ በኩል ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን ርእዮተዓለም አደግድገው አይቀበሉም። በመሀከላቸው በዓይን የማይታይ ጠንካራ ፉክክር፥ ፍጥጫና ትግል ይኖራል[18]። ለዚህ ነው፥ ግራምሺ፥ መምህሩ ተማሪውን በደንብ ለማስተማር የሚችልበትን መንገድ መቀየስ የሚችለው፥ በመጀመሪያ የተማሪውን ፎክሎር አጥንቶ ነው ያለው። ለዚህ ነው፥ ለመምህሩ ፎክሎር ማወቅ ማለት የወጣቱን ትውልድ ምግባር እና አእምሮ (አስተሳሰብ) ለመቅረፅ የሚሻሙትን ሌሎች አመለካከቶች ማወቅ ማለት ነው ያለው[19]።

እንደ ሶስተኛ ነጥብ አድርጎ ያነሳው የሚመስለኝ ነጥብ፥ የፎክሎር ጥናቶችን በተመለከተ መካሄድ አለበት ያለው የአመለካከት ለውጥ ነው። ይኸውም ፎክሎር እንደ እንግዳ ነገር፥ እንደ ጉድ፥ እንደ ቧልት መታየት የለበትም የሚለው ነጥብ ነው። እንደመዝናኛም ብቻ መታየት የለበትም ይላል። ፎክሎር ምር (serious) ስለሆነ ሲጠናም የምር (seriously) መሆን አለበት ነው የሚለው ግራምሺ። እንደትምህርት መሰጠቱ ውጤት የሚያመጣው፥ የብዙኃኑ ሕዝብ ባህልም የሚለማው ፥ በዘመናዊና በጥንታዊ ባህል መሀከል የሚደረገው መነጣጠል (separation) የሚጠፋው በዚህ መንገድ መሆኑን ግራምሺ አጠንክሮ ይናገራል።

---

[18] ለዚህ ይሆናል ፥ ያለፈው መንግስት «ሶሻሊዝም፥ ኮሚዩኒዝም፥ ማርክሲዝም፥...» እያለ እንዳሉ ሊቀዳቸውና ሊተገብራቸው 17 ዓመት ሙሉ የዳከረላቸው ርእዮተዓለሞች፥ ተቀባይ ህዝብና መሬት አጥተው ከርመው፥ ድንገት አንድ ቀን መንበረ ሥልጣናቸውን ለቀው፥ በሔሊኮፕተር ተሀገር የወጡት።

[19] ግራምሺ ይህንን ያለው የዛሬ 81 ዓመት ገደማ (በ1921 ዓ.ም አካባቢ) ነው። በእኛና እኛን በመሰሉ ሀገሮች ደግሞ ይህንን ለመገንዘብ ቀርቶ ወሬውን ለመስማትም፥ እንኳን ያንዬ ዛሬም የምንፈልግ መሆኑ ብዙ ያነጋግራል። ብዙ፥ በመልማት ላይ ያሉና የለሙ ሀገሮች ግን ይህንን እውነት ተረድተው ፎክሎራቸውን ማጥናትና በትምህርት ቤት ውስጥም በልዩ ልዩ ምክንያት ማስተር ከጀመሩ ቆይተዋል።

## 6.2 «ፎክሎርን ጥቅም ላይ ማዋል» ብለን ልንተረጉመው በምንችለው መጽሐፍ ውስጥ አዳቹ (the editor) ፥ ማይክል ኦውን ጆንስ ፥ ስለተግባራዊ ፎክሎር ያቀረባቸው የምርምር ውጤቶች፤

ማይክል ኦውን ጆንስ የተባለው ታዋቂ የአሜሪካ ፎክሎረኛ *Putting Folklore to Use*[20] የተባለ መፅሐፍ እ.አ.አ. በ1994 አድቶ አውጥቷል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በፃፈው "Applying Folklore Studies: An Introduction" በሚለው የመግቢያ ምእራፍ ውስጥ ፥ ፎክሎርን በስርዓት ሰብስቦ ፥ በስብስቡ አንድ ማኅበራዊ ፋይዳ መስራት ረዥም ታሪክ እንዳለው ለማሳየት፥ በተለይ የአራት ሀገሮችን ምሳሌዎች ጠቅሶ ያስረዳል። ምሳሌዎቹን የጠቀሰው ከስዊድን ፥ ከፊንላንድ ፥ ከጀርመንና ከአሜሪካ ነው።

በየሀገሩ የተሰበሰቡ ፎክሎሮች እምን-እምን ተግባር ላይ እንደዋሉ ለማሳወቅ ከጠቀሳቸው መሀከል ስለስዊድኑ ንጉስ አዋጅ ፥ ስለፊንላንድ የመልሶ መቋቋሚያ ፕሮግራም ፥ ስለ ጀርመን ብሔረተኝነት ያቀረበውን እና በመጽሐፉ ውስጥ ከተገለጹት የአሜሪካውያን ልምዶች ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል አቀርባለሁ።

### 6.2.1. የስዊድኑ ንጉስ አዋጅ

ጉስታቭ 11ኛ (አዶልፍ) የተባለ የስዊድን ንጉስ ፥ ስለሕዝቡ ጥንታዊ አኗኗር የሚናገርና ፥ የሚገልፅ ማስረጃ ያላቸው ባህሎች እንዲሰበሰቡ ፥ እንዲመዘገቡ እ.አ.አ. በ1630[21] አዋጅ አውጥቶ ነበር። ዋና ዓላማው ፥ ስዊድን ረዥም ታሪክ እንዳላት ፥ ረዥም ታሪክ ላላቸው የአውሮፓ ሀገሮች፥ በእነዚህ ጥንታዊ ባህሎች አማካይነት ማሳየት ነበር። ሃሳቡ፥ በወቅቱ ፊንላንድን እና ሌሎች ሀገሮችን ትገዛ የነበረችው ስዊድን ረዥም ታሪክ ያላት አንድ ብሔር መሆኗን የሚያሳይ መረጃ ከባህሎቹ ጨምቆ ማውጣት ነበር ማለት ነው። አዋጁ በወጣ በ36 ዓመቱ የጥንታዊ ቅርሶች ጉባዔ (An Antiquities Council) በስቶክሆልም እ.አ.አ. በ1666 (በእኛ በ1658/1659) ተቋቋመ። ከስምንት ዓመት በኋላ (እ.አ.አ. በ1674)፥ ጉባዔው የፊንላንድ ቀሳውስት ጥንታዊ፥ ተራኪ ዘፈኖችን እንዲሰበስቡ ተማፀነ። ይህንን ያደረገው፥ ተራኪዎቹ ዘፈኖች ስለ ስዊድን አባቶች የጀግንነት ገድሎች የሚናገሩት

[20] Michael Owen Jones, ed. *Putting Folklore to Use: Essays on Applied Folkloristics*, 1994 Lexington: The University Press of Kentucky.

[21] በእኛ አቆጣጠር በ1622/1623 ገደማ መሆኑ ነው። እነዚህን ዘመናት ወደ እኛ አቆጣጠር እየለወጡ በጊዜው እኛ ምን እናደርግ እንደነበረ ማስላሰል አረዳዳችንን የሚያዳብር ይመስለኛል። ታድያ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ብዙ ሐቅ ይኖራል በሚል እምነት ነበር። ፎክሎር የብሔራዊ ማንነት መቅረጫ ወይም ማዋቀሪያ መሳሪያ ተደርጎ ነበር ማለት ነው።

### 6.2.2. የፊንላንድ የመልሶ መቋቋሚያ ፕሮግራም

በ18ኛው ክፍለ ዘመን ፥ በታላቁ የሰሜን ጦርነት (the Great Northern War)[22] ምክንያት ከደረሰባት ጉዳት ለማንሰራራት የመልሶ መቋቋሚያ ፕሮግራም አውጥታ ነበር። የተሻለ የአስተዳደር ዘዴ መፈለግን እና ምርታማነትን ማሳደግን ዋና ዓላማ ያደረገው ፕሮግራም ሀገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ ልቅም አድርጎ በዝርዝር መሰነድና መተንተንን የመጀመሪያ ተግባሩ አደረገ። እ.አ.አ. ከ1730ዎቹ እስከ 1800 ገደማ ድረስ ብዙ ወጣቶች በየሚኖሩበት አካባቢ ያለውን ነባራዊ እውነታ ይሰበስቡና ያብራሩ ጀመር። የእርሻ ዘዴዎችን፥ የእነፃ (የግንባታ) ስልቶችን (architectural traditions)፥ የህክምና አገልግሎቶችን፥ የአመጋገብ ዘዴዎችን፥ የጋብቻና የቀብር ስርዓቶችን፥ ዓመታዊ በዓላትን፥ የመዝናኛ ስርዓቶችን፥ ሌጀንዶችን፥ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፥ አምልኮዎችን፥ እፀዋትንና እንስሳትን በማጥናት ላይ የተመሰረቱ ከመቶ በላይ ምርምራዊ ፅሁፎችም አሳተሙ። ይህ እንግዲህ ፥ ቢያንስ ለሰባ ዓመታት በትእግስት፥ ሳይታክቱና ሳያቋርጡ የመስራት ውጤት ነበር ማለት ይቻላል።

### 6.2.3. የጀርመን ብሔረተኛነት (በ18ኛው ምዕተ ዓመት ማምሻ እና በ19ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ)

ጆን ጎትፍሪድ ኸርደር እና ሌሎችም የሮማንቲክ እንቅስቃሴ ተከታዮች የጀርመንኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ በፈረንሳይኛ በመተካቱ አጥብቀው አዝነው ነበር። ቃልግጥም የአንድን ብሔር የፈጠራ ቅርስ ጨመቅ[23] (essence) አካቶ ይዟል ብለው ያምኑ ስለነበር ጥንታውያኑን ባህሎቻቸውን መሰብሰብ ጀመሩ። ይህንን ያደረጉት ፥ ከነዚህ ባህሎች ውስጥ የአያቶቻቸውን የጀግንነት እና ከፍተኛ ሰናይ እሴቶች ቆፍሮ ለማውጣት ነበር። ለዚህ ብለው ፎክሎር ሰብስበው ይሰንዱ፣ የብሔርን እሴቶች ፥ በጎ ባሕርዮች እና ይትባህሎች እንዲያሳዩ የስነፅሁፍ ስራዎችም ይለዋወጡ፥ እንደገናም ይፃፉ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በ19ኛው ክፍለ ዘመን እና

[22] እ.አ.አ. ከ1700-1721 በስውዲንና ግንባር በፈጠሩባት ሀገሮች መሀከል የተካሄደ ጦርነት ነው። ከ1714-1721 ፊንላንድ በሩስያ ከተያዘችባቸው ጊዜያት አንዱ እንደነበርና ወቅቱ "The Greater Wrath ታላቁ ዘመነ ፍዳ" ይባል እንደነበር ዊኪፒድያ ውስጥ አንብቤያለሁ። የመልሶ መቋቋሚያ ፕሮግራሙ የተነደፈው ከዚህ ፍዳ ለመውጣት ይሆናል።

[23] በዚህ ቃል የተጠቀምሁት ባለቅኔው አቶ ዮሐንስ አድማሱ ለወዳጁ ጽፎት በነበረ ደብዳቤ ውስጥ ተጠቅሞበት አግኝቼው ስለሳበኝ ነው።

በ20ኛው መባቻ ላይ በፊንላንድ፥ በስኮትላንድ፥ በአየርላንድ እና በሌሎች ብዙ ሀገሮች ተከናውኗል።

## 6.2.4. የአሜሪካውያኑ ልምዶች

- **ለትምህርትና ለቱሪዝም ዋና መስህብ ማድረግ፤** ፎክሎረኞች፥ ፎክሎርን በተፈጥሮ ታሪክ ሚዩዝየም (Natural History Museum) ከማሳየት አልፈው ሙያቸው ለትምህርቱና ለቱሪዝም ዋና መስህብ እንዲሆን አድርገዋል።
- **የዘርና የሰራተኛ አመፅን ማብረድ፤** የቻይናዊ-አሜሪካውያን (Chinese Americans) በአሜሪካ መኖር ያስከተለውን የዘርና የሰራተኛ አመፅ፥ በእነሱ ወደአሜሪካ መግባት መቀጠልም ላይ በአሜሪካ ኮንግሬስ በ1882 (እ.አ.አ.) የተጣለውን ማእቀብ በማስተዋል፥ ኩሊን (Culin) የተባለ ፎክሎረኛ ፥ በማእቀቡ መጣል ምክንያት ከሚነሱ ችግሮች ጋር በተያያዘ ፎክሎር ሊኖረው የሚችለውን ተግባራዊ ሚና ያውጠነጥን ነበር።
- **ወታደሮች በጠላት ባህል ውስጥ መኖርን እንዲቋቋሙ ማድረግ፤** ለ12 ዓመታት የጀነራል ጆርጅ ክሩክ አማካሪ የነበረው፥ እ.አ.አ. በ1896 የአሜሪካ ፎክሎር ማኅበር ፕሬዝደንት ሆኖ የተመረጠው ጆን በርክ (John G. Bourke) ስለሕንዳውያን-አሜሪካውያን እና ስለ ሜክስካውያን-አሜሪካውያን ፎክሎር፥ ስለ ምግብ አመጋገባቸው ጨምሮ፥ ዝርዝር ማስታወሻ ይወስድ ነበር። ይህንን ያደርግ የነበረው፥ ወታደሮቹ በጠላት ሰፈር የመኖርን ፈተና መቋቋም እንዲችሉ አድርጎ ለማዘጋጀት የፎክሎር እውቀቱ እንዲያስችለው ነበር።
- **የማላመድ ተግባር 1፤** ፎክሎር፥ ከተለያዩ ሀገሮች ወደ አሜሪካ የተሰደዱ ሰዎች ፥ አዲሱን የመኖሪያ ስፍራቸውን እንዲለምዱ የማድረግ አገልግሎትም ነበረው። ይህ አገልግሎት ጄን አዳምስ የተባለች ሴት "ኸል ሀውስ" (Hull House) በሚል ስም በቺካጎ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሴፕቴምበር 18/1889 ባቋቋመችው ስፍራ በሁለት መንገድ ተግባራዊ ሆኗል። በመጀመሪያ ፥ ስፍራውን ፥ እኒህ ሰዎች ፥ የታወቁ በዓላትን አብረው የሚያከብሩበትና የሀገረሰብ ልብሳቸውን ለብሰው የሚሄዱበት ፥ነባር ዘፈኖቻቸውን የሚዘፍኑበትና ያለፉትን ዓመታት በትዝታ የሚያስታውሱበት እንዲሆን አደረገች። እ.አ.አ. በ1900 እዚያው የሰራተኞች ሙዝየም ፈጥራ ምርቶች ፥ ፎቶግራፎችና ሰርቶ የማሳየት ትርኢቶች እንዲታዩ አደረገች። በልብስ፥ በሸክላ ፥ በብርና በነሐስ ስራዎችና በሌሎች የእጅ ስራዎች መሀከል ያለውን ተመሳሳይነትና ታሪካዊ እድገት በማሳየት፤ ሙዝየሙ ግሪኮችን ፥ ሶርያውያንን ፥ ጣልያኖችን ፥ አየርላንዳውያንን እና

ሩስያውያንን እርስ በእርስ አገናኙ፡፡ በተጨማሪም፥ በትውልድ ሀገራቸው በነበራቸው አኗኗርና ተሰደው ባሉበት በ'አዲሱ ሀገራቸው' አኗኗር መሀከል ተቀጣጣይነትን ከማመልከቱም በላይ፥ በስደተኞቹና በልጆቻቸው መሀከልም ድልድይ ሰርቷል፡፡ ስለዚህም ፥ በ10 ዓመት ውስጥ የጄን ሀሳብ ተቀባይነትን አተረፈ፡፡ እ.አ.አ. በ1910 ሕዝባዊ መጽሔቶች (መጋዚኖች) አሜሪካ "melting pot" ነች የሚለውን የአነጋገር ፈሊጥ ትተው ፥ የእያንዳንዱ ጎሳ ባህል እንዲጠበቅ ይረዳል ያሉትን "mixing bowl" ነች በሚል የአነጋገር ዘይቤ ተክተው መጣጥፎች ያትሙ ነበር፡፡

- **የማላመድ ተግባር 2፤** የፖላንድ ተወላጆች ወደአሜሪካ ከመጡ በኋላ በአዲስ ቦታና ባህል ውስጥ ያጋጠማቸውን ራስን አመቻችቶና አስተካክሎ የመኖር ያለመኖር ፈተና ገጥሟቸው ነበር፡፡ አዲሱ ባህል ከእናት ባህላቸው የአኗኗር ዘይቤና ደንብ ጋር ያለው ግንኙነት ታውቆ ኑሯቸው እንዲሻሻል የፎክሎር ጥናት ተግባራዊ ሚና ተጫውቷል፡፡

- **የማላመድ ተግባር 3፤** በፊሊስ ዊልያምስ የተፃፈ ***የደቡብ ኢጣልያ ፎክሎር በአሜሪካና በአውሮፓ*** የሚል መጽሀፍ ለመምህራን፥ ለነርሶች፥ እና ለሀኪሞች መመሪያ ሊሆን በሚችልበት መንገድ እ.አ.አ. በ1938 ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ በ1940ዎቹ ደግሞ አንድ የማኅበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ፥ ውይይት በሚያመቻች ሰው በሚታገዝ የቡድን ወግ (group conversation) አማካይነት ሰዎች ስለልጅነት ትዝታዎቻቸው እንዲያወሩ በማድረግ በመሀከላቸው መቀራረብን ለማምጣት እንደተቻለ ተፅፏል፡፡ በወጋቸው መሀል፥ ከትረካዎቻቸው ጋር እየተያያዙ የሚመጡ ዘፈኖችና እስክስታዎች ለግኑኝነታቸው ድምቀት እንደሰጡም ተነግሯል፡፡

- **ትምህርታዊ ተግባር፤** ሌላው የፎክሎር ተግባር ከትምህርት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ዶሮቲ ሚልስ ሀዋርድ፥ እ.አ.አ. በ1950 ባሳተመችው መጣጥፍ ፥ ፍልስፍናዋ ተማሪዎች ፎክሎርን እንዳንድ ትምህርት ይማሩ የሚል ፥ ወይም ደግሞ ልጆቹን ፎክለረኛና የፎክሎር ምሁራን እናድርግ የሚል አይደለም፡፡ በእርሷ አስተያየት የፎክሎር ትምህርት፥ ከአጠቃላዩ ከልጅ የማሳደግና የማነፅ ሂደት ጋር ተቀናብሮ መዘጋጀት የሚገባው ነው፡፡ ልጆቹ የፎክሎርን ምንነት እያወቁ፥ በራሳቸው ሕይወት ውስጥና በአካባቢያቸው ባለው ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሚና እያስተዋሉ ፥ ጠቅላላ ሕይወታዊ ሂደቱን የሚማሩበት መሆኑን ተናግራለች፡፡

- **ተግባራዊ ፎክሎርና የአሜሪካ መንግስት ሚና፤**

⇨ ለፎክሎር ምርምር የአሜሪካ መንግስት ከሚያደርጋቸው የገንዘብና የቁሳቁስ ልገሳዎች በተጨማሪ ልዩ ልዩ ተቀዋማት አቋቁሞ ለፎክሎር ስብሰባ ፥ ስነዳ እና ጥናት መንግስታዊ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

⇨ ያቋቋማቸው ተቋማት የፎክሎር ሙዝየሞች መስርተው ፎክሎሮች በሕዝብ እንዲታዩ ያደርጋሉ፥ ፎክሎር ይቀርሳሉ፥ ፎክሎር የማሓዘብ ስራ ይሰራሉ፥ ልዩ ልዩ የፎክሎር ጉባኤዎች ያኪያሄዳሉ ፥ ፌስቲቫሎች በየጊዜው እያዘጋጁ ፎክሎሮች በአደባባይ ሕያው እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ተግባራት የመንግስት ተቋማት ፎክሎር ንቁ የሕይወት አካል እንጂ ትኙና በምሁራን ብቻ የሚሰበሰብና የሚጠና ጉዳይ አለመሆኑን ያሳያሉ፡፡ በባህል የሚለያዩ ሕዝቦች አንዳቸው ስላንዳቸው ያለውን ግንዛቤም ያሰፋሉ ፥ ያዳብራሉ፡፡

⇨ ተቋማቱ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የአሜሪካ ኤትኖሎጂ ቢሮ (American Ethnology Bureau) የተቋቋመው እ.አ.አ. በ1879 ነው፡፡ የተለያዩ የመንግስት ፕሮጀክቶችም (የፌደራል የኪነጥበብ ፕሮጀክት፥ የፌደራል የሙዚቃ ፕሮጀክት፥ የፌደራል ትያትር ፕሮጀክት፥ የፌደራል የደራሲዎች ፕሮጀክት እና የታሪክ መረጃዎች ቅኝት ፕሮጀክት) ፎክሎር ይሰበስቡና ይሰንዱ፥ የፎክሎር ፌስቲቫሎች ያዘጋጁ፥ ፎክሎር ያሳትሙ ነበር፡፡ ቀረብ ወዳለው ዘመን ስንመጣ ሶስት ብሔራዊ ድርጅቶች፥ በመንግስት የተደጎሙ የተግባራዊ ፎክሎር ስራዎች እንዲከናወኑ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ እንገነዘባለን፡፡ እነርሱም እ.አ.አ. በ1974 የተቋቋመው Smithsonian Folklife Festival, እ.አ.አ. በ1974 የተቋቋመው The Folk Arts Program of the National Endowment for the Arts እና እ.አ.አ. በ1976 የተቋቋመው American Folklife Center ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ካከናወኗቸው ተግባራት አንዳንዶቹን ለአብነት ያህል ጠቅሼ በዚህ ክፍል የማቀርበውን አበቃለሁ፡፡ እ.አ.አ. በ1980 ዎቹ ከ56ቱ የአሜሪካ ግዛቶች (የአስተዳደር ክልሎች) 50ዎቹ በፎክሎር እና በሀገረሰብ ሙዚቃ የሰለጠኑ ሰዎችን ቀጥረዋል፡፡ የቀጠሯቸው፥ የሀገረሰብ ኪነጥበብን፥ የከዋኞችን እና የእደጥበበኞችን ስራዎች ለሕዝብ የማሳየትንና የመሰነድን ስራ እንዲያስተባብሩ ነው፡፡ በፎክሎር እና በአሜሪካ ጥናት ከኢንድያና ዩኒቨርስቲ የዶክትርና ዲግሪ ያገኘችውን (እ.አ.አ. በ1973) ራይና ግሪን (Rayna Green) የአሜሪካን የሳይንስ ማስፋፊያ ማኅበር (The American Association for the Advancement of Science)፥ ባህላዊ መሰረት ያለውን

ሳይንስ የማነቃቃት ስራ እንድትሰራ ቀጥሯል። በምእራብ ኬንታኪ ዩኒቨርስቲ ያለው የሀገረሰብ (የfolk) ጥናት ፕሮግራምም ተግባራዊ የሆነ የድኅረምረቃ ፕሮግራም ደዝኖ፥ አስተምሮ ያስመረቃቸው ብዙ ሰዎች የኪነጥበብ አስተባባሪዎች ፥ የአፈታሪክ ባለሙያዎች፥ የሙዝየም ጠጋኞች (curators)፥ የፓርኮችና የመዝናኛ ስፍራዎች ሰራተኞች ሆነው ተቀጥረዋል። ሌሎችም በተለያዩ ቦታዎች መምህራን ሆነው ተቀጥረዋል።

## 7. እኛስ ምን እናድርግ ?

በመጨረሻ ፥ ስለ ኢትዮጵያ የፎክሎር ትምህርትና ምርምር ባጭሩ አስተዋውቅና «የኢትዮጵያ የፎክሎር ኢንስቲትዩት» ስለማቋቋም ፋይዳ አንዳንድ አጣዳፊ የመሰሉኝን አንኳር ነጥቦች ከእናንተ ጋር እጋራለሁ። የመሰሉኝ ነገሮች ዝም ብለው የመሰሉኝ ተደርገው እንዳይወሰዱብኝ አደራ እላለሁ። ምክንያቱም የመሰሉኝ ነገሮች ፥ ከ30 ለማያንሱ ዓመታት በፎክሎር ማስተማርና ምርምር ካገኘሁት ተመክሮ ነጥረው ወጥተው የሚወተውቱኝ ናቸው[24]።

### 7.1. የፎክሎር ትምህርት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት (በኢ.ቋ.ስ.ክ.) ከ1971/1972 ዓ.ም. ጀምሮ "Oral Literature" (ስነቃል) የሚባል ኮርስ ብቻ ነበር የሚሰጠው። ከዚያ በኋላ የኮርሶቹ ቁጥር ወደ ሁለት ከፍ አለ። በፎክሎርና በስነጽሑፍ የኤም.ኤ. ፕሮግራም ከ1995 ጀምሮ መካሄዱ እንደ እድገት የሚታይ ቢሆንም ከ1999 ጀምሮ ፎክሎር በዲግሪ መስጠት መጀመሩ ደግሞ ልዩ እመርታ ሆነ። ከ2002 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ደግሞ በፎክሎር እና በስነጽሑፍ ሁለት የዶክትርና ፕሮግራሞች ተጀምረዋል። ይህ ሁሉ መሆኑ ባንድ በኩል ፥ ጥቂት ከማይባሉ ሰዎች እንደምሰማው ጥሩ ነው።

በሌላ በኩል ግን ፥ በቢ.ኤውም ሆነ በጥምሩ የኤም.ኤ. ፕሮግራም ውስጥ ያለው የፎክሎር ትምህርት ሲካሄድ የቆየው በጣም ውሱን በሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል፥ የመስክ ስራ በጀት፥ የመጻሕፍትና የማንበቢያ ቦታ ግብአቶች እየታገዘ ነው። የፎክሎር ላቦራቶሪ (ቴፕ ማድመጫና መመልከቻ ፥ ፎቶግራፍ ማጥቆሪያና ማተሚያ፥ የቴፖችና የዲጂታል ምንጮች ማደቻ -edit ማድረጊያ )፥ የፎክሎር

[24] በዚህ ክፍል የማቀርበው አብዛኛው፥ ሰኔ 19 እና 20 ቀን 2001 በተካሄደው በ"21ኛው የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ጉባኤ" ላይ በቃል አቅርቤ፥ በኋላ ደግሞ ጽፌ ፥ ከሸኚ ደብዳቤ ጋር በመላክ ከተወሰኑ የአዲስ አበባ የዩኒቨርስቲ አስተዳደር ኃላፊዎች ጋር የተጋራሁት ነው።

ቤተመዛግብት፥ የፎክሎር የቴፕና ቪዲዮ አርካይቭ፤ ቴፕሪከርደሮችና ካሜራዎች፥ የመስክ ድንኳኖችና የመስክ መጓጓዣ መኪናዎች በሌሉበት ነው መምህራኑ አስተማሩ፥ ተማሪዎችም ተማሩ የምንለው፡፡

### 7.1.1 በፎክሎር የሰለጠነ ሰው ኃይል

የሰው ኃይልን በተመለከተ ብዙ ችግር አለ፡፡ በፎክሎር ከቢ.ኤ. እስከ ዶክትሬና ደረጃ የተማረ አንድም ኢትዮጵያዊ አላውቅም፡፡ አቶ ሰይፉ መታፈሪያ፥ ካርቱም ዩኒቨርስቲ አማርኛ በሚያስተምሩበት ጊዜ በፎክሎር የኤም.ኤ. ዲግሪ እንዳገኙ ይታወቃል፡፡ አቶ (አሁን ዶ/ር) ጌቴ ገላዬ ወደፎክሎር መሸጋገሪያ እንዲሆነው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ስፖንሰርነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነሰብእና የሶሲዮሎጂ ክፍለትምህርት ኤም.ኤ. ዲግሪ፥ በኋላም ከሀምቡርግ ዩኒቨርስቲ ዶክትርናውን አግኝቷል፡፡ ዶ/ር አዲሱ ቶሎሳ በኢንድያና ዩኒቨርስቲ ከሚገኘው ከታወቀው የፎክሎር ኢንስቲትዩት በፎክሎር ዶክትርናውን አግኝቷል፡፡ ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው በ2002 ዶክትርናውን ከሆላንድ አግኝቷል፡፡ አቶ ብርሃኑ ገበየሁ[25] እና አቶ አብርሃም ዓለሙ በሆላንድ የሚያኪያሄዱትን የዶክትርና ትምህርት ያጠናቅቃሉ ተብሎ ተስፋ ተደርጓል[26]፡፡ ከ1995 ጀምሮ ፎክሎርን ከስነጽሑፍ ጋር አጣምረው የኤም.ኤ. ዲግሪ ያገኙ ምሩቃን አሉ፡፡ ከ1999 ጀምሮ ደግሞ ፎክሎር ለመጀመሪያ ጊዜ በቢ.ኤ.ዲግሪ እየተሰጠ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ተመራቂዎችም በ2001 ተመርቀዋል፡፡ በመስኩ ከነበረን ፥ ካለን እና ከሚኖረን ውስጥ መቆጠር ስላለበት መጠቀስ ያለበት ነጥብ አለ፡፡ እ.አ.አ. በ2005-2006 የትምህርት ዘመን በፎክሎር የዶክትርና ዲግሪ ያላቸው፥ ዶ/ር ማርክ ሊቨንጉድ የተባሉ አሜሪካዊ በድኅረ ምረቃ ፕሮግራማችን ውስጥ ለአንድ ዓመት አስተምረዋል፡፡

«አንተ ራስህ ማነህ? ምንድነህ?» የሚል መኖሩ አይቀርም፡፡ ተገቢም ነው፡፡ እኔ በ1965 መጨረሻ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ተመርቄ ምሩቅ ረዳት የሆንኩ ፥ በ1971 እንግሊዝ ሀገር ለሁለተኛ ዲግሪ የአፍሪካ ስነጽሑፍ ያነበብኩ ነኝ፡፡ የዶክትርና ዲግሪዬ በስነጽሑፍ ነው፡፡

---

[25] አቶ ብርሃኑ ሐምሌ 12 ቀን 2002 በድንገት በሞት ተለይተውብናል፡፡

[26] ከእነርሱ ሌላ ምናልባት በየውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አባል የነበሩትን አቶ ገብረሃና ገብረ መድኅንን መጥቀስ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ተፍጻሜ ያደርሱት አያደርሱት በእርግጠኛነት የምናገረው ባይኖረኝም ካናዳ ውስጥ በፎክሎር የዶክትርና ትምህርት ይማሩ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ የመስክ ምርምር ለማድረግ አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜያትም ስለምርምራቸው ተጨዋውተናል፡፡

የተማረ የፎክሎር የሰው ኃይላችን ታሪክ እና ፕሮፋይል ፥ እኔ እስከማውቀው ድረስ ይኼው ነው። የእያንዳንዳቸውን አስተዋጽኦ እዚህ አላነሳም[27]። ከፍ ብዬ ከዘረዘርኳቸው ውስጥ እስካሁን «የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር» በተሰኘው የድኅረ ምረቃ ፕሮግራም ውስጥ በማስተማር ላይ ያለሁት እኔ ነኝ[28]። ስለዚህ የፎክሎር የዶክትርና ፕሮግራም በ2002 የሚጀመር ከሆነ ፥

(1ኛ) ቢያንስ ለመጀመሪያዎቹ አምስት ገደማ ዓመታት ፥ ከታዋቂ የፎክሎር ትምህርት ቤቶች ከእኛ የተሻለ የኢንተርናሽናል ፎክሎር ተሞክሮ ያላቸው ፕሮፌሰሮች ተቀጥረው ፥ አሁን እየተለመደ በመጣው በ"ብሎክ" ዘዴ የሚያስተምሩበትንና በማማከር ስራም የሚጣመሩበትን መንገድ መምከር አለብን።

ፕሮግራሙ በጠንካራ መሰረት ላይ መተከል አለበት ብዬ ተምር አምናለሁ። ጠንካራ መሰረት ለመጣል ደግሞ ከፍ ብዬ የጠቀስኳቸውን ዓይነት ሰዎች ፈልገን ማግኘት እንዳለብን ግልጽ ነው። እንዲህ ዓይነቱን መሰረት ለመጣል ደግሞ «የዶክትርና ፕሮግራሞች ይከፈቱ!» እያልን እንደምንፈክረው የመሰረቱ ምሰሶ የሚሆኑትን ፎክለረኞች ለመፈለግና ለማግኘት አስላጊውን ገንዘብና የጊዜ በጀት መድቦ በሥርዓት ፥ በእውቀት ፥ በቅልጥፍና እና በፍጥነት መንቀሳቀስ ያስፈልገናል። እነዚህን ያለ ብዙ ወጪ ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ቢኖርም ለኢትዮጵያ ፎክሎር ይህ መንገድ እስካሁን ዝግ እየሆነ አስቸግሯል። ምን ማለቴ እንደሆነ የግል ተሞክሮዬን አሳጥሬ ላውጋችሁ።

እ.አ.አ. ከነሐሴ 2005 እስከ ነሐሴ 2006 አሜሪካን ሀገር በሚገኘው የኢንዲያና ዩኒቨርስቲ ፥ «የፎክሎርና የኤትኖሚዩዚኮሎጂ ክፍለ ትምህርት» በሰባታም (sabbatical) አንድ ዓመት ቆይቼ ነበር። ወደዚያ ከማቅናቴ በፊት የክፍለ ትምህርቱ ሊቀመንበር ከነበሩት ከፕሮፌሰር ሩት ስቶን (Ruth Stone), እዚያ ጥቂት እንደቆየሁ እርሳቸውን ከተኳቸው ከፕሮፌሰር ሪቻርድ ቦውማን (Richard Bauman) ፥ የእኔ የግል ባልደረባ (host) ሆነው ከተመደቡልኝ ከፕሮፌሰር ጆን ጆንሰን (Jhon Johnson) ፥ ከዩኒቨርስቲው የአፍሪካ ጥናት ዳይሬክተር ጆን ሀንሰን (John Hanson) እና ከምክትል ዲሬክተሯ ከማርያ ግሮስንጋተ (Maria Gross-Ngate) ጋር ጥምር የፎክሎር የዶክትርና ፕሮግራም ስለሚጀመርበት መንገድ ፥ እኔ የጫርኩትን የመወያያ

---

[27] በሌላ መጣጥፍ (JES, June 2001) ግን ስለስራዎቻቸው መጠነኛ ማስተዋወቂያ ጽፌያለሁ፡፡ የዛሬው ጉዳዬ በፎክሎር ሙያ ያለን የሚመስለኝን የሰው ኃይል ማመልከት ነው፡፡

[28] በኢ.ቋ.ስ.ክ. ባለው የፎክሎር የዲግሪ ፕሮግራም እና በስነልሳንና ፊሎሎጂ ክፍለትምህርት በ"documentary Linguistics" የድኅረምረቃ ፕሮግራም ውስጥ የሚያስተምረው፤ "የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ማእከል" ዲሬክቴር፥ ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው ፥ በያዝነው ወር መገባደጃ ላይ በተባለው ፕሮግራም ውስጥም ማስተማር ይጀምራል።

ጽሑፍ መነሻ አድርገን ብዙ ተነጋግረን ነበር። ሁሉም ፍላጎቱ ነበራቸው። የበጀት ጉዳይ ነበር ማነቆ የሆነው። እንኳን እኛን ሊያግዙን ስለራሳቸው የምርምር በጀትም ይጨነቁ ነበር። በወቅቱ ፥ በቀላሉ ሊያገኙት የሚችሉት የምርምር በጀት ከ"መከላከያ ቋት" (ከ"Defense Fund") እንደነበር ጠቅሰው ፥ ከቋቱ ገንዘብ መውሰድ ከሙያና ከየግላቸው የሕይወት መርሕ ውጪ መሆኑን የጠቀሱልኝም ነበሩ።

ፕሮፌሰር ጆን ጆንሰን ተክህኗቸው (specialty/specialization) በሶማሌ ፎክሎር (በተለይ ደሞ በቃልግጥም) ላይ ስለነበረ በኢትዮጵያ የፎክሎር ፕሮግራም እንዲከፈት ትልቅ ጉጉት ነበራቸው። ተብዙ የዩኒቨርስቲው ባለሥልጣናት ዘንድ እኔን ይዘው በመሄድ ልዩ ጥረት አድርገው ነበር። ይህም ብቻ አይደለም። ጡረታ ሊወጡ እየተዘጋጁ ስለነበር የጆርናል ክምችታቸውን እና መጽሐፎቻቸውን በሙሉ ስንወያይበት ለነበረው የፎክሎር ፕሮግራም ቤተመጻሕፍት እርሾ እንዲሆን አበርክተው ነበር። የማንጓጊያ ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች ለአራት ወራት ያህል ከእርሳቸው ጋር ፈልገን ስላላገኘን ሳይሳካ ቀረ። ገንዘቡን ሊያገኙልን ካልቻሉት መሀከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ክፍሎች አሉበት። አንዱ ክፍል፥ «ገንዘብ ሞልቷል»ን በመደጋገም ዝና በማትረፍ ላይ የነበረ ነው።

ሌላው ፕሮብሌም ፥ ስለ ጥምር የዶክትርና ፕሮግራም ላወጋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ እቢሯቸው ስሄድ ፥ ፕሮፌሰር ቦውማን በቁጭት መልክ ያጫወቱኝ ነው። ስለ ኢትዮጵያ ለማጥናት ትልቅ ጉጉት ፥ የወጣት ንቃትና ጉልበት በነበረኝ ጊዜ መጥተህ ቢሆን (ከ40-50 ዓመታት በፊት የሚሉ መሰለኝ) ድንቅ ነበር። የዛሬዎቹ ወጣቶች የምርምር አዝማሚያ የተለየ እንዳሚመስላቸው ከገለጹ በኋላ ነበር ሶስት ሆነን እንነጋገርበት ብለው እኔ የውይይት መነሻ ሃሳብ የጻፍኩት። ይህንን የጠቀስኩት ወጣቶቹን ማግኘት የሚቸግር ስለመሰለኝ እነርሱን ተከታትዬ ሃሳባቸውን ለማወቅ ያልሞከርኩበትን ምክንያት ለመጠቆም ነው።

በስካንዲኔቪያ ለሚገኙ ፥ በተለይም እፊንላንድ ባለው ታዋቂው ቱርኩ (Turku) ዩኒቨርስቲ ወደሚገኙ የፎክሎር ፕሮፌሰሮችም በመመየል (ኢሜይል በመላክ) የተደረገ ሙከራም ነበር። በየዋህነት ያደረግሁት መሆኑ በኋላ ተሰምቶኛል። ከኮንፈረንስ ፥ ከትምህርትና ከምርምር ስራ ጋር በተገናኘ መድረክ ላላወቁት የጥምር ፕሮግራም (Joint program) ለማኝ ፥ ሁሉም እንደጻፈላቸው ሰው በጉጉት አይመልሱም። የሚመልሱትም ተክህኗቸው ሌላ አካባቢ ላይ መሆኑን ጠቅሰው ይሰናበታሉ ፤ አንዳንዶቹ ጀምረው በእንጥልጥል ይተዉታል። እስካሁን የተረዳሁት፥ የሚፈለገው በግል መንፈራገጥ ብቻ በቀላሉ እንደማይገኝ ነው።

ስለዚህ ልዩ ዘዴ መፈለግ ያስፈልጋል[29]:: ወደታወቁ ዩኒቨርስቲዎች ተጉዞ በእውቀታቸው አንቱ ከተባሉት ጡረታ የወጡትን አነጋግሮ ፥ አሳምኖ ፥ እንዲመጡ የሚሞክር ሰው መላክ እያደር እየተገለጸልኝ የመጣ ፈጣንና ጠቃሚ መንገድ ነው:: የገንዘብና የጊዜ በጀት ያስፈልጋል ያልኩት ለዚህ ነው::

(2ኛ) በተራ ቁጥር 1 ያመለከትሁት የማይሆን ከሆነ ፥ ECA ፥ UNESCO እና AU ውስጥ የሚሰሩ የፎክሎር/የባህል ባለሙያዎች መኖር አለመኖራቸውን አጣርቶ፣ ከተገኙ እነርሱን እና በፕሮግራሙ ውስጥ የተጠቀሱትን የእኛዎቹን አዲስ የዱክትርና ተመራቂዎች ይዞ የአቻ-ለአቻ ፕሮግራም በማካሄድ ማዝገም ነው::

(3ኛ) አይሆንም የሚል ስጋት አለኝ እንጂ ፥ ሌላው ግልጽና አስቸኳይ ጊዜያዊ መፍትሔ በዩኒቨርስቲው ውስጥ በተለያዩ ስሞች የሚሰጡትን የፎክሎር (የባህል) የድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞች ፥ ያለንን የሰው ኃይል የምር ተግምት ባስገባ መንገድ እንደገና ቀርጾ ፥ መምህራኑንም በአንድ ጊዜያዊ ፑል አሰባስቦ ፥ ለተወሰኑ ዓመታት ፕሮግራሙን ማካሄድና ፤ የተማረ የሰው ኃይላችን ሲጠናከር ደግሞ በልዩ ልዩ ሙያ የተካኑ (specialize ያደረጉ) ሰዎችን የሚያፈሩ የዱክትርና ፕሮግራሞችን መቅረጽ ይመስለኛል::

### 7.1.2 የትምህርት መሳሪያዎችና ቦታዎች

በኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ያሉት የፎክሎር መጻሕፍት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል:: በቂ ነው የሚባልበት ደረጃ ግን ገና አልደረሰም:: ይህ የሆነው በበጀት እጥረት ብቻ የሆነበት ጊዜ ነበር:: ከዚያ በኋላ ደግሞ በበጀት እጥረትና በመምህራኑ የክትትል ጊዜ ማጣት የሆነ ይመስለኛል:: ተስፋ መቁረጥ የነበረበትም ጊዜ ነበር:: ይሁንና አንዳንድ መምህራን ባለፉት ሶስት አስርታት በተለያዩ መንገዶች በግል የሰበሰቧቸውን መጻሕፍት ፥ ከመጻሕፍትና ከጆርናሎች የሰበሰቧቸው መጣጥፎችና ምእራፎች ያሉባቸውን መድበሎች ለትምህርት ክፍሉ ለማበርከት ወስነው ፥አንድ የማንበቢያ ክፍል እንዲመደብ ከፍተኛና የበታች ባለስልጣናትን ጠይቀው ፥ የተጠየቀውን ክፍል ሳያገኙ አምስት ዓመት ሆናቸው:: በተጨማሪም ፥ ዶ/ር ማርክ ሊቨንጉድ በፉልብራይት በኩል ለክፍለ ትምህርቱ

[29] ይህ ከተባለ በኋላ ፥ Archival Platform በሚል የፎክሎር ምሁራን መገናኛ መድረክ (Listserv) ለፎክሎር የዱክትርና ፕሮግራም የውጭ አስተማሪ የሚያስፈልጋቸውን ኮርሶች ፥ የኮርሶቹን መግለጫ ፥ «ብሎክ ቲቺንግ» በሚባለው ዘዴ ለአንድ ወር ለማስተማር የሚመጣ ፎክሎረኛ ከዩኒቨርስቲው የሚያገኘውን ጥቅም በማውጣት ከዲሴምበር 2009 እስከ ጁላይ 2010 የሚያስተምሩ 5 ፎክሎረኞች ለማግኘት ተችሏል:: ሁለት ከ አሜሪካ (Dr. Tok Thompson, Dr. Luisa Del Giudice) አንድ ከፊንላንድ (Dr. Outi Fingerroos) መጥተው አስተምረው ሄደዋል:: ሁለት ከህንድ (Prof. Muthukumaraswamy) እና ከአሜሪካ (Prof. Claus) የፊታችን ሰኔ እና ሐምሌ እንደሚመጡ ቃል ገብተዋል::

የለገሷቸው መጻህፍት በባለአዳራው ዘንድ ሶስት ዓመት ገደማ ቆይተዋል። በዚህ የተነሳ የፎክሎር መምህራን እና ተማሪዎች በእነዚህ መጻሕፍትና ስርዓት ባለው መንገድ የሚገለገሉበት ቦታ እንዳጡ አሉ።

ስለ ትምህርት መሳሪያዎች ከዚህ በላይ ያልኩትን ካልኩ በኋላ ስለ ፦

- የፎክሎር ላቦራቶሪ (ቴፕ ማድመጫና መመልከቻ ፥ ፎቶግራፍ ማጥቆሪያና ማተሚያ ፥ የቴፖችና የዲጂታል ምንጮች ማደቻ ወዘተ.)፤
- ኮምፒዩተሮች፤
- የፎክሎር ቤተመዛግብት ፤
- የፎክሎር የቴፕ ፥ የቪድዮ ቴፕ ፥ የሲዲ እና የዲቪዲ ክምችት አርካይቭ፤
- ቴፐሪከርደሮች፥ መስክበሪያዎች (transcribers) ፥ ካሴቶች ፥ ሲዲዎች ፥ የፎቶና የቪዲዮ ካሜሪዎች፤
- የመስክ ድንኳኖች እና
- የመስክ መጓጓዣ መኪናዎች አለመኖር በዝርዝር ባወሳ የእኔንም የእናንተንም ጊዜ ማጥፋት ይሆናል። በቅርብ ቀናት ውስጥ ተገናኝተን ፥ ተመካክረን ለ2002 የትምህርት ዘመን ዝግጅት እንድናደርግ ፥ በተለይ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዲንን እንደገና እያስታወስኩ አንድ አጣዳፊ የሚመስለኝን ነጥብ ብቻ ጠቅሼ፥ ስለትምህርት መሳሪያዎች የማወሳውን አበቃለሁ።

ነጥቡ በሚቀጥሉት አራት ወራት ቦታ ማሰናዳትን የሚመለከት ነው። አራት ኮንቴይነሮች ባስቸኳይ ተፈልገው/ተገዝተው ለዱክትርናው ፕሮግራም በሚያገለግሉበት መንገድ መዘጋጀት ያለባቸው ይመስለኛል። አራት ይሁኑ ያልኩት በጣም ተቆጥቤ ነው። የሚውሉት ለቢሮ ፥ ለማንበቢያ ፥ ለአርካይቭና ቤተመጻህፍት እና ለኮምፒውተርና ለዲጂታል መሳሪያዎች መማሪያና ለሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ነው[30]።

### 7.1.3 የመስክ ስራ - ትምህርቶች እና መልመጃዎች

እስከ ዛሬ የፎክሎር የመስክ ትምህርት የተካሄደው በክፍል ውስጥ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። መምህሩ የሚሰጠው የፎክሎር የተርም ወረቀት (መልመጃ) ስራ የሚያስከትላቸው የመስክ ወጪዎች የተሸፈኑት በተማሪዎቹ ነው። በሁለት ዓመት ቆይታቸው የሚሰሯቸው የፎክሎር የመስክ መልመጃዎች ደግሞ ከ5 ወይም ከ6

[30] ቦታውን የማሰናዳት አጋጣሚ ይመጣል የሚል ናፍቆት ዛሬም አለ።

አያንሱም፡፡ በዚህም ላይ መምከር አለብን፡፡ ለፎክሎር የመስክ ስራ ልምምድ ወጪ መመደብ ለሳይንስ ፥ ለምህንድስና እና ለህክምና የመስክ ስራዎችና የላብራቶሪዎች ጥናቶች ወጪ እንደ መመደብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የዚህን ዝርዝር በመጠኑ ለማስረዳት አሁን ጊዜ የለም፡፡

## 7.1.4 የመስክ ስራ - የቲሲስ ወጪ

ለፎክሎር ፥ የመስክ ጥናት የሚመደበው ገንዘብ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይኼ እንኳን ከዘመነ ደርግ ጀምሮ ረዥም ታሪክ ካለው በመሰረቱ ከአመለካከት ችግርና ካለማወቅ የመነጨ ቢሆንም ፤ በሚያውቋት የራስ ሙያ እውቀት ላይ ተመስርቶ በማያውቁት ብዙ ሙያ ላይ የመወሰን አቅም ባለቤት ከመደረግ ጋርም የተያያዘ ነበር ፥ ዛሬም የተያያዘ ይመስለኛል፡፡ የኋለኛው ነጥብ ቀስ በቀስ ውገናን (በግልጽ ቋንቋ «የሙያ ጎጠኝነት»ን) በምርምር በጀት ውስጥ እንዲገባ የፈቀደ ይመስለኛል፡፡ «የዩኒቨርስቲው የምርምርና ኅትመት ቢሮ ቢያንስ-ቢያንስ ራሳቸውን የቻሉ የሳይንስና የሶሻል ሳይንስ ንዑሳን ክፍሎች ይኑረው፡፡» የሚሉ ውትወታዎች [እኔ እስከማስታውሰው ባለፉት ሶስት ተኩል አሰርቶች (decades)] ሰሚ አግኝተው ቢሆን ኖሮ ችግሩ ቀለለ ይል ነበር፡፡ የዚህ ችግር ዋና መፍትሔ ግን ፋክልቲዎች ሊኖራቸው ከሚገባ ራስን የማስተዳደር ነጻነት ጋር ተያይዞ የሚሰላና የሚወሰን ቢሆንም እስከዚያ ግን እየተመካከርን ጊዜያዊ መፍትሔ መፈለግ ያለብን ይመስለኛል፡፡

## 7.1.5 የመስክ ስራ - የአማካሪ ወጪ

ተማሪዎች ለሚጽፏቸው የኤም.ኤ ቲሲሶች ፥ ከመስክ ሰብስበው የሚያመጧቸው ጥሬ መረጃዎች (raw data) ከመስክ ይምጡ አይምጡ ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በሌሉበትም ነው በመረጃዎቹ ላይ የምርምር ስራ ተካሂዶ ቲሲስ የሚጻፈው፡፡ እያንዳንዱ አማካሪ ከንባብ በቀሰመውና የመስክ ስራ ልምድ ካለውም በራሱ ተሞክሮ ላይ ተመስርቶ ብቻ ነው የመጡትን መረጃዎች ምንጭ አስተማማኝነት የሚገመግመው፡፡ ባንጻሩ ፥ ዛሬ ፥ የመመረቂያ ጽሑፍ እንጽፋለን የሚሉ ማስታወቂያዎች በአደባባይ እየወጡ ነው፡፡ ነገሩ ያሳሰባቸው የአዲስ አድማስ እና የአዲስ ነገር ጋዜጣ ጸሓፊዎች ስለ ፕሮብሌሙ ጽፈዋል፡፡ ትምህርትና ምርምር የሚጠይቋቸውን ስርዓቶችና ምግባሮች ለመጠበቅና ፥ በወቅቱ በመልማት ላይ ያሉት የመመረቂያ ጽሑፍ ፋብሪካዎች በድኅረ ምረቃ ደረጃ ይበልጥ እንደይስፋፉ ለመከላከል ሲባል ይህንን በጀት መያዝ ያስፈልጋል፡፡ አማካሪው ፥ ተማሪዎቹ ጥናት በሚያደርጉባቸው አካባቢዎች ሄዶ መረጃዎቹ ተገኙ ከተባሉበት መገኘታቸውን እና በትክክል መመዝገባቸውንም ለማረጋገጥ እንዲችል መጓጓዣና የወጪ አበል ያስፈልገዋል፡፡

### 7.1.6 የመስክ ስራ - በክፍለ ትምህርቱና በማኅበረሰቡ መሀከል ግንኙነት መመስረቻ ወጪ

ጥናቱ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ካለው ማኅበረሰብ ፥ ከአውራ የመረጃ አቀባዮች እና ካካባቢው ባለስልጣናት ጋር እየተገናኙ የመስክ ችግሮችን ለማቅለል የሚረዱ የመተዋወቅ ፥ የመግባባትና ስምምነት የማድረግ ተግባራትን ለማከናወን የሚያግዙ ግብአቶችም ዛሬ የሉም። ወደእነርሱ እየሄዱ ክፍለ ትምህርቱ ስለሚያደርገው ምርምር ፋይዳ ማሳወቅና መመካከር ያስፈልጋል። የምርምሩ ውጤት እንዴት በተግባር ሊውል እንደሚችልም መወያየት ይጠቅማል። የምርምር ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ቅን ማኅበራዊ ግንኙነትም መፍጠር የግድ ነው። ይህ ሁሉ ግን ጊዜና በጀት ያስፈልገዋል። ሌላ መንገድ እንዳይፈለግ በየጊዜው የምንቀበላቸው ተማሪዎች ቁጥር ከመምህራኑ አቅም በላይ እየጨመረ ይሄዳል። ስለዚህም የማስተር ፥ የማማከር ፥ አዳዲስ ፕሮግራሞችን የመቅረጽ ፥ ሌሎች የኮሚቴ ስራዎችን ማከናወን እና በተለያዩ ስብሰባዎች መካፈል ብዙ ጊዜ ይወስዳሉ። በዚህ የተነሳ ፥ ተማሪዎች በመስክ ስራ ላይ ከሚገባው በላይ ይጉላላሉ። ይሄም የሚያሳስብ ፕሮብሌም ነው።

## 7.2 አጣዳፊ የሚመስለኝ ፎክሎር-ነክ የምርምር ስራ

ምርምርን በተመለከተ ዛሬ የማተኩረው ፥ መጠቁም ያላቸው መግለጫዊ የፎክሎር መዘርዝሮችን (Indexed and annotated folklore bibliographies) እማዘጋጀት ላይ ነው። ይህንን የማደርገው እጅግ መሰረታዊ የምርምር ጉይ ስለሚመስለኝ ነው። እነዚህን መዘርዝሮች አዘጋጅቶ ማሳተምና በየቤተ መጻሕፍቱ ማኖር የፎክሎር ሙያተኞች ግዴታ ብቻ አይደለም። የማንኛውም የትምህርት እና የምርምር መስክ ባለሙያ ግዴታም ነው ማለት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ መዘርዝር በሌለበት አንድ የእውቀት መስክ ከምን ተነስቶ እምን እንደደረሰ ማንም ባለሙያ በሙሉ አፉ መናገር አይቻለውም። ምክንያቱም ፥ በምን-በምን ርእሶች ላይ ፥ ምን እንደተጻፈና እንዳልተጻፈ በእርግጠኝነት ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ይህ ደግሞ የነበረውንና ያለውን እንድናውቅ ብቻ ሳይሆን ባለማወቃችን ደግመን ደጋግመን ጊዜ እንድናባክንም ያደርጋል። የባሰም ነገር አለ። ቁጥራቸው በቀላሉ የማይገመት ሰዎች አድፍጠው ፥ እነዚህን ስራዎች እያደኑ ለተለያዩ ኮርሶች እና ፕሮግራሞች በተርም ወረቀት መልክና በመመረቂያ ጽሑፍ መልክ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ለምሳሌ ፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (አ.አ.ዩ) የተጻፈ የዲግሪ ማሟያ ድርሳን (ቲሲስ) ዲላ ዩኒቨርሲቲ ፥ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተጻፈው ጂማ ዩኒቨርስቲ ሊቀርብ ይችላል። በኤም.ኤ ደረጃ ብኩርናውን (ባለቤቱን) ሳይገልጹ ፥ እንዳለ ገልብጠው የተደረሰባቸው አንዳንድ የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች አልጠፉም። በተጨማሪም ፥ በተለይ በአማርኛ

የተጻፉትን ስራዎች ፥ ባለቤቶቻቸውን ሳይጠቅሱ በአማርኛና በእንግሊዝኛ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚያሳትሙም አይጠፉም።

ስለዚህ ፥ መጠየቅ ያለብን ብዙ ጥያቄ ያለ ይመስለኛል። ጥቂቶቹን እነሆ፡-

- ሌላው ይቅርና ባለፉት 45 ዓመታት ፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀረቡት የቢ.ኤ. እና የኤም.ኤ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (ዲማጾች) መዘርዝሮች ፥ በእቅድና በስርዓት ታትመው በቤተመጻሕፍት ይገኛሉ?
- ይሄም ይቅር ፥ በ "የቋንቋዎች ጥናት ተቋም" ውስጥ ላሉት የኤም.ኤ. ፕሮግራሞች የቀረቡ የኤም.ኤ. ዲማጾች ጉዳይ ላይ በስርዓት ተወያይተን መግለጫዊ መዘርዝር አዘጋጅተን ተማሪዎቻችን ርእስ ሲመርጡ ፥ እኛም ርእስ ስናጸድቅ ፥ ስራቸውና ስራችን ኃላፊነትና ቅልጥፍና ባለው መንገድ እንዲከናወን አድርገናል?
- ይህን ባለማድረጋችን የደረሰ ጥፋት ይኑር አይኑር በተጨባጭ ማስረጃ ለማወቅ እንችላለን?

ዝርዝሩን ሁላችንም እንደምንገምተው ብዙ ነው። የሚቀጥለው ነጥቤ ይህ ለምን የሆነ እንደሚመስለኝ ጠቋሞ ወደፊት ማድረግ አለብን የምለውን መሰንዘር ነው።

በመጠቁም (index) የተደገፉ መግለጫዊ መዘርዝሮች (annotated bibliographies) በብዙ ሙያዎች ያልተዘጋጁት ዩኒቨርስቲያችን ትምህርትን ፥ እውቀት ማመንጨትን ፥ ልማትን እና ስነዳን (documentation ን) ያቀናጀ አጠቃላይ እቅድና ፖሊሲ ስሌለው ይመስለኛል። እንዲህ ዓይነት አጠቃላይ መምሪያ ኖሮት ፥ ፋክልቲዎች ፥ የምርምር ኢንስቲትዩቶችና የትምህርት ክፍሎች በዚያ ላይ ተመስርተው የየራሳቸውን እቅድና መምሪያ አውጥተው ቢሆን ኖሮ ዛሬ እምንገኝበት ሁኔታ ላይ አንገኝም ነበር የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ለምርምር በወጣው ገንዘብ ለትውልድ የምናስተላልፈው እውቀትም እንዲህ በየቦታው በተዝረከረከ ፥ በሌላ አነጋገር ባልተደራጀ መልኩ ፥ አይገኝም ነበር የሚል አስተያየትም አለኝ።

ልንካነው በየምንፈልገው ልዩ መስክ በተቻለ መጠን የተሟላ መሰረታዊ መዘርዝር ከተለያዩ ምንጮች አደራጅተን ምርምር የመጀመርና ያዘጋጀነውንም የማሳተም ልምድ አለማዳበራችንም አንድ ሌላ ምክንያት ይመስለኛል። የዚህ ምንጭ ደግሞ ያለፍንበት የትምህርት ስርዓት ይመስለኛል።

ሶስተኛው ምክንያት ፥ ከሁለተኛው የሚመነጭ ነው። ብዙዎቻችን ፥ ጥቂት የማንባል ከፍተኛውን የአካዳሚያ ማእረጎች የያዝነውን ጨምሮ ፥ ለመዘርዝር ስራ

የምንሰጠው ዋጋ አነስተኛ ነው። ለምሳሌ ፥ «ይሄ'ኮ የወዛደር ስራ ማለት ነው!» የተባልኩበት ጊዜ ነበር። ባይዎቹ እስከዛሬ ያሳዝኑኛል። የዩኒቨርሲቲው የምርምር ቢሮና የዩኒቨርሲቲው የእድገት መርህም እንዲህ ዓይነቶቹ ስራዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መሆናቸውን የሰበኩበትንና የቀሰቀሱበትን ጊዜ አላስታውስም። የነዚህ ሁሉ ዝርዝር ብዙ ስለሆነ «ባለን አቅም እና እያንዳንዳችን ፥ በዩኒቨርሲቲው መጠነኛ ትብብር ጭምር ፥ ምን እናድርግ?» ለሚለው ጥያቄዬ አንዳንድ ነጥቦችን በሩጫ ልሰንዝር።

## የምን-የምን መዘርዝር ይዘጋጅ?

- **የጥሬ መረጃዎች** (ብዛትና ዓይነታቸውን ገና ያላወቅናቸው ግጥሞች ፥ ተረኮች ፥ ምሳሌያዊ ንግግሮች ፥ ቀልዶች ፥ እንቆቅልሾች ወዘተ. ማለት ነው።)
- **የአስተያየቶች** (የተለያዩ ሰዎች ስለፎክሎር ፥ ስለ ስነጽሁፍ ፥ በጥቅሉ ስለባህል በየዘመኑ የጻፏቸውን መጣጥፎች ማለቴ ነው)
- **የምርምር ስራዎች** (ከአስተያየት የላቁ ስለስነጽሁፍና ስለፎክሎር በባለሙያዎች የተከናወኑ ምርምሮች፥ ቁዘማዎች ወዘተ. ማለት ነው።)

## ከምን-ከምን ምንጭ ይዘጋጁ ?

ከብራና ጽሑፎች፥ ከአርካይቮች፥ ከጋዜጦች፥ ከመጽሔቶች፥ ከጆርናሎች፥ ከመድበለ ጉባኤዎች (Proceedings)፥ ከመጻሕፍት፥ ከመዝገበቃላት፥ ከኢንተርኔት ወዘተ.

### እንዴት ይዘጋጁ?

- «በመጠቀም የተደገፉ መግለጫዊ መዘርዝሮች ፕሮጀክት» ነድፎ የፎክሎሩን በፎክሎር መምህራን ፥ የስነጽሑፉንም በስነጽሑፍ መምህራን ነድፎ በእነርሱ መሪነት በመስራት ፤
- ለፕሮጀክቱ ደጎና ገንዘብ ማግኘት ከተቻለ በስነጽሑፍ እና በፎክሎር የኤም.ኤ. ዲግሪ ካላቸው መሀከል መርጦ በኮንትራት ቀጥሮ ማሰራት ጥሩ ውጤት ያስገኛል ብዬ አምናለሁ[31]።

[31] በነገራችን ላይ ፥ ከፍ ብዬ እንደጠቀስሁት እንዲህ ዓይነቱ መሰረታዊ የምርምር መሳሪያ እስካሁን ምንም ያልተዘጋጀባቸው የማኅበራዊ ሳይንስ ፥ የተፈጥሮ ሳይንስ ፥ የምህንድስና ፥ የህክምና እና ሌሎች ሙያዎች ካሉ በየባለሙያዎቹ መዘጋጀት አለባቸው ብዬ ተምር አምናለሁ።

- ለፕሮጀክቱ ገንዘብ የማይገኝ ከሆነ ግን ሌላ ዘዴ መፈለግ ያስፈልጋል። በመምህራኑ መሪነትና የቅርብ ክትትል በሚካሄድ ሌላ ፕሮጀክት መዘርዝሮቹን በኤም.ኤ. የተርም ወረቀቶች መልክ ማዘጋጀት ይቻላል። ይሄንንም የምለው ለስራው የሚያስፈልገው ገንዘብ በተፈለገው መጠን ካልተገኘ በመጠነኛ ወጪ እንዲሰራ በማሰብ ነው። የስራው ጥራት በዚያው መጠን ሊቀንስ እንደሚችል እያወቅሁ ካለመሰራቱ መሰራቱ ይሻላል በሚልም እምነት ነው። ጥራትስ ቢሆን የሚገኘው በሂደት አይደል? የታሰበውን ስራ መስራት ጀምሮ ፥ ውጤቱን ይፋ አድርጎ ፥ ትችት ሲሰጥበትና በዚያ መሰረት በየዘመኑ የሚጨመረው እየተጨመረበትና የማያስፈልገው እየተቀነሰለት አይደል? የፎክሎር ትምህርትና ምርምር በአ.አ.ዩ. በ1970 እና በ2001 አንድ ነው?

ሁሉንም ነገር በዝርዝር መናገር በዚህ መድረክ የሚዘለቅ አይደለም። ይህንን ያህል ሃሳቤን ካጋራሁ በኋላ አንድ ነጥብ አንስቼ ስለ መዘርዝር የማወሳውን ለጊዜው አበቃለሁ።

«ምን እናድርግ?» ብዬ ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸው ተግባራት ይከናወኑ ስል እስካሁን በተለያዩ የአ.አ.ዩ ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ በተለያዩ ግለሰቦች የተደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ሳልዘነጋ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ። ለምሳሌ ፥ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል (ኢ.ቋ.ስ.ክ.) ከተሞከሩት የመዘርዝር ስራዎች መሀከል የሚከተሉትን መጥቀስ አግባብ ነው።

- በ ኢ.ቋ.ስ.ክ. ተማሪዎች የተሰሩ ፥ ግን ደግሞ እስከ ዛሬ ያልታተሙ ፥ የቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (ዲ.ማ.ጽ.) [በፎክሎር፥ ከ9 የማያንሱ ፤ በስነጽሁፍ ፥ ከ74 የማያንሱ ፤ በቋንቋ ጥናትና ትምህርት ፥ ከ11 የማያንሱ ወዘተ.] አሉ።
- የፈቃደ አዘዘ ሙከራዎች ፤ የታተሙና ያልታተሙ አሉ።
- የአቶ ወርቁ ገዳ ሙከራዎች ፤ ያልታተሙ አሉ።

ከእነዚህ ሌላ በ የውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በሚሰጠው የስነጽሑፍ የኤም.ኤ. ፕሮግራም አስተምራቸው ለነበሩ ኮርሶች ፥ ተማሪዎች በተርም ወረቀት መልክ መዘርዝሮች እንዲያዘጋጁ አደርግ ነበር። እነዚህ በእኔ እጅ አሉ።

«የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር» የተሰኘው የኤም.ኤ. ፕሮግራም በኢ.ቋ.ስ.ክ. ውስጥ መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ የፎክሎር መዘርዝሮች

በማዘጋጀት ተማሪዎች ስራውን እንዲለማመዱ ተደርጓል። እነዚህም እኔ ዘንድ አሉ[32]።

አሰባስቦ የማደራጃ ፥ የተደራጀውን በኮምፒውተር የማስተየቢያ ፥ የማስፖረፌያ ፥ የማባዣ ፥ የማስጠረዣና ሌሎች የጽሕፈት መሳሪያዎች መግዢያ ገንዘብ በማያታክት ውጣ ውረድ ቢገኝ እነዚህን እንዳሉ፥ ለጊዜው ብዙም የማጣራት ስራ ሳንሰራ ፥ ቤተመጻሕፍት እንዲገቡ ማድረግ ይቻላል። በመምህሩ ቢሮ ተቀምጠው ነቀዝ ከሚበላቸው ባሉበት መልክ አገልግሎት ላይ ቢውሉ በስነጽሑፍ እና በፎክሎር ምርምር የሚሞሉት ቀዳዳ ብዙ ነው። እነርሱ አገልግሎት እየሰጡ ሳሉ የማጣራቱ ስራ በነቂስ ከተካሄደ በኋላ እንዲታተሙና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ፥ ወደ ምርምር ማእከሎችና በሀገሪቱ ውስጥ እና በውጭ ሀገር ወደሚገኙ የኢትዮጵያ ጥናት ማእከሎችና ቤተመጻሕፍት ፥ ዋጋቸው እየተከፈለ ፥ እንዲሰራጩ ማድረግ ይቻላል።

## 7.3 የኢትዮጵያ የፎክሎር ኢንስቲትዩት

ይህንን ርእስ የምጀምረው ፎክሎር የተለያዩ የትምህርት ክፍሎችን እየማረከ የመምጣቱን አስደሳች ዜና በመግለጽ ነው። የዛሬ 32 ዓመት ለሴሚናር በቀረበ ፎክሎር ነክ ጽሑፍ ላይ ራስ መኮንን አዳራሽ ውስጥ ውይይት ሲደረግ «እንዲህ ዓይነቱ ምርምር ምን ፋይዳ አለው?» ያሉ ሁለት ሶስት ሰዎች ነበሩ። በተለይ አንዱ ተሳታፊ ፥ «ዛሬ በችጋር ላይ ባለንበት ጊዜ የእርሻ ምርምር እንጂ የተረት ምርምር ምን ያደርጋል?» የሚል ዓይነት ጥያቄ ጠይቆ ነበር። ባንድ በኩል ፥ ዛሬም ይህንን የሚሉ እንዳሉ ጥርጥር የለኝም። ባንጻሩ ግን ፥ እመግቢያው ላይ እንደገለጽሁት ኢ.ቋ.ስ.ክ. የፎክሎር ትምህርትን አንድ ኮርስ በመስጠት ጀምሮ ዛሬ የዱክትርና ፕሮግራም ከፍቷል። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማእከል (ELRC) እና የልማት ጥናት ኮሌጅ (CDS) በትብብር ለማኪያሄድ ያቀዱት ባህልን ተቁምነገር የጣፈ ፕሮግራም አለ ሲባል ሰምቻለሁ። «የኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም» (IES) ፥ የትምህርት ኮሌጅ ፥ እና የሥነልሳን ክፍልም (ILS) ከፎክሎር (ባህል) ጋር የተያያዘ የድኅረ ምረቃ ፕሮግራም አላቸው። በስነሰብእ ትምህርት ክፍል የሚከፈት ባህል ነክ ፕሮግራም ሊኖር ይችላል።

ባንድ በኩል ፥ ይኼ ድንገተኛ ጥረትና ርብርቦሽ ለባህል ጥናት መስፋፋት ለጣሩና ዛሬም ለሚጥሩ ሁሉ አስደሳች ነው። በሌላ በኩል ዩኒቨርስቲው ያለውን የሰው

[32] በኢትዮጵያውያን እና በውጭ ሀገር ዜጎች የተሰሩ ሌሎች መዘርዝሮች አሉ። ይሁን እንጂ፥ በየትኛውም ሙያ፥ በመጠቁም የተደገፈ፥ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በሌሎች ሰዎች የተዘጋጀ፥ የተሟላና ሥልጣን ያለው (comprehensive and authoritative የሆነ) መግለጫዊ መዘርዝር እስከዛሬ አላጋጠመኝም፥ ሲነገርለትም አልሰማሁም።

ኃይል ገምተን ስናስብ አንዳንድ ጥያቄዎች አንስተን እንድንመካከር እንገደዳለን፡፡ የዚህን ዝርዝር የተነደፉትን ፕሮግራሞች ቅጂዎች መጀመሪያ አግኝቶ ፥ ከዚያ በኋላ እነርሱን በወጉ አጥንቶ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ እስከዚያው ግን በሕዝባዊ ኢንተርኔት (በወሬ-ወሬ) ያገኘሁትን እና ከየፕሮግራሙ ጋር የቅርብ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጠይቄ የተረዳሁትን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ሃሳብ አቀርባለሁ፡፡ ሃሳቡ ጨርሶ እንግዳ አይደለም፡ በተለያዩ መድረኮች በጽሑፍም በቃልም የተለያዩ ስሞች ይዞ ቀርቧል፡፡ ከሁኔታዎች ጋር እየተለዋወጠ ባለፉት 15 ዓመታት ሲነገር ቆይቷል፡፡

ይሁንታው (the recommendation) «የኢትዮጵያ ፎክሎር ኢንስቲትዩት» (The Ethiopian Folklore Institute) ይቋቋም የሚል ነው፡፡ ለጊዜው «የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ኢንስቲትዩት» (Institute of Ethiopian Languages and Cultures) ቢባል ደግሞ ይበልጥ ይመረጣል ፤ ብዙ ጉዳዮችን ያካትታልና፡፡ ይህንን ኢንስቲትዩት ማቋቋም፡-

- ያለንን የሰው ኃይል አሰባስቦ ትምህርቱንና ምርምሩን አቅዶ፥ በጥራት ለመስራት ይጠቅማል ብዬ አስባለሁ፡፡
- ያለንን የተወሰነ 'ሪሶርስ'ም በአግባቡ የምንገለገልበትን መንገድም ይከፍታል፡፡
- ስለባህልና ልማት ያወሳናቸውን ጉዳዮች በእውቀትና በጥልቀት ለመመርመር የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መሰረት ጣልን ማለትም ይሆናል፡፡

**ለነገሩ ፥ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ፥ የነቃን ዕለት ይህ ኢንስቲትዩት መቋቋሙ አይቀርም-ምናልባትም በደቡብ ኢትዮጵያ !!!!**

# አባሪ 1

## በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተነሱ ሃሳቦች በየጊዜው በተለያዩ መንገዶች በአማርኛ ቋንቋ የተነሱባቸው የጸሓፊው ፎክሎር-ነክ ስራዎች መዘርዝር፤ በዘመን ቅደም-ተከተል

970፤ «የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፍአዊ ኪነተቃል ጥናት»፥ *መጀመሪያ* «የቋንቋ ጉዳይ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት» በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ተዘጋጅቶ ፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፥ መኮንን አዳራሽ ፥ ከሰኔ 22-24/1970 ፥ ለተኪያሄደው ሴሚናር የቀረበ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በስቴንስል እየተባዛ ለተማሪዎች በማስተማሪያነት ሲያገለግል የቆየ እና ፤ በኋላ በ *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ መፅሄት* ፥ ቁ.2 ፥ 1984፡ 1-19 የታተመ፡፡

1973 ፤ «ትውፊት በስነፅሁፍ ውስጥ» ፥ «ትውፊት» በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ተዘጋጅቶ፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፥ ድኅረምረቃ አዳራሽ፥ ከሐምሌ 1-3/1973፥ ለተኪያሄደው ሴሚናር የቀረበ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በስቴንስል እየተባዛ ለተማሪዎች በማስተማሪያነት ሲያገለግል የቆየ እና፤ በኋላ በ *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ መፅሄት* ፥ ቁ.3፥ 1985 ፡ 1-19 የታተመ፡፡

1976 ፤ «የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ስነቃል ጥናት ቅኝት፥ ግምገማና የስነቃል ስብስቦችና ጥናቶች መዘርዝር (Bibliography) » *መጀመሪያ* ጥር 1976 ተዘጋጅቶ ፤ ከዚያ ለሀገር ፍቅር ቴአትር 50ኛ ዓመት በዓል ሲምፖዝየም ፥ ሐምሌ 1977 የቀረበ ፤ ጥናታዊ ፅሁፉ 53 ገፅ ሲሆን ፥ ከዚህ ውስጥ ጥናቱ 42 ገፅ ሲይዝ መዘርዝሩ 11 ገፅ ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ ከመነሻው በስቴንስል የተባዛ ስለነበረ ለተማሪዎች ታድሎ በማስተማሪያነት አገልግሏል፤ ከ1978 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ "ELAM 306 ስነቃል (የማስተማሪያ መጣጥፎች)" በሚል ርእስ፥ በዚሁ ፀሀፊ በተዘጋጀው መድበል ውስጥ ከሌሎች የፀሀፊው መጣጥፎች ጋር አገልግሏል፡፡ ከመጠነኛ እደታ (editing) በኋላ ጥናቱ በ የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የስነፅሁፍ መፅሄት፥ ቁ.6፥ 1988፡ 1-28 ታትሟል፡፡

1988 ፤ «የስነቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ በኢትዮጵያ»፥ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም 8ኛ ሴሚናር የቀረበ፥ *ታኅሣሥ* 10-11/1988፥ አ.አ.ዩ. ባህል ማዕከል፤ ከዚያ በ Ethiopian Journal of Education (የኢትዮጵያ

የትምህርት ጆርናል)፥ ቅፅ XVI፥ ቁ. 2፥ እ.አ.አ. 1996፡54-85 ታትሟል፡፡

1991፤ «በአማርኛ የሚነገሩ የትምህርት ስነቃሎች ዓበይት ይዘቶች» ፥ በ Non-formal Education in Ethiopia: An Overview of the Current Situation. (Proceedings of the National Conference on the Situation of Non-Formal Education in Ethiopia, 12-13 March 1999, Schoool of Graduate Studies Hall, Addis Ababa). Edited by Habtamu Wondimu, Habtegiorgis Berhane, and Wanna Leka. Printed by AAU Printing Press, Addis Ababa, Ethiopia, 1999. ከመጠነኛ እደታ (editing) በኋላ ሰሚ ያጡ ድምፆች በተባለ መጽሐፍ ውስጥ፥ በ1996 ታትሟል፡፡

1991፤ «ወጣቱና ባህል- አንዳንድ ነጥቦች ስለ ፈጠራ ተግባራት»፥ «የባህል ዕድገት ሲምፖዝየም» በሚል ርዕስ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል «የቋንቋ፥ የታሪክና የሶሲዮሎጂ ባለሙያዎች ማኅበር» ላዘጋጀው ጉባኤ የቀረበ ሐምሌ 23-25 1991 ፥ አዋሳ፡፡ ያልታተመ፡፡

1991 ፤ ፈቃደ አዘዘ ፥ <u>የስነቃል መምሪያ</u>፥ መጀመሪያ ጥር 1991፥ በድጋሚ በ1993 ታተመ፡፡

1993፤ «መልካም ዜጎችን ለማፍራት የመገናኛ ብዙኃን፥ የግለሰቦችና የወላጆች ሚና በኢትዮጵያ (ሶስተኛ ረቂቅ)»፤ «ትምህርት ቤቶች ዋነኛ ተልእኳቸው የሆነውን 'መልካም ዜጎች' የማፍራት ተግባር በብቃት እንዲወጡ መወሰድ ስለሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች የሚወያይ አገር አቀፍ ሲምፖዝየም» በሚል ርዕስ ከጥር 30/1993- የካቲት 02/1993 ፥ ለተኪያሄደው የቀረበ ፅሁፍ፤ ትምህርት ሚኒስቴር፥ አዲስ አበባ፡፡

1994፤ «መብትና ግዴታውን የሚያውቅ፥ በመልካም ምግባር የታነፀ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ለማፍራት ቤተሰብ፥ ግለሰብ፥ ማኅበረሰብ፥ ትምህርት ቤቶችና መገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸው ሚና»፥ <u>**The Situation of Child Rights Education in Ethiopia**</u>, በሚል ርእስ ጥር /1994 ለተኪያሄደ ኮንፍራንስ የቀረበ፥ አዲስ አበባ፡፡ በኋላ በ ሰሚ ያጡ ድምፆች ውስጥ፥ 1996፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ ታትሟል፡፡

1995 ፤ «ፎክሎር ምንድን ነው?» ፥ የወጣቶች ፥ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴር በየክልሉ ለሚገኙ የባህል ሠራተኞች ከግንቦት 12-14/1995 ላኪያሄደው ዓውደ ጥናት የቀረበ፥ ናዝሬት፡፡

1995፤ «የስነቃል አሰባሰብ እና አሰናነድ»፥ የወጣቶች፥ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴር በየክልሉ ለሚገኙ የባህል ሠራተኞች ከግንቦት 12-14/1995 ላኪያሄደው ዓውደ ጥናት የቀረበ፥ ናዝሬት።

1996፤ «ቁዘማ፤ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ»፥ «የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር» ባዘጋጀው ፥ የ"ርዕይ 2020" መድረክ ፥ ሰኔ 18 ቀን 1996 ፥ በሂልተን ሆቴል የተደረገ ንግግር፤ በኋላ በ ልሳነ ኢኮኖሚክስ፥ ቅፅ 7፥ ቁ. 2፥ June 2004፥ ገጽ 1-25 የታተመ። የእንግሊዝኛ ትርጉሙ ከገጽ 26-57 ታትሟል።

1996፤ **ሰሚ ያጡ ድምፆች**፥ ብራና ማተሚያ ድርጅት ፥ አዲስ አበባ።

1999፣ «የሲዳማን የተሟላ ታሪክ እና ባህል ለመመዝገብ ፥ ለመቅረስ ፥ ለትውልድ ለማስተላለፍ ፥ ለማጥናት ፥ ለመተንተን እና ለማሳተም ምን ይደረግ?» ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. «የሲዳማ ቋንቋና ባህል ዓመታዊ ሲምፖዝየም» በሚል ርእስ ፥ በሲዳማ ዞን ለተኪያሄደው ጉባኤ ተዘጋጅቶ የተነበበ። ያልታተመ።

2000፤ «አንዳንድ ነጥቦች ስለ ፎክሎር (ስለባህል) ትምህርት፥ ምርምር እና 'የኢትዮጵያ የባህል ጥናት ኢንስቲትዩት' የማቋቋም ፋይዳ»፥ ማኅበራዊ ማንነት፥ ቋንቋ፥ ሥነ ጽሑፍ እና ባህል በሚል ርእስ ተዘጋጅቶ፥ ሰኔ 19 እና 20 ቀን 2001 ለተኪያሄደው፤ ለ 21ኛው የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓመታዊ ጉባኤ ፥ አ.አ.ዩ. የቀረበ። ያልታተመ።

## 2. Author's Folklore Publication in English

"Folklore in Literature: Some aspects of Achebe's use of proverbs in Things Fall Apart and Arrow of God" **Studies and Documents** (A bi-lingual journal published by EACROTANAL, Zanzibar, Tanzania), No. 3, 1982, pp. 1-14.

"A bibliography of Theses on Oral Literature Submitted to the Department of Ethiopian Languages and Literature. Addis Ababa University". **Journal of Ethiopian Languages and Literature**. No. 3,1993, pp. 48-60.

**Unheard voices: drought, famine and God in Ethiopian Oral poetry**. Addis Ababa University Press and Norwegian University of Science and Technology, Addis Ababa, 1998.

"The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospects". A paper presented to the **Plenary Session** of XIV **International Conference of**

**Ethiopian Studies**, November 6-11, 2000, Addis Ababa, Ethiopia. Published in **Journal of Ethiopian Studies**. Vol. XXXIV, No. 1, Special Issue, June 2001, pp. 43-85, in English.

"Mengistulore: oral literatures depicting the man, his regime, officials and proclamations." A paper presented to the workshop on THE VIEW FROM BELOW; DEMOCRATIZATION AND GOVERNANCE IN ETHIOPIA. GEYON HOTEL. 24-25 JANUARY 2000. In Bahur Zewde and Pausewang, Sigfried, ed., **Ethiopia, the challenge of democracy from below**. Published by Nordisk Afrikanistitutet, Uppsala and Forum for Social Studies, Addis Ababa. Printed in Sweden by Elanders Gotab, Stockholm, 2002.

"The Possible Role of Folklore Studies in the Research Programme: Well-being in Developing Countries-WeD (Discussion Notes)". Presented at the Workshop held on March 1 / 2003, at Semen Hotel, Addis Ababa, Ethiopia. Posted on: **<http://www.wedethiopia.org/docs/FEKADE.pdf>,** and later edited and printed as "Folklore in development: a bird's eye view of perceptions of poverty and wealth in Amharic proverbs". In *Berritu*. A quarterly magazine published by The National Bank of Ethiopia. No. 100, 2007-2008. Special Issue, pp. 35-47.

# እምነት-ነክ ክብረ በዓላት፣ ባሕላዊ ክንውኖችና የልማት አንድምታቸው

*ፈለቀ ታደለ*

## *መግቢያ**

ይህ አጭር ጽሑፍ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ "ባሕልና ልማት" በሚል አቢይ ርዕስ ሥር በተከታታይ ለሚያዘጋጃቸው ውይይቶች ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ጽሑፉ እምነታዊ በዓላትና ባሕላዊ ክንውኖች የልማት ሂደትን በማራመድ በኩል የሚኖራቸውን አሉታዊና አዎንታዊ ገፅታ ይቃኛል።

ፎረሙ ቀደም ሲል አዘጋጅቷቸው በነበሩት የውይይት መድረኮች ላይ በ"ባሕል"ና "ልማት" ንድፈ ሀሳቦች ዙሪያ ሰፊ ዘገባ መቅረቡና ውይይት መደረጉ የሚታወስ ነው። ስለሆነም ድግግሞሽን ለማስወገድ ሲባል ይህ ጽሑፍ በሁለቱ ንድፈ ሀሳቦች ላይ ዝርዝር ፅንሰ ሀሳባዊ ትንተና ለማቅረብ አይሞክርም።[1] ይሁን እንጂ በቀጣይ ለሚኖረው ውይይት መነሻ እንዲሆን ስለባሕል ምንነት በጥቂቱ ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል።

እ.ኤ.አ. በ2007 የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የባሕል ፖሊሲ እ.ኤ.አ በ1982 የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) ጠቅላላ ጉባኤ ባሕልን አስመልክቶ የደረሰበትን የትርጉም ስምምነት ይቀበላል፡፡ ባሕል የሰው ልጆች የፈጠሩ፣ የሥነ ምግባር፣ የቁሳዊና የሌሎች ቴክኖሎጂ መስተጋብሮች የሚፈጥሩት የሥነ-ማኅበራዊ መገለጫና የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጡሮች የሚለዩበት መሣሪያ መሆኑን ያሰምርበታል። የዩኔስኮው ፍቺ ላይ በመመርኮዝ የኢትዮጵያ የባህል ፖሊሲ ባሕል የሰው ልጆች የሞራል፣ የቴክኖሎጂና የሌሎች የዕውቀት ዘርፎችን መሠረት በማድረግ ራሳቸውን ለማስተማርና ለማሰልጠን ሲሉ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚፈጠር ሂደት መሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም ባሕል የአንድ ማኅበረሰብን የአኗኗር ዘዴ፣ እምነት፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ በአጠቃላይም ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴት በአንድ ላይ አቅፎ የያዘ የማንነት መገለጫ እንደሆነ ይተነትናል።

---

* ይህ ፅሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ መረጃዎችን በማጠናከር በኩል የተባበሩኝን ወ/ሮ ስምረት አልታዬን፣ ወ/ት ጥሩወርቅ ገ/ዮሐንስን፣ አቶ ሳሙኤል ሉሌንና አቶ በቀለ ኃይሌን አመሰግናለሁ።

[1] የራስወርቅ አድማሴ፣ "ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፦ ፅንሰ ሀሳቦች ፣ ፍችዎችና ትስስር" በሚል ርዕስ በባሕልና ልማት የውይይት መድረክ መጀመሪያ ላይ በ2002 ዓ.ም. ያቀረቡትን በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ተሻሽሎ «ባሕልና ልማት፦ ምንነታቸውና ትስስራቸው» የሚል ርእስ ይዞ ከገጽ 1-25 የተካተተውን ይመልከቱ።

ከዚህም በላይ ፖሊሲው ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔርና ብሔረሰቦች መኖሪያ እንደመሆኗ መጠን "ባሕል" ስንል የእነዚህን የኅብረተሰብ ስብስቦች የኑሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የሞራል፣ የሃይማኖትና የሥነልቦና ክንውን ውጤት መሆኑን ያስገነዝበናል:: አያይዞም ባሕል የእነዚህ ብሔር ፣ ብሔረሰቦች ቋንቋ፣ ታሪክ፣ አፈ-ታሪክ፣ የቤት አሠራር፣ የምርት አመራረት፣ የምግብ አመጋገብ ሥርዓት፣ የአለባበስ ሥርዓት፣ የሃይማኖትና የእምነት ክንውን፣ የሥነልቦናና የሥነምግባር ሁኔታዎችን ሁሉ በአንድ ላይ ያካተተ እንደሆነ ያስረዳል:: ከዚህም በላይ ከልደት፣ ከሠርግ፣ ከሞት ጋር የተያያዙ የበዓል አከባበር ሥርዓቶች፣ የዘመድ፣ የጉርብትና፣ የባህላዊ አስተዳደር በአጠቃላይ የባሕል መገለጫዎች እንደሆኑ ይገልፃል:: (FDRE 2007, 3-10):: በዚህም መሠረት የእምነት በዓላትና ክንውኖች የባሕል መገለጫ ንዑስ ፈርጦች መሆናቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል:: ይህ እንግዲህ አንድ ማኅበረሰብ የኑሮውን የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የአስተሳሰብ ዘይቤና የማንነት መገለጫ ለማረጋገጥ የሚያደርገውን የውል የለውጥ ሂደት ወይም ሁለንተናዊ ዕድገት በመወሰን በኩል የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያሳያል:: በሌላ አገላለፅ የአንድ ማህበረሰብ ዕድገትና ለውጥ ባሕልን በተለይም ደግሞ ቋንቋን፣ ሙዚቃንና እምነት ነክ ሥርዓቶችንና ማኅበራዊ ክንውኖችን ማዕከላዊ ሳያደርግ ዘለቄታዊና አስተማማኝ ለውጥና የለውጥ ሥርዓት ሊፈጥር አይችልም::

በሌላ በኩል ይህ ጽሑፍ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጤነው "ልማትን" ሲሆን፣ ይኸውም ጽንሰ ሀሳብ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ እየታወቀ እንደመጣና ሲደረግ የቆየው የዕድገት ትልምና መርሐ ግብር (በአብዛኛው እንደ ኢትዮጵያ ያሉትን የአፍሪካ አገሮችን ጨምሮ) የኢኮኖሚ ዕድገትን ትኩረት በመስጠት፤ ባሕልን በተለይም ደግሞ መንፈሳዊ እሴትንና የማንነት መገለጫን በቅጡ ያላገናዘበና፣ አልፎ ተርፎም የባሕል ተቋማትንና ዕሴቶችን በመጫን የኢኮኖሚና ቁሳዊ መሠረት አውታሮችን የማስፋፋት ሂደት ሆኖ ቆይቶ ነበር:: ይህም ዘላቂ የአስተሳሰብ ለውጥና የባለቤትነት ስሜትን በተለይ በመልማት ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ሊፈጥር አልቻለም:: (Ellis and ter Haar 2004, 1):

ከዚህም ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ነው ይህ ጽሑፍ በአገራችን በተለይም ከ45 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ተከታይ ምዕመናን ያላትን የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የእምነት በዓላትና ባሕላዊ ክንውኖችን መሰረት አድርጐ እነዚህን ባህላዊ ልምዶችንና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቃኘት በልማት ላይ የሚኖራቸውን አንድምታ ለመዳሰስ የሚሞክረው::

ይህንን የጽሑሁፍ ማስታወሻ ለማዘጋጀት አቅራቢው የሃይማኖት መምህራንንና ምዕመናንን አማክሯል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በሌሎች ባለሙያዎች የተዘጋጁ ሰነዶችንና መጣጥፎችን ቃኝቷል:: ከዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የመስክ የሥራ ልምድና የልማት አመራር ተሳትፎም አኳያ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ በዓላትን በመከታተል የራሱን ግንዛቤ ግምት ውስጥ አስገብቷል:: ይሁን እንጂ አብዛኛው የመስክ ጉብኝት የተደረገው በአማራ

ብሔራዊ ክልል ውስጥ፣ ሰሜን ወሎና ምስራቅ ጎጃም አካባቢ ስለሆነ የመስክ መረጃዎቹ ብሔራዊ ገጽታውን አያሳዩ ይሆናል፡፡ የሚሰጠውም ትንታኔ እንደዚሁ በሌሎች ክልሎች እየተከናወኑ ያሉ ክንውኖችን በተሟላ መልኩ ስለማያካትት ብሔራዊና ወጥ የሆነ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጂ ወደፊት በዚህ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች እርሾ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህ ጽሑፍ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል የታቦት አከባበር ሥርዓትና ባህላዊ ልማዶች ለልማት የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ይመለከታል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ የበዓላት አከባበር ሥርዓትና የሥራ ባሕል እነዚህም በልማት ላይ የሚኖራቸውን አንድምታ ያቀርባል፡፡ በሦስተኛው ክፍል፣ ከሰው ሕይወት እልፈት በኋላ የሚደረጉ ክንውኖችንና ድግሶችን፣ እነሱም በልማት ሂደት ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ይቃኛል፡፡ በመጨረሻም በአገራችን ባሕልን መሠረት ያደረገ የልማት ስልት እንዲፈጠር ከማድረግ አኳያ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ የዚህ ጥናት ግኝቶችን ይጠቁማል፡፡

እንደተገለፀው፣ የጽሑፉ ትኩረት ልማትን ከእምነት ነክ በዓላትና የአከባበር ሥርዓቶች አኳያ መቃኘት በመሆኑ አወዛጋቢ አስተያየቶች ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ስለሆነም፣ በጽሑፉ የቀረቡት ሀሳቦች በሙሉ ከቀና መንፈስ የመነጩ እንጂ የአንዱን እምነት ለማሞገስም ሆነ ለሟንኳሰስ ወይም ከሌላ ድብቅ ፍላጐት ጋር የተገናኙ እንዳልሆኑ ታዳሚዎችም ሆኑ አንባቢዎች እንዲረዱት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የተፈጸሙ ግጽፈቶች ካሉ በቅድሚያ አቅራቢው ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በዚህ አጭር ጽሑፍ ወደ ርዕሱ በጥልቀት መግባት ስለሚያስቸግር መድረኩ በሚያካሂዳቸው ውይይቶች በጽሑፉ የቀረቡት አንድ አን ድ ሃሣቦች ጠቃሚ እንደሚሆኑ እምነት አለኝ ፡፡

## 1. የታቦት በዓላትና ክንውኖች የልማት አንድምታዎች

የታቦት በዓላትና ባህላዊ ክንውኖች ከልማት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከመቃኘታችን በፊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት አኳያ የታቦት ሥርዓትን ታሪካዊ አመጣጥ ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም አገራችን ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ በፊት በብሉይ ኪዳን እምነት ማእቀፍ ውስጥ አምልኮተ እግዚአብሄር የምትፈጽም ሀገር እንደነበረች የቤተክርስቲያንን ትውፊቶችና ሰነዶች ይጠቁማሉ፡፡ የብሉይ ኪዳን እምነት ወደ አገራችን መግባት የጀመረውም ከክርስቶስ ልደት በፊት ዘጠኝ መቶ አመት ዓመት አካባቢ ንግስተ ሳባ በኢየሩሳሌም ጉብኝት አድርጋና ከንጉሥ ሰለሞን ጋርም ተወያይታ ከተመለሰች በኋላ መሆኑ ይነገራል፡፡ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን “ጅውዶ-ክርስቲያን” ማለትም ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የተሸጋገረ ህዝብ ቤተክርስቲያን ተብላ እንደምትታወቅ በቅርቡ በኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተዘጋጀ ፅሁፍ ያስረዳል (ኢ.ኦ.ቤ.፤ 2000 ዓ.ም፣ ገጽ ፲፬ ይመለከቷል፡፡)

የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ደግሞ በመጀመሪያው መቶ ዓመተ ምህረት በንግስት ህንደኬ ጃንደረባ መሆኑ ይታመናል፡፡ (ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ይመለከቷል)፡፡ ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያኗ በመንበረ ቅድስና ደረጃ ተደራጅታ ህልውናዋን በተሟላ መልኩ መምራት የጀመረችው ግን ዘግይታ በ4ኛው መቶ ዓመተ ምህረት ነው፡፡ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጳጳስም በኋላ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የተባሉት ቅዱስ አባት ፍሬምናጦስ ነበሩ፡፡ ጵጵስና የተጀመረውም በእስክንድርያው ቅዱስ ፓትሪያርክ አትናቴዎስ እንደነበር ድርሳናት ይጠቁማሉ፡፡

በኋላም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከ1921 ዓ.ም ጀምሮ በራስዋ ጳጳሳት ከዚያም ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ በራስዋ ቅዱስ ፓትሪያርክ በመመራት፣ ራስዋን በራስዋ ስታስተዳድር የቆየች ሲሆን ተከታዮቿም የቤተክርስቲያኗን በዓላትና ቀደም ሲል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የታቦት አከባበር ሥርዓት እየተከተሉ እስከአሁን ደርሰዋል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የ2000 ዓ.ም እትም፣ ቤተክርስቲያኗ 54 አገረ ስብከት፣ 59 ሊቃነ ጳጳሳት፣ 500,000 ካህናት፣ 40,000 የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት፣ እንዲሁም 45 ሚሊዮን ተከታዮች (ምዕመናን) እንዳሏት ይገመታል፡፡ (ኢ.ኦ.ቤ፣2000 ዓ.ም፣ ገጽ pxii፣)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ታቦተ ጽዮን ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ታቦታት እስከ ዛሬ ድረስ የአምልኮ መፈፀሚያ በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ይህም የኦሪት እምነት ከክርስትና በፊት በኢትዮጵያ እንደገባና የታቦት አከባበር ሥርዓት በአገራችን ተስፋፍቶ እንዲቆይ አስተዋጽኦ ማድረጉን ይጠቁማል፡፡ የታቦት አከባበር ሥርዓት ቤተክርስቲያኒቱ በዓለም መድረክ ልዩ ቦታና ግምት እንዲሰጣት አድርጓል፡፡ በተለይም ደግሞ የኦርቶዶክስ እምነት በሚያከብሩና ሲያከብሩ በቆዩ ጥንታዊና ምስራቃዊ አገሮች ዘንድ ለአብነትም ያህል በሩሲያ፣በጆርጅያ፣ በሰርቢያ፣በቡልጋሪያ፣ በሩማንያ፣ በግብፅ፣ በሶሪያ፣ በአርመን፣ በህንድና በእስራኤል በሚኖሩ የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ አግራሞትን እንድትስብና ልዩ ዓለማቀፋዊ ቦታ እንዲኖራት አስችሏል፡፡ ስለዚህም የታቦት አከባበር ድምቅትና ግዝፈት እንደየታቦቶቹ ትውፊትና ገድል የሚለያይ ቢሆንም፣ ታዋቂ የታቦት ቦታዎች የቱሪስት መስህብ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ይህም በበጎ መልኩ ጥቅም እንዲሰጥ ከተደረገ የአገራችንን ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማጠናከር በኩል የሚጫወተው ሚና የጐላ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለቱሪስት መስህብነት በማገልገል ላይ ያሉትን እና ወደፊት ሊያገለግሉ ይችላሉ የሚባሉትን የዐበይት የታቦት ስሞችንና የታላላቅ ክብረ በዓላት ቦታዎችን በወራት በመለየት በሠንጠረዥ 1 አቅርቤዋለሁ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- የታቦት ስሞችና መከበሪያ ቦታዎች በወርና በቀን

| ወር | ቀን | የታቦት ስም | ዋና መከበሪያ ቦታው |
|---|---|---|---|
| መስከረም | 1 | ዮሐንስ | ሸንኮራ |
| መስከረም | 10 | ፀደንጻ ማርያም | ቡራዩ |
| መስከረም | 16-17 | ደመራ/መስቀል | በአዲስ አበባና መላው አገሪቱ |
| መስከረም | 21 | ማርያም | ግሸን |
| ጥቅምት | 5 | አቦ | ዝቋላ |
| ጥቅምት | 27 | መድኃኒዓለም | በመላው ኢትዮጵያ፣ (አዲስ አበባ ቀጨኔ ይደምቃል) |
| ጥቅምት | 30 | ማርቆስ | 6 ኪሎ፣ አዲስ አበባ |
| ህዳር | 6 | ማርያም | ቁስቋም (ሽሮ ሜዳ አዲስ አበባ) |
| ህዳር | 12 | ሚካኤል | ዋሻሚካኤል (ጎሐፅዮን) - ኦሮሚያ-ሸዋ |
| ህዳር | 21 | ማርያም | አክሱም ፅዮን - ትግራይ |
| ህዳር | 24 | ተ/ሃይማኖት | ደብረሊባኖስ - ኦሮሚያ |
| ታህሣሥ | 1 | ኤልያስ | እንጦጦ አዲስ አበባ - ሸዋ |
| ታህሣሥ | 3 | በአታ ማርያም | ግቢ ገብርኤል፣አዲስ አበባ (እንዲሁም /የረር በአታ) |
| ታህሣሥ | 19 | ገብርኤል | ቁልቢ - -ሐረርጌ፣ኦሮሚያ |
| ታህሣሥ | 24 | ተ/ሃይማኖት | እቲሳ (ሰንዳፋ) ኦሮሚያ |
| ታህሣሥ | 29 | ልደታ | ላሊበላ - አማራ ክልል |
| ጥር | 1 | እስጢፋኖስ | አዲስ አበባ (መስቀል አደባባይ) |
| ጥር | 4 | ዮሐንስ ወ/ነጎድጓድ | አዲስ አበባ - ጉለሌ |
| ጥር | 10 | ከተራ | በመላው ኢትዮጵያ |
| ጥር | 11 | ጥምቀት | በመላው አገሪቱ፣ (ጎንደር ይደምቃል) |
| ጥር | 12 | ቃናዘገሊላ | ጎንደር |
| ጥር | 24 | ተ/ሃይማኖት | ደ/ሊባኖስ - ኦሮሚያ |
| የካቲት | 16 | ኪዳነምህረት | እንጦጦ፣ አዲስ አበባ |
| ሰኔ | 12 | ሚካኤል | ዋሻ ሚካኤል (ጎሐፅዮን) - ሸዋ፣ ኦሮሚያ |
| ሰኔ | 13 | ዮሐንስ መጥምቁ | ሸንኮራ - ሸዋ፣ አማራ ክልል |
| ሐምሌ | 5 | ጴጥሮስ ወ/ጳውሎስ | አዲስ አበባ፣ ጉለሌ |
| ሐምሌ | 7 | ሥላሴ | 4 ኪሎ ካቴድራል፣ አዲስ አበባ |
| ሐምሌ | 19 | ገብርኤል | ቁልቢ - ኦሮሚያ፣ ሐረርጌ |
| ነሐሴ | 16 | ፍልሰታ (ኪዳነምህረት) | በመላው አገሪቱ |
| ነሐሴ | 24 | ተ/ሃይማኖት | ደብረሊባኖስ - ሸዋ፣ ኦሮሚያ |

(ምንጭ፣ በአቅራቢው የተጠናቀረ፣ 2002 ዓ.ም.)

ከላይ የተገለፁት አበይት የክብረ በዓላትና የታቦት ቦታዎች ለአብነት ያህል ተጠቀሱ እንጂ የእምነቱ ተከታይ በሆኑ ምዕመናን ዘንድ በየቀበሌውና

በየአጥቢያው በሚገኙ በርካታ ቤተክርስቲያናት ውስጥ የሚከበሩ መሆናቸው እሙን ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት አበይት የታቦት ቦታዎች የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ቢያንስ በከተማ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው ወደ 7 ሚሊዮን የሚጠጋውን የሕዝብ ብዛት የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ምዕመናን የተለያዩ የክልል ከተሞችንና የገጠር ቀበሌዎችን አቆራርጠው ረጅም መንፈሳዊ ጉዞ አድርገው የሚያከብሯቸው ክብረ በዓላት ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የዝቋላ አቦን የታቦት አከባበር አስመልክቶ ቦታው ከመንፈሳዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ መልክአ ምድራዊ አቀማመጡና ዘርፈ ብዙ ባህላዊ እሴቱ ከፍተኛ መሆኑን አንድ ጥናት እንዲህ ይገልፀዋል:-

> ሰፊ የማኅበረሰብ ክፍልን የሚወክሉ ምዕመናን ገና ከዋዜማው በዓሉን ለመታደም መጥተው ነበር:: አብዛኞቹ ከአዲስ አበባና ተጓዳኝ ከተሞች እንደዚሁም በርቀት ከሚገኙ እንደ መቀሌ ካሉ ከተሞች የመጡ ምዕመናን ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በአካባቢው የሚኖሩ የገጠር ነዋሪዎችና የተቀሩትም አርሶ አደሮች ከቢሾፍቱ፣ አዳማና፣ አርሲ አካባቢ የመጡ ነበሩ፡፡ እንዲሁም ከሌሎች ከተማዎች (በአሁኑ አጠራር ከኦሮሚያ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከአማራ፣ ከትግራይና ከደቡብ ክልሎች) የመጡ ምዕመናን እንደሆኑና በበዓሉ ላይ የእስልምናና የባሕላዊ እምነት ተከታዮችም እንደተገኙ እኚሁ ፀሐፊ አውስተዋል፡፡ አብዛኞቹ በአውቶቡስ በተለይም ደግሞ ሎንችና ተብለው በሚታወቁት መለስተኛ የህዝብ ማመላሻዎች እየተጫኑ የመጡ ሲሆን ተሽከርካሪዎቹ ከቢሾፍቱ ጀምሮ እስከ ዝቋላ ተራራ መዳረሻ ድረስ ያለውን ጥርጊያ መንገድ አቋርጠው፣ አዋራውን እያጨሱ ሲሽከረከሩ ማየት ድባብ የሚሰጥ ነበር" ብለዋል፡፡ (Generre ፣ እ.ኤ.አ 1991)

በላሊበላ እንደዚሁ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚጎርፉ ምዕመናንና ቱሪስቶች በአጠቃላይ በግምት በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ምዕመናን በየዓመቱ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ያከብሩታል፡፡ የዓለም መድኃኒት (ቤዛ ለኩሉ) ተብሎ በሚጠራው አከባበር፣ ከ11ዱ የውቅር አብያተ ክርስትያናት አንዱ በሆነው በቤተ ማርያም ካህናቱ ለሁለት ተከፍለውና በማማው ዙሪያ በጋራውና በተዳፋቱ ቦታ ላይ በመሆን ያሸበሽባሉ፡፡ "ያለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ" እያሉ እየዘመሩ ምልክት እየተቀበሉ ያከብሩታል፡፡ በተለይም ደግሞ ኢየሩሳሌም ተጉዞ የተመለሰው ንጉሥ "ዳግማዊት ኢየሩሳሌም፤ ሁለተኛዋ የአዲሱ ትውልድ ቦታ" ብሎ የሰየማትን ላሊበላን ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ወደ እየሩሳሌም ሳይሄዱ እዚሁ ባገራቸው ሆነው የልደቱን በዓል ማክበር እንዲችሉ የውቅር አብያተ ክርስቲያናቱን እንደሰራና ይህም በድምቀት እንዲከበር አስተዋፅኦ ማድረጉ ይገለፃል፡፡

ሌላው በቅርቡ እድሉን አግኝቼ ከቁልቢ ገብርኤል የንግሥ በዓልን አክብረው ሲመለሱ ያነጋገርኳቸው አንድ በዕድሜ የገፉ አባት እንዳጫወቱኝ "በበዓሉ እንደ እኔ ዓይነት ሥጋ ወደሙን የወሰዱ (ወንዶችም፣ ሴቶችም) በቁልቢ ገብርኤል በዓል ተገኝተው መንፈሳዊ በዓሉን ያከብራሉ፡፡ የከተሜውን ሕዝብ ያህል፣ የገጠሩ ነዋሪም በበዓሉ ላይ ይገኛል፡፡ አሁን፣ አሁንማ በሀብት የበለፀገም

በዕድሜ ለጋ የሆነውም ዘመናዊ ወጣት ሁሉ አቅም ያለው በአይሮፕላን ወይም በግሉ መኪና፣ የቀረው በህዝብ ትራንስፖርት ተሳፍሮ፣ በመስክና በድንኳን፣ እንዲሁም በሆቴል እያረፉ ሲፀልይ፣ ስለት ሲያደርስ፣ ዝክር ሲያበላ ባህሉን ሲጫወትና ታቦት ሲያጅብ ይውላል። መቼም ላላየው ለመገመት የሚያስቸግር ነው ነበር" ያሉኝ። ታዲያ ይህ አይነት የታዋቂ ታቦት አከባበር ሥርዓት ከመንፈሳዊ ጠቀሜታው ባሻገር ቱሪዝምን በማስፋፋት፣ የማኅበራዊ መረዳዳት ሥርዓትን በማጐልበት፣ የተፈጥሮ ሀብትን በመንከባበክብና በሌሎች የልማት ዘርፎች ላይ ምን አንድምታ ሊኖረው ይችላል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

በሚቀጥለው የጽሑፍ ክፍል የታቦት መከበሪያ ቦታዎች መሠረታዊ የመንፈሳዊ ጉዞ ዓላማቸውን ሳይስቱ አጋጣሚውን በመጠቀም ለማኅበራዊ እድገት፣ ለልማት እና ለበጐ ተግባር እንዴት ማዋል እንደሚቻል ሀሳብ ያቀርባል።

### *ሀ) የታዋቂ ታቦታት ክብረ በዓላት ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ያላቸው አስተዋጽዖ*

ሃይማኖታዊ ተቋማት ለቱሪዝም መስህብ በመሆን የመጀመሪያዎቹ ምንጮች መሆናቸው በታሪክ ይታወቃል። ለምሳሌ እንደ እንግሊዝ፣ ጣሊያን፣ ግሪክና ስፔን በመሳሰሉ የአውሮፓ አገሮች ከኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን በፊት የቱሪዝም እንቅስቃሴ ይዘወተር የነበረው ምዕመናን ወደ ሃይማኖት ቦታዎች በሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህንንም እንደ መነሻ በመውሰድ በ19ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመናት የሕዝብ ቱሪዝም መስፋፋት እንዲችል አስተዋፅኦ እንዳደረገና ከእምነት ቦታዎች ባሻገር የተፈጥሮ መስህብን፣ የታሪክ ቅርሶችንና የኢኮኖሚ አውታሮችን ማዕከል ያደረገ የቱሪዝም ዘርፍ በብዛትና በዓይነት እንዲስፋፋ መሠረት ጥሏል። ከመገናኛ አውታሮችና ከትራንስፖርት አገልግሎት መሻሻል ጋር ተዳምሮም፣ የቱሪዝም ባሕል በስፋት በእነዚህ አገሮች በመዳበሩ፣ ከብሔራዊ ደረጃ አልፈው ዜጐቻቸው ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ሊሆኑ ችለዋል። ወደ አገራቸውም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቱሪስቶች ለመጐብኘት ሲሄዱ ይስተዋላል። (Bharia 2004 እ.ኤ.አ)

ይህ ደግሞ ቢያንስ 7 ሚሊዮን ለሚጠጉትና በከተማ ይኖራሉ ተብሎ ለሚገመቱት ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ምዕመናንና ቤተሰቦቻቸውን የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ጉዞ መነሻ በማድረግ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ለማስፋፋት የተጠቀሱትን ተስፋን የሚሰጥ ይሆናል። ከዚህም በላይ ቀደም ሲል በመግቢያው ተጠቅሶ የነበረውን የቤተክርስቲያን ልዩና ብርቅዬ ቦታዎች ትኩረት በመስጠት ዓለማቀፋዊ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ዕድል እንደሚፈነጥቅ በተለያየ ወቅት አገራችንን ለመጐብኘት የመጡ የውጪ አገር ዜጐች የሚገልፁት ነው።

ለአብነት ያህል፣ የዝቋላ አቦን ክብረ በዓል የታደሙ የውጪ ዜጎችም አድናቆታቸውን ከመግለጻቸውም በላይ በዓሉ ዓለም አቀፍ ባህሪይ ሊኖረው እንደሚችል እንዲህ ዘግበውታል።

የዝቋላ አቦ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓለ-ሲመት በሶሪያ ከቅድመ ክርስቲያን ዘመን በፊት የአቲራት አምላክን ለማክበር ይደረግ ከነበረውን በዓል ጋር ይመሳሰላል:: የአቲርጋቲስ መታሰቢያ ከተራራው ጫፍ ለአይን ማራኪ በሆነ ቦታ የሚገኝና ለአሳ መራቢያ የተስማማ ሐይቅ የሚገኝበት ቅዱስ ቦታ ነበር፡፡ እንደ ዝቋላ ሁሉ በዓሉ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበር ነበር፡፡ ምናልባትም ከሶሪያ በመጡ ዘጠኙ ቅዱሳን አማካይነት ኢትዮጵያ ክርስትናን ተቀብላ ይሆናል፤ ተብሎ ሲነገር የቆየውን አስተሳሰብ የሚመሰክር በዓልና ቦታ ይሆን? የሚያሰኝ ነው"፡፡ (Boll 1991 እ.ኤ.አ.)

***

ዝቋላን በጥሞና ስመለከታት በእሳተ ጎሞራ የተፈጥሮ ሐይቅ ተከባ የቅዱሳን በዓል የሚከበርባትን በጣልያን በደቡብ የሮም ግዛት የምትገኘውን የእኛኑ አሚ በምትባል የምትታወቀውን ቅዱስ ሥፍራ ያስታውሰኛል ፡፡ (Generre፣ 1991 እ.ኤ.አ)

እነዚህ ለአብነት ያህል ይጠቀሱ እንጂ ላሊበላን፣ ጎንደርን፣ አክሱም ፅዮንን፣ አቡነ አረጋዊን፣ ግሸንን፣ ቁልቢንና ደብረሊባኖስን ተመልክቶ በቤተክህነት ኪነጥበባዊ ሥራ፣ በተፈጥሮ አቀማመጣቸው የማይደመም ዓለም አቀፍ ጎብኚ ይኖራል ማለት ያስቸግራል፡፡ ታዲያ እነዚህ ቅዱስ ቦታዎች ሊኖራቸው የሚችለውን ዓለማቀፋዊ ዝናን ግምት ውስጥ በማስገባት ምን ያህል ዓለምአቀፍ ቱሪስቶችን ለማፍራት የጋራ ጥረት አድርገናል? እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ አለኝታ ተቋማት፣ በውጪ ከሚገኙ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች ጋር በመተባበር ምን ያህል የተቀናጀ የቱሪዝም ማስፋፊያና ማበረታቻ ሥራ ሠርተዋል? እነዚህን መንፈሳዊ የታቦት አከባበር በዓላት ለቱሪስት ልማት ለማዋል አጋጣሚውን በመጠቀም ምን ያህል አስተምረዋል? በእምነት ቦታዎቻቸው መታወቅ የተነሳ በዓመት ብዙ ሚሊዮን የሀጂ ተጓዥዎችን ከሚያስተናግዱት እንደ መካ መዲና ወይንም የቅዱስ ከተማ ተብላ ከምትታወቀው እንደ እየሩሳሌም ካሉ ከተሞች ምን ለመማር ችለናል? እነዚህ ጥያቄዎች ሊነሱና ምላሽ ሊሰጣቸው የተገባ ነው፡፡ በጣም ዘርፈ ብዙ የሆነ የቱሪዝም ማስፋፊያ ፣ ማበረታቻና ማጠናከሪያ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባ ግን መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ አገሪቱ የወጠነችው ብሔራዊ የቱሪዝም ማስፋፍያ ዕቅድ መልካም መነሻ ሲሆን የታቦት በዓላትንና የመንፈሳዊ ጉዞ ሁኔታዎችን ለቱሪዝም ለማዋል ይቻል ዘንድ ቀጣይ ጥናት ተደርጎ፣ መርሐ ግብር ተቀርፆና በበጀት ተደግፎ ሊሰራ የሚገባ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል፡፡

### *ለ) ለማኅበራዊና ኢኮኖሚ አውታሮች መስፋፋት የሚኖረው አስተዋፅዖ*

ከላይ እንደተገለፀው የታዋቂ ታቦት መከበሪያ በታዎችና በዓላቱ የበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን፣ ከተሞችንና የገጠር ቀበሌዎችን የሚሸፍኑ በመሆኑ የመንፈሳዊ ጉዞ መረብ ተጓዳኝ የሆኑ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲስፋፉ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ምግብ ቤቶች፣

ሆቴል ቤቶች፣ የሸቀጥና የቁሳቁስ ሱቆች፣ የአልባሳት መደብሮችና የጉዞና የስንቅ እቃዎች መሸጫ ቦታዎችን ለማስፋፋት ይረዳል:: በተጓዳኝም አቅሙ ላላቸው ተጓገሮች እግረ መንገዳቸውን ሌሎች የቱሪስት መስህብና የታሪክ ቦታዎችን ለመጐብኘት ማበረታቻ ዘዴዎች ቢዘጋጁ በየዓመቱ አዳዲስ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን ለመሳብ ከማስቻሉም በላይ የገጠሩም ህዝብ በማህበረሰብ የቱሪዝም ልማት በተሟላ መልኩ እንዲሳተፍ እድል የሚከፍት ነው::

### ሐ) የማኅበራዊ እሴትን ለማዳበርና ለጋራ የልማት መንፈስ ለማነሳሳት የሚኖረው አስተዋጽዖ

ከመንፈሳዊ ገፅታው አኳያ ምዕመናን ወደ እነዚህ ቦታዎች የሚጓዙት በተለያየ መልኩ ራሳቸውን በማደራጀት ነው:: የፅዋ ጠጪዎች፣ የሰፈር ልጆች፣ አብሮ አደጎች፣ የሰንበት ት/ቤቶችና የመ/ቤት ባልደረቦች ወ.ዘ.ተ የሚያደርጉት ጉዞ የእርስ በርስ የመተሳሰብ መንፈስን ከማጠናከሩም በላይ ያለው ለሌለው እንዲያካፍል፣ የታረዙትን እንዲያበላ፣ የተጎዱትን እንዲደጉም ስለሚያደርግ የሚኖረው ማኅበራዊ ካፒታል ከፍተኛ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል:: ይህንንም መሠረት በማድረግ እነዚህ ተቋማት ወይም የህብረተሰብ ስብስቦች ለኢኮኖሚና ለሌሎች የልማት ዘርፎች ዓላማ ለማስፈፀም ዓይነተኛ መሳሪያ ይሆናሉ:: ለምሳሌ፣ በእነዚህ አብያተ-ቤተክርስቲያናት ዙሪያ የአረጋውያን መጦሪያ ማዕከላት፣ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት፣ ት/ቤቶችና ጤና ጣቢያዎች (በእነዚህ ምዕመናን ስብስብና ቀጥተኛ ተሳትፎ) መመሥረትና ማጠናከር ይቻላል:: በተመሳሳይም፣ በእነዚህ የማኅበረሰብ ስብስቦች ተሳትፎ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያቶች እርቃናቸውን የቀሩትን ኮረብቶችና ሸንተረሮች በደን እንዲሸፈኑ ማድረግ ይቻላል::

## 2. አምልኮታዊ በዓላት፣ የባሕል ክንውኖችና የልማት አንድምታቸው

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት ሰጥቶት የቃኘው ሌላው ጉዳይ የአምልኮታዊ በዓላትና የክንውን ሥርዓቶቻቸው የሚኖራቸውን የልማት አንድምታ ነው::

"በዓል" ማለት ይላሉ አቶ ግርማ ዘውዴ የተባሉ ጸሐፊ፣ "አንድ ጻድቅ ወይም ሰማዕት የሚባል ሰው የተወለደበት፣ የሞተበት ወይም ከፍተኛ የሆነ ተዓምር ሥራ አድርጓል የሚባልበትና ስለ ሃይማኖት ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፈለ የተባለበት ዕለት መከበሪያና ይኸው በቤተክርስቲያን መሪዎች ሲታዘዝ የሚፈፀም ድርጊት ነው::" አንድ ሰው እንዲሟላለት የሚፈልገውን ለሚያመልከው ታቦት "አሟላልኝ" ወይም "ያሟላልኛል" ብሎ ፍላጐቱን ሲገልፅ፣ ስለት አገባለሁ ብሎ ሲፈፀምለት ደስታውንና አክብሮቱን የሚገልፅበት ሁኔታ ነው:: (ግርማ ዘወዴ፣ 1985 ዓ/ም፣ ገጽ 63 ይመለከቷል)::

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀኖና በዓልን የማክበር ሥርዓት ሰው ሰራሽ ያልሆነና በሰው ፈቃድና ትዕዛዝ ያልተሰጠ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ቤተክርስቲያን የበዓላት አከባበር በእግዚአብሔር ቃል፤ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ እንደተሰጠና አምልኮታዊ ሥርዓት እንደሆነ ታስረዳለች፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሰነድ፣ በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይም ቁጭ ብሎ መዋልን የወደደ ሰነፍ የፈጠራቸው አይደሉም፡፡ ምንጫቸው ሃይማኖት ነው፡፡ ለዚህም ነው ቤተክርስቲያኗ የበዓላት ቀኖና እና የራሷ የሆነ ሥርዓት በሊቃውንቶቿ አማካይነት በ1976 ዓ.ም. እንዲሁም በ1983 ዓ.ም. ያወጀችው፡፡

ይሁን እንጂ በቅርቡ ተዘጋጅቶ በቀረበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሰነድ እንደተጠቀሰው አብዛኛው ክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን በወረሰው ትውፊት መሠረት በበዓላት ቀን ማናቸውንም ሥራ አይሰራም፡፡ ሌላው ቀርቶ ቅዳሜና እሁድ የተቀዳ ውሃ የማይጠጡ፣ ወንዝ የማይሻገሩና እንዲሁም በእነዚህ ቀናት የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ አሉ፡፡ በበዓላት ቀን ሥር መማስ፣ ቅጠል መበጠስ፣ መጽሐፍ መፃፍና መደጎስ፣ ልብስ ማጠብ በዓል እንደመሻር ይቆጠራል፡፡

ታዲያ በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት የሚታወቁት በዓላት የትኞቹ ናቸው? ለምንስ ይከበራሉ? በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት የጌታ በዓላት ዘጠኝ ናቸው፡፡ እነዚህም "አበይት በዓላት" በመባል የሚታወቁ ሲሆን እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

በቅድሚያ ቤተክርስቲያን ቅዳሜና እሁድን በእኩልነት ታከብራለች፡፡ የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን፣ እሁድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሳበት የጌታ ቀን ተብላ በሐዲስ ኪዳን የነበረች ናት፡፡ በእነዚህ ሁለት ቀናት ምንም እንኳ ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች አከባበር እንደ አይሁድ ሰውን የሚያመንን እንዳይሆን ብታስተምርም፣ ክርስቲያኖችም በእለተ ሰንበት እንደ አይሁድ ሥራ ሳይፈቱና ሳይጠናቀቁ ሰንበትን እንዲያስቡ ዘንድ ብቻ መደንገጓን ትናገራለች፡፡ እረፍትም በፅኑ ደዌ እንደታመመ ሰው አይሁን ብላ ታምናለች፡፡ ነገር ግን በቅዳሜና በእሁድ ቀኖች ቤተክርስቲያን ምዕመናን ወዳጆችዋ እንዲሆኑ ዘንድ በመዓልትና በሌሊት እንዲተጉ ትፈልጋለች፡፡ ሌሎችም አቢይ በዓላት እንደሚከተሉት የሚታሰቡና የሚከበሩ መሆናቸውን ታስተምራለች፡-

**1ኛ. ብሥራት፡-** መጋቢት 29 ቀን ይውላል፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም የአምላክን ከእርሷ መወለድ ያበሠረበት ቀን ነው፡፡ ለሰው ዘር ታላቅ የምሥራች ነውና የምሥራች ቀን ወይም "ብሥራት" ተብሎአል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዘንድ አቢይ በዓል ሆኖ ይከበራል፡፡

**2ኛ. ልደት** ፡- የእግዚአብሄር ልጅ በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር፣ ማለትም ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ የተወለደበት ዕለት ነው። በየዓመቱ ታህሳስ 29 ቀን ይከበራል። በዘመነ ሉቃስ ጳጉሜን 6 ቀን ስለምትሆን ተከታዩ ዘመን፣ በዘመነ ዮሐንስ ፣ ልደት ታህሣሥ 28 ቀን ላይ ይውላል። ይህም የተጀመረው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት በ1298 ዓ.ም. ነው ይባላል።

**3ኛ. ጥምቀት**፡- ክርስቶስ በተወለደ በ 30 ዓመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሯል። በዓለ ጥምቀት የሚከበረውም ጥር 11 ሲሆን፤ በዓሉ ለህዝቡ ትምህርት በመስጠት፣ የጥምቀትን አስፈላጊነትና የንስሐ መግባትን ግዴታ ለማስረዳት የሚከበር ነው። በዓሉ የእርቅ፣ የሰላምና አዲስ የመወለድ መንፈስን በማጠናከር በሕዝቦች መካከል አንድነት እንዲፈጠር ያደርጋል ይባላል።

**4ኛ. ደብረታቦር**፡- በዓሉ ነሐሴ 13 ቀን ይከበራል። ይህ በዓል በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በተለይም በምዕመናን ዘንድ ቡሄ በመባል ይታወቃል። ይህም በዓል በህዝቡ ዘንድ (በተለይ በልጆች በህፃናት ዘንድ) በስፋት ይከበራል።

**5ኛ. ሆሳዕና**፡- ከትንሳኤ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በሚገኘው እሁድ የሚከበር ነው። በአብዛኛው በፀሎት ታስቦ ይውላል።

**6ኛ. ስቅለት**፡- ለዓለም ቤዛ ሊሆን ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለት ነው። በስግደትና በፀሎት በስፋት ይከበራል።

**7ኛ. ትንሳኤ**፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ ቢቀበርም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት፣ ሞትን ድል የነሳበት ቀን ትንሳኤ ይባላል። ይህ መሠረታዊ በዓል በፀሎትና በመታሰቢያ ድግስ ይከበራል።

**8ኛ. ልደት**፡- ጌታ ሙታንን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ 40 ቀን ለሐዋርያት እየተገለፀ ታይቷቸዋል። ትምህርትም አስተምሯል። በዓሉ በቤተክርስቲያን በጸሎትና በማሕሌት ይከበራል።

**9ኛ. ጰራቅሊጦስ**፡- ጌታ በአረገ በ10ኛው፣ በተነሳ በ50ኛው ቀን ለሐዋርያት በነገራቸው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። ጰራቅሊጦስ ማለትም በጎን የሚቆም፣ የሚረዳ፣ የሚያፅናና ማለት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዓሉም በብሉይ ኪዳን ወቅት የእሸት በዓል በሚል ይታወቅ ነበር። ከላይ ከተጠቀሱት ዘጠኝ የጌታ በዓላት ሌላ «ንዑሳን በዓላት» የሚባሉ አሉ። እነሱም፡-

1. መስቀል (መስከረም 17)
2. ስብከት
3. ብርሃን
4. ኖላዊ

5. ግዝረት
6. ልደተ ስምኦንና
7. ቃና ዘገሊላ ናቸው::

10ኛ. <u>የእመቤታችን በዓላት</u፤ ግንቦት 1 ቀን ልደቷ፣ ህዳር 21 ቀን ፅዮን ፣ ጥር 21 ቀን እረፍትዋ፣ ነሐሴ 16 ቀን ፍልሰትዋ፣ ታህሳስ 3 ቀን በአታና ውስተ ቤተ መቅደስ፣ የካቲት 16 ቀን ዳግም የምህረት ቃል ኪዳን የተቀበለችበት ቀኖች ስለሆኑ ይከበራሉ፡፡

11ኛ. <u>የመላእክት በዓላት</u>፤ ህዳር 12ና ሰኔ 12 ቀን በዓለ ሚካኤል ሲሆን፣ ታህሳስ 19 ቀን ዳግም በዓለ ገብርኤል ነው:: እንደነሱም የሌሎች መላእክት በዓላት በስማቸው ቤተክርስቲያን በታነፀበት ቦታ ሁሉ ይከበራል::

12ኛ. <u>የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በዓላት</u>፤ እንዲሁ በዕረፍታቸው ቀን በዓመት አንድ ጊዜ ቤተክርስቲያኖቻቸው በታነፁበት በማህሌትና በቅዳሴ እንዲከበር ቤተክርስቲያን ታዛለች:: ይሁን እንጂ ሕዝቡ ሥራ ፈትቶ እንዲውል የቤተክርስቲያን ቀኖና እንደማያዝ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትገልፃለች::

እንደ ግርማ ዘውዴ ዘገባ ግን ከላይ የተዘረዘሩት 9ኙ የጌታ፣ 33ቱ የማርያም፣ 12 የሐዋርያት፣ 12ቱ (የወሩ) የገብርኤል፣ 12ቱ (የወሩ) የሚካኤል፣ 12ቱ (የወሩ) የመደሃኒዓለም፣ 12ቱ (የወሩ) የባለእግዚአብሔር ሲሆኑ፣ በድምሩ 102 በዓላትና በዓመት ውስጥ 104 ጊዜ የሚውሉት ቅዳሜና እሁድ በዓላት በአጠቃላይ 206 የበዓል ቀናት ይሆናሉ ማለት ነው:: እነዚህም በአላት በዓመት ውስጥ 56 ከመቶ የሚሆነው ጊዜ በዓላትን በማሰብ ብቻ እንዲጠፋ ሊያደርግ እንደሚችል ያስገነዝባሉ:: (ግርማ ዘውዴ፣ ገጽ 66)

## 3. ክብረ በዓላት በሥራ፣ በባሕልና በኢኮኖሚ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ

ከላይ እንደተዘረዘረው በዓላት የህብረተሰቡን የሥራ ባሕል እንደሚጫኑና በተለይም ብዙ አድባራትና ታቦታት በሚገኙባቸው የገጠር ቀበሌዎች የእርሻ ሥራ እንዲስተጓጐል እንደሚያደርጉ ግልጽ ነው፡፡

ለምሳሌ ያለፈው ግማሽ ምዕተ አመት ገደማ ስለ አማራ ብሔር ጥናት ያደረጉት Levine (እ.ኤ.አ.1965፣ ገጽ 67-8) እንደጠቀሱት ገበሬው በሚኖርበት ስፍራ ሁሉ ለአምላኩ ያለው ፅናት ከፍተኛ ነበር:: ከብት ሲታረድ፣ ምግብ ሲቀርብ፣ አዲስ ቤት ሲጀመርና፣ ሲጠናቀቅ ሁሉም ነገር የሚታሰበው በፀሎትና በበዓላት ክብር ብቻ ነበር:: ይህም ለብዙ ድግሶችና ክብረ በዐሎች እንደዚሁም ለእምነታዊ በዓላት መብዛት አስተዋጽኦ አድርጎ ሊሆን ይችላል ብለው ዘግበዋል::

በተመሳሳይ የዛሬ 36 ዓመት ገዳማ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በወቅቱ በ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የኢትዮጵያ ጥናት ሲሚናር ላይ "የባሕል ችግሮች ለልማት" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ዘገባቸው እንደገለጹት 240 የበዓል ቀኖች በዓመት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ (Mesfin W/Mariam እ.ኤ.አ. 1966፣ ገጽ 38-40) ትንንሾቹ ሳይቆጠሩ፣ ትላልቆቹ በራሳቸው በዓመት ውስጥ 125 የሥራ ቀናት ብቻ ለሥራ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለሰርግ፣ ለተዝካር፣ ለለቅሶ የሚውሉትን ቀናት ሳይጨምር ነው፡፡" ብለው ነበር፡፡ ስለሆነም በእነዚህ የበዓል ቀኖች ሥራ ላይ የሚሰማራ የገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ግለሰብ ካለ "በዓል ሰብሮ የከበረ፣ ፆም ፈትቶ የወፈረ" የለም በሚል አስተሳሰብ ማኅበራዊ ተፅዕኖና መገለል ይደርስበት እንደ ነበር፤ አልፎ ተርፎም የመንግስት ህግጋትን እንደመሻር እንደሚቆጠርበት በታሪክ ከነበሩት ነገሥታት ሥርዓት ጋር በማነፃፀር ገልፀውታል፡፡

ለምሳሌ የቤተክርስቲያኒቱ በዓላት ዛሬ በሚታዩበት ቅርፅና ይዘት እንዲከበሩ ያስገደደው አፄ ዘርዓያቆብ (ከ1426-1460 ዓ.ም.) እኤአ ከ1434-1468 እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ንጉሡ ስለበዓላትና ትሩፋት መጻሕፍት በተለይም ታምረ ማርያምን አፅፈው ሕዝቡን እንዲያስተምሩ አስደርገው ነበር፡፡ ይህንንም ያልፈፀመ ከፍተኛ የአካል ቅጣት እንደሚደርስበት ደንግገው ነበር፡፡ ይህ ትዕዛዝም ለአገዛዝ እንዲያመችና ግዛት ለማስፋፋት እንደነበር ይገመታል፡፡ ሌሎችም ነገሥታት እንደዚሁ ህግ ደንግገው ነበር፡፡ ለአብነት ያህልም ንጉሥ ምኒልክም የሚከተለውን አዋጅ እንዳወጡ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም *ዝክረ ነገርን* ዋቢ በማድረግ ባቀረቡት ጥናት ላይ እንዲህ አስታውሰዋል፡፡

> ከዚህ ቀደም ህዝቡ በሰንበትና በበዓል ቀናት ሥራ እንዳይሰራና ይህን አድርጐ ቢገኝ ተግሣፅ እንዲደርስበት ሥርዓት ተበጅቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በበዓላት ቀናት ሕዝቡ በመሥራቱ የእግዜር ቁጣ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰብን መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለዚህ ሰንበትንና ሌሎች የበዓል ቀናትን አስብ፡፡ በእነዚህ ቀናት አትሥራ፡፡ በህዝቡ ሥርዓት መሠረት በበዓል ቀን የሚሰራ ይቀጣል፡፡ ብለው ደንግገው ነበር፡፡ (መስፍን ወልደማርያም እ.ኤ.አ. 1966)

እንደሚታወቀው እንደ ምኒልክ ባሉ የለውጥ ሐዋሪያና የአዲስ ቴክኖሎጂ አስፋፊ መሪዎች እንኳን ይህ ዓይነቱ አዋጅ መታወጁ ሕዝቡ ለሥራ በሚሰጠው ትኩረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲኖረው አድርጓል ለማለት ያስችላል የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶችም ቤተክርስቲያኗ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የፍትሐ ነገሥት አሠራር በታሪክ ሲጫናት እንደቆየና ከፖለቲካው ሥርዓት በተጨማሪ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን የሃይማኖት ጦርነት ጀምሮ ሌሎች ሃይማኖቶች እየበዙ እንዳይሄዱና ሁኔታውን ለመከላከል ሲባል በዓላትን ማብዛትና በጥብቅ ማክበር እንደአማራጭ እንደተወሰደ ይናገራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በ5ኛው ምዓተ ዓመት ገደማ ከሶሪያና ከግሪክ የመጡት ዘጠኙ ቅዱሳን እንዲሁም እስከ 20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ድረስ በተከታታይ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በበላይነት ሲያስተዳድሩ የቆዩት ግብፃውያን ጳጳሳት የበዓላት አከባበር በኢትዮጵያ

ውስጥ እየተስፋፋ እንዲሄድና ይኸውም አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይገምታሉ (ግርማ ዘውዴ፣ 1985 ዓ.ም.፣ ገጽ 65-68 ያመለክታል)::

ይኸም ቀላል በማይባሉና የቤተክርስቲያን እምነት ፀንቶ በሚገኝባቸው የገጠር ክፍሎች ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣና እስከ አሁን ድረስ እንደቆየ ይታወቃል:: ለምሳሌ በሸዋ ተክለሃይማኖትና፣ ዜና ማርቆስ፤ በጐጃም ገብረ መንፈስ ቅዱስና በትግራይ አቡነ አረጋዊ ተዘውትረው የሚከበሩና ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸው በዓላት ሆነው ቆይተዋል::

ከእነዚህ የሃይማኖት በዓላት መብዛትና ሥራ አለመሥራት ጋር ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የመጠጥና የምግብ ግብር ወይም ድግስ ማዘጋጀት ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ምዕመናን የዓመት ጉርሳቸውን ሰውተው ብድር እስከ መግባት እስኪደርሱ ድረስ ድግስ እንደሚደግሱ ተዘግቧል:: ድሮ ድሮማ አዝመራ ተሰብስቦ የተደገሰው እስኪሟጠጥ ድረስ ለ3-4 ቀናት ያህል በድግስ ቤት መከርቸምና መቀለብ የተለመደ እንደነበር ፕሮፌሰር መስፍን በዚሁ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሴሚናር ባቀረቡት ጽሑፍ አስታውሰዋል:: ይህም ለእድገት ሥጋት እንደሆነም ገልፀው ነበር (መስፍን ወ/ማርያም፣ 1966 ዓ.ም.፣ ገጽ 38-41 ያመለክታል)::

ይህ ታዲያ በአንድ በኩል ብዙ በዓላትን ማክበር ወይም ማሰብ፣ ሥራ አለመሥራትን በማበረታታት ለምርት ማነስና ለድህነት እንደሚዳርግ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂቱ ተሰርቶ የተገኘው ጥሪት በበዓላት መብዛት ምክንያት ለድግስ ወጪ በመዋሉ ለበለጠ የኢኮኖሚ ችግር የሚያጋልጥ ሆኖ እንደሚገኝ መረዳት አያስቸግርም:: ይህ ደግሞ "ድህነት ቁምጥና" አይደለም"፤ "ባለጌን ገንዘቡ አይገድለውም" ከሚሉ የህብረተሰብ አስተሳሰቦች ጋር ተዳምሮ የሀብት ሁሉ ምንጭነቱ ሥራ መሆኑ እንዲናቅ ማድረጉ ይታወቃል::

ከሶስት አሰርት ዓመታት በኋላ በተለይም ከሁለት ዓመታት በፊት በአማራ ክልል በእብናት ወረዳ በተደረገ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት 80 ከመቶ የሚሆነው የገጠር ነዋሪ የክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን ቁጥሩም 250,000 እንደሚሆን ተገምቷል:: በወረዳውም 210 አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ሲሆን በአንድ ደብር በአማካይ 952 አማኞች እንዳሉ ቅኝቱ ይጠቁማል:: ለመጥቀስ ያህል፤ ግብፃዊት ማርያም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በቆመችበት ቦታ 1500 ምዕመናንና 21 የቤተክርስቲያን አገልጋዮች (12 ቄሶች፣ 3 ዲያቆናት፣ 4 መዘምራንና 2 መሪጌታዎች) አሉ:: በወረዳውም የሚከተሉት በዓላት ይታሰባሉ፣ ይከበራሉ::

ሠንጠረዥ 2፡- የታዋቂ በዓላት ብዛት በደብር ስም

| ደብር | ታዋቂ በዓላት | ተጨማሪ በዓላት | ድምር | ዓ.ም./ መቶኛ በዓመት |
|---|---|---|---|---|
| ግብፃዊት ማርያም | 125 | 46 | 171 | 1998/ 46.8% |
| ወንበሮች ኪዳነምህረት | 120 | 20 | 142 | 1997/ 38.9% |

በእነዚህ አካባቢዎች በበዓላት ቀናት አረምን፣ እህልን፣ ክምርንና፣ የማገዶ እንጨትን ማጓጓዝ የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ አጥርን ማጠር፣ እንስሳትን መመገብ፣ ውሃ ማጠጣትና ምግብ ዝግጅት በበዓላት ቀናት ይካሄዳሉ፡፡ በሽተኞችንና ዘመድን መጠየቅ፣ የተጣለን ማስታረቅ፣ ንግድ መነገድ፣ ስብሰባ መሳተፍና የእርሻ መገልገያ ዕቃዎችን ማዘጋጀት ይፈቀዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንጨት መቁረጥ፣ እርሻ ማረስ፣ ዘር መዝራት፣ እህል መውቃትና ሰብል መሰብሰብ፣ አረም ማረም፣ አልፎ አልፎም ልብስ ማጠብና፣ የቤት ግንባታ ሥራዎች ማካሄድ የተወገዙ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ እንደአብነት የሚያሳየው ምንም እንኳ የቤተክርስቲያን ቀኖና የበዓላት ቀናት ውስን እንዲሆኑ ቢደነገግም በተግባር ግን፤ ከ39%-47% በሚሆነው የገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ አሁንም በበዓላት መብዛት ምክንያት ለእርሻ ወሳኝ የሆኑት የዘር መዝራት፣ የምርት መሰብሰብና የአረም ማረም ስራዎች ስለሚተጓጎሉ በመርታማነት ላይ አሉታዊ ጫና ይፈጠራል፡፡ ቤተክርስቲያኗም እንደ እድሜዋ ሁሉ በባሕልና በዘልማድ ተግባሮች ውስጥ የምትኖር በመሆኗ ካህናቷ በሙሉ ልባቸው የሚችሉትን ያህል ለማስተማርና የህዝቡን አስተሳሰብ ለመቀየር አልቻሉም፡፡

## 4. የለውጥ ጐዳና

ይሁን እንጂ አንዳንድ ተስፋን የሚጭሩ ለውጦች ግን አልፎ አልፎ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ይስተዋላሉ፡፡ ሰፊና የጎላ ለውጥ ስለመምጣቱ የተሟላ መረጃ ባይኖርም በቅርቡ ለመስክ ስራ ወደ አማራ ክልል ጉባ ላፍቶ፣ መቄትና ግሸን ወረዳዎች ውስጥ ወደሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች በሄድንበት ወቅት ያነጋገርኳቸው የህብረተሰብ ስብስቦች እንዳጫወቱኝ በዓላትን በማሰብና ድግስ በማብዛት የሚደረግ የነበረውን ልምድ፣ ከቤተክርስቲያናት አለቆች ጋር በመመካከር ለመቀነስ እየተሞከረ ነው፡፡ ካህናትም እንደኑሮው ውድነት ባይሆንም ከድሮ የተሻለ የደመወዝ ሥርዓት ስለተዘረጋላቸው በወር ውስጥ ከአራት ያልበለጡ በዓላት እንዲከበሩ እየተደረገ ነው፡፡ እነሱም ቅዱስ ሚካኤል (12)፣ ማርያም (21)፣ ባለእግዚአብሄር (29)ና ሌላ አንድ ተጨማሪ በአል በደብሩ ወይም በጐጡ ታቦት የቀመለት ቅዱስ ወይም ሐዋርያ ቀን ናቸው፡፡ ይህ ልማድ በወረዳ ደረጃ ስለተስፋፋ አባቶቻቸው ከነበሩበት ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ የተሻለ መሆኑን

አጫውተውኛል። ይህ በአርአያነቱ የሚጠቀስና በረጅም ጊዜ ውስጥ ስፊ ቦታን ሊሸፍን የሚችል ተግባር ነው።

የዚህ ዓይነቱ ሕዝብን የማስተማርና የመቀየር ሥራም ኢትዮጵያ የሶሻሊስት ሥርዓትን በምታራምድበት ወቅት በተለይም የባሕል አብዮት ዘመቻ በታወጀበት ዘመን ተሞክሮ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፣ (መስከረም፣ 1976 ዓ.ም.)። ነገር ግን ሥርዓቱ ከመነሻው ሃይማኖትን የማይቀበልና ያመጣው የለውጥ እርምጃዎችም ድጋፍ ስላልነበራቸው በቀጣይነት ሕዝብን ለመለወጥ አልቻለም ነበር። በተቃራኒው፤ በገጠሩ አካባቢ ተከስቶ የነበረው ድርቅና ቸነፈር መንስኤው የእምነት መደፈርና የባሕል አብዮቱ "የሰይጣን ዘመቻ" እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱ ወደምስራቅ ጎጃም ለመስክ ሥራ እግረ መንገዴን ስሄድ ያጫወቱን አርሶአደሮች አውግተውኛል። ለነገሩማ ታዋቂው ደራሲ በአሉ ግርማ "ኦሮማይ" በሚል መፅሐፉ እንደገለፀው በጊዜው የህብረተሰቡ የአስተሳሰብ አድማስ የጠዋት ጤዛ ይመስል፣ የሚቀየረው በዘመቻ፣ በአዋጅና በመፈክር ጋጋታ ተድርጎ ይቆጠር ስለነበር የሕብረተሰቡን ስነልቦና ለማሸነፍና የባለቤትነት ስሜት ለመፍጠር አለመቻሉን ገልፆ ነበር (በዓሉ ግርማ፣ 1984 ዓ.ም. ገጽ 9-10)። ምናልባትም ካለፈው በመማር እንደ ሰሜን ወሎ ባሉ ዞኖች ከማህበረሰብ ስብስቦች ጋር የሚደረጉ ተከታታይ ውይይቶችና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚካሄድ ትምህርት መልካም ተሞክሮዎች ናቸውና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ፤ የዕውቀት ሽግግርና የአመለካከት ለውጥ የሚያስገኝ ትምህርት በርጋታና በጥንቃቄ በረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካቶ ቢሰጥ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል የሚጠቁም ነው።

የበዓላት መብዛትና ከሥራ መቅረት በከተሞች አካባቢ ግን የተለየ ባህርይ ይዞ እናገኘዋለን። ምንም እንኳ በኢትዮጵያ የከተሞች ዕድገት ሂደት አኳያ ከገጠር እየፈለሱ የሚመጡ አዲስ ከተሜዎች የገጠርን ኑሮ ዘይቤና ባሕል ያንፀባርቃሉ ተብሎ ቢገመትም፣ በተግባር ግን የእርሻን ሥራ ከመለወጥ ጀምሮ የበዓል ቀናትን የማብዛትና ከሥራ መቅረት እንዳልተለመደና እንደገጠሩ ቁጥራቸው እንደማይበዛ ይገመታል። ይኸም የከተማ ኑሮና የሥራ ዘርፍ ለውጥ የሥራ ቀናትንና የበዓል ሥርዓትን በመለወጥ ረገድ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ይጠቁማል።

ስለ በዓላት ቀናት መብዛትና የሥራ ባሕል በተለይም በአማራ ክልል ስላለው ሁኔታ ስናወጋ በፍፁም የተለየ ሁኔታ የሚንፀባረቅበትን የአውራ-አምባ ማህበረሰብ ለአብነት ያህል ጠቅሶ ማለፉ ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል። ይህ በአማራ ብሔራዊ ክልል በፎገራ ወረዳ ከወረታ ከተማ በ14ኪ.ሜ ርቀት የሚገኘው ማህበረሰብ 364 ነዋሪዎች (96 የቤተሰብ ኃላፊዎች) የሚኖሩበት ሲሆን (2005 እ.ኤ.አ) በአባላት ዘንድ ምንም ዓይነት የበዓል ቀናት እንደማይከበሩና የሥራ ባሕልም ከፍተኛ ትርጉም እንደሚሰጠው በተጨባጭ የሚታይ ነው። ይሁን እንጂ እምነታቸው በአንድ አምላክ ከክርስትናም ሆነ ከእስልምና እምነት ወጣ ያለ ስለሆነ፣ እንዲህ ዓይነት ለውጥ መሠረታቸው ገጠር በሆነው የኦርቶዶክስ

ቤተክርስቲያን ተከታዮች ዘንድ ለማምጣት ይቻላል የሚለው ጥያቄ ሌላ ዝርዝር ጥናት እንዲካሄድ ሀሳብ የሚፈነጥቅ ጉዳይ ነው፡፡

ለማጠቃለልም፣ በማኅበረሰብ ውይይት ሳቢያ፣ በመደበኛ ትምህርት መስፋፋት ምክንያት፣ ከካህናት የደሞወዝ ሥርዓት መቀረፅ አኳያ፣ በአንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ልዩ ተነሳሽነትና ከሌሎችም የቴክኖሎጂና የመሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር በተያያዘ የበዓላት ቀናት ከድሮው በእጅጉ እየቀነሰ መምጣቱና ለዚህም ተግባር ይውል የነበረው የድግስ ወጪ እየቀነሰ መሄዱን ልናሰምርበት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የእምነት አባቶች፣ የልማት አስተዳዳሪዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 5. ከሕልፈት በኋላ የሚከናወኑ በዓላትና ድግሶች በልማት ላይ የሚኖራቸው አንድምታ

የዚህ ጽሑፍ የመጨረሻ ክፍል የሚያተኩረው ከእምነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚከናወኑ በዓላትን የሚመለከት ሲሆን ይህንኑ አያይዞ የሚደረጉ ድግሶችንና የሚኖራቸውን አንድምታ ይቃኛል፡፡ በተለይም ደግሞ ሰው ሲሞት የሚከናወነውን "ተዝካርና" ድግስ በትኩረት ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡ "ተዝካር" ቃሉ እንደሚያመለክተው (ግሱ ዘከረ፣ አስታወሰ፣ ወይም አሰበ ነው)፡፡ አንድ በሞት የተለየ የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብ አባልን ለማሰብ የሚደረግ ሥርዓት ነው፡፡ ሟቹ በፀሎትና ለስሙ በተዘጋጀ ፀበል ፀዲቅም ይታወሳል፡፡

ሙታንን ማሰብ በአንዳንድ የክርስትና በተለይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ አገሮች በይፋ እንደሚከበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በቅርቡ ለጥቂት አመታት በኖረባት የቀድሞ የሶቪየት ኅብረት ግዛት በነበረችው፣ በጆርጅያ አገር ውስጥ "የሙታን መታሰቢያ" ዕለት በዓመት አንድ ጊዜ በዳግማዊ ትንሳዔ እለት ታስቦ ይውላል፡፡ የሟች ቤተሰቦችና ዘመድ አዝማዶች በመሰባሰብ ወደ ሞተው ሰው መካነ መቃብርና ሐውልት በመሄድ የመቃብሩን አፀድ በማጽዳት፣ መታሰቢያ አበባዎች በማኖርና፣ ማቹ ይወዳቸው የነበሩትን (በአብዛኛው በቤት የተጠመቀ የወይን ጠጅ) የመጠጥ ዓይነቶች በመጠጣት ዕለቱን ያሳልፋሉ፡፡ በመንፈሳቸውም ከሟቹ ነፍስ ጋር እንደሚገናኙ፣ በዕለቱ ማቹ ደስ ብሎት እንደሚውልና ጠባቂ አምላኩ እንደሚደሰት ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሚደረገው ድግስ መጠነኛና የገንዘብ ጫናን የማይፈጥር ነው፡፡ ያም ሆኖ ቤተዘመዱ ወጪውን ይጋራል፡፡

ወደ አገራችን የተመለስን እንደሆነ፣ የዚህ ዓይነቱ ሙታንን የማሰብና የመዘከር ሥርዓት ከዕለተ ሞተ ጀምሮ፣ ሰልስት፣ ሰባት፣ አሥራ ሁለት፣ ሰላሣ፣ ሰማኒያ፣ መንፈቅ፣ ሙት ዓመት እያለ እስከ 7ኛው ዓመት ድረስ እንደሚዘልቅ ይታወቃል፡፡ በተለይም እምነቱን በጽናት ለሚከታተሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በፍፁም የሚቀየር ሥርዓት አይደለም፡፡ ይሁንና የአከባበሩ መጠን እንደግለሰቡና ቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ይለያያል፡፡

በምስራቅ ጎጃም ከሁለት ዓመት በፊት በመስክ ሥራ ላይ ሆኜ ያጋጠመኝን ላካፍላችሁ::

በእግር እየተንዝን ሳለን አንድ ድንኳን ከተጣለበት ሥፍራ ደረስን:: በመንገድ ስናልፍም ዝግጅቱን ያዘጋጁት ቤተሰብ ኃላፊ ጎራ እንድንል በትህትና ጠየቁን:: ሰውየው ዛሬ የወንድሜ ተዝካር ነውና ጎራ ብላችሁ ከተዘጋጀው ቅመሱ በማለት ጠየቁን:: ለግብዣው ከበሬታ በመስጠት ወደ ውስጥ ዘለቀን:: ትንሽ ካረፍን በኋላ ስነ ሥርዓቱን አጫወቱን:: እንዲህም አሉን፣ "ስማችሁ! ይህን ዝክር ያደረኩት ለባለቤቴ ወንድም ነው:: በጣም ባለውለታዬና መልካም ሰው ነበረ:: ካቻምናና አምና መታሰቢያ ላደርግለት አስቤ፣ እህሉ ከዳኝ፣ አልቻልኩም፣ እንዲሁ ሳብላላ ቆይቼ ዘንድሮ ቀን ሞልቶልኝ ባስበው ብዬ ነው:: እንዳው ይቀየመኛል አምላኩ፣ ይታዘበኛል ብዬ ተፀፅቼ ነበር:: ይኸው እናንተንም እንግዳ አመጣልኝ:: "ነብሱን ይማርልን" ብላችሁ ይቺን ቅመሱልኝ ብለው ወደ መስተንግዶው ዘለቁ::

ከምሳሌው እንደምንረዳው ተዝካር በህይወት ያለነው ካለንበት ከአሁኑ የዓለም ኑሮና ሟቾች ባሉበት የመንፈሳዊ ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ መተሳሰሪያ ሥርዓት መሆኑ ነው:: ለቤተሰብ፣ ለዘመድ አዝማድና ለወገን አለኝታና መከታ የነበሩ ሙታን በከንቱ እንዳይዘነጉ መታወሳቸው ለነዋሪው መሰባሰቢያና መተሳሰቢያ መድረክ ከመሆኑም በላይ የኑሮ ተምሳሌትነታቸው እንዲቀጥል በማድረግ በኩል የማኅበራዊ ዕሴት ግንባታ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው:: እንደ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ተዝካር አቅም በሚፈቅድ መልኩ እንዲታሰብ ይፈቅዳል:: ለምሳሌ ለ40 መታሰቢያ (ፀበልና ፀዲቅ 40 ሙልሙልና አንድ እንሥራ ጠላ)፣ ከ20 ብር የአገልግሎት ክፍያ ጋር ያስከፍላል::

ይሁን እንጂ በገጠር የህብረተሰብ ክፍሎች ከመሠረታዊ የፀበል ፀዲቅና የአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ (አዘውትሮ እንደሚታየው) አቅምን ያላገናዘበ ድግስ እንደሚደገስና ይህም የአንድን ገበሬ ቤተሰብ ዋነኛ እሴት የሆኑትን የእርሻ በሬዎችና የወተት ላሞች እስከመሸጥ ያደርሳል:: በተለይም የደቡብ የህብረተሰብ ክፍላችንን ጨምሮ ይህ ክንውን ከፍተኛ የወጪ መጠን እንደሚያስከትል መረጃዎች ይጠቁማሉ (ፈለቀ ታደለ፣ ኦክስፋም 1997 እ.ኤ.አ ያመለክታል)::

የተዝካር ድግስ ደግሳችሁ አስፈቱት፣ ካልሆነ የንስሐ አባት አልሆንም ስለሚባል ብዙ ሰው ሀብቱን አራግፎ ደግሶ በማብላት በችጋር አለንጋ ይገረፍ እንደነበረ ግርማ ዘውዴ ገልፀውታል:: (ግርማ ዘውዴ፣ 1985 ዓ.ም. ገጽ 73 ያመለክታል)::

ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ዓመት ለመስክ ሥራ ሰሜን ወሎ ሄጄ በነበረበት ጊዜ ያነጋገርኳቸው ገበሬዎች ይህ ከፍተኛ ድግስ ተገቢ እንዳልሆነና መቅረት እንደሚኖርበት፣ በጎጂ ባሕልነት መታየት እንዳለበት በማህበረሰብ ውይይት ወቅት ምክክር እየተደረገበት እንደሆነ ገልጸውልኛል:: ከካህናትና ከነፍስ አባቶች ጋር በመመካከርም የድግሱ መጠን ቤተክርስቲያን በሚፈቅደው መልኩ እየቀነሰ

መምጣቱን አውግተውኛል፡፡ ይህ የምክክር ሥራ በቀጣይነት የሚካሄድ ከሆነና የሃይማኖት አባቶችን ጨምሮ ጠንካራ ተሳትፎ ከተደረገበት "የባለቤትነት" ስሜት ከመፍጠሩ በላይ "ተመካክረው ያደረጉት" እንዲሉ ነውና ውጤቱ መልካም እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡

በከተማ ነዋሪዎችም በኩል እንዲህ ዓይነቱን የመታሰቢያ ሥርዓት ማዘጋጀት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይሁንና አልፎ አልፎ አሉታዊና አዎንታዊ ሥርዓቶች ሲከናወኑ ይታያሉ፡፡ በአንዳንድ በተለይም በከተማ በሚኖሩ የህብረተሰባችን ክፍሎች መታሰቢያነቱ ከሚኖረው መንፈሳዊና አምልኮታዊ ባህርይ ውጭ የሀብት ማሳያና የመፎካከሪያ መድረክ እንዲሆን የማድረግ አዝማሚያ ይታያል፡፡ ይህ ምንም እንኳ ቁጥራቸው በርካታ ባልሆነ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የሚተገበር ቢሆንም ተምሳሌትነቱ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ለማለት ያስችላል፡፡

በሌላው ጫፍ ደግሞ እሰየው የሚያሰኝ ተግባር አልፎ አልፎ ሲከናወን ተመልክተናል፡፡ የመታሰቢያ በዓልን ምክንያት በማድረግ በፀሎት ከማሰብና ከመሰባሰብ ባለፈ ለድግስ ሊውል የሚችለውን ወጪ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ለሚንከባከቡ የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከሎችና ለአረጋውያን መጦሪያ ተቋማት መስጠት ብቅ ማለት የጀመረ ነገር ነው፡፡ ይኸም ለማኅበራዊ እሴታችን መዳበር፣ ለእርስ በርስ መተሳሰባችን፣ ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ በማድረግ በተምሳሌትነት የሚጠቀስ ነውና በስፋት ሊለመድና ሊበረታታ ይገባል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

በዚህ አጭር ዘገባ ውስጥ ሦስት ዋና ዋና የእምነት ነክ ጉዳዮችንና የሚኖራቸውንም የልማት አንድምታ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ በአጠቃላይ እምነት በጭብጡ ከሃይማኖት የሚለይ ሲሆን ሃይማኖታዊ ተቋም ደግሞ ኅብረተሰቡ ከሚኖርበት የባሕል፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር የሚዋሃድና የሚወራረስ ስለሚሆን እምነቱ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያዘው ውጪ ክብረ በዓላትና ሥርዓቸው እየተለወጡና ቁጥራቸውም እየበዛ እንደሚሄድ ንገነዘባለን፡፡

በአገራችን የፈሪሀ እግዚአብሄር፣ የግብረገብነትና የእርስ በርስ መተሳሰብ ባሕል የማኅበራዊ ዕሴታችንን በማጠናከር ለዕድገትና ለልማት አስተዋጽኦ ማድረጉ እሙን ነው፡፡ ይህን መንፈሳዊ እሴት መጠበቅ በጐ ተግባር በመሆኑ፣ የበዓላት አከባበርና ሥነሥርዓት የቤተክርስቲያኗ ቀኖና በሚፈቅደው ብቻ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ያለአግባብና በዘልማድ የሚደረጉ በዓላት ለመቀነስ፣ አልፎ ተርፎም ለማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ በተወሰኑ የገጠር የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የተደረጉ ተሞክሮዎች ፍንጭ ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ዕቅድና የልማት መርሐ ግብር አካል ሆነው ቢቀጥሉ ውጤታቸው የላቀ ይሆናል፡፡ ለዚህም ቤተክርስቲያኗ በግንባር ቀደምነት ሕዝቡንና ተከታዮቿን በስፋትና በተከታታይ ማስተማር ይጠበቅባታል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ በክርስትናም ሆነ በእስልምና እምነቷ ታዋቂ ቦታ ስላላት ይህም ምዕመናን መጠነ ሰፊ መንፈሳዊ ጉዞ እንዲያደርጉ አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ቱሪዝምን ለማስፋፋት ዕድል ይፈጥራል። በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የንግዱ ህብረተሰብ ሃይማኖታዊ ዕሴቶችን በበጎ መልኩ በመጠቀም ቱሪዝምን ለማስፋፋት፣ የማኅበረ-ኢኮኖሚ አውታሮችን ለመዘርጋትና የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመንከባከብ ተግባር ሊያውሉት ይገባል በዚህም በርካታ አነስተኛና መለስተኛ የንግድ ተቋማትን ማስፋፋት ይቻላል።

ሙታንን ከአለፉ በኋላ ማሰቡ ሙታን በሕይወት በነበሩ ጊዜ ትተው ያለፉትን በጎ ተግባር ለመዘከርና የማኅበራዊ እሴትን ለማጠናከር የሚረዳ አጋጣሚ ነው። ነገር ግን እንደነዚህ ያሉ አጋጣሚዎችን በመጠቀም የሀብትን የበላይነት ለማሳየት የሚደረግ ፉክክር ሊወገዝ ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ ለድግስ የሚውለው ገንዘብ ለተጐዱ ወገኖች ቢሰጥ በህይወት ያሉና የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳት ጥሩ ዕድል የሚፈጥር ስለሆነ፣ ይህንኑ አጉልብቶ መቀጠል ተገቢ ይሆናል። በአጠቃላይ "በዓል ሰብሮ የከበረ፣ ጾም ገድፎ የወፈረ" የለም በሚል አስተሳሰብ ለድህነት ተዳርጐ የቆየው የኅብረተሰብ ክፍላችን እየተቀየረ እንዲሄድ በተለያዩ አካባቢዎች የተጀመሩ የምክክርና የትምህርት ሂደቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ልማትን እንዲያበስሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

# የአደባባይ ልመና-ምፅዋት

## *የራስወርቅ አድማሴ*

ከዚህ በፊት ይህ ርዕስ በሌሎች መድረኮች ተዳሷል:: ጥቂት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም የመመረቂያ ጽሑፎቻቸውን አቅርበውበታል:: በተለይ ደግሞ የዛሬ ስድስት ዓመት ገደማ «ሃምሳ ሎሚ» በተሰኘው የቴሌቪዥን መድረክ አማካይነት፣ «ልመና - የአደባባይ ምስጢራችን» በሚል ርዕስ የታዳሚውን ህዝብ ትኩረት በመሳቡ የተነሳ ተደጋግሞ ለአየር የበቃ ውይይት እካሂዶበት እንደ ነበረ ይታወሳል:: ይሁንና፣ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ይኸንን ርእስ «ባሕልና ልማት በኢትዮጵያ» በተሰኘው በዚህ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሚያካሂደው የውይይት መርሐ ግብር መዳሰስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: እነዚህም የጽሑፉ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ/ ባጠቃላይ ልመና ስለምንለው ክስተትና ስለ ዓይነቶቹ፤ በተለይ ደግሞ ስለ አደባባይ ልመና-ምፅዋት ምንነት ትክክለኛ ግንዛቤ ለመጨበጥ፤

ለ/ በሀገራችን ተንሰራፍቶ የሚገኘውንና እየጨመረ የመጣውን የአደባባይ ልመና-ምፅዋት ክስተት ምንነት፣ ዓይነት፣ አመጣጥና፣ መሠረቶች ለመቃኘት፤

ሐ/ በሀገራችን የአደባባይ ልመና-ምፅዋት ነባር-ልምድ እንደ መሆኑ ከባህላችን ጋር ያለውን ትስስር ለመመርመር፤

መ/ የአደባባይ ልመና-ምፅዋት ክስተት ባጠቃላይ በልማት፣ በተለይም በማህበረሰባዊና በሰብዓዊ-እድገት (ሶሺያልና ሂዩማን-ዴቬሎፕመንት) ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለመመልከት፤

ሠ/ ይህ ክስተት ሊወገድ፤ ሊቀነስ፤ እንዲሁም የተሻሻለ ሰብዓዊ መልክ ሊይዝ የሚችልበትን፤ ክፍት ዕድሎችና እንዲሁም እንቅፋቶች ለማመዛዘን፣ እና

ረ/ እንዴት ይህንን ማድረግ እንደሚቻል፣ የሀገር ውስጥ የመፍትሔ ሀሳቦችና ተሞክሮዎችን (በተለይም የቅርብ ጊዜዎቹን) በመቃኘት፣ ጭብጦችን አጠቃሎ ለውይይት ማቅረብ ነው::

በሌላ በኩል ይህ ፅሑፍ የሚዘለው ወይም የማያተኩርበት ርዕስ ቢኖር፣ የልመና መልኮች የሚባሉት፣ ለምሳሌ ለማኙ ለልመና የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች፣ አባባሎች፣ ዜማዎች፣ ወዘተ... ነው:: ይህም የተደረገበት ምክንያት፣ ጉዳዩ በበቂ ስለሚታወቅና በሌሎች መድረኮች የተሸፈነ ስለሆነ ነው::

# 1. የልማት-ምፅዋት ክስተት ምንነትና ፍች

ልመና ማለት ማንኛውም ራስን ዝቅ አድርጎ በመማፀን የሚደረግ ስጦታ መጠየቅ ነው። ታዲያ፣ እንደኛ ባለ ሁሉም ሰውና ሁሉም ቤተሰብ ራሱን ችሎ በማይኖርበት ኅብረተሰብ ግለሰቦች ከግለሰቦች፣ በተለያየ መንገድና ደረጃ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ ወይም የአገልግሎት ስጦታ ይጠይቃሉ። ይለምናሉ። የቤተሰብና የቤተዘመድ አባላት፣ አብሮአደጎች፣ ጓደኞችና፣ ጎረቤቶች ሁሉ፣ አንዱ ከሌላው በተለያየ ጊዜና ምክንያት ስጦታ መጠየቅ፣ መለመን፣ የተለመደ ድርጊት ነው።

ከዚህም አልፎ፣ እንደ ስፖርት ክበቦች፣ ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ ወይም የልማት ድርጅቶችና፣ የመሳሰሉትን በተመለከተም ከሌላ ለጋሽ-ድርጅት፣ መንግስታዊ ተቋም ወይም ግለሰብ ስጦታ መጠየቅ የተለመደ ነው። መንግስታትም ከሌሎች መንግስታትና ከአለም-አቀፋዊና ክልላዊ ለጋሽ-ድርጅቶች መለመን እየተለመደ መጥቶ ከጠቅላላው የልመና እንቅስቃሴ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው ይኸው መንግሥታዊ ልመናና ዕርዳታ ሆኗል። ባለፈው ዓመት የደረሰውን ዓለም-ዓቀፋዊ የፋይናንስ ቀውስ ተከትሎ የመጣው የናጠጡት ድንበር ዘለል ኩባንያዎችና አንዳንድ የአውሮፓ አገሮች «በነፍሳችን ድረሱልን» እሪታዎች ደግሞ «ትልቅ ሲደኽይና ሲለምን በትልቁ» መሆኑን አመላክቶናል።

እርግጥ፣ የልመናውና የምፅዋቱ አድማስ በሰፋባቸውና የዘመናዊነትን ጠባይ በተላበሰባቸው አካባቢዎች፣ ልመናው «ልመና» መባሉ ቀርቶ «ፈንድ-ሬዚንግ»፣ «ምፅዋቱ» ደግሞ «ዶኔሽን»፣ «መፅዋቹ» «ስፖንሰር»፣ «ለማኙ» እና «መፅዋቹ» ባንድነት «ፓርትነር» እየተባሉና እየተባባሉ በስም ይደጋገፋሉ። በስም መደገፍ (ዩፌሚዝም) ምንም የቆየና ቀድሞም በእኛም ሀገር ያለ ቢሆንም፣ በቆዬው ጊዜ፣ «መፅዋቹ» «ለማኙ»ን «የኔ-ቢጤ» ብሎ በመጥራት ሁለቱ ዛሬ የሚጫወቷቸው ሚናዎች ነገ ሊለዋወጡ እንደሚችሉ በማመልከት ትህትና ያሳየዋል እንጅ፣ «ሸሪክ» እያለ ሊሸነግለው አይሞክርም።

ስለዚህ፣ የሳንቲም ወይንም የቢሊዮኖች ዶላር ጉዳይ ይሁን አይሁን፣ ልመና ይባል ፈንድ-ሬዚንግ ልመና-ምፅዋት ዓለም-አቀፍ (ዩኒቨርሳል) ክስተት ነው ማለት የምንችል ይመስለኛል። ይኽ ክስተት ይኸን ያህል ሰፊ ከሆነ ደግሞ፣ የዛሬው ውይይታችን መልክ ይይዝልን ዘንድ የርእሳችንን ዳር-ድንበር መወሰን ይኖርብናል ማለት ነው። እንደሚከተለው በጠባብ ፍች በማሰር።

እኛ ለተነሳንበት ጉዳይ ስንል፣ *«ልመና» ማለት ማንኛውም፣ በዋነኛነት ከማያውቁትና ለቅፅበት ብቻ የህዝብ መዘውተሪያዎች በሆኑ አደባባዮች፣ ጎዳናዎች፣ ገበያዎች፣ የአውቶቡስና የታክሲ መናሃሪያዎች፣ የቀብር ቦታዎች፣ የፀሎት-ቤት አካባቢዎች፣ ወዘተ... ፊት ለፊት ከሚገናኙት ሰው ራስን ዝቅ አድርጎ በመማፀን የሚደረግ የገንዘብ፣ የምግብ፣ ወይም የሌላ ቁሳቁስ ስጦታ መጠየቅ ነው*፣ ብለን እንፈታዋለን።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ምፅዋት የምንለው ደግሞ፣ ባጭሩ፣ *ከላይ ለገለፅነው ዓይነት ልመና ምላሽ ሆኖ የሚደረግን ማንኛውንም የገንዘብ፣ የምግብና፣ የቁሳቁስ ልገሳ ነው።*

ልመና ያለ ምፅዋት፣ ምፅዋትም ያለ ልመና ስለማይኖሩ ያንን ልመናና ምፅዋትን ያቀፈ አጠቃላይ ስርዓትና፣ የለማኙንና የመፅዋቹን ኀብረተሰባዊ ግንኙነት ለማመልከት «ልመና-ምፅዋት» በሚል ሐረግ አልፎ አልፎ እንጠቀማለን::

እነዚህ ከላይ ለ«ልመና»፣ ለ«ምፅዋት» እና ለ«ልመና-ምፅዋት» የተሰጡት ፍችዎች ይህ ጽሑፍ በምን ዓይነቱ ጠበብ ያለ የ «ልመና-ምፅዋት» ክስተት ላይ እንደሚያተኩር ግልፅ ሲያደርግልን ሳለ፤ በሌላ በኩል፣ ፍችው የልመናን ክስተት መሠረታዊ ምንነት (ኤሰንስ) በበቂ እንደማይገልፀው እናምናለን:: ከዚህ አኳያ፣ ከላይ ፍች የሰጠነው ልመና በቋሚነት በሚካሄድበት ጊዜ ከዝቅተኛ የኢኮኖሚ ተግባርነት የሚመደብ ነው የሚሉ ተመራማሪዎች አሉ:: (ለምሳሌ ያህል፣ ዲን 1999):: በሌላ በኩል፣ በተለይ ድኅረ-ቀውስ ልመናንና ደኅሚ ልመናን ከጊዚያዊ የችግር መቋቋሚያ ስልቶች (ኮፒንግ ሜካኒዝምስ) የሚመድቡም ሞልተዋል (ለምሳሌ፣ ደሳለኝ ራህመቶና አክሊሉ ኪዳኑ 2001፣ እንዲሁም ውብሸት ደሞዙ 2003)::

## 2. የልመና-ምፅዋት ዓይነቶች

ልመና-ምፅዋት ዩኒቨርሳል ክስተት የሆነውን ያህል፤ የልመና ምክንያቶችንና የአለማመን-አመፀዋወት ሂደትን በተመለከተ ደግሞ፤ ልመና ከኀብረተሰብ-ኀብረተሰብ፣ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ ይለያያል:: ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳትም፣ የአደባባይ የልመና-ምፅዋት ዓይነቶችን እንደሚከተለው ለያይተን ማየት እንችላለን::

**ሀ/ ቋሚ ልመና:-** ስሙ እንደሚገልፀው ለማኙ በቀጣይነት እየለመነና ለዘለቄታው ለማኝ ሆኖ የሚኖርበት የልመና ዓይነት ሲሆን፤ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ጠባዮቹ ዋነኞቹ በዚህ ዓይነት ልመና የተሰማሩ ሰዎች:- 1ኛ/ ልመናን እንደ «ሙያቸው» የያዙት መሆኑና፤ 2ኛ/ አብዛኛ ዎቹ በእርግጥ የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞች አልያም መስለው የሚቀርቡ መሆናቸው ነው::

**ለ/ ወቅታዊ ልመና:-** ለማኙ፣ በታወቁ የምግብ ችግር በሚከሰትባቸው ወይም የግብርና ስራ እጅጉን በሚረግብባችው የዓመቱ ወቅቶች ደጋግሞ በልመና የሚሰማራበት ዓይነት ወቅታዊ (ሲዝናል) ልመና ነው:: ይህ ዓይነቱ ልመና ከሌሎቹ ሁሉ በልመና ከተሰማራው ዜጋ ጥቂቱን የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም::

**ሐ/ ድኅረ-ቀውስ ልመና:-** የምንለው አልፎ አልፎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱ ተፈጥሯዊና ማኀበረሰባዊ ቀውሶችን ተከትሎ የሚከሰትና በአንፃራዊ ደረጃ ለተወሰነ አጭር ጊዜ የሚካሄድ የልመና ዓይነት ሲሆን፤ በተለይ የገጠር ሰዎችን ይመለከታል:: ድኅረ-ቀውስ ልመና ከቀውሶች አመጣጥና ስፋት ጋር ተያይዞ የሚመጣና እነሱን ተከትሎ የሚዋዥቅ ነው:: በአንድ የተወሰነ ወቅት በዚህ ዓይነቱ ልመና የሚሰማራው ሕዝብ ብዛት በመንግስት የአደጋ መከላከል እርምጃ

ስኬታማነት የሚወሰን ሲሆን፣ የአደጋ መከላከሉ ስራ በከፍተኛ ደረጃ ቢሳካም እንኳን አንዳንድ ግለሰቦች ከመከላከያው መረብ ማምለጣቸው ስለማይቀር ቁጥሩ ይቀንስ እንደሆነ ነው እንጂ ቀውሶችን ተከትሎ መከሰቱ ግን አይቀሬ ነው።

**መ/ ደጓሚ ልመና፡-** ይኸኛው ዓይነት ልመና፣ ገቢ እያላቸው ሳለ፣ ገቢያቸው በቂ ባለመሆኑ የተነሳ ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው የሚማቅቁ ዜጎች ገቢያቸውን ለማሟላት የሚያደርጉትን ልመና ይመለከታል። ልመናን እንደ ገቢ መደጎሚያ ከሚያካሄዱት ሰዎች ዋነኞቹ ከአንድ ወይም ከሌላ ምንጭ እጅግ አነስተኛ የሆነ የጡረታ አበል ወይም አድሮ-ብቅ የሚል የዘመድ ወዳጅ እርዳታ የሚያገኙ አዛውንት ናቸው።

**ሠ/ ውስን ዒላማዊ ልመና፡-** ለማኙ ከሆነ እርግጠኛ ወይም የይምሰል ግብ ለመድረስ የሚያካሂደው ልመና ነው። የልመናው አቀራረብ ባብዛኛው የዘመናዊነት መልክ አለው። በሀገራችን የልመና ጥያቄው ብዙውን ጊዜ በደብዳቤ፣ አልፎ አልፎም በህዝባዊ መገናኛዎች ይቀርባል። በሌሎች ሀገራት በኢንተርኔት ጭምር ልመና ማቅረብ በመዘውተሩ «ኢ-ቤጊንግ» የሚል ስም ተሰጥቶታል።

**ረ/ የዘመቻ ልመና፡-** ይህም እንደ ላይኛው ቀደም ብለው የተጠቀሱትን የልመና ዓይነቶች የሚተካ አይደለም። እንዲያውም፣ ውስን ኢላማዊ ልመና ያልነው ንዑስ ክፍል ሆኖ መወሰድ ይችላል። የዘመቻ ልመና የአንድ አካባቢ ሰዎች በአንድ ጊዜ ወይም በፈረቃ ዓይነት፣ ከሆነ ተመሳሳይና ውስን ኢላማቸው ለመድረስ የሚያካሄዱት ሲሆን፣ አንድም፣ ሰዎቹ ሆን ብለውና ተስማምተው የሚወስዱት እርምጃ፣ አልያም አንዱ የሌላውን እርምጃ በመቅዳት ተከታትለው የገቡበት የልመና ሞገድ ሊሆን ይችላል። እነዚህን ሁለት አካሄዶች በተመለከተ፣ ቤታቸውን በልመና ገንዘብ ቆርቆሮ ለማልበስ እንዳሉ ነቅለው ወደ አዲስ አበባ የሚመጡትን መንደረተኞችንና፣ ለምና ለባሏ የእርሻ በሬዎች የገዛች አንዲት ሴትን አርአያ ተከትሎ የተነሳውን የእናቶችና ህፃናት ማዕበል ጉዳይ እንደ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። የሌላዋን (በጋዜጣ እንዳነበብነው) ለባሏ ካላሺኒኮቭ ጠመንጃ ለመግዛት ልመና የገባችዋን ሴት ግን የተከተላት እንደሌለ ተስፋ በማድረግ እንተወው።

**ሰ/ የማስመሰል ልመና፡-** በአገራችን ከሚገኙት ለማኞች የማይናቀውን ክፋይ የሚይዙት ያልሆኑትን ሆን፣ ያልደረሰባቸውን ደረሰብን፣ እና የማያደርጉትን ልናደርግ ነን፣ ወዘተ... በማለትና መስሎ በመቅረብ የሚለምኑ እንደሆኑ ይነገራል — ምንም እንኳን የግምቶቹ መሰረት አስተማማኝ ባይሆንም። ይህ የማስመሰል ልመናም ቀደም ብለው የተጠቀሱትን የልመና ዓይነቶች የሚተካ አይደለም፣ በሁሉም በሌሎቹ የልመና ዓይነቶች ባልናቸው ውስጥ ከሃቀኛው ልመና ጎን ለጎን የሚሰራበት እኩይ የሆነ መንትያው ብቻ ነው።

ሸ/ **የቤተሰብ ልመና፡-** ከላይ የተጠቀሱትን የልመና ዓይነቶች የሚተካ ሳይሆን ከነሱ ባንደኛው፤ በተለይም ቋሚ፣ ወቅታዊና፣ ድኅረ-ቀውስ የልመና ዓይነቶች በሚካሄዱበት ጊዜ ተዳብሎ የሚከሰት፤ ማለትም አንድ ቤተሰብ እንዳለ ወይም የቤተሰቡ ክፋይ የሆኑት አባላቱ ባንድነት የሚሳተፉበት ዓይነት ንዑስ ክፍል ነው።

ከነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት የአደባባይ ልመና-ምፅዋት አይነቶች በተጨማሪ ሌሎች ለየት ባሉ ነባር እምነቶችና ስርዓታት ላይ ተመስርተው የቆዩና ከዚህ የአደባባይ ልመና-ምፅዋት ብለን ፍች ከሰጠነው ክስተት በተጨባጭ ወጣ ያሉም እንዳሉ እንገነዘባለን። በመሆኑም፣ ዘለናቸው ማለፍ ሳይሆን ለብቻቸው ለይተን በመቀጠል ዘርዝረን እናቀርባቸዋለን። እነሱም፤ የተዝካር ምፅዋት፣ የቆሎ ተማሪ ሥርዓት፣የባሕታውያን ልመናና፣ የሃሚና የዝማሬ ልመና ናቸው።

ሀ/ **ተዝካር – ልዩ የሆነ ምፅዋት፡-** ተዝካር፣ ማለትም በሞት ለተለዩ ሰዎች በማስታወሻነት የሚደረግ ግብዣ እንደመሆኑ፣ የልመና ሳይሆን የምፅወታ ዓይነት ነው። በተጨማሪ፣ ይኸን የምፅዋት ዓይነት ልዩ የሚያደርጉት አምስት ጠባዮች አሉት። አንደኛ፣ የተዝካር ምፅዋት የሚከናወነው አንድም በደጀ ሰላም አልያም በደጋሹ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ነው። ሁለተኛ፣ ምፅዋቱ በምግብና በመጠጥ ልገሳ ብቻ የተወሰነ ነው። ሦስተኛ፣ መፅዋቹ አንድ ግለሰብ ወይም አንድ ቤተሰብ ብቻ ሲሆን፣ ተመፅዋቹ ደግሞ በርካታ ታዳሚ ነው። አራተኛ፣ ተመፅዋቹ መጣ አልመጣ ሳይባል ቀድሞ ወደ ተዘጋጀ ማዕድ «ተጠርቶ የሚገባበት» ወይም የሚሰጠው እንጅ በራሱ ሰዓት ጠይቆ የሚደረግለት ዕርጥባን አይደለም። አምስተኛ፣ የተዝካር እድምተኛ ወጥ ሳይሆን ቅይጥ ነው። ቋሚውን፣ ወቅታዊውን፣ ድኅረ-ቀውሱን፣ ባለ ውሉን ኢላማውንና፣ በተለይ ደግሞ፣ ደኅሚ ለማኙን፣ ጎዳና ተዳዳሪውንና ሌላ ሌላውን እግሩ የጣለውን ሁሉ ያጠቃልላል። በመጨረሻ፣ ተዝካር ዕምነታዊ መሰረት ያለው በመሆኑ ጭምር ከሌሎቹ የልመና-ምፅዋት ዓይነቶች እንደሚለይ ሊሰመርበት ይገባል።

ለ/ **የቆሎ ተማሪ ሥርዓት፡-** በአንድ በኩል የቤተክህነት ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች የዕለት ጉርሳቸውን ከየአካባቢው ማኅበረሰብ የሚያገኙበትና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ችግርን በመለማመድ የለዘበ ስነልቦና የሚላበሱበት፣ በሌላ በኩል ማኅበረሰቡ የትምህርትን ሂደት የሚደግፍበት ለዘመናት ተፈላጊ ሆኖ የቆዬ ነባር ሥርዓት ነው። ልመናውም የሚያተኩረው ከትምህርት ጊዜ ውጭ ከመንደር መንደር በመዘዋወር የበሰለ ምግብ ሰብስቦ ወደ ትምህርት ተቋሙ በማምጣት የወል ወደሆነው ገበታ ማቅረብ ላይ ነው። በመሆኑም፣ የቆሎ-ተማሪ ልመና ከተወሰነ የልጅነትና የተማሪነት ህይወትና ከፍ ተደርጎ ከሚታዬው የመማር ማስተማር ሂደት ጋር የተያያዘ የሚያከራ ተግባር እንጅ እንደ ተራው የአደባባይ ልመና በውርደትና መገለል የታጀበ ሆኖ አያውቅም። በአሁኑ ጊዜ፣ የቆሎ ተማሪነትም የማስመሰል ልመና ተጠቂ እየሆነ መጥቷል። ደበሎ ወይም አረንጓዴ ጋቢ ለብሰው እንደ ቆሎ ተማሪ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች መከሰት ከላይ የተባለውን አይሽርም።

የነዚህ ዓይነቶቹ ለማኞችም ተግባር «አስመሳይ ልመና» ባልነው ስር የሚጠቃለል ነው እንጅ የቆሎ ተማሪ ሥርዓት አካል አይደለም።

ሐ/ **የባሕታውያን ልመና፡-** ይህ የሚመለከተው በዋነኛነት ክህነት የሌላቸውንና ከቤተክህነት አስተዳደርም ውጭ የሆኑና የማንኛውም ማኅበረሰብና ተቋም አባል መሆንን ንቀው ትተው ከእምነት ቦታ ወደ እምነት ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ ነፃ መንፈሳዊ ሰዎችን ነው። እነዚህ ንብረት-ዓልባ መንፈሳውያን ሰው በሚገኝባቸው አካባቢዎች በሚተላለፉበት ጊዜ እጅግ አነስተኛ የሆነ የዕለት ጉርስ ፍላጎታቸውን በልመና እንዲያሟሉ ተፈጥሮ ሲያስገድዳቸው፣ ለንብረትና ለዓለማዊ ጉዳዮች ያላቸው ንቀትና ራሳቸውን ዝቅ አድርጎ የመገኘት ዝንባሌያቸው ደግሞ ከመንደር መንደር ተዘዋውሮ እንጀራ መለመንን እንደ እምነታዊ ግዴታቸው አይተው እንዲቀበሉት አድርጓቸዋል። ስለሆነም፣ የባሕታውያን ልመና ቀጥተኛ የድህነት ውጤት ሳይሆን ከእምነት ከመነጨ መስዋዕትነትን የመሻት ግላዊ ፍላጎት የሚመነጭ ነው።

መ/ **የሃሚና የዝማሬ ልመና፡-** ሃሚናዎች በሰሜናዊና ሰሜን-ማዕከላዊ የአገራችን ክፍሎች የሚኖሩና በጎጃም "አሚና"፣ ፣ በሸዋ "ላሊበላ"፣ በወሎ "አባ ውዴ"፣ በትግራይ "ሓምየን" ወዘተ... በመባል የሚታወቁ፣ ከአካባቢው ህዝብም በዘር ሐረጋቸው ተለይተውና በነባር ልምድ ተገልለው በዝማሬ ልመና የሚተዳደሩ ልዩ የሆኑ አነስተኛ ማኅበረሰቦች (ቡድኖች) አባላት ናቸው። ታሪካዊ አመጣጣቸው በውል የማይታወቀው እነዚህ የሃሚና ማህበረሰቦች ጋብቻቸውን እርስ በርስ በነዚያው በአነስተኛ ማኅበረሰቦቻቸው ውስጥ በመወሰን የዘር ሐረጋቸውን ወጥነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንዲኖር አድርገው ኖረዋል ወይንም እንዲያደርጉ በሰፊው ኅብረተሰብ ተገደዋል። በሃሚናዎች ዘንድ ሰፍኖ የኖረው፣ የዝማሬ ልመና ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው የማኅበረሰቡ በሥጋ ደዌ የመጠቃት አዝማሚያ ይከላከላል የሚለው ነባር እምነት፣ ማኅበረሰቡ የዝማሬ ልመናን እንደ ዋና መተዳደሪያው አድርጎ እንዲይዘው አስተዋፅዖ አድርጓል (መሰለ 2010)። ይሁንና፣ የማኅበረሰቡ ከማምረቻ መሳሪያዎችና ከሌሎች ሙያዎች መታቀቡ የክስተቱ ስረ-መሰረት ሳይሆን አይቀርም።

የሃሚናዎች የዝማሬ-ልመና ልዩ መልኮችም አሉት። 1ኛ/የዝማሬ ልመናው የሚካሄደው ጎሕ ከመቅደዱ በፊት ብቻ ነው። 2ኛ/ ዝማሬው የሚካሄደው በቡድን ወይም በጥንድ ተሳታፊዎች ሆኖ ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ አጃቢነት ነው። 3ኛ/ ለሃሚናዎች የሚሰጠውና እነሱም የሚቀበሉት ምፅዋት እህል፣ ጥራጥሬ፣ የቁም እንስሳና ገንዘብ እንጅ የበሰለ ምግብ ወይም መጠጥ አይደለም። 4ኛ/ ሠርግና ሌላ ሌላ ድግሳቸውን የሚያወጡትም ከሌላው ማኅበረሰብ አባላት የተዝካር ድግስ ጋር በማያያዝ ነው።

እነዚህ በሁለተኛ ደረጃ ከላይ የዘገብናቸው፣ ለየት ባሉ ነባር እምነቶችና

ሥርዓታት ላይ ተመስርተው የቆዩና ከአደባባይ ልመና-ምፅዋት ወጣ ያሉ የልመና ዓይነቶች፤ ማለትም የተዝካር ምፅዋት፣ የቆሎ ተማሪ ሥርዓት፣ የባሕታውያን ልመናና፣ የሣሚና የዝማሬ ልመና፤ በዘመናዊነት ለውጥ እየተገዘገዙ ሄደዋል:: ዘመን ያመጣቸው የዋጋ መናርና የኑሮ መወደድ፣ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትና የሃይማኖት ትምህርትም ዘመናዊ ሥርዓት እየያዘ መምጣት፣ የቤተክህነት አስተዳደርና ብሕትውና ደንቦች መሻሻልና፣ በተለይ ደግሞ የመሬት ይዞታን ጨምሮ የኢትዮጵያ አብዮት ያመጣቸው ኢኮኖሚያዊና ኅብረተሰባዊ ለውጦች እነዚህን አራቱን የልመና-ምፅዋት ዓይነቶች በተለይ ደግሞ የኋለኛዎቹን ሦስቶች መሠረት አሳጥተዋቸዋል:: የጠቀስናቸው ለውጦች መሠረት እየያዙና እየሰፉ በሄዱ ቁጥር፣ እነዚህ ለየት ባሉ ነባር እምነቶችና ሥርዓታት ላይ ተመስርተው የቆዩና ከአደባባይ ልመና-ምፅዋት ወጣ ያሉ የልመና ዓይነቶች እየተዳከሙ ሄደው እንደሚከስሙ መገመት ይቻላል::

## 3. የልመና-ምፅዋት መሠረቶች

አስቀድመን ለ «ልመና» እና «ለምፅዋት» የሰጠናቸው ፍችዎች እንዳሳዩት አንድ ለማኝ የሚለምነውና መፅዋቹም የሚቸረው ገንዘብ፣ ምግብ፣ ወይም ቁሳቁስ ነው:: እነዚህም የእለት ኑሮ ለመግፋት የሚያስፈልጉ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግብአቶች እንጅ ሌላ አይደሉም:: ከነዚህ ውጭ የሆነውን «እግዚአብሔር ይስጥህ» የሚል ምርቃት ከቸረም ልመናውን አልተቀበለም ማለት ነው:: ስለዚህ «ልመና-ምፅዋት» በዋነኛነት ከቁሳዊ እጥረት ወይም ችግር፤ ማለትም ከቁሳዊ ድህነት የሚመነጭ እንደሆነ ግልፅ ይመስለኛል:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ በመለስተኛ ደረጃም ቢሆን ከኢኮኖሚ ውጭ የሆኑ ኅብረተሰባዊ ሁኔታዎች የ«ልመና-ምፅዋት»ን መልክ በመቅረፅ በኩል ለሚጫወቱት ሚና እውቅና መስጠት ተገቢ ይሆናል:: የእነዚህ አባባሎች ትክክለኛነት በተለይ በሃገራችን በሚታየው የ«ልመና-ምፅዋት» ክስተት በሚገባ የተረጋገጠ ይመስለኛል::

ባጭሩ፣ ባንድ በኩል «ልመና የድህነት ጉዳይ አይደለም» ከሚለው አባባል፣ በሌላ በኩል «ልመና የድህነት ነገር ብቻ ነው» ከሚለውም ድምዳሜ፣ ከሁለቱም እለያለሁ ማለት ነው:: እንደኔ፣ *ድህነት ለልመና መከሰት አስፈላጊ ግን በቂ ያልሆነ ቅድመ-ሁኔታ* ነው ብንል የተሻለ ድምዳሜ ይሆናል::

ከልመና መሠረቶች መካከል ዋነኛዎቹ፣ ቅደም-ተከተላቸውን ሳይጠብቁ፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ይመስሉኛል:: እነዚህን ሁኔታዎች «ምክንያቶች» ሳይሆን፣ «መሠረቶች» ያልንበት ምክንያት ሊሰመርበት ይገባል:: ሁሉም ሁኔታዎች፤ ለልመና መስፋፋት ወይም አንድ ሰው ለማኝ ይሆን ዘንድ ምቹ አካባቢ ይፈጥራሉ እንጅ በራሳቸው የግድ አንድን ሰው ለማኝ አያደርጉትም[1]::

ከነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ህብረተሰብ ወይም ማኅበረሰብ-አቀፍ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው::

[1] "They are contextual and not direct causal factors" የሚለው የእንግሊዝኛ አባባል፤ ለማለት የፈለግነውን በበለጠ ይገልፀው ይሆናል::

- አጠቃላይ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ኋላቀርነት፡- ኋላቀርና ዝቅተኛ ምርትና አመራረት፣ ኋላቀርና ዝቅተኛ የመሰረታዊ ልማት አውታሮች ስርጭት፣ ወዘተ... እና ከነዚህ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱት ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ ወዘተ...

- የተፈጥሮ አደጋዎች፡- ድርቅ፣ በረዶ፣ የውሃ መጥለቅለቅ፣ ተምች፣ ወረርሽኝ የሰውና የከብት በሽታዎች፣ ወዘተ...

- ሰው-ፈጠር አደጋዎች፡- ጦርነትን፣ አካባቢያዊ ግጭቶችንና አልፎ አልፎ ደግሞ የተለያዩ በበቂ ያልታሰበባቸውን የ«ልማት» እርምጃዎችን ተከትለው የሚመጡ እንደ አካባቢ ብክለትና የማኅበረሰብ መናጋት ያሉ ችግሮችን ጨምሮ፤

- ፈጣን የህዝብ ፍልሰት፡- የቤተሰብ መፍረስን፣ ስራ አጥነትን፣ መጠጊያ አጥነትን፣ ለአደጋ ተጋላጭነትንና የመሳሰሉትን የሚያስከትለው የህዝብ ካንድ አካባቢ ወደ ሌላ፣ በተለይም ወደ ከተሞች የሚደረግ ፈጣንና በፕላን ያልተመራ የህዝብ ፍልሰት ራሱ ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች የሚመነጭ ቢሆንም፣ ለልመና መስፋፋት አስተዋፅዖ ያደርጋል።

በነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ላይ የሚጨመሩ ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ። ከዚህ አንፃር ልናተኩርበት የሚገባን ግን ሰዎች ወደ ልመና የሚያመሩበትን ጎዳና የሚጠርጉ ኅብረተሰባዊ ሁኔታዎችን ገና በእንጭጫቸው ወይንም ገና በአዝማሚያነታቸው ለይተን የማሳዬትን ስራ ነው። ወደፊት ጎልተው ሊወጡ ከሚችሉ የዚህ ዓይነት ሁኔታዎች መካከል እጅግ አሳሳቢ የሚመስለኝን ልጥቀስ። ዛሬ የምናያቸው የመኖሪያ ቤት እጥረት መባባስ፣ የመኖሪያ ቤት ኪራይ መናርና፣ የድሆች መጠለያ ሆነው የቆዩት የቤተክርስቲያን አካባቢ ምድሮችና ደሳሳ መንደሮች ለዘመናዊ ሕንፃዎች ግንባታ የማዋል ሂደት ባንድነት ተዳምረው ፍፁም የሆነ የመጠለያ አልባነት ማስከተላቸው አይቀርም። ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንዳስተዋልነው ደግሞ የሰው «እንደ አቅሙ» አንገቱን የሚያስገባበት መጠለያ ፈፅሞ ማጣት በራሱ ታታሪውን ዜጋ ጭምር እያንደረደረ ወደ ልመና አዘቅት የሚጥል ዋነኛ ምክንያት ነው።

ግለሰቡን የሚመለከቱት ሁኔታዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- ቋሚ የአካል ጉዳተኛነት፡- በቋሚነት የመስራት ችሎታን ፈፅሞ የሚያውክ፤ ወይንም ከአካል ጉዳተኛው «አቅም» በላይ የሆነ ስልጠና ወይም ዕርዳታ ካልተጨመረበት በስተቀር የመስራት ችሎታን የሚያውክ የአካል ጉዳተኛ መሆን፤

- መገለልን የሚያስከትሉ በሽታዎች ተጠቂ መሆን፡- የመስራት ችሎታ እያለም፣ በበሽታ መተላለፍ ስጋት ወይንም መፀየፍ ሳቢያ በቀጥታም ሆነ በዘወርዋራ መንገድ ከስራ መገለል፣ የስራ ዕድል መነፈግ፤

- የአዕምሮ ጤና መታወክ፡- በቋሚነት የመስራት ችሎታን ፈፅሞ የሚያውክ የአዕምሮ ጤና መታወክ ሰለባ መሆን፤

- ጡረታ-አልባ አረጋዊነት፡- በመንግሥት፣ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣

በግል አሰሪ ድርጅቶች ወይንም ግለሰቦችና በምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች የሚካሄዱ የተደራጁና ቀጣይ የጡረታ ሥርዓቶች ያልታቀፈና በተጨማሪ ደግሞ ጧሪ ቀባሪ ዘመድ አዝማድ የሌለው አረጋዊ መሆን፤

- አሳዳጊ-አልባነት፡- የወላጅ ወይንም የማደጎ ግለሰብም ሆነ ድርጅት አሳዳጊ ቢስነት፤ በለጋ ዕድሜ በመገኘታቸው ራሳቸውን ያልቻሉ ልጆች መጠለያ ሰጪ፣ አብይ አጠጪ፣ አልባሽና፣ ተከላካይ ማጣት፣

## 4. የልመና-ምፅዋትና የባሕል ግንኙነት

ልመና-ምፅዋትን የመሰለ ኅብረተሰባዊ ክስተት የግድ (እምነትን፣ አመለካከትንና ሌሎች ሌሎችንም ከሚያቅፈው) ከባሕል ጋር ግንኙነት እንደሚኖረው ሳይታለም የተፈታ ነው። ይህ ማለት ግን ባሕል ልመናን ይፈጥራል ማለት አይደለም። ሊሆን እንደማይችል ማስረዳቱም ከባድ አይደለም። በዓለም ላይ እጅግ ብዙ ኅብረተሰቦች ሲገኙ እያንዳንዳቸው ከሞላ ጎደል የየራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ባሕሎች ባለቤቶች ናቸው። በሌላ በኩል ግን፣ ምናልባት አንዳንድ የህዝባቸው ቁጥር እጅግ አነስተኛ ከሆነ ኅብረተሰቦች በስተቀር ልመና-ምፅዋት ባንድ ወይም በሌላ መልኩ ፈፅሞ የማይገኝባቸው የሉም። ከኅብረተሰብ ሳንካዎች በከፍተኛ ደረጃ ቀንሰዋል ተብለው በሚነገርላቸው በስካንዲኔቪያ አገሮችና በኔዘርላንድስ ሳይቀር ልመና በተወሰነ ደረጃ «እንደሚሰራበት» በቦታው ተገኝተን የታዘብነው ስለሆነ ዋቢ ማቅረብ አያሻንም። ታዲያ፣ ልመና በሁሉ ዘንድ ያለ (ማለትም፣ ዩኒቨርሳል) ከሆነና ባሕል ደግሞ ከኅብረተሰብ ኅብረተሰብ የተለያየ ከሆነ ዘንድ፤ የባሕል ልዩነት ባይሆን በልመና ቅርፅና ስፋት ላይ እንጅ በልመና *መኖር አለመኖር* ላይ ልዩነት አያመጣም ማለት ነው። ስለዚህም የፊተኛው ለኋለኛው መከሰት አስፈላጊ ምክንያት አይደለም ማለት ነው።

ያም ሆኖ ታዲያ፣ የተለያዩ ኅብረተሰቦች ለልመና-ምፅዋት ክስተት ያላቸው አመለካከትና የማስተናገድ አዝማሚያ የተለያዬ እንደሆነ አይካድም። ይህ ልዩነት ግን ከአጠቃላይ የኅብረተሰቡ ምጣኔ ሀብት ደረጃ ጋር አብሮ ከፍና ዝቅ እያለ የሚሄድ እየሆነ፤ የበለፀጉቱ ኅብረተሰቦች ባሕላት ለልመና-ምፅዋት ይበልጥ ቅራኔ ሲያሳይ በድህነት አረንቋ የሚማቅቁት ኅብረተሰቦች ባሕላት ደገሞ ለልመና-ምፅዋት በጎ አመለካከትና ተቀባይነት ሲቸሯቸው ይስተዋላል። ይህ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር ባሕል (እምነትና አመለካከትን ጨምሮ) የሚጫወተው ሚና መኖር እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ውስን መሆኑን፤ የምጣኔ ሀብት ጫና ግን ወሳኝ መሆኑን ነው።

## 5. የልመና-ምፅዋት አመጣጥና ዕድገት

ለአገራችን ኢትዮጵያ ተፈጥሯዊ፣ ኅብረተሰባዊና ግለሰባዊ ችግሮቿ በተለያዩ መንገድና ደረጃ እየተዳመሩ በተለያዩ ጊዜያት ከህዝቧ አነስተኛ የማይባለውን ክፍል ሲያጠቁና ወደ ከፍተኛ የድህነት አዘቅት ሲያወርዱ ኖረዋል። በክብት ወረርሺኝ ሳቢያ የእርሻ በሬ ጠፍቶ መሬት ጦም ሲያድር፣ መሬቱ ይታረስና

ዝናብ ሲጠፋ፣ የዝናብ ወቅትን ያለመጠበቅ ወቅቱንም ቢጠብቅ በረዶ ሲያስከትል፣ ይህን ሁሉ ያመለጠውን ቡቃያ ደግሞ ዋግ ሲመታው፣ ያፈራውን ደግሞ ተምችና አንበጣ ሲቀባበሉት፣ ከተወቃው ላይ የባለጉልቶቹ ወኪሎች አስራት ሲያነሱለት፣ ከዚያ ተርፎ ጎተራ የገባውን ነቀዝ ሲዘምትበት፣ የተጋገረውን ደግሞ ደሞዝ የለሹ ወታደር ሲሰራበት (ሲመደብበት) የኖረች አገር ናት::

በዛሬ ጊዜ በቀላሉ የሚወገዱ ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ሳያደርሱ በህክምና የሚድኑት በሽታዎች፣ እንዲሁም ዛሬ ብዙ መላ የሚበጅላቸው በአደጋና በጦርነት ሳቢያ የሚመጡ የአካል ጉድለቶች፣ በአካል ቅጣት መዘዝ የሚከሰቱትን ጨምሮ፤ ስፍር ቁጥር የሌለውን ህዝብ የመስራት ችሎታ ሲነሱት እንደኖሩ በሚገባ የተዘገበ ነው[2]:: በዚህም የተነሳ፣ የቀጥታ ተጠቂው ብቻ ሳይሆን የቤተሰብ አባላቱ ጭምር ተጠልፈው ወደ ድህነት አዘቅት እየወረዱ የደግ ዘመን ጥሪታቸውን አሟጠው ሲያበቁ የግዳቸውን ለልመና ይዳረጉ እንደነበር ይታወቃል::

ለልመና-ምፅዋት መዳረጉም ቢሆን መፅዋቾች ሲገኙ ሲገኝ ነበር:: እንዳሁኑ የአደጋ መከላከያ ኤጀንሲ፣ የዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ ዓለም አቀፋዊና አገር በቀል ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች በማይታወቁበት በዚያ ቀደም ባለው ጊዜ ለጋሽ የማግኘቱ ጉዳይ ፈታኝ ተግባር ነበር:: ለምሳሌ፣ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያን ሁኔታ የታዘቡ ፖርቱጋላዊ ጎብኝዎች ከአንበጣ ጥቃት ተከትሎ የሚከሰተውን የህዝቡን በልመና መሰማራትና የመፅዋቾችን ብርቅ መሆን እጅግ በሚያሳዝን አገላለፅ ዘግበውት ይነበባል[3]::

ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው፤ በአገራችን ልመና ይከሰትና ይኖር ዘንድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሁሌም ነበሩ፤ ምንም እንኳን ዛሬ በተወሰነ ደረጃ የተለወጡ ቢሆንም:: ባሁኑ ጊዜ፣ የአንበጣ መከላከያን ምስጋና ይድረሰውና ይህ ነው የሚባል የአንበጣ ወረርሺኝ አይከሰትም፤ ነገር ግን፣ እንደ አካባቢ ብክለት፣ በበቂ ያልታሰበባቸው የ«ልማት» እርምጃዎችና የህዝብ መብዛትንና የእርሻ መሬት ማነስን ተከትሎ የመጣው ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፈጣን የህዝብ ፍልሰት ዓይነት የዘመኑ ችግሮች የቀድሞዎቹን ስለተኳቸው፤ ልመናን በሚያስፋፉ ሁኔታዎች በኩል አሁንም እጥረት የለብንም::

ቀደም ባለው ጊዜ ችግሩ የለማኝ ሳይሆን የመፅዋቾች በበቂ ብዛትና በውስን አካባቢ አለመገኘት ነበር:: ኢትዮጵያ የገጠር ስልጣኔ ያየለባትና በከተሞች በኩል የተበደለች ሆና እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና የ20ኛው መባቻ ድረስ

---

[2] "Alvares was told … the stress of famines caused by hail, drought, and plagues of locusts was often exacerbated by plagues of a more insidious nature. Leprosy was commonplace. Disease and epidemics were rife… Alvares reported seeing 'more than 3,000 cripples, blind men, and lepers' gathered at a religious shrine near Axum, …" (John Reader 1998: 358-9).

[3] "This country was entirely covered with locusts… The people were going away from this country, and we found roads full of men, women, and children, on foot, and some in their arms, with their little bundles on their heads moving to a country where they might find provisions (it was a pitiful sight to see them) (Alvares in John Reader 1998: 358 እንደጠቀሰው).

እንደመቆየቷ፤ ትርጉም ያለው ልመና ሊካሄድባቸው የሚችሉ፤ወይም በቋሚነት ጥቂት ለማኞች እንኳን ሊያስተናግዱ የሚችሉ፣ ህዝብ ተሰብስቦ የሚገኝባቸው ቦታዎቿ (ፖይንትስ ኦፍ ኮንሰንትሬሽን ኦፍ ፒፕል) በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ — ከአድባራቱና ከታላላቅ መስጊዶች በስተቀር ማለት ነው። ለዚህ ነው እንግዲህ፣ ባጠቃላይ በበጎ ምግባር ላይ፣ በተለይ ደግሞ ታሞ፣ ተርቦና፣ ታርዞ፣ ወይም በጉዞው መጠጊያ አጥቶ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ ለሚለምን ሰው በመታደግ ላይ የሚያተኩሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ድርጅቶቻቸውን ለነዳያን መጠጊያ ሲያደርጉ የኖሩት[4]። በአጭሩ ይህ ሊሆን የቻለው በዚያን ጊዜ ምንም ሌላ አማራጭ ስላልነበረ ነው።

ከ19ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና ከ20ኛው መባቻ አንስቶ የማዕከላዊውን መንግስት መጠናከርና የግዛት መስፋፋት፣ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት መጠናከርና የውስጥና የውጭ ንግድ መስፋፋትን ተከትሎ ከተሞች በብዛት መቆርቆርና መስፋፋት ያዙ። አዳዲሶቹ ከተሞችም በቀጣይ ያድባራት መናኽሪያ ሆኑ፤ አንዳንድ ቀደምት አድባራትም ከአዳዲሶቹ ከተሞች ለአንዳንዶቹ እርሾ ሆኑ። ከዚህ ተያይዞ፣ ቀደም ሲል ወደ ልመና የገባውም ሆነ በአዲስ የደኸየው ሁሉ ወደ ከተሞቹ ጎረፈ። በከተሞቹ ላይ ማጎተሙን አሳረፋባቸው። በዚህ ሁኔታ የኢትዮጵያ ከተሞች ከልደታቸው ጀምሮ «የድሆች ከተሞች» ብቻ ሳይሆን «የድሆችና የለማኞች ከተሞች» ናቸው።

ስለዚህ የጊዜው ጥያቄ፤ እንዴት እነዚህን መጤ ለማኞች ከከተሞች ወደ መጡበት ገጠር እንመልሳቸው? ብቻ ሳይሆን፤ በዋናነት፣ በእንዴት ነው ይህን ከተሞቻችንን ከልመና አቆራኝቶ የያዘ ዕትብት ሰብዓዊነት በተላበሰ መንገድ የምንቆርጠው? እንዴት ነው የመረዳዳቱን የቆዬ ልምድ ዘመናዊ ሥርዓት የምናሲዘው የሚለው ይመስለኛል። መፍትሔዎችን በተመለከተ ዝቅ ብለን የምንመለስበት ይሆናል።

## 6. ልመና-ምፅዋትና ልማት

የመፍትሔ ሀሳቦችን ወደ መቃኘቱ ከመግባታችን በፊት፣ ለምን ልመና-ምፅዋት አሁን ባለበት መልኩ ሊቀጥል እንደማይችል፣ እንደማይገባ፣ ወይም እንደሌለበት አሳማኝ ምክንያቶችን አቅርበን ማሳዬት ይኖርብናል። «የታወቀ ነው» እያልን አደባብሰን ያለፍነው እንደሆነ ወደ መጨረሻችን በልመና መፍትሔ ሀሳቦች ላይ የምናደርገውን ውይይት መሠረት ስለሚያሳጣብን ወደዚሁ ወደ ልመናና ልማት ጉዳይ እናምራ።

ቀደም አድርገን አንዳንድ ተመራማሪዎች ልመናን እንደ *ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ተግባር* እንደሚያዩትና ሌሎች ደግሞ እንደ *ጊዚያዊ የችግር መቋቋሚያ ስልት* እንደሚገነዘቡት ገልፀናል። ሆኖም፣ ልመና እሴት ከማምረት ጋርም ሆነ ከልውውጥ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው እንቅስቃሴ ነው። በመሆኑም፣ እሴት

[4] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በምፅዋት ላይ ስላላት አቋምና፤ የ19ኛው ምዕተ ዓመት አውሮፓውያን የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን በሱና በልማት ግንኙነት ላይ ይሰነዝሩት የነበረውን ነቀፌታ በተመለከተ፣ የዴቪድ ቻፕልንና የአሁኑን ጸሐፊ ትችቶች (በ ቻፕል 1986 እና የራስወርቅ አድማሴ 2010) ይመልከቱ።

ከማምረትና ከመለዋወጥ አንፃር ለኅብረተሰቡ የሚያበረክተው ምንም የኢኮኖሚ ጥቅም የለም፤ ቁጥሩ የማይናቅ ህዝብን ከማምረትና አገልግሎት ከመስጠት ተግባር ውጭ በማድረግ ያገር ኢኮኖሚን ይጎዳል እንጅ።

በሌላ በኩል ግን፣ ልመና በፍጆታ-ቁሳቁሶች ድልድል በኩል ይህ ነው የማይባል ልዩነት ያመጣል። በምርትና በልውውጥ ውስጥ ምንም ቦታ የሌላቸውና በዚህም የተነሳ ለኢኮኖሚያዊም ሆነ ለሕጋዊ ይገባኛል ባይነት ያልበቁና ያልታደሉ ሰዎች ቢያንስ ለዕለት ጉርስና ልብስ የሚያስፈልጓቸውን የፍጆታ ቁሳቁሶች እንዲያገኙ በር ይከፍትላቸዋል። በዚህም ሁኔታ አነስተኛ ግምት የማይሰጠው የነፍስ ማዳን ሚና ይጫወታል። የልመና ይህ ነው የሚባል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ካለ ይኸና ይኸ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን ታዲያ በብዙ ህብረተሰባዊ ኪሳራዎች ታጅቦ የሚመጣ ስለሆነ በተሻለ አማራጭ ቢተካ የሚያጐድል ሳይሆን፣ የሚረዳ ነው።

አሁንም ከሌላ አንፃር፣ ልመና በኢኮኖሚ ህይወት፣ ዕድገትና ልማት ላይ ተጨማሪ አሉታዊ ጫና ያደርጋል። የልመና ኑሮ በተፈጥሮው ቁጠባ-ተኮር ነው። በአንድ በኩል የተገኘውን ያህልና ሁሉን ዓይነት ለዕለት ኑሮ አስፈላጊ የፍጆታ ቁሳቁሶች በመሰብሰብ ላይ የተመሠረተ ተግባር ሲሆን፤ በሌላ በኩል ሁልጊዜ መራቆት፣ መጎሳቆል፣ አዳፋ ሆኖ መገኘትና በገላጣ ስፍራ መውደቅ የ «ሥራው» ተፈላጊና ወሳኝ ጠባይ እንደመሆኑ፤ ልመና ገንዘብ ማውጣትን ብሎም ግብይትን ይፃረራል።

በተጨማሪ፣ ከላይ የገለፅነው የልመና ጠባይ እንደሚጠቁመው፣ ለማኝ ሰው የሚተዳደረው ከመፅዋቹ ህዝብ በቀጥታ በሚቸረው ገንዘብ፣ ምግብና፣ እንደ አልባሳት ባሉ ሌሎች ቁሳቁሶች ብቻ አይደለም። እንደ ጎዳናዎች፣ አደባባዮች፣ መናፈሻዎች፣ ክፍት ቦታዎች፣ የውሃ ምንጮች፣ የዝናብ ውሃ ማስተላለፊያ ቦዮችና ፉካዎች፣ የፀሎት ቦታዎች፣ የቀብር ስፍራዎችና መቃብር ቤቶች የመሳሰሉትን የጠቅላላ ኅብረተሰቡ ይዞታ የሆኑ ንብረቶችን (ፓብሊክ ጉድስ) ያለ ምንም ክፍያና መዋጮ ለመለመኛው፣ ለመኖሪያው፣ ለመፀዳጃውና ለመዝናኛው ይገለገልባቸዋል። እነዚህን ንብረቶች የማዘጋጀቱ፣ የማስተዳደሩ፣ የመጠበቁ፣ ጠብቆ የማቆየቱና የማደሱ ኃላፊነትና ወጭ የጠቅላላ ኅብረተሰቡ ሲሆን ተጠቃሚነቱ ብቻ ወደ ለማኙ ይፈሳል። ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት፣ «በነፃ ይጋልባቸዋል»። ይህ ልብ ሳይባል፣ ሳይሰላና፣ ሳይከፈል «ወጭው የሚቀር ክፍያ» ደግሞ ማንንም ሳይነካና ምንም ሳያጎል በአየር ላይ ተንሳፎ የሚቀር ሳይሆን ጠቅላላ ህብረተሰቡ እያስተናገደው የሚኖር ኪሳራ ነው። «ነፃ ግልቢያ» በለማኞች ላይ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑ የታወቀ ቢሆንም፣ በጠቅላላ የህብረተሰቡ ይዞታዎች ላይ መካሄዱ ከመለያ ጠባዮቹ አንዱ የሆነው ልመና፣ በዚህ አኳያ እያደረሰ ያለው የተለየ ኪሳራና የሚጫወትው ልማት ጎታች ሚና አሌ የማይባል ነው።

ከዚህም ባለፈ፣ ልመና የሀገራችንን ሰብዓዊ ዕድገት (ሂዩማን ዴቬሎፕመንት) በተመለከተ የማይናቅ አሉታዊ ጫና እያሳደረ ይገኛል። አንደኛ፣ የመሥራት ችሎታ ያላቸውን ወይንም ሊኖራቸው ይችል የነበረ ብዙ ዜጎችን ሥራ ፈትና ሙያ አልባ ያደርጋል። በተለይ ሕፃናትንና ወጣቶችን በተመለከተ፣ የጎዳናው

ብልጭልጭና ግርግር ተጨምሮበት ይቅርና ብቻውንም ሆኖ ሱስ የመሆን ችሎታ ያለው የጎዳና ልመና፤ በጥረትና ግረት ከሚታጀበው የሥራ ኑሮ የተሻለ አማራጭ ሆኖ እየሳበ ከልማት ዓለም ውጭ እያደረጋቸው ይገኛል:: ሁለተኛ፣ ልመና ከፍተኛ ቁጥር እንዳለው የሚነገርለትን የለማኝ ማህበረሰብ በመስፋፋት ላይ ያሉት የትምህርት፣ ጤና፣ ንፁህ ውሃ፣ ሃይጅን፣ ወዘተ... አገልግሎቶች ተጠቃሚ በመሆን ፋንታ ከዳር ቆሞ እንዲታለፍ አድርጎታል:: ሦስተኛ፤ ቤተሰብ የልጆች መወለጃ ብቻ ሳይሆኑ ልጆች አስፈላጊ የሆኑ ችሎታዎችን እየጨበጡ ተኮትኩተው በማደግ የተሙዋሉና ብቁ የህብረተሰብ አባላት የሚሆኑበት ሥርዓት መሆን ሲገባው፤ ልመና ግን፣ የለማኙን ቤተሰብ ልጆችን የልመና ስራው መጠቀሚያ አድርጎ በማኖር ከህፃናቱ ሰብዓዊ መብት መደፈር ባሻገር የአገርን ሰብዓዊ ልማትና ብሎም ኅብረተሰባዊ ልማትን በተመለከተ አፍራሽ ሚና እየተጫወተ ይገኛል:: አንዳንድ ለማኞችም የራሳቸው ልጆች አልበቃ ብሏቸው የሌሎችን እንደሚፈነግሉና ይህም ተግባር ወደ «ቢዝነስ» ደረጃ ከፍ ከማለቱ የተነሳ አንዱ የብዙ ሕፃናት ባለቤት የሆነ «ልመናዊ ባለሀብት» እነዚህ ልጆች እኮ ለኔ ሚኒባሶቼ ናቸው እስከ ማለት መድረሱን አድምጠናል (ሃምሳ ሎሚ - ልመና የአደባባይ ምስጢራችን)::

ለሀገራችን ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል የሚባለው የቱሪዝም ኢንዱስትሪም በበኩሉ የተለዩ የልመና ሰለባ ነው:: እንደ ዕድል ሆኖ፣ አብዛኛ ዎቹ የሀገራችን ዋነኛ የቱሪስት መስህቦች የሆኑ ታሪካዊ ቦታዎች፣ ከነሱም ውስጥ በቁጥር የሚበልጡት ህዝብ በብዛት በሚኖርባቸው ከተሞች የሚገኙና የህዝብ የማምለኪያ ቦታዎች ናቸው:: እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ቀደም ብለን ባወሳነው የአድባራት፣ የከተሞችና የልመና ታሪካዊና ኅብረተሰባዊ ትስስር የተነሳ፤ በቀጥታ የልመና ማዕከሎች ናቸው:: ይህ ሳያንስ፣ ቱሪዝም ራሱ ለማኞችን ጨምሮ የጠቅላላው «የጎዳና ተዳዳሪ» ማግኔት እንደመሆኑ፣ ብርቅዬ የቱሪስት መስህቦቻችን ለማኙንም ስበው ያመጣሉ:: በዚህም ነው ንግዲህ የአገራችን ቀዳሚ የቱሪስት መስህብነቱ የሚነገርለት ላሊበላ «የልመና ዋና ከተማ» የሚል የፋተታ ስያሜ ሊቀዳጅ የበቃው:: በዚህ መንገድ ነው ልመና የአገሪቱን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ አንቆ ሙጭጭ በማለት አላራምድ ያለው::

እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ጉዳዮች፣ ልመና በአገራችን ልማት ላይ እያሳደረ ያለውን አሉታዊ ጫና በሙሉ አይሸፍኑም:: ለምሳሌ፣ የልመናንና የወንጀልን መተሳሰርና ወንጀል በተራው በልማት ላይ የሚያሳድረውን ጫና አልዳሰስንም:: እንደዚሁ ያለፍናቸው ሌሎች ሌሎችም እንዳሉ እናምናለን:: የፈለግነው ዋና ዋናዎቹን ትስስሮች በማንሳት ልመና የልማት ማነቆ መሆኑን በማያሻማ አኳኋን ማሳዬት ነበር:: ይህም በበቂ የተከናወነ ስለሚመስለን፣ ወደ መፍትሔው እናልፋለን::

# 7. ልመናን-ምፅዋትን ማስቀረት ወይም መልክ ለማስያዝ የተሰነዘሩ የመፍትሔ ሀሳቦች፣ እስካሁን የተደረጉ ሙከራዎችና የታቀዱ እርምጃዎች

ልመናን የማስቀረት ሀሳብ ሀ-ብሎ መነሳት የጀመረው እጅግ ቀደም ብሎ ነው:: የመጀመሪያው መረጃ ያገኘንለት የመፍትሄ ሃሳብ የመነጨውም እ.ኤ.አ. በ 1911 ዓመተ ምህረት ሊቁ ጥዑመልሳን ካሣ በሚባሉ በጊዜው የቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አለቃና መምህር ነበር:: የመፍትሔ ሀሳባቸውም ዋና ጭብጦች የሚከተሉት ነበሩ:- 1/ በአደባባይ ተንቀሳቅሰው የሚለምኑ ለማኞች የተወሰነ የመንቀሳቀስ ችሎታ ያላቸው እንደመሆናቸው፣ በርካታ የባሰባቸው አቅመ ደካሞች በየስርቻው ወድቀው ለምፅዋት ሳይበቁ ስለሚቀሩ፤ 2/ ለማኞች እጅግ አስፈላጊያቸው የሆነውን ህክምና ስለማያገኙት፣ተዘዋዋሪ ልመናም ተላላፊ በሽታዎችን ስለሚያዛምት፤ 3/ ልመና በአገር ጎብኚዎች ዘንድ አገርን ስለሚያስነቅፍ፤ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዱ:-1/ ለማኞች እየተመረመሩና እንደየበሽታቸውና ሁኔታቸው እየተለዩ ለዚሁ ሲባል በሚሰሩ ቤቶች ይግቡ፤ 2/ በዚያም ህክምና እየተሰጣቸው ይጦሩ፤ 3/ ከነሱም ውስጥ ስራ መስራት ለሚችሉት በዚያው ተቋም ውስጥ ይስሩ፤ 4/ ልጆቻቸውም ትምህርት እንዲያገኙ ይደረግ፤ 5/ ይህን ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጭ ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን መንግሥት አቅም ሊያንሰው ስለሚችል፣ ሕዝብ ገንዘብ እያዋጣ ይርዳ፣ ቤተክህነትም ትደጉም (ሊቀ ጥዑመልሳን ካሣ 1911 እ.ኤ.አ.)::

ይህ ሀሳብ በሥራ ላይ ይውል ዘንድ የተደረገ ሙከራ መኖር አለመኖሩን የሚያሳይ ምንም ፍንጭ አላገኘንም:: ሆኖም 92 ዓመታት ያስቆጠረው ዝርዝር የተግባር መመሪያ ረቂቅ፤ ባንድ በኩል የልመና ችግር ምን ያህል አሳሳቢ ሆኖ እንደኖረ ሲያመለክተን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ በመደረግ ላይ ላለው መፍትሔ የመሻት ጥረትና በመከናወን ላይ ላሉት ሙከራዎች አቅጣጫ በመጠቆም ይረዳል::

ቀረብ ባለው ጊዜ፣ ልመናን በተመለከተ በመንግሥት የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም የተቀናጁና በሀሳብ ዳብረው የተጀመሩ አይመስሉም:: በ1940ዎቹ፣ በ50ዎቹና በ60ዎቹ በመንግሥት የተወሰዱት እርምጃዎች ሁለት ዓይነት ነበሩ:: አንደኛው ከለማኞች የአካል ጉዳተኞች ያልሆኑትን ጨምሮ ማንኛውንም ሥራ የፈታ ሰው በግዴታ ወደ አዶላ የወርቅ ማዕድን ቁፈራ የማጋዝ ፕሮግራም ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ለማኞችን ሰብስቦ በአንድ ቦታ (በተለይ ሾላ አከባቢ) በማኖር ከተማውን «ለማፅዳት» የተደረገ ሙከራ ነበር:: ይህ የኋለኛው በበቂ ያልታሰበበትና ምናልባትም ከአዲስ አበባ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቀመጫ ከመሆን ጋር ተያይዞ የመጣ ግብታዊ እርምጃ ይመስላል:: በመጨረሻም ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አመች የተቃውሞ ኢላማ ሆኖ ሳያምርበት ከስሞ ቀርቷል::

ከዚያ ተከትሎ የመጣውን ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ አብዮት የፈጠረው እንደ ልመና ያሉ ኅብረተሰባዊ ችግሮችን በአብዮቱ ሂደት እንደሚወገዱ አድርጎ የማየት አስተሳሰብ ዓይነተኛ ያደርገዋል። ሆኖም በደርግ አገዛዝ ዘመን ከፍተኛ ወጭ የተደረገባቸውና ብዙ ተስፋ የተጣለባቸው አንድ አንድ የአካል ጉዳተኞችን ስልጠና የመስጠትና ሥራ የማስያዝ (ጃንጥላ ፋብሪካ)፣ ሌሎችን ደግሞ በጡረታ ቤት የማኖር (ጀግኖች አምባ)፣ አሳዳጊ አልባ የሆኑትን ደግሞ ወደ ማሳደጊያ ቤት ማስገባት (ሕፃናት አምባ) ሙከራዎች ተደርገዋል። ይሁንና እነዚህ እርምጃዎች በመሰረቱ በጦርነት ጉዳተኛ ወታደሮችና በወታደር ልጆች ላይ ያተኮሩ እንጅ በቀጥታ በለማኞችና በልመና ላይ ያነጣጠሩ አልነበሩም።

የ1976/77ቱን ረሃብ የተከተለው ወቅት መንግሥታዊ ያልሆኑ ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች በብዛት የተፈጠሩበት ጊዜ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ወደ ልመና ሊያመሩ ይችሉ የነበሩ የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንንና አሳዳጊ አልባ ሕፃናትን በመርዳት ላይ ሲሰሩ እጅግ ጥቂቶቹ ደግሞ በተለይ በለማኞች ላይ መስራት ጀመሩ። ከነዚህ ውስጥ የጎላ ስራ በማከናወን ታዋቂነትን ያተረፈው ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ. በ1971 የተመሰረተው «ተስፋ ድርጅት» ሲሆን ከሌሎች በርካታ ተግባሮቹ በተጓዳኝ ለአያሌ አመታት ሲያካሂደው የነበረው የገንዘብ ምፅዋትን በምግብ-ትኬት ለመተካት የሚያስችል አሰራሩ ከአርአስታችን አንፃር ተጠቃሽ ነው።

ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት፤ የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን የሚመለከቱ በርካታ ቁልፍ ብሄራዊ የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተው እንደታወጁ ይታወቀል። ከነዚህም ሰነዶች ውስጥ በዋነኛነት ተጠቃሾቹ፤ የ1989ኙ *የማኅበራዊ ደኅንነት ልማት ፖሊሲ* (ወይም *ልማታዊ የማኅበራዊ ደኅንነት ፖሊሲ*)፤ እንዲሁም፣ የ1993ቱ *የአካል ጉዳተኞች ተሐድሶ ብሔራዊ የድርጊት መርሐ-ግብር*፤ እና *የ1998-2007 ብሔራዊ የአረጋውያን የድርጊት መርሐ-ግብር* ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ፤ ያለፈው *የ1998-2002 ፈጣንና ዘላቂ የልማት ዕቅድና* በአሁኑ ወቅት በመተግበር ላይ ያለው *የ2003-2007 የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ* ውስጥ፤ በሀገሪቱ ሰፍኖ የኖረውን የድህነት መጠን መቀነስ፣ የሁሉንም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ማሻሻልና፣ በሀገር ልማት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት በአላማነት ተቀምጠዋል። ከፖሊሲና ከዕቅድ ሰነዶች ባሻገር ደግሞ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑና በማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱና ልዩ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ለይ የሚያተኩሩ የተለያዩ ፕሮግራሞችና እርምጃዎች እንዳሉ ይታወቃል። ያም ሆኖ ታዲያ፤ እነዚህ ሰነዶችና ፕሮግራሞች የልመና ምንጭ የሆነውን ድህነትን በመቀነስና ልዩ ድጋፍ ካልተደረገላቸው በስተቀር ለልመና የመዳረግ ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነውን የኅብረተሰብ ክፍሎች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታን በማሻሻል ላይ እንጅ፤ ቀድመው ወደ ልመና የወረዱትን ዜጎች ከዚህ አስከፊ አረንቋ በማውጣቱ ላይ በቀጥታ አያተኩሩም። በተለይም፤ በአካልና በአዕምሮ ችግር የተነሳ ምንም የቤተሰብ ወይም የማኅበረሰብ ድጋፍ ለሌላቸውና፣ ተቋማዊ እንክብካቤ ሊዘጋጅላቸው የሚገባ ሰዎችን በተመለከተ የሚሉት የለም።

ከደርግ አገዛዝ ዘመን ማብቂያ በኋላ በቀጥታ ልመናን በተመለከተ ከተወሰዱ መንግሥታዊ እርምጃዎች ቀዳሚ የሆነው በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና በጣሊያን ትብብር ድርጅት እ.ኤ.አ. በ1986 ዓ.ም. ተጀምሮ የነበረው እርምጃ ነው (ሠማጉሚ/ር 1986)፡፡ ይሁንና፤ ይህም ቢሆን 13 መንግሥታዊ ድርጅቶችን ያቀፈ ብሔራዊ ኮሚቴ ለማቋቋም ከተደረገ ሙከራና ይህን አስመልክቶ ከተካሄደ አንድ ሴሚናር ያለፈ ስኬት መቀዳጀቱን የሚጠቁም ምንም መረጃ አላገኘንም፡፡

በ1990ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ላይ ልመናን በተመለከተ በአንዳንድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሚካሄዱ ይፋዊ ያልሆኑ ውይይቶች ላይ መረዳት እንደተቻለው ለማኞች የሚረዱበትና በቋሚ የሕዝብ መዋጮ የሚካሄድ ፈንድ በመፍጠር ልመናን የማስወገድ ሀሳብ ይንሸራሸር ጀመር፡፡ በአንድ ጋዜጣ በተደረገለት ቃለ መጠይቅ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም ይህንኑ ሀሳብ ሰንዝሮ እንደነበር ይታወሳል፡፡

የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ ደግሞ «ሃምሳ ሎሚ» በተሰኘው የቴሌቪዥን የውይይት መድረክ «ልመና፤ የአደባባይ ምሥጢራችን» የሚል ፕሮግራም ለአየር በቅቶ የታዳሚውን ትኩረት በመሳቡ በተጨማሪ ሁለት ጊዜ መተላለፉ ይታወሳል፡፡ በዚያ ፕሮግራም ላይ ከላይ የጠቀስነው ሀሳብ ዘርዘር ባለ መንገድ ቀርቦ ተንሸራሸረና ዳበረ፡፡ የሀሳቡም ይዘት ባጭሩ፡- 1/ የአደባባይ ልመና በኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ስለማይጠፋና እንዲያውም ለልማት ማነቆ ስለሚሆን የቆየውን የግለሰብ ለግለሰብ የፊት ለፊት ልመና-ምፅዋትን በዘመናዊና ማኅበራዊ ሥርዓት መተካት ያስፈልጋል፤ 2/ ልመናን በሕግ የማገድ እርምጃ ከመወሰዱ አስቀድሞም እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን በልመና የተሰማሩ ዜጎች የሚንከባከብ ተቋም መደራጀት ይኖርበታል፤ 3/ ለዚህም፣ መንግሥት፣ የሲቪል ማኅበረሰቡ አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና፣ ግለሰብ ዜጋው ሁሉ በሚሳተፍበት የቋሚ መዋጮ ስርዓት የሚሚላና ለነሱ ተጠያቂ በሆነ ቦርድ የሚመራ ብሄራዊ ሙዳይ (ናሽናል ፈንድ) መፍጠር ያሻል የሚል ነበር፡፡

የፕሮግራሙ መቀረፅ እንዳበቃ፣ ተሳታፊዎች ከተያዘው መርሐ ግብር ወጣ ያለ ማሳሰቢያ ለፕሮግራሙ መሪዎች አቀረቡ፡፡ ከመበተናችን በፊት ይህንን የውይይታችንን ጭብጥ በመወያየት ብቻ ፈሶ እንዳይቀር የተግባር መነሻ ሊያደርገው የሚችል ማስሪያ እናብጅለት ሲሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ከቴሌቪዥን ቀረፃው ውጭ የሆነ አጭር ውይይት ተደርጎ ሲያበቃ፤ እዚያው ለነበሩት የሠራተኛና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠሪዎች፣ በዚህ ሀሳብ ላይ ተመስርተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ማዕከል ያደረገና የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች ያሳተፈ አንድ ዓይነት የተግባር እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ አደራ ሰጥተዋቸው ተበተኑ፡፡

ከዚያ ወዲህ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጉዳዩ ባለቤት እንደመሆኑ፤ የተለያዩ ተቋማት በማድረግ ላይ ያሉትን እንቅስቃሴና እንደ ሃምሳ-ሎሚው ያሉ ወይይቶች የጫሩትን ተነሳሽነት በመገንዘብ፤ ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዲቬሎፕመንት አሶሴሽን የተባለ «ከትግራይ ክልል ወደ አዲስ አበባ በመምጣት

... በልመና ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ 22,000 ዜጎችን ወደ ቀያቸው (ትግራይ ክልል) በመመለስ አኩሪ ተግባር» ለመፈፀም የበቃ ድርጅትን አርአያ በመከተል፤ መንግሥታዊ አካላትን፣ ባለድርሻ የሲቪል ማኅበረሰብ አባላትን፣ የግል ክፍለ ኢኮኖሚውን አባላትና፣ ለታሰበው እርምጃ ቀና አመለካከት ያላቸውን ሌሎች ግለሰቦች በማሰባሰብ፣ *በልመና የተሰማሩ ዜጎች ማቋቋሚያ ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ* በሚያዝያ 2000 ዓ.ም. እንዲመሰረት ማድረጉን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያሰራጨው የመወያያ ሰነድና አንዳንድ የጋዜጣ ዘገባዎች ይጠቁማሉ:: (ሠማጉሚ/ር 1999፣ 2-3)

በርከት ባሉ ኮሚቴዎቹ አማካይነት የተለያዩ ተግባራቱን የሚያከናወነው ብሔራዊ ኮሚቴ የአጭር ጊዜ ዕቅዶች የሚከተሉት ናቸው (ሠማጉሚ/ር 1999)::

ሀ/ ልመናን ለመዋጋት የሚያስችል አገር አቀፋዊና ክልላዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋም፤

ለ/ ልመና ሰብዓዊ ክብርን የሚቀንስ ሥራ-ጠልነትነት የሚያንፀባርቅ ጎጅና ጎታች ልማድ መሆኑንና ሊደገፍ እንደማይገባው ቅስቀሳ ማድረግ፤

ሐ/ በአሁኑ ጊዜ በመዲናችን ውስጥ የሚገኙትን ለማኞች ወደ መጡበት ክልሎች በማጓጓዝ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አስፈላጊውን ጊዜያዊ የማቆያ መጠለያ ማዘጋጀት፤

መ/ የተሰባሰቡትን ለምኖ አዳሪዎች እንደተጨባጭ ሁኔታቸው ከህብረተሰቡ ጋር ማቀላቀል፣ አስፈላጊ የሆነውን ሀብት ማሰባሰብና ሊሰማሩ የሚችሉበትን መስክ መለየት፤

ሠ/ ልመናን ሽፋን በማድረግ ምርታማ ሳይሆኑ የቀሩትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደየክልላቸው በማጓጓዝ በልማት ስራ ላይ ማሰማራት፤

ረ/ አቅመ ደካማና መሥራት የማይችሉ ዜጎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ሆነው ዘላቂ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፤

የኮሚቴው የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅዶች ደግሞ እንደሚከተለው ቀርበዋል (ሠማጉሚ/ር 1999: 9)::

ሀ/ በራስ የመተማመን መንፈስና ሠርቶ የማደር ፍላጎት በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርፅ በየመድረኩ ተከታታይ ትምህርት መስጠት፤

ለ/ የልመናን መንስዔ፣ ጥልቀት፣ ስፋትና ገፅታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማጥናት፤

ሐ/ ጥናቱን መሠረት በማድረግ ከልማቱ ጋር የተቀናጁ፣ ቤተሰብንና ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረጉ ልማታዊ የመከላከልና የማቋቋሚያ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ የተለያየ ገቢ ማፈላለግና የሚተገበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

መ/ ልመናን ከምንጩ ለማድረቅ ልማትን ማስፋፋት፣ ቤተሰብንና ኅብረተሰቡን ማጠናከርና ችግሩ እንዲፈታ ማስቻል፤

*በልመና የተሰማሩ ዜጎች ማቋቋሚያ ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ የምስረታ* እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ከ1999/2000 ዓ.ም. ወዲህም አንዳንድ ተጨማሪ እርምጃዎች ተወስደዋል፤ እየተወሰዱም ነው:: ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን መጥቀስ ይቻላል::

ሀ/ በሠራተኛና በማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ሰንሻይን ኮንስትራክሽን ትብብር፣ በዶ/ር ሚናስ ሕሩይ ሰፊ ጥናት ተካሂዶ "A Proposal for the Introduction of the Social Development Fund of Ethiopia" (September 2009) የተሰኘ ረቂቅ ጽሑፍ ለሚመለከታቸው ወገኖች ተሰራጭቶ ውይይት በመጠበቅ ላይ ነው::

ለ/ ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዲቬሎፕመንት አሶሴሽን በበኩሉ ሲያካሂደው የቆየውን የመልሶ ማቋቋም ስራ በሰፊው እያካሄደ ይገኛል:: (ERDA Undated, *The Reporter* Saturday 10 April 2010; *Addis Fortune*, 25 April 2010)

ሐ/ በላሊበላ ከተማ በከተማው መስተዳድር፣ በቤተክህነትና፣ በሌሎች ባለድርሻዎች አማካይነት በተወሰደ ቀጣይነት ያለው እርምጃ ለማኞች ሥርዓት ያለው መጠለያ አግኝተው ከተማዋም «የልመና ዋና ከተማ» ከሚለው ስያሜ ተላቃለች::

መ/ በአዲስ አበባ ከተማም አስተዳደሩ በያዝነው ዓመት በስራ ላይ ያዋለውን የትራፊክ ደንብ ተከትሎ ከመኪና ሆኖ ምፅዋት መስጠት ተከልክሏል::

ከነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት የተወሰዱ ዕርምጃዎች በተጨማሪ ሌሎችም ሙከራዎችና ገና ያልተፈተሹ የመፍትሔ ሀሳቦችም ስላሉ፣ ዋና ዋና የሆኑትን ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ አጠቃለን አቅርበናቸዋል::

ልመናን-ምፅዋትን ለማስቀረት/ለማሻሻል የተደረጉ ሙከራዎችና
የቀረቡ ሀሳቦች ማጠቃለያ ሠንጠረዥ

| *የመፍትሔ ዓይነቶች* | *የተደረጉ ሙከራዎችና* (በሀሳብ ደረጃ ብቻ ያሉ) |
|---|---|
| ድጋፍ የሚያሻቸውን ለይቶ ማውጣት ፤ | 1. ኤልሻዳይ - ትግራይ (ሌሎች ክልሎች)<br>2. የላሊበላ ከተማ አስተዳደርና ባለድርሻዎች ፕሮጀክት |
| ወደመጡበት መልሶ በዚያ ማቋቋም፤ | ኤልሻዳይ - ትግራይ (ሌሎች ክልሎች) |
| በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዳሉ መርዳት፤ | (ሠማጉሚ/ር - በልመና የተሰማሩ ዜጎች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራም የውይይት መነሻ ሰነድ) |

| | |
|---|---|
| በተለየ ቦታ በመሰብሰብ መርዳት፤ | (በ«ሃምሳ ሎሚ» የኢቲቪ ውይይት መድረክ «ልመና የአደባባይ ምሥጢራችን» የቀረበ) |
| የገንዘብ ምፅዋትን በምግብ ትኬት መተካት | የተስፋ ድርጅት ፕሮግራም (የተቋረጠ?) |
| ቋሚ የምግብ እርዳታ የሚያገኙበትን ማደራጀት፤ | 1. የላሊበላ ከተማ አስተዳደርና ባለድርሻዎች ፕሮጀክት<br>2. የባህር ዳር ከተማ ሠማት ቢሮ የፍተሻ እርምጃ (የተቋረጠ) |
| ከመኪና ምፅዋት መስጠትን መከልከል ፤ | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ደንብ |
| ልመናን በህግ መከልከል፤ | የላሊበላ ከተማ አስተዳደርና ባለድርሻዎች ፕሮጀክት |

*ማስታወሹ- ሙከራዎቹ በደመቁ ፊደላት የተፃፉት ሲሆኑ ከቅንፍ ውጭ፣ በሃሳብ ደረጃ ብቻ ያሉት ደግሞ በመደበኛ ፊደላትና በቅንፎች ውስጥ በመደረግ መለየታቸውን ያስተውሉ።*

ቀደም ብለን እንዳየነው ደግሞ፣ በአገራችን የተለያዩ የልመናና የለማኝ ዓይነቶች በመገኘታቸው፤ እነዚህ የተለያዩት የልመናና የለማኝ ዓይነቶች የሚፈጥሯቸውን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች አርክቶና የሚያስነሷቸውን ፈተናዎች አሸንፎ የሰመረ ተግባር ለማከናዎን ከተፈለገ፤ ከሁሉ አስቀድሞ ለሁሉም ዓይነት የልመና ሁኔታዎች መፍቻ የሚበጅ አንድና አንድ ብቻ ተዓምራዊ ቁልፍ ሊኖር እንደማይችልና እንደሌለ መገንዘብ ይኖርብናል። ለምሳሌ በአገራችን በኢትዮጵያ በርካታ የተቸገሩ የማኅበረሰብ አባሎች ወደ ልመና እንዳይገቡ የሚያደርጉ የተለያዩ የመረዳጃ ነባር ልማዶችና ሥርዓቶች በየአካባቢው እንደመኖራቸው፣ ለነዚህም ቁብ ሰጥቶ የለውጡ ግብአቶች ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህን ሁሉ ማድረግ የሚቻለንና ወደ ዋና ግባችን የምንደርሰውም በርግጥ በተለያዩ መንገዶች ተጉዘን እንጅ በአንድ አማራጭ-የለሽ አውራ ጎዳና በመጠርነፍ አለመሆኑን መቀበል አለብን። ስለዚህም ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ ያቀፋቸውና ሌሎችም የተሞከሩና ገና በሀሳብ ደረጃ ብቻ የሚገኙ መፍትሔዎች፣ ሁሉም፣ በተለያየ ደረጃና ለተለያየ ሁኔታ ጠቃሚነት ሊኖራቸው እንደሚችል ተቀብለን እንደየ አግባብነታቸው ለወደፊቱ እርምጃችን ግብአት በማድረግ ልንገለገልባቸው ይገባል።

ይህንንም ስናደርግ፣ አስቀድመን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊነሱ የሚችሉ ስጋቶችን ትክክለኛ ግንዛቤ በሚያስጨብጡ ውይይቶች አማካይነት ማስወገድ ይኖርብናል። ለምሳሌ፣ በአንዳንድ ሃይማኖቶች ዘንድ ምፅዋት ከሃይማኖታዊ ተግባርና ግዴታ አንዱ እንደመሆኑ፣ ምፅዋትን ከልመና ጋር ማያያዝና አብረው እንዲከስሙ መሞከሩ ችግር ሊጋብዝ ይችላል የሚል ተገቢ የሆነ ስጋት አለ። ለዚህ ስጋት ማስወገጃው አጭር ማብራሪያ ነው። ከየአቅጣጫው በመቅረብ ላይ ያሉት

የልመና-ምፅዋት የመፍትሔ ሀሳቦች፣ በጎ አድራጊዎች ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዳይለግሱ የሚከለክሉ ሳይሆኑ፣ የምፅወታውንና የዕርዳታውን አተገባበር ይበልጥ ሰብዓዊ፣ ይበልጥ ጠቃሚና፣ ይበልጥ ልማታዊ በሚያደርግ ሥርዓት ለመተካት የተሰነዘሩ ናቸው፡፡ በተጨማሪ፣ ይህ ዓይነቱ መሻሻል የመመፅወትን ሃይማኖታዊ ግዴታ መልክ በያዘ መንገድና ከፍ ባለ ደረጃ ለመወጣት የሚያስችል እንጅ በሩን የሚዘጋ እንዳልሆነ የሌሎችን አገሮች ተሞክሮዎች በመጠቃቀስ በይበልጥ ማሳመንና የዚህን ሰብዓዊና ታዳጊ ለውጥ ደጋፊዎች ማበራከት ይቻላል፡፡

ሌላም ከፀጥታና የህዝብ ደህንነት ጋር የተያያዘ ስጋት ይደመጣል - ልመና ከቀረ ለወንጀል ድርጊት ይበልጥ አመች የሆነ ሁኔታ አይፈጠርም ወይ በሚል መነሻ፡፡ ለዚህም መልሱ አጭር ነው፡፡ እርግጥ የሚወሰደው እርምጃ፣ ለዘመናት ያገኘ ውንና ያጣውን የኅብረተሰብ ክፍል በሰብዓዊ ርህራሄ ላይ በተመሠረተ ፈቃደኝነት አስተሳስሮ የኖረውን የልመና-ምፅዋት ግንኙነት ያለበቂ ዝግጅትና ያለምንም መተኪያ የማቋረጥ ጉዳይ ከሆነ ወንጀልን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኅብረተሰባዊ ቀውሶችን ጭምር ሊፈጥር ወይንም ሊያባብስ ይችላል፡፡ ከላይ ከቀረበው ሰሌዳ በግልፅ የሚታየው ግን የተለየ ስዕል ነው፡፡ ተደጋጋፊ ሆነው በስራ ላይ እንዲውሉ እየታሰቡ ካሉት ስምንት እርምጃዎች ውስጥ ስድስቱ የሚመለከቱት በልመና ተሰማርተው ለቆዩት ወገኖች የሚደረጉ ዕርዳታዎችንና ድጋፎችን ሲሆን፣ ሁለቱ ብቻ ዕገዳን ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ሁኔታም፣ የእንቅስቃሴው ዓላማ ልመና-ምፅዋትን በሥርዓታዊና ተቋማዊ የማሻሻያ እርምጃዎች ሰብዓዊና ዘመናዊ መልክ ማስያዝ እንጅ ለማኞችን የኑሮ አማራጭ የማሳጣት አስገዳጅነት ወደ ወንጀል ድርጊት የሚገፋ እገዳ በመጣል ብቻ የተወሰነ «የያዘው ጣለው» እርምጃ አይደለም፡፡ ስለዚህም፣ የእርምጃው መወሰድ ወንጀልን የበለጠ የሚቀንስ እንጅ የሚያባብስ አይመስለንም፡፡

ሌሎች ደግሞ፤ ለምኖ መኖር ከሰው ልጆች መብት እንደ አንዱ፣ ለማኝነትም በዚህ ተግባር ለተሰማሩ ዜጎች እንደ የማንነት መገለጫቸው የማይታይበት ምንም ምክንያት ስለሌለ፣ ልመና-ምፅዋትን በተሻሻለ የዕርዳታ ሥርዓት መተካት የሰዎችን መብት ከመድፈር ይቆጠራል ሲሉ ተደምጧል - የ60ዎቹን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ተቃውሞ በማስተጋባት (በብርሃኑ ነጋ ቃለመጠይቅ ላይ በጊዜው የተሰነዘረ አንድን ትችት እናስታውስ)፡፡ ያሁኑ የመፍትሔ እንቅስቃሴ፤ ለማኞችን ሰብስቦ በአንድ ካምፕ በመዝጋት አዲስ አበባን ለመሪዎች ጉብኝት ለማፅዳት ከተወሰደው ከዚያ ግብታዊና ያልተቀናጀ እርምጃ ጋር በምንም አይገጥምም፤ «ድህነት ወንጀል አይደለም!» በሚል መፈክር ሥር የሚሰለፍ ተቃውሞም አይጋብዝም፡፡ ከናካቴው፣ የዚህ ዓይነቱ ትችት እጅግ መረን የሳተ በመሆኑ የለውጡን ተፈላጊነትና ወቅታዊነት የበለጠ ገሃድ በማወጣት ረገድ ይጠቅም እንደሁ እንጅ አይጎዳም፡፡

አሁንም ከሌላ አቅጣጫ በተደጋጋሚ የሚሰነዘር፣ አሁን ሰፍኖ የሚገኘውን የአደባባይ ልመና-ምፅዋትን በሥርዓታዊና ተቋማዊ መፍትሄዎች የማስወገድን ሃሳብ የሚያጣጥል ነቀፌታ አለ፡፡ የዚህኛው ትችት ፍሬ ሀሳብ፣ ልመና-ምፅዋት «የአመለካከትና የባሕርይ» ጉዳይ ስለሆነ ሊጠፋ የሚችለውም በለማኞቹና በመፅዋቾቹ ዘንድ «የአመለካከትና የባሕርይ ለውጥ» ሲመጣ ብቻ ስለሆነ ሌላ

ሌላውን ትተን ሰዎቹን በማስተማር አመለካከታቸውንና ባሕርያቸውን እንዲለውጡ እናድርግ የሚል ነው። እርግጥ ሰዎችን በማስተማር አመለካከታቸውንና ባሕርያቸውን እንዲለውጡ ማድረግ ከሌሎች እርምጃዎች ጋር በተጓዳኝ ሲካሄድ ጥቅም ይኖረዋል፤ ግን በብቸኝነት ለሁሉ ችግር መፍቻ ቁልፍ ተደርጎ የተወሰደ እንደሆነ ሌሎች ሥርዓታዊና ተቋማዊ እርምጃዎች በመንግሥት፣ በሲቪሉ ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ በሃይማኖት ተቋማትና፣ በሕዝብ ተሳትፎ እንዳይወሰዱ የመከላከል ጉዳይ ሆኖ ይቀራል።[5]

ልመና ከድህነት የሚመነጭ እንደመሆኑ፣ ድህነት ሲጠፋ ልመናም አብሮት ከሳሚ ነውና ልመናን የማስወገዱ ጉዳይ የተለየ ትኩረት ስለማያሻው እንዲህ ዓይነቱ የማሻሻል እንቅስቀሴ አላስፈላጊ ድካም ነው፤ የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፣ በሃምሳ ሎሚ - ልመና የአደባባይ ምሥጢራችን ውይይት ላይ በኢኮኖሚስት ተሳታፊዎች የተሰነዘረ)። ለዚህ መልሱ አጭር ነው። ልማትን በተመለከተ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የሚገኙትንና የህዝባቸውም አማካይ ገቢ የኛን ከሁለት መቶ እጅ በላይ የሚያጥፈውን አገሮች ጨምሮ ልመና በመላው ዓለም ሲካሄድ ይታያል። ስለዚህ ከልማቱ በተጓዳኝ በሱም ላይ ካልተዘመተበት በስተቀር፣ ገና ለገና ልማት ስለመጣ ብቻ ልመና ይቀንሳል እንጅ እንዳለ አይከስምም። ማኦ ዜዱንግ ለሌላ ጉዳይ እንዳለው «መጥረጊያው ባልደረሰበት አቧራው በራሱ ተኖ አይጠፋም!» ማለት ነው። እያልን ያለነውም፣ ድህነትና ልመና በዕርግጥ የተሳሰሩ ናቸውና በሁለቱም ላይ ጣምራ ዘመቻ ይካሄድባቸው፤ ድህነትን የማጥፋቱ ረዥም ጉዞ እስኪጠናቀቅ ደረስ በአንድ በኩል የሰብዓዊ ውርደትና ሰቆቃ መገለጫ በሌላ በኩል ደግሞ የልማት ነቀዝ የሆነውን ልመናን ላንድ አፍታም ቢሆን በዝምታ አንለፈው፣ ነው።

እናጠቃል። የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ ከልመና ለማላቀቅ ሰብዓዊነትን የተላበሰ፣ ቋሚና ሁሉ-አቀፍ የሆነ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ፣ የተረጅዎች ማቋቋሚያ፣ የአረጋውያን መጠሪያና፣ የሕፃናት ማሳደጊያን ያቀፈ ሥርዓትና የመተግበሪያ ተቋሞች ማቆም ያስፈልጋል። ይህንንም እርምጃ የዛሬው ለኅብረተሰባዊና ለሰብዓዊ ልማት አመች የሆነ አጠቃላይ የአገራችን ሁኔታ የሚጠይቀው፣ የሚፈቅደውና የሚያስችለው ነው።

[5] ይህንን «የአመለካከትና የባሕርይ ለውጥ»ን ለኅብረተሰባዊ ለውጥ ዋነኛ መሣሪያ አድርጎ የመውሰድ አስተሳሰብ በኢትዮጵያ የመንስራፋትን ጉዳይና የአመክንዮ ችግሩን በተመለከተ ለተሰጠ ሰፋ ያለ ትንተና፤ የራስወርቅ አድማሴ 2006 ይመልከቱ።

# ሥነ ጥበብ እና ልማት

## *አስፋው ዳምጤ*

ዛሬ በዓለማችን በመልማት ላይ ያሉ አገሮች በልማት ረገድ ወደፊት እንዲራመዱና ልማታቸውም ዘለቄታና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን፣ በየሀገራቱ ተቋማትና መንግሥታት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ *የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ከነልዩ ልዩ ዘርፎቹ)* ባሉ ዓለማቀፍ ተቋማት እና እርዳታ ሰጪ በሚሰኙ አገሮችም ትኩረት ከተደረገበት ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ዘልቋል:: ጉዳዩ ዓለማቀፍ ትኩረት የሳበውም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲቋቋም እና የዓለም ባንክ የሚባለውና ሌሎች ተዛማጅ ዓለማቀፍ ተቋማት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል ::

ይሁን እንጂ፣ የእስከዛሬ ጥረቶች ሁሉ በአንዳንድ አግጣጫዎች የመሻሻል ለውጥ አላመጡም ባይባልም፣ የሕዝቡዋ ብዛት እየናረ፣ በልማት የቀደሙ አገሮች አዳዲስ ክስተቶች እውን እያደረጉ ወደፊት በሚሮጡባት ዓለማችን ላይ ፣ በሚገባ ለምተው ደርጅተዋል የሚባሉት ሀገሮች ዛሬም ዉሱን፣ ድኽነት በባሰ ሁኔታ አግጥጦ፣ ለመወገድ አሁንም ገና የላቀ ጥረት እጠየቀባቸው ያሉ ዛሬም እጅግ ብዙ ሆነው ይገኛሉ ::

ሀገራችንም ይኸ የላቀ ጥረት ከሚጠየቅባቸውና ከሚጠበቅባቸው ሀገሮች አንዷ ሆና ስለምትገኝ፣ በዚህ የልማት ተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ፣ ከሌሎች ጥረቶች ጎን ለጎን ሥነ ጥበብ የአለው ቦታ እና ሚና ምንድን ነው ? የሚለውን ነጥብ በማንሣት ድርሻውን ለማመላከት በዚች ጽሑፍ ጥረት ይደረጋል::

ከሁሉ አስቀድሞ፣ በሥነ ጥበብ ስያሜ ሥር የሚጠቃለሉት ዐበይት ረቂቅ ጥበባት ፣ (ቀለም ቅብንና ቅርጻቅርጽን ማእከል ያደረገው *ሥነ ሥዕል፣ ሙዚቃ እና ሥነ ጽሑፍ (ጥበበ ቃላት)* ሲሆኑ፣ በዛሬው ጊዜ የነዚህ ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ተግባራትም ይካተቱባቸዋል :: ለምሳሌ፣ የሲኒማ እና የፎቶግራፍ ጥበብ:: በአጠቃላይ የሥነ ጥበባት ዐይነተኛ ተግባር እና የግባቸው ቁንጮ የሰውን ልጅ መንፈስና አእምሮ ማነጽ ፣ ማልማት ነው ::

ሰው በተፈጥሮው ከአራዊት ወይም ከእንስሳት ጋር የሚዛመድባቸውን ባሕርያት መሞረድ፣ ማለዘብ እና የሰብአዊነት ባሕርያቱን ማጎልበት፣ ብሎም የማኅበራዊ ሕይወት ንቃቱን ከፍ በማድረግ፣ በጎና ሁለንተናዊ ለሆኑ የልማት የጋራ ግቦች ለመነሣሣት ምቹ የሚያደርገው የአስተሳሰብ ዝንባሌ እና አመለካከት ማስረጽ ነው :: ይህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከላይ የጠቀስናቸው የጥበብ ዘርፎች ሁሉ ዋና ዐላማ እና ግብ ነው ::

በኋላ ዘመን ከተነሡት ኢትዮጵያውን ምሁራን መካከል አንዱ፣ ዶ/ር እጓለ ገብረ ዮሐንስ *የክፍተኛ ትምህርት ዘይቤ* በተሰኘው ድንቅ ድርሰቱ ውስጥ በልማቱ ተግባር ቁንጮ ላይ ስለሚገኙት አውሮፓውያን ሲጽፍ፣

> በአውሮፓ ሥልጣኔ መካከል የሚገኘው ሰው ነው:: እነሱ ራሳቸው እንደሚጠሩት ሥልጣኔያቸው anthropocentric ይባላል:: በዚህ አንጻር የሀገራችንን ሥልጣኔ (theocentric) ብሎ መጥራት ይቻላል:: የማናቸውም

> ነገር ማእከል የሰብአዊ ጥረት ሁሉ ምክንያት እግዚአብሔር ነው:: አነሣስቶ የሚያስጀምር ረድቶ የሚያስጨርስ፣ የነገሩ ሁሉ ጥንት ተፍጻሜት አምላክ ነው:: እሊህ ሁለት አስተያየቶች ሁለት ትልልቅ ፈላስፎች የተጣሉበት ነው::፤ አንደኛው፣ ፕሮታጎራስ ይባላል:: ሁለተኛው ፕላቶን ነው:: የመጀመሪያው እንደሚለው፣ ላሉት ነገሮች ሁሉ መኖራቸውን ለሌሉትም አለመኖራቸውን፣ ለማናቸውም ነገር መወሰኛ መስፈርት ወይም መዳልው ሰው ነው ይላል (ገጽ 64)::

ደራሲው *ሥልጣኔ* ያለው ስያሜ የልማትን ጽንሠ ሐሳብ በውስጠ ታዋቂ ያቀፈ ስያሜ መሆኑን ብቻ እንጠቁማለን:: በዚህ አግጣጫ ሌላ ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልገንም:: የሰው ልጅን ቁሳዊ ድሎት ከመንፈሳዊ ደኅንነትና እርካታ ጋር ያዋሐደ እሳቤ ነው - *ሥልጣኔ* ሲል:: ማእከልነቱን አስመልክቶ ግን፣ አልሚው ወይም አምራቹ ሰው፣ በልማት ውጤቱ ተጠቃሚውም ሰው ሆኖ በመገኘቱ ነው:: ስለዚህ፣ በልማት ጉዳይ ውስጥ የሰው ልጅ ማእከልነት ከሁለቱም አግጣጫ ሲታይ የሚገኝ ነው:: በተረፈ፣ በፈላስፎቹ ክርክር ወደ እውነቱ የሚጠጋው የፕሌቶ አተያይ ይመስላል::

የልማት ተግባር የመጨረሻው ግብ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ማኅበራዊ ደኅንነት ሲሆን፣ ለልማቱ አስፈላጊ ቁሳዊ ግብአቶችን አቀናጅቶ የራሱን አካላዊ ጉልበትና የአእምሮ ብልሀቱን አክሎ በመምራት ውጤት አምጪው፣ አሰራጪው እና አከፋፋዩ ደግሞ የሰው ልጅ ራሱ ነው::

ስለዚህ፣ ከላይ የተጠቆመው የጥበባት ሚና እና የመጨረሻ ግብ፣ ማለትም፣ *የሰው ልጅን አእምሮ የማነጽ፣ ቀና አመለካከትን የመቅረጽ እና አዎንታዊ እምነትን የማስረጽ* ተግባር ውጤት፣ ከአጠቃላዩ የልማት እንቅስቃሴ ጋር ያለው ውስብስብ ቁርኝት ግልጽ ነው ::

እነዚህ ጥበባት በየውስጣቸው ዐቢይ የሆኑ ዘርፎች ያሏቸው ከመሆናቸውም በላይ የእርስበርስ መስተጋብርም አላቸው:: በተጓዳኝ የሚገኙ፣ ደግሞም ተደጋጋፊዎችም ናቸው ::

ለምሳሌ በመድረክ የሚቀርብ የቲያትር *ሥራ*፣ ከነዚህ ሦስት ዐበይት የ*ሥነ* ጥበብ ዘርፎች ልዩ ልዩ ንዑሳን ክፍሎቻቸውን ያሳትፋል :: *ቃለ* ተውኔቱ የ*ሥነ* ጽሑፍ፣ የመድረክ ገጹ የ*ሥዕል*፣ አጃቢ ዜማዎችና ድምፆች የሙዚ*ቃ* ጎራ ናቸው::

ከዚህ ዐለፍ ብሎ ሲኬድም፣ *ሥዕል* በግንባር አግኝቶ ሊነግሩት ለማይችሉት ሰው መልእክቱን በምስል በማስተላለፍ ረገድ የመጀመሪያው ጥበብ ነበር :: የዋሻ ውስጥ *ሥዕሎችን* ያስታውሷል :: እንዲሁም፣ አንዳንድ የጥንት ቋንቋዎች ከንግግር ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት ሲሸጋገሩ የመነሻ ፊደሎቻቸው የ*ሥዕል* መልክ ነበሯቸው :: ስለዚህ፣ *ሥዕል* ለ*ሥነ* ጽሑፍ መሠረቱ ለሆነው ለቋንቋ ከንግግር ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት መሸጋገር ወሳኝ ሚና ነበረው ማለት ይቻላል :: በአንጻሩ ደግሞ፣ ስለ *ሥዕልም* ሆነ ስለ ሙዚ*ቃ* ለመግለጽ ወይም ለማብራራት ቋንቋ የሚጫወተው ቁልፍ ሚና አለው ::

እነዚህ ጥበባት በተናጠልም በኅብረትም ፣ ዛሬ በደምሳሳው ልማት በሚባለው የየሀገራት ዐቢይ ጉዳይ ውስጥ ሁነኛ ሚና እየተጫወቱ ነው :: በኢንዱስትሪ ዘርፍ የዲዛይንን *ጥበብ* ሚና ያጤኗል:: ሙዚ*ቃም*፣ ከአዝናኝነቱ ባሻገር፣

የመንፈስ ጭንቀትን የመሳሰሉ የሰው ልጅን ጤና ነሺ ክስተቶች የመፈወስ ወይም የማስወገድ ባሕርያት አሉት፡፡

በ1950ዎቹ የሥዕል እና የሙዚቃ ትምህርት በሀገራችን በተቋማት ደረጃ መሰጠት ተጀምሮ ነበር፡፡

ቢሆንም፣ በዓለማቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ድጋፍ ሰጪ ተቋማት እይታ የኢትዮጵያ የልማት ተግባር ሒደት ዘገምተኛ ፣ ትገኝ የነበረበትም የእድገት እርከን ከሁላቀሮቹም ዝቅተኛ የሚባል ነበረና ፣ በሀገሪቱ ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ እድገትና ልማት የማምጣት እንቅስቃሴ ላይ ውይይት ሲነሣ፣ የሥነ ጥበባትን መጎልበት ጉዳይ እንደ ሒደቱ አስፈላጊ አካል ሳይሆን ፣ እንዲያውም በአንዳንድ ወገኖች እንደ ቅንጦት የመቍጠር አዝማሚያ ይታይበት ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ «ለራበው ዳቦ እንጂ ሥዕል አታጎርሰው» ፣ «ለጠማው ንጹሕ ውሃ እንጂ ሙዚቃ አታጠጣው» እና «ለታረዘው ጨርቅ እንጂ መጽሐፍ አታለብሰው» የሚሉ ሥላቅ አዘል የማጣጣል አባባሎች ይደመጡ ነበር ፡፡ የዚህ አዝማሚያ ርዝራዥ ዛሬም አለመኖሩ በእርግጠኝነት አይታወቅም ፡፡

ለነዚህ ዐይነት ዝንባሌዎች መከሰት ዋና ምክንያቶቹ ሁለት ይመስላሉ፡፡ አንደኛው፣ ሀገሪቱ ከአላት ምጥን ሀብት ላይ ቁልፍ ለተሰኙ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች የሚገባውን ያህል ቀርቶ በቂ ሊባል በሚችል መጠን ሀብት (ንዋይ) ለመመደብ ችግር በሆነበት ሁኔታ፣ እንደ ቅንጦትና ጌጥ ለሚመለከቱት ወገኖች፣ የጥበባትን ማስፋፋት ጉዳይ ያን ያህል አንገብጋቢ አይሆንም ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው እና መሠረታዊው ነጥብ ፣ የሥነ ጥበባት ዘለቄታ ያለው መሠረታዊ ተጽእኖው የሚከሰተው በቀጥታ ሳይሆን እጅግ በረቀቀና ዘወርዋራ በሆነ መንገድ ከመሆኑም በላይ፣ ረዘም ባለ የጊዜ ሒደት የሚከሰት መሆኑ ነው፡፡

ያም ሆኖ ዋነኛ ውጤቱ በሜትር፣ በሊትር ወይም በኪሎ ግራም ሊሰፈር የሚችል አለመሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ኪሎግራም ጥሬ ስንዴ ተፈጭቶ ተቦክቶ ዳቦ ሲሆን ውጤቱ በሚዛን ሊታወቅ ይችላል፡፡ የአንድን የጥበብ ሥራ በሰው ባሕርይ ላይ የሚያመጣውን አዎንታዊ ውጤት በዚህ መልክ መስፈር አይቻልም፡፡ ስለዚህ ውጤቱ በግልጽ ተከስቶ አይታይም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የጥበባት ተግባር ውጤቶች ለልማት ቀጥተኛም አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እውነተኛ አገር ጎብኚዎች ወደየሀገራት ለጉብኝት የሚሳቡት በጥንታዊ የጥበብ ቅርሶች ሳቢያ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን፣ የተከታይ ትውልዶችን ለጣቂ ሥራዎች ከዚያ ባላነሰ መጠን ለማየትና ለማወቅ ፍላጎት እንደሚኖራቸው አያጠራጥርም፡፡ ይኸን ለማስተናገድ ዘመናዊ የጥበብ ሥራዎችን በቋሚነት ማሳያ ቦታዎች (ለምሳሌ ፣ ዘመናዊ ሚዩዚየሞች፣ ጋለሪዎች) ለማደራጀት ሀብት ማፍሰስ ይጠይቃል፡፡ ይገባልም- የነገ እና የተነጎዲያው ቅርስ የሚፈጠረው ዛሬ ነውና ፡፡ ይኸን ማበረታታቱ የልማት ሥራ ተግባር ነው፡፡

ይህ የሀገር የልማት ጉዳይ ፣ ከ20ኛው ምዕተ ዓመት መነሻ ላይ ጀምሮ በነበሩ ቀደምት የኢትዮጵያ ምሁራን እና የጥበብ ሰዎች ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ስለ ኢትዮጵያ እድገት እንበለው መዘመን ተቆርቋሪ ሆነው በጽሑፍ ሐሳባቸውን የገለጹ ብዙዎቹ ጸሐፍት ወይም ደራስያን ፣ በአገላለጻቸው ወይም በስያሜ አሰጣጣቸው ለየት ስላለ ጉዳይ የሚያነሡ፣ የሚያወሱ ሊመስል

ቢችልም ፣ ግንዛቤያቸው ይኸው አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ ከሥራቸው የሚታይ ነው ።

እንዲያውም፣ የነዚህ ደራስያን አተያይ ሁለአቀፍ ያገር ማደግና መበልጸግ ስለነበር፣ የጥረቶቻቸው ትኩረት በአንድ ወይ በሌላ ውሱን አግጣጫ ላይ ብቻ ያነጣጠረ አልነበረም። አጠቃላይ የሀገር በየዘርፉ መነሣት፣ ከፍ ማለት፣ ወደፊት መራመድ ጉዳይ ላይ ነበር ትኩረታቸው። የምዕራቡ ዓለም የሚያደርገውን የፍጥነት ግሥጋሤ (በሥጋዊ ሥልጣኔ ቢባልም) ያስተዋሉ ኢትዮጵያውን ምሁራን፣ ጸሐፍትና ደራስያን መንፈሳቸው ተነሣሥቶ ሌላውን ለማነሣሣት ተግተዋል ።

ከነዚህ መካከል ትምህርቱና ሙያው ሕክምና የነበረው፣ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የተባለው ወጣት ምሁር፣ ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ግንዛቤ እና ጉዳዩን የአቀረበበት መንገድ፣ ይኸን ሐቅ ቁልጭና ግልጽ አድርጎ ያሳየናል።

በልጅነቱ ከሀገሩ ወጥቶ፣ አብዛኛውን የእስከዚያን ጊዜ ዕድሜውን ያሳለፈው በአውሮፓ የነበረ ቢሆንም፣ አገሩ እንደገባ ወዲያው ነበር የሀገሩን ሁኔታ የተረዳው ማለት ይቻላል። ለታየው የወቅቱ ሀገራዊ ችግር የመፍትሔ ሐሳቡንም ግልጽ በሆነ ቋንቋ ጽፎ ትቶልናል።

በዚህ *መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* (1916) በተባለው ኗሪ መጽሐፉ *መቅድም* ውስጥ የሚከተለውን አንኳር ሐሳብ በዚያኑ ዘመን አቅርቧል።

> ሕዘቦች ከተፈጠሩ ዠምሮ እስኪያልፉ ድረስ ምንስ ሕዝቦቹ ዘራቸውና ቋንቋቸው ልዩ ልዩ ቢሆን አስማምቶ የሚያስሔደው ሥርዐት ግን መሠረቱ አንድ ነው። ሕዝቦች ሁሉ የሚፈጠሩ በዚች ምድር ላይ ነው። ሁሉም ምድር የምትሰጠውን ሲሳይ ለማገኘት ይጥራሉ። ቢያገኙ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይለብሳሉ፣ ይመቻቸዋልም። ቢያጡም ይራባሉ፣ ይጠማሉ፣ ይታረዛሉ፣ ይቸገራሉም ።
>
> ሕዝቦችን ሁሉ የሚፈጥር አንድ አምላክ ነው። ይህም አምላክ የምንለው የሕዝቦች ፈጣሪ ሕዝቦቹን ሁሉ ትክክል አድርጎ ፈጥሮ ላኗኗራቸውና ለልማታቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ከሙሉ ፈቃድና ሥልጣን ጋር በጃቸው ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ማናቸውም ሕዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ እጁ ነው።
>
> ሕዝብ የሚጠፋበት አንዳንድ ጊዜ ምክንያት ቢገኝ፣ ያውም ምክንያት ባንዳንድ ሰው ቢመካኝ ነገሩ ትክክል አይሆንም።
>
> የልማትን መንገድ ለማግኘት የሚጥር ሕዝብ ቢገኝ ባንዳንድ ክፉ ሰው ምክንያት ሊጠፋ አይችልም። እንዲሁም ደግሞ፣ የልማትን መንገድ ለማግኘት የማይጣጣር ሕዝብ ባንዳንድ ደጎና ሰው ኀይል ልማት ሊያገኝ አይችልም። ደግሞም፣ ማናቸውም ሕዝብ የሚለማበት መንገድ አንድ መንገድ ብቻ ነው። ማናቸውም ሕዝብ የሚጠፋ ይህንን የልማት መንገድ ትቶ በሌላ መንገድ የሔደ እንደ ሆነ ነው።

ይኸም ብቸኛ መንገድ *የሕዝብ አስተዳደር ትምህርት* የሚቀይሰው ትክክለኛ መንገድ መሆኑን ይህ ወጣት የብዕር ሰው ይጠቁማል። ይኸ ጽሁፍ ቀጥተኛ የልማት ጎዳናን አመልካች ብቻ ሳይሆን፣ ጎዳናውን አገራችን እንድትከተል ግልጽ ግፊት አድራጊ መጽሐፍ ነው ።

ከመቅድሙ ከጠቀስንለት ከዚህ *መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* ከሚለው መጽሐፉ ባይበልጥ ባልተናነሰ ርቱእ አገላለጽ ፣ ወደ ልማት መንገድ ለመግባት ወሳኝ የመሰሉትን የእርምጃ ዐይነቶች ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በቀጥታ እንዲህ ይደረግ በሚል መልክ ሊወሰዱ የሚገባቸውን በርካታ እርምጃዎች በዐሥር ተራ ቁጥሮች በማጠቃለል ፣ *ዐጤ ምኒልክ እና ኢትዮጵያ* በተሰኘ ድርሰቱ ውስጥ አካትቶ፣ ከተጠቀሰው መጽሐፍ መታተም በጣም ቀደም ብሎ (በልጅ ኢያሱ ዘመን 1904) አበርክቶ ነበር።

በዚህኛው ድርሰት ውስጥ የሚያቀርባቸው *መሠረታዊ የማሻሻያ ሐሳቦች* በዐሥር ተራ ቁጥሮች የተጠቃለሉ ይሁኑ እንጂ ፣ ለምሳሌ *መጀመሪያ* ያለው የተራ ቁጥሩ መነሻ እንኳ በርካታ ወሳኝ ጉዳዮችን አምቆ የያዘ ነው ። እስከ አራት ተራ ቁጥሮች ሊዘረዘሩ የሚችሉ ዋና ዋና ሐሳቦች የያዘ ነው። የመጀመሪያውን ተራ ቁጥር ጸሐፊው በራሱ ቃል እንዳቀረበው እንመልከተው ።

> *መጀመሪያ*፣ ለመንግሥት የሚሆን ገንዘብና ለንጉሥ የሚሆነው ገንዘብ በሥርዓት ይለይ ። ሹሞችም በደሞዝ ይደሩ ። ካገር የሚወጣውም ግብር ለመንግሥት ይግባ።
>
> የጦርም ሠራዊት ሁሉ የንጉሥ ይሁን። ያገር ምስለኔና የጦር አለቃ በያገሩ ይለይ። መጀመሪያው ባላገሮቹን የሚያዝ ሁለተኛው ግን ወታደሮቹን። የንጉሡና የመንግሥት ገንዘብ የተባለው ትርጉሙ እንዲህ ነው። የንጉሥ ገንዘብ ማለት ያ ለግብርና ለሌላ የንጉሥ ቤት ጉዳይ የሚያስፈልግ ገንዘብ ነው። የመንግሥት ገንዘብ ማለት ግን ያ ለሠራዊት ደሞዝ፣ ለመንገዶችና ለትምህርት ቤቶች ማሠሪያ የጦር መሣሪያዎችም መግዣ፣ ለሌላ እንዲህ የመሰለውም (የውጭ?) የወጪ ጉዳይ የሚሆነው ገንዘብ ነው።

ከዚህ በግልጽ ልናየው የምንችለው፣ እነዚህ ሐሳቦች ለልማት የማይበጁ ግን ለዘመናት ሳይጠየቁ የኖሩ፣ ከባድ የፖለቲካ እንድምታዎች ያሏቸውን ልማዶችና ያገር ጉዳይ አመራር አያያዞችን ጭምር በወቅቱ የሚጋፉ ሐሳቦች ነበሩ ።

የመጀመሪያው ቁምነገር፣ *መንግሥት* እና *ንጉሥ* በሚሉት ሁለት ስያሜዎች ወካይነት የተገለጹትን ነገሮች የበስተጀርባ ጉልህ ልዩነቶች የሚጠቁም ነው ። አብሮም የመንግሥት ግምጃ ቤት ገንዘብ ሊውል የሚችለው (የሚገባውም) ለሀገራዊ የጋር ጥቅም ጉዳይ ብቻ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

ደግሞም፣ ከዜጎች የሚሰበሰበው (በእርሱ አገላለጽ፣ *ካገር የሚወጣው*) የግብር ገንዘብ በሁለቱ ግምጃ ቤቶች መካከል በምን መጠን እንደሚከፋፈል ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፤ ለመታዘብም አመቺ ያደርገዋል።

ሁለተኛ፣ የሲቪል እና ወታደራዊ አስተዳደር እንዲለይ፣ እንዲሁም የመንግሥት ሹማምንት ከመንግሥት በሚሰጥ ደሞዝ እንዲተዳደሩ እንጂ፣ ደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ አንዱ ጽሑፉ ውስጥ በሥላቅ እንደሚገልጠው «ሕዝቡን ደሞዝ» ማድረጋቸው እንዲቀር የሚያሳስብ ነው።

በተራ ቁጥር ሁለትም፣ ሁለት ዐቢይ ጉዳዮችን አካትቶ ይገኛል። የመንግሥት ግብርን የአወሳሰንና መርሁ ምን መሆን እንደሚገባው፣ እና እንዲሁም፣ የሕዝብ ቆጠራ (የልደትና ሞት ምዝገባን ያካተተ) ሥርዐት እንዲኖር የሚያሳስብ ነው ።

በሦስተኛው ተራ ቁጥር ግብር አከፋፈልን በሚለከት ግን፣ ቀደም ሲል «ሕዝቡ ለመንግሥት የሚከፍለው ግብር እንደየሀብቱ መጠን ቁርጥ ሁኖ ይታወቅለት » ያለውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ መክፈል የሚገባው በብር እንጂ በዐይነት (ማለትም *በእህል፣ በማር* ወይም *በፍሪዳ* ) እንዳይሆን ያመላክታል:: የመክፈያ ብሩን በሚመለከት ስላለው ችግር ደግሞ፣ በተራ ቁጥር ሰባት በሚከተለው መንገድ ሐሳቡን ያቀርባል::

> ሰባተኛ፣ የዛሬው የመንግሥታችን ብር የተበላሸ ነው:: ሥርዓት ውል የለውም:: ባንዱ አውራጃ በጨው፣ በሌላው በጥይት ይሸረፋል:: ስለዚህ፣ መንግሥት ለመላው ኢትዮጵያ የሚሆን የገንዘብ ሥርዓት በቶሎ ያላወጣ እንደሆነ፣ ንግድ ሊለማ አይችልም::

በማለት የጉዳዩን አሳሳቢነትና መሠረታዊነት ያሠምርበታል:: እነዚህን ከመሰሉ ዝርዝርና ተጨባጭ ሐሳቦች በተጨማሪ፣ ስለ ፍትሕ ሥርዐቱ ማርጀትና የዘመኑን ጉዳዩች ለማስተናገድ የሚችል ሥርዐት አስፈላጊነት፣ ስለ መንግሥት ጦር ሠራዊት ሥልጠና፣ ለንግድ ሥራ ሥርዐት ስለ ማበጀት፣ የሀገሪቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች እየተዘዋወሩ የሚቆጣጠሩ ሹሞች ስለመመደብ እና የሃይማኖት ነጻነት ስለማወጅ ቅን መንፈስና ድምፀት ባላቸው፣ አንዳንዴም ፈገግ በሚያሰብሉ አገላለጾች በሳል ሐተታዎች ያቀርባል:: በነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ ለልማት እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያገለግሉ እና ቀጥታ የልማት እርምጃው አካል ተደርገው ሊታዩ የሚችሉም አብረው ተካተተው ይገኛሉ::

በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊታዩ ከሚችሉት መካከል ፣ በራሱ ዝርዝር ውስጥ፣ በአራተኛ ተራ ቁጥር ትምህርትን አስመልክቶ፣ የትምህርት ደረጃን፣ የመምህራን ዐይነትና ቁጥር፣ እንዲሁም በዓመት ሊፈጅ ስለሚችለው የበጀት ገንዘብ መጠን ራሱ ገምቶ በመወሰን የሚያቀርባቸውን ሐሳቦች ድርሰቱ አካትቷል:: (ገጽ 23-27)

ሌሎቹ ቀደምት የኢትዮጵያ ደራስያን ፣ እንደ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በቀጥታ ስለ ልማት ጉዳይ ቃሉን እየጠቀሱ ባይጽፉም፣ እነርሱም አንዳንድ ጊዜ እንደሱዉ በቀጥታ ገለጻ፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን በምሳሌ እና በፈጠራ መልክ ሐሳባቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ በማቅረብ፣ ከላይ እስከ ታች ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ አዳዲስ ሐሳቦችን መቀበል እንዲችል የማዘጋጀት ጥረት በማድረግ ለልማት የሚበጁ መንገዶችን መከተል የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የተለያዩ ሥራዎች አቅርበዋል ::

ከነዚህ መካከል አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፣ *ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ (1901)* ለተሰኘ ው መጽሐፉ እንደ *መግቢያ* በጻፈው መነሻ ክፍል ውስጥ ሐሳቡን በቀጥታ ለመግለጽ በሚያስችለው ስልት ተጠቅሞ ፣ ቤተ ክህነትን ተገን አድርጎ ለምዕተ ዓመታት በቤተ መንግሥትም ጭምር ብቸኛው ዐቢይ ቋንቋ ከነበረው ከግእዝ አላቆ የወደፊት የጽሑፍ ሥራችንን ሐሳቦች መክተቢያ እና ማስተላለፊያ፣ ማሸጋገሪያ ብዛት ያለው ሰው በሚገባው ቋንቋ መሆን እንደሚገባው እንደሚከተለው በአጽንኦት ይገልጻል ::

> ይሄን አሮጌ ቋንቋ ለቤክርስቲያን ትተው የቀረውን የዓለሙን ነገር የዓለሙን ሥራ ግን ሁሉ በሚአውቀው ሁሉ በሚናገረው ቋንቋ ባማርኛ ቢጽፉ ደግ ነበረ:: ደግሞም ለንግድ ለጥበብ ለመንግሥት ሥራ የሚጠቀመውን አማርኛ ውን ማረም ማሳመር ማስተማር ማልማት ይሻላል ይገባልም ... ግእዝ ብቻ

*ማሳመር፣ አማርኛ ንቆ ግእዝ ብቻ ማክበር፣ አባቱን ገሎ ላማቱ ይነጭ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ የሚሉት ነገር ነው ::*

... በፈረንጅ አገርም የጥንቱን ቋንቋ ሮማይስጡን ለቤተክርስቲያናቸውና ለሌላ ነገር ትተው ሁሉም አዲስ ቋንቋቸውን እያረሙ አሳመሩ፣ ለልጆቻቸውም ያስተምራሉ:: ኢትዮጵያም እንዲሁ ማድረግ ይገባታል:: (ገጽ 7፣8)

ከቋንቋው በስተጀርባ ይዞት የሚገኘው የሐሳብ ጭነት እና የአገላለጽ ልምድ ስላለው ለዓለሙ *ሥራ* የግእዝ ቋንቋ እንደ አማርኛው ሊታዘዝ፣ ሊቀና አይችልም የሚል አስተሳሰብም ከዚህ በስተጀርባ ይኖራል:: በግእዝ የተጻፉት ታሪከ ነገሥት ወደ ገድልነት ማዘመም በምሁራን ሲተች የኖረ መሆኑም ፣ ለአዲስ ተግባርና አካሔድ ይኽ ልምዱ ያን ቋንቋ አላስመረጠውም ይሆናል::

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝም የአፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን መጽሐፍ ዋና ይዘት በትዝብት ቢተቸውም፣ የዚችን የቋንቋዋን ሐሳብ ቁም ነገር ግን የተቀበለለት ይመስላል:: ከላይ በተመለከትናት በራሱ ድርሰት ውስጥ በተራ ቁጥር አራት እርሱም ጉዳዩን ደግሞ ያነሣዋልና:: የሚከተለውን እንመልከት፣

> *«አራተኛ፣ ያማርኛ ቋንቋ ገና ሥርዓት አልተበጀለትም:: ስለዚህ መንግሥታችን ከያገሩ ሰዋስው የሚያውቁትን ሊቃውንት ሰብስቦ ያማርኛን ቋንቋ ሰዋስው ቢያስወጣ ደግ ነው:: በያገሩ አውራ ከተሞች እንደ ኤሮጳ ሥርዓት ያበሻን ፊደልና ያማርኛ ቋንቋን ማስተማሪያ ቤቶች ይከፈቱ ... ፊደልን ያላጠና ልጅም በአውሮፖቹ የትምህርት ቤቶች (የውጭ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው) አይግባ:: የፊደል ማስተማሪያ ቤት ግን ያውራጆች ገዦች እንዲያስቡባቸው መንግሥት የግድ ይበላቸው»* ይላል:: (ገጽ 24፣ 25)

የተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም አገርን የመታደግ መነሻ ሙከራ ደግሞ ዐላማ አድርጎ የተነሣው፣ *ታዳጊውን መሪ ልጅ ኢያሱን፣ ፋቡላ* (1905) በተሰኘች ምሳሌያዊ ተረታተረቶች በያዘች የግጥም መጽሐፍ አማካይነት ቀርቦ፣ ከዚያ

ስለ ሀገር ጉዳይ ትክክለኛውን መንገድ ለማመላከት እንደ ነበር ጽፏል:: መቃረቡ የተሳካ የነበር ቢሆንም፣ በመተማመን ላይ ተመሥርቶ ሊዘልቅ ግን አልቻለም ነበርና ዋና ዐላማው ሳይሳካ እንደ ቀረ ደራሲው ይገልጻል::

በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን መነሻ ላይ ደግሞ በተውኔት መልክ ተክለ ሐዋርያት ያቀረበው *የአውሬዎች ኮሜዲያም* የንግሥቲቱን ቁጣና ቅያሜ ቢያተርፍም፣ ሁለቱንም *ሥራዎቹን* አግኝተው ባነበቧቸው እና ቲያትሩን በተመለከቱ ዘንድ ተወዳጅነት እንዳላጡ ጠቋሚ መረጃ አለ::

ይኸውም፣ በዚያ ዘመን ታትሞ ይወጣ በነበረው፣ *ብርሃንና ሰላም* ይሰኝ በነበረው ጋዜጣ ላይ፣ (ትያትሩ *መጀመሪያ* አንድ ጊዜ ብቻ ታይቶ በተከለከለ በ12 *ዓመቱ*) የኅሙስ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. እትሙ ገጽ ፪ ላይ፣ *ጥቅም ያለው የትያትር መጽሐፍ* በሚል ርእስ ሥር እንደሚከተለው የሚነበበው ነው:: ዋና አዘጋጁ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ነበር::

> ይህን ጥቅም ያለው የትያትር መጽሐፍ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ጽፈው፣ ለሕፃናት አስጠንተው በሺ.9)03 ዓዓመተ ምሕረት በሙሴ ቴራስ ሆቴል የትያትሩን ጨዋታ አሳይተው ፣ ጥቂቶቹን ሰዎች እንጂ ብዙዎችን ሰዎች ደስ ለማሰኘት አልሆነላቸውም ነበር:: ምክንያቱም በዚያ ዘመን ከዐዋቂዎች አለዐዋቂዎች በኃይል ስለበዙ ነው::

> ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ይስጥልን እንጂ፣ ጊዜው እጅግ የተሻሻለ ስለሆነ፣ እነዚህን ስደተኛ መጻሕፍት በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ፈልገው አጠራቅመው፣ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲያስጠና ለዲረክተሩ ለአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ሰጥተውት፣ ተማሪዎቹ ደኅና አድርገው ካጠኑት በኋላ በኅዳር 01 ቀን (1925) በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተደረገና የተሰበሰቡትን ሰዎች እጅግ ደስ አሰኙ::
>
> ይህን ደስ የሚያሰኝ መጽሐፍ፣ ከላይ እንዳመለከትነው፣ የአለዐዋቂዎች ኃይል ስለበዛ እንዲጠፉ መክረው የታተሙትን ብዙዎች መጻሕፍት አጠፏቸው::
>
> ነገር ግን፣ ምንም በረዶ ቢበላው የተዘራ ፍሬ ለዘር ያህል በጭራሽ አይጠፋምና፣ ከደኅና ቦታ ተጠግተው ተመክራ የዳኑ ጥቂቶች ተገኙ::

ይህ ደራሲ *ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት* (1922) የተሰኘው መጽሐፉ በሀገሪቱ ዋና ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ መሆኑ ስለ ልማት ያውጠነጥን የነበረ ጸሐፊ/ደራሲ ስለመሆኑ ይመሰክራል:: መጽሐፉ የተጻፈው እስር ላይ እያለ ፣ ከሌላ ሰው ጋር እጁን ተቆራኝቶ አንድ ሹም እስር ቤት ውስጥ ነበር:: ይኸ በዐይኑ ኅሊና ሲታይ፣ ስለ ሀገሩ መዘመን እና መልማት ተክለ ሐዋርያት የቱን ያህል ቁርጠኛ ምኞት እንደ ነበረው በተጨባጭ የሚያሳይ ነው::

ወደ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ስናተኩር ጥረቱ ፈርጀ ብዙ መሆኑን እናስተውላለን:: የብዙዎች የጽሑፍ *ሥራዎቹ* ያቀራረብ ፈርጆች ከዚያ ቀደም በሀገራችን ያልተለመዱና ያኔ ሠለጠኑ በሚባሉ አገሮች ግን በመደበኛነት የሚታወቁ ተግባራት ነበሩ:: ለምሳሌ፣ በአንድ አገር ያሉ መጻሕፍትን ዝርዝር ከማብራሪያ መረጃ ጋር ማሳተም፣ የግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ ማቀናበር፣ በውጭ ሀገር ጉዞ ላይ ስላዩትና ስለሰሙት ጽፎ በማሠራጨት፣ በተለይ ያን ዕድል ላላገኙ ብዙኃን የራስ ወገኖች፣ ስለሌሎች ሕዝቦች እና ሀገሮች ማሳወቅ... ወዘተ ጥቂቶቹ ሙከራዎቹ ሲሆኑ እነዚህ *ሥራዎችና* ሙከራዎቹ ራሳቸው የአመለካከት አድማስን የሚያሰፉ በመሆናቸው፣ የቀጥታም ሆነ የተዘዋዋሪ የልማት ተግባር አንድምታ ነበራቸው::

*ማኅደረ ብርሃን* የሚል ንዑስ ርእስ በሰጠው *ሀገረ ጃፓን (1924)* በተሰኘው መጽሐፉ፣ ስለ ጃፓን ሕዝብና መንግሥት በአጠቃላይም ስለሀገሪቱ ሁኔታ፣ እንዲሁም ከሀገሩ እስከ ጃፓን ሲሔድና ሲመለስ ስላለፈባቸው አገሮች በዝርዝር በመጻፍ፣ ከሀገሩ ወጥቶ የማያውቅ አንባቢውን የምናብ አድማስ ለማስፋት ጥሯል:: በተጨማሪም ፣ የጃፓንና የኢትዮጵያን የረጃጅም ዘመን ታሪኮች (እስከነ አፈ-ታሪካቸው) ጎን ለጎን ሆነው ለመታየት እንዲችሉ ለማድረግ ይሞክራል:: ከዚህ በመነሣትም፣ ለዘመናት የኖረ ውስብስብ ባህል ያለው አገርም በፍጥነት እና አጠር ባለጊዜ ለመዘመን ስለ መቻሉ ፣ ኅሩይ ኢትዮጵያ ጃፓንን እንደ አብነት እንድትወስድ አድርጎ ነበር ማለት ይቻላል:: የከበደ ሚካኤል *ጃፓን እንደምን ሠለጠነች* (1946) ከ22 ዓመታት በኋላ መታተም፣ ኅሩይ የጫረው ሐሳብ ሥር ሰዶ መዝለቁን የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል::

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ *የልብ አሳብ* (1923) እና *አዲስ ዓለም* (1925) በተሰኙት የልቦለድ *ሥራዎቹ* በወቅቱ ሰፍኖ የነበረውን ማኅበራዊ እውነታ ለመለወጥ፣ አንዳንዱንም ለማስወገድ የነበረውን ምኞትና ያደረገውን ጥረት ያሳያሉ::

ለምሳሌ ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻንና፣ የሴት ልጅን የምርጫ መነፈግ ፣ ምናብ ወለድ በሆነው በ*ብርሃኔ እና በጽዮን ሞገሳ የጋብቻ ታሪክ* ተራኪው ይሞግታል::

በ*አዲስ ዓለም* ውስጥ ደግሞ፣ በውጭ ሀገር ትምህርትና ልምድ አዲስ አተያይ ባጎለበተ በአንድ ወጣት እና የጥንቱን ልማድ የሙጥኝ ባሉት በወጣቱ አባት የነፍስ አባት አማካይነት በማኅበራዊ ኑሮና ከቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አስተምህሮ ውጭ የተከማቹ ልማዶችን ይሞግታል:: በሁለቱም የፈጠራ *ሥራዎቹ* ውስጥ አዎንታዊዎቹ አመለካከትና አስተሳሰቦች የበላይነት እንዲያገኙ አድርጎ ነው የሚደመድመው ::

ይህ ደራሲ በቀጥታም በተዘዋዋሪ መንገድም ለልማት አስተሳሰብ በአዎንታዊነታቸው አጋዥ የሆኑ ሌሎች *ሥራዎችም* አቅርቧል::

በዚሁ *አዲስ ዓለም* በተሰኘ ልቦለዱ *መቅድም* ውስጥ *መሠረታዊ* አመለካከቱን የሚጠቁመን ሐሳብ ይገኝበታል::

> አንዳንድ ሰዎች ብዙ ዘመን የኖረውን ልማድ ማሻሻል ማደስ እንደ ነውር ይመስላቸዋል:: ይኸውም የቀድሞውንና የዛሬውን ታሪክ ካለማንበባቸውና ካለመረዳታቸው የተነሣ ነው እንጂ ፣ ታሪክ አንብበው በነበሩ ዛሬ በዓለም ላይ ልማዱን ያላሻሻለና ያላደሰ ሕዝብ አለመኖሩን ያገኙት ነበር::

ይልና ለዘመኑ ሰዎች በተለይ አንባቢዎቹ አድርጎ ለሚገምታቸው ሰዎች ተስማሚ የሆነ ምሳሌ እየመረጠ ያቀርባል ::

ከላይ ያነሣነው ደራሲ ከበደ ሚካኤል ፣ *«ኢትዮጵያና የምዕራባውያን ሥልጣኔ»* (1941) ከሚለው ተነሥቶ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ደጋግሞ ጽፎ በድምሩ ከአራት ያላነሱ መጻሕፍት አሳትሟል:: በግጥም ስብስብ *ሥራዎቹ* ውስጥም ይኸው የመዘመንና የመሠልጠን መንፈስ የሚነጸባረቅባቸው ግጥሞች አያሌ ናቸው:: ለዚህ እንደ ዐይነተኛ አብነት ሊቀርቡ ከሚችሉት አንዱ፣ ገና ከጧቱ በ*የዕውቀት ብልጭታ* እንደ መግቢያ የጻፈው ግጥም ነው::

> *ሌት ተቀን አድርጎ መንፈሱን ጠንካራ*
> *ሕፃን ተግቶ ሲማር ዐዋቂም ሲሠራ*
> *የዕውቀቱ ብልጭታ እየሆነ ጮራ*
> *ጮራውም ተስፋፍቶ በመሆን ውጋጋን*
> *እንደ ቀትር ፀሐይ የጥበቡ ብርሃን*
> *ሞቆ ይደምቅና ኃይሉ እየገነነ*
> *ለማለት ይቻላል አገር ሠለጠነ . . .*

*አርአያ* (1941) በተሰኘው ግርማቸው ተክለሐዋርያት በጻፈው ልቦለድ ውስጥም፣ ስለ 1928 የፋሺስት ወረራ፣ ስለአርበኝነት ትግል ፣ እንዲሁም በከተሞች ያ ወቅት ስላስከተለው ሁናቴ አንኳር ጉዳዮች አድርጎ ቢያቀርብም፣ ይኸ የለውጥና ወደፊት የመራመድ ርእስ ጉዳይ በዋናነት የሚንጸባረቅ ነው:: ይኸ በተለይም ዋናው ገጸባሕርይ አርአያ፣ ከመኳንንትና ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ከሚያደርጋቸው ውይይቶች ይታያል::

የሥነ ጥበባትም ዐይነተኛ ተግባር፣ ተልእኮ እና ማእከል የሰው ልጅ ነውና፣ ከተለያየ አግጣጫ ቢመጡም ሁለቱ (ሥነ ጥበባት እና ልማት) እዚህ ላይ እንደሚገናኙ ተደጋግሞ ተጠቁሟል:: የጥበባት ውጤቶች አዝናኚነት ባሕርይ

ያላቸው ቢሆኑም፣ መድረሻቸው ግን የሰው ልጅ አእምሮን ማነጽ፣ መቅረጽ ነው።

በአንድ በኩል የልማት የመጨረሻና መድረሻ ግቡ የሰው ልጅ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱን በበቂ መጠንና ጥራት እንዲያገኝ ማስቻል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ይኸንኑ የልማት ግብ ከዳር ለማድረስ ቁልፉ ያው ሰው ነው። ማለትም በአንድ ወገን የልማት ውጤቱን ተጠቃሚው እርሱ ሲሆን፣ ልማቱን በማምጣትም ረገድ ማእከላዊውን ሚና የሚጫተው እርሱ ራሱ ነው።

ስለዚህ፣ ሀገራት ስለልማት ሲያስቡ ለሥነ ጥበብ ተገቢ ትኩረትና በቂ ገንዘብ ወይም ሀብት መመደብ የምርና በቁምነገር የሚታሰብበት ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። በአንድ ሀገር የቲያትር ቤቶች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ሚዩዚሞች፣ የኮንሰርት አዳራሾች... ወዘተ ተበራክቶ መገኘት ለልማቱ መኖር አጋዥም ምስክርም ናቸው። ሰው በሥጋውም በመንፈሱም እኩል ሲረካ ሲችል ነው ጤናማ ኅብረተሰብ ሊኖር የሚችለው። አንድ ሀገር እንደዚያ ዐይነት ኅብረተሰብ ሲኖረው ብቻ ነው የልማት ተግባሩ ትክክለኛውን ፈር የተከተለ የሚሆነው።

በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ረቂቅ ጥበባት ደርጅተው ለልማት ጥረቱ ትርጉም ያለው ዘላቂ ሚና እንዲጫወቱ፣ መንግሥት በሥሩ ያሉ ተቋማት ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና እንዲሰጡ ለማድረግ በአደረጃጀትና በገንዘብ ዐቅም እንዲደረጁ የማድረግ ጥረቱ ይበልጥ መጠናከር አለበት። ይኸንኑ ተግባር ባለ ሙያዎች በግልም በቡድንም ከመንግሥት በተጓዳኝ በየፈርጁ ለሚያደርጉት መፍጨርጨር ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና ድጋፍ በመስጠት የጋራ ግባቸውን እንዲመቱ ማስቻል ይገባዋል። ለክፍላተ ኢኮኖሚዎች የሚሰጠው ትኩረት ለዚህ ቁልፍ ዘርፍም መነፈግ የለበትም። አስተዋጽኦው ወሳኝነት አለውና።

# የሥዕል ጥበብ ለባህልና ልማት ዕድገት

### *እሸቱ ጥሩነህ*

እሳት ወይ አበባ

እና እንደ እኔና እንደ አንቺው የውበት ዓይኑ የታወረ፣

እግረ ሕሊናው የከረረ፣

ባሕረ ሃሣቡን ያልታደለ፣

የውበት ዓይኑ የሰለለ፣

ሰማይ ጨለማ እንጂ አበባ አይደለም አለ።

ያልታደለ።

-------------------

ሌት ከዋክብቱ እንደ ፀደይ፣

አጥለቅልቆን በቀይ አደይ፣

ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ፣

ተሸለምልሞ አንፀባርቆ፣

ፊክቶ አሸብርቆ ደምቆ፣

..............................

*ከፀጋዬ ገ/መድኅን፤ እሳት ወይ አበባ፤ ሥነ ግጥም* (1966)፣ ገጽ 134 - 148

# 1. ተንኳሽ ሃሣብ

እኛ የሰው ልጆች የቃላተ ድምፅ ንግግሮች በተንሠራፉበት፣ የቃላተ ፊደላት ጽሑፎችና ንባቦች በገነኑበት፣ የእዝነ ኅሊናዊ (የመስማት) ስሜቶችና መረጃዎች በበዙበት፣ ግን የዝርጋዊና የቅርጻዊ፣ የብርሃናዊና የጥላዊ፣ የፍካታዊና የድባባዊ፣ የሻካራዊና የልስላሴያዊ እንዲሁም የአንፃራዊና የኑባሬያዊ ሕብረ ቀለማት ዕይታዊ ምስሎች በመሉበት ውብና ድንቅ ዓለም ውስጥ እንኖራለን:: እናያለን:: እንዳስሳለን:: በመሆኑም የውብ ዓለምን ተፈጥሮ በዓይናችን ዓይተንና በእጃችን ዳስሰን ሕብረ ቀለማዊ መልኩን፣ ሽልማዊና ንቅሳዊ ጌጡን፣ ሻካራዊና ልስላሴያዊ (ሻካልሴያዊ) ገጽታውን የምናደንቅና የምንደሰት! ተደስተንም የምንረካ! ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን?

እኛ ኢትዮጵያውያን አብዛኞቻችን «በእምነትም» ይሁን «በዕውቀት» ነገረ ምክንያት «ማየት ማመን ነው፣» እንበል እንጂ፣ ከምናየው የምንሰማውን ድምፀ ቃላትና ንግግሮችን በይበልጥ እናምናለን:: በተጨባጭ ያየነውንና የዳሰስነውን አንድ ነገር ወይም አካል:- ምንድን ነው? ስለ ምን ነገር ነው? ብለን በተጨማሪ ቃላዊ መረጃና ጽሑፋዊ መግለጫ እንጠይቃለን:: በሥዕላዊ ምስል ወይም በቅርጻዊ ምስል ወይም በፎቶግራፍ ምስል ወይም በተንቀሳቃሽ ቅርጻዊ ምስል፣ ብቻ ምንነቱን ዓይተን ያለምንም ቃላዊና ጽሑፋዊ ማብራሪያ የምንገነዘብና የምናውቅ፣ ባጭሩ በሥዕላዊ ቋንቋነቱ የምንገነዘብና ከበረታንም ውስጣዊ ስሜቶቻችንና እሳቤዎቻችንን በሥዕላዊ ቋንቋ የምንገልጽ ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን ?!

ሁላችንም በተፈጥሮ የታደልናቸው ከሞላ ጎደል:- የማየት፣ የመስማት፣ የመንካት፣ የማሽተትና የማጣጣም ቅቡል ሕዋሳተ-ስሜቶች አሉን:: ከነሱ መካከል ለመሆኑ ይበልጥ የምንጠቀመው በየትኛው ሕዋስ ነው? በአንዱ ወይስ በሁለቱ ብቻ? ራሳችንን ጠይቀን እናውቃለን ? ከተጠቀምንባቸውስ ተፈጥሮ በለገሠችን ደመነፍሳዊ ግንዛቤያችን ወይስ በነቃ ኅሊናዊ አስተሳሰባችን ? የስሕተት ሁሉ ስሕተት መጀመሪያ እኛው እራሳችን ባመጣነው ልዩነቶችና አድልዎ እኛው ራሳችን የችግሩ ሰለባ መሆናችን ነው:: ይኸውም:-

እኔ ሥዕል አይገባኝም፣ መሣል አልችልም፣

እኔ ሙዚቃ አይገባኝም፣ ማዜም አልችልም፣........ ወ.ዘ.ተ. እንላለን::

"… one must learn to read, as one must learn to see and learn to live" እንዳለው ፈረንሳዊው ሠዓሊ ቫንሳን ቫንጎሕ፣ ለመሆኑ ለመናገር፣ ለመጻፍና ለማንበብ ስንት ዓመት ተማርን? ሠለጠንን? የዚያን ያህል ለሌሎች ሕዋሳተ ስሜቶቻችን ያደረግነው ትምህርትና ሥልጠና ምን ያህል ነው? ይቅርና ለመጻፍና ለማንበብ የወሰድነውን ጊዜ ግማሹን ያህል? እሺ. ሩቡን ያህል? ...... ፊደል ያልለየ፣ ያልጻፈና ያላነበበ፣ የንግግር ቋንቋ ያልተማረና ያልተናገረ መሃይም ተብሎ

ይፈረጃል:: የሥዕልንና የሙዚቃን ቋንቋዎች ያልለየ መሃይም ተብሎ ቢፈረጅ ያስነውር ይሆን?

ለአዎንታዊም ሆነ ለአሉታዊ መልሶቻችን አሁንም ምን ያህል እርግጠኞች ነን? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ለትንክሳና ለሃሣብ መቀስቀሻ ይበቃሉ:: በዚሁ ይቆዩ::

## 2. መንደርደሪያ ሃሣብ

በጠቢባኑ ልሂቃን ተደጋግሞ የተነገረና የተጻፈ ነገር ቢኖር፤ በሰው ልጅ የሚከናወን ማንኛውም ዓይነት ተግባር ወይም ሥራ በራሱ ምንነቱን ገላጭ (expressive) እንደሆነ ነው:: ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ ስንነሣ ማንኛውም ዓይነት የፈጠራ ጥበብ፤ የፈጣሪው ወይም የጠቢቡ ማለትም:- የደራሲው፣ የሠዓሊው፣ የማኅሌታዩ፣ የተዋናዩ፣ የዳንኪረኛው ወ.ዘ.ተ. የጥልቅ ስሜቱና እሳቤው (emotion and thought) መገለጫ፣ መተንፈሻ፣ ማሳያና ማስሚያ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን::

የሰው ልጅ ሰውአዊ ጥልቅ ስሜቱንና ረቂቅ አስተሳሰቡን በደመ ነፍሱም ሆነ በነቃ ኅሊናውም ቢሆን ወዲያው ወይም ዘግይቶ ለመግለጽ አማራጮቹ ብዙ ናቸው:: አካላዊ እንቅስቃሴው በቀዳሚነት፤ አንደበታዊ ድምፁ በሁለተኛነት አማካይና የጋራ ደመ ነፍሳዊ መገለጫዎቹ ናቸው:: በነቃ ኅሊናው ለመግለጽ ግን ማሰብ ስላለበት በቅድሚያ አእምሮውን በዕውቀት ማበልጸግ፤ ችሎታውን በክሂሎት ማሠልጠን ግድ ይለዋል፤ በዚያ ላይ የካበተ የሕይወትና የኑሮ ልምድ ደጀኖቹና አስፈላጊዎቹ ናቸው::

አንዳንዴ ተደጋግመው የሚጠየቁና ተደጋጋሚ መልሶች ያገኙ ግን ተመልሰው በየትውልዱ ውስጥ በድጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች አሉ:: ገጣሚው ሰሎሞን ደሬሳ «አንዳንድ ጥያቄ አለ አሥሬ ተጠይቆ አሥሬ መልስ አግኝቶ አሥሬ የሚጠየቅ» (ልጅነት 1963) እንዳለው ዓይነት እጅግ በጣም ብዙ አሉ:: እስቲ እኔም ልጠይቅ:: በዓለም ላይ የተፈጠረው የመጀመሪያው የሰው ልጅ መጀመሪያ ዓየ? ወይስ ሰማ?፤ መጀመሪያ ሣለ? ወይስ ጻፈ? መጀመሪያ በአካላዊ እንቅስቃሴው? ወይስ በአንደበታዊ ቃለ ድምፁ ተግባባ? የትኛው ቀደመ? ወይም ለጠቀ? ብዬ በዚህ መድረክ ላይ የእሰጥ አገባ ጥያቄና የመልስ ሐተታዊ ክርክር ማድረግ አልፈልግም:: መልሳችሁን ግን በእያንዳንዳችሁ ኅሊና ውስጥ አገናዝባችሁ አስቀምጡት:: በሌላ አምሳያ ለመነሻ የሚሆነኝን ላመላክት::

ወደዚህች ዓለም የመጡ ሕፃናት በልጅነታቸው ከመስማት በፊት ማየትን፣ ድምፀ ቃልን ከመለየታቸው በፊት የአካላዊ እንቅስቃሴን ቋንቋ፣ ቃላተ ፊደላትን ከመጻፍ በፊት ሥዕል መጫራቸውን፤ ወይ በልጆቻችን ወይም በማንኛውም ሕፃን ላይ ሳናይ፣ ሳንመለከት ወይም ሳናስተውል አንቀርም:: ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚህ ርእሰ ጉዳይ እኛን በይበልጥ የሚመለከቱን የማየትና የመንካት ወይም የመዳሰስ

ቅቡል ሕዋሳተ ስሜቶቻችን ሊረዱት፣ ሊገነዘቡት፣ ሊያስተውሉትና ሊገልጹት የሚችሉትን ሥዕላዊ ጥበብን ወይም ዕይታዊ ቋንቋን ነው::

## 3. ዐቢይ ሃሣብ - *ጥበብና ሥዕል፤ ሥዕልና ጥበብ*

ጥበብንና ሥዕልን መሳ ለመሳ በቀላሉ ለመግለጽ ቀላል አይደለም:: ምክንያቱም ዘርፈ ብዙ መልሶች ያሉት ትንታኔ ስለሚያስከትሉ:: በመሆኑም ባጭሩ ለጥቆማ ብቻ የሚያነጋግሩንን ነገረ እሳቤዎች እናነሳለን::

### 3.1 ጥበብና ሥዕል

**ጥበብ የአንድ ሕዝብና ሀገር የባህል አካል ነው፤** የቁሳዊና የኅሊናዊ ባህል መገለጫ፣ መገንዘቢያና መለያ ነው:: ጥበብ በሰው ልጅ ብቻ የሚሠራ የአእምሮአዊ አስተሳሰብና ዕውቀት፤ የአካላዊ ክሂሎትና ቅልጥፍና የሚፈጥሩት ኪነ ጥበብ ነው:: (Work of Art) ሥዕል ፣ ሙዚቃ ፣ ሥነ ጽሑፍ ፣ ቴአትር ፣ ወ.ዘ.ተ. የጥበብ አካል ናቸው:: ጥበብ በእኛም ሆነ በሌሎች ሕዝቦች አስተሳሰብ ያለው አጠቃላይ ትርጓሜና ግንዛቤ ሙሉ ለሙሉ ከነገረ ሥነ ወይም ከነገረ ውበት ጋር የተያያዘ፤ በከፊል ደግሞ ከሳይንሣዊ ነገረ ሃሣብና ተግባር ጋር የተጣመረ ነው::

**ጥበብ፤ በጥቅሉ ሲታሰብ:-** በኅብረተሰብ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሰው ልጅ የረዥም ዘመናት ሰብአዊ ተሞክሮዎችና ልምዶች ያካበተበትና ያስተጋበረበት፤ ራሱን ከተፈጥሮ እንስሳዊ ማንነቱ፤ ከድንቁርናና ከኋላ ቀርነት አስተሳሰቡና ተግባሩ ነፃ ያወጣበት፤ ሕያው የኅሊናዊ ዕውቀቱ ብልጽግናና ሀብቱ፤ የቁሳዊ ሥልጣኔው ቅርሱና ምስክሩ ነው:: እንደ:- ደ'አርሲ ሂይማን (D'Arcy Hyman)

> ***Art, which is the imaginative and skillful interpretation of experience in an esthetic object, has played through out history important roles in men's attempts to enjoy their environments and to liberate themselves.***

**ጥበብ፤ በዝርዝሩ ሲታሰብ:-** ደግሞ፤ የሰው ልጅ ጥልቅ ስሜቶችና ረቂቅ አስተሳሰቦች በምስላዊና ዕይታዊ ቅርጽ፣ ውብና ድንቅ፣ ግልጽና ስሉጥ፣ የበለጸጉና የዳበሩ ሆነው እንዲገለጹ ያስችላል:: የሰው ልጅ ጥልቅ ስሜቶች (Emotions) ማለትም:- ቅቡልና ገላጭ ስሜቶችን (Impressions and expressions) በምንታዊነት፤ ረቂቅ አስተሳሰቦችን (Thoughts) ማለትም የነቃና ያልነቃ እሳቤዎችን (Conscious and unconscious Thoughts) መሳ ለመሳ በመያዝ ያንፀባርቃል:: በመሆኑም እነዚህ ስሜቶችና አስተሳሰቦች በጥበባዊ ትምህርት ዕውቀትን፤ በጥበባዊ ሥልጠና ክሂሎትን፤ በቁስ ጥበባዊ መገለጫ ቅልጥፍናን በማጣመር ኪነ ጥበብን መፍጠር ይቻላል:: ኪነ ጥበቡ ውበታዊ ቅርጽ ያለው ገዛድና ተጨባጭ ይሆናሉ:: ይኸውም በኪነ ሥዕል ይታያሉ:: በኪነ ቅርጽ ይዳሰሳሉ:: በኪነ ሙዚቃና ዜማ ይሰማሉ::

በኪነ ጽሑፍ ይነበባሉ:: በኪነ ሕንፃ ይታያሉ፣ ይዳሰሳሉ:: በኪነ ቴአትርና ሲኒማ ይታያሉ፣ ይሰማሉ:: እንደ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሣይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) አገላለጽ የጥበብ ተግባርና ሚና ዓይነተ ብዙ ነው:: ይኸውም፦

«ጥበብ እንደ ግኝት ነው (as discovery)፤ ጥበብ እንደ ጥልቅ ስሜት ነው (as intensification)፤ ጥበብ እንደ መገለጫ ነው (as expression)፤ ጥበብ እንደ መዝገያ ነው (as record)፤ ጥበብ እንደ መግባቢያ ነው (as communication)፤ ጥበብ እንደ መተርጎሚያ ነው (as interpretation)፤ጥበብ እንደ ተሓድሶ ነው (as reformation)፤ ጥበብ እንደ ብልጽግና ነው (as enhancement)፤ ጥበብ እንደ ሥርዓትና ደንብ ነው (as order)፤ ጥበብ እንደ መስተጋብር ነው (as integration) » በማለት D' Archy Hyman በስፋት ያስገነዝባል::

## 3.2 ሥዕልና ጥበብ

የሥዕል ጥበብ ከላይ እንደተገለጸው የጥበብ አካል ነው፤ የባህልም:: የሥዕል ጥበብ ባጭሩ ሲገለጽ፦ ዕይታዊ ቋንቋና የፈጠራ ውጤት ነው:: የሥዕል ጥበብ በጥቅሉ ሲገለጽ፦ ደግሞ የአንድ ግለሰብ ወይም ኅብረተሰብ ወይም ሀገር የኅሊናዊና የቁሳዊ ባህል ማንነት መገለጫና መለያ ነው:: በመሆኑም የሥዕል ጥበብ በሥርዓተ እምነትና ሃይማኖት፣ በሥርዓተ እውቀትና ፍልስፍና፣ በሥርዓተ ማኅበረሰብና አኗኗር ውስጥ የሚከሠት፤ ለኅሊናዊና ለሰው ልጅ ሁሉ አገልግሎትና ጠቀሜታ የሚውል፤ እሴትና ፋይዳው የከበረና የላቀ፤ ታላቅ የባህል ሀብትና ቅርስ ነው::

የሥዕል ጥበብ መነሻና መድረሻ በተፈጥሮና በኅብረተሰብ ከባቢ ዓለም ውስጥ የሚኖር የሰው ልጅ ነው:: እያንዳንዱ ኅብረተሰብና ዘመን የየራሱን ጠቢብ ወይም ጠቢባንን፤ ሠዓሊ ወይም ሠዓልያንን፤ ኪነ ሥዕልን ወይም ኪነ ጥበብን፤ ፈጥሮ አልፏል፤ አሁንም እየፈጠረ ይገኛል፤ ወደፊትም ይፈጥራል::

በኢትዮጵያ የሥዕል ጥበብ ከጥንታዊ እስከ ዘመናዊ ድረስ የኅብረተሰቡን ኅሊናዊና ቁሳዊ ባህል በዓይነተ ብዙ ልዩነትና አንድነት በማጣመር የያዘ፤ ሰፊ፣ ጥልቅና ረቂቅ፤ ነገረ ሃሣብን (logic) በዕይታዊና በምስላዊ ገጹ በጋሃድና በተጨባጭ ያስቀረ፤ በተከታታይነት የነበረና ያለ ነው:: እንደ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ልሂቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሥዕል የአማርኛ ቋንቋ ከጥንታዊ የግዕዝ ቋንቋ እንዳለ በቁሙ የወረሰው ነገረ-ቃል (Terminology) ነው:: ሲተረጉሙትም፦

> ሥዕል፦ በቁሙ፤ መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ አምሳል፣ ንድፍ፣ ቢጋር፣ በውሃ፣ በመጽሔት፣ በጥልፍ፣ በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ፣ ተጽፎ ከጽብር፣ከእብን፣ ከዕፅ ፤ከማዕድን፣ ታንጦ፣ ተቀርጦ፣ ተሸልሞ፣ ተጊጦ፣ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር::

በማለት ያብራራሉ:: እንደዚያውም ሁሉ በዘመናዊው የሥዕል ጥበባት ፍልስፍና ሲታይ:-

- «ሥዕል- (Art)» የሚለውን ቃለ ግንዛቤ በመሻማት፤ ሥዕል ማለት ዕይታዊ ጥበብ (Visual Art) ሆኖ በሚታይና በሚዳሰስ ቁስ ጥበባት (Art materials) የሚከሠት ኪነ-ጥበብ (Work Art) መሆኑን፤
- ሥዕል በሁለት አውታረ መጠን (2 Dimensional) ዝርግ ሠሌዳዎች ላይ (በብራና፣ በወረቀት፣ በሸራ፣ በእንጨት፣ በብረት፣ በመስተዋት፣ በግድግዳና በግንብ፣ በበርና በመስኮት) ላይ በሥዕል አናሥራት ማለትም:- በመስመር፣ በዝርግ፣ በቅርጽ በብርሃንና ጥላ፣ በፍካትና በድባብ፣ በሻካራና ልስላሴ (ሻካልሴ)፣ በኅብረ ቀለማት ሙቀትና ቅዝቃዜ የሚሠራ:- ኪነ-ንድፍ (Drawing)፣ ኪነ-ቅብ (Paintings)፣ ኪነ-ኅትመት (Graphics)፤
- እንደዚሁም፤ሥዕል በሦስት አውታረ መጠናት (3 Dimensional) ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቁስ ጥበባት ላይ በጭቃ፣ በሸክላ፣ በእንጨት፣ በድንጋይ፣ በብረት፣ በከበሩ ማዕድናት፣ በዝሆን ጥርስ፣ በምስል ማፍሰስ ወይም ሰም-ተክ፣ በማነጥ፣ በመጥረብ፣ በመፈልፈልና በመቅረጽ የሚሠራ:- ኪነ-ቅርጽ (Sculpture) እንደሆነ በስፋት ያብራራሉ::

የሥዕል ጥበብ ዋነኛ መገለጫ በጥበባዊ የፈጠራ ሂደት የሚከሠቱ ኪነ ሥዕላት እንደመሆናቸው መጠን፤ ኪነ ሥዕላቱም በጥበባዊ ጥራትና ብቃት መሥፈርት እሴትና ፋይዳቸው ይመዘናል::

ይኸውም የሥዕል ጥበብ:-

- የዕይታዊና የምስላዊ ጥበብ ፈጠራ መሆኑን፤
- የኅሊናዊና የነገረ-ሥናዊ ግንዛቤ፣ ጣዕምና እርካታ (Esthetical taste and Satisfaction) ያለው መሆኑን፤
- ዘወትር ወጥና አዲስ (Original and New) መሆኑን፤
- በተናጠል የተፈጠረ፣ የማይባዛና፣ የማይደጋገም መሆኑን፤
- ተመሳሳይ የዋጋ እሴትና ተመን የሌለው መሆኑን፤ በተመልካች ዘንድ ከፍተኛ ግንዛቤ ማግኘት አለበት::

ከዚህ አኳያ ሲታይ በኢትዮጵያ ውስጥ የዋሻ ኪነ ሥዕላት በድሬዳዋና ሐረሪ ዙሪያ፤ የኪነ ሕንፃና ኪነ ሐውልት በቅድመና ድህረ አክሱም ዙሪያ፤ የትክልና የፍልፍል ደንጊያ በጥያና በጌዲዮ ዙሪያ፤ የኪነ ቅብና የኪነ ሕንፃ በላሊበላ፣ በጎንደርና በጣና ዙሪያ፤ እንዲሁም በዘመናችን በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም የክልል ከተሞች ዙሪያ የተሠሩት የታሪካችን፣ የባህላችንና የሥልጣኔያችን መገለጫ፣ መለያና ዓይነተኛ ነጸብራቅ በመሆናቸው እሴትና ፋይዳቸው እጅግ የተከበረ ነው::

## 3.3 ሠዓሊና ፈጠራ

በኢትዮጵያ የሥዕል ጥበብን የሚሠራ ባለሙያ ሠዓሊ ይባላል:: ይህም ነገረ ቃል ከጥንታዊ የግዕዝ ቋንቋ የተወረሰ የአማርኛ ነገረ ቃል ነው:: አሁንም አለቃ ኪዳነ ወልድ:-

*ሠዓሊ- /ሊት፣ ልያን፣ ልያት/ በማለት*
*የሚሥል፣ የሚፈጥር፣ ሣይ፣ ፈጣሪ*

እንደሆነ ሲገልጹ፤ ፈጠራን በተመለከተ ደግሞ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ:-

*ፈጢር:- መፍጠር፣ ማስገኘት፣ ካለመኖር ወደ መኖር ማውጣት፤ ......*
*ዐዲስ ነገር ማውጣት፣ መውለድ፤*
*ፈጣሪ:- በቁሙ አስገኝ፣ አምጭ፣ ሠሪ፤*
*ፈጠራ:- በቁሙ ልብ ወለድ ነገር፤*

በመሆኑም:- ሠዓሊ ሥዕል የሚሥል ብቻ ሳይሆን፤ አንድን ሃሣብ ካለመኖር ወደ መኖር የሚያመጣ፤ የሚያስገኝ፣ ከልብ የሚያፈልቅ፣ አዲስ ነገር የሚያወጣና የሚወልድ እንደሆነ ከነገረ ቃሉ ትርጓሜና ግንዛቤ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል::

ይህ ትርጓሜና ግንዛቤ በነባሩ የግዕዝ ቋንቋ የነበረውን ያህል በዘመናዊው የሥራ ቋንቋችን፤ አማርኛ እኩል ግንዛቤ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ እጅግ የረቀቀ ስሜትንና የበለጸገ እሳቤን የሚያሠርጽና የሚወደድ በሆነ ነበር:: ካልሆነም ወደ ኋላ ተመልሰን የነገረ ቃሉን ጽንሰ ሃሣብና ተግባራዊ ምስጢር በጥልቀት መገንዘብ ግድ ይለናል::

## 3.4 ሥዕልና ፈጠራ

በቅድሚያ የሥዕል ጥበብ የፈጠራ ጥበብ ሂደት ውጤት መሆኑ መታወቅ አለበት:: ለመፍጠርና ለመጠበብ ደግሞ ልዩ ተሰጥዖ ይጠይቃል:: *«ማንም ሰው:- ኪነ-ሥዕልን፣ ኪነ-ሙዚቃን፣ ኪነ-ዳንኪራንና፣ ኪነ-ጽሑፍን ሊማር ይችላል፤ ጥቂቶች ብቻ በሙያው ይሠለጥኑበታል::»* እንደሚባለው ያለ ሥዕል ተሰጥኦና የፈጠራ ሂደት የተሟላ አይደለም:: ይህም በበለጠ ሲገለጽና ሲብራራ:-

በሥነ-ጥበብ ሕይወትን ለመፍጠር፤ መጀመሪያ ፈጣሪው (ወይም ሠዓሊው) በውስጣዊ ጥልቅ ስሜቱ እውነታና በሥዕል ፍቅር ልቡ የነደደ፣ በአስተሳሰቡ የመጠቀና የበለጸገ መሆን አለበት:: ይህን በሥዕል ጥበባዊ ፍቅርና እውነት የተሞላ፤ የሠዓሊው ሥራ ወይም ውጤት ወይም ኪነ-ሥዕል ወይም ኪነ-ጥበብ፤ የዘመኑ ኅብረተሰብ ባይገነዘበውና ባይቀበለው እንኳን እያደር የሰው ልጅና ታሪክ በአክብሮት ይቀበለዋል::

በማለት ከፈጠራ ጽንስ ሃሣቡ ጀምሮ እስከ ተግባራዊ የጥበብ ፈጠራው አገላለጽ ድረስ፤ አልፎም ወደ ኅብረተሰቡ እስከሚደርስበት ድረስ ያለውን ሂደትና የኪነ ሥዕሉን የመጨረሻ ዕድል ሳይቀር በመግለጽ ሰፊና ጥልቅ ትንተና በሥዕል ሃያስያን መቅረብ እንዳለበት ሠዓልያኑና የሥዕል አድናቅያን ይናገራሉ::

ሠዓሊውም እንዲሁ ከሌሎች ሠዓልያን የሚለይበት የራሱ የፈጠራ ሂደትና ባህርያት አሉት::

*በመጀመሪያ:- ሠዓሊው የፈጠራ ጽንሰ ሃሣቡ ወይም የሥዕላዊ ድርሰቱ አመንጪና አቀነባባሪ ነው::*

*በሁለተኛ:- ሠዓሊው የዕውቀታዊና የክሂሎታዊ ብቃቱ ገላጭ፣ አከናዋኝና ፈጻሚ ነው::*

*በሦስተኛ:- ሠዓሊው በግላዊም ሆነ በማኀበራዊ ባህርያቱ የኀብረተሰቡ ሕይወት ተካፋይ ነው::*

በዚህም ምክንያት የሠዓልያኑ ግላዊ ዕውቀትና ችሎታ እንደሚኖሩበት አገር ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ማህበራዊ አኗኗርና ባህላዊ ሥርዓት የተለያየ በመሆኑ የየራሱ ማንነትና ግጼታ አለው:: ስለዚህ የአንድ ሠዓሊ ተግባርና ግዴታ:-

- ለሥዕል ጥበብ ያለው ተሰጥዖ፣ በዕውቀትና ችሎታ ላይ የተመሠረተ፣ በካበተ ልምድና ተግባር የደረጀ፣ በጥበብ ፍቅርና ሥነ ምግባር የተገራ መሆን አለበት::
- ዘወትር ወጥ፣ አዲስና የማይደጋገሙ የፈጠራ ኪነ ጥበባት መፍጠር አለበት::
- ወገናዊነቱ ለጥበብ፣ ለሰው ልጅ ፍቅር፣ ነፃነትና ሰላም፣ ለሀገራዊ ልማትና ማኀበራዊ እድገት መሆን አለበት::
- የፈጠራ ኪነ ጥበባቱን በሥዕል ትርዒት ለሕዝብ ማቅረብ አለበት::

ይህም በመሆኑ ሠዓሊውና ኪነ ሥዕላቱ:-

- በጥበብ አፍቃርያን፣ በሥዕል ሃያስያንና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኛል::
- ጥበባዊ የፈጠራ ኪነ ሥዕላቱ ከጊዜያዊነት አልፈው ቋሚና ዘላለማዊ እሴትን በማትረፍ በቅርስነት ከክብራቸው ጋር ለትውልድ ይተላለፋሉ::

## 3.5 ሥዕልና ሌሎች የሙያ ዘርፎች

«ከአንድ ሺህ ቃላት አንድ ሥዕል» እንዲሉ፣ የሥዕል ጥበብ አንድን ጥልቅ ውስጣዊ ስሜትና የነቃ ሃሣብ በዕይታዊ ምስል በቀላሉ ለመግለጽም ሆነ ለማስገንዘብ በቂ ኃይል አለው:: በመሆኑም ከጥንት ቅድመ ታሪክ ጀምሮ እስከ ታሪክ ዘመንና የዘመናችን የሥልጣኔ ደረጃ ድረስ፣ ተፈጥሮንና ኅብረተሰብን መሠረት አድርጎ የሚፈጠረው የሥዕል ጥበብ የሰው ልጅን ኅሊናዊና ቁሳዊ ባህል በማዳበርና በማበልጸግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በየሁሉም የሥራ ዘርፎች ውስጥ በግብአትነት እያገለገለ ይገኛል:: ይኸውም:-

*ሀ፦ የሥዕል ጥበብ በቀጥታ የሥነ-ጥበብ ሙያ ነው::* እንደ ሥነ ጥበብ ሙያና ባለሙያ እውቀትና ችሎታ ውበትን ተላብሰው በሚገለጹ አዲስና ወጥ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ፦ በኪነ ቅብ፣ በኪነ ኅትመት፣ በኪነ ቅርጽ፣ በኪነ ሕንፃ ጥበባት ላይ፤ በምስላዊ አስተሳሰብና አገላለጽ ተግባራዊ ሆኖ *በቀጥታ* ይገኛል::

*ለ፦ የሥዕል ጥበብ በከፊል የዕደ ጥበብ ሙያና* እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶች ሥዕላዊ ማቀናበሪያ ነው::

- ትውፊታዊና ባህላዊ የእጅ *ሥራዎች* (በሸክላ፣ በእንጨት፣ በብረት፣ በደንጊያ፣ በቆዳ፣ በልብስ፣ ወዘተ *ሥራዎች*)፤
- እንዲሁም በዘመናዊ ቴክኒዎሎጂ የኢንዱስትሪ ውጤቶችና ምርቶች ውስጥ (ከጫማ እስከ ልብስ ዲዛይን፣ ከመርፌ እስከ ሮኬት ዲዛይን ወ.ዘ.ተ ድረስ) በምስላዊ አስተሳሰብና አገላለጽ ተግባራዊ ሆኖ *በከፊል* ይገኛል::

*ሐ፦ የሥዕል ጥበብ በተዘዋዋሪ በማንኛውም ሙያ ውስጥ ያለ ሙያ ነው::*

ለምሳሌ፦ በትምህርት ዘርፍ፣ በህክምና ዘርፍ፣ በንግድ ዘርፍ፣ በግብርና ዘርፍ፣ በስፖርት ዘርፍ፣ በቱሪዝም ዘርፍ ወ.ዘ.ተ. በሣይንሳዊና በምርምራዊ ዕውቀቶችና ክሂሎቶች ውስጥ በምስላዊ አስተሳሰብና አገላለጽ *በተዘዋዋሪ* ሲያገለግል ይገኛል::

## 4. ማጠቃለያ ሃሣብ

- ***የሥዕል ጥበብ ለባህልና ልማት ዕድገት***

የሥዕል ጥበብ ከሥነ ጥበባትና ከሌሎች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ጋር ያለው ትስስርና ግንኙነት እጅግ በጣም ረቂቃዊና ድንቃዊ ነው:: በሌላ አባባል ከሥዕል ጥበብ ጋር ያልተያያዘና ግብአት የማያገኝ የሥራ ዘርፍ ስለ አለመኖሩ በእርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል:: በእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ ውስጥ በቀጥታ፣ በከፊልና በተዘዋዋሪ እንደአለ የታወቀ ነው::

<u>በቅድሚያ ዕሊናዊ ልማት፤</u> የሥዕል ጥበብን ለመገንዘብ፣ ለመረዳትና ለማወቅ፤ በመጀመሪያ የዓይንን ሕዋሳተ ስሜት በሚገባ እንዲያይ ማሠልጠን፤ በሁለተኛ ከዓይነ ሕዋስ የሚደርሰውን መልዕክት አእምሮ በሚገባ እንዲገነዘብ ማሳወቅ፤ በሦስተኛ አካልን በተለይም እጅን ከአእምሮ የመጣለትን ትእዛዝ በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዲያከናውን ማሠልጠን ያስፈልጋል:: ሦስቱም በአንድነት ተስተጋብረውና ተሳልጠው፤ በብቃትና በጥራት ሥዕላዊ ጥበብን እንዲፈጥሩ ማስቻል የዕውቀትም የክሂሎትም ውጤት ነው::

ለመሆኑ አስበነው እናውቅ ይሆን? እንዴት እናያለን ብለንስ ጠይቀን ይሆን? ማየት:- ማየት ነው፤ ለማየት ደግሞ ምን መሠልጠን ያስፈልጋል? የምንል አንጠፋም:: ብዙ ሰዎች ስለማየት የሚናገሩትና የሚያስገነዝቡት ዓይነቱ ብዙ ነው::

ማየት የዘልማድ ነው፣
የምናየው ማየት የለመድነውን ብቻ ነው የሚሉ አሉ፣
ማየት የፍላጎት ነው፣
የምናየው ማየት የፈለግነውን ብቻ ነው የሚሉ አሉ፣
ማየት የልዩ ሙያ ትምህርትና የሥልጠና ውጤት ነው፣
የምናየው ማየት የተማርነውንና የሠለጠንበትን ብቻ ነው የሚሉ አሉ::

ለምን በልማድ፣ በፍላጎትና በልዩ ሥልጠና ላይ ብቻ እንወሰናለን? ዓይነ ሕዋሳችን ሊያይ፤ ዓይነ ኅሊናችንም ሊገነዘብ የሚችለውን ያህል እንጠቀምበት የሚያስገድደን የተፈጥሮ፣ የሰው ልጅነትና የማኅበረሰብ ግዴታ አለብን:: ማየት ጥበብንና ማስተዋልን ይጠይቃል:: ለመጠበብና ለማስተዋል ደግሞ የማየት ጥበብን መማርና መሠልጠን ግድ ይላል::

ጤነኛ ዓይን ያለው ማንኛውም ሰው ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ሳይወስኑት የማየት ጥበብን ቢማርና ቢሠለጥን የውብ ዓለምን ተፈጥሮንና የሰው ልጅን ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ከነገረ አካል እስከ ነገረ አእምሮ ድረስ ያለውን በምስላዊ ገጽታ ለመገንዘብ፣ ለመረዳትና ለማወቅ አልፎም ለማሰብና ለማስተዋል ሰፊ ዕድል ይሰጣል::

የሥዕል ጥበብ ለባህልና ልማት ዕድገት እንዲውል ከተፈለገ፤ በመጀመሪያ ሕፃናትን ከልጅነት አንስቶ በተፈጥሮ የታደሉትን ሕዋሳተ ስሜት እንዲያበለጽጉ (እንዲያዩና እንዲመለከቱ፤ እንዲሰሙና እንዲያዳምጡ፤ እንዲነኩና እንዲዳስሱ፤ እንዲያሸቱና እንዲለዩ፤ እንዲቀምሱና እንዲጣጥሙ)፤ የሚሰማቸውንም ስሜት እንዲገነዘቡት፣ እንዲረዱትና እንዲያውቁት አግዟቸው፣ ተንከባክቧቸው የሚባለው:: ያን ጊዜ በተመጣጠነ ሕዋሳተ ስሜት የሚያገኙትን መረጃ በመጠቀም ኅሊናቸው ይለማል፤ አእምሮአቸው ያስባል፤ የለማ ኅሊናና የሚያስብ አእምሮ ያስተውላል፤ ሁለገብ እውቀትንና ችሎታን ያጎናጽፋል:: ቀደም ሲል እንደተገለጸው በባህል ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሣይንስ ዘርፍም ጭምር አማካይ እውቀትና ግንዛቤን ይሰጣል:: በዚያውም ልክ አካላዊ ችሎታ ይቀላጠፋል፣ ይካናል አልፎም ይጠበባል:: በሥነ ጥበብ ግብአት በአእምሮም በአካልም የበለጸገ ዜጋ ለልማትና ለዕድገት ሁለገብ አቅም ከማግኘቱም ሌላ የውብ ዓለምን ተፈጥሮና የሰው ልጅን ኪነ ጥበብ ለማድነቅ ታላቅ ኃይል ይቀዳጃል::

ዛሬ የዓለም ሀገር ጎብኚዎችን (የቱሪስትን) ዓይንና ልብ በመሳብ የውጭ ምንዛሪ ከሚያስገኙት ቅርሶች መካከል በቀዳሚነት:- የአክሱም ኪነ ሐውልቶች፣ የጥንታዊ ቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ኪነ ሥዕላት፣ የላሊበላና የጎንደር ቤተክርስቲያናትና ቤተ መንግሥታት ኪነ ሕንፃዎች፣ የሐረሪ ግንብ፣ የጥያና የኮንሶ የመቃብር ሐውልቶች፣ እንዲሁም በዘመናችን የሀገራችን ታላላቅ ሠዓሊያን ኪነ ሥዕላት፣

የአዲስ አበባ ታሪካዊ ሐውልቶች፣ የመቀሌ፣ የባሕር ዳርና የአዳማ ሰማዕታት መታሰቢያ ኪነ ሐውልቶች የተፈጠሩት በሥዕል ጥበብ ሙያና በጠቢባን ባለሙያዎች ሙሉ ዕውቀትና ክሂሎት የተሠሩ ለመሆናቸው ማንም አሌ ሊለው የማይችላቸው ናቸው::

ዛሬ ሀገራችን በተያያዘችው ፈጣን የልማትና የለውጥ እድገት ውስጥ:- መልካም ዜጋን ለመፍጠር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ መልካም አገራዊ ገጽታን ለማስተዋወቅ፣ መሃይምነትንና ድህነትን ለማጥፋት፣ ከሚደረገው ትግል አኳያ የሥዕል ጥበብ የሚኖረውና የሚጫወተው ሚና እጅግ በጣም ጠቃሚና ወሳኝነት ያለው ነው::

## 5. ምርቃት

- ***እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬየት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ***

***የመስቀል አበባ (1951/52)***

**1959 - 60 (እ.ኤ.አ.) የተሣለ ሥዕል ነው:: የወቅቱን ሁኔታ ለማንፀባረቅ:: ስለዚህ ለምን የፊውዳሉ ገጽታ ኖራት አይባልም፤ ቁም ነገሩ ሥዕል ምንን ይወክላል? ምን ይናገራል? ከሚለው ነው:: በርግጥ የቤተ መንግሥት ሰው ናት:: ቆንጆ ናት ግን ይህንንም ያህል ውበት የሚታይባት አይደለችም:: በዚያን ወቅት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ቆንጆዎች ብቻ ሣይሆኑ ሁሉም ዓይነት መልክ ቆለኛው፣ ደገኛ ው፣ ሰሜኑ፣ ደቡቡ፣ ፊውዳሉ፣ ገበሬው ወ.ዘ.ተ. ይታይ ስለነበረ መልኳ ያን ይወክል ይሆናል:: አቀርቅራለች በአንድ እጇ አበባ (የአደይ) ቁርጣ ይዛለች:: መቼም ሊሸተት ወይም ሊጌጥበት መሆን አለበት፤ ግን ተክዛለች፤ አበባው ከእጇ ሊወድቅ ደርሷል:: ሌላኛው እጇ ካባ ጨብጧል ከላይዋ ለማንሳት ወይም እንዳይወድቅ ለመከላከል አለሁ ለማለት ይመስላል.....አንደኛው እግር በደንብ በመራመድ ላይ ነው፤ ሁለተኛው የት እንዳለ አይታወቅም፤ መኖሩ ግን አይጠፋንም:: ሌላው በዚህ ሥዕል ላይ የሚታየው በቀለም አጠቃቀም ረገድ የተፈጠረው ጥበብ ነው:: እንደሚታወቀው አረንጓዴና ቀይ ተጻራሪ ቀለሞች ናቸው:: ሁለቱን ለማዋሀድ (ሀርሞናይዝ ለማድረግ) እጅግ ያዳግታል፤ እዚህ ሥዕል ላይ ግን ውህደት አግኝተው ይታያል:: ሌላም ማንሣት ይቻላል:: ካባው፣ ቀሚሱ፣ የፀጉር አሰራሩ በዚያን ዘመን ይዘወተር ነበር? ከውጭ የመጣ ነው ወይስ የሀገር ውስጥ ዲዛይን? የካባውን፣ የቀሚሱን ዲዛይን ማን ሠራው? ጥሩ ተመልካች እነዚህን ነቅሶ ለማውጣትና ትርጉማቸውን ለመረዳት የሚጥር ነው::**

*አዲስ፣ ሚያዝያ 1993፣* **ቅጽ 6 ቁጥር 3፣ ከገጽ 20 ኘ 37፣ (በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በባህልና ማስታወቂያ ቢሮ በየሶስት ወሩ ከሚዘጋጅ መጽሔት ላይ የተወሰደ ቃለ መጠይቅ)::**

**የመስቀል አበባ፤ 1951 የዘይት ቀለም በሸራ ላይ፤ 170 X 75 ሣ.ሜ.**

***አነስተኛ ኅልዮታዊ ሐተታ***

- የመስቀል አበባ ቆንጆ ወጣት ሴት ናት፤ ቀይ ካባ የለበሰች፤ ነጭ ረዥም ቀሚስ ያጠለቀች፤ ሳንቃ ደረቷ የተገለጠና በደረቷ ላይ መስቀል ያንጠለጠለች፤ ፊቷ ከሳ ያለ፤ ዓይኖቿ የጎሉ፤ ፀጉሯ ተሰብስቦ ወደ ላይ የተሠራ፤ በጆሮዋ ላይ ጉትቻ ያደረገች፤ ግራ እጇ ካባዋን የያዘ፣ የብር አምባርና ቀለበት ያጠለቀ፤ ቀኝ እጇ የአደይ አበባን ይዞ ወደ ፊት የሚያመለክት ግን በሆዷ አካባቢ የሚታይ ነው፤

- ከጨለማ ወደ ብርሃን የምትወጣ ሰልካካ ወጣት በተመስጥዖ መንገዷን ወደታች የምትመለከት፤ ግን በረዥም ርምጃ ግራ እግሯ የነጠላ ጫማ ተጫምቶ ቀደም ብሎ የሚታይ ሲሆን፤ ቀኝ እግሯ በለበሰችው ሸማ የተሸፈነ ነው፤

- ሁለት እጆቿ የራሳቸው ዕይታዊ ቋንቋ አላቸው፤ አንዱ የጥንቃቄ አንዱ የአበባ ተምሳሌት፤ አለባበሷ ደግሞ በዘመናዊ አቀራረብ የተቀናጀ የዚያ ዘመን የፊውዳል ሥርዓት አለባበስ እንደሆነ ይታያል፤

- ይህ የመስቀል አበባ ኪነ ቅብ ከሃምሣ ዓመታት በኋላ በዘመኑ አነጋጋሪ የሆነውን እሳቤ አልፎ ዛሬ አዲስ ግንዛቤ የሚያስገኝ፣ በተምሳሌት የተመላ ኪነ ጥበብ ነው፡፡

ሀ. ወጣት ሴት፤

ለ. ቀይ ካባ፤

ሐ. የጥቁር አረንጓዴ ሕብረ ቀለም ደጀን፤

መ. ነጭ ሸማ፤

ሠ. አደይ አበባ፤(ከአበባ ቀጥሎ ፍሬ እንደሚያፈራ ሁሉ በሆዷ አካባቢ መታየቱ ደግሞ...)

ረ. እርምጃ፤ (ከጭለማ ወደ ብርሃን...)

# የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ

*ውዱ ጣፈጠ*

## 1. መግቢያ

ቀደም ባሉት መንግሥታት ስለነበረው የሃይማኖት መቻቻል ጉዳይ ንግግር ማድረግ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ በሃይማኖት ላይ ይደረግ ስለነበረው ጭቆና መናገር የሚቀል ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ግን የሃይማኖት መቻቻልን የሚያመላክቱ አንዳንድ ነገሮች አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ ምሳሌ ሊሆኑ ስለሚችሉ አንዳንድ ነገሮችና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተመርኩዘን ለእኛ የሚበጀንን ነገር ለመገንባት የሚያስችሉ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ህዝብን ሊያሳምኑ ሊያስተባብሩና የህብረተሰብን ማንነት ሊገነቡ የሚችሉ ቁምነገሮች አልባሌ ከሚመስሉን ነገሮች ላይ እያወጣጣን ምሳሌ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡ ወደሌላው ነገር ከመግባታችን በፊት እስኪ የሚቀጥሉትን ኩነቶች እናስተንትን፡፡

አሁን የምነግራችሁ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትን ስላጋጠማቸው ልምድ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ታደሰ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህር የነበሩና *ቤተክርስቲያንና መንግሥት በኢትዮጵያ* (Church and State in Ethiopia 1972) እና ሌሎች ብዛት ያላቸውን መጣጥፎችን ያበረከቱ የታሪክ ሊቅ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በጡረታ ተገልለው በአሜሪካን አገር ይኖራሉ፡፡

በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ለዶክተሬት ጥናታቸው ከለንደን ወደ ኢትዮጵያ ይመጡና ለመስክ ጥናት ወሎ ክፍለ ሃገር ይሄዳሉ፡፡ በዚሁ ምክንያት ስሙን አሁን የማላስታውሰውን ትልቅ ደብር ይጐበኛሉ፡፡ ይህንን ደብር ለመጐብኘት እንደሄዱ ደብሩ ያለውን መጻህፍት ለማየት አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም የዚህን ደብር የእቃ ቤት ቁልፍ የሚይዘው ሰው በአካባቢው አልነበረም፡፡ ስለዚህም ለመጠበቅ ይገደዳሉ፡፡ ቁልፍ ያዡ ተፈልጐ ሲመጣ ቁልፉን ከፈተና ቁጭ ብለው ሲጠብቁ ለነበሩት ቄስ ይግቡ ይላቸዋል፡፡ ፕሮፌሰር ታደሰም አንተ ግባና መጻሕፍቱን አሳየን እንጂ ብለው ይጠይቁታል፡፡ ጌታየ እኔ መግባት አልችልም ሙስሊም ነኝ ይላቸዋል፡፡ በጉዳዩ የዛ ጊዜው ታደሰ ግራ ይጋባሉ፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም የቤተ ክርስቲያን እቃ ግምጃ ቤት ቁልፍ ያዥና የንብረት ጠባቂ የሆነ ሙስሊም ሰው አጋጥሟቸው አያውቅምና፡፡ በኋላ እንደተረዱትም፣ ቁልፍ ያዡ ሙሲሊም ለደብሩ የመጀመሪያው አገልጋይ እንዳልሆነና ከሱ በፊት አባቱ ቁልፍ ያዥ እንደነበሩና የአባቱን ስራ በመውረስ ለብዙ ጊዜ በስራው ላይ እንደነበር

ይገልጽላቸዋል። ይህ የሆነበትም በጃቸው ያለው መሬት በጊዜው የሰሞን መሬት የነበረና ያንንም መሬት የሚጠቀም ሰው ቤተክርስቲያንን የማገልገል ግዴታ ስላለበት ነው። ወይ ራሱ ያገለግላል ወይም ቀጥሮ ሌላ ሰው (ቶፉ) እንዲያገለግል ያደርጋል።

አንድ ሌላ ምሳሌ እዚሁ ልጨምር። ቀሲስ ሀዲስ የተባለ ጓደኛዬ በትምህርት አሜሪካን አገር በነበርኩበት ጊዜ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከተመለሰ በኋላ ያጫወተኝ ነው። ኢትዮጵያ የመጣው በ2000 ዓ.ም. ነበር። ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወደ ውርጌሣ (ወሎ) በሄደበት ጊዜ ያጋጠመው ነው። ውርጌሣ ከተማ አጠገብ በከተማው በስተምዕራብ በኩል ካለው ተራራማ ጥግ በደርግ ዘመን የወጣ ጋቲራ ጊዮርጊስ የተባለ የጠበል ቦታ አለ። ቤተክርስቲያኑና ጠበሉ የሚገኘው ሙስሊሙ ህብረተሰብ በብዛት በሚኖርበት አካባቢ ነው። ካህናቱ የሚያገኙት ቀለብ አነስተኛ ሆኖባቸውና መሬትም ስለሌላቸው በየጊዜው እየለቀቁ ይሄዳሉ። በዚህ ምክንያት ቤተክርስቲያኑ እንዳይዘጋ የአካባቢው ሙስሊሞች ገንዘብ እያዋጡ ለካህናቱ ይከፍሉ ነበር። ከዚያ ወዲህ እንዴት እንደሆነ ግን አላውቅም።

ሌሎች ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል። ወደፊት ስለምመለስበት አስቀድሜ የሃይማኖት መቻቻል ምን ማለት ነው ለሚለው ጥቂት ሃሳብ ልስጥ። ከዚያም ስለሃይማኖት መቻቻል የሚያስረዱ ጥቂት ነገሮችን አቀርባለሁ።

## 2. የሃይማኖት መቻቻል ሁኔታዎች

የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰ ሀሳብ የተጀመረው በአውሮጳ ሲሆን ይህም በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን በተጀመረውና ሪፎርሜሽን (Reformation) በተባለው የሃይማኖት ንቅናቄ ጊዜ ነበር። ከዚህ በፊት በሃይማኖት ልዩነቶች ምክንያት ሰዎች መሰደድና በሞት የመቀጣት እድል ይገጥማቸው ነበር። ከዚህ በኋላ ግን ቀስ በቀስ የሃይማኖት መቻቻል ጉዳይ ስር እየሰደደ ሄደ።

የሃይማኖት መቻቻል ማለት የሌላውን ሃይማኖታዊ እምነት እንዲሁም ሥራ ከራስህ ሃይማኖት ጋር የማይዛመድ ቢሆንም እንዲያካሂዱ መፍቀድና ልዩነትን መቀበል ያመለክታል። የሃይማኖት መቻቻል ለሌላው መጥፎ አመለካከትና ጥላቻ ሳያሳድሩ ተቻችሎ መኖርን ያንፀባርቃል። አንዱ ለሌላው ያለውን ቅን አመለካከትም ያሳያል።

በሃይማኖት የቁጥር የበላይነት ያለው ክፍል በቁጥር አናሳ ለሆነው የሃይማኖት ክፍል ያለውን ቅን አመለካከት ያሳያል። በሌላ በኩልም የሃይማኖት መቻቻል አንዱ ለሌላው ሃይማኖት የሚያሳየውን ቻይነት ስለሚያመለክት እኩልነት ያልሰፈነበትና መለያየትን የሚያመለክት ነገር መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ሃይማኖቱ የመንግሥት የሆነ እንደሆነ የሃይማኖት መቻቻል ማለት መንግሥት በሀገሪቱ ለሚገኙ ሌሎች የሃይማኖት ክፍሎች ሃይማኖታቸውን እንዲያራምዱ መፍቀዱንና ሌሎች አማኞችን አለማሳደዱን የሚጠቁም ነው። ነገር ግን ሃይማኖቱ የመንግሥት ከሆነ በተለያየ መንገድ በሌሎች አማኞች ላይ አንዳንድ ተፅዕኖዎችና ልዩነቶች መኖራቸው አይቀርም።

የሃይማኖት መቻቻል የመንግሥት ፖሊሲ ከሆነ በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት መሳደድ የለም ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም ሁሉም ሃይማኖቶች በህግ ፊት እኩል ናቸው ማለት አይደለም። የሃይማኖት መቻቻል በመንግሥት የተሰጠ ልዩ መብት እንጅ ይገባኛል ተብሎ የሚጠየቅ መብት እንዳልሆነ የሚገልጹ መረጃዎችም አሉ። ምክንያቱም መንግሥታት ለአንዳንዱ ሃይማኖት መቻቻልን ሲያሳዩ ለሌሎቹ ይነፍጉዋቸዋልና።

የሃይማኖት ነፃነት እምነትን በነፃነትና ያለፍራቻ የማምለክ ጉዳይ ነው። የሃይማኖት ነፃነት በታወጀበት አገር ሰዎች ያለምንም ፍራቻና ስጋት እንዲሁም አደጋ እምነታቸውን ያካሂዳሉ። የሃይማኖት እኩልነት ስንልም ሁሉም አይነት አማኞች በእኩልነት የሚኖሩበት ሁኔታ ነው። አንዱ እምነት ሌላውን ሳይቆጣጠረውና ሳይገድበው በእኩልነትና በሰላም አብረው የሚኖሩበት ነው።

የሃይማኖት መቻቻል በእያንዳንዱ ግለሰብ እይታ በአጠቃላይ ለሌላው እምነት አማኞች የሚያንፀባርቀውን ቅበላ የሚያረጋግጥ ነው። በግለሰብ እይታ አንዱ እምነት ከሌላው ሃይማኖት ያለምንም እንከን እኩል ባይሆንም የራሳቸውን እምነት ማመንና በስራ ላይ የማዋሉን መብት መቀበል ነው።

መንፈሳዊ መቻቻል በአንድ እምነት ውስጥ የሚገኙ ልዩነቶችን የመቀበል አዝማሚያ ነው። ነገር ግን መንፈሳዊ ቀኖናን የሚጥስ ነገር የሚያራምዱ ሰዎች ከኖሩ መቻቻል ሊኖር አይችልም።

የታሪክ ሰነዶችን ወደኋላ ተመልሰን ያገላበጥን እንደሆነ ከክርስቶስ ልደት 600 ዓመታት ቀደም ብሎ የፋርስ ንጉስ ታላቁ ሲረስ (Cyrus) አይሁዶችን ከእንግልት ነፃ በማድረግ በግዛቱ የሃይማኖት መቻቻልን አውጆ ነበር። እ.ኤ.አ. 313 ዓ.ም. የሮማው ቆስጠንጢኖስ ፩ኛ በሮማ ግዛት የሃይማኖትን መቻቻል አውጆ ነበር። እ.ኤ.አ. በ1190 ዓ.ም. ጋንጀስ ከሀን በግዛቱ ውስጥ ተመሳሳይ ህግ አውጥቶ ነበር። እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ አለማቀፋዊ የሰብአዊ መብትን አውጆ ነበር። በዚሁ መግለጫ አንቀጽ 18 ላይ ማንም ሰው ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የመለወጥ፣ በነፃነት በግለሰብ ደረጃ ወይም በማህበራዊ ሁኔታ የማምለክ ወይም በነፃነት ማካሄድ ይችላል ይላል። እ.ኤ.አ. በሚያዚያ 1988 ዓ.ም.

ሚካኤል ጉርባቾቭ ባካሄዱት የግላስኖት እንቅስቃሴ ሰፊ የሃይማኖት መቻቻል እንደሚኖር ቃል ገብተው ነበር።

በአለማችን የተለያዩ ሀገሮች የሃይማኖት ጭቆና፣ ዲሞክራሲን አስፍኛለሁ በምትለው አሜሪካ ጭምር፣ ተንሠራፍቶ የቆየ ነገር ነው። ከዚህ የተነሳ ብጥብጥና አለመግባባት ሰፍኖ ኖሯል። በህንድ፣ በአይርላንድ፣ በናይጀሪያና በሌሎች አገሮች ላይም አስቸጋሪ ነገር ሆኖ ነበር። ይሁን እንጅ ከእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ወደ መቻቻል እየተሸጋገሩ ሲሄዱ አልፎ አልፎ ብጥብጡ የሚከሰትባቸው አገሮች አሁንም አሉ።

## 3. የአገራችን ሁኔታ

ታሪክን ወደ ኋላ ተመልሰን ስናጤን ለሃይማኖት መቻቻል ጠንካራ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ታሪካዊ ድርጊቶችን እናገኛለን። በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት በአንደኛው የአክሱም ንጉሥ ዘመን ከአረቢያ የተሰደዱና በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ወደ ሀገሪቱ የመጡ ብዛት ያላቸውን ሙስሊሞች በወዳጅነትና በመግባባት አክሱም ተቀብላ አስተናግዳለች። በተለይም የስደተኞቹ ጠላቶች መልእክተኛ ልከው ወደ አረቢያ ለመውሰድ ያቀረቡትን ጥያቄ ችላ በማለት በነፃነት አዲሱን ሃይማኖታቸውን እንዲከተሉ እድል ሰጥታለች።

የአክሱም መንግሥት ይህንን የመሰለ የማስተናገድና የማስጠጋት መብት በመስጠቱ ነቢዩ መሐመድ ኢትዮጵያ ጽድቅና፣ ግብረገባዊነት፣ ፍትህ የሰፈነባት አገርና፣ ፈጣሪ ለተገፉና ለተጐሳቆሉ ሰዎች ከሰቆቃቸው እንዲፅናኑ የሰጣት አገር ናት ማለታቸውን የአረብ ፀኃፊዎች ይገልፃሉ። በተጨማሪም በጊዜው ይካሄድ ከነበረው የአረብ መንግሥት መስፋፋት ኢትዮጵያ ጥቃት እንዳይሰነዘርባት በመምከር ኢትዮጵያውያን ጥቃት እስካልከፈቱ ድረስ ተዋቸው በማለት ለተከታዮቻቸው መመሪያ ሰጥተዋል።

እስልምና ወደ ሀገሪቱ የተስፋፋው በጦር ኃይል ሳይሆን ሰላማዊ በሆነ መንገድ በንግድ ግንኙነት ነበር። ሙስሊም ነጋዴዎች በገበያ ቦታዎች ላይ በመቀመጥ ከአካባቢው ሰው ጋር እየተጋቡ ቀስ በቀስ ሃይማኖታቸውን ማስፋፋት ችለዋል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በመካከለኛው ዘመን በነበረው "የሰሎሞናዊ" ስርወ-መንግሥት መሪዎችና በግብጽ ሀገር መካከል ተመስርቶ የነበረው መግባባትና መቀራረብ ነበር። "የሰሎሞናዊ" ስርወ-መንግሥት መስራች የነበረው አፄ ይኩኖ-አምላክ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ከየመንና ከግብፅ መሪዎች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንደነበረው የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። እንዲያውም ከሁሉም ሙስሊሞች ጋር ወዳጅ እንደነበር ያስረግጣል።

የየመኑን መሪ መልካም ፈቃድ በማግኘት የግብፁ ሱልጣን ወደ ሀገሩ ጳጳስ እንዲልክለት ይኩኖ-አምላክ በጻፈው ደብዳቤ፣

> ወደ ግዛታችን የሚመጡ ሁሉንም ሙስሊሞች ጥበቃ እናደርጋለን፣
> በግዛታችን ውስጥ እንደፈለጉ እንዲዘዋወሩ ፈቃድ እንሰጣቸዋለን

በማለት የነበረውን የሃይማኖት መቻቻል ይገልጻል፡፡ አክሎም በሠራዊቱ ውስጥ ብዛት ያላቸው የሙስሊም ወታደሮች እንደነበሩ ያረጋግጣል፡፡[1]

የስልጣኑ ወራሽና ልጁ አፄ ይግባ ፅዮን ለግብፁ ሱልጣን በላከው ደብዳቤ በግዛቱ ከሚኖሩ ሙስሊሞች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዳለው ገልፆ፣ የግብፁ ሱልጣን በግብፅ ከሚኖሩ ክርስቲያኖች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲመሰረት አስገንዝቦታል፡፡ አያይዞም

> በግዛቴ የሚኖሩ ሁሉንም ሙስሊሞች ጥበቃ አደርግላቸዋለሁ፣
> እንደዚሁም ሱልጣኑ በግዛቱ ውስጥ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች
> ተመሳሳይ ድርጊት እንደሚያደርግ እመኛለሁ፡፡ በዚህም
> በመካከላችን ዘላቂ የሆነ ጓደኝነት እንዲሰፍን፣ እንዲሁም
> በጋራ የተወካይ መልእክተኞች (አምባሳደር) እንዲጠናከር…"

በማለት ምኞቱንና ፍላጐቱን ገልጿል፡፡[2] ወደ ግብፅ የተላከው የኢትዮጵያ መልእክተኞች የተመራው ዩሱፍ አብዱራህማን በተባለ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ዩሱፍ ካይሮ እንደደረሰ ከዚህ ዓለም በመለየቱ በሌላ ሰው ተተክቷል፡፡

ነገር ግን ሁለቱም ነገሥታት የጠየቁት ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣቱ ምክንያት ይህ በጥሩ መሠረት ላይ ገንብተውት የነበረው ወዳጅነት ዘለቄታ ሳይኖረው ቀረ፡፡ በምትኩ ሁለቱም መሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በተመሰረቱት የሙስሊም የአካባቢ መንግሥታት ላይ ጥቃት እንደሰነዘሩ ይታወቃል፡፡

የመካከለኛው ዘመን ታሪክ በአብዛኛው በክርስቲያን መንግሥቱና በሙስሊሞች መካከል በተካሄደ የፖለቲካዊና የምጣኔ ሀብታዊ ውዝግብ እጅግ የታወቀ ነው፡፡ የገበያ ማዕከላትንና የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር፣ የገበያ ሸቀጦች የሚያመርቱ አካባቢዎችን ለመያዝ ያለማቋረጥ የተደረገ ጦርነት ተካሂዷል፡፡ የአካባቢው የሙስሊም መንግሥታትም ለኑሮ አመች ካልሆነው ደረቅ አካባቢ በመነሳት ወደለማውና ወደ ደጋው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ግዛት ለመስፋፋት ጥረት በማድረግ

---

[1] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,1270-1527* (London: Calendar Press, 1972), p. 126

[2] *Ibid.*, p. 129

ተጋድለዋል፡፡ ነገር ግን ይካሄድ የነበረው ትግል በእጅጉ ሃይማኖታዊ ይዘት እንዳልነበረው ስፔንሰር ትሪሚንግሀም ባደረጉት ጥናት ግልጽ አድርገዋል፡፡ ተከታይ ወታደር ለማግኘት የሃይማኖት ቅስቀሳ አስተዋጽኦ ያለው ቢሆንም፣ ዋናው ምክንያት ፖለቲካዊ የበላይነት ለማግኘት የተደረገ ጦርነት እንደነበር ትርሚንግሀም ያስምሩበታል፡፡ [3]

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦችና የሃይማኖቶች አገር በመሆኗ በታሪካችን በተደረጉ ጦርነቶች የነበረው ወታደራዊ አሰላለፍ አንዳንድ ጊዜ አስገራሚ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች የአህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (በተለምዶ አህመድ ግራኝ) ጦርነት በእስልምናና በክርስትና መካከል የተደረገ የሃይማኖት ጦርነት ብቻ ያደርጉታል፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የጦርነቱ ዋና ምክንያት የሆኑት የግዛት መስፋፋት፣ በለሙና በበለፀገው ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ላይ ቤተ መንግሥት መስርቶ አገር የመግዛትና፣ ንግዱን የመቆጣጠር ፍላጐት መሆኑን ግንዛቤና ግምት ውስጥ አያስገቡትም፡፡ በተለይም ደግሞ በአህመድ ግራኝ ጐን ብዙ ክርስቲያኖች፣ እንዲያውም ቁልፍ የፖለቲካ አመራር ጨብጠው የነበሩት ታዋቂ አካባቢያዊ መሪዎች፣ እንዲሁም በንጉሡ በልብነ ድንግል ጐን ሙስሊሞች እንደነበሩ የማያውቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ ከክርስቲያኑ ንጉሥ ከልብነ ድንግል ጋር አለመግባባት ፈጥረው የነበሩት የጐጃም ገዥና የትግሬ መኰንኑ (የትግሬ ገዥ) ከታሰሩበት ቦታ አምልጠው ከአህመድ ግራኝ ጦር በመቀላቀል የክርስቲያኑን መንግሥት ወግተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተን ከጦርነቱ ዋና ምክንያቶች ባሻገር የሃይማኖት ልዩነት ምክንያት በጦርነት ላይ አብሮ ተሰልፎ ጠላትን ለመውጋት እንቅፋት እንዳልነበር ነው፡፡

በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ነግሶ የነበረው አፄ ሱስንዮስ የካቶሊክ ሃይማኖትን ተቀብሎ ሀገራዊ የሆነችውን የኦርቶዶክስ እምነት በማውገዙና በመከልከሉ ምክንያት ሀገሪቱ ከአስር ዓመታት በላይ በዘለቀ የሃይማኖት ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃ ነበር፡፡ ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት መዘጋት፣ ለካህናትና ለአማኙ ህዝብ እልቂትን የፈጠረ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. በኃምሌ 1632 ዓ.ም. ሱስንዮስ በሀገሪቱ ላይ የተከሰተውን እልቂት በመገንዘብ ስልጣኑን ለቆ ልጁን አፄ ፋሲለደስን አነገሠ፡፡ አዲሱ ንጉሥ ፋሲለደስ በሀገሪቱ የደረሰውን መከራ በማጤን ነጮች ወደሀገሪቱ እንዳይገቡ አደረገ፡፡ በምትኩ ወዳጅነቱን ከጐረቤት ሙስሊም አገሮች ጋር በተለይም ከየመን ጋር አደረገ፡፡ ወደ የመን መልእክተኞች ላከ፣ በምትኩም የየመንን መልእክተኞች በመቀበል ወዳጅነቱን አጠናከረ፡፡ በስልጣን ወራሾቹ ዘመን ተጠናክሮ አይቀጥል እንጅ ፋሲለደስ የጀመረው በአርአያነት ሊቀጠልበት የሚገባ ርምጃ ነበር፡፡

[3] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, (London, Frank Cass, 1952), p. 146

አንዳንድ ጥናት ያደረጉ ግለሰቦች በደንብ ያላተኰሩበት እውነት አለ። እነዚህ ግለሰቦች ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የመሬት ባለቤትነት መብት አልነበራቸውም ይላሉ። ጉዳዩ እውነት የነበረበት አካባቢ ቢኖርም፣ ሙስሊሞች መሬት የያዙባቸው አካባቢዎችም ነበሩ። በወሎ የሚኖሩ ሙስሊሞች የመሬት ባለቤትነት መብት አልተነፈጉም።[4] በተለያዩ ጊዜያት የተለያየ አይነት ግብር ይጣልባቸው ወይም የሚገብሩት ገንዘብ መጠን ያድግ ነበር እንጅ ፍፁም የሆነ የመሬት እጦት አላጋጠማቸውም። በእርግጥ እ.ኤ.አ. በ1878 ዓ.ም. አፄ ዩሐንስ ፬ኛ ሙስሊሞችን ወደ ክርስትና ለመመለስ ባደረጉት ታሪካዊ ሂደት ምክንያት አምፀው ሀገራቸውን የለቀቁ ሙስሊሞች ነበሩ። እኔ ባደረግሁት የላስታና የዋግ ታሪክ ጥናት በሰቆጣ ወረዳ አካባቢ የባለቤትነት መብትና የመሬት ባላባትነት የነበራቸው ሙስሊሞች እንደነበሩ አውቃለሁ። አንዳንዶቹም መረጃ የሰጡኝ ናቸው።

መኰንን ብርሃኔ ስለ እንጦጦ ማርያም ባደረገው የመጀመሪያ ድግሪ ሚሚያ ጥናት እንደተመለከተው ሰባት ሙስሊሞች የቤተክርስቲያን መሬት ተሰጥተው ለእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ግብር የሚከፍሉ ነበሩ። መሬታቸው የሚገኘው ሜታሮቢ፣ ዓለም ገና፣ ፉሪና በሌሎችም ቦታዎች ነበር። ስዎቹም በገዳሙ የመሬት መዝገብ ውስጥ ተፅፈዋል። በዚህ ጉዳይ ሰፊና ዝርዝር ጥናት መደረግ የሚኖርበት ሲሆን ተጨማሪ ትምህርት ወደፊት ልናገኝነበት እንችላለን።

የሃይማኖት መቻቻል ጐልቶ ያልታየባቸው ወይንም ፈጽሞ ያልነበረባቸው ታሪካዊ ወቅቶች የነበሩበትን ዘመን ያህል የሃይማኖት መቻቻል እንዲኖር ያስገነዘቡ መሪዎችም ነበሩ። እ.ኤ.አ. በ1878 ዓ.ም. ቦሩ ሜዳ ላይ አፄ ዮሐንስ በግድ ሙስሊሙንና ሌላ ሃይማኖት ያላቸውን ሰዎች ወደ ክርስትና ለመመለስ ያወጁት አዋጅና ያስከተለው መዘዝ እንዳለ ሆኖ ሁኔታው ችግር እንደሚያስተከትል ያስገነዘቡ ሌሎች የመንግሥትም ሆነ የቤተክርስቲያን መሪዎች መኖራቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። የሸዋው ንጉሥ የነበሩት ሚኒልክ ወደ አፄ ዩሐንስ ቀርበው "ጃንሆይ እግዚአብሔር ይወድልናልን በግድ ቁረብ እያልን ሕዝባችንን ብንፈጀው" ብለው ማሳሰባቸውን አለቃ አፅሜ በመድኃፋቸው ዘግበዋል።[5] በእርግጥም ምኒልክ በበኩላቸው ትዕዛዙን ተቀብለው መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ መጣራቸው አልቀረም፣ ሠራዊታቸውም አመፁን ለመደምሰስ ተሳትፏል። አፄ ዮሐንስ የወሎ ሃዋሪያ አድርገው የሾማቸውና የቦሩ ሜዳ ስላሴን የመሰረቱት ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ መምህር አካለ ወልድ ሃይማኖት ከማስለወጥ በፊት ማስተማር ተቀዳሚ ተግባር እንደሆነ አስገንዝበው ነበር።

---

[4] Kalkelachew Ali, "Religion, Rituals and Mutual Tolerance in Wollo," (M.A. Thesis, Department of Sociology and Social Anthropology, Addis Ababa University, June 1997), p. 37

[5] አፅሜ፣ገጽ 688

በእደማርያምና የበእደማርያም የልጅ ልጅ ልብነ-ድንግል የሃድያ ሴቶችን ማግባታቸው ተመዝግቧል።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገሡት አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ያገቧት የአፋር ሴት ነበረች። ወደ ሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት በአፋር በረሃ በሽፍትነት በነበሩበት ጊዜ ያገቧት ናት። አዎ ከማግባቷ በፊት ክርስትና ተነስታለች። ነገር ግን ዓላማው ከአፋር ሕዝብ ጋር የጋብቻ ዝምድና ለመፍጠር ነበር። እነዚህን ፖለቲካዊ ጋብቻዎች ልንላቸው እንችላለን። ለእንዲህ ዓይነቱ ጋብቻ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነው ከድርጊቱም ትምህርት ሊሰጥ የሚችለው የወሎ ታሪክ ነው። ከልክላቸው አሊ ለሁለተኛ ድግሪው ሚሚያ እ.ኤ.አ. በ1997 ዓ.ም. በፃፈው የምርምር ውጤቱ በዛ ያሉ ገጠመኞችን አቅርቦልናል። ርዕሱ *"Religious Rituals and Mutual Tolerance in Wollo: The Case of Kabe, South West Wollo,"* የሚል ነው።

በቅርብ ጊዜ በሞት የተለየው አቶ ብርሃኑ ገበየሁ የዶክትሬት ትምህርት የጥናት ሥራው ወሎ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት መቻቻል የሚመለከት ነበር። አቶ ብርሃኑ ምርምሩን አጠናቆ ውጤቱን ለማቅረብ ተዘጋጅቶ ነበር። ግን ሞት ቀደመው - ላዕሌሁ ሰላም። የጥናቱ ርዕስ *"The Trajectories of Tolerance: A Comparative Study of Religious Discourse & Social Consensus in Wollo, Ethiopia"* የሚል ነበር። አማካሪው ፕሮፌሰር ጆን አቢንክ ይህንን ጥናት አስተካክለው ለማሳተም ጥረት እንደሚያደርጉ አጫውተውኝ ስለነበር ወደፊት ጠቃሚ መረጃችን ሊሆን ይችላል።

ወሎ ውስጥ በሁለቱ አማኞች መካከል የሚደረገው የመፈቃቀድ ጋብቻ ሁለቱም ሃይማኖቶች በመቻቻል መኖራቸውን የሚልጽ ነው። አቶ ከልክላቸው ግልጽ እንደሚያደርገው በጋብቻ ወቅት ወንዱን ወይም ሴቷን ወደ ሌላው ሃይማኖት የመመለስን፣ በጋብቻ ተሳስሮ፣ ልጅ ወልዶና አሳድጐ የመኖርን ወይም እያንዳንዳቸው የራሳቸውን ሃይማኖት ጠብቀው በጋብቻ አንድ ላይ የመኖርን ሁኔታ ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም *Suffering Under God's Environment, A Vertical Study of the Predicament of Peasants in North Central Ethiopia,(1991*, p. 18) በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሃፍ እንደሚጠቁሙንም ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ወሎ ውስጥ "ጐን ለጐን ፍፁም በሆነ መግባባትና ሰላም ይኖራሉ። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንኳ ግማሾቹ ክርስቲያን ግማሾቹ ሙስሊም ናቸው" በማለት ያሰምሩበታል።

አቶ ከልክላቸው በጥናቱ ባቀረበልን አንድ ትልቅ ምሳሌ ነገሩን እንዲህ አቅርቦታል። ሁለት እጅግ የሚዋደዱ፣ አብረው ያደጉና የሚተማመኑ ሙስሊም ወጣቶች ነበሩ።

አንደኛው አንዲት ጥሩ ቆንጆ ልጅ ይወዳል - ክርስቲያን የሆነች። የልጅቱ አባት ክርስቲያን ካልሆንክ ልጄን አልድርልህም ይሉታል። ማግባት የፈለገው ሃይማኖቱን ከቀየረ በጫጉላ ቤት ውስጥ ከሙስሊም ጓደኛው ጋር አብሮ መመገብ አይችልም። በጫጉላ ቤት ውስጥ ክርስቲያን ወይም ሙሲሊም ያረደው ሳይባል ሚዜዎች አንድ ላይ በመብላትና በመደሰት እንደሚቆዩ ያወቁት የልጅቷ አባት ሚዜዎችህ ክርስቲያን ካልሆኑ ይሉታል። በዚህ ጊዜ ነበር ሁለቱ ጓደኞሞች ላለመለያየት ሲሉ ክርስትና የተነሱት። ሰርጉ ተደገሰ፣ የጫጉላው ጊዜም አለፈ። ነገር ግን ሙሽሮቹ ከሁለት ዓመታት በኂላ ተፋቱ። የሙሽራው ቤተሰቦች ልጃቸው ክርስቲያን ሆኖ ሲያገባ ቅር አልተሰኙም ነበር። ይሁን እንጅ ልጃቸው ከተፋታ በኂላ በአንድ ማዕድ ተቀምጠው ተካፍለው ለመብላት አልቻሉም። ሙሽራውም እንደገና ወደጥንት ሃይማኖቱ ወደ እስልምና እንዳይመለስ፣ ለሱ ጋብቻ ሲል ክርስትና የገባውን ጓደኛውን እያሰበ አዲሱን ሃይማኖቱን መለወጥ አልቻለም።[6]

ሌላው ከልከላቸው ያቀረበልን ምሳሌ አንዲት ሴትዮ በጋብቻ ምክንያት ከክርስትና ወደ ሙስሊምነት፣ ከዚያም ከባላቸው ሲፋቱ ወደ ክርስትና፣ በሌላ ጊዜ ሲያገቡም ወደ እስልምና ሃይማኖታቸውን በተደጋጋሚ ለውጠዋል። ልጆቻቸው ግማሾቹ ክርስቲያን፣ ግማሾቹ ሙስሊም ሲሆኑ ያለምንም ችግር በቤተሰባዊ ፍቅር ተጠምደው ኑሮአቸውን በመምራት ላይ ይገኛሉ።

ከሌላ አካባቢ በሥራ ጉዳይ መጥተው ካቢ የሚኖሩ ሁለት ሴት መምህራን - ሙስሊምና ክርስቲያን - በፍቅር በአንድ ቤት ውስጥ አብረው ይኖራሉ። መቻቻልና አብሮ መኖር የዘወትር ልማዳቸው ነው። ይሁን እንጅ ሁለቱም ለየብቻ የሚመገቡትን የስጋ ቋንጣ በአንድ ገመድ ላይ ይሰቅላሉ። በዚች ነገር ላይ ብቻ ይለያያሉ። ቋንጣቸው በየት በኩል እንደተሰቀለ ለመለየት ሲሉ በገመዱ መካከል ላይ ጨርቅ አስረውበታል።[7]

በሁለቱ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል የሚፈፀመው ጋብቻ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈፀም ይችላል። ጤና አጣሁ ብሎ፣ ወይም በዛር ወይም ወዳጃ፣ ወይም የባሕላዊ መድሐኒት ፍለጋ፣ ሃይማኖቱን ቀይሮ ኑሮውን እንዲፈትን ተመክሮ ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ይሆናል። በጓደኝነት ምክንያት ሃይማኖትህን ቀይረህ ከሴት ወይም ከወንድ የፍቅር ወዳጅህ ጋር መኖር ወይም ተጋብቶ መቀመጥ ይቻላል። የአካባቢ የሥልጣን እርከን ላይ ለመቀመጥ ሲባል ወደ መንግሥቱ ሃይማኖት መግባት ይቻላል። ለዚህ ዓይነቱ ነገር ማስረጃ የሚሆነን በ19ነኛው ክፍለ ዘመን የወሎ ባላባት የነበሩት እና ከቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ በኂላ ክርስትና የተነሱት

[6] Kalklachew, pp. 116-117

[7] *Ibid.*, pp. 200-2

አመዴ ሊበን (አባ ዋጠው) በአፄ ምኒሊክ ክርስትና አባትነት ክርስትና ተነስተው ደጃዝማች ኃይለ ማርያም የተባሉት እና፣ መሐመድ አሊ በአፄ ዮሐንስ ክርስትና አባትነት ራስ ሚካኤል (በኋላ ንጉሥ) የተባሉት ናቸው።

ለሥልጣን ብለው ክርስትና ተነስተው በሥልጣን እርከን ላይ የተቀመጡ ሌሎች ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። አንዳንዶቹ ክርስቲያን ሆነው ከክርስቲያን መንግሥቱ ጋር ተመሳስለው ከኖሩ በኋላ በሞት አፋፍ ላይ ሲደርሱ "በልባችን ሙስሊም ነበርን በሙስሊም መቃብር በእስልምና ሕግ መሠረት ቅበሩን" ብለው የተናገሩ፣ የተናዘዙና በቃላቸውና በኑዛዜያቸው መሠረት ቀብራቸው የተፈፀመላቸው አሉ። አንዲት ምሳሌ ላክል። ደጃች መንገሻ አቦዬ የተባሉ ታዋቂ የቃሎ አርበኛ እና ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር በጥሩ የሥራ ግንኙነት የአካባቢው ገዢ ሆነው የኖሩ ነበሩ። ክርስቲያን ሆነው የኖሩ። ፍፃሜ እድሜያቸው በደረሰ ጊዜ "በልቤ ሙስሊም ነበርኩ" በማለት ልጆቻቸውን በታዋቂው የጀማ ንጉስ የሃይማኖት ቦታ እንድትቀብሩኝ ብለው ለቤተሰባቸው አደራ ሰጡ። በቀብራቸው ቀን አልጋ ወራሹ በመጡ ጊዜ ለቤተሰባቸው ጭንቅ ሆነ። መቼም መላ አይጠፋምና የእንጨት እርብራብ ተሰርቶ አልጋ ወራሹ በተገኙበት ደሴ መድኃኒዓለም ተቀበሩ። ሬሳቸው ግን በሚስጢር በሌሊት ጀማ ንጉሥ እንዲቀበር ተደረገ። መቼም ወሬው አፈትልኮ መውጣቱ አልቀረም።

ከቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ በኋላ ተቻችሎ ለመኖር ሲባል የወሎ ሙስሊም ሕዝብ ብዙ ነገሮችን ቀይሶ ቀኑን አሳልፏል። ችግር መላን ይፈጥራል እና ቀን ክርስቲያን ሌሊት ሙስሊም እየሆኑ፣ ሲሞቱ በሙስሊም መቃብር እየተቀበሩ ቀኑን ገፍተውታል። ከችግሩ ከጦርነቱና ከእንግልቱ ባሻገር ለጥሩ ነገር ምሳሌና ትምህርት የሚሆኑን ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። በነዚህ ምሳሌዎች ላይ የሚቻቻልና የሚተሳሰብ ማሕበረሰብ ለመፍጠር ይቻላል።

የወሎ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድ ቅሬ ወይም እድር የታቀፉ ናቸው። አሁን በቅርብ ይህ አይነቱ ትስስር እየላላ መጥቷል እንጂ። የሞተ ዘመዳቸውን ለማሰብ በሚያዘጋጁት ተዝካር ወይም ሰደቃ በአንድ ላይ ይሳተፋሉ። በሥራ ለመረዳዳት ሲሉ በአንድ ላይ በደቦ፣ ወንፈል ወይም በመቃኞ ሥራ በጋራ ይረዳዳሉ። ሙስሊም ሕፃናት ቄስ ት/ቤት ሄደው ፊደል ይቆጥራሉ። ሚዜዎች ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በጫጉላ ቤት ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ ልማዳዊ ከሆነውና የሙስሊምም ሆነ የክርስቲያን ሥጋን ከሚከለክለው ሕግ ነፃ ይሆናሉ።

ክርስቲያኖች ታዋቂ ወደ ሆኑ የሙስሊም የሃይማኖት ቦታዎች ለዝየራ (ሰላምታ ለማቅረብ) ይጓዛሉ። የሚመኙትን ለማግኘት፣ ከጤና እክል ለመፈወስ፣ የጠፋ ዕቃን ለማግኘት ወደ ሙስሊም አዋቂዎች ይጉርፋሉ። በሚካሄደው የዝየራና የወዳጃ ሥነ ሥርዓት ያለ ምንም ልዩነት የሁሉም ሃይማኖት ተከታዩች ይሳተፋሉ። ጀባታ

(ሥጦታ) ለመስጠት ይመጣሉ፣ ይመረቃሉ። ነፍሰ ጡር በሰላም እንድትወልድ ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም አማኞች በጋራ በሚዘጋጀው የፋጢማ ቅሬ ላይ ይሳተፋሉ። ዝናብ ሊያመጡ ይችላሉ ተብሎ ለሚታመነባቸው አባገር ሁሉ አማኞች ገንዘብ ይከፍላሉ።

ካቤ አጠገብ በሚገኘው የፍርዴ የሙስሊም የእምነት ቦታ፣ በሼህ አሊ ዩሱፍ ብርቄ በተቋቋመ ቦታ፣ በሚካሄደው ፀሎት ክርስቲያኖችም ይገኛሉ። በፍርዴ በሚካሄደው የመውሊድ በዓል ላይ የአካባቢው ቤተክርስቲያን የመካነ ሥላሴ ደብር አለቃ፣ የርዕሰ ደብሩ ባለቤት ለፀሎት ለሚመጡት ክርስቲያኖች እንጀራ ጋግረው ወጥ ሰርተው ይጋብዛሉ። ኮምቦልቻ አጠገብ በሚገኘው የገታ የሙስሊም የእምነት ማዕከል ከሚመጡት አንድ ሦስተኛው የሚሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው።

ካቤ ከተማ የሚገኘው የሚካኤል ቤተክርስቲያን የተተከለው ቀደም ብሎ የሙስሊም የዕምነትና የፀሎት ቦታ ላይ ነበር። በዚህ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ በአንዱ ቦታ ላይ የሙስሊሞች በየጊዜው ዱብርቲ ወዳጃ ይካሄድበታል። ሙስሊሞችም፣ ክርስቲያኖችም፣ ቄሶችን ጨምሮ ለዱብርቲው ወዳጃ ጀባታ (ስጦታ) ያቀርባሉ። ሃይማኖት ሳይለያቸው በመቻቻልና በመከባበር የሃይማኖት ሥርዓታቸውን ያካሂዳሉ።

የታመሙ ሰዎች መድሃኒት ፍለጋ ወደ ፀበል ይመጣሉ። ፀበል በክርስትና እምነት ውስጥ የሚገኝ ልማድ ሲሆን ፀበል ባለበት ቦታ ሙስሊሞችም ጤንነትን ለማግኘት ሲሉ ለመጠመቅ ይመጣሉ። የሚከለክላቸው የለም። ደሴ አጠገብ ባለ የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሁለት ፀበሎች አሉ። አንዱ የክርስቲያን ሌላው የሙስሊም ፍል ውሃ። ሁሉም በነዚህ ይጠመቃሉ። እንደተነገራቸውና እንደየ ክፍላቸው ሁኔታ ወደ ተለያዩ ጠበሎች ይመጣሉ። ሙስሊም ሰፈር አጠገብ በሚገኘው የሰቆጣ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሙስሊሞች ፀበል ይጠመቃሉ፣ መስቀል ይታሻሉ። ማንም አይከለክላቸውም። በየአመቱ በሚካሄደው የጥምቀት በዓል ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር በበዓሉ በመሳተፍ ይዘፍናሉ። የአካባቢያቸው በዓል ስለሆነ በዚያውም የአንዱ ቤተሰብ ከሌላው አማኝ ጋር የታሰሰረ እና የተዛመደ በመሆኑ በአንድነት ሲያከብሩት ይስተዋላል።

በዚያ በክፉው የደርግ ዘመን ሙስሊሞች እና ክርስቲያኖች ተባብረው የሰሩበት ጊዜ ነበር። በሚያዚያ ወር 1966 ዓ.ም. ተካሂዶ በነበረውና ከ150,000 በላይ ሰው በተሳተፈበት ትልቁ ሰላማዊ ሰልፍ የተሳተፉት ክርስትያኖች ቁጥር እጅግ አያሌ ነበር። ሰልፉ የሃይማኖት ነፃነትና እኩልነትን ለመጠየቅ የተዘጋጀ ነበር።

በ1967 ዓ.ም. ወሎ ሩጋ በተባለ ቀበሌ ውስጥ የአርቤሮ ሚካኤል ቤተክርስቲያን መሬት በመወረሱ ምክንያት ቄሶች መተዳደሪያ አጥተው መቀደሱ ተቋረጠ። የክልሉ

ሊቀ ጳጳስ ሁኔታውን ተገንዝበው ታቦቱን ወደ ደሴ ለመውሰድ ባሰቡ ጊዜ የአካባቢው ነዋሪ ሙስሊሞች (95% የሩጋ ነዋሪ ሙስሊም ነው) ተወያይተው ታቦቱ የኛም ቅርስ ስለሆነ ታቦቱ አይነሳብንም፣ ለመተዳደሪያ የአንድ አባወራ መሬት እንሰጣለን እንዲሁም በገንዘብ እንደግፋለን በማለት በአለበት እንዲቀር አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ካቤ ከተማ መስጂድ አልነበረም፡፡ መስጂድ ለመስራት በታሰበበት ወቅት የመስጂድ አሰሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ሆነው ያስተባበሩት የካቤ ሚካኤል አለቃ ነበሩ፡፡ በየከተማው ለሚሰሩት መስጂድም ሆነ ቤተክርስቲያን ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያኑ መዋጮ መክፈሉን የተለመደ ተግባር አድርጐታል፡፡

በግንቦት 1977 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ራጉኤል ቤተክርስቲያን እንዲነሳ እና ወደ እንጦጦ ኤልያስ/ራጉኤል ቤተክርስቲያን እንዲደረብ በተወሰነ ጊዜ የተፈፀመውን የሕዝብ ትግል እናስታውሳለን፡፡ የመርካቶ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ቢነሳ ለመርካቶ አንዋር መስጂድ ጥሩ አይሆንም፣ ማን ያውቃል ቀጥሎ ማን እንደሚነሳ በማለት ከክርስቲያኑ ጎን እኩል ተሰልፎ እንዲከሽፍ ያደረጉትና ችግር ቢፈጠር ጉልበታቸውን ለማሳየት የመጡት ብዙዎቹ የመርካቶ ሙስሊሞች ነበሩ፡፡[8]

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በየትምህርት ቤቱ የግብረ ገብነት ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ ደሴ ወ/ሮ ሥሂን ትምህርት ቤት ግን ከግብረገብነት ትምህርት ጐን ለጐን የሙስሊም የሃይማኖት ትምህርት ለሙስሊም ተማሪዎች ይሰጥ ነበር፡፡ መሪጌታ ሀሩይ የተባሉ ካህን ግብረገብነት ሲያስተምሩ፣ ሐጂ መሐመድ ሳኒ ዑመር (በኂላ የታላቁ አንዋር መስጂድ ኢማም የሆኑ) ቁራን ያስተምሩ እንደነበር ብዙዎቻችን ሳናውቅ እንችላለን፡፡ ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀልበት ጊዜ እግዚአብሔርንም አላህንም የማያነሳ የጋራ ፀሎት ይደረግ እንደነበር መረጃዎች አሉ፡፡[9]

ክርስቲያኑና ሙስሊሙ የሚኖረው ኩታ ገጠም በሆኑ መንደሮች ነው፡፡ በሰላምም እንደሚኖሩ የ19ኛው ክ/ዘመን አውሮጳውያን ተጓዦች ይህንን ዓይነቱን የጋራ ኑሮ አረጋግጠውልናል፡፡ እ.ኤ.አ. በጥቅምት 1938 ዓ.ም. በንጉሥ ሳሕለ ሥላሴ ዘመን ሸዋን የጐበኘው የፈረንሳዩ ተጓዥ ሮሼ ዴሪኩር ጨኖ በተባለች መንደር 500 የሚሆኑ ነዋሪዎች - ሙስሊሞች እና ክርስቲያኖች - በጋራና በስምምነት ይኖሩ እንደነበር ገልጿል፡፡ ቻርልስ ጆንስተር የተባለ ተጓዥ በዚያው ዘመን ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ሃይማኖታዊ መቻቻል ስላሰፈኑ የክርስቲያኖች እና የሙስሊሞች ግንኙነት እጅግ ጥሩ እንደነበር አረጋግጠናል፡፡

---

[8] Wudu Tafete, "The Twin Churches of Raguel," (BA essay submitted to the Department of History of AAU, 1989), pp. 74-75
[9] Kelklachew, p. 84

ሙስሊሞች የመንግሥት መልዕክተኞ በመሆን አገራቸውን አገልግለዋል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በአፄ ይግባ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ወደ ግብፅ ተልኮ የሄደው ኢትዮጵያዊው ሙስሊም ዮሱፍ አብዱራህማን እንደነበር እንስቻለሁ፡፡ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን መሐመድ ሰዒድ የተባለ የአረብኛ አስተርጓሚ ነበራቸው፡፡ በየዘመኑ ወደ ሥልጣን የመጡት ንጉሦች ለዚሁ ሥራ ሙስሊሞችን ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን ማንነታቸውን ለማወቅ ሰፊ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የንግዱን ሥራ ያካሄዱ የነበሩትና ቀረጥ የሚቀርጡት ነጋድራሶች ብዙዎቹ ሙሲሊሞች ነበሩ፡፡ በተለይም በጐንደር ዘመነ መንግሥት ፡፡ አሁን ማንነታቸውን ለመግለጽ ባልችልም፡፡ በአፄ ምኒሊክ ግቢ የነበሩት ብዙዎቹ አናፂዎች ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ የአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት፣ የእንጦጦ ራጉኤልንና የአዲስ አለም ማርያምን አብያተ ክርስቲያናትን በኃላፊነት የሰሩት ዋናው ግንበኛ የሕንድ ሙስሊም ነበሩ፡፡ ሐጂ ቀዋስ የተባሉ፡፡ የልጅ ልጆቻቸው ሰራተኛ ሰፈር ይኖራሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሙስሊሞቹ ባላቸው የስራ ችሎታ ከቤተመንግሥቱ ጋር ቀረቤታ ፈጥረው ሃይማኖት ሳይለያያቸው ሰርተው መኖራቸውን ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለሃገራቸው ነፃነት፣ ለዳር ድንበራቸው መከበር ወደ ጦር ሜዳ ዘምተው ተዋግተው ወድቀዋል፡፡ ቀድም ባለው ዘመን በትልቁ የአድዋ ጦርነትም ይሁን ከ1928-33 ዓ.ም. አገርን ከፋሽሽት ኢጣሊያ ጦር ለመከላከል በተደረገው የጦርነት ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በጦርነት ተካፍለዋል፡፡ አንዳንዶቹ የጦር መሪ ነበሩ፡፡ ቀኝ አዝማች ዑመር ሰመተር በትውልዳቸው ሱማሌ የሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ በጀግንነት የተዋጉ ናቸው፡፡ አውሳና ይፋት ውስጥ በአርበኝነት የተዋጉት ያየሁ አመደ፣ ጊሌ ውስጥ የተንቀሳቀሱት ቀኝ አዝማች ሐሰን ዑመር፣ ወሎ ገምዛና ኮምቦልቻ አካባቢ የነበሩት ቀኛአዝማች ሀሰን መሐመድ ያሲን፣ ገዋኔ አካባቢ የተዋጉት መሐመድ ዑመር አሊሻ፣ በ1928 ዓ.ም. በክረምት ወራት አዲስ አበባ ላይ ጥቃት ከከፈቱት ከደጃች ፍቅረማርያም ጋር እና በሌላም ቦታ የተሰለፉት አህመድ ኩሉ ባስ፣እንዲሁም ሌሎችን በምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ በኂላ የሙስሊም ንቅናቄውን የመሩት ሸህ ጠለሀ ከአድዋ ጦርነት በፊት ከጣልያኖች ጋር እየተላላኩ አፄ ምኒልክን አስቸግረው የነበሩ ቢሆንም በመጨረሻዋ ሰዓት በአድዋ ጦርነት ተካፍለዋል፡፡ በኂላም ከአፄ ምኒልክ ጋር እርቃቸውን አፅንተው በሐረር አካባቢ ተሹመው ገዢ ሆነው ሰርተዋል፡፡

የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ የተሻለ ጊዜ ነበር፡፡ ይህንን ስንል መንግሥታቸው ኦርቶዶክስ ሃይማኖትንና አማርኛ ቋንቋን በመያዝ ብሄራዊ አንድነትን ለመገንባት ያደረገውን ሙከራ እናስታውሳለን፡፡ በዘመናቸው ተፈጥሮ የነበረውን የብሄርና የሃይማኖት እንቅስቃሴ፣ በአባይ ወንዝ ላይ የነበረውን የግብፅ

አመለካከት፣ የአካባቢው እስላማዊና አረባዊ መንግሥታት ኢትዮጵያ ውስጥ ለተቋቋሙት የብሔርና የሃይማኖት ፖለቲካዊ ድርጅቶችን በማነሳሳታቸው፣ እርዳታ በመለገሳቸው፣ ወታደራዊ ስልጠና በመስጠታቸው፣ ጦር መሣሪያ በማስታጠቃቸው እና በሌሎችም ጉዳዩች ምክንያት የሃይማኖትና የብሔር ጭቆና መፈፀሙን ማንም አይዘነጋውም፡፡ የግብፅ መሪ ገማል አብደል ናስር ያራምድ የነበረው ፖለቲካዊ ሁኔታ በአገር ውስጥ ብጥብጥ የሚያበረታታ በመሆኑ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ልዩ ልዩ ጨቋኝ እቅዶች በመዘርጋታቸው ሁኔታው የሌሎችን አማኞች ኑሮ እንዳስከፋው እናስታውሳለን፡፡ ይሁን እንጂ አፄ ኃይለ ሥላሴ የሰሩት ጥሩ ሥራም አለ፡፡

"አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው" በሚል መሪ ቃል አንዳንድ እርምጃዎች ተነድፈው ነበር፡፡ መሪ ቃሉ በትክክል በሥራ ላይ ባይውልም፡፡ ሼሪአ እና ናኢባ ፍርድ ቤት ተቋቁመው የሙስሊሞችን የሕግ ጉዳይ ይከታተሉ ነበር፡፡ ንጉሡ በሚያደርጉት ጉብኝት መስጂዶችን ጭምር ይጎበኛሉ፣ ለሚሰሩ መሲጅዶች የገንዘብ እርዳታ ያደርጋሉ፡፡ ቅዱስ ቁርአን ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ እንዲተረጎም እና እንዲታተም አድርገዋል፡፡ ሼህ ሳኒ ሐቢብ በዚህ ሥራ ላይ በንቃት ተሳትፈዋል፡፡

በሙስሊም ዓመታዊ በዓላት የሙስሊም ተወካዮች ወደ ቤተመንግሥት ሄደው እጅ ይነሱ ነበር፡፡ ለበዓሉ ክብርም መድፍ ይተኮስ ነበር፡፡ ነገር ግን የሙስሊም በዓላት ብሔራዊ በዓላት ሁነው አልተከበሩም፡፡ ብዙ እንኳን ባይሆኑ በትላልቅ የሥራ ኃላፊነቶች ላይ ሙስሊሞች ተሹመው ነበር፡፡ በ1966 ዓ.ም. የመጀመሪያው የሙሲልም ሚኒስቴር ተሹመዋል፡፡ ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም በጦሩ ውስጥ ተቀጥረው ነበር፡፡ ትልቅ እርምጃ የተካሄደው ከጊዜ ወደ ጊዜ ሙስሊሞች በዘመናዊ ትምህርት በብዛት መሳተፋቸው ነበር፡፡ ያለምንም ልዩነት በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ዩኒቨርስቲን ጨምሮ ተሳትፈዋል፡፡ ለሀገራቸውና ለወገናቸው በማሰብ በተማሪዎች ትግል ውስጥ በንቃት ተሳትፈዋል፡፡ አንዱ ጉልህ ምሳሌ አቶ አብዱልመጅድ ሁሴን ነበሩ፡፡

በደርግ ዘመነ መንግሥት ሀይማኖትና መንግሥት ተለያዩ፡፡ የሃይማኖት እኩልነት ታወጀ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሦስት የሙስሊም በዓላት ብሄራዊ በዓላት እንዲሆኑ በመወሰኑ እስከ አሁን ድረስ በድምቀት እየተከበሩ ነው፡፡ "በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሙስሊሞች" የሚለው አባባል "ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች" በሚል ተተክቷል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የራሳቸው የሆነ የሀይማኖት ጉዳይን የሚመለከት መሥሪያ ቤት ተቋቁሟል፡፡ ካለፈው የዘውዳዊ ሥርዓት በተሻለ ሁኔታ ሙስሊሞች መብታቸውን ተጎናፅፈዋል፡፡ ይሁንና በደርግ ያፈና ሥርዓትም ሙስሊሞች ተጎጂዎች ነበሩ፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላ አሁን ባለንበት የመንግሥት ሥርዓት የሙስሊሞች መብት፣ የሃይማኖት ነፃነት እና መቻቻል የተረጋገጠበት ወቅት ነው፡፡ ከ1980ዎቹ

ዓመታት ወዲህ የሙስሊሙን ሃሣብና እምነት የሚያንፀባርቁ እስላማዊ ጋዜጦች በብዛት ተቋቁመዋል፡፡ የሙስሊሙን ታሪክ፣ ፍላጐትና ማንነት የሚገልፁ ጽሑፎችን ያወጣሉ፡፡ ጥሩ የመማሪያ መድረኮች ሆነዋል፡፡ የመንግሥት ፖሊሲ በሃይማኖት ጉዳዩች መንግሥት ጣልቃ አይገባም ስለሚል ሁሉም ሃይማኖቶች የራሳቸውን ጉዳይ በሕግ ማዕቀፍ ሥር ለማካሄድ አመቺ በር ከፍቶላቸዋል፡፡ በሃይማኖት መቻቻል መርሕ ሥር ለመኖር ጥረቶች እየተደረጉ ነው ከአንዳንድ ጥሩ ያልሆኑ አጋጣሚዎች በቀር፡፡

ለወደፊቱ በሃይማሃኖት ተቻቻችለን እንድንኖር ሊጠቅሙን የሚችሉ ነገሮችን በመጠቆም ንግግሬን ላጠቃልል፡፡

- በሃገራችን ስላለው የሃይማኖት መቻቻል ዝርዝር ጥናት ጠለቅ ባለ ሁኔታ መካሄድ ይኖርበታል፡፡
- የሃይማኖት ውጥረትንና አለመግባባትን የሚፈጥሩ ጉዳዩችን በመመካከር ማስቀረት
- ባሉን ጥሩ ጐኖች ላይ በርትተን መስራት
- የሌላውን ሃይማኖት ከሚጎዳና ከሚያስቀይም ነገር መቆጠብ፣
- አስፈላጊ ያልሆኑ ክርክሮችን፣ አላስፈላጊ የሆኑና የሌላውን ሃይማኖት የሚጐዱ ጽሁፎችን አለማሰራጨት፣
- በሃይማኖት መቻቻል ላይ የሚያተኩር ትምህርት መስጠት፣
- በሁሉም ሃይማኖት የሚገኙ እና ችግር ለመፍጠር የሚሯሯጡ አክራሪዎችን መዋጋት፣
- የህዝቡን የሃይማኖት መቻቻል ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የሃይማኖት ውጥረት የሚፈጥሩ አስተሳሰቦችን እና ነገሮችን ማስወገድ፣
- የሁሉም ሃይማኖት መሪዎች፣ አባቶች እና የማህበረሰብ መሪዎች የሃይማኖት መቻቻልን ለማስፈን በርትተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# “የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት” አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ

*አበባው በቀለ*

## 1. መግቢያ

ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዘው ለሚመጡ በጐ የአኗኗር ዘይቤ ለውጦች ዋጋ የምንሰጠውን ያህል ተከትለው ለሚመጡ ማህበራዊ ቀውሶችና ችግሮች እውቅና ትኩረት መስጠት ይኖርብናል፡፡ ዋና ዋና ከተሞቻችንን እያጋጠሙ ካሉ ማህበራዊ ችግሮች ውሥጥ አንዱና ዋነኛው አዳራቸውንና ውሎአቸውን ጐዳና ላይ ያደረጉ ህፃናት ቁጥር ከከተሞቹ መስፋፋት ጋር እየጨመረ መምጣት ነው፡፡ ይሄ ጽሑፍ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስሉ ጠቅላል ባለ መልኩ ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡

ጽሑፉ ስድስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል “ጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት” ለሚለው ሐረግ በተለያዩ ወገኖች የተሰጡ ፍቺዎችንና የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ጽንሰ ሐሳቡን ዘርዘር አድርጐ የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥርና ሥርጭት በአለም ዙሪያና በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስሉ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን እያጣቀሰና እየመረመረ ለማቅረብ ይሞክራል፡፡

ሦስተኛው ክፍል የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ሕይወት ዙሪያ ዳሰሳ የሚያደርግ ሲሆን የጐዳና ሕፃናትን ሁኔታ በእድሜ፣ በፆታና በመሳሰሉ መለኪያዎች ምን እንደሚመስል ከመግለጽም ባለፈ ህፃናትን ለጐዳና ህይወት የዳረጉዋቸው ምክንያቶችን ይመለከታል፡፡ በመቀጠልም የጐዳና ሕይወት ገጽታዎች ማለትም እነዚሁ ህፃናት በጐዳና ሕይወታቸው ዙሪያ የደረሰባቸው፣ እየደረሰባቸው ያሉ በደሎች፣ ችግሮችና ሌሎች አስከፊ ሁኔታዎች ላይ መጠነኛ ዳሰሳ ያደርጋል፡፡

አራተኛው ክፍል የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት በጐዳና ላይ እያጋጠማቸው ያሉ ችግሮችን እንዴት እየተቋቋሙ እንዳሉ የሚመለከት ሲሆን አምስተኛው ክፍል መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጋር ለተያያዙ ችግሮች እየሰጡዋቸው ያሉ ምላሾችን ይመለከታል፡፡ የመጨረሻው ክፍል በቀጣይነት የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናትን ችግሮችን ለመቅረፍ መወሰድ ባለባቸው እርምጃዎች ዙሪያ አንዳንድ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማቅረብ ጽሑፉን ያጠቃልላል፡፡

## 2. "የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት" ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ የተሰጡ ፍቺዎች

ማህበራዊ ክስተቱን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ በተለያዩ ድርጅቶችና ምሁራን የተለያዩ ፍቺዎች ሲሰጥ የቆየ ሲሆን እነዚህኑ ፍቺዎች በሚከተሉት አንቀጾች እንመለከታለን።

የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት "የጐዳ"ና ተዳዳሪ ህፃናት" ለሚለው ሐረግ ጐዳና ከሚለው ቃል ጋር አቆራኝቶ ፍቺ ለመስጠት ይሞክራል። ጐዳና የሚለው ቃል በከተማ ውሥጥ የሚገኙ እነዚህ ህፃናት የሚኖሩበት ቦታዎችን እና መንገዶችን ያካትታል። እነዚህ ቦታዎች የቆሻሻ መጣያና የሽንት መሽኚያ ቦታዎችን፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን፣ የአውቶብስ ፌርማታዎችን፣ ለምንም ጥቅም ያልዋሉ ቦታዎችን በሙሉ እንደሚያካትቱና እነዚህን ቦታዎች ለመኖሪያ፣ ለመሥሪያና ለመዋያ የሚገለገሉባቸውን ሕፃናት ደግሞ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚል ሥያሜ ይሰጣቸዋል።

የአለም ጤና ድርጅት በበኩሉ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ለሚለው ሐረግ በቤተሰቦቻቸው የተረሱ ወይም ቤተሰብ የሌላቸውና ከቤተሰብ የተለዩ፣ ጐዳና ላይ በመጠለያ ውስጥ ወይም ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ ሕፃናትን በሙሉ እንደሚያካትት ይገልፃል።

የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት በበኩሉ "የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት" ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ አጠቃላይ የሕፃናቱን ሁኔታና አኗኗር ለአራት በመክፈል ፍቺ ይሰጣል። የመጀመሪያው ክፍል ከቤተሰቦቻቸው ጋር ምንም አይነት ግንኙት የሌላቸው፣ ውሎአቸውን እና አዳራቸውን በሙሉ ጐዳና ላይ ያደረጉትን ሕፃናት ሲያካትት ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ለመደጐም ቀን ቀን ጐዳና ላይ በሥራ ተጠምደው አመሻሽ ላይ ለአዳር ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ህፃናትን ያካትታል። ሶስተኛው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ዓይነት ደግሞ በከተማ ውሥጥ ድህነት ባቆራመዳቸውና መሰረታዊ ፍላጐታቸው ባልተሟላቸው ቤተሰብ ውሥጥ የሚኖሩ ህፃናት ያልተሟላቸውን ፍላጐት ለማሟላት ወደ ጐዳና ይወጣሉ በሚል እሳቤ እነዚህን ህፃናት የሚያካትት ነው።

አራተኛው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቡድን ደግሞ በወላጅ ሞት፣ ወይም ደግሞ በቤተሰባቸው አለመፈለግ ምክንያት ወደ ጐዳና የወጡ ሕፃናትን ያጠቃልላል።

አንድ ሌላ ጥናታዊ ጽሁፍ በበኩሉ፣ ማናቸውም ጐዳናን ማለትም ጥቅም ላይ ያልዋለ ቦታ፣ የአውቶብስ ፌርማታና የመሳሰሉ ቦታዎችን መኖሪያቸው ያደረጉ ህፃናት የጐዳና ሕፃናት ተብለው ይጠራሉ ሲል ፍቺ ይሰጣል፡፡ [1]

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ለሚለው ሐረግ በተለያዩ ወገኖች የተሰጡ ፍቺዎችን በጥልቀት በመመልከት ለዚህ ጽሑፍ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ለሚለው ሐረግ የሚከተለውን ፍቺ እንጠቀማለን፡፡

የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ስንል በአንድ በኩል አብዛኛውን ጊዜያቸውን ጐዳና ላይ በሥራ የሚያሳልፉና ሲመሽ ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ህፃናትን የሚያካትት ሲሆን በሌላ በኩል ውሎአቸውን እና አዳራቸውን ጐዳና ላይ ያደረጉ ሕፃናትን ማለታችን ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት" በሚለው ሐረግ ውስጥ ህጻናት የሚለው ቃል ቀጥተኛ የአማሪኛ ትርጉሙን ተከትሎ ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት በታች ያሉትን ሰዎች ብቻ የሚያካትት ሳይሆን ከሰባት ዓመት በላይ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ያሉ ልጆችን ጭምር የሚያካትት ትርጉም እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

በዚህ ለጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት በፍቺነት ለመጠቀም ባሰብነው ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ፣ በጎዳና ላይ የተለያዩ *ሥራዎችን* ማለትም መኪና በማጠብ፣ ጫማ በመጥረግ፣ ጥቃቅን ንግድ በመነገድ፣ በልመና በመሳሰሉ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ህጻናትን ሲያካትት በሌላ በኩል ውሎአቸው ብቻ ሳይሆን አዳራቸውን ጭምር ጎዳና ላይ ያደረጉትንም ያካትታል፡፡

# 3. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ብዛትና ሥርጭት

## 3.1 አለማቀፋዊ ስርጭት

ከጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጋር የተያያዙ ችግሮች አለማቀፍ ክስተቶች ናቸው፡፡ በየአለማችን የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የማይገኙባቸው ሀገራት ወይም ከተሞች የሉም፡፡ በአደጉም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ችግሩ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ላቲን አሜሪካ፣ እስያና አፍሪካ የችግሩ አሥከፊነት ጐልቶ የሚታይባቸው የአለማችን ክፍሎች ናቸው፡፡ በአለም ላይ የሚገኙትን የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ቁጥር በትክክል ለመገመት ቢያዳግትም ከመቶ እስከ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ሊደርሱ

[1] M.W. Lusk, F, Peralta, and G.W. vest, "Street Children of Juarez; A field study". International Social Work Vol.3 (1989), pp 289-302.

እንደሚችሉ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ2005 የተደረገው የጥናት ግምት ያስረዳል፡፡

አሃዙ አሁን ካለው የሕዝብ ቁጥር እድገትና የከተሞች መስፋፋት ሁኔታ ጋር ሲታይ ከዚህ ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል፡፡

ከላቲን አሜሪካና እስያ ካሉ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ከጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጋር የተያያዙ ችግሮች ለአፍሪካ አዲስ ክስተት ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ አፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና አዝጋሚ የከተሞች መስፋፋት ያሉባት በማደግ ላይ ያለች የአለማችን ክፍል ናት፡፡ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመር በከተሞች በዝቅተኛና በተጨናነቀ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ኑሮ ላይ ጫና መፍጠሩ አልቀረም፡፡ የተፈጠረው ጫና ወላጆችን ልጆቻቸው ወደጐዳና ወጥተውና ሥራ ሠርተው ቤተሰባቸውን እንዲደጉሙ ግፊት ስለማድረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

የኤች አይቪ ኤድስ መስፋፋትና በዚህም ሳቢያ በርካታ ህፃናት ወላጆቻቸውን በሞት መነጠቅ ሕፃናት የጐዳናን ሕይወት እንዲቀምሱ ማድረጉ በዚህ አካባቢ የተደረጉ ጥናቶች ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡ ከዚህ ቀደም እድሜያቸው እጅግ በጣም ዝቅ ያሉ ህፃናትን ጐዳና ላይ መመልከት በአፍሪካ ያልተለመደ ነበር፡፡ አሁን ግን ችግሩ አሥከፊ ደረጃ ላይ እየደረሰ በመምጣቱ የሦስትና አራት አመት ህፃናትን ጐዳና ላይ መመልከት በአፍሪካ የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቶአል፡፡

በአብዛኛው የአፍሪካ ሐገራት ሕፃናት በጦርነት፣ በረሃብ፣ እና በበሽታ ከሚደርሱባቸው ጥቃቶች ለማምለጥ ወደ ጐዳና ሲወጡ ይስተዋላሉ፡፡

## 3.2 ጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ብዛትና ሥርጭት በኢትዮጵያ

በአገራችን ኢትዮጵያ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ብዛትና ሥርጭት አሥመልክቶ በተሟላ መልኩ የሚዘግብ የተጠናቀረ መረጃ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ድርጅቶች የሚያወጡዋቸው መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ የሚደርሱ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በኢትዮጵያ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ውሥጥ 60,000 የሚደርሱት በመዲናችን በአዲስ አበባ ከተማ ይገኛሉ፡፡ ሌሎች ድርጅቶች ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት አሃዝ ላይ እንደማይስማሙና ቁጥሩ ከዚህ እንደሚያሻቅብ ይገልፃሉ፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር ስድስት መቶ ሺ እንደሚደርስና ከዚህ ውስጥ ደግሞ አንድ መቶ ሺ የሚሆኑት በአዲስ አበባ እንደሚገኙ ይገምታሉ፡፡

ከእነዚህ የተለያዩ ግምቶች በመነሳት በትክክል የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ቁጥር በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ለማወቅ አሥቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህ ጽሑፍ አንባቢያን በጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ዙሪያ በኢትዮጵያ የተደረጉ ጥናቶችንና ግምቶችን ከዚህ በመቀጠል ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግስትን ትኩረት በመሳብ የዳሰሳ ጥናት በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ የተደረገው እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1974 ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ጥናቱ የተካሄደው Rehabilitation Agency for the Disabled በሚባል መንግስታዊ ድርጅት ሲሆን የጥናቱ ርዕስ ደግሞ "Addis Ababa Street Boys Survey" ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ የዳሰሳ ጥናት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር 5004 እንደሚደርስ ተገምቶአል፡፡ ከእነዚህም ውሥጥ የወንዶቹ ቁጥር 4955 ሲደርስ የሴቶቹ ደግሞ 49 መሆኑን ጥናቱ ያስረዳል፡፡

የዳሰሳው ጥናት ከተደረገ ከስድስት አመት በኂላ ማለትም በ1980 ዓ.ም የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ችግር በዋና ዋና ከተሞች መታየት መጀመሩን የተደረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

በመቀጠልም በ1988 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሲዊድን ህፃናት አድን ድርጅት ጋር በመሆን በተመረጡ የአዲስ አበባ አካባቢዎች በጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ላይ ጥናት አድርጓል፡፡

በ1991 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት ፒተር ተኮን የሚባል አማካሪ ቀጥሮ ባስደረገው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት የጐዳና ህፃናት ቁጥር 100,000 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ ይኸው ጥናት ቁጥራቸው ግማሽ ሚሊዮን የሚደርሱ ሕፃናት በድህነት አረንቋ ውሥጥ በሚገኙም ቤተሰቦች ውሥጥ እንደሚኖሩና የጐዳና ህይወትን ለመቀላቀል አፋፍ ላይ እንደሚገኙ ይጠቁማል፡፡

"Protection, Respect and Opportunity for the Street Children of Ethiopia" በሚል ርዕስ በተጻፈው ሪፖርት ከሁለት አመት በኂላ በ1993 ዓ.ም በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ እና በተባበሩት መንግስታት የህፃናት መረጃ ድርጅት (አየርላንድ ከሚገኘው ኮርክ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር በመተባበር) በአራት የተመረጡ ከተሞች ላይ በተደረገው ጥናት ፒተር ታኮን ካቀረበው ሪፖርት ከተዘረዘሩት ግኝት ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በኢትዮጵያ እንደሚገኙ ግምት ተወስዷል፡፡

በ1995 ዓ.ም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ ብሔራዊ የዳሰሳ ጥናት ተደርጐ በኢትዮጵያ ውሥጥ አንድ መቶ ሺ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ ይኸው ብሔራዊ የዳሰሳ ጥናት ከተደረገ

ከአንድ አመት በኂላ ማለትም 1996 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ሕፃናት መርጃ ድርጅት በኢትዮጵያ ያሉትን የጐዳና ሕፃናት ቁጥር ሁለት መቶ ሺ ገምቶአል፡፡

የጐዳና ህፃናት ወዳጆች ማህበር በ2003 በስምንት ከተሞች ላይ ባደረገው ጥናት በኢትዮጵያ የሚኖሩ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ቁጥር አንድ መቶ ሺ እንደሚደርስ የገመተ ሲሆን በየከተሞቹ ያሉ የጐዳና ሕፃናትን ቁጥር (ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት) አቅርቧል፡-

ሠንጠረዥ 1፤ በስምንት ከተሞች በ2003 እ.ኤ.አ. የተመዘገቡ የጐዳና ሕፃናት ብዛት

| ተ.ቁ | ከተማ | | የጐዳና ሕፃናት ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ | | 60,000 |
| 2 | ባህር ዳር | | 1,505 |
| 3 | ሐዋሳ | | 2,555 |
| 4 | ሻሸመኔ | | 1,740 |
| 5 | ናዝሬት | | 1,326 |
| 6 | ደሴ | | 2,012 |
| 7 | መቀሌ | | 1,900 |
| 8 | ድሬዳዋ | | 5,643 |
| | | ድምር | 76,681 |

ከላይ በተዘረዘሩ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ብዛት በተለያዩ ድርጅቶች በተደረጉ ጥናቶች የተለያዩ አሀዞች የተሰጣቸው ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በቅርቡ በ2007 እ.አ.አ. በአዲስ አበባ በኢኮኖሚና ፋይናንስ ልማት ቢሮ፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከአለም የህፃናት መርጃ ድርጅት ጋር በመሆን ባስጠኑት ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ውሎአቸውንና አዳራቸውን ጐዳና ላይ ያደረጉ ህፃናት ቁጥር ከ6,600 እስከ 10,000 እንደሚደርስ ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በሐምሌ ወር 2010 በተደረገ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቆጠራ ውሎአቸውንና ሕይወታቸውን ጐዳና ላይ ያደረጉ ሕፃናት ቁጥር ከ4,000 በላይ እንደሚደርስ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

ቆጠራው የተደረገው በክረምት ወራት ውስጥ በመሆኑና በዚህ ወቅት የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት የክረምት ብርድና ዝናብ ሊያደርስባቸው የሚችለውን አደጋ

መቆቆም ስለሚሳናቸው በዚህ ወቅት አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሞቃት አካባቢ ስለሚሰደዱ የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት ቁጥር ከዚህ በከፍተኛ ደረጃ ሊጨምር እንደሚችል ግምት መውሰድ ይቻላል።

ከላይ ከተዘረዘሩ ጥናቶችና ግምቶች በስተቀር የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ቁጥር በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል በትክክል የሚገልጽ አስተማማኝ መረጃ ማግኘት አልተቻለም። ለዚህም በዋነኛነት ሕፃናትን የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ብሎ ለመፈረጅ የተጠቀሙበት መመዘኛ የተለያዩ መሆናቸው ነው። እነዚህም ሁኔታዎች በኢትዮጵያ የጐዳና ሕፃናት ቁጥር ይህን ያህል ነው ብሎ ለመፈረጅ የሚደረጉትን ሙከራዎች አስቸጋሪ ያደርጉታል።

# 4. የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ሁኔታ

## 4.1. የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ዲሞግራፊያዊ ሁኔታ

### 4.1.1. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የእድሜና የፆታ ሁኔታ

በአለም አቀፍ ደረጃ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የዕድሜ ክልል ይሄ ነው የሚል የለም። የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ዕድሜ ከቦታ ቦታ ይለያያል። በአብዛኛዎቹ በዚሁ አካባቢ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ እድሜያቸው ስምንት አመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ህፃናት ያለ ወላጅና አሳዳጊ ድጋፍ እራሳቸውን ችለው እንደሚኖሩ ይገልፃሉ። በበለፀጉ አገሮች ደግሞ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የእድሜ ክልል ከአሥራ ሁለት አመት በላይ መሆኑ ይነገራል።

ከጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት መካከል የወንዶቹ ቁጥር በመልማት ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ ከ70% በላይ ሲሆን የሴቶቹ ቁጥር ደግሞ ከ30% እንደሚያንስ የጥናት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ በተለየ መልኩ በአደጉ ሀገራት የወንድና የሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር ተመሳሳይ ነው።

በአለም የጤና ድርጅት የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ከሆነ በመልማት ላይ ባሉ ሀገራት የሴት ጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር ሊያንስ የቻለው በሚከተሉት ምክንያቶች መሆኑን ይገልፃል።

1. በማህበረሰባችን ልጃገረዶች ለቤተሰቦቻቸው ታዛዥና አገልጋይ ሆነው እንዲያድጉ ስለሚደረጉ የባህሪ ችግር በመፍጠር ከቤተሰቦቻቸው ጋር ግጭት ውስጥ የመግባትና ወደ ጐዳና የመውጣት ሁኔታ ከወንድ ልጆች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑ በምክንያትነት ይጠቀሳል። ከዚህ በተጨማሪም

ልጃገረድ ሕፃናት እድሜያቸው አስራ ሶስት ሲደርስ የሚዳሩበት ሁኔታ መኖር የሴት ህፃናትን ወደ ጐዳና መውጣት እንደሚቀንስ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

2. ጐዳና ላይ የሚኖሩ ሴት ህፃናት ከወንዶች ይልቅ በማህበረሰቡ አባላት መሪዎችና ባለስልጣናት እይታ ውስጥ በቀላሉ ስለሚወድቁ እና እነዚህን ሴት ሕፃናት ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚቀላቀሉባቸው፣ ግለሰብ ቤት ውስጥ ለቤት ሰራተኝነትና በወሲብ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚመለመሉባቸው ሁኔታዎች በብዛት ስለሚኖር የጐዳና ህይወትን በዘለቄታው የሚገፉበት ሁኔታ አናሣ ነው፡፡ ይሄም የጐዳና ተዳዳሪ ሴት ህፃናት ቁጥር አናሳ ለመሆኑ አስተዋጽኦ አድርጐአል፡፡

3. ሌላኛው ምክንያት ሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከአጥኚዎች እይታ ውጪ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ይበረክታሉ፡፡ ከተለያዩ ወገኖች ሊደርስባቸው ከሚችሉ ትንኮሳዎችና ጥቃቶች እራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከአለባበስ ጀምሮ እራሳቸውን እንደ ወንድ በመቁጠር ከአጥኚዎች እይታ እንደሚርቁ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በኢትዮጵያ የሚገኙ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የእድሜ ክልል በዋነኛነት በአስርና በአስራ አምስት መካከል ይገኛል፡፡ ነገር ግን ለጋ ሕፃናት በሌሎች በመበልፀግ ላይ ባሉ አገሮች ትልልቅ ከተሞች እንደሚታየው (በአራት አመታቸው) ወደ ጐዳና ይወጣሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚሁ ጥናቶች የሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር ከ30% እንደሚያንስ ይጠቁማሉ፡፡

### 4.1.2. የቤተሰብና የስደት ሁኔታ

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በከተሞች ውስጥ ከሚገኙ ቤተሰቦች፣ ከችግረኛና በትዳር ቀውስ ውሥጥ ከሚገኙ ቤተሰቦች፣ ከገጠር አካባቢ ከሚፈልሱና የመደበኛ ሥርዓተ ትምህርት የተፋቸው ህፃናት፣ ከተፈጥሮ አደጋ ሽሽት እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች እንደሚመጡ በመስኩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

በስምንት ከተሞች የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ከሆነ አብዛኛዎቹ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከወላጆቻቸው ቢያንስ አንዱ በህይወት እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በርካታ የጐዳና ህፃናት ከሌሎች ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች በስደት እንደሚመጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 4.2. ሕፃናቱ ወደ ጐዳና እንዲወጡ የሚገፋፉዋቸው ምክንያቶች

የተለያዩ ጥናቶች የተለያዩ ምክንያቶችን ለሕፃናቶቹ ወደ ጐዳና መውጣት በዋነኛነት ይጠቅሳሉ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት በዋነኛነት ይገኛሉ፡፡

1. ሕፃናቶች የሚያድጉበት ቤተሰብ ሁኔታ በዋነኛነት ለልጆቹ ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ባህሪ ቀረፃዎች ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ይታወቃል፡፡ በቤተሰብ ውሥጥ በልጆች ላይ የሚፈፀሙ ድብደባዎችና አካላዊ ቅጣቶች ለልጆች ከቤት መልቀቅና ወደ ጐዳና መውጣት በዋነኛነት እንደሚጠቀሱ ብዙ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

2. የቤተሰብ መፍረስ ለልጆች የጐዳናን ህይወት እንዲቀላቀሉ ከሚዳረጉዋቸው ምክንያቶች በዋነኛነት ይጠቀሳል፡፡

3. የቤተሰብ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ መገኘትና ለልጆች ወደ ጐዳና መውጣት በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

እንደ የአለም ጤና ድርጅት ጥናት ሕፃናት ወደ ጐዳና በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚወጡና ከእነዚህ ውስጥ ባደጉም ይሁን በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ድህነት በዋነኛ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ ጥናቱ በመቀጠልም

ሀ) ጐዳና ላይ ሥራ በመሥራት የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ኑሮ ለመደጐም የትምህርት ቤት ክፍያቸውን ለመሸፈን ወዘተ በማለት እንደሚወጡ፤

ለ) አንዳንድ ሕፃናት የቤተሰቦቻቸው መኖሪያ በመጨናነቁና ለራሳቸውም ሆነ ለአንዳንድ የቤተሰብ አባላት ቤት ለመከራየት ሲሉ ወደ ጐዳና ወጥተው ሥራ እንደሚሰሩ፤

ሐ) በቤት ውሥጥ ከሚደርስባቸው ጥቃትና ድብዳባ ለመሸሽ ሲሉ አንዳንድ ሕጻናት ወደ ጐዳና እንደሚወጡ፤

መ) ቤተሰብ ከሚፈጥርባቸው የሥራ ጫና ለመሸሽ ሲሉ ወደ ጐዳና የሚወጡ ሕፃናት እንዳሉ ያሳያል፡፡

የጎዳና ሕይወት የሚቀላቀሉ ህጻናት ምንጭ በአብዛኛው ከገጠራማው የሀገራችን ክፍሎች ስለመሆናቸው በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ከተማ የተሻለ ኑሮ፣ ትምህርትና አገልግሎት ፍለጋ ከገጠር ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የሚሰደዱ ህጻናት ቁጥር በቀላሉ እንደማይገመትና እነዚህ ህጻናት ከተማ ከደረሱ በኃላ የሚያጋጥማቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ለጎዳና ሕይወት እንደሚዳርጋቸው እነዚሁ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

## 4.3. የጐዳና ሕይወት ገጽታዎች

የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት በአንድ ቦታ በቋሚነት የመኖር ባህሪ እንደሌላቸው ለበርካታ ችግሮች ማለትም ለብርድ፣ ለፀሐይ፣ ለጉልበት ብዝበዛ፣ለምግብ እጥረት፣ ለጥቃት ለአደንዛዥ ዕፅ፣ ለተለያዩ ጤና ችግሮች ተገላጭነታቸው በተለያዩ ጥናቶች የተዘገበና ዕውቅና የተሰጠው ጉዳይ ነው።

ከሦስት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ውሥጥ ሁለቱ በመጠለያ ውሥጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ወይም ለብቻቸው እንደሚኖሩ የተጠኑ ጥናቶች መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከጠቅላላ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ውስጥ 15% የሚሆኑት ውሎአቸውንና አዳራቸውን ጐዳና ላይ ስለማድረጋቸው ጥናቶች ይጠቁማሉ። አብዛኞዎቹ የጐዳና ህፃናት በሚኖሩት የጐዳና ሕይወት ላይ ደስተኛ አለመሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ።

አብዛኞዎቹ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከወላጆቻቸው ጋር ግንኙነት ቢኖራቸውም አብዛኛውን ጊዜያቸውን ግን ጐዳና ላይ ሥራ በመሥራትና የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ገቢ በመደጐም ያሳልፋሉ።

ጥቂት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሥለመሆኑና ጥቂት ሌሎች ደግሞ በተለይም ውሎአቸውና አዳራቸውን ጐዳና ላይ ያደረጉ ህፃናት በልመና ለዕለት ጉርስና ለመሳሰሉት ፍላጐቶቻቸው ማሟያ የሚሆናቸውን ገንዘብ እንደሚያገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ሠርተውም ሆነ ለምነው በሚያገኙት ገንዘብ ምግባቸውንና ልብሳቸውን እንደሚገዙበት፣ ቤተሰባቸውን እንደሚደጉሙበት፣ የትምህርት ቤት ወጪያቸውን እነደሚሸፍኑበት፣ ለመጠለያና ለሌሎች የሚያስፈልጉዋቸውን ወጪዎች ጭምር እንደሚሸፍኑበት ጥናቶች ያስረዳሉ።

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በጐዳና ህይወታቸው ለበርካታ ችግሮች ስለመጋለጣቸው ጥናቶች የሚያስረዱ ሲሆን ከእነዚህም ውሥጥ በፖሊስ አካላዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው፣ በጉልበተኞች አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ጥናቶች ያሳያሉ።

### 4.3.1. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የጤና ሁኔታ

የተለያዩ ጥናቶች እንዳመለከቱት አብዛኞቹ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በተለያዩ የጤና ጠንቆች ይጠቃሉ። የሚኖሩበት አካባቢ ለጤና ምቹ አለመሆን፣ የጤና አገልግሎቶች አቅርቦት እጥረት እንዲሁም ያለውን አቅርቦት በተፈላጊው መጠን አለመጠቀም ከጤና ጋር በተያየዘ ለሚያጋጥማቸው ችግሮች አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች ተደርገው በበርካታ ጥናቶች ውስጥ ሲጠቀሱ ይስተዋላሉ።

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከሚያጋጥሟቸው የተለመዱ የጤና ችግሮች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

- የሆድ ጤና መታወክ፤ ይህ በአብዛኛው ጊዜ የተጣሉና የተመረዙ ምግቦችን በመመገብ አልያም ህፃናቱ የራሳቸውን የእጅ ንፅህና ሳይጠብቁ ምግብና መጠጥ በሚጠቀሙበት ጊዜ ሊከሰት ይችላል፡፡
- የመተንፈሻ አካላት የጤና ችግር ይህ የጤና ችግር የተመጣጠነ ምግብ ባለመግኘት፣ ዝናባማና በጣም ቀዝቃዛ በሆነ የአየር ሁኔታ እንዲሁም እጅግ በተፋፈነ መኖሪያ ውስጥ በመኖር የሚከሰት ነው፡፡
- ልቅ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚከሰቱ የአባላዘር በሽታዎች፣ እንደወባ፣ የቆዳ በሽታዎች፣ ከአይን ጋር የተያያዙ የጤና ጉድለቶች የሚስተዋሉ የተለመዱ የጤና ችግሮች ናቸው፡፡

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚጠቁባቸው የጤና ችግሮች ህፃናቱ የሚገኙበት አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ነፀብራቅ ናቸው፡፡ ከሆድ ጋር በተያያዘ ከሚከሰቱ የጤና ችግሮች የተጣሉና የተበከሉ ምግቦችን በመመገብ ሊከሰት ይችላል፡፡ በጐዳና ላይ የሚገኙ ህፃናት የቆሻሻ ገንዳ ውስጥ የተጣሉ ምግቦችን ሲመገቡ ማየት የሚያስገርም ክስተት ነው፡፡ ከመተንፈሻ አካላት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱትም ቢሆኑ የተመጣጠነ ምግብን ካለማግኘት፣ በአስቸጋሪ የአየር ፀባይ ውስጥ በመኖር በተለይ ደግሞ በትንፋሽ የሚተላለፉ በሽታዎች በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው እንዲተላለፉ በሚያደርጉ የተፋፈጉ መኖሪያዎች ውስጥ ከመኖር ሊከሰቱ ይቻላሉ፡፡

ስለዚህ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ለሁሉም አይነት የጤና ችግሮች የተጋለጡና ሊጋለጡ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ባሻገር በስምንት ከተሞች ውስጥ በተደረገው ጥናት ውስጥ በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱ ህፃናት ውስጥ በአባላዘር በሽታ የተጠቁት ህፃናት ብዛትና የዕድሜያቸው ለጋነት ምን ያህል ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ እንደተጋለጡ ያመለክታል፡፡

አብዛኞቹ የጐዳና ህፃናት ነፃ የህክምና አገልግሎቶችን የሚያገኙበት መንገድ የለም፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ለአብነትም የነፃ ህክምና ለማግኘት ከቀበሌ መስተዳድሮች የሚሰጡ የነፃ ህክምና ሰርተፍኬትን በቀላሉ ማግኘት አለመቻላቸው ይጠቀሳል፡፡ ለዚህ ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኙ የቀበሌ መስተዳድሮች ውስጥ በነዋሪነት ያለተመዘገቡና የነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የከፋው ደግሞ ነፃ ህክምና በሚሰጥባቸው የመንግስት የጤና ጣቢያዎች ያለው ወረፋ ኑሮአቸውን በዕለት ገቢ ላይ ላደረጉት ለነዚህ ህፃናት የዕለት ጉርሳቸውን ለመፈለግ እንቅፋት የሚሆንባቸው መሆኑ ነው፡፡

ለነዚህ ህፃናት የህክምና እርዳታ አለማግኘት በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ የገቢ ሆኔታቸው በዋናነት ይጠቀሳል። ገቢያቸው ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ የጤና ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ለህክምና የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን አይችሉም። በከተሞች ውስጥ ለነዚህ ለችግር ተጋላጭ ህፃናት የነፃ ህክምና ዕድል አለመኖር ሁኔታውን እጅግ የከፋ ያደርገዋል።

### 4.3.2. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት አመጋገብ ሁኔታ

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በቀን የሚመገቡት ምግብ ከሚያስፈልጋቸው አንፃር በቂ ስላለመሆኑ የተጠኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በጎዳና ላይ እየዋሉ በምሽት ወደ ቤተሰቦቻቸው ቤት የሚገቡ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ምግባቸውን ከቤት ያገኛሉ። እነዚሁ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑ የጐዳና ህፃናት (በአብዛኛው ወንዶች) ምግብን ከአነስተኛ ካፍቴሪያዎች በመግዛት ይመገባሉ። ከአንድ ሶስተኛ እስከ ሁለት አምስተኛ የሚሆኑ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የተጣሉ ምግቦችን ብቻ በመመገብ ህይወታቸውን ይገፋሉ።

### 4.3.3. አደንዛዥ ዕፅ፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ የወሲብ ጥቃትና ወንጀል

ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል የጐዳና ተዳዳሪ ተዳዳሪ ህፃናት የአንዳንድ ሱስ አምጪ ዕፅ ተጠቃሚ ናቸው። በዋና ከተሞች ከሚገኙ ጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ውስጥ ከአንድ አምስተኛ እስከ ሁለት አምስተኛ የሚሆኑት በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ የተጠመዱ ናቸው። እነዚህ ህፃናት በብዛት ከሚጠቀሙባቸው ውስጥ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ጫት፣ ካናቢስና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

ለጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚሰጠው ትኩረት በአብዛኛው በህፃናቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ ማለትም በድህነት፣ በመኖሪያ ቦታ ዕጦት፣ በትምህርት ዕድል ማጣት፣ በኤች አይቪ ኤድስ እና በአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት ላይ ያተኩራሉ። ይሁን እንጂ በብራዚልና በኮሎምቢያ የጐዳና ህፃናት ላይ የህግ አስከባሪ አካላት የሚያደርሱባቸው ህገወጥ ጥቃት የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው። ይኼም በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ውስጥ የተረጋገጡትን ሁሉን አቀፍ መብቶች በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ትኩረት ያለማግኘታቸው ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በህብረተሰቡ ዘንድ እንደ ማህበራዊ ጠንቅ አልያም እንደ ወንጀለኛ መቆጠራቸው ወይም ደግሞ በቱሪስት ለሚሞሉት የከተማ መንገዶች እና የንግድ አካባቢዎች ችግር ፈጣሪ ተደርገው መወሰዳቸው፤ ፗሪዎችና ህግ አስከባሪ አካላት እነዚህ ህፃናት በማንኛውም መንገድ ከጐዳና ላይ መወገድ አለባቸው የሚል አቋም እንዲይዙ አድርጓቸዋል።

በመላው አለም የሚገኙ የጐዳና ተዳዳሪዎች በመንግስታትት፣ በህግ አስከባሪዎችና በግል የፀጥታ አስከባሪዎች የተለያዩ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ እነዚህ ህፃናት ድብደባ፣ ዝርፊያ፣ ወሲባዊ ጥቃት ከዚህ ከፍ ሲልም ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡

የጐዳና ህፃናት በአብዛኛው በሌብነትና ዝርፊያ ተጠርጥረው ክስ ይመሰረትባቸዋል፡፡ ጐዳና ላይ በመኖራቸው አልያም መኖሪያ ቤት የሌላቸው በመሆኑ ብቻ በተደጋጋሚና በዘፈቀደ እየተያዙ ለእስር ይዳረጋሉ፡፡ ህጋዊ ባልሆኑ አነስተኛ ንግዶች ውስጥ በመሳተፋቸው፣ በሌብነት፣ ከአደንዛዥ ዕፅ ጋር በተያያዙ ወንጀሎች እንዲሁም በሴተኛ አዳሪነት ውስጥ በመገኘታቸው ለእስር ይዳረጋሉ፡፡ ጥቂት የማይባሉ የጐዳና ልጆች ሌሎች የፈፀሙትን ወንጀል ለመደበቅ ወይም ሌሎችን አሳዶ ለመያዝ እንደ ምንጭ ይሆናሉ በማለት ለእስር ይዳረጋሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የጐዳና ህፃናት በሚኖሩበት አካባቢ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ መረጃ አላቸው፣ ከወንጀለኛ ቡድኖች ጋር ግንኙት አላቸው የሚል የተሳሳተ አመለካከት በህግ አስከባሪዎች ዘንድ መኖሩ ነው፡፡

የተፈፀመው ወንጀል ምንም ይሁን ምን የጐዳና ህፃናት በፖሊስ ይሳደዳሉ ወደ እስር ቤትም ይወረወራሉ፡፡ ከአዋቂዎች ጋር ተቀላቅለው አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ለበርካታ ቀናት በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ይደረጋሉ፡፡ በእስር ቤቶች ውስጥም ለተለያዩ ጥቃቶች ይጋለጣሉ፡፡ በተለይ ሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ከእስር ለመፈታት የወሲብ ግንኙነት እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡፡ የአስገድዶ መደፈር ድርጊት ሊፈፀምባቸው ይችላል፡፡

### 4.3.4. በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች

በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች መንስኤ፣ ጥልቀትና ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ወሲባዊ ጥቃት፣ አካላዊ ጥቃትና ስነልቦናዊ ጥቃት በማለት በሦስት ክፍሎች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

በጥንት ጊዜ ህፃናትን ለወሲብ መጠቀም ተቀባይነት ያለው እና የሚበረታታ ድርጊት ተደርጐ ይወሰድ ነበር፡፡ (See Benjamin and Masters, 1964; Mrazek,1981a; Rush, 1980; Schetky, 1988a; L.G.Schultz,1982) ይህ ድርጊት እንደ ስህተት አልያም እንደ ጐጂ ድርጊት የሚታይ ሳይሆን ለህፃናቱ አስፈላጊና ጤናማ እንደሆነ ነገር ይታሰብ ነበር፡፡

በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች በሁሉም የአለማችን ማህበረሰቦች ውስጥ ይፈፀማሉ፡፡ ጥቃቶቹ በሚስጥር የሚያዙ በመሆኑ የችግሩ ሥፋትና ጥልቀት

እንዳይታወቅ አድርጎት ቆይቷል። በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ለረጅም ዘመናት ሲፈፀሙ ቢቆይም አሁንም በብዙ ማህበረሰቦች እንደ ችግር አይቆጠርም።

የህፃናት ወሲባዊ ጥቃት ዘርፈ ብዙና እጅግ የተወሳሰበ ባህርይ አለው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ የችግሩ ግዝፈት በመጠኑም ቢሆን እየታወቀ መጥቷል። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንድ አራተኛ የሚሆኑት የጐዳና ተዳዳሪ ሴት ህፃናት በሴተኛ አዳሪነት ህይወት ውስጥ ገብተው ለወሲባዊ ጥቃት ይጋለጣሉ። ለዚህ ደግሞ ድህነት በዋና ምክንያትነት ይጠቀሳል። የተወሰኑ የጐዳና ተዳዳሪ ሴት ህፃናት ለወሲብ ንግድ መጠቀሚያነት በደላሎች አማካይነት ለህገ ወጥ ንግድ ይጋለጣሉ። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህም በወንድ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ የሚደርሰው የወሲብ ጥቃት የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቷል።

### 4.3.5. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የትምህርት ሁኔታ

አብዛኞቹ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ (ከ5-18 ዓመት) ቢሆንም ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት እየተከታተሉ አይደሉም። ስለዚህ በዕድሜያቸው ሊያገኙ ከሚገባቸው እንደ ትምህርት ካሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በሙሉም ሆነ በከፊል የተገለሉ ናቸው።

በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ለእነዚህ ህፃናት የሚመቹ ሁኔታዎችን ብዙዎቹ የጐዳና ህፃናት አሁን ባሉት መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው ትምህርት ለመከታተል ዕድሉ የላቸውም።

## 5. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚደርስባቸው ችግሮች የሚቋቋሙባቸው መንገዶች

ለጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የመኖር ህልውና ማለት በቂ ምግብ፣ መጠለያና ልብስን የመሳሰሉት መሰረታዊ ፍላጐቶች መሟላት ብቻ ሳይሆን ራስን ከተለያዩ ጥቃቶች ጠብቆ ማቆየትን ያካትታል።

በርካታ ጥናቶች እንዳመለከቱት የጐዳና ተዳዳሪዎች ራሳቸውን ከተለያዩ ጥቃት ለመጠበቅ በቡድን ይደራጃሉ። ከዚህ ባሻገር የመኖሪያ ድንበራቸውን በተለይም የሥራ አካባቢያቸውንና የማደሪያ ቦታቸውን ከሌሎች ጥቃት አድራሾች ለመጠበቅ በቡድን ይንቀሳቀሳሉ። ሌላው በቡድን መደራጀታቸው በዕለት ተዕለት የሚያጋጥማቸውን በተለይም በህመምና ችግር ጊዜ እርስ በርስ ለመደጋገፍና ለመረዳዳት ያስችላቸዋል።

በመሆኑም የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት በቡድን ውስጥ በአባልነት ሆኖ በመንቀሳቀስ አስቸጋሪ የሆነው የጐዳና ህይወት ለመቋቋምና ለማሸነፍ ይጥራሉ።

ሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚደርስባቸውን አስከፊ ወሲባዊ ጥቃት ለመቋቋም የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ። ለምሣሌ አንዲት የጐዳና ተዳዳሪ በአካባቢዋ ከሚገኙና ተሰሚነት ካላቸው ወንዶች ከአንዱ ጋር ግንኙት በመመስረት እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ። በዚህም ከወንዱ ጥበቃ ታገኛለች። ከዚህ ውጭ ግን ለጥቃት የሚያጋልጣቸው ሁኔታ ካለ ወይም ደግሞ ጥቃት ከደረሰባቸው ሁኔታውን ለፖሊስ ሪፖርት በማድረግ ራሳቸውን ለመጠበቅ ጥረት ያደርጋሉ።

## 6. የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ችግር ለመታደግ የተደረጉ ጥረቶች

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ችግር ከመቅረፍ አኳያ የሚደረጉ ጥረቶች የመንግስትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የህብረተሰቡን፣ የሀይማኖት ተቋማትን እንዲሁም የግል ተቋማትን የተቀናጀ እንቅስቃሴ ይፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ ለችግሩ ምላሽ ከመስጠት አኳያ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ከችግሩ ጽናት አንፃር እጅግ አናሳ ናቸው።

የጐዳና ተዳዳሪዎችን ከችግር ለመታደግና መልሶ ለማቋቋም በመንግሥትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ቀጥለን እንመለከታለን።

### 6.1. በመንግስት በኩል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ችግሮች ከመቅረፍ አኳያ በመንግስት በኩል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ጥበቃና ከለላ መስጠት፣ የትምህርት ድጋፍ፣ የሙያ ስልጠና እንዲሁም የገቢ ማሳደጊያ ድጋፍ ላይ እንደሚያተኩር ከወጣቶች፣ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ሥራዎች በአቅም ግንባታ፣ የህፃናትን መብት መከበርን ማበረታታት፣ እንዲሁም በዩኒሴፍ ድጋፍ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን በመደገፍ ዙሪያ የተቀረፁ ናቸው። ይህ ኘሮግራም በ14 ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ እየተተገበረ ይገኛል። የዚህ ኘሮግራም ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች የሆኑት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት፣ ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ያጡ ህፃናት እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ናቸው።

በዚህ ኘሮግራም ከሚሰጡት መሀል የትምህርት ድጋፍ አንዱ ሲሆን በዚህም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ

የማድረግ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን፣ ዩኒፎርሞችን ያካተተ ድጋፍ ይሰጣል።

የሙያ ስልጠና የሚሰጠው ለጐዳና ተዳዳሪ ወጣቶችና እናቶች ሲሆን እናቶች የብድር አገልግሎት አግኝተው በገቢ ማስገኛ ሥራዎች እንዲሰማሩ እገዛ ይሰጣል። የመኖሪያ ችግርን ከመቅረፍ አኳያ ለኑሮ አመቺ ያልሆኑና የፈራረሱ ቤቶችን የመጠገን እንዲሁም ጊዚያዊ መጠለያን ማዘጋጀትን ያካትታል። ኘሮግራሙ ጤናን በተመለከተ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል። ለአብነትም የህክምና ድጋፍ፣ የጤና ትምህርት፣ የአካባቢ ንፅህና እና የመፀዳጃ ቤቶች ግንባታ ይጠቀሳሉ።

የኢኮኖሚ ድጋፍ ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ያጡ ህፃናትን እና የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ላይ ያተኮረ ሲሆን ለህፃናቱ ወይም ለወላጆች አልያም ለአሳዳጊዎቻቸው የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። በአጠቃላይ በዚህ ኘሮግራም ቁጥራቸው ከ24,000 በላይ የሆኑ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትና እናቶች ተጠቃሚ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥረቶች በተጨማሪ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን ለመደገፍ የሚሰሩ ብሔራዊና ክልላዊ የሥራ ግብረ ሃይሎችን አቋቁሟል። ህብረተሰቡን በመቀስቀስ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎችም እየተካሄዱ ነው። የህፃናት ፈንድ ለማቋቋምና አጠቃላይ የህፃናት ፖሊሲ ለመንደፍ በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር እየተሰራ ስለመሆኑ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

## 6.2. መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች

በኢትዮጵያ ከ60 በላይ የሚሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በቀጥታ በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ ለመስራት ተመዝግበው ይንቀሳቀሳሉ። በተመሳሳይ ከ105 በላይ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን የሚያግዙ፣ ግን ቀጥተኛ ያልሆኑ፣ ኘሮግራሞችን ያካሂዳሉ። መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ከመደገፍ አኳያ የሚያካሂዷቸውን ኘሮግራሞች እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

ሀ. አስቀድሞ የመከላከል ሥራ፡-

- የቤተሰብን፣ እንዲሁም የወጣቶችን፣ የኑሮ ሁኔታ በገቢ ማስገኛ ሥራዎች በማገዝ የማሻሻል ሥራ፤
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ ህፃናትን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎችን ማካሄድ፤

- መሠረታዊ የሆኑ ቀጥተኛ ድጋፎችን በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ህፃናት ማድረግ (እንደ የትምህርት ድጋፍ፣ የምግብ ድጋፍ፣ የህክምና እንዲሁም የመጠለያ አገልግሎቶችን ማቅረብ)፡፡

ለ. የማበረታታትና የድጋፍ ሥራዎች:-

- ከመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ድጋፍ ባሻገር የጎዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ ሌሎች በችግር ውስጥ ያሉ ህፃናት ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የሚያስችሉ አማራጭ መሰረታዊ የትምህርት ማዕከላትን ማቋቋምና ማስተዳደር፤
- ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ቀጥተኛ ድጋፍ ማድረግ፤ ማህበረሰቡን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶችና ማህበራትን በማሳተፍ ለነዚህ ህፃናት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲደረግ የማበረታታት ሥራ፤
- በህግ አስፈፃሚ አካላት መዋቅር መሥራት ውስጥ ለህፃናት ተስማሚ የሆኑ አሰራሮችና አገልግሎቶች እንዲኖሩ የማስቻል ሥራ (የህፃናት ጥበቃ ክፍሎች፣ የህፃናት እርምት ማዕከላት ይጠቀሳሉ)፤
- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ደህንነት ጥበቃ ስርዓት በሁሉም ደረጃ መዘርጋት፤
- ከመንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙት በመፍጠር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ህፃናት ህክምናን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

ሐ. የመልሶ ማቋቋምና የተሐድሶ ኘሮግራሞች:-

- በተለያየ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች በጎዳና ህይወት ውስጥ ገብተው ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ የተጋለጡ ሴት ህፃናትን መደገፍና ከዚህ ህይወት ወጥተው የራሳቸውን ጤናማና ውጤታማ ህይወት እንዲኖሩ የማገዝ ሥራ ማከናወን፤
- የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናትን በተለያዩ የድጋፍና የተሐድሶ ፕሮግራሞች፣ ለምሳሌ የሙያ ሥልጠና በመስጠት፣ በማሳተፍ እና ራሳቸውን እንዲችሉ የማገዝ ሥራ፤
- ማህበረሰቡን ያማከሉና በህብረተሰቡ እገዛ የሚካሄዱ ሴት የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናትን የማገዝና ካሉበት ህይወት የማውጣት ሥራ ፡፡

በአጠቃላይ በነዚህ ኘሮግራሞች ውስጥ ተካተው በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ቁጥር ከ35 ሺህ እንደማይበልጥ ይገመታል፡፡

# 7. የመፍትሔ ሐሳቦች

ሀገራት እጅግ ለተገፉና በችግር ውስጥ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለህፃናት ለወጣቶችና ለሴቶች ህይወት መለወጥ ብዙ መስራት እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ በርግጥም ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ፖሊሲ አውጭዎችና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የጐዳና ተዳዳሪነት ችግር መነሻ ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ከተቋማዊ ወይም ከመዋቅራዊ፣ ከነባራዊ ሁኔታ እና ከፖሊሲ ጋር በማያያዝ በሦስት ይመድቧቸዋል፡፡ እስካሁን የጐዳና ተዳዳሪነትን ችግር ለመቅረፍ በሁሉም አካላት የተደረጉ ጥረቶች የችግሩን መጠን በመቀነስ፣ የህብረተሰቡን የተሳሳተ አመለካከት በማስተካከል በኩል የሚፈለገውን ያህል ለውጥ ሳያመጡ ቆይተዋል፡፡

ስለዚህም በጐዳና ተዳዳሪነት ችግር ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እንደሆኑ ለችግሩ መነሻ በሆኑ ምክንያቶች ላይ ባተኮረ መልኩ ለሁሉም በአንድ ጊዜ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ሥራ መሰራት አለበት፡፡ ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎችን ቀጥሎ በተዘረዘሩት አራት ደረጃዎች ማከናወን እንደሚያስፈልግ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

## 7.1. ጥናት ማከናወን

በዚህ ጥናት ውስጥ እንደተገለፁት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የጐዳና ሕፃናት ቁጥር በትክክል ለማወቅ የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ማህበራዊ ክስተትን ከሌሎች ክስተቶች በመለየት የጐዳና ሕፃናት ለሚለው ቃል ሁሉን ወገን የሚያስማማ ፍቺም መስጠት አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ስለዚህ በዚህ አካባቢ መንግሥትና መንግሥታዊ ድርጅቶች የትብብር ሥራ መስራት እንዳለባቸው ለመጠቆም እንወዳለን፡፡ በትክክል የጐዳና ሕፃናት ቁጥር፣ የችግሩ ሥፋትና ጥልቀት እንዲሁም መወሰድ ባለባቸው እርምጃዎች ላይ ጥልቅ ጥናት መደረግ እንዳለበት ይሄ ጥናት ሃሳብ ያቀርባል፡፡

- *መሠረታዊ የሆኑ ቀጥተኛ ድጋፎችን በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ህፃናት ማድረግ (እንደ የትምህርት ድጋፍ፣ የምግብ ድጋፍ፣ የህክምና እንዲሁም የመጠለያ አገልግሎቶችን ማቅረብ)፡፡*

ለ. የማበረታታና የድጋፍ ሥራዎች፡-

- ከመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ድጋፍ ባሻገር የጐዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ ሌሎች በችግር ውስጥ ያሉ ህፃናት ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የሚያስችሉ አማራጭ መሰረታዊ የትምህርት ማዕከላትን ማቋቋምና ማስተዳደር፤
- ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ቀጥተኛ ድጋፍ ማድረግ፤ ማህበረሰቡን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶችና ማህበራትን በማሳተፍ ለነዚህ ህፃናት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲደረግ የማበረታታት ሥራ፤
- በህግ አስፈፃሚ አካላት መዋቅር መሥራት ውስጥ ለህፃናት ተስማሚ የሆኑ አሰራሮችና አገልግሎቶች እንዲኖሩ የማስቻል ሥራ (የህፃናት ጥበቃ ክፍሎች፣ የህፃናት እርምት ማዕከላት ይጠቀሳሉ)፤
- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ደህንነት ጥበቃ ስርዓት በሁሉም ደረጃ መዘርጋት፤
- ከመንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙት በመፍጠር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ህፃናት ህክምናን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

ሐ. የመልሶ ማቋቋምና የተሐድሶ ኘሮግራሞች፡-

- በተለያየ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች በጐዳና ህይወት ውስጥ ገብተው ለወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ የተጋለጡ ሴት ህፃናትን መደገፍና ከዚህ ህይወት ወጥተው የራሳቸውን ጤናማና ውጤታማ ህይወት እንዲኖሩ የማገዝ ሥራ ማከናወን፤
- የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን በተለያዩ የድጋፍና የተሐድሶ ፕሮግራሞች፣ ለምሳሌ የሙያ ሥልጠና በመስጠት፣ በማሳተፍ እና ራሳቸውን እንዲችሉ የማገዝ ሥራ፤
- ማህበረሰቡን ያማከሉና በህብረተሰቡ እገዛ የሚካሄዱ ሴት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን የማገዝና ካሉበት ህይወት የማውጣት ሥራ ፡፡

## 7.2. ተቋምን ወይም መዋቅርን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች

ተቋምን ወይም መዋቅርን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች በተቋማት ደረጃ የሚደረጉ ችግሩን የማስወገድ ጥረቶች በሚከተሉት ሥራዎች ላይ ሊያተኩሩ ይገባል፡፡

- **በጉዳና ላይ ለሚገኙና ሥራ ለሚሰሩ ህፃናት ጥበቃና ከለላ መስጠት**

በርግጥ ይህ ማድረግ ህፃናት የጉልበት ሥራ እንዲሰሩ የሚከለክሉ ህጐችና ኮንቬንሽኖች አንፃር ሊቃረን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ህፃናቱ ሥራ እንዲሰሩ እንደመፍቀድ ስለሚቆጠር፡፡ ይሁን እንጂ ሌላ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ በብሄራዊና በክልል ደረጃ የሚገኙ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አካላት፣ ፖሊስ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሐይላቸውን በማስተባበር ህፃናቱ ለበለጠ ጥቃት እንዳይጋለጡ መስራት ይገባል፡፡

- **የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት**

በቅርቡ የአዲስ አበባ መስተዳድር የጉዳና ተዳዳሪዎች መልሶ ለማቋቋም በዘረጋው ፕሮግራም ዙሪያ ከተሰሩት ውጭ የመገናኛ ብዙሀን በችግሩ ዙሪያ ብዙም የዘገባ ሽፋን ሲሰጡት አይስተዋልም፡፡ ስለሆነም በህብረተሰቡ ውስጥ የጉዳና ተዳዳሪነት ችግር ግንዛቤ ለማስጨበጥ ስልታዊ ዘዴዎችን በመንደፍ ሁሉም አካላት ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በቅርብ ተቀናጅተው ሊሰሩ ይገባል፡፡

- **የፖሊሲ ትግበራ**

የተመጣጠነ ክልላዊ ልማትን ለመፍጠር በገጠሩ አካባቢ የተለያዩ ሥራዎችን አጠናክሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም በገጠሩ አካባቢ በሚስተዋለው ድህነት ዜጐች (ህፃናትን ጨምሮ) ወደ ከተማ የሚያደርጉትን ፍልሰት እንዲገታ አስተዋፅኦ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በከተማና በገጠር የሚስተዋለውን ድህነት በፍጥነት ለመቅረፍ የወጡ ፖሊሲዎችን በመተግበሩ በኩል አፋጣኝ ምላሾችን ሊሰጡ ይገባል፡፡

- **የፖሊሲ ቀረፃ**

መንግስት በትምህርት ዙሪያ በተለይም ትምህርት ማቋረጥን የሚያስቀሙና ህፃናት ተኮር የሆኑ መሰረታዊ ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ የሚያግዙ ውጤታማ የሆኑ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ፖሊሲዎችን ሊያዘጋጅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

- የጤና አገልግሎት

የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ነፃ ህክምና እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ የማስፋፋት ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

- የሙያ ሥልጠና

የተጠቃሚዎቹን ፍላጐት ያገናዘበና የተቀናጀ የሙያ ሥልጠና በዚህ አስቸጋሪ ህይወት ውስጥ ላሉ የጐዳና ልጆች ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ እዚህ ላይ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህን በማስተባበሩ አኳያ ግንባር ቀደም ሊሆኑ ይገባል፡፡

## 7.3. ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች

በማህበረሰቡ ውስጥ ለዘመናት የቆዩ የተሳሳቱ አመለካከቶችና ጭፍን ጥላቻዎች ለጐዳና ተዳዳሪነት ችግር መባባስ የራሳቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በመሆኑም ለችግሩ መስፋፋት ትልቁን ድርሻ የያዘውን የአመለካከትና የአስተሳሰብ ችግር መቀየር የግድ ይላል፡፡ ከዚህ አኳያ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን ከችግር አውጥቶ በህብረተሰቡ ውስጥ ጤናማና ሰላማዊ ኑሮ እንዲቀጥሉ ለማስቻል የሚደረጉ ጥረቶች ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ሥራዎች መከናወን አለባቸው፡፡

- ማህበረሰቡን መሰረት ያደረገና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ የህፃናት ጥበቃ ስርዓትን መዘርጋት፣ ማበረታታት፤
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማህበረሰብ ንቅናቄ እና ማህበረሰቡን የራሱን ሀብት ተጠቅሞ ችግሩን በራሱ የሚፈታበትን መንገድ እንዲያዳብር የሚያስችለውን አቅም በስልጠና ማዳበር፤
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ማህበራትና ክበባትን በመጠቀም ህብረተሰቡን ወደ ተግባር የማንቀሳቀስ አቅም እንዲኖራቸው የማህበረሰቡን አቅምና ሀብት የመለየትና የጋራ ፕሮጀክቶችን ቀርፀው መንቀሳቀስ እንዲችሉ በሥልጠና ማገዝ፤
- መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወላጆቻቸውን በተለያየ ምክንያት ላጡ አሳዳጊና ተንከባካቢ ለሌላቸው ልጆች የፎስተር ኬር እና የስፖንሰር ሺፕ ፕሮግራሞችን እንዲተገብሩ ድጋፍ ማድረግ፤
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትን በቡድን በማደራጀትና ለአደጋ በማያጋልጧቸው እንደ መኪና

እጥበት፣ አነስተኛ ንግድ በመሳሰሉት ሥራዎች ውስጥ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን እንዲሰሩ ማገዝ፤

- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች የጐዳና ተዳዳሪ ልጆች ክበባትን በማደራጀትና እነዚህ ክበባት የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ለአካላዊና አዕምሮአዊ ዕድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ የመዝናኛ አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲያመቻቹ ድጋፍ መስጠት።

## 7.4. ተቋማትን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች

በአሁኑ ጊዜ ያለው ሁኔታ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ህፃናትን በተቋማትና መጠለያዎች ውስጥ በማቆየት ድጋፍና ተሀድሶ እንዲያገኙ የማድረግን አካሄድ የሚያበረታታ አይደለም። ይሁን እንጂ ሌላ ምንም አይነት አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን በመጠለያ ተቋማት ውስጥ አስገብቶ ድጋፍ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። ይህ በመሆኑም ተቋማትንና መጠለያን በመጠቀም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ህፃናትን ለሚደግፉ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አቅም በአጭር ጊዜ የሚያጐለብቱ ተግባራትን በሚከተሉት ሁኔታዎች ማከናወን ያስፈልጋል።

- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት ጊዜያዊ የመጠለያ አገልግሎት ለሚሰጡ ድርጅቶች ድጋፍና እርዳታ በማድረግ፤
- በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ዙሪያ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የሚሰሩ ድርጅቶችን አድራሻ፣ የሚሰጡትን አግልግሎት የያዘ የመረጃ ወይም የማውጫ ሰነድ ማዘጋጀት፤ ይህ ማውጫ ድርጅቶቹ የሚሰሩትን ሥራዎች፣ የሚሰጡትን አገልግሎቶች፣ እንዴት ድርጅቶቹን ማግኘት እንደሚቻል የሚያመለክቱ መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል። ይህም የገቢ ማሰባሰቢያ ሥራዎችን ለመስራት፣ የጋራ ኘሮጀክቶችን ለይቶ ለመፈፀም ያስችላል።
- በጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ላይ የሚሰሩ ድግግሞሽ አሰራሮችንና እነሱም የሚያስከትሉትን የሀብት ብክነትን ለማስወገድ እንዲሁም የመረጃ ልውውጥ ለማካሄድ በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች የጋራ በጋራ የሚወያዩበት መረጃ የሚለዋወጡበትና የሚሰሩበት የጋራ መድረክ እንዲያቋቋሙ ማነሳሳት፤
- ህፃናትን መልሶ ወደ ቤተሰብና ህብረተሰብ የማቀላቀል ኘሮግራም በጋራ ተዘርግቶ እንዲፈፀም ማገዝ፤ ይህ ኘሮጀክት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

# ዋቢ መጻሕፍት


*መስከረም መጽሔት*፣ ቅጽ 4፣ ቁጥር 18፣ ሰኔ 1976 ዓ.ም።

ማኅተመ ሥላሴ ገብረ መስቀል፣ 1942 ዓ.ም፣ *ዝክረ ነገር*፣ አዲስ አበባ።

ሠማጉሚ/ር. ከነሐሴ 25 እስከ ነሐሴ 27፤ 1986 ዓ.ም. የተካሄደ ሴሚናር ሪፖርት፤ አዲስ አበባ ፤ 1986

_____.በልመና የተሰማሩ ዜጎችን መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራም፤ የውይይት መነሻ ሰነድ፤ አዲስ አበባ፤ 1999

በዓሉ ግርማ፣ 1984 ዓ.ም፣ *ኦሮማይ*፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

*ብርሃንና ሰላም (ጋዜጣ)*፣ *፰ኛ ዓመት ቁጥር ፶* ፣ አ.አ. ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፱

*ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት*፣ አዲስ አበባ 1926

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ *የልብ አሳብ*፣ አዲስ አበባ ፲፱፻፳፫

_____ *አዲስ ዓለም*፣ አ.አ. ፲፱፻፳፭

_____*ሀገረ ጃፓን (ማኅደረ ብርሃን)*፣ አዲስ አበባ ፲፱፻፳፬

ከበደ ሚካኤል ፣ *የዕወቀት ብልጭታ* ፣ አዲስ አበባ ፲፱፻፴፪

_____*ጃፓን እንደምን ሠለጠነች* ፣ አዲስ አበባ ፲፱፻፴፮

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1948

አባ ጉርጉሪዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ታሪክ*፣ አዲስ አበባ፤ 1974

አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና እደ ጥበባት ልማት ማስፋፊያ ድርጅት 1974 *አኢማድ በአምስት አመት* አዲስ አበባ፣ ነሀሴ 20፣ 1974 ዓ. ም።

አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፣ *ዳግማዊ አጤ ምኒልክ*፣ ሮማ፣ ፲፱፻፮

ኢ.ኦ.ቤ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ (2000 ዓ.ም)*፣ አዲስ አበባ፤ 2000 ዓ.ም.

እሸቱ ጥሩነህ፣ «በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥዕል ጥበብና የአዲስ አባ ሥነ-ጥበብ ት/ቤት እንቅስቃሴ» (የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ-መጻህፍት የሚገኝ፣ *ያልታተመ*) 1993 ዓ.ም.

እጓለ ገብረ ዮሐንስ ፣ *የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ*፣ አ.አ. ፲፱፻፵፮

የራስወርቅ አድማሴ። «ሥርዓታት፣ የፖለቲካ ነፃነትና ልማት በኢትዮጵያ።» *ቪዥን 20/20 ፦ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር*። አዲስ አበባ ፤ 2006

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: *አማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ ፤ 1993

የኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ቅርሶች፤ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ምርምርና ማዕከላዊ ዶክመንቴሽን መምሪያ የተዘጋጀ፤ 1999 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (ኅዳር 1989) *የማኅበራዊ ደኅንነት ልማት ፖሊሲ*፤ አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (ሰኔ 1993) *የአካል ጉዳተኞች ተሐድሶ ብሔራዊ የድርጊት መርሐ-ግብር*፤ አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (ሰኔ 2002) *የ1998-2007 ብሔራዊ የአረጋውያን የድርጊት መርሐ-ግብር*፤ አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (1997) *የአምስት ዓመት (1998-2002) ፈጣንና ዘላቂ የልማት ዕቅድ*፤ አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (ሰኔ 2002) *የአምስት ዓመት (2003-2007) የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ*፤ አዲስ አበባ::

ገብረ ህይወት ባይከዳኝ፣ *ሥራዎች*:: ነባር ምርጥ መጻሕፍት ሕትመት:: አአዩ ፕሬስ:: 2002 ዓ.ም.

_____፣ *ዐፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ* ፣ እ.አ.አ. 1912

_____*መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር*፣ አዲስ አበባ ዓ.ም፣ ፲፱፻፲፮

ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት፣ *አርአያ* ፣ አዲስ አበባ ዓ.ም፣ ፲፱፻፵፩

ግርማ ዘውዴ፣ *ኢትዮጲስ*፣ አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም.

Addis Ababa Bureau of Social and Civil Affairs, Addis Ababa Bureau of Finance and Economic Development and United Nations Children's Fund (2007). Baseline Survey of Children Living on the Streets of Addis Ababa.

*Addis Fortune*. 25 April 2010.

Ambaye Degefa 1997. "Social organization and status of occupational groups; the case of woodworkers in Megnako and Gambela villages, Wolisso District, Southwestern Shoa". MA thesis in Social Anthropology, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

Bharia, A.K. 2002. *Tourism Development: Principles and Practice*. New Delhi: Sterling Publishers.

Black, Jan Knippers. 1991. *Development in Theory and Practice: Bridging the Gap*. Boulder: Westview Press.

Boll, Verena. 1991. "Thoughts on Zeqwala and the Syrian Goddess Atagatis." *Sociology and Ethnology Bulletin,* Vol. 1, Dept. of SOSA, Addis Ababa University, Addis Ababa.

Brandt, Steven and C. Weedman 1997 "The Ethnoarchaeology of Hide Working and Flaked Stone Tool Use in Southern Ethiopia", in K. Fukui *et al.* (eds) *Ethiopia in Broader Perspective: Papers of the 13th International Conference of Ethiopian Studies*. Kyoto: Shokado Book Sellers. 1:351-61.

Brokensha, David, *et al.* 1980. *Indigenous Knowledge Systems and Development*. Lanham: University Press of America.

Burley, Dexter 1979 "The despised weavers of Addis Ababa" in R. Hess (ed.) *Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies,* University of Chicago.

Calhoun, Craig (ed.). 2002. *Dictionary of the Social Sciences.* Oxford University Press. Oxford and New York

Chambers, Robert. 1980. "Understanding professionals: Small farmers and scientists," IADS Occasional Paper. New York International Agricultural Development Service.

_____. 1992. *Rural Development: Putting the Last First.* New York: Longman.

Chapple, David. 1986. "Protestant missionary attitudes in Ethiopia: Gobat, Isenberg and Krapf". *Proceedings of the Third Annual Seminar of the Department of History*. Addis Ababa: Addis Ababa University.

*Collins Concise English Dictionary*. Harper Collins Publisher, 3rd edition. G. B. 1992.

Crewe, Emma and Elizabeth Harrison 1998. *Whose Development? An Anthropology of Aid.*

D' Archy Hyman, *The Arts and Man: A World View of the Role and Functions of the Arts in society (* UNESCO CourlerMagazine-1969)

Development Agency for Handicrafts and Small Industries 1997 *DAHSI Newsletter* 1(1). July.

Douglas, Mary. 2004. "Traditional Culture-Let's Hear No More About it" in Rao, V. and M. Walton (eds.) *Culture and Public Action.* Stanford University Press, Stanford.

Durkheim, E. (1893) 1984. *The Division of Labor in Society*. Macmillan. London.

Elsen, Rlbert E. *Purpose of Art.*

Elshadai Relief & Development Association (ERDA). Untitled text.Undated.

Ethiopian Tourism Commission 1996 *Feasibility Study of Traditional Handicrafts Development in the Tourist Industry of Ethiopia. Volume 1. Draft Final Report.* Prepared by Jacques Dubois for Caisse Française de Développement. Addis Ababa: Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Tourism Commission,

Expert group meeting on the role of men and boys in achieving gender equality October 2003 Brasilia, Brazil

Federal Democratic Republic of Ethiopia (FDRE). 2007. Cultural Policy of Ethiopia, Addis Ababa.

Feleke Tadele. 1997. "What Is Next in Damote Gale? Field Note," Oxfam-UK/I (unpublished).

Ferraro, Gary. 2001. *Cultural Anthropology: An Applied Persprective.* 4th edition. Wadsworth. Belmont, CA.

Fitsum Dechasa. 2009. "An assessment of street begging problem in Ethiopia: the case of Shashemene Town". MA thesis School of Graduate Studies, Addis Ababa University, Addis Ababa.

Forum on Street Children Ethiopia-FSCE (2003). Summary Report of the studies on the Situation of Street Children in Eight Major Towns of Ethiopia. Addis Ababa, Ethiopia.

Freeman, Dena and Alula Pankhurst (eds) 2001. *Living on the Edge: Marginalised Minorities of Craftworkers and Hunters in Southern Ethiopia.* Department of Sociology and Social Administration, Addis Ababa University.

Fre man, Dena and Alula Pankhurst (eds) 2003. *Peripheral People: The Excluded Minorities of Ethiopia.* Hurst, London

Fukuyama, Francis. 1992. *The End of History and the Last Man.* The Free Press, New York.

Gallagher. J. 1974 'The Preparation of Hides with Stone Tools in South Central Ethiopia' *Journal of Ethiopian Studies* 12(1):177-82.

Gebre Yntiso. 2005. *Culture and Development in Africa: Building on Positive Cultural Practices.* Addis Ababa: UNFPA and African Union.

Gender Issues and Civic Education by Christian Boeser, Germany

Gender Stereotypes and the Socialization Process by Jivka Marinoua

Generre, Maunizion. 1991. "Sacred Volcano Lakes: Reflections Comparing Zeqwala and Nemi." *Sociology and Ethnology Bulletin,* Vol. 1, Dept. of SOSA, Addis Ababa University, Addis Ababa.

Gervers, Michael 1988 "Cotton and Cotton Weaving in Medieval Ethiopia" in A. Gromyko (ed.) *Proceedings of the Ninth International Congress of Ethiopia Studies, Moscow 26-29 August 1986*. Moscow: Nauka Publishers. 5:212-24.

Grahms, John. 1971 *Systems and Dialectics of Art.*

Hallpike, Christopher 1968. 'The status of craftworkers among the Konso of Southwest Ethiopia. *Africa* 38(3): 258-69.

Hobbs, Donald A., and Stuart J. Blank. 1975. *Sociology and the Human Experience.* John Wiley & Sons, Inc. New York, London, Sydeney, and Toronto.

HOPE Enterprises. 2006. Achievements. hopeenterrises.org/achievements.htm

Huntington, Samuel and Myron Weiner. 1987. *Understanding Political Development*. Little Brown, Boston

Jenks, Chris . 2007. " Culture: Conceptual Clarifications". In George Ritzer (ed.). *The Blackwell Encyclopedia of Sociology*. Blackwell Publishing, Malden, USA and Oxford UK.

Johnson, Allan G. (ed.). 2000. *The Blackwell Dictionary of Sociology: A User's Guide to Sociological Language.* Second Edition. Blackwell Publishing. Malden, USA and Oxford UK.

Karsten, D. 1972 *The Economics of Handicrafts in Traditional Societies. An Investigation in Sidamo and Gemu Goffa Province Southern Ethiopia.* Afrika-Studien 79. Weltforum Verlag, München.

Knight, Gregory. 1974. *Ecology and Change: Rural Modernization in an African Community.* Duke University Press, Durham.

Levine, Donald N. 1965. *Wax and God. Tradition and Innovation in Ethiopia.* Chicago University Press, Chicago.

Lusk, M.W.; Peralta, F. and G.W West, (1989) "Street Children of Juarez: A Field Study." *International Social Work*. Vol.32, PP.289-302.

Marx, Karl, and Friedrik Engels, 1962. *Selected Works, Vol II.* Foreign Language Publishing House, Moscow.

McCann, James 1995 *People of the Plow: An Agricultural History of Ethiopia, 1800-1990.* University of Wisconsin Press, Madison.

Merab, Paul 1929. *Impressions d'Ethiopie.* Paris: Editions Ernest Leroux.

Mesele Terecha Kebede. 2010. *Origins and transformation of the Hamina Song-Mendicant Tradition. African Study Monographs*, Suppl.41: 63-79.

Mesfin W. Mariam. 1966a. "Cultural Problems of Development." A Paper prepared in advance for the Seminar of Ethiopian Studies, HSI University, Faculty of Arts, Addis Ababa (unpublished).

Mesfin Wolde-Mariam. 1966b. "Some Aspects of Urbanization in Pre-Twentieth Ethiopia. " *Ethiopian Geographical Journal.* Vol. III, No. 2, pp 13-19.

Minas Hiruy. September 2009. "A proposal for the introduction of the Social Development Fund of Ethiopia". (First Draft). Addis Ababa

Ministry of Commerce and Industry 1976 *Report of the Seminar on Small-Scale Cottage and Handicraft Industries, Africa Hall 23-30 June 1975.* Ministry of Commerce and Industry Small-Scale Cottage and Handicraft Industries Department, Addis Ababa.

Ministry of Labour and Social Affairs (1974). Survey of Street-Children. (Unpublished report in Amharic) Addis Ababa, Ethiopia

Ministry of Labour and Social Affairs (1974). Survey of Street-Children. (Unpublished report in Amharic) Addis Ababa, Ethiopia

Ministry of Labour and Social Affairs/Radda Barnen, Sweden (1988) Survey on Street Children in Selected Areas in Addis Ababa. Addis Ababa, Ethiopia

Ministry of Labour and Social Affairs/Radda Barnen, Sweden (1988) Survey on Street Children in Selected Areas in Addis Ababa. Addis Ababa, Ethiopia

Mittler, Gene A. 1971. “Art in Focus”

MOLSA 1992. “Study on begging in Addis Ababa: Action-oriented”. Addis Ababa.

Moncrieffe, Joy M. 2004. “The Role of Culture in Development”. Overseas Development Institute. London.

Moura, Sergio Luiz de (2002). "The Social Construction of Street Children: Configuration and Implications". *British Journal of Social Work* 32, 353-367.

-------(1995). "The National Study on Street Children: Nature and Magnitude of the Problem and Methods of Intervention. " The Federal Democratic Republic of Ethiopia. Ministry of Labour and Social Affairs December, Addis Ababa.

Nahu Senay 1998. "Social organization and status of artisans in Emdibir Area (Gurage)." MA thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

ORDA/ German Agro Action. 2006. " Ethiopia: Fact Sheet. Orthodox Church and Development. " Addis Ababa (unpublished).

Pankhurst, Alula 1999. "Caste in Africa: The Evidence from Southwestern Ethiopia Reconsidered". *Africa* 69:4.

______ 2000a "Decline, survival and development of crafts: Comparison of tanning, ironwork, pottery, woodwork and weaving with particular reference to southwestern Ethiopia. " *Ethiopian Journal of Development Research* 22(2):1-64.

_____ 2000b. "Globalization and the survival of craftwork in Ethiopia", *Ethiopian Development Forum* 1 (1):47-66.

Pankhurst, Alula and Worku Nida 1999. "Mänjiyé Tabäta, artist and actor: A Fuga Craftsman among the Guragé" in Raymond Sılverman ed. *Traditions of Creativity*. University of Washington Press, pp. 112-31, Seatle.

Pankhurst, Richard 1964 "The Old-Time Handicrafts of Ethiopia, with a Note on Traditional Dress" *Ethiopia Observer* 8:221-42.

Paulitschke, P. 1888 *Harar*. Leipzig.

Reader, John. 1998. *Africa: A Biography of a Continent.* Penguin Books, London and New York.

Sen, Amartya. 2001. "Culture and Development. " Unpublished paper read for World Bank Meeting, Tokyo, December 13.

Sen, Amartya. 2004. "How Does Culture Matter?" In Rao, V. and M. Walton (eds.) *Culture and Public Action.* Stanford University Press. Stanford

Serageldin, Ismail and June Taboroff (1994). *Culture and Development in Africa.* Washington, DC: The World Bank.

Shack, William 1964. "Notes on occupational castes among the Gurage of Southwest Ethiopia." *Man. 54:50-2.*

Solomon Atnafu. 2005. "Social Transformation among Awra Amba Community, Northwestern Ethiopia, Amhara Region." M.A. Thesis, A.A University,

Solomon Gebre. 1993. "The condition of the poor in Addis Ababa: A social problem not yet addressed." *Dialogue (Journal of Addis Ababa University Teachers Association)*, 3rd Series, 2 (1): 1-31.

Stephen, Ellis and Gerrieter Haar. 2004. "Religion and Development in Africa." (unpublished).

Stromquist, Nelly P. 2007 "The Gender Socialization Process in Schools: A Cross National Comparison" UNESCO.

Tacon, Peter.(1991). "Protection, Respect, and Opportunity for the Street-Children of Ethiopia."

Teclehaimanot Gebre Sellassie 1999. "The Fuga: A History of a Low-caste Occupational Group of South-central Ethiopia." PhD Dissertation, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

*The Reporter*. 10 April 2010.

The World Travel and Tourism Council, Progress and Priorities, 2008/09.

Theodros Atlabachew. *Tourism development in the World Heritage Site of Harar*. Harar Revitalization Forum, organized and published by the World Bank and the Ethiopian Cultural Heritage project, March 05/2008.

Todd, Judith 1985 "Iron production of the Dime of Ethiopia", in R. Haaland and P. Shinnie (eds) *African Iron Working. Ancient and traditional*. Bergen, 88-101.

Tsehai Berhane-Selassie 1991 "Gender and Occupational Potters in Wolayta: Imposed Femininity and Mysterious Survival in Ethiopia", in Tsehai Berhane-Selassie (ed.) *Gender Issues in Ethiopia*. Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University, 15-30.

UNDP. 2004. *Human Development – Human Development Reports 2004.* http://hdr.undp.org/en/media/HDR_2004.

UNDP. 2009. *Human Development – Human Development Reports 2009.* http://hdr.undp.org/en/humandev/.

UNESCO website: www.unesco.org

UNESCO. 2000. *Change in Continuity: Concepts and Tools for a Cultural Approach to Development*. Culture and Development Series. Paris: UNESCO publishing.

UNESCO's Convention concerning the protection of the world cultural and natural heritage, adopted by the General Conference at its seventeenth session, Paris, 16 November 1972, Article 1.

UNSCO. 1995. *The Cultural Dimension of Development: Towards a Practical Approach*. Paris: UNESCO publishing.

Urban Management Programme (2000). *Street Children and Gangs in African Cities: Guidelines for Local Authorities*. Working Paper Series 18, May.

Warren, D. Michael. 1991."The Role of Indigenous Knowledge in Facilitating the Agricultural Extension Process," Paper presented at the *International Workshop on Agricultural Knowledge Systems and the Role of Extension*. Bad Boll, Germany, May 21-24, 1991.

____.1990. "Using indigenous knowledge in agricultural development," World Bank Discussion Paper 127. Washington DC: The World Bank.

_____.1989. "Linking scientific and indigenous agricultural systems," in *The Transformation of International Agricultural Research and Development*, J.L. Compton (ed), Pp. 153-170. Boulder: Lynne Rienner.

Weber, Max. (1930) 1971. *The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism.* Unwin University Books. London

Weber, Max. 1946. *From Max Weber: Essays in Sociology*, Oxford University Press, New York.

Webster, Andrew. 1984. *Introduction to the Sociology of Development*. Macmillan Education Ltd. Houndmills, Basingstoke, Hampshire, and London.

Woubishet Demewozu. 2005. *Begging as a Means of Livelihood: Conferring with the Poor at the Orthodox Religious Ceremonial Days in Addis Ababa. African Study Monographs*, Suppl. 29: 185-191.

____. 2003. "Begging as a survival strategy: Conferring with the Poor at the Orthodox Religious Ceremonial Days in Addis Ababa". MA Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, Addis Ababa

# ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎች

**ዶ/ር ቴዎድሮስ አጥላባቸው፡-** የኢትዮጵያ ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር መሥራች አባልና የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት፣ የኢትዮጵያ የዱር አራዊት ተፈጥሮ ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንትና የቅርስ ባለአደራ ማኅበር የሥራ አመራር ቦርድ አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኢንዱስትሪን ለማሳደግ ከተሰለፉት ባለሙያዎች በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በዚህም ረገድ አያሌ የቱሪዝም ማስፋፊያና ማሳደጊያ ፕሮጀክቶችን የመሩና ያስተባበሩ፤ በተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮችም ላይ በቱሪዝም ላይ የምርምር ጽሑፎችን ያቀረቡ ባለሙያ ናቸው፡፡

**ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት፡-** የማስትሬትና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በእንግሊዝ አገር ከማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ በአንትሮፓሎጂ ያገኙ ሲሆን፤ ለ16 ዓመታት ያህል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ በአግልግሎት ዘመናቸው አያሌ የምርምር ሥራዎችን ያሳተሙ ሲሆን ጥናቶቻቸው ያተኮሩትም በሠፈራ፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ ኀዳጣን ማኅበረሰቦች፣ እድሮችና ባሕላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች ላይ ነው፡፡

**አቶ አስፋው ዳምጤ፡-** የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቀድሞው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ(የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በእንግሊዝ አገር በኬምብሪጅ ዩኒቨርስቲ በኢኮኖሚክስ ያገኙት አቶ አስፋው በገንዘብ ሚኒስቴርና በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት በተለያዩ የኃላፊነት እርከኖች ሠርተዋል፡፡ በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ በሥነ ጽሑፍና ባሕል ላይ አስተያየታቸውን ያቀረቡ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ቀደም ሲል ባዘጋጀው «ከድህነት ወደ ልማት፡- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» በተሰኘው የውይይት መድረክም«ትምህርት፣ ባህልና እድገት» በሚል ርእስ ለሕትመት የበቃ ጽሑፍ ያቀረቡ ናቸው፡፡ ላለፉት ብዙ አመታት፣ የአማርኛ ስነጽሁፍን ታሪክ እያጠኑ አያሌ መጣጥፎች አሳትመዋል፡፡ በፈጠራ ስራም በኩል፣ አጫጭር ልብወለድ ታሪኮችንና ግጥሞችን ይጽፋሉ፡፡

**አቶ አበባው በቀለ፡-** በሶስዮሎጂ ትምህርት መስክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ በ1979 ዓ.ም፣ የማስተርስ ዲግሪ በ2002 ዓ.ም. አግኝተዋል፤ በቀድሞው የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ውስጥ ለ10 አመታት ካገለገሉ በኋላ በተለያዩ መያዶች ውስጥ በህጻናት ጉዳይ ስራ ላይ ለ12 አመታት በመስራት ላይ ናቸው፡፡

**አቶ እሸቱ ጥሩነህ፡-** ከ1962-66 በቀድሞው የአዲስ አበባ ስነጥበብ ት/ቤት ከሰለጠኑ በኋላ ለሶስት አመት ሀገር ፍቅር ቲያትር በመድረክ ገጽና በፖስተር ሰአሊነት ሰርተዋል፡፡ ከዚያም ወደ ቀድሞው ሶቭየት ህብረት ለከፍተኛ ትምህርት ሄደው ሞስኮ በሚገኘው የሱሪኮቭ ስነጥበብ አካዳሚ ከ1970-1976 ዓ.ም ድረስ ሰልጥነው ከተመለሱ በኋላ በመምህርነት አዲስ አበባ ስነጥበብ ትምህርት ቤት ለሶስት አመታት አስተምረዋል፡፡ ቀጥሎም በባህል ሚኒስቴር ውስጥ ለአያሌ አመታት አገልግለው ጡረታ ወጥተዋል፡፡ የ Enlightenment Art Academy መስራቾች ውስጥ አንዱ ሲሆኑ እዚሁ የስእል ትምህርት ቤት በዳይሬክተርነትና በመምህርነት ይሰራሉ፡፡ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ብዙ የስእል አውደርእዮች አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም በስነጥበብ ጉዳዮች ጥናት እያደረጉ ጹሁፎቻቸውን አሳትመዋል፤ የተዋጣላቸው የግጥም ደራሲም ናቸው፡፡

**አቶ ክቡር ገና፡-** የማስትሬት ዲግሪያቸውን ከኒው ዮርክ ስቴት ዩኒቨርሲቲ (ስቶኒ ብሩክ) ያገኙ ሲሆን የአፍሪቃ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማኅበራት አጋርነት ሥራ አስፈፃሚ

ዳይሬክተርና የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤቶች ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል። በኢትዮጵያ ‹ጥራት› በሚል ስያሜ የሚታወቀው ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተባለው ዓለም አቀፍ ፀረ-ሙስና ድርጅት ቅርንጫፍ መሥራች የሆኑት አቶ ክቡር ባሁኑ ወቅት ኢንሽዬቲቭ አፍሪቃ የተባለ በመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ላይ የሚያተኩር መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ናቸው።

**ዶ/ር ውዱ ጣፈጠ፡-** በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ረዳት ፕሮፌሰርና የታሪክ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ናቸው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም በዋግና ላስታ ላይ ምርምር አድርገዋል። አንዳንድ መጣጥፎችንም አሳትመዋል።

**ወ/ሮ ዘውዴ አበጋዝ፡-** ለብዙ አመታት በስርአተ ጾታ ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ሰርተዋል፤ ብዙ ጥናቶችንም አካሂደዋል። በዩኒሴፍም (UNICEF) ውስጥ በስርአተ ጾታ ኤክስፐርትነትና በሀላፊነት አገልግለዋል።

**ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ፡-** የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ያገኙት ስዊድን ከሚገኘው ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፤ ከሃያ ዓመታት በላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶስዮሎጂ መምህርነት አገልግለዋል። የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ መሥራች አባል፣ የመጀመሪያው የማኔጅመንት ኮሚቴ አባልና ባሁኑ ወቅትም የቦርድ አባል ሲሆኑ በባሕልና ልማት ትስስርና በሥርዓታት ጠቀሜታ ላይ በተለያዩ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል።

**ዶ/ር ገብሬ ይንቲሶ፡-** የማስተርስ ዲግሪያቸውን በ1985 ዓ.ም በሶሻል አንትሮፖሎጂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በ1992 ዓ.ም በአንትሮፖሎጂ አሜሪካ አገር ከሚገኘው የፍሎሪዳ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል መምህር ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የጥናታቸው ትኩረትም በህዝብ ፍልሰት፣ ባህልና ልማት፣ የብሔረሰቦች ግንኙነት፣ ባህላዊ ዕውቀት፣ የምግብ ዋስትናና የህፃናት ጉዳይ ሲሆን፤ አብዛኛዎቹ ሥራዎቻቸውም ለህትመት በቅተዋል።

**ደ/ር ፈቃደ አዘዘ፡-** በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎርና የሥነ ጽሑፍ መምህር በመሆን ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን፤ በሁለቱም መስኮች ሰፊ ምርምር በማድረግ መጻሕፍትና መጣጥፎችን አሳትመዋል። ከነዚህም መካከል መጀመሪያ በእንግሊዝኛ ታትሞ ኋላ ደግሞ በአማርኛ *ሰሚ ያጡ ድምፆች* በሚል ርእስ የመለሱት፣ *የሥነ ቃል መምሪያ*ና አምስት ያህል የግጥም መጻሕፍትን መጥቀስ ይቻላል። ከመጣጥፎቻቸውም መካከል በባሕልና ልማት ላይ በኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር የውይይት መድረክ ላይ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ይገኝበታል።

**አቶ ፈለቀ ታደለ፡-** ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የኦክስፋም ካናዳ ተወካይ ሆነው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በሕፃናት አድን ካናዳ፣ ኬር ኢንተርናሽናል፣ ኦክስፋም ግሬት ብሪትንና ሕፃናት አድን ኖርዌይ ድርጅቶች በከፍተኛ አመራር ላይ ተመድበው አገልግለዋል። በሶሻል አንትሮፖሎጂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስትሬት ዲግሪ ያላቸው አቶ ፈለቀ፣ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የሶሲዮሎጂና የሶሻል አንትሮፖሎጂ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንትና የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርድ አባል ናቸው። በዓለም አቀፍ እድገት ላይም የዶክትሬት ዲግሪ ምርምራቸውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።



በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች

አርታኢ ሺፈራው በቀለ

Printed @ Eclipse +251 118 501264 Addis Ababa, Ethiopia